ይከተር አሕጉር

እና ሌሎችም



ኣፈትሕ ኣንብቦ

10ኛ ዕትም

ማውጫ

1. አስር የሽቶ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ ——— 5
2. ተሰቀለ ቢሉኝ 'ባርኔጣው' ነው ብዬ ——— 15
3. ከሰሀራ ቢታች ——— 21
4. ትንሽ ወደግራ ዘምበል... ——— 44
5. አገዛላታለሁ...!! ——— 49
6. የፍርምጣ ጦርነት ——— 54
7. ተሸከመናታል!! ——— 57
8. ደወል ——— 59
9. የአባዬ ሰልከአና ባዮሎጂ ——— 65
10. ሁለት ብር ሰንት ዶላር ነው? ——— 72
(አንዷን ወንዝ ሁለት ጊዜ ሰንሻገራት)
11. አግዚኦኦኦኦኦኦኦኦ ——— 77
12. ንፋስ ወዴት ነህ ቢሉት ማርና ወተት ወዳለበት ——— 84
13. 'ቆጠራ ላይ ሰለሆንን መግባት ክልክል ነው' ኮሚቴው!! ——— 88
14. የመግቢያ ፈተና ——— 92
15. አብድ አና ዘመናይ ——— 96
16. ከፍሪጅ የተጫረ አሳት ——— 101
17. የታረሙ ነፍሶች ——— 112
18. በብረትና ቻፕስቲክ በተከበበ ከተማ አነሆ የመልአክ ድምጽ ተሰማ ——— 119
19. ዝግመተ ለውጥ ——— 126
20. ፈንዲሻ ሲቆሉት ድምፅ ሲበሉት ድምፅ ——— 137
21. "ሸረኛ" "እና" "ደህና" "በአንድ ላይ ሲሄዱ ——— 141
በሸረኛው በኩል ተናደ መንገዱ
22. የመደርደሪያው ጫፍ ——— 150
23. አለሁላት...!! ——— 162
24. ትንቢት... ——— 168
25. ዶክተር አሸብር ——— 172

አሰር የሽቶ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ 1

እሽከም...እሽከም...እሽከም (ያዝ እንግዲህ!)

ደግሞ እሰከሰሰሰሰሰሰሰ (አሳየው...ላላየው)

አልልልልልልልልልልልልልልልልልልልል...ችቦ አይሞላም ወገቧ (ያዝ እንግዲህ!)

የጎረቤታችን ሰርግ ነው:: የኑአሚን ተፈራ:: ዘፋኝ ስለሆነች ይሆን ዘፈኑ የደመቀው:: ማንትስ ባንድ የሚባል፣ እንደ አንበሳ አዳኝ "ያዝ እንግዲህ" ማለት ከሚያበዛ የባህል ዘፋኝ ጋር ሰርጉን እያደመቁት ነው:: መንደሩ አብዷል:: ቢራ አራት መኪና ሙሉ ተዘርግፎ "ጠጡ!" ተባለ :: ጠጅ፣ ወይን ጠጅ፣ አባይ ቢጫ ልብስ ለብሶ ሰርጉ ላይ የተገኘ እስኪመስል ስክርርር እስኪል አላፊ አግዳሚው::

ከሰርጉ በፊት...፣

"የልጃችን የወይዘሪት ኑአሚን ተፈራ እና የታደለ ግርማ የጋብቻ ሥነሥርዓት የሚፈፀመው እሁድ ከቀኑ 7:00 ሰዓት 19... ዓ ም ስለሆነ ከባለቤትዎ ጋር ተገኝተው የደስታችን ተካፋይ እንዲሆኑ ተጋብዘዋል::"

ጥቅስን እንደመፈክር፣ "እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ማንም አይለየውም...ምዕራፍ 7፣ ቁጥር 3"፣ ሌላ መፈክር፣ "ከእንግዲህ አንድ ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም:: ...ምእራፍ፣ ...ቁጥር፣ የምር ምስጋና፣ "አድርገህልኛልና ለዘላለም አመሰግንሀለሁ" (እንደገና ስጦታ ካርድ የሚከፋፈተው፣ አብረቅራቂ የጥሪ ወረቀት ላይ በየገፁ ጥቅስ አለ::የሙሽሪት የሕይወት ገፅ ቢገላበጥ፣ እንኳን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፣ የዘወትሩ "አባታችን ሆይ..." በወጉ አይገኝም:: "የዕለት እንጀራችን..." ላይ ያልቃል እምነቷ!!)

አድራሻችን፣ "ከፊታውራሪ አሰፋ ግዛው ቤት ጎን":: ይሄ የጥሪ ካርድ የተሰጠው ለአባቴ

"ፈታ-ውራሪ አሰፋ ግዛው" ነው!! ያውም በወርቃማ ቀለም ተሸሞንሙኖ እንደግቢ በር በትልቁ ግራና ቀኝ ተከፋች ተደርጎ፣ የሙሽራውና የሙሽሪት ፎቶ አስማት በሚመስል ቀለም ተሥሎበት፣ ደግሞ ካርዱ በጨለማ ውስጥ ያበራል። (እዮብ አንድ ቀን የሚያበራ ፅሁፍ ያለበት እስክርቢቶ ያዘ፣ "እንዴት በጨለማ ያበራል?" አልኩት፣ "በፎስፎረስ ነው ፅሁፉ የተፃፈው" አለኝ::ከዛች ቀን ጀምሮ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ አብሪ ትል፣ የቤታችን አምፖል ከፎስፎረስ የተሰሩ መሰለኝ::)

አባቴ ተቃጠለ ::ነደደ :: የጥሪ ካርዱን ሲያይ በከዘራው መሬቱን ቀጭ ቀጭ እያደረገ በእግሩም እየተመታመ ወይኑን የሚያሳርፍበት ቦታ አጥቶ ተንከራተተ:: በሰንሰል ቅጠል፣ በቆርቆሮና በጥሬ ካብ የተዋቀረውን ዘበተሎ የግቢያችንን አጥር፣ ተገንጥሎ ቋሚው ጋር በሸቦ የታሰረውን የግቢውን የቆርቆሮ በር አየ - መዛግ ጀምሯል በሩ:: ሲዝግ ይገነጠላል:: የበሰበሰውን የበረንዳ መደገፊያ ጣውላ ቃኘ፣ "እንዲህ ምልከት አድርጉኝ እንጂ በወግ ማዕረግ ለመዳሩማ አልታደልኩም:: አም ከአዬ ቤት ነን ሰርገኛው ይጉረፍ" አለ::'ወይኔ አባባ፣ ሊያለቅስ ነው እንዴ' አልኩ እኔ:: ከምር እንባው በዓይኑ ሞልቷል::

እህቴ እዮብን አፈቀረችው ፤ እዮብም አፈቀራት ፤ በጣም ተፋቀሩ :: (እዮብ ማነው ካላችሁ እዮብ የእህቴ ፍቅረኛ ነው፤ ሌላ መታወቂያም ማንነትም የለውም:: እህቴ የእዮብ ባንዲራ ናት፤ ኢትዮጵያዊያን ሮጡም ተዋጉም ባንዲራው ነው አይደለም ቀድሞ የሚታየው:: እዮብ ይኑርም አይኑርም በእህቴ ነው የሚከበረው (እዮብ ማነው? ይሄ የሳምሪ ጓደኛ?) አይነጣጠሉም 'ጠይም ባንዲራው' ናት::)

ሁሉም ሰው እዮብን "እድለኛ ነው" ፤ "አፈሰ" ይለዋል:: ለእህቴ የሚሰጠው አስተያየት ግን ይቀላቀላል:: ፒያሳ ታክሲ እየጠበቀ፤ "የምትገርም አፍቃሪ፤ የእግዜር ሰው፤ ትሁት" ያለው አስተያየት ሰጪ ቄራ ሳይደርስ፣ "ምን ነክቷት ነው እዚህ (ጣሙጋ...ሬሳ...ጣውላ...ቀድረ ቀላል... ጠኔያም...'ሱሰኛ'...በዘኔ...የቆመ እባብ የመሰለ...እህል አይቶ የማያውቅ የመሰለ) ልጅ ላይ ሙጫጭ ያለችው? እችን የመሰለች (ኬክ...መልአክ...ውብ...መለሎ...ሞናሊዛ...ወለላ...የማር ሰፈፍ...ፀሐይ... ፅጌሬዳ...አንቡጥ...ጠይም አሳ መሳይ...'ሴክሲ')..." ይላል ፤ በዕርግጥ እዮብ እንዳሉት ነው- 'ሱሰኛ' ከሚለው ውጪ፤ እህቴም እንዳሏት ናት ፤'ሴክሲ' የምትለዋ ቃል ግን ተናጋሪዎቹ ሲናገሯት ከሰሪቷ ታፈነግጣለች:: አርፈው (አማላይ) ቢሉስ !!

ቆንጆ ሴት መውለድን፣ ቤት ውስጥ የነዳጅ ጉድጓድ እንደማግኘት አድርጎ የሚወስደው 'የአዲስ አበባ' ህዝብ፣ እህቴን ሲያይ "የብረት መዝጊያ የሚሆን አማች አምጥታ እዚህ እድሜ ልኩን ክፍቱን የኖረ፣ በሩ የዛገ ቤት ላይ ትገጠግጠዋለች" ብሎ በኩራት ይናገር ነበር !!

እህቴ ግን እዚህ ግባ የማይባለውን፣ ለሰው ዐይን እንደፉዬ ገላ የቀለለውን፣ የህይወት ነፋስ ማሳረፊያ አሳጥቶ የሚያንሳፍፈውን እዮብን አፈቀረች :: ያውም በፍፁም ልቧ፣ በፍፁም ነፍሷ እንደእግዜር !! እዮብ የእህቴ እግዜር ነው:: እግዜር በእህቴ አይቀየምም:: እግዜር እንደመንደራቸን ጎረምሶች አይደለም:: የፍቅር አምላክ ስለፍቅር እስከጥግ መውረድን መዋረድን ያውቃታል::

እናም እዮብ የእኔ መልአከ፣ የእህቴ እግዜር ነው...!!

"ኧ...ረ እጂ ላይ እንዳይሞት! ይሄ ሞት የጀመረው ልጅ" ይላሉ እህቴን የሚቋምጡ ቁምጥና ልብና ሀሊናቸውን ያጠቃው ባለጉንድሽ ልብ ጎረምሶች :: ጠዋት ሲወጡ ሰባት ልብስ ለክተው ስምንተኛውን መርጠው የሚለብሱ ሴት አውሎች !! እዮቤን ያሙታል (እዮቤ የኔ ሚስኪን በድሪቶ የተጠቀለለ ወርቅ::) እነዚህ የሴት ስም ሲያቆላምጡ የሚውሉ የዘነጡ ቆሻሾች እዮቤን ያሙታል ::

"እዩብዬ ና እኛ ጋር ዋል ዛሬ" ትለዋለች እህቴ ደውላ::

"አባባ አሉ እንዴ ?" በፍርሃት ይጠይቃል::

"ችግር የለውም:: እንደውም 'ያ ልጅ የት ጠፋ?' ሲል ነበር ማታ" ትላለች እህቴ ፤ አባባ ግን ማታ እንደዛ አላለም:: አባቴ እዮብን ለአይኑ ይፀየፈዋል:: ሲያየው ደሙ ይፈላል:: እዮብ ሲመጣ አባቴ ተነስቶ ከቤት ይወጣል:: እየፈራ፣ "አባባ ደህና ዋሉ" ሲለው እንዳልሰማ ያልፈዋል:: እዮብ ዞር ብሎ ሰው ያያል ሃፍረቱን ማን እንደተጋራው ሊቃኝ:: ምንጊዜም እኔን ብቻ ነው ከስሩ የሚያየኝ :: እኔ የእዮቤ ጋራ ነኝ :: በሰለለ ህይወቱ፣ ብቸኝነት በሚረጭ አይኑ 'የኔ ጋራ የሚሆን? ሲል፣ 'እኔኔኔኔ' ብዬ ላንቃዬ እስኪሰነጠቅ የጮህኩ :: እናም ከጎኑ የቆምኩ:: እህቴማ ጎኑ አይደለችም፣ ውስጡ ናት::

"ከምን ተሰራሽ ?" ብትባል፣ "ከስጋ ፣ ከመንፈስና ከእዮብ" የምትል እህቴ !!

ታደለ የሚባል ሰው ወደ ሰፈራችን እህቴን ወደድኩ ብሎ መጣ:: የት እንዳያት አላውቅም:: (በከፉ አይኑ) ቁመቱ የሚያምር፣ ፈገግታው 'ሳቁ እንሳቅ' አዋጅ !! የቀይ ዳማ፣ አንዳች ግርማ ሞገስ ያጎናፀፈው 'ሳድግ እንደሱ ነው የምራመደው' ብያለሁ:: 'ሳድግ እንደሱ ነው እጄን በመስኮት ላይ አስደግፌ መኪና የምነዳው' ብያለሁ:: 'ሳድግ እንደሱ ነው በእርጋታ የታሸገ ውሃ 'ቷ' አድርጌ የምከፍተው' ብያለሁ:: 'ሳድግ አማርኛን በእንግሊዝኛ ላንቃ የምለፋደድባት እንደሱ ነው' ብያለሁ፤ ይሄ ሰው እህቴን ወድዶ ወደ እኛ ሰፈር መጣ:: ያውም በቆመችበት ሰው ሲነካት "ፂው ፂው" የምትል መኪና ይዞ !!

ሰፈሩ ሁሉ የታደለ መሪ ጠቋሚው ሆነ:: አማልዱኝ ሳይል፣ ድፍን አገር አማላጁ ሆነ:: (እንግዳ ተቀባይ...ሂሂሂ)
"አውስትራሊያ ዘጠኝ ዓመት፣ አሜሪካ ሶስት፣ ስዊዲን ሁለት ዓመት ኖሮ የመጣ ዶክተር ነው" አሏት::

"ሁለት ሴቶች በፍቅሩ በረኪና ጠጥተዋል፣ አንዲቷ መኪናው ጎማ ስር ተነጥፋ 'ካላገባኸኝ ጨፍልቀኝ!' ብላው ቆስላ ተርፋለች፣ ሶስት ከህንፃ ዘለው ተፈጥፍጠዋል፣ አስራ ሰባት የት

እንደደረሱ ላይታወቅም ፤ ልብሳቸውን ጥለው ብን ጥን ብለውለታል :: (አምስት ሙት፣ አንድ ቁስለኛ፣ ለሰራ ሰባቱ የት እንደደረሱ ያልታወቁ...ሂሂሂ)" ለእህቴ ይሄን ዜና አንብበውላታል፡፡ ('ዓለሙን ሁሉ ንቆ ተከተለሽ' ብለው ሴትነቷን ሊለኩሱት)::

"መኪናው ሚሊየን፣ ሰልኩ ሃምሳ ሺ ፈሪ ነው፣ ቤቱ ከውበቱና ከታላቅነቱ ብዛት አንድ ቀን ጠቅላይ ሚንሰትሩ፣ 'ውይ ዛሬ ከምን ጊዜው ቤተ መንግስት ደረሰኩ!' ብለው ዘው ብለዋል አዚህ ፍልውሃ ጋ" አሏት::

እዮቤ አጠገቧ ቆሞ እየሰማ፤ "የወንዶች አውራ ባል መጥቶልሻል፣ አልጋ ሲሉሽ አመድ አትሁኝ!" አሏት::

"እረ የወንድ ጡር አለው" እነሄለን፣ እነሜሮንና ገሊላ (የመንደራችን ዘመነኛ ሴቶች ! ባዶ ቦርሳቸውን አንጠልጥለው ቦሌ ለቦሌ ሲያቃጥኑ ያጡት 'ዲያስፖራ' መንደራቸው ድረስ ሲከሰት 'አሳዝኗቸው'::)

"የወንድ ጡር አለው አታንገላቸው" አሏት፤ በወንድ ጡር የተገዛ ቀሚሳቸውን እየነሰነሱ፣ በወንድ ጡር ግብኖ የገዘፈ ዳሌያቸውን እያውረገረጉ:: ('እኔ ብሆን ኖሮ አይነት ቁጭት...') የስጋ ከምሮች ! ሰው መሆን ሰውነታቸውን ለቅቆ የጠፋባቸው ባዶ የኪራይ ቤቶች !! (ባለትዳር አናከራይም...ሂሂሂ)

"ወደዛ ቶሎ እንደሚሆን አድርጊውና ሰርጉን አብዪን" ያሉም አሉ:: (አፈር፣ ጠጠር ይብሉ::) አንድ ቀን ሳምሪ ከፍል ውስጥ ቡና ተፈልቶ ከፍሏ በእጣን ታፍና ሳምሪ በቢጃማ ፍራሹ ላይ ተቀምጣ አስቴር እየዘፈነች ('ቁጭ ብለህ አጫውተኝ አትለይ ከጎኔ' እያለች) እንዲህ አለ፣

"ሳምሪ"

"ወይዬ እዩ" በአፏ አቤት ማለቷ አልበቃት ብሏት በእጇ እጁን እየያዘችው:: እዮብ መናገር ይፈራል:: እጁን ይዛ አይን ዐይኑን እያየች ጠበቀችው::

"አንድ ነገር ልነግርሽ ነበር እንዳትቆጭ" እየፈራ ፊቱ በሐዘን ተወርሮ አስፈቀዳት:: እጁን ቀስ ብላ ለቀቀችው፣ ፊቷ ተቀያየረ:: ምን እንደሚል ቀድማ የሰማች ይመስል፣ ሳግ በተናነቀው ድምፅ፣ "ተወው አትንገረኝ ...እ..ን ዳ ት ና ገ ረ ው!" አለች ::

"ታ...ዲያ ከእኔ ጋር እስከመቼ ሳምሪ..." እዮብ በምሬት ተነፈሰ:: "ካልፈለግከኝ ሂድ፣ 'አልፈለግኩሽም ሰለቸሽኝ' በል - ሰበብ አታብዛ" እንባዋ ተዘረገፈ::

ዝምምምምምምምምምምምምምም !! የተጣደው ቡና ይንተከተካል...!! እንባዋ ጠብ ጠብ ጠብ ጠ.ብ ጠ..ብ ጠ....ብ ....ጠ.....ብ ጠ.....ብ! ጠ....

"ልሂድ!" አለና ተነሳ እዮብ። እጇን ይዞኝ ከእጁ ጋር እየተጫወትኩ ነበር። እጁ ላይ ባለችው የነሀስ አምባር ('ማን ሰጥቶህ ነው?'...'እናቴ' ብሎኛል አንድ ቀን።) እህቴ ዝም አለች። እዮብ አፍንጫዋ ጠመም ያለች ቆዳ ጫማውን አጠለቀ። ጫማውን ሊያጠልቅ ጎንበስ ሲል አየዋለሁ ከኋላው። ጥቁር ጅንስ ሱሪው የኋላ ኪሶቹ ጠርዝ ላይ በረዶ መሰሎ ጨርቷል፣ ሳስቷል፣ ሳውቀው ጀምሮ እችው ናት ሱሪው - ወጥቶ ሄደ።

እህቴና እኔ ተነሰተን በሩ ላይ ቆምን። ከኋላው እያየነው መንገዱን ቀጠለ። ሲያፍተለትላት የነበረችውን የማስቲካ ልባስ እጁን አወናጭፎ ወረወራት - ወደ አበባው ውስጥ።

ድንገት "እዩዬ" ብላ ተጣራች እህቴ። ዞረ እዮብ።

"ጠብቀኝ!" ወደ ቤት ገባች። ለቅቃው የሄደችውን እጇን በአየር ላይ እንዳንከረፈፍኩት አሰብኩ፣ ወደ እዮብ ልሂድ ወይስ...እንደቆምኩ በፈስታል የተጠቀለለ ነገር ይዛ መጣች። በአጠገቤ ስታልፍ ዱለት ሸተተኝ።:አሃ ዛሬ በግ ታርዶ ነበር ለካ!! አቀብላው የሆነ ነገር ተነጋግረው ተመለሰች። ወደ እኔ ስትቃረብ እዮብ እንዲህ አላት፣

"ሳምሪ፣ የበቀደሙን ሰሀን ሳላየው ቆሜበት ተሰበረ" በይቅርታ ዓይነት...።

"ደንባራ ማሚ እንዳትሰማ ከዚህ ጥፋ" ተሳሳቁ።

ወደ ቤት ስንመለስ "የትኛው ሰሀን ነው የተሰበረው?" አልኳት።

"ዝም በል!"

ዝም!!
ዲያስፖራው ለሰማይ ለምድር የከበዱ ሽማግሌዎች ወደቤታችን ላከ። አባቴ ፊታውራሪ አሰፋ ግዛው በደስታ አበደ። እናቴ በፍርሃት ዝም ብላለች። ጎረቤቱ አሰፍስፎ ሰርጉን ጠበቀ። ለሰርጉ የሚለብሰውን መረጠ። "ያው ዲያስፖራ ጠይቆ እንቢ አይባልም፣ ያውም አንዲት ተራ ፀሃፊ የጡረተኛ ልጅ"። ይሁንና መልሱን ለመስማት አሰፈሰፈ፤ የብሔራዊ ቡድን ወሳኝ ጨዋታ ውጤት ለመስማት እንጂ የእህቴን 'አገባለሁ' ፣ 'አላገባም' ምላሽ ለመስማት አይመስልም አሰፋሰፋ - ሰፍሳፋ ሁሉ!!

እህቴ ሳምራዊት ላቧን ጠብ አድርጋ የምትኖር ጨዋ መሆኗን ማንም ያውቃል ። በወር 1600 ብር ደመወዝ እየተከፈላት ቴሌ በአፕሬተርነት ትሰራለች። ጥሩ ልብስ አትለብስ፣ አትኳኳል- ጓደኛ የላት። 1600 ብር ትቀበልና 700 ብር ለእማማ ፣300 ብር ለአባባ ትሰጣለች። 300 ብር ለይታ ታስቀምጣለች - በቀጣዩ ቀን ሥራ የምትገባ ከሆነ በሚስጥር፣ "እዮብ ሲመጣ ይሄንን ስጠው እሺ እንዳትጥል" ብላ 300 ብሩን ትሰጠኛለች። እዮብ ሲቀበለኝ ደስ አይለውም። እኔ ብሆን እጨፍርለት ነበር ይሄን ሁሉ ብር ባገኝ። አንዳንዴ የታከሲ ብር ስታጣ፣ (ብዙ ጊዜ አታጣም) "ማሚ ትንሽ ከአስቤዛ የተረፈ ብር ይኖርሻል?" ትላለች።

ሥራ ስትሄድ ከመሬት ተነስቼ እናፍቃታለሁ:: ከዛ እደውልላታለሁ:: "ጤና ይስጥልኝ የሰሚን ምስራቅ ሪጅን ቴሌ ኮሚዩኒኬሽን ፅ/ቤት አባከዎ ምን ልርዳዎት ?" ትላለች ሳምሪ:: መንፈሰ ትመስለኛለች:: የማላውቃት ደግሞ ፍጥነቷ - ሳምሪ እኮ ስትናገር ቀስ ብላ ነው:: እንዴት ቻለችበት?! እንደትልቅ ሰው ስላናገረችኝ እህቴን አፈራታለሁ:: ቀስ ብዬ ስልኩን እዘጋዋለሁ:: ድምጿን ስሰማ ደስታ በመላ አካላቴ ይፈሳል - እወዳታለሁ :: አንድም ቀን ግን ደውዬላት እንደነበረ ነግሬያት አላውቅም::) በዚች ደመወዝ ቤተሰባችንን ታስተዳድራለች:: የአባባም ጡረታ ተጨምሮበት::

ሽማግሌዎቹ ለሳምንት ተቀጥረው ከሄዱ በኋላ አባባ ምን አለ፣ "እግዜር ቀኝ እግሩን ቤታችን አስገባ::" ሳምሪ ሲነገራት ምንም ሳትደናገጥ፣ "አይ አባባ የማይሆን ነገር ለምን ታስባለህ"

"ምን...? ('ምናልሽ አንች ጨምላቃ!' በሚመስል የፊት ገፅታና ድምፅ) ምኑ ነው የማይሆነው ነገር፣ የተከበረ፣ ጨዋ፣ ምራቁን የዋጠ ባል ማግባቱ ነው - የሚሆነውን ንገሪኛ" አለ በደም ፍላት ዐይኑን እያጉረጠረጠባት :: እየው አባቴ ፊታውራሪ አሰፋ ግዛው ባንዴ ፊታውራሪ መሸሻ ሲሆን - ያውም መሐል አዲስ አበባ ላይ !!

"አባባ እኔ አሁን ማግባት አልፈልግም " ትንሽ የፈራች መሰለች::

"ምን ዳር ዳር ትያለሽ! ይሄ እንደተተኮሰባት ሚዳቆ ውቃቢው የተገፈፈ ዱርዬ ጋር ስጃጃል ቆሜ ልቅር አትይም" (የእግዜርን ቀኝ እግር ገፍታ ከቤት ስታስወጣ ምን ያድርጋት::)

ሳምሪ እንባዋ መጣ:: ጭንቅ አትወድም:: አማርኛው ሁሉ ያጥራታል:: ለፍቅር ብቻ ፈጥሯት ለንትርክ የሚሆን ቃል ከየትአባቷ ታምጣ::

አባቴ ቀጠለ፣ "የማንንም ስልክ እየተቀበልሽ 'ሃሎ' ስትይ ከመዋል በከብር ብትንፈላሰሽ አይሻልም?" (አንዳንዴ አዲስ ነገር ሊጭኑብን ሲፈልጉ ያለንን የሚያስጥሉብን ልምጭ ብዛቱ)

"ስራዬን እወደዋለሁ አባባ፣ አንተስ 'በጀግንነት የተዋጋህለትን የቆሰልክለትን' ሕዝብ አይደል 'ሃሎ' እያልኩ ሳገለግል የምውለው" እንዴ ሳምሪ ናት የተናገረችው - ገረመኝ::

"በጀግንነት የተዋጋህለትን" የሚሉት ሁለት ቃላት አባባን ለሁለት ደቂቃ ዝም አስብለውት ቆዩና፣ ወደነበረ ቁጣው ተመለሰ:: "እሱን ተይው፣ ድፍን የኢትጵያን ሕዝብ 'ሃሎ' ከማለት ከአማሪካ የተደወለ አንድ ስልክ ማንሳት ይሻላል:: ደሃ ቢደውልም ቢያነሳም ትርፉ ብር ማስቆጠርና ጆሮ ማደንቆር ነው::"

"አባባ አጭሩ ነገር እኔ አላገባም" ብላ ብድግ ስትል፣

"ተቀመጭ !" ብሎ ጮኸባት:: በድንጋጤ ዘፍ ብላ ተቀመጠች:: የሆነ ሰው ከኋላዋ ፀጉሯን ጎትቶ ያስቀመጣት ነበር የምትመስለው:: እኔ ራሴ ተከትያት ልነሳ ነበር:: ለሷ

የተወረወረው "ተቀመጭ" አስቀመጠኝ:: እንደለማዳ ውሻ ምንጣፉ ላይ ከእግሯ ስር ኩስስ ብዬ ነው ይሄን ሁሉ የምሰማው:: ስታወራ በደመነፍስ ፀጉሬን በጣቶቿ ታበጥርልኛለች::

ከዛን ቀን ጀምሮ በገባች በወጣች ቁጠር ከአባቴ ጋር ዱላ ቀረሽ አምባጓሮ ሆነ:: አባባ የሚናገረው ቃል ሁሉ ያበሳጫል፣

"አንችን ከመውለድ ጦር ሜዳ በሞትኩ:: ለአሞራ እራት በሆንኩ" ይላል::

ሽማግሌዎቹ እንደነገ ወዲያ ሊመጡ እንደዛሬ ሳምሪ ድክም ብሏት ስትገባ ገና ከበረንዳው አባባ ተቀበላት:: እስከ ማታ ሰደባት፣ "የሰው ትንሽ..." አላት:: "ቤቴ ድረስ ወንድ እየጎተትሽ ስትዳሪ ዝም ማለቴ አስናቀኝ" አላት::

ሳምሪ በአንድ ሳምንት የቀኝ ዐይኗ ስር ማዲያት የሚመስል ነገር ወጣባት:: ፊቷ ጠቆረ፣ ስታለቅስ የምታድርበት ዐይኗ ያስታውቃል:: ....

ብዙ ነገር ያየን ሰዎች ነን፣ ማግኘትንም ማጣትንም - ገና ለገና እያመጣሽ የምትወረውሪልንን ደመወዝ ጠባቂ አድርገሽን ናቅሽን - ማን አለብኝ አልሽ::"

"ኧረ ተው እንዲህ አይባልም" አለች ክፉ ደግ ተንፍሳ የማታውቀው እናቴ በቁጣ አይኗ እየተንቀለቀለ:: እንባዋ እየቀደማት:: እናቴ ከተናገረች ጉዳዩ መርሯል ማለት ነው !!

"ዝም በይ! አንች ነሽ የልብ ልብ የሰጠሻት:: እንደሰዎቹ እናቶች ስትንዘላዘል አትመክሪያትም? ጭራሽ ለእርሷ ከማበር:: ለነገሩ አንችስ ማን ሆንሽና - የእናቷ ልጅ!!" ብሎ እናቴን ኩም አደረጋት :: (እናቴን ከቡና ቤት አግኝቶ ነው ያገባት)

ወደ እህቴ ዞሮ፣ "አይንሽን እዚህ ቤት እንዳላየው:: መድሃኒያለም አይለመነኝ:: አንዱ ቦታ ሂጂ አንጥፌ እለምናለሁ እንጂ ያንቺን ገንዘብ ከእንግዲህ አልበላም...!!" አላት እየተንዘፈዘፈ::

"አባባ እኔ ካለ እናንተ ምን መሄጃ አለኝ ?" አለች ሳምሪ:: (ሳግ ባነቀው ድምፅ)

"መሄጃሽንማ ገፋሽ፣ ወርቅሽን ጭቃ ላይ ጣልሽው:: ሂጃ እዛ ከንቱ ጋር፣ አብረሽው በየጎዳናው ዙሪ! አባይ ማደሪያ ሳይኖረው አሉ..."

እህቴ ዝም ብላ ፀጉሬን ታሻሻለች:: አያያዟን ግን እስኪያመኝ ድረስ አጥብቃው ነበር፤ በጣቶቿ መቆፈር ዓይነት::ለአባባ ያላትን ፍቅር እናቴ ላይ ገድላ ልትቀብረው ያሰበች ነው የምትመስለው:: እንደውም በዚህ ሳምንት በጠና ታምሞ ነበር:: ተነስታ ወደከፍሏ ሄደች:: ተከትያት ሄድኩ:: ከፍሏ ውስጥ ገብታ እንደወትሮው ጫማዋን

አልቀየረችም:: ሻንጣዋን አነሳች ከፈተችው፣ አልጋዋ ትራስጌ የነበረውን የእዮብን ፎቶ ስታነሳ አለቀሰች:: በቲሸርት ጠቅልላ ሻንጣዋ ውስጥ አስቀመጠችው:: አንድ የቆየ ባዶ የሸቶ እቃ ወደ ቦርሳዋ ጨመረች::

"ሂድ ወደ ሳሎን" አለችኝ::

"አልሄድም" ብዬ እግሯ ላይ ተጠመጠምኩ:: ብር ብላ የምትሄድብኝ መሰለኝ :: እንቅ ! እጇ እስከደረሰበት አቅፊያት::
እቅፍ አደረገችኝ:: እቅፏ ላይ እንቅልፍ እንደወሰደኝ ትዝ ያለኝ ጠዋት ሰነቃ ነበር:: የለችም፣ የእዮብ ፎቶ የለም:: ሻንጣዋ የለም:: ጫማዎቿ የሉም:: ፎጣዋ የለም:: የጥርስ ቡርሽ፣ የጥፍር መቁረጫና መሞረጃዎቿ የሉም:: የእህቴ ትዝታዎች ቤቱ ውስጥ የሉም - ልቤ ውስጥ ብቻ:: ቤቱ ቤት ብቻ ሆኗል:: ላይ ቤቱ በረንዳ ሆኗል - እኔ በረንዳ አዳሪ::

ትራሱ ላይ፣ "ይሄን ለእማማ ስጣት፣ ይሄን ለእዮቤ እንዳትጥል!..." ከሚል ማስታወሻ ጋር የመቶ እና የሃምሳ ብር የብር ኖቶች::(የት ሄደች?) በጥድፊያ ሳሎኑን አልፌ ወደ በረንዳው ሄድኩ፣ አባቴ ውዳሴ ማሪያሙን በተመስጦ ይደግማል::

"አባባ ሳምሪስ ?" አልኩት ሳልፈራው::

"ሂድ ወዲያ...!!" አለኝና ወደ ውዳሴው 'አንች የማለዳ ብርሃን ነሽ፣ አንች መጠጊያ ላጡ...' ወደ ቤት ገብቼ...::

"እማማ ሳምሪስ ?" ፀጥ ብላ አየችኝና በማይሰማ ደካማ ድምፅ "ሄደች" ብላኝ ወደ ጓዳ ገባች ::

ተንደርድሬ ወደ ሰልኩ ሄድኩ:: አባባ ያየኛል ብዬ ሳልፈራ ደወልኩ፣ "ጤና ይስጥልኝ ቴሌ ነው ምን ልርዳዎት" አለ አንድ ጎርናና ድምፅ ያለው አፕሬተር::

"ሳምሪን ነው የምፈልገው፣ ሳምሪ እህቴን - አለች ? ነይ እኔንም ውሰጅኝ ብሎሻል በልልኝ:: 'እኔ እኮ እወድሻለሁ ለምን ትተሽኝ ሄድሽ' በልልኝ - ሳምሪ እህቴን"

"ማሙሽዬ ይሄ እኮ ቴሌ ነው...ሃሃሃሃ"

*** *** ***

ዲያስፖራው እዛው ጎረቤታችን ኑአሚን የምትባል የማታ ጭፈራ ቤት የምትሰራ ዘፋኝ አገባ:: አስተማሪ ቦይ ፍሬንዷን 'አፍንጫህን ላስ' ብላው:: ለእህቴ በተተኮሰው የህብት ጥይት ፍቅሯን ገደለች !!

*** *** ***

ቁራሌ የሚሰራ አንድ የሰፈራችን ልጅ አለ:: ከነስሙ 'ጃምቦ ቁራሌው' አንድ ቀን የሰፈር ልጆች ጋር "ኢላማ ኢላማ" ስንጫወት ደረሰና ኬሻውን አስቀምጦ ተቀላቀለን:: የእኛን ኢላማ ሰብረን ኢላማ የሚሆን ነገር ስናፈላልግ ድንገት ከእቃ ማስቀመጫው ውስጥ አንድ ጠርሙስ አወጣና አስቀምጦ ጠርሙሷን ለመስበር ድንጋይ አነሳን፣ጃምቦ ወረወረ - ሳታት:: ተረኛ እኔ ነኝ አነጣጠርኩ፣ ጠርሙሱን አየሁት:: ልቤ ደነገጠ:: ቀርቤ አየሁት - የሳምሪ የሽቶ ጠርሙስ!! ቢቆሸሸም ራሱ ነው::

"አንተ የት አባህ አገኘኸው ?" አልኩት ግራ ተጋብቼ ፤ እንባዬ መጥቶብኝ:: ሳምሪዬን ያገኘኋት ነው የመሰለኝ:: ሳምሪዬን ኢላማ አድርገን በድንጋይ ያባረርናት፣ ቤተሰቡ፣ ሰፈሩ፣ ጎብረተሰቡ፣ ዲያስፖራው...ሳምሪን የወገርናት...:: "ከእናንት ሀጢያት የሌለበት ይውገራት" ሲባል ዘራፍ እኛ፤ሀጢያት የለብንም:: እኛ ቅዱሳን:: እኛ ንፁህን ብለን ሳምሪ ላይ የወረወርን:: መሄጃ የሌላትን ወፍ በድንጋይ ከደሃ ጎጆዋ ያባረርናት::

"እረ ማሪያምን ሰርቄው አይደለም፣ እህትህ ሻንጣ ይዛ የሄደች ቀን እዛ ሱቁ አካባቢ አገኘችኝና 'ይሄን ትገዛለህ...?' ስትለኝ ብር ከስሙኒ ገዛኋት:: የሚፈለግ መስሎኝ ነበር:: ግን በቃ አይፈለግም ሲሉኝ ዝም ብዬ አስቀምጬው ነበር::ከፈለግከ ውሰደው" አለ ጃምቦ::

ጠርሙሱን ወሰድኩት :: እቅፍ አድርጌ፣ በቲሸርቴ ስር ሰውነቴ ላይ ለጥፌ:: (ይሄ ጠርሙስ ባዶ የሆነው ምን ሆኖ ነው?ሽቶው ሳምሪ የምትባል ሚስኪን፣ እዮብ የሚባል ፍቅሯ እግር ላይ ደፍታው ነው፣ በቃ እንደዛ ነው:: 'ሽቶውን ስለምን እናባክነዋለን፣ ሸጠን ለድሀ አንመፀውተውምን?' ብለዋት ነበር ጎረቤቶች አባቴን ጨምሮ !!) ከሳምሪ የቀረኝ ነገር አንድ ባዶ የሽቶ ጠርሙስ ብቻ - ከኋላ ጓደኞቼ ሌላ ጠርሙስ ሲሰብሩ ሰማሁ - ከሸሸሸሸ!!

አስር የሽቶ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ - አንዱን ስንከሰከሰው ምንም ይቀራል፣

ምንም ይቀራል...

ምንም ይቀራል...

ምንም ይቀራል...

(ተጠንቀቅ !! ባንዲራውን አውርድ፣ ጠይሙን ባንዲራ - ለሞላ ንፋስ እንዳይውለበለብ የከለከልከው ቆንቋና ሁሉ !! ባወረድከው የከብር ባንዲራ ፋንታ ድሪቶህን ሰቀል ! ቀለም አልባ፣ ታሪክ አልባ ድሪቶህን !! ቡቱቷም::)

ሂሳብ ምናባቱ ያገባዋል ስለ ስሜት - ቁጥር አባቱ ይብላና !!

ሌላ ቀን ማታ፣ አባባ አንድ ነገር ጠየቀኝ:: ሰርጉ ባለፈ በሰንት ወሩ:፣ "ይሄ የሰርግ መጥሪያ ሌሊት ሌሊት እንደ አብሪ ትል የሚያበራው ለምንድን ነው ?"

ረጋ ብዬ መለስኩለት - እንደ ሳይንቲስት፣ “ጽሁፉ ከፎስፎረስ ስለተፃፈ ነው::”

አባባ ዝም ብሎ ቆየና፣ “ወደዛ ወስደህ ጣልልኝ !!” አለ

መኝታ ቤቴ ወስጄ የሳምሪ ሸቶ ጠርሙስ ጎን አስቀመጥኩት:: ማታ መብራቱን ሳጠፋ ካርዱ ላይ ያሉት ፅሁፎችና ጌጣጌጦች ተብረቀረቁ:: ግን ‘ፎስፎረስ’ ምንድን ነው:: ካርዱ ያበራል የሳምሪ የሸቶ ጠርሙዝ ግን አያበራም::

ያልታደለ ዘመን ላይ ቅጥፈት ነው የሚያብረቀርቀው ::

ይነጋል ! የሳምሪ ጠርሙስ ያበራል !

ይነጋል - ቀጣፊው ካርድ ይጨልምበታል::

ይነጋል ! የበራው ሁሉ ብርሃን አለመሆኑ የሚገለጥበት ዘመን ይመጣል !

አንስቼ በጨለማው ውስጥ ወረወርኩት:: ራሴ እስኪፈነዳ ጨለማው ላይ አፍጥጬ አሰብኩ::

እህት አለችኝ:: ጥቁር ዘንፋላ ፀጉር ያላት:: ሳቋ ‘እንደ ፎስፎረስ’ በጨለማ የሚያበራ:: እህት አለችኝ እጆቿ ፀጉሬ ላይ ሲርመሰመሱ የሚያስፈነጥዙኝ:: እህት አለችኝ - ሙዘቃ ድምፅ ያላት:: እህት አለችኝ ለተራበ ዱለት የምትሰጥ-ታድዬ !! እህት አለችኝ አንድ ቦታ...ስሟ በከፉ የማይነሳ : ሴቶች ላይ ከፉ ሊናገር የጀመረ ሁሉ እሷን ሲያይ ዝም የሚልላት ጨዋ እህት አለችኝ::

እህት አለችኝ ሳምሪ የምትባል:: ፍቅሯን ሸጣ በሊሙዚን ከመሄድ የሸቱ ጠርሙስ ለቁራሌ ሸጣ በታክሲ መሄድን የመረጠች:: ያላትን ለእማማ ሰጥታ የዓለምን ችግር በብር ከስሙኒ ልትፋለመው የወጣች::ስሟ ሳምራዊት ነው !! የአባቷን ስም አላውቀውም:: አባት የላትም:: እኔም አባት የለኝም !!

ኃይለኛ ዝናብ ጣለ::

2 ተሰቀለ ቢሉኝ ‘ባርኔጣው’ ነው ብዬ

የአራተኛ ዓመት ተማሪዎች ሳለን፣ አስቻለው የሚባል ጓደኛችን ለስምንት የምንጋራው ዶርም ውስጥ ራሱን በቀበቶ ሰቅሎ ተገኘ:: አስደንጋጭ፣ አሳዛኝ ጉዳይ !! አስቻለው የለየለት ሱሰኛ ነበር (የሞተ ሰው ወቀስክ አትበሉኝና...):: ያጨሳል፣ ይቅማል፣ ይጠጣል...(ያገኘውን ሁሉ ይጠጣል...በተለይ ጠላ ነፍሱ ነው):: ውሀ እንኳን ሲጠጣ ‘ትፍ ትፍ’ ይላል፣ በጠላ ገፈት ለምዶበት !! ሀሺሽ ምናምንም ከመውሰድ አልፎ ግቢ ውስጥ ያከፋፍል ነበር:: ኧረ አበዛኸው እንዳትሉኝ እንጂ ሴተኛ አዳሪ ሳይቀር ዶርም ይዞ ይመጣ ነበር (አልፎ አልፎ እንግሊዝኛ ጣል የምታደርግ ሴተኛ አዳሪ ከገጠመቻችሁ፣ ግቢ ጎራ ብላ ልታውቅ ትችላለች ብላችሁ ጠርጥሩ::)

ያው አንዳንዴ ደግሞ ታጥቦ የተሰጣ ልብስ ያነሳ ነበር እየተባለ ይታማል(እኔ ‘ንኳ ቲሸርቴን ከወሰደብኝ በኋላ እንዲህ ሲል አስፈቅዶኛል...‘አብርሽ...ያንተ መሆኗን ሳላውቅ ያችን ሁልጊዜ የምትለብሳትን ሰማያዊ ቲሸርት ወስጃታለሁ...’):: እና አስቻለው ራሱን ሰቅሎ ሞተ ::

ታዲያ ብዙ ተማሪዎች እኛ ዶርም እየመጡ አስተዛዘኑን፤ “አስቹ አሪፍ ልጅ ነበር...አይዞን.... ወይ አስቺ ሆዱኮ ንፁህ ነው ፤ ላፉ ይናገራል እንጅ...አንዴ ምን አደረገ መሰላችሁ...” እያሉ ስለደግነቱ ስለቸርነቱ እንደጉድ አወሩ ::ሲቆይ ዶርማችን በር ላይ በቀይ ተፅፎ የተገኘው ሙሾ እንዲህ ይል ነበር፤

ተሰቀለ ቢሉኝ ባርኔጣው ነው ብዬ፣ (የዲግሪው ቆብ)
ተሰቀለ ቢሉኝ ያ ሱሪው ነው ብዬ (የነበረው አንድ ያረጀ ጅንስ ሱሪ ብቻ ነበር)
ተሰቀለ ቢሉኝ ‘ግሬዱ’ ነው ብዬ
ለካስ አስቻለው ነው ትልቁ ዱርዬ !!

ቢከፋንም ነገሩን በቅሬታ ፈገግታ አለፍነው (ይቅርታ...አላለፍነውም !):: ማታ ግማሹ ተኝቶ አንዳንዶችም አልጋቸውን ጋርደው እያጠኑ...አስናቀ የሚባለው የዶርማችን ልጅ፣ “ግን ምን ለማለት ተፈልጎ ነው ?” አለ ፊቱ ላይ ቁጣ እየተንተገተገ፤ እኔን ነበር የጠየቀኝ::

ጫማዬን እየፈታሁ ነበር ልተኛ::

"ምኑ አስኔ" አልኩት አይኔን ከጫማ ማሰሪያዬ ላይ ሳልነቅል...

በር ላይ የተፃፈው ግጥም ነዋ !!"

"ያው ሙድ ለመያዝ ምናምን ነዋ የሚሆነው...የግቢ ነገር ታውቀው የለ...ያንተ ሀዘን የሌላው ሀዘን ላይሆን ይችላል" አልኩ ቀለል አድርጌ...

"ኖ ኖ...ሙድማ አይደለም...ሆን ተብሎ የጎጃምን ህዝብ ታሪክ ለማጉደፍ የተሰራ ሴራ ነው" ብሎ ጠረጴዛውን በቡጢ ደቃው::

"ኧረ...አስኔ ምን ያገናኘዋል...ጎጃም እዛ ማዶ...ዩኒቨርስቲው እዚህ..."

"ዩኒቨርስቲ እንጂ ስንቱን ታሪክ ኩል የሚኩል...ስንቱን ጥላሸት የሚቀባ የተንኮል ማጀት::"

"ቆይ...አስቻለው የሽሮሜዳ ልጅ...የተፃፈው ስለሱ...እና ጎጃም..." አልኩ ሳቅ እየተናነቀኝ::

"ተሰቀለ ቢሉኝ ባርኔጣው ነው ብዬ፣
ለካስ በላይ ኦሯል ትልቁ ሰውዬ"

የሚለውን ግጥም እኮ ነው ቀይረው ለማንም ዱርዬ የሚጠቀሙበት..."

"አይ...አስቻለውንማ 'ማንም' አትለውም፣ አይደብርህም ትላንት ተለይቶን ዛሬ..." አንዱን ጫማዬን ፈትቼ አንዱን ሳልፈታ ከርከር...

"አይ ዶን ኬር...የበላይ ክብር በማንም ደደብ አይጎድፍም..." አለ:: እንደዛሬው ሲበሳጭ አይቼው አላውቅም::በጣም እየጮኸ ስለነበር የሚናገረው የዶርም ልጆች ከተኙበት እየበረገጉ ተነሱ:: የሚያጠኑት ግርዶሻቸውን ገለጥ እያደረጉ ብቅ አሉ::

"ምንድን ነው ሰላም አይደላችሁም..." አለ ገብረ መስቀል በአስናቀ ጩኸት ከእንቅልፉ በርግጎ ተነስቶ::

"ማን ጠራህ አንተን ?!" አለ አስናቀ በበለጠ ቁጣ ለነገር ተጋብዞ::
"እ..."

"ደንቆሮ"

"ማነው ደንቆሮ" አለ ገብረ መስቀል ሕልም ይሁን እውነት ግራ ገብቶት::
"አንተ ነሃ ! ሴታ ሴት ! በር ላይ እየተደበቅክ የሰው ታሪክ ከማጉደፍ እንደ ወንዶቹ ፊትለፊት አትናገርም..."

"ዋይ...ምን ጉድፍ ታሪክ ነው እሱ...አተ...ግሬድ ተለጠፈ እንዴ ?" አለ ገብረ መስቀል:: የታሪክ ተማሪ ነው፣ ቀልድ መስሎት ነበር::

"በላይ ሀገር አላስገነጠለም ! በላይ ወንዱ በዘር አልከፋፈለንም ! ለአንድ ኢትዮጲያ ሕይወቱን የሰጠ ጀግና ነው::"

"ዋ...ይ ታዲያ በዚህ ሌሊት በላይ በላይ ምትሎው ሙን ሁነ ኖው...?"

"በላይን እንኳን በር ላይ የተፃፈ ዝባዝንኬ፣ ባህር በር ላይ በመርከብ የተዘረገፈ ሰላቶ ጣሊያን ከብሩን አልነጠቀውም::"

"ባከህ አትጩህብን እናጥናበት" አለ ቶሎሳ ከግርዶሹ ብቅ ብሎ::

"ዝም በል ባከህ ! አንተ ላይ ማን ደረሰ..."

"ጩኸትህ ረበሸኛ" (ቶሎሳም የታሪክ ተማሪ ነው::)

"ጩኸቴ ጩኸትህ ነበር ቢገባህ...በላይ ላንተም ከብር ነበር የታገለው...ኢትዮጵያዊነት ስሜት ቢኖርህ ይቆጭህ ነበር..." አለው ሽቅብ ወደ ቶሎሳ አልጋ እየተመለከተ::

"ማነው የኢትዮጵያዊነት ስሜት የሌለው?"
"አንተ ነሃ ! ለስሙ የታሪክ ተማሪ ነህ ! በርህ ላይ ታሪክ ታንክ እንደሄደበት የቤት መኪና ተጨራምቶ እየተጻፈ አንተ ጋርደህ የአውሮፓ ተረት ታነባለህ...'ማንትስ በመርከብ ተጉዞ አሜሪካን አገኘ' በል የራስህ አገር ከእጅህ ላይ እየጠፋች::"

"አብርሃም...ኧረ በክርስቶስ ይሄን ሰው ፀበል ውሰዱት" አለ ዲንሳሞ እየሳቀ:: ቀልድ ይቀናዋል፣ ሁልጊዜ ሳቂታ ነው::

"ስርዓት ! ፀበል መቀለጃ መሰልህ እንዴ" አልኩት በብስጭት:: ጴንጤ ስለሆነ 'አርቶዶክስ እምነቴ ላይ ምናባቱ ያላግጣል' ብዬ ቱግ አልኩ ::

"እንዴ ፀበል ያድናል ትሉ የለ እንዴ ?"

"መቀለድ ሳይሆን ሞክረው...አንተም ከዚህ ዕብደትህ ትፈወሳለህ" አልኩት አፍጥጬበት !በዕምነትና በሚስትማ ቀልድ የለም (ሚስት እንኳን ....)::

"እኔማ ቃሉ እንደሚል፣ 'መዳን በሌላ በማንም የለም ትድኑበት ዘንድ..."
"ዝጋ እዛ !የምትሰብከውን ስበክ...ይሄን ተረትህን..."

"ጌታ ይገስፅህ"

"ማንን ነው የሚገስፀው አንተ ?..." በብስጭት ከአልጋው ላይ ጎትቼ ላወርደው ስንደረደር የጫማ ማሰሪያየ አወላከፈኝና አልጋው ስር ጥቅልል አልኩ::

ዲንሳሞ ጭራሽ መዘመር ጀመረ...
"ነብሱ በትዕቢት ያበጠ...
ጠላቴ ተገለበጠ.... ሃሌ ሉ...ያ"::

ተነስቼ ላጋጨው ስል ሄኖክ ከዛ ተወርውሮ መጥቶ ገላገለን ::

ዲንሳሞ ሊያቆም ነው..."እሽ ካልቻላችሁ ሪፈር ጻፉለት እንፀልይለት...በእየሱስ ስ.....ም!" አለ እጁን ወደ አስናቀ ዘርግቶ እየሳቀ...::

"መናፍቅ ! ዋና ታሪክ አጥፊዎቹ እናንተ ናችሁ...ምን ታሾፋለህ...ዘረኞችን አትገስፅም?!" አለ አስናቀ ወደ ገብረመስቀል በለገጩ እየጠቆመ::

"አተ አትጨሚለቅ...ሞታገስ አታውቅም ? ዙም ብለህ ሰው ጭቅላት ላይ ፉጥ ትላለህ...ጩምላቃ" ብሎ ዘሎ ከመኝታው ወረደ:: ...ዶርሙ...ቀውጢ ሆነ ::

አስናቀ ባለ በሌለ ኃይሉ ገብረ መስቀልን ሲደረግመው ከአልጋው ብረት ጋር ተጋጨ:: ወዲያው የገብረ መስቀል እርግጫ አስናቀን ከፉ ቦታ ላይ አገኘው:: እንደምንም አገላገልናቸውና ገብረ መስቀል ወጥቶ ሄዶ ሌላ ዶርም አደረ:: በቀጣዩ ቀን አስናቀ ከየት እንደተወረወረ ባልታወቀ ድንጋይ ተፈንክቶ ክሊኒክ ዋልን :: ነጭ ፋሻውን አናቱ ላይ ጠምጥሞ ሲፎክር፣ ቅስናውን የገፈፉት የእግዜርን መንግሥት ይቆየኝ ብሎ ለምድራዊ መንግሥት የዘመተ አርበኛ ቄስ ይመስል ነበር :: በዚህች መነሻ ሰላም ጠፋ:: ግቢ ውስጥ በአንድ ሳምንት ብቻ አራት ተማሪ ተፈነከተ...ቀላልና ከባድ ጉዳት !

የተፈነከቱ ተማሪዎች ዝርዝር:-
ሰኞ.... አስናቀ
ማክሰኞ ማታ.... ጎይቶም
እሮብ.... አረጋ
ሐሙስ.... ተክላይ
አርብ.... መላኩ
ቅዳሜ.... ትርሀስ (የሴቶች እኩልነት)
እሁድ.... አትጠገብ (ቤተ-ክርስቲያን ስትሄድ...)
ሰኞ ማታ.... ሚስኪኑ አብርሃም !! ሰምታችሁኖል ? አብርሃም እኮ እኔ ነኝ !!

ስለአፈነካከቴ አጭር ገለፃ...
ሰአቱ ማታ 3:00 ሰዓት አካባቢ ይሆናል...በግ ተራ...ሂሩት እና እኔ ጨለም ያለ ቦታ መርጠን በነፋሻው አየር እየተሳሳምን ነበር::

ሚ...ሚኧኧኧ..."እስከዘላለሙ እወድሻለሁ ሂሩትዬ"

...ኧኧኧሚ፣ "አ..ብርሽየ ለምን ስልክ ስደውል ትዘጋብኛለህ ?"

..."ላይብረሪ ነበርኩ የኔ ማር...ኧኧኧ"

"አብርሽ ምንም ቢፈጠር እስከዘላለሙ አብሬህ መሆን እፈልጋለሁ"

...ቀኝ እጇ በቲሸርቷ ስር አልፎ የጡት ማስያዣዋን ጠንካራ ከፈፍ መሰርሰር ጀመረ:: (ጡት የላትም ለምንድን ነው የጡት ማስያዣ የምታደርገው ?! አንዳንድ ሴቶች በሌለ ጡት የጡት ማስያዣ ሲያደርጉ ልባቸውን ለመያዝ የሚጠቀሙበት ነው የሚመስለኝ...ታዲያ ጡት ከሌላት እጇ ምን እየፈለገ ነው ? ምን አፈላሰፈኝ ዝም ብዬ አልሰምም ኧኧኧሚ...)

ዓይኖቻችንን ጨፍነን በፍቅር አየር ላይ መንሳፈፍ ጀመርን...ሚፅፅፅፅፅ...ድንገት ትልቅ '...ጓ...!!!!!'። ከፍቅር ሰማይ የሚያምዘገዝግ የአየር መቃወሚያ !! ከነበርኩበት ከፍታ አምዘግዝጎ እውነተኛው ዓለም ላይ የፈጠፈጠኝ ድንጋይ ከኋላዬ ራስ ቅሌን ነረተኝ !! "ሂሩት ባል አላት እንዴ?..." የሚል ሀሳብ ብልጭ አለብኝና ራሴን ስቼ ወደቅኩ::

ክሊኒክ ውስጥ ስነቃ ግቢው ቀውጢ ሆኗል...ፌዴራል ፖሊስ...የአመፅ መበተኛ መኪና... የተማሪ አመፅ...ጩኸት... መዝሙር !!
"አስቻለው ለምን ለምን ሞተ ?"
"አብርሃም ለምን ለምን ሞተ...?"

"ምን ? አ ብ ር ሃ ም...?" አይኔን ስገልጥ የዩኒቨርስቲያችን ነርስ (ያምሮት) እና ሦስት ፌዴራል ፖሊሶች ቆመዋል:: "ሲስተር!...አብርሃም ለምን ሞተ ሲሉ ሰማሁ ?..." "አዎ ! እንዴት ነህ አሁን ?" ጣረ ሞት የጠራት ይመስል ደንግጣ::

"አንችኑ ልጠይቅሽ እንጂ ተማሪዎቹ እንደሚሉት ሞቻለሁ ወይስ ....????" ከት ብላ ሳቀች:: እንደምንም ተነስቼ አልጋው ላይ ቁጭ ስል፣

"ስማ..." አለኝ ፌዴራል ፖሊሱ::

"አ...ቤት" አልኩ በድንጋጤ የጨበጠውን ጥቁር ዱላ እያየሁ:: ዱላው አፍ አውጥቶ የጠራኝ ነበር የመሰለኝ፣

"ተሻለህ ?"

ውይ ለዚህ ነው እንዴ..."አዎ አሁንማ..." ብዬ ከአልጋዬ ላይ ወርጄ ወደ በሩ ሳመራ፣

"ወዴት ነው ?" አለኝ በግርምት እያየኝ::

"ወደ ውጭ" መለስኩ::

“ተመለስ !!” ‘ዘሩ ቀለጠ’ አለ ያ ሰውዬ !! ለካስ ሦስት ፖሊስ ሉኔው ነበር !!

“አብርሽዬ እስኪ ተረጋጋ...ከርስቶስ እንኳን በሦስተኛ ቀኑ ነው ከሞት የተነሳው...ገና ባንድ ቀን የክሊኒክ በር ከፍተህ ሰላም ለእናንተ ይሁን ልትል አማረህ?...ሂሂሂሂ” አለች ነርሷ...::

“ሲስተር ምንድን ነው ?”

“እስረኛ ነህ !!” አለች በሹክሹክታ !!

“እ...”

“ሰ ም ተ ኻ ል”
“...ዩኒቨርስቲው ውስጥ በዘር በተነሳ ግጭት አንተና አስቻለው ባልታወቁ ሰዎች ተገድላችኋል፤ ! አሁን ተማሪው ለምን እንደተገደላችሁ እንዲገለፅለት እየጠየቀ ነው:: እና ደግሞ ግጭቱን ያስነሳችሁት አንተ...አስናቀ እና ...ዲንሳም ናችሁ:: የኃይማኖትም ጉዳይ አለበት...አብርሃም አርፈህ ብትማር ምናለበት...” አለችኝ:: የመጨረሻ ቃሎቿን ኮስተር ብላ ነበር የተናገረቻቸው:: ወዲያው ፌዴራል ፖሊሱ ቆፍጠን ባለ አነጋገር፣
“አልጋህ ላይ ተሰቀል!” ብሎ አዘዘኝ::

“እሺ...” ብዬ ወደ አልጋው ተጠጋሁ:: ድንኩ አልጋ እንደ ቀራኒዮ ራቀብኝ:: በሁለት ጊዜ ሙከራ አልጋው ላይ ተሰቀልኩ::

በሀሳቤ...

ተሰቀለ ቢሉኝ ባርኔጣው ነው ብዬ (የዲግሪው)
ተሰቀለ ቢሉኝ አስቻለው ነው ብዬ
አብርሽም ታዘዘ ኧረ እናንተ ሆዬ....

ብዬ ቀና ስል...ከነርሷ ትልልቅ ጡቶች መሐል መስቀሏ ተንጠልጥሏል:: መስቀሉ ላይ ጌታ እየሱስ ተሰቅሎ አየሁት::
“ሂሩትዬስ...” ብዬ ነርሷን ጠየቅኳት:: ፍቅራችንን ታውቃለች፣ ስንታመም ሁሉ ወደ ክሊኒክ የምንመጣው ከሂሩት ጋር አብረን ነበር::
“ሂሩትዬማ...አንተ ተፈንክተህ እንደወደቅክ ሂሩት ተያዘችና ሦስቱም ፖሊሶች በየተራ ‘ታውቂዋለሽ ?’ እያሉ ሲጠይቋት፣ ሦስት ጊዜ ‘አላውቀውም’ ብላ ወደ ቤቷ ሄደች” አለችኝ አሁን መሰቀል ሙሉ ሆነች...ኤሎሄ፣ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ?

ከሰሀራ በታች 3

የፍቅርተ ጂንስ ሱሪ ታጥቦ ከተሰጣበት የልብስ ማስጫ ገመድ ላይ ጠፋ:: "የትኛው ሱሪ?" የሚል ይኖራል፤ - ፍቅርተ የነበራት አንድ ሱሪ ነበር:: የጠፋውም ይሄው አንድ ለናቱ የሆነ ሱሪ ነው:: የመንደሩ ሱሰኛ ጎረምሶች ለዕለት ሱሳቸው ማስታገሻ ወስደው ሸጠውት ይሁን አልያም ሞገደኛ ነፋስ እያግለበለበ ወስዶ አንዱ ቂርቂራ ሸጉጦት እግዜር ይወቅ:: ግራም ነፈሰ ቀኝ ከተገዛ ገና ስድስት ወር ብቻ የሆነው፣ ግርጌው ቀበኛ ከብት አኝኮ እንደተወው ጨርቅ የተተፈተፈው የፍቅርተ ጥቁር ጅንስ ሱሪ ታጥቦ ከተሰጣበት ገመድ ላይ ጠፋ:: ትልቅ የአገር ቅርስ የጠፋ ያህል ነበር አንጀቴ ቁርጥ ያለው:: ደምና አጥንት የተከፈለለት የአገር ድንበር የተቆረሰ ያህል ነበር ውስጤ በቁጭት የተንገበገበው::

በእርግጥ ይሄ ሱሪ በመታጠብ ብዛት የልጅነት ጥቁር ቀለሙ ተገፍፎ ግራጫ መሆን ጀምሮ ነበር:: ኧረ እንደውም እንደ ሰው ፀጉር በስተርጅና ነጫጭ ጭረት ጣል ጣል ያደረገበት ሱሪ ነበር:: ቢሆንም እርጅናው ከሱሪው ህያው ዋጋ ላይ ሽራፊ ሳንቲም ሊቀንስ አይቻለውም:: እርጅና የማያደበዝዘው እውነት፣ የዘመን ብዛት የማያጠፋው ሃቅ አለና፤ የዛ እውነት ማህደር ነው የተወሰደው::

የፍቅርተ ሱሪ ጠፋ ማለት የመንደራችን ባንዲራ ጠፋ እንደማለት ነው:: ይሄ ሱሪ ተራ ሱሪ ብቻ አልነበረም፤ የማንነት መቋጠሪያ ጨርቅ፣ የተገፉ ድሆች እንባ ማበሻ መሃረም፣ የፍቅር መከተቻ ከረጢት ነበር:: ምን ያደርጋል ! ታጥቦ ከተሰጣበት ገመድ ላይ ጠፋ ::

አንዳንዱ የደላው መንደርተኛ የፍቅርተ ሱሪ መጥፋቱን ሲሰማ "ይሄ ሁሉ ላይ ታች ማለት ለአንድ አሮጌ ሱሪ ነው ?" እያለ ወደየ ጉዳዩ ይጣደፋል:: "በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት" ቢባልም ቅሉ እንዴት ሰው በራሱ ቁስል እንጨት ይሰድዳል? ስለፍቅርተ ሱሪ የማይመለከተው ማነው?

እኔ በበኩሌ የፍቅርተ ሱሪ ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ ባይ ነኝ:: ስንለው ስንጮኸው የኖርነው ቃል ነበር የፍቅርተ ሱሪ ! አብሮን የኖረ ቃል ጨርቅ ለብሶ የተከሰተው በፍቅርተ ሱሪ ነበር:: ድንገት የቀኝ እጇን ስመለከተው ሁለት ጣቶቼን ከቦታቸው ላይ ባጣቸው እንኳን የዚህን ያህል የምደነግጥ አይመስለኝም:: እዚህ መዲናችን ውስጥ ያለው የአፍሪካ ህብረት ሕንፃ ድንገት ከስሩ ተነቅሎ የደረሰበት

ጠፋ ቢባል የፍቅርተን ሱሪ ያህል አያስደነግጠኝም፤ ኧረ ፍቅርተ ራሷ ብትጠፋ የሱሪዋን ያህል አታስደነግጠኝም:: ስለዚህ ሱሪ የተዳፈነ ተሰፋ፣ የተኮላሸ ፍቅር አለና ሱሪው ሱሪ ብቻ አልነበረም::

ሱሪው የጠፋ ቀን ከሰዓት በኋላ ወደ ስምንት ሰዓት አካባቢ ከምማርበት ኮሌጅ ስመለስ እማማ አመለወርቅ በራቸው ስር ሁልጊዜ የሚቀመጡባት ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ተቀምጠው አገኘኋቸው:: ዓይናቸው ቡዝዝ ብሎ በሀሳብ በመመሰጣቸው እስካናግራቸው ድረስ አጠገባቸው መድረሴንም አላዩም ነበር:: ለወትሮው እዚህች ድንጋይ መቀመጫ ላይ የሚቀመጡት እጃቸው አጠር ሲል ለዕለት ቡና ብር ቢጤ ሲቸግራቸው ነበር:: የድንጋይ ወንበሯ የመተከዣ መድረካቸው ናት::

“ማዘር ምነው ሰላም አይደሉም እንዴ?” አልኳቸው፤

ቀጥ ብለው እንባ በኳተሩ ዐይኖቻቸው ተመለከቱኝና ሳግ በተናነቀው አሳዛኝ ድምፅ ፡ “የፍቅርየን ሱሪ ወሰዱባት አብርሽ!” አሉኝ፤ ሊያናግሩኝ ቀና ሲሉ እያለቀሱ እንደቆዩ ፊታቸው ላይ ዳናውን የተወ እንባቸው ይናገራል::

“እነማን ናቸው የወሰዱት?” አልኳቸው የሰማሁትን ባለማመን፤ ቅስም ከሚሰብር ዜና ኋላ የተከሰተ የጅል የሚመስል ጥያቄ::

“ምናውቄ ብለህ አብርሽ ! ከዚህ ከተሰጣበት ገመድ ላይ አንስተው ወሰዱት” አሉና እንባቸውን ዘረገፉት:: ድህነት እንደ ሸንኮራ መጥጦ ካደረቀው ሰውነት ይሄን ያህል እንባ ይወጣል ብዬ አላሰብኩም ነበር:: ሕይወት ምንጊዜም አዲስ እንባ አላት::ከእንባቸው የበለጠ ፊታቸው ላይ ያረበበው ሐዘንና ምሬት ያሳዝን ነበር::አንጋጥጬ የልብስ ማስጫ ገመዱን ተመለከትኩት:: ወዲህ የኤሌክትሪክ ምሰሶ ላይ ወዲያ ደግሞ የአንዲት ጎረቤት የቤት ጣራ ማገር ላይ የተወጠረው ገመድ የተወረረ ከተማ መስሏል:: ባንዲራውን እንዳወረዱበት የሰንደቅ ምሰሶ ትከሻው ቀሏል:: ባዶ !! ለፍቅርተ፣ ለእኔ፣ ለእማማ ዓመለ፣ ለመንደሩና ለአገሩ ባዶነትን ትቶልን የሄደው ማነው?

ይሄ ገመድ ባዶውን ውሎ አያውቅም ነበር:: ቢጠፋ ቢጠፋ የጉግሳ አውራ ጣቱ የተሸነቆረ ካልሲ ወይም አሁን የጠፋው የፍቅርተ ሱሪ ተሰጥቶበት ነበር የሚውለው:: የፍቅርተ ሱሪና የጉግሳ ካልሲ ሁልጊዜም ገመዱ ላይ ጎን ለጎን ተሰጥተው ስለማያቸው የልብ ወዳጆች ይመስሉኝ ነበር ::የፍቅርተ ሱሪ ከፍ ያሉት ንቀውት ዝቅ ብሎ የካልሲ ጓደኛ የሆነ:: ካልሲውም ቢጤዎቹ ንቀውት ቀን ከገፋው ሱሪ ጋር የዋለ ዓይነት::

አንጋጥጬ ስመለከት ከገመዱ በላይ ጥርት ያለው ሰማይ ተዘርግቷል:: የፍቅርተን ሱሪ የወሰዱት ሌቦች ለወትሮው ሰማዩ ላይ የማይጠፋውን ደመና የወሰዱት ይመስል ነበር:: ሰማዩ ባዶ! የልብስ ማስጫው ገመድ ባዶ!! አይ አይ ሰማዩ እንኳን ባዶ አልነበረም:: ነግቶ የረፈደባት የምትመስል ግማሽ ጨረቃ ትታያለች:: የሱሪ ሌባው ግማሿን ጨረቃ ሸርፎ የወሰዳት ይመስል::

ቆይ ግን ሱሪውን የወሰደው ሌባ ከሆነ ሌባውን ምን ነካው? እንዴት የፍቅርተን ሱሪ ይወስዳል? እሺ ነፋስም ከሆነ ንፋሱን ምን ነካው ? አቧራ ያስነሳ፣ የቤት ጣራ ይገነጣጥል ቢፈልግ ! ያንን ከሰፈራችን ወደታች ያለውን 'የአድባር ዛፍ' ከስሩ ገርስሶ ይጣለው ! ግን እንዴት የፍቅርተን አንድ ለአናቱ የሆነ ሱሪ ይወስዳል ? ምን ቁርጥ አድርጎት የመንደራችንን ባንዲራ ይደፍራል ? በሌባው ተቆጣሁ :: በነፋሱ ተቆጣሁ :: በፈጣሪም ተቆጣሁ :: መምሬ ልሳኑ ታዲያ (የእማማ አመለ ንስሃ አባት) የሱሪውን መጥፋት ሲሰሙ፣ እማማ አመለን ለማፅናናት ብለው ይሁን አልያም አምነውበት እንጃ ብቻ ጥቅስ አጣቀሱ፤ "ላለው ይጨመርለታል፣ ከሌለው ግን ያለውም ይወሰድበታል - ወለተ ኪዳን አይዞሽ" በዚህ ማፅናኛቸው በጣም ተበሳጨሁ፤ እንደውም በፈጣሪ ላይ የተሰማኝ ቅሬታ ተባባሰ::

ፈጣሪ የሌባው እጅ ወደ ፍቅርተ ሱሪ ሲዘረጋ እንደ ደረቅ እንጨት ድርቅ አድርጎ ማስቀረት ይችል ነበር:: ነፋስና ማዕበልን የሚገስጽ ፈጣሪ እንዴት ዝም አለ ? አሳት ከሰማይ የሚያወርድ አምላክ ከዚህ በላይ በደል፣ ከዚህ በላይ ግፍ ምን አለና ታገሰ ? የፍቅርተን ሱሪ የወሰደው ንፋስ ከሆነም መገሰጽ ይችል ነበር፣ ስለምን ዝም አለ ? እንኳን አጋጣሚውን አገኘሁ እንጂ ፈጣሪ ጋርማ በፍቅርተ ጉዳይ ብዙ ጥያቄ አለኝ ! ብ....ዙ ! ሲጀመር ፍቅርተን ስለምን እንዲህ አድርጎ ፈጠራት...እኮ ለምን !? ለእሱስ ለስሙ ጥሩ ነው ?

**** **** ****

"የእናት ሆድ ዥንጉርጉር ነው" ይሉት ብሂል ስጋ ለብሶ የተገለጠው እማማ አመለ ቤት ነበር:: እማማ አመለ በመልክ ይሁን በባህሪ የማይገናኙ፣ ከፆታቸው በቀር አንድ የሚያደርጋቸው አንድ ነገር እንኳን ፈልጎ ማግኘት የሚከብድ ሁለት ሴት ልጆች ያሏቸው፣ እድሜያቸው የገፋ ደግ ሴት ነበሩ :: ከሁለት ክፍል ቤታቸው አንዷን ተከራይቼ ለአራት ዓመታት ቤታቸው ውስጥ ኖሬያለሁ::

ለስሙ ሁለት ክፍል ተባለ እንጂ አብረን በደባልነት እንደኖርን ነበር የሚቆጠረው:: እማማ አመለ ከሁለቱ ልጆቻቸው ጋር የሚኖሩበትን ክፍል ረግጬ የእኔ ክፍል ወደሆነችው ጓዳ አልፋለሁ፤ አንዳንዴ ታዲያ ወደ እኔ ክፍል ለማለፍ የተደረደሩትን እቃዎች መዝለል ይኖርብኛል:: በተለይ ቡና ከቀራረበ ረከቦቱን መራመድ ግድ ነበር:: የእኔ ክፍል ከእነ እማማ አመለ ክፍል የሚለየው በአንድ ስስ መጋረጃ ነበር :: እኔ ቤት ሆኖ የእነማማ አመለን ቤት አጠቃላይ እንቅስቃሴ መመልከት ይቻላል ፤ ድንበራችን ስስ መጋረጃ ነበርና::

ፍቅርተ የእማማ አመለ ሁለተኛ ልጅ ናት:: ፍቅርን ጨምሮ ሁሉንም ነገር የነሳት፣ የአርባ ቀን እድሏ በየቀኑ አርባ የሰቆቃ ጅራፍ የሚያሳርፍባት መልከጥፉ ወጣት ናት:: ልቅም ያለች መልከ ጥፉ ነበረች:: ቁንጅና እንደተመልካቹ ነው ቢባልም ፍቅርተን "ቆንጆ" የሚል ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም፤ ራሷን ፍቅርተን ጨምሮ::

ፍቅርተን ድንገት የተመለከታት ሰው ድንገት የተከሰተ ሰይጣን ፊት የቆመ ሊመስለው ይችላል:: መጀመሪያ ግማሽ ፊቷን የሞላ የሚመስለው ትልልቅ እና የተፍረከረከ ከንፈሯ ድራማ ለመስራት

የተጠለቀ ጭምብል እንጂ በእርግጥም የአንዲት የአሰራ ስምንት ዓመት ወጣት ከንፈር አይመስልም፤ ከላይኛው ከንፈሯ የተረፈው ቦታ ላይ ለምልከት የተቀመጠው አፍንጫዋ ወደላይ ቀና ብሎ ሰፋፊ ሽንቁሮቹ ፊት ለፊት የቆመ ተመልካች ላይ የተደገኑ መንታ የከባድ መሳሪያ አፈሙዞች ይመስላሉ::የመርፌ ቀዳዳ የሚያካክሉ ዓይኖቿ ሁሌም ጉሸርጥ መስለው እንደቀሉ ናቸው:: የፀጉሯ ነገር አይነሳ ! የፍቅርተ ፀጉር ቀለም የለውም ፤ የማለዳ ጠል የሰፈረበት የሜዳ ላይ ችፍርግ ! ሲታበጥረው አሰቃቂ ፉጨት የመሰለ ድምፅ ይወጣል::

ይህን ሁሉ ተፈጥሯዊ በደል የተሸከመችው ፍቅርተ በዚህ በቃሽ ቢላት ጥሩ ነበር፤ ከቁመቷም ከፉኛ በድሏትል:: በእጥረቷ ላይ ሲበዛ ትልልቅ ጡቶቿና አጠቃላይ የሰውነቷ ውፍረት ተዳምሮ በሰቆቃ እንድትኖር ፈርዶባታል:: በእርግጥ ሰዎች "እግዜር የሰጣትን በፀጋ መቀበልና መኖር ነው ለምን ትሳቀቃለች?" የሚል ጉንጭ አልፋ ንግግር ሲናገሩ ይደመጣሉ:: ግን እንደባለቤቷ ሰቆቃው ሊገባቸው አይችልም:: "ምከርና ቡጢ ለሰጪው ቀላል ነው" እንዲሉ :: የልብሳቸው መዛነፍ፤ የከንፈር ቀለማቸው አለመስተካከል የሚያስጨንቃቸው ቆነጃጅት "እግዜር የሰጠውን..." ይሏታል፤ ይሄን ሁሉ ነገር የተሸከመችውን ፍቅርተን !

እንግዲህ የእናት ሆድ ሲዥጎረጎር ፋና ተወለደች ፤ "ያየሽ ይውደድሽ!" የሚል ምርቃት አብሯት የተወለደ:: ከባህሪውም ከቁንጅናውም አትረፍርፎ የሰጣት ውብ የአሰራ ዘጠኝ ዓመት ወጣት ነበረች - መልዓክ ! ፋናን ዓይኗን ትከ ብዬ ማየት አልችልም:: ርዳለሁ ... እፈራታለሁ:: ቁንጅናዋ ከተለመደው የሴት ልጅ ቁንጅና ያልፋል::

በዕድሜ ከእኔ ብታንስም ሁልጊዜም አጠገቧ ሰቆም ትገዝፍብኛለች:: ፋና ለእኔ ቆንጆ ብቻ አልነበረችም፤ የቁንጅና ማነፃፀሪያ ሚዛኔም እንጂ:: ልክ የሌለው ቁንጅና፣ ቃል የማይገልፀው መስህብ ነበራት:: የፊቷ ቆዳ ነፋስ እንደቆለለው የምድረበዳ አሸዋ ለስላሳ ነበር:: እንዲሁ በዓይን ሲመለከቷት በእጅ የዳሰሷት ያህል ልስላሴዋ ይሰማል:: ዓይኖቿ ልብን የሚያስጨንቁ ነገሮች ናቸው:: ፋና በልብ ውስጥ ለዘላለሙ የሚታተም ግን ቃል አውጥተው የማይናገሩት ቁንጅና የነበራት ልጅ ነበረች፤ ህያው ፈተና !

*** *** ***

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ንግድ ሰራ ኮሌጅ (ኮሜርስ) ተማሪ ነበርኩ:: ለአንድ የከፍለ ሐገር ልጅ ይቅርና አዲስ አበባ ተወልደው ላደጉ ልጆችም ቢሆን ንግድ ሰራ ኮሌጅ መማር ከባድ ነበር፤ የመጀመሪያው ችግር ኮሌጁ ለተመደቡ ተማሪዎች የመኝታም ይሁን የምግብ አገልግሎት ሰለማይሰጥ በየወሩ ለተማሪዎች አዚህ ግባ የማይባል የኪስ ገንዘብ እየከፈለ ከግቢ ውጭ እየኖሩ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ያደርጋል:: ተማሪው በአካባቢው ቤት አፈላልጎ በመከራየት ትምህርቱን ይቀጥላል::

ገና ከጅምሩ አዚህ ኮሌጅ መመደቤን ሰሰማ አልቅስ አልቅስ አያለኝ ነበር ከከፍለ ሐገር ወደ አዲስ

አበባ የመጣሁት:: የኮሌጁን ተማሪዎች የማሰቃየት ጀብዱ በሩቁ ሰምቻለሁ:: በዛ ላይ ለአዲስ አበባ አዲስ ስለነበርኩና የማውቀው ሰው ስላልነበረኝ እንኳን እየዞርኩ ቤት መፈለግ ቀርቶ አምስት ርምጃ ብራመድ ተመልሼ አልጋ የያዝኩበትን ሆቴል የማገኘው አይመስለኝም ነበር:: በዚህ ግራ በተጋባሁበት ወቅት ነበር ባረፍኩበት ሆቴል አልጋ አንጣፊ በኩል የእማማ አመለን ቤት ለመከራየት የበቃሁት ::

"እንደው መንደሩም ቤቱም ይሆንህ አይመስለኝም እንጂ የሚሆንህ ከሆነ አንዲት ጎረቤታችን አንዲት ከፍል ቤት አለቻቸው" አለችኝ የሆቴሉ አልጋ አንጣፊ:: ቤቱን ልናይ ጎተራ አሁን ቀለበት መንገዱ የተሰራበትን ወደቀኝ ትተን ወሎ ሰፈር የሚባለው አካባቢ ሄድን፤ በመንገዱ ግራና ቀኝ የተሰደሩት ትላልቅና ውብ ሕንፃዎች ጀርባ ውስጥ ለውስጥ ሂደን እዚህ አካባቢ ይኖራል ተብሎ የማይታሰብ ጭርንቁስ መንደር ውስጥ ገባን:: እርስ በርስ ተደጋግፈው የቆሙት ቤቶች ግድግዳ ላይ ተለጥፈው የተሰሩ የውሻ ቤቶች እንጂ የሰው ቤት አይመስሉም:: "ጨረቃ ቤት" እንደሚባሉ በኋላ ሰማሁ:: አፈር አፈር የመሰሉ ሕፃናት መንደሩ ውስጥ ውር ውር ይላሉ:: ትንሽ ተጉዘን ካገኘናቸው መደዳ ቤቶች ያሉበት ቦታ ሰንደርስ በአንዱ በር ላይ ቆምን:: ፍቅርተ እና እናቷ እማማ አመለ ነበሩ ያናገሩኝ::

እውነቱን ለመናገር ፍቅርተን ሳያት ላማትብ ቃጥቶኝ ነበር:: በስመአብ በ...:: ድንገት ፍቅርተን የተመለከተ ሰው ሊሰማው የሚችለው ነገር ቢኖር ይሄው ነው:: ለምን እንደሆነ ባላውቅም አዲስ አበባ ውስጥ የዚህ ዓይነት ቤትም፣ የዚህች ዓይነት ልጅም ይኖራሉ ብዬ አስቤውም አልሜውም አላውቅም::እንደውም ያመጣኝ አውቶብስ በትክክል አዲስ አበባ እንደጣለኝ ተጠራጠርኩ:: የእኔ ቤተሰቦች መካከለኛ ኑሮ የሚኖሩ የክፍለ ሐገር ሰዎች ናቸው:: ያደግኩበት ቤትና ግቢ ግን በስፋትም በንፅህናም ከዚህ "ቤት" ጋር ሲወዳደር...ኧረ አይወዳደርም:: ወይ አዲስ አበባ !! "ለኒዜው እዚህ ቤት አረፍ ብዬ አገሩንና ሰዉን ስለምደው የተሻለ ቤት እፈልጋለሁ" ብዬ የ'አዲስ አበባ' የቤት ችግር መፈናፈኛ ያሳጣኝ እኔ ጓዳዋን በሶስት መቶ ብር ለመከራየት ተስማማሁ::

ከሰዓት በኋላ አንዲት የስፖንጅ ፍራሽ ገዝቼ ካረፍኩበት ሆቴል ሻንጣዬን በመያዝ ወደተከራየሁት "ቤት" ስመለስ ያጋጠመኝ ነገር ባንድ ራስ ሁለት አስወራኝ:: "ያመጣኝ አውቶብስ አዲስ አበባ ነው ወይስ ገነት ያወረደኝ?!"፤ ፋና በር ላይ ቆማ ነበር:: ፋና የእኔ የማለዳ ጀምበር...! ፋና የእኔ ደግ ፊት ! ሩህሩህ ፊት፣ የተከሰተች መልአክ...!

ሻንጣዬን ልትቀበለኝ እጇን ዘረጋች:: ለስላሳ ጣቶቿ የእጇን መዳፍ ነኩኝ! የከተማው የኤሌክትሪክ ኃይል ሁሉ በፋና እጅ በኩል አድርጎ ልቤን ቀጥ እስኪያደርገው ነዘረኝ:: አዲስ አበባ በጨለማ ተውጣ በጥቁር አዲስ አበባ ላይ ፋና የምትባል ፀሐይ ፍንትው ብላ ወጣች ! እነሆ ይህቻትና አዲስ አበባ የልዩነት አገር... ሁሉን ቻይ አዲስ አበባ! የሁሉ መኖሪያ አዲስ አበባ! ከትላልቆቹ ሕንፃዎች ኋላ ሲአልና ገነት በፍቅር በመተሳሰብና በአንድነት ተቃቅፈው የሚኖሩባት አዲስ አበባ! የአዲስ አበባ ልጅ የሆንኩ መሰለኝ፤ አዲስ አበባ ተወልጄ ያደግኩ መሰለኝ:: ፋና ፋና ፋና ፋና ያለችበት ቤት ውስጥ ልኖር ነው::

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ንግድ ሰራ ኮሌጅ እግዜር ይስጠው፤ አካውንቲንግ ላስተምርህ ብሎ ጠርቶ፣ ከቁጥሮች ክምር ውስጥ እውነትን ማውጣት ላስተምርህ ብሎ ጠርቶ፣ ድህነት ከቀበረው መንደር ውስጥ የወርቅ ፍልቃቂ የመሰለች ልጅ እንዳወጣ የተላከኩ መልአከ አደረገኝ:: እኔኮ ቆንጆ ሴት ሲያዩ የሚደነግጡት የፊልም 'አክተሮች' ብቻ ይመስሉኝ ነበር:: ፈዘዝኩ ! ፋናን ስመለከት ፈዘዝኩ::

ከዚች ቤት እንኳን ራሴ ልወጣ ውጣም ቢሉኝ እግሬን እንደማላነሳ የገባኝ ገና ፋናን እንዳየኋት ነበር:: "ለልማት መንደሩ ሊፈርስ ነው መድረሻህን ፈልግ" ቢሉኝም "አብራችሁ አፍርሱኝ" ከማለት ወደኋላ እንደማልል የገባኝ የፋና ጣቶች ሲነኩኝ ነው ::ማን አለ ለርስቱ የማይሞት! ፋና እኮ ርስት ናት፤ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መግቢያ ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ የተዘረጋች:: እግዚዮ ! ፋናን እዚህ መንደር ውስጥ ምን እግር ጣላት ?! መቼም ከዚህ ቤት በሆነ መንገድ አውጥተው ቢጥሉኝ አርቀው እንደጣሉት ውሻ፣ ጫካ ወስደው እንደወረወሩት ድመት የፋናን ኮቴ እያነፈነፍኩ ተመልሼ እዚሁ መገኘቴ አይቀርም::

ማንም 'ችኩል' ቢለኝ ግድ አይሰጠኝም:: ፋናን ገና ስመለከታት ልቤ ውስጥ የማይናወጥ የፍቅር ሐውልት ቆሟል:: ማንም ብትሆን ግድ አይሰጠኝም፤ ቤት ውስጥ ምንሸር የታጠቀ፣ ጓንዴ ትራሱ ስር ያስተኛ ባሏ ቢቀመጥ፣ ሰባት ልጆቿ "እማ እማ!" እያሉ የሚንጫጩ ሴት ብትሆንም ግድ የለኝም:: ፋናን አየኋት፣ ወደድኳት በቃ!! ይሄ ሁሉ ነገር የሆነው አንድ ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነው:: እና ይሄን ሁሉ ሴኮንድ፣ ዘላለም የሚያህል ደቂቃ ፋናን አይቼ ባፈቅራት "ቸኮልክ" የሚለኝ ማነው?!

*** *** ***

ቤተሰቦቼ በየወሩ የሚልኩልኝ ብር ከዚህ የተሻለ ቤት እንድከራይ የሚያስችለኝ ቢሆንም ፋና የምትባል የእግር ብረት ተጠናውታኝ በየት በኩል ! ቤቱ ለአንድ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ምኑም የሚመች አልነበረም:: ከእኔ ክፍል ኋላ የታወቀ ጠላ ቤት ነበር፤ ጫጫታው፣ ሁካታው፣ ዘፈኑ፣ ፀቡ ሁሉ ይረብሸኛል :: በሳምንት ሦስት ቀን !!

የጠላ ቤቱ ጩኸት ጋብ ሲል ኳስ የሚጫወቱ ልጆች ይተካሉ:: ግድግዳየን በኳስ ሲነርቱት የቤቴ ምርጊት አፈሩ በለጠፍኩት የግድግዳ መሸፈኛ ወረቀት ስር እየተንኮሻኮሸ ሲፈርስ ይሰማኛል:: ይህን ሁሉ ስችለው ደግሞ የጠላ ቤቱ አሻሮ ሲታመስ ፣ የጠላ ቂጣው ሲጋገር አሻሮ አሻሮ የሚሸትት እንኩሮ እንኩሮ የሚተነፍግ ጭስ ጠባብ ክፍሌን ይሞላታል:: ይህ ሁሉ ችግር ግን ቤቱን እንድጠላው አላደረገኝም:: ፋናን ስመለከት ጫጫታው የፍቅር ሙዚቃ፣ ጭሱ ፍቅርን የሚያጥን የገነት ከርቤ እስኪመስለኝ ይሰማማኛል::

እዚህ ቤት ውስጥ ለስድስት ወራት ስኖር ከፍቅርተ ጋር ተግባባን፤ እማማ አመለ ጋር የእናትና የልጅ ያህል ተቀራረብን፤ ከፋና ጋር ግን ከሰላምታ ውጭ አንዲት ቃል ተለዋውጠን አናውቅም :: ፋና እዛው ተቀምጣ አንድ ቤት እየኖርን ትናፍቀኛለች ፤ አትናገር አትጋገር ! ዝም:: ፋና

ቤት ውስጥ አለች ማለት ማንም ቤት ውስጥ የለም እንደማለት ነው፤ ዝምታ ይነግሳል:: የፋናን ድምፅ አንዳንዴ ለአራት ለአምስት ቀናት አልሰማውም፤ እዛው እያለች:: አይገርምም ? እኔም በቤተሰቦቼ "እሱ አይናገር አይጋገር ዝም ነው!" እየተባልኩ እሞካሽ ነበር:: ጉዳቸውን ባዩ ! እዚህ ሞት የሚያስንቅ ዝምታ የሰፈረባት ጋግርታም ጋር በፍቅር ወድቄ አንድ ቃል ሲናፍቀኝ::

የፋና ዝምተኝነት የጤና አልመስል ብሎኝ ነበር:: እንጀራ እየበሉ ወጥ ሲያልቅባት እንኳን ወጥ ጨምሩልኝ አትልም:: ደግነቱ እናቷ እማማ አመለ ዓይናቸው ከፋና ላይ ስለማይነቀል ገና ወጡ ሲያልቅባት በላይ በላዩ ይጨምሩላታል:: ፋና በቀን ውስጥ የምትናገራቸው ቃላት ቢደመሩ እህቷ ፍቅርተ በግማሽ ደቂቃ ከምታዘንበው ንግግር እሚበልጡ አይመስለኝም:: ፍቅርተ ሙሉ ቀን ስታወራ፣ ስትስቅ፣ ስትጫወት ነው የምትውለው:: አንዳንዴ ፈገግታ የሚያጭርብኝ ነገር ፋናና ፍቅርተ ሲያወሩ መስማት ነበር:: ፍቅርተ ብቻዋን የምታወራ ነው የምትመስለው:: ፋና አንድ ቃል አትመልስም፤ ፍቅርተም ብትሆን የእህቷን አመል ያወቀች ይመስል መልስ አትጠብቅም፤ ዝም ብላ ታወራለች ::

የፍቅርተን ወሬ መስማት አይሰለችም:: እንደው ፍቅርተን መልኳን ሳይመለከት ድምጿን ብቻ ያደመጠ ሰው በዓለም አንደኛዋ ቆንጆ ሴት እየተናገረች ሊመስለው ይችላል:: በተለይ ሳቋ ! የፍቅርተ ውበት ግን ድምጿ ብቻ ነው:: "ስምን መልአከ ያወጣዋል" የሚባለው ብሂል እውነት ከሆነ የፍቅርተን ስም ያወጣው መልዓከ ድምጿን ብቻ በሆነ መንገድ አድምጦ "ፍቅርተ" ብሎ ሳይሰይማት አልቀረም::

*** **** ****

እማማ አመለወርቅ ብርቱ እናት ነበሩ:: ሁለቱን ሴት ልጆቻቸውን ያሳደጉት ካለ አባት ነው:: ዛፍ ቆራጭ የነበሩ ባለቤታቸው አንድ ቀን ዛፍ ሲቆርጡ የዛፉ ቅርንጫፍ የተላጠ ኤሌክትሪክ መስመር ጋር የተነካካ ሆኖ በአሰቃቂ ሁኔታ ሕይወታቸው አለፈ:: ያኔ ፋና የሶስት፣ ፍቅርተ የሁለት ዓመት ሕፃናት ነበሩ:: እነዚህን ሁለት ልጆች ለማሳደግ ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም:: ያለፉበትን አሰቃቂ የድህነት መንገድ ተመልሰው ሲያስቡት ያንገሸግሻቸዋል:: ታዲያ ከተቀራረብንና እኔም ከቤተሰቡ አባል እንደ አንድ ተቆጥሬ ገመናቸውን ተካፋይ ስሆን ማታ ማታ ቡና ተፈልቶ ታሪካቸውን ያወሩልኝ ነበር:: እማማ አመለ ወሬ ይችላሉ፤ አሁን በሐዘን ዐይናችንን በእንባ ሞልተውት ድንገት ጣል በሚያደርጉት ቀልድ ለሐዘን የኳተረ እንባችን በሳቅ ይፈሳል::

የማታ ቡና አብሬያቸው መጠጣት የጀመርኩበት ቀን ትዝ ይለኛል:: በፊት ቡና ሲያፈሉ ፍቅርተ መጋረጃዬን ገለጥ አድርጋ አንድ ስኒ ታቀብለኝና እጠጣለሁ፤ እጣኑም ቢሆን እየተጥመለመለ መጋረጃዬን አልፎ ከፍሌ ይደርሳል ::

"አብዬ" ይሉኛል እማማ አመለ ሲጠሩኝ እንዲህ ነው፤

"አቤት ማዘር !"

"ሁለተኛ ትጠጣለህ?"

"አይ ይበቃኛል ማዘር" አላለሁ:: እየፈራሁ እንጂ ብጠጣ ደስ ይለኝ ነበር::

አንድ ቀን ታዲያ ቡናው ተፈልቶ፣ እጣኑ ቤቱን ሞልቶት፣ እኔም ነቃ ብዬ ፍቅርተ መጋረጃዬን ገለጥ አድርጋ ቡናዬን እስክታቀብለኝ ስጠብቅ እማማ አመለ ጠሩኝ::

"አብዬ !"

"አቤት ማዘር"

"እንደው ከሰውም አልተፈጠርክ ? ምናለ ወዲህ ወጣ ብለህ ብትጫወት፣...ጀበናውንም እያየህ ቡና ብትጠጣ፣ እኔም እናትህ ነኝ፣ እነፍቅርዬም እህቶችህ ናቸው" አሉኝ:: ይሄ የመለአከት ጥሪ ነው ! ልብሴን ቀየርኩ፤ (ምርጥ የምላትን ልብስ ነው የለበስኩት፣ ከዚህች እዚች የመጋረጃ ድንበር ለማለፍ ሽክ!!):: እናም መጋረጃዬን ገለጥ አድርጌ ብቅ አልኩ፤ ሁሉም በአክብሮት ተቀበሉኝ:: የተዘጋጀችልኝ ኩርሲ ላይ ተቀመጥኩ :: እዩት እንግዲህ እግዜር ጨዋታውን ሲያሳምረው! ፋና ፊት ለፊቴ ነው የተቀመጠችው:: ከዚህ በፊት ፊት ለፊቴ ተቀምጦ የሚያውቅ ውብ ነገር ምን ነበር?...ምንም !!

በእኔና በፋና መሃል የሲኒ ረከቦት፣ ሲኒዎቹ ስድስት ጨረቃ መስለው፣ ከረከቦቱ ጎን ማጨሻው እንደ ደመና በቀስታ ሽቅብ ወደ ጠቆረው ጣራ፣ ከሚሳብ የእጣን ጭሱ ጋር:: ከስሱ የእጣን መጋረጃ ባሻገር ፋና አንገቷን ደፍታ መሬት መሬት እየተመለከተች ተቀምጣለች:: አዲስ ሰው ስለተቀላቀልኩ ጨንቋታል:: አቤት እንዲህ ፊቷ ተቀምጠው በእጣኑ ጭስ ውስጥ ሲመለከቷት! "ምነው ባልነቃሁ" በሚባልበት እንቅልፍ ውስጥ የተከሰተች ጣፋጭ ህልም ነው የምትመስለው፤ ፋና የኔ ውብ::

ድህነትን አፈር ድሜ ያስጋጠ ውበት በዚህ ጭርንቁስ ቤት ውስጥ ፊት ለፊቴ በእጣን ደመና ተከብቦ ተቀምጧል፤ እኔም ከአግር ጥፍር እስከራስ ፀጉር በሚነዝር በሚያስረቀርቅ ደስታ ውስጥ ህያውና ዘላለማዊ ሥዕል ላደርጋት እያጠናኋት ነው ::ነፍሱ በፍቅር ፍላፃ እንደተወጋች አፍቃሪ ቢምድር ላይ ምርጥ ሠዓሊ የለም ::አፍቃሪ እንደፎቶ አንሽ ያፈቀረውን ስጋ ብቻ አይደለም የሚያሳምረው፤ የተፈቃሪውን ነፍስ ይመለከታል፤ ነገን ይመለከታል፤ በዝምታ ውስጥ ያለ ሰላምን የሚቃኙ ዐይኖች ይታደላል:: ከተከዘ ፊት ፈገግታን ያወጣል:: እውነትን በዓይነ ህሊናው ይቃኛል! አፍቃሪ ሠዓሊ ነው!

ከዛን ቀን ጀምሮ ፋና ጋር በእጣን ጭስ መሃል መተያየት የዘወትር ተግባራችን ነበር:: የእማማ አመለ ጣፋጭ ወግ፣ የፍቅርተ የማያባራ ሳቅና ጨዋታ፣ የፋና የማይገሰስ ዝምታና የዝምታዋ ውበት፣ የውበቷ ግዝፈት እንደ መንፈስ በቤቱ ውስጥ ያረብብ ነበር:: ያችን የድህነት ጎጆ ሙሉ

ያደረገ መልካም ቤተሰባዊ ፍቅራችን ለአራት አመታት አብሮን ኑሯል::

*** *** ***

ድህነት ከፉ ነው:: ድህነት ምኑም አያኮራም፤ ድህነት ያስጠላኛል:: አንድ ቀን ትንሽ ራሴን ስላመመኝ በጊዜ ወደቤት ተመለስኩ፤ ማንም አልነበረም፤ የት እንደሄዱ እኔንጃ:: ወደ ከፍሌ ገብቼ ፍራሽ ላይ በደረቴ ተደፍቼ ተኛሁ:: ብዙ ሳልቆይ ፍቅርተ ከውጭ አየተጣደፈች ገባች፤ መኖሬን አላወቀችም:: እኔም ካለወትሮዬ ዝም ብዬ በመጋረጃው አሻግሬ እመለከታታለሁ:: አለ አይደል አንዳንዴ መናገር የሚታከትብን ጊዜ...

ፍቅርተ የሆነ ቦታ ልትሄድ በጥድፊያ ላይ እንደሆነች ታስታውቃለች:: ከአሮጌው አልጋ ስር ዚፑ የተበላሸ አንድ የልብስ ማስቀመጫ ሻንጣ ጎትታ አወጣች:: ይህ ሻንጣ የቤተሰቡ ብቸኛ የልብስ ማስቀመጫ ነበር:: ከፈተችውና ልብስ መምረጥ ጀመረች፤ ትእይንቱ አሳዛኝ ነበር:: አንዱን ታነሳና በሁለት እጆቿ ራቅ አድርጋ ይዛ እያገላበጠች ትመለከተዋለች፣ አልጋው ላይ ትጥላለች፤ ሌላውን ታነሳለች ትጥላለች:: የእማማ አመለ የክት ቀሚስና ነጠላ፣ የፋና አንድ ሁለት ተራ ቀሚሶች እናም የፍቅርተ በርካታ ነጫጭ ቲሸርቶች...ሻንጣው ውስጥ የነበረው ልብስ በሙሉ አለቀ:: ፍቅርተ ልትሄድ ላሰበችበት ቦታ የሚመጥን አንድም የረባ ልብስ አላገኘችም:: በረዥሙ ተነፈሰችና በአንድ እጇ ወገቧን ይዛ በሌላ እጇ ጠጉሯን እያከከች ግራ ተጋብታ ለብዙ ደቂቃዎች በትካዜ ቆመች:: ከዛም በቁጣ ልብሱን ከአልጋው ላይ ገፍፋ ወደ ሻንጣው ወረወረችውና ሻንጣውን ዘግታ በእርግጫ ወደ አልጋው ስር ገፋችው:: በዚህች ቅፅበት ጓደኞቿ ከውጭ ጠሯት፤

"...ፍቅር ቶሎ በይ እንጂ...ረፈደ እኮ!"

"እናንተ ሂዱ ኤልሲ ! ሌላ ቀጠሮ አለኝ ረስቼው ነበር" አለቻቸው፤ ጓደኞቿ ሄዱ:: ፍቅርተ አልጋው ጫፍ ላይ ተቀምጣ ስቅስቅ ብላ ማልቀስ ጀመረች::

"ኤጭ! ወይ መልከ የለኝ፣ ወይ ደህና ቤተሰብ የለኝ፣ ሰው ጋር መቀላቀያ እንኳን አንዲት ልብስ ያጣል ሰው ?...አንዲት ልብስ...እግዚአብሄር አሁንስ ብትገለኝ ምናለበት ! በስንት ነገር ከሰው በታች ታደርገኛለህ?" አለች በምሬት:: አልቅሳ ሲወጣላት እንባዋን ጠራርጋ አንዲት ትንሽ መስተዋት ወደተሰቀለችበት ጥግ ሄደችና መስተዋቷን አውርዳ አንዴ ከንፈሯን ሰብሰብ አንዴ ለቀቅ እያደረገች መልኳን ስትመለከት ቆየችና መስተዋቱን ወደ ቦታው እየመለሰች "አስቀያሚ!" ብላ በምሬት ተናገረች:: ማታ የተለመደው ቡናችን ላይ ግን ፍቅርተ በሳቅ ስትፍለቀለቅና ምንም ነገር ያልተሰማት ልጅ መስላ አመሸች:: "ሳቅ የደስታ ምልክት ነው" የሚሉ የዋሆችን ታዘብኳቸው::

ከዛን ቀን ጀምሮ የፍቅርተን ልብሶች ማስተዋል ጀመርኩ:: የፍቅርተ የሚበዙት ልብሶቿ ነጫጭ

ቲሸርቶች ነበሩ። እነዚህ ቲሸርቶች ከተለያዩ ድርጅቶች በነፃ የሚታደሉ የተለያዩ መፈክሮች ደረታቸው እና ጀርባቸው ላይ በተለያዩ ቀለማት የታተሙባቸው ሲሆኑ ብዙዎቹ ለአንድ በዓል ወይም ለሆነ ቀን መታሰቢያነት የተዘጋጁ ናቸው። አንድ ቀን ታዲያ ፍቅርተ ልብስ አጥባ ቲሸርቶቹ የተሰጡበት ቆሜ ስመለከት ገረመኝ። የፍቅርተ ቲሸርቶች ታጥበው ሲሰጡ የኢትዮጵያ ችግሮች በሙሉ ታጥበው የተሰጡ ነበር የሚመስሉት።

"የእናቶች እና ህፃናት ሞት ይቁም" በቀይ ቀለም ደረቱ ላይ የተፃፈበት ቲሸርት፤

"ከ ኤች አይ ቪ ኤድስ ራሳችንን እና ቤተሰባችንን እንጠብቅ" በሰማያዊ፤

"ፖሊዮን ከኢትዮጵያ እናጠፋለን" በጥቁር፤

"መስኮት በመክፈት የቲቢ በሽታን እንከላከል" በቀይ፤

"ችግኝ በመትከል አካባቢያችንን ውብና ፅዱ እናድርግ" በአረንጓዴ፤

ከነጫጮቹ ቲሸርቶቹ ለየት ያሉት ደማቅ ቀይና ቢጫ ቲሸርቶች ደግሞ የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አርማ የታተመባቸው ነበሩ። ፍቅርተ ብትበሳጭ እውነት አላት።የዘመኗን ወጣቶች፣ የአዲስ አበባን ቆነጃጅት በእነዚህ ቲሸርቶች መወዳደር ዘበት ነው። እያንዳንዷ ወጣት ሴት ውስጥ እድሜ የሚያመጣው የቁንጅና ውድድር አለ። መልክ ያለው በመልኩ፣ የሌለው በዘመናዊና ውብ ልብሶች ውድድሩ ውስጥ አለበት። በዚህ የታይታ ዘመን ግባቸው መታየት የሆነ እልፍ አእላፍ ወጣቶች የማይታዩ መስዋዕትነቶችን የሚከፍሉት ወደው አይደለም፤ መታየት መኖርን ማረጋገጫ አንድ ምስክርነት ስለሆነባቸው እንጂ። እናም ለመታየት፣ ዕይታ ውስጥ የሚገባ አልባሳት አንዱ መሰፈርት ነው። በዚህ ውድድር ላለመውደቅ የከፋ አዘቅት ውስጥ የሚወድቁትንም ቤት ይቁጠራቸው።

*** *** ***

ፋና ጋር መቀራረብ በጣም ከባድ ነበረ። አንዳንዴ ባህሪዋ ያበሳጨኛል። "ምናይነት የደነዘዘች ልጅ ናት" እልና ለራሴ ቁጣ ቁጣ ይለኛል። ለምን እንደ ፍቅርተ አታናግረኝም ? ሌላው ቢቀር አንድ ዓመት ሙሉ እዚህ ቤት ስኖር ቤቴን እንኳን ተሳስታ ረግጣው አታውቅም። ፍቅርተ እኮ እናት ማለት ናት። ረፍዶብኝ ፍራሼን ሳላነጣጥፍ ከወጣሁ ፍራሼን አነጣጥፋ፣ ያዝረከረኩትን ወረቀት አስተካክላ የሚጠጣ ውሃ ቀድታ አስቀምጣልኝ ነው የማገኘው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ምግቤንም የምትሰራልኝ ፍቅርተ ናት። እች ፋና የሚሏት ዝግ ግን...ዝምታዋ ሰልችቶኝ ነበር።

የሆነ ጊዜ ታዲያ ድንገት ታመምኩ። ለሳምንት ትምህርት ቤት አልሄድኩም፤ ፍቅርተና እማማ አመለ ተጨንቀው ሲሯሯጡ ሰነበቱ። ፋና ዝርም ብላ አታውቅም። ከዛን ጊዜ በኋላ የፋና

ነገር በቃኝ። "እግዜር ይማደልህ !" ማንን ገደለ? አንድ ቀን ሳትጠይቀኝ በቃ ድኜ ተነሳሁ። ፋና የምትባል ልጅ በቃ በቃችኝ። ሳልፍ ሳገድም እወረውርላት የነበረውን ሰላምታዬን እኔም አቆምኩ። ስገባ ብቻዋን ተቀምጣ ባገኛት እንኳን ሰላም አልላትም። እንደውም ከብስጭቴ ብዛት ቤት ለመቀየር አሰብኩ። ግን ለእማማ አመለ ምን ሰበብ እንደማቀርብ ጨነቀኝ። ከእኔ ከሚያገኟት የኪራይ ብር በላይ ለእኔ ያላቸው ቤተሰባዊ ፍቅር ቦታ አለው፤ ለእርሳቸው። ደግሞም ብቸኛ መተዳደሪያቸው ከእኔ የሚያገኟት የኪራይ ብር ነበረች። ምን ሆንኩ ብዬ ከዚህ ቤት ልውጣ ? እች ጉልት ሰወጣ ሰገባ እንደ ግኡዝ ነገር ተጎልታ ማየቴ ያበሳጨኛል። ማታ ማታ ቡና ሲጠሩኝ በህመሜ አሳብቤ ልቀር ብሞክርም አልተሳካም።

"ቡና ባትጠጣ እንኳን ና እና ተጫወት፤ በሽታውም ለብቻ ሲሆኑ ነው የሚጠናው" አሉኝ እማማ አመለ። ጨዋታው እንደወትሮው አልጥምህ አለኝ፤ እጣኑ ከነከነኝ፤ ከእጣኑ ወዲያ አቀርቅራ የምትቀመጠው ፋና ሰለቸችኝ። እወዳታለሁ፤ ግን ግኡዝ ናት በቃ ! ወይስ ከራሷ ውበት ጋር በፍቅር ወድቃ ዓለምን ረስታለች ? ምናይነት ድንዛዜ ነው ይሄ ?

ፍቅርተ ጋር ቅርርባችን ተጠናከሮ ነበር። ማታ ማታ ቡናው እስከሚፈላ ደብተሯን ይዛ ወደ ከፍሌ ትመጣለች። ግን አታጠናም፤ ቤታቸው ውስጥ ቴፕ ስለሌለ ሁልጊዜ የደብተሯ ቦርሳ ውስጥ የምታኖረውን የአስቴርን ካሴት ይዛ ትመጣና በእኔ ቴፕ ታዳምጣለች። ግጥሙን ሸምድዳዋለች፤ ጀምሮ እስኪጨርስ በቃሏ ትወጣዋለች። ሙዚቃውን እንደ ሙዚቃ ሳይሆን እንደ መርዶ ነበር ፊቷን አጨፍግጋ የምታዳምጠው። አንድ ቀን ሙዚቃውን እያዳመጠች እንባዋ በጉንጯ ላይ ኮለል ብሎ ወረደ፤

"ምን ሆንሽ ፍቅርተ" አልኳት ደንግጬ፤

"ምንም" ብላ ተነስታ ከክፍሌ ወጣች።ከዛን ቀን ጀምሮ ፍቅርተ የወትሮዋ አልነበረችም፤ የሌላትን አመል መነጫነጭ ጀመረች። ከመሬት ተነስታ ታለቅሳለች፤ በትንሽ ነገር ይከፋታል። ከወራት ልመና በኋላ ጭንቋን ተነፈሰችው፤ ፍቅርተ ፍቅር ይዟት ነበር። ፍቅር እንደያዛት ስትነግረኝ "እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፣ የነገስታት ንጉስ፣ የዓለም ሁሉ ፈጣሪ ታያል! እባክህ ይህች ልጅ ፍቅር የያዛት ከእኔ እንዳይሆን እርዳኝ" ብዬ ፀለይኩ።

"ከሰምንተኛ ክፍል ጀምሮ አብረን አንድ ክፍል ነው የተማርነው፤ ቶማስ ይባላል" ስትለኝ "ሃሌሉያ!" ብዬ ልጮኽ ቃጥቶኝ ነበር። ኡፍፍፍፍፍ ! አሁን እዳው ገብስ ነው ! ተረጋግቼ አዳምጣት ጀመር። የከፍሎቿ ልጆች ተሰባስበው የተነሱትን አንድ ፎቶ እየሰጠችኝ ልጁን ጠቆመችኝ፤ ሲበዛ ቆንጆ ልጅ ነበር። ከግራና ቀኙ ሁለት ቆነጃጅት እንደ መሸገር ተጣብቀውበታል።

"አንቺ የታለሽ ታዲያ!" አልኳት፤

"እኔ ፎቶ መነሳት አልወድም" አለችኝ ትከዝ ብላ። ለምን ብዬ አልጠየቅኳትም።

"ከወደድሽው ሰንት ጊዜ ሆነሽ?" አልኳት ፎቶውን እያየሁ፤

"እኔንጃ ግን ቆይቷል ፤ ሶስት አመት"

"እና ሦስት ዓመት ሙሉ ስታፈቅሪው እርሱ ምን አለ ?"

"እያውቅም::"

"ተነጋግራችሁ አታውቁም"

"አንድ ቀን አናግሮኛል..."

"እና ምን አለሽ?" አልኳት በጉጉት::

"እርሳስ አጥቼ ስጠይቅ ሰጠኝ...ስመልስለት 'ውሰጂው!' አለኝ" አለችና እዛኛው ክፍል ሄዳ አንድ ቢጫ እርሳስ ይዛ ተመለሰች:: እንደ ትልቅ ቅርስ በፍቅር እርሳሱን እየተመለከተች...፣ "አየኸው የእሱ ነው" አለችኝ:: ፊቷ ላይ የነበረው ደስታ... ናፍቆት...ፍቅር ያሳዝን ነበር:: ትቀጥላለች ብዬ ጠበቅኳት:: የተነጋገሩት ግን እችኑ ነበር:: አንድ ቃል "ውሰጅው" አላት፤ በቃ:: ይሄ ቃል ለፍቅርተ "ንግግር" ነበር::

"ለምን አታናግሪውም ታዲያ ? በቀጥታ መናገር እንኳን ባትችይ በሆነ መንገድ እንደወደድሽው አሳውቂው:: እሱም ሊወድሽ ይችላል" አልኳት እንደው ለማፅናናት እንጂ ያልኩትን ለራሴም አላመንኩበትም:: ይሄ ልጅ ፍቅርተን ቢወዳት በሺ ዓመት አንድ ጊዜ የሚከሰት አጋጣሚ አድርጌ ላየው ሁሉ እችላለሁ::

በድንጋጤ አፍጥጣ እያየችኝ፣ "ትቀልዳለህ ?!" አለችኝና አፏን በሁለት እጆቿ አፍና እንደዘገነነው ሰው ሰውነቷ ተንዘረዘረ፤

"በጣም የሃብታም ልጅ ነው፤ በዛ ላይ ከላሳችን ውስጥ ካሉ ሰላሳ ሴቶች ግማሹ በሱ ፍቅር ያበዱ ናቸው:: በአረፍት ሰዓት ጎታቹ ብዙ ነው፤ በዚያ ላይ ጎበዝ ተማሪ፤ ኤጭ" ብላ በምሬት ፊቷን አጨፈገገች:: ዝም ብዬ አየኋት፤ ፍቅርተ ይበልጥ በቀረቧት ቁጥር ይበልጥ መልከጥፉ የምትሆን ሚስኪን ነበረች:: በቦዙ አይኖቿ ባዶውን እየተመለከተች ምሬቷን አምበለበለችው:: "የሆነ ነገር ያስፈልግሃል፣ ለመፈቀር አንድ የሆነ ነገር ያስፈልግሃል፤ መልከ ወይም ሃብት...ብቻ የሆነ ነገር፤ እኔ ደግሞ ምንም የለኝም፤ መልከ የለኝ፣ ሃብት የለኝ፣ በትምህርት እንኳን እንዳላካከሰው እንደ ትምህርት የሚያስጠላኝ ነገር የለም፤ እማማ እንዳይከፋት ነው የምማረው፤ ችኮኛል:: ከቤት ባልወጣ ደስታዬ ነው፤ ማንንም ባላይ፣ ማንም ባያየኝ ደስታዬ ነው" አለችና እንባዋ ይፈስ ጀመረ::

"ፍቅርተ ለፍቅር ሃብት ፣ መልከ ምናምን ቢያስፈልግ ኖሮ እኮ አታፈቅሪም ነበር" አልኳት::

ከአፌ ነጥቃ በቁጣ መናገር ጀመረች::ንግግሯ በምሬት የተሞላ ነበር:: "እንኳን ለፍቅር ለተራ

ሰላምታም ሀብት ያስፈልጋል ::መልክ ያስፈልጋል :: አንተ አስቀያሚ ወጣት ሆነህ ታውቃለህ ? አስቀያሚ ሴት ሆነህስ ታውቃለህ ? ሀመሙ አይገባህም::አብርሽ መገፋቱ ስሜት አይሰጥህም... እየውልህ እንኳን አሁን ሕፃን ሆነን እኔና ፋና መንገድ ላይ ሰንሄድ ያገኘን ሁሉ ፋናን አገላብጦ ጉንጯን ይስምና እኔን..." መጨረስ አልቻለችም እንባዋ ቀደማት::

"...አስራ ስምንት ዓመት አልፎኛል:: እስካሁን አንድ ወንድ እንኳን ጠይቆኝ አያውቅም:: አንዳንዴ እንዴት እንደተፋቀሩ ይቅርና ያፈቀሩት ጋር እንዴት እንደተጣሉ ሴቶች ሲያወሩ እቀናለሁ...ከፍቅረኛ ጋር መጣላት በራሱ ያስቀናል፤ ይናፍቅሃል፤ ሰው ሆነህ በፍቅር መጋጨትህ በራሱ ከሰው እኩል ያደርግሃል:: የሚጣላህም የሚወድህም በሌለበት ዓለም መኖር ካለመኖር እኩል ነው" ፍቅርተ ባንዴ ተቀየረችብኝ፤ አስፈሪ ሆነችብኝ:: ንፍጧ በአፍንጫዋ ተዝረከረከ፤ እንባዋ ፊቷን አጨቀየው፤ አስቀያሚነቷ ሙሉ ሆነ:: ስታሳዝን!

"አስራ ስምንት ዓመት እኮ ትንሽ እድሜ ነው...ገና ነሽ ወደፊት የሚያፈቅርሽ የራስሽ ሰው ይመጣል" አልኳት ልክ የሚያፈቅራትን ሰው የቀጠርኩት ይመስል በእርግጠኝነት:: ግን ውስጤ መቼም ቢሆን ፍቅርተን የሚያፈቅር ሰው በምድር ላይ የሚፈጠር አይመስለውም፤ እናገራለሁ፤ ግን የምለውን እኔም አላምንበትም::

በቅሬታ ፈገግ ብላ ልትሄድ ተነሳች:: እስካሁን በስሜት ባወራችኝ ነገር ሃፍረት ተሰምቷት ነበር...ማታ ቡና ላይ ግን ስትስቅ ስትጫወት ዓለም የሞላላት ደስተኛ ወጣት ትመስል ነበር:: ስቃይን አፍኖ እንደፍቅርተ መሳቅ ትልቅ ብቃት ሳይጠይቅ አይቀርም::

*** *** ***

ፋናን እንዳኮረፍኳት አስራ አምስት ቀናት አለፉ:: አስራ አምስት የሚያንገሸግሹ ቀናት:: ወደ ጓዳዬ ስገባ ፋና ያለችበትን ክፍል ማለፍ በሲኦል ውስጥ እንደማለፍ ነበር ለእኔ::የመገፋት ሥሜት ይሰማኝ ነበር ፣ የመናቅ ስሜት ይሰማኝ ነበር:: ልክ በአስራ አምስተኛው ቀን ከትምህርት ቤት ስመለስ ፋና ብቻዋን ቤት ውስጥ ተቀምጣ ነበር:: ሰላም ሳልላት አልፌ ወደ ክፍሌ ገባሁና ደብተሬን ፍራሼ ላይ ወርውሬ እኔም ፍራሼ ላይ በጀርባዬ ተንጋልዬ ተኛሁ::ለምን እንደሆነ እንጃ ፋናና እኔ ብቻችንን ቤት ስንሆን ይጨንቀኛል፣ የማደርገው ሁሉ ግራ ይገባኛል:: እንዳናግራት የሚገፋፋኝ ነገር አለ ግን አፌ አይከፈትም፣ እግሬም ወደ ርሷ ስንዝር መራመድ አይችልም:: ለራሷ ደንዝዛ እኔንም አደንዝዛኛለች::

በጀርባዬ ተኝቼ እያሰብኩ እያለ የበር መጋረጃዬ በቀስታ ሲገለጥ እና የውጪው ብርሃን ያሳደደው የሰው ጥላ ሲያርፍብኝ ታየኝ:: መጀመሪያ ፍቅርተ መስላኝ ነበር:: ቀጥ ብዬ ተመለከትኩ የተሰበሰበውን መጋረጃ በእጇ እንደያዘች ፋና በሬ ላይ ቃፊር መስላ ቆማለች...መንፈስ !! ዝም ብዬ አየኋት::

"ተሻለህ ?" አለችኝ:: እውነቱን ለመናገር ሳቄ ነበር መጀመሪያ የመጣው::

"አ..ዎ ደህና ነኝ" አልኳት መጋረጃውን ለቅቃ ተመልሳ ሄደች:: ውስጤ ሊዳፈን ዳር ዳር ሲል የነበረውን ፍቅር ቆስቁሳው ሄደች:: የተዳፈነ ፍላጎቴ በአንዲት ቃል እንደገና ነበልባል ሆኖ ፋናን በመሻት ያንገበግበኝ ጀመረ:: ለሌላ ዘላለም እዚሁ ቤት እንደምኖር እያሰብኩ ነበር:: ምን ጉድ ናት ይህቺ ፋና !! ሲቆይ የገባኝ አንድ ነገር ቢኖር ፋና እንኳን ሌላ ሰው ጋር ራሷም ጋር ለማውራት የምታፍር አይነት ልጅ መሆኗ ነበር::

የተቋረጠ ሰላምታዬን ቀጠልኩ:: ፋናም ከወትሮው ትንሽ፣ በጣም ትንሽ ቀረብ ያለችኝ መሰለኝ:: ይህን ቀረቤታ በሌላ መንገድ ለመግለፅ ካስፈለገ በዓይን የማይታይ በጣም ደቂቅ የሆነ የመቀራረብ ለውጥ ልንለው እንችላለን:: ከተለመደው መቀራራብ በመቶ ሚሊየን እጅ ያነሰ ረቂቅ የነፍስ መቀራረብ:: ለእኔ ግን ይታየኛል ፍቅር የሚሉት አጉሊ መነፅር ዓይኖቼ ላይ ተደንቅሮ ነበርና የማያሳየኝ ነገር አልነበረም ::

የማይታዩ መቀራረቦች ተደማምረው ወደሚታይ መቀራረብ ለመቀየር ዓመት ወስደዋል:: ይሄ ቀስ እያለ የተገነባ ፅኑ የመቀራረብ ግንብ የወሬ ዛዛታ፣ አሰር ጊዜ የመማማል ስሚንቶ አልነበረም ፀንቶ እንዲቆም ያደረገው - መሰረቱ ዝምታ ነበር:: በእኔና በፋና ውስጥ ዝምታ ነበር:: በዛች ውድና ዘላለማዊ በምትመስል የቡና ሰዓት በእጣን መጋረጃችን ውስጥ ሁለታችንም ዓይኖቻችን ሲገጣጠሙ ነፍሶቻችን የሚያወሩት ነገር ነበር:: ፍቅርተና እማማ አመለ በሚያወሩን ነገሮች የጋራ ሳቅ ስቀናል፣ ፋና ስትስቅ ሳቋን አጅቤ እስቅ ነበር ምንም ይሁን ጉዳዩ፤ እኔም ሳወራ ፋና ትስቅ ነበር - ድጋፍ ነው:: ሳቋ ውስጥ "ለዘላለሙ ሳቅ አይለይህ" የሚል ምርቃት ነበር::

ፋናን በየቀኑ አፈቅራት ነበር:: አዳዲስ አይነት ፍቅር፣ ሰርክ አዲስ ፍቅር:: እንተያያለን:: ዓይኖቻችን ውስጥ ከብረት የጠነከረ መሻት ነበር:: ቃል ሳንተነፍስ ነገሩን ጨርሰነው ነበር...
"ፋኒ የኔ መልአክ እንዴት ነሽ"

"አብርሽዬ የኔ ጌታ ዛሬ ናፍቀኸኝ ነበር የት አምሽተህ ነው"

"ምን አንድ ሞዛዛ አስተማሪ ሲሚዘዝብን አመሸ ፋኒዬ የኔ ውብ..." በቃ እንደዚህ የምናወራ ይመስለኛል:: ራሴ በፈጠርኩት የሀሳብ ንግግር በደስታ አብዳለሁ:: እኔና ፋኒ ተግባብተናል:: እማማ አመለ እና ፍቅርተ እዚህ ቤት ውስጥ የታፈነ ገሞራ ሊፈነዳ እየተብላላ መሆኑ በጭራሽ አልገባቸውም:: ፍቅር ወሬ አያስፈልገውም፣ አዳሜ ጉድ የሆነው የሰጋም የነፍስም ዓይኖቹን ዘግቶ ስለፍቅር እየደሰኮረ ነው:: እኔና ፋኒ ዓይኖቻችንን ከፍተናቸው ነበር:: እናም በዓይኖቼ የፋናን ልብ እየተመለከትኩት ነበር - ወዶኛል ! የፋናም ዓይኖች ልቤ ላይ ከተደገሰላቸው የፍቅር ድግስ ድርሻቸውን አንስተው ሲመለሱ ይታወቀኛል:: የሰው ልጅ እድሜ በወራት ቢሰየም ያ ጊዜ ለእኔና ለፋና መስከረም ነበር:: የህይወታችን መስክ በአደይ አበባ የተሸቆጠቆጠበት የመኖር ጅማሬ::

ቀስ በቀስ ፋና ወደከፍሌ ጎራ ማለት ጀመረች፡ ፍራሽ ፊጫፍ ላይ ትቀመጥና እናወራለን፡፡ ስለምን እንደምናወራ አላውቅም፡፡ ብቻ ፋና ካለች አውራ አውራ ይለኛል፡፡ ለፍላፊ እሆናለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ ፍቅርተም አብራን ስለምትሆን ነፃ ሆነን እናወራም ::

አንድ ቅዳሜ ቀን ከሰዓት በኋላ ፍቅርተ የት እንደሄደች እንጃ ቤት አልነበረችም፡ እማማ አመለም ለቅሶ ቤት ሄደው ነበር፡፡ ፋና መጣችና መጋረጃዋን ገለጥ አድርጋ በር ላይ ቆመች፡ ፋና ግቢ ካላልኳት አትገባም፡፡

"ፋኒ ግቢ!" አልኳት ገባችና ፍራሹ ፊጫፍ ላይ ተቀመጠች፡፡ እኔም ፍራሽ ላይ ተቀምፊጫለሁ-ጎን ለጎን ነን፡፡ ፋና አንደ እንግዳ መሬት መሬት እያየች ተቀምጣለች፡፡ ውስጤ በሐሴት ይጨፍራል፡፡ በዓለም ላይ ካሉ አፀብ ድንቅ ነገሮች ሁሉ ትልቁ ነገር ጎኔ ተቀምጧል-ፍቅር!!

ከብዙ ዝምታ በኋላ፣ "ታምሜ ያልጠየቅሽኝ ለምንድን ነው?" አልኳት ጥያቄዬ ድንገተኛ ነበር፡፡ደግሞ የመቼውን ሀመም አንስቼ እንደወቀስኳት ለራሴም ገርሞኛል፡፡

"ቤተክርስቲያን ስሄድ እንዲሻልህ ስፀልይልህ ነበር፡፡ በጣም ነበር የተጨነቅኩት ...ደግሞ እንዲሻልህ ተስዬልህ ነበር" አለችኝ፡፡ ውስጤ አዘነ፡፡

"እና ስእለትሽን አስገባሽ?" አልኳት እንደ ቀልድ ነበር የጠየቅኳት፡፡ ፋና አቀርቅራ ዝም አለች፡፡ ፋና የተሳለችው አንድ ፓኮ ሻማ ነበር፡፡ብር ስላጣች ስእለቷን አላስገባችም፡፡ ስትነግረኝ አንጀቴ ነው የተላወሰው፡፡ እጇን በእጄ ያዝኩት፤ ደነገጠች፡፡ ቀስ አድርጋ እጇን ወደ ኋላዋ ለመሳብ ሞከረች፤ እኔ ግን እጇን ይገሬ ወደ እኔ ሳብኳት ፤ ሰውነቷ ይንቀጠቀጥ ነበር፡፡ ቀና ብላ አየችኝ ፤ ዓይኖቿ በእንባ ተሞልተው ነበር፡፡ ከንፈሮቻችን ሲገናኙ የፋና ጉንጮች ላይ እንባዋ ተዘረገፈ፡፡ ጥብቅ አድርጌ አቀፍኳት ፤ ደረቴ ላይ ተለጥፋ በእጆቿ የወገቤን ዙሪያ አቀፈችኝ፡፡

*** *** ***

ከፋና ጋር ከተሳሳምንባት ቅዳሜ በኋላ ዋና ስራችን የእማማ አመለ እና የፍቅርተ እግር ሲወጣ መጠበቅ ሆነ...በቃ ወጣ ሲሉ ፋና ወደ ከፍሌ ሮጣ ትመጣና እቅፌ ላይ ናት፣ ከንፈሮቻችን እንዳይገናኙ ማድረግ ከሁለታችንም አቅም በላይ ነበር፡፡ በፍቅር ሰከርን፤ አንዳንዴ እማማ አመለ ቤት ውስጥ ሆነውም ፋና ተነስታ ወደ ከፍሌ ትገባለች፣"አብርሽ ስራ ይዘሃል እንዴ?" ትላለች::እማማ አመለ ከትምህርት ጋር የተያያዘ ነገር አድርገው ስለሚያስቡት በጭራሽ አይጠራጠሩም::ፋኒ ወደ ከፍሌ ትገባና እንደ እብድ ትስመኛለች! ከሚፈታተነኝ ስሜት ጋር እየታገልኩ እማማ አመለ እንዳይሰሙ የተቻለኝን ሁሉ አደርጋለሁ፤ ፋኒ ግን መሳሳም ከጀመርን ነፍሷን አታውቅም፤ ማንም ቢመጣ ግድ አይሰጣትም::

ማታ ማታ ቡናችን ላይ ስንቀመጥ ፋኒ ዓይኖቿን ከእኔ ላይ መንቀል አትችልም፤ በቃ ዓይኗ ቡዝዝ ብሎ ታየኛለች:: አስተያየቷ ይጨንቀኛል:: ፍቅርተ ድንገት ብትጠራጠር ብዬ እፈራለሁ::

ደግነቱ ፍቅርተ ሳታቋርጥ ስለምታወራ ሁለታችንንም አትመለከተንም:: ፋና ትምህርት ማጥናታ
ሁሉ እርግፍ አድርጋ ተወችው:: በየምክንያቱ እኔ ክፍል መመላለስ ሆነ ስራዋ:: መቸም እኔና
ፋና ከዚህ በፊት እማማ አመለ አዕምሮ ውስጥ የፈጠርነው እምነት ረዳን እንጂ የፋና ባህሪ
መቀየር፣ የሁለታችንን የፍቅር ግንኙነታችንን አፍ አውጥቶ የሚናገር ነበር:: አንዳንድ ሰው አ
መሃል ላይ መቆም የማይችል፣ ወይ ጥቅልል አድርጎ ራሱን ይሰጣል፣ አልያም ገና ከሩቁ ከሰው
ይሸሻል - ፋና እንደዛ ነበረች:: ሙሉ እሷነቷን ለእኔ ስለሰጠችኝ ለምትሰራው ነገር ሁሉ ሌ
ሰው አልታይ አላት::

*** *** ***

የነፋና ኑሮ ሊገልፁት በማይችሉት ድህነት ውስጥ የተዘፈቀ ነበር:: ባጭሩ ቤት ያላቸው የጎዳና
ተዳዳሪዎች ይመስሉኛል:: አንዳንዴ እማማ አመለ የከሰል መግዣ ብር ያጡ ስለነበረ ከቤታ
ጋር ተያይዛ የተሰራች በላስቲክ የተጋረደች ኩሽና ውስጥ ምናምኑን ጓድፈው ይማግዱና ቡና
ያፈላሉ:: ቡናው ታዲያ ጣዕሙ ጭስ ጭስ ይላል:: እኔ ያን ያህል ብር ባይተርፈኝም አንዳንዴ
ከቤተሰብ ሲላክልኝ ለፋና አልያም ለፍቅርተ ትንሽ ብር ልሰጣቸው እሞክራለሁ:: ሁለቱም ቢሞቱ
ብር ከእኔ አይቀበሉም:: ብዙ ጊዜ ሞክሬ ሲቸኩኝ መጠየቁንም ትቼዋለሁ:: አንድ ቀን ታዲያ
ፋና ወደ ክፍሌ ገባችና እየፈራች "አብርሽ ሰላሳ ብር አለህ ?" አለችኝ ፊቷ ላይ የነበረው ሀፍረት
ያሳዝን ነበር:: ደስ ብሎኝ ለፋና ድፍን ሃምሳ ብር ሰጠኋት፣ ደስ ብሏት እየተጣደፈች ወጣች::

ፋና ወደ ማታ አንድ የተጠቀለለ ነገር ይዛ ወደ ክፍሌ ገባች:: ፊቷ በደስታ ፈገግታ ተጥለቅልቋል
: ጥቅልሉን ፈታታችና አንድ ጥቁር የሴት ጅንስ ሱሪ አወጣች፣ "ለፍቅርዬ ገዛሁላት" አለችኝ::
ሱሪውን ሳይሆን ፋና ፊት ላይ የነበረውን ፈገግታና ደስታ አይቼ መጥገብ አልቻልኩም:: ፋና
እንደዚህ በደስታ ስትሰክር አይቻት አላውቅም::

ትምህርት ቤታቸው ውስጥ በነበረ የስነተዋልዶ ስልጠና ላይ ተሳትፋ በተሰጣት አበል ከእኔ ሰላሳ
ብር ጨምራ ለፍቅርተ ይህን ሱሪ ገዛች:: ፋና እንዲህ አይነት ልጅ ነበረች:: ቁንጅናዋ የልብሷን
ተራነት ይሸፍነዋል እንጂ ለራሷ አንድም የረባ ልብስ የላትም:: አዲሱን ሱሪ ይዛ ፍራሽ ጫፍ
ላይ ተቀመጠችና በጀርባዋ ተደገፈችኝ:: የሆነ ርካታ ይነበብባት ነበር::

"ፍቅርዬን እወዳታለሁ ከህፃንነታችን ጀምሮ ሁሉም ሰው እንደገፋት ነው የኖረችው:: ሁልጊዜም
ስለሷ እያሰብኩ እሰቃያለሁ::" አብርሽ ፍቅር እኮ እንደ መልካ አይደለችም ደግ ነች፣ ጥሩ
እህት፣ ጥሩ ጓደኛ ናት:: ሁሉም ሰው ግን ይርቃታል" አለችና ማልቀስ ጀመረች:: እንባዎቿን
ጠረግኩላት:: እንባዋ በንፁህ ጉንጮቿ ላይ ሲንኳለል መሰተዋት ላይ የፈሰሰ ውሃ ይመስል ነበር፤
ጉንጯን ሳምኳት ፤ ወዲያው ግን በየት በኩል እንደተንሸራተተኩ እንጃ ከንፈራችን ተገናኘ::
ቅልጥ ያለ መሳሳም ውስጥ ገብተን ይሄን የዘቀጠ ኑሮ የጠቆረ ድህነት ለደቂቃዎች ተሰናበትነው::

ሱሪው ፍቅርተን ቀየራት:: ስትለብሰው ዳሌዋን ሰፋ አድርጎ ወገቧን ሸንቀጥ ስላደረገው የፍቅርተ

ቁንጅና መቃብሩን ፈንቅሎ ወጣ። ሱሪውን ስትለብስ አንድ የጥንካሬ መንፈስ የለበሰች ይመስል አስገራሚ በራስ መተማመን ይታይባታል። ጓደኞቿ ጋር መውጣት፣ አመሻሹ ላይ ከጎረቤት እኩዮቿ ጋር ተያይዛ መዘር ጀመረች። በዕርግጥም ሱሪው የሰውነቷን ቅርፅ ጎላ አድርጎ አሳምሯት ነበር። ይህንን እድናቆት ከአንዳንድ ወንዶች ጭምር እንደተቸራትም ፍቅርተ ራሷ በደስታ ለእኔና ለፋና እየነገረችን ስታስቀን ነበር። ልብስ መንፈስ ነው። ሲጋን ሸፍኖ የሲጋን ውበት የሚያጎላ መንፈስ። ይሄ መንፈስ ሱሪ ተመስሎ ፍቅርተ ላይ አርፎ ነበር ።

*** *** ***

የእነፋና ህይወት ከቀን ወደቀን ወደባሰ ድህነት እየተዘፈቀ ነበር የሚሄደው። እማማ አመለ አልፎ አልፎ ልብስ ያጥቡላቸው የነበሩ የመንገድ ስራ ሙያተኞች ነበሩ። ከዛች የሚያገኟት ገቢ እኔ በየወሩ ከምሰጣቸው የኪራይ ብር ጋር ተዳምራ ኑሯቸውን ስትደጉም ኖራለች። ታዲያ የመንገድ ስራ ባለሙያዎቹ መንገዱን ሰርተው ስለጨረሱ የእማማ አመለም ገቢ ተቋረጠና ቤተሰቡ የባሰ ችግር ላይ ወደቀ። አንዳንድ ቀን የወትሮውን ቡና ማፍሊያ ብር ስለሚያጡ ሁላችንም በጊዜ እንተኛለን። ቤቱ እንደ መቃብር ቤት ፀጥ ይላል። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በሰፈሩ ለሚያልፈው መንገድ ግንባታ ቤታቸው በቅርቡ እንደሚፈርስ ለእማማ አመለ ተነገራቸው። እማማ አመለ ይህን መርዶ እንደሰሙ ሙሉ ቀን ታምመው ከአልጋቸው ሳይነሱ ዋሉ።

አንድ ቀን ታዲያ ፍቅርተ ትምህርቷን አቋርጣ ካፍቴሪያ በእቃ አጣቢነት ለመቀጠር መወሰኗን ለቤተሰቡ አሳወቀች፤ መርዶ ነበረ። እማማ አመለ እያለቀሱ እግሯ ላይ ወድቀው ለመኗት። ፋና ፊቷ ገርጥቶ እና አይኖቿ በእንባ ተሞልተው ዝም ብላ ፍቅርተን እና እናቷን ትመለከታለች። በብዙ ልመና ፍቅርተ የዛን ቀን ትምህርት ቤት ሄደች። ፋና ፊቷ በሐዘን ድባብ ተውጦ ከወትሮ ዝምታዋ ሺ ጊዜ የገዘፈ ዝማታ ውስጥ ሰጥማ ዋለች። የዛን ጊዜ ፋና የአስራሁለተኛ ክፍል ፈተና ወሰዳ ውጤት እየተጠባበቀች ነበር።

በቀጣዩ ቀን ወደ ማታ ላይ ፋና ወደ ክፍሌ መጣች። አልሳመችኝም፣ ትከዝ ብላ ፍራሽ ጫፍ ላይ ተቀመጠችና "አብርሽ አረብ አገር ልላክሽ የሚለኝ የሆነ ጎረቤታችን አለ፣ ብዙ ልጆች ልኳል እዚሁ እኛ ሰፈር ነው ተፈሪ የሚባለው ታውቀው የለ ?" አለችኝ።

"እና..." አልኳት አሁኑኑ ብርር ብላ ትሄድብኝ ይመስል ስጋት ሁለመናዬን ወርሮት እጆቿን በእጆቼ እየያዝኩ። ደንግጬ ነበር፤ መተንፈስ ሁሉ አቅቶኝ ነበር።

"አይ ቢያንስ ፍቅር ትምህርቷን እስክትጨርስ ለሁለት ዓመት ሰርቼ ብመለስ ብዬ አሰብኩ፤ በዛ ላይ ይሄ ቤት ከፈረሰ የት እንወድቃለን - ዘመድ የለን መጠጊያ" አለችኝ። ድንጋጤዬ አሰደንግጧት ሳይሆን አይቀርም ስትናገር ፈርታ ነበር።

"አብደሻል ፋኒ...ምን ሰይጣን ነው ይሄን ያሳሰበሽ...እንደኤት እንደዚህ አይነት መጥፎ ነገር

ታስቢያለሽ" ፍህክባት...::

"እረ አብርሽ ቀስ እማማ እንዳትሰማ" አለችኝ በሚንሾካሾክ በአገሬ, ወይዛንኛው ከፋፋል እየጠቆመች::

"ስሚኝ ፋኒ ! ትምህርቴን ልፈጽርስ፣ አንድ ዓመት የማትሞላ ጊዜ ናት የቀረችኝ:: እንደጨረስኩ እንጋባለን፣ ስራ እይዛለሁ:: ከዛ በኋላ አንቸገርም ፣ እባክሽ ለዘሀች አሞር ጊዜ ብለሽ መጥፎ ነገር አታስቢ!" ፋናን ጨምድጄ ይዤ እንደ አብድ ለፈለፋኩ:: የምናገረው ከልቤ ነበር:: ፋናን ማግባት በምድር ላይ ካሉ ጉዳዮች ሁሉ ቅድሚያ የምሰጠው ጉዳይ ነበር:: ፊቷ ላይ የነበረው ባደነት ፣ ዓይናኟ ውስጥ የነበረው ተሰፋ መቁረጥ የነገረኝ ነገር ነበር:: ፋና ሰጋዋን አሰቀምጣ ቀድማ ወደማታውቀው ዓለም ሄዳለች:: በቃ የለችም :: ሳምኳት ምንም አልተሰማትም ! ፋና የኔ ውብ የእኔ መለአከ እንኳን ስሚያት ዓይናቿችን ሲተያዩ ፊቷ በፍቅር ስሜት የሚቀላው ፋና አይኔ እያየ ከስማለች:: እንደ ግዑዝ ተራራ ከሰሩ ውሃ እንደሚያመነጭው ማዑዝ ሰጋዋ ብቻ እንባ እያፈለቀ አጠገቤ ተቀምጧል::

"ምናባቴ ላድርግ አብርሽ ጨነቀኝኮ...ለሰሙ የመጀመሪያ ልጅ ነኝ...ትልቅ እህት ነኝ:: ቤተሰቦቼ በችግር ሲያልቁ እጄን አነባብሬ ማየት ብቻ ሆነ ስራዬ:: እህቴ በብሰጭት አንድ ነገር ብትሆንብኝ ዘላለም ሲፀፅተኝ ይኖራል:: ማነው የዚህ ቤተሰብ ታዳጊ:: ዘመድ የለንም፣ ማን መጥቶ ከዚህ መከራ ያውጣን ? ...መሃል አዲስ አበባ ላይ ቤተሰቦቼ በረሃብ ሲሞቱ ዝም ልበል ?...መሃል አዲስ አበባ ቤተሰቦቼ በድርቅ ይለቁ ? ...ጎረቤት የሚሰራ ወጥ እየሸተታቸው እንጀታቸው ታጥፎ ሲተኙ ዝም ልበል ? ንገረኛ አብርሽ ! እሺ ምን ልሁን፣ ሴተኛ አዳሪ ልሁን? እናቴ የቡና ሱስ እያሰቃያት አይኗ እንባ እያጎረፈ ጎረቤት የሚወቀጥ ቡና ድምፅ እያዳመጠች "ቡና በጠሩኝ" እያለች ስትመኝ እያየሁ ስንት ዓመት በዝምታ ልኑር?...አንዲት ልጅቿን ለማሳደግ አድሜ ልኳን የተራበች የተንከራተተች ባልቴት ልጅቿም ደርሰው በርሃብ ስትሰቃይ እያየች ዝም የምትል ልጅ ልጅ ትባላለች ? አሄዳለሁ ! የትም ቢሆን አሄዳለሁ" ብላኝ እንባዋን ጠራርጋ ከከፍሌ ወጣች:: አፈር ለብሶ በዝምታ የኖረ ፈንጅ የድህነት ጨካኝ እግር ረግጦት ፈነዳ ፤ ውስጤ በፍንዳታው ሲናጥ ይሰማኛል፤ የአብሮነት ከተማ ሲፈራርስ፣ የፍቅር ቅርስ ሲወድም ይታየኛል::

ማታ ላይ ፍቅርተ ፊቷ ሳቅ ለብሶ ሳቅ ጎርሶ መጋረጃዬን እስኪገነጠል በርግዳው ገባች:: ተጠምጥማ ጉንጬን ሳመችኝ :: እውነቱን ለመናገር በዛ ከንፈር አፈሰችኝ ማለት ይሻላል ! ከዛም ድምጿን ቀንሳ፣ "ቀጠረኝ" አለችኝ:: ለሶስት ዓመት ያፈቀረችው ልጅ ቅዳሜ ሊያገኛት ቀጥሯት ነበር:: "ለምን?"..."እንዴት?" አላልኳትም የፋና ጉዳይ እያብሰለሰለኝ ነበር:: ብቻ ለማስመሰልና አብሬያት ለመደሰት ሞከርኩ:: ፍቅር ግን እንዴት ኃያል ነው በእግዚአብሔር ! ችግር አያግደው ድህነት - በቃ በመከራ የተከበበን ሰው ከመሬት አስነስቶ ያሰፈነድቀዋል ወይንስ ያፈቀረ ሰው ለሌላው የማይታይ ላፍቃሪው ብቻ የሚገለጥ ከችግር፣ ከድህነት፣ ከመከራ የሚታደግ የመላእክት፣ የእሳት ሰረገላ አገሩን ከብቦ ይታየዋል ?

ለፍቀርተ ቀጠሮ በነገረችኝ ሰዓት ቸልተኛ ልሁን እንጂ በእርሷ ደስታ የፋና የስደት ሐሳብ

ይጨነግፋል ብዬ ስላሰብኩ በሚያስፈልጋት ሁሉ ከጎኗ ሆኜ ድጋፍ ለመስጠት ወሰንኩ:: ቅዳሜ ጧት ሃምሳ ብር ሰጠኋት:: ላለመቀበል እንገራግራ ነበር፣ "ፀጉርሽን ተሰሪ! ደግሞ ቀጠሮ ቦታ ባዶ እጅ አይኬድም" ብዬ አሳመንኳት:: ብሩን ተቀበለችኝ::

ጥቁር ሱሪዋን ከአሮጌው ሻንጣ አወጣችና ማጠብ ጀመረች፣ "ይሄ ሱሪ አዳውን አየ እስቲ አሁን መች ለበሽውና የምታጥቢው?" አሉ እማማ አመለ:: ፍቅርተ እያንጎራጎረች አጠባዋን ቀጠለች:: በዚህ ሰዓት እግዜር ወርዶ ቢናገራትም መስማቷን እንጃ ! ሱሪውን አጥባ ስትጨርስ አስተካከላ ገመድ ላይ አሰጣችና ወደ ፀጉር ቤት በደስታ እየተንሳፈፈች ሄደች:: እኔም "ከላስ" ስለነበረኝ ወደ ግቢ ሄድኩ::

*** *** ***

ከሰዓት በኋላ ወደ ስምንት ሰዓት አካባቢ ከምማርበት ኮሌጅ ስመለስ እማማ አመለወርቅ በራቸው ስር ሁልጊዜ የሚቀመጡባት ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ተቀምጠው አገኘኋቸው::አይናቸው ቡዝዝ ብሎ በሀሳብ በመመሰጣቸው እስካናግራቸው ድረስ አጠገባቸው መድረሴንም አላዩም ነበር:: ለወትሮው እዚህች ድንጋይ መቀመጫ ላይ የሚቀመጡት እጃቸው አጠር ሲል ለእለት ቡና ብር ቢጤ ሲቸግራቸው ነበር:: የድንጋይ ወንበሯ የመተከዣ መድረካቸው ናት::

"ማዘር ምነው ሰላም አይደሉም እንዴ ?" አልኳቸው::

ቀጥ ብለው እንባ በቋጠሩ ዓይኖቻቸው ተመለከቱኝና ሳግ በተናነቀው አሳዛኝ ድምፅ ! "የፍቅርዬን ሱሪ ወሰዱባት አብርሽ" አሉኝ ሌባ ቁሳቁስ ብቻ ሳይሆን ተስፋ ጭምር እንደሚሰርቅ የገባኝ ያኔ ነው:: ፍቅርተ ለዓመታት ስትመኘው ከኖረችው ፍቅር፣ በተዓምር ከተሳካ ቀጠሮ በአንድ ሱሪ ምክንያት መቅረት አልፈለገችም:: የሆዷን በሆዷ አድርጋ ሰፈር ውስጥ ወዳሉ እኩዮቿ ሁሉ እየሄደች ልብስ እንዲያውሷት ጠየቀች - አልተሳካላትም:: ሁሉም ልብስ አላቸው፣ ሁሉም ልብሳቸውን የማያውሱበት ምክንያትም አላቸው:: ሁሉም ግን አንድ ተራ ልብስ በዚያች ቀን ለፍቅርተ ከንጉሰ ካባ የበለጠ ዋጋ እንደነበረው አያውቁም ነበር::

ፍቅርተ አንገቷን ደፍታ ወደ ቤት ገባችና ሁልጊዜ ፋና ትቀመጥበት የነበረው ኩርሲ ላይ ተቀመጠች :: የፋናን ወንበር ብቻ ሳይሆን የፋናን ዝምታ ወረሰች:: ከዛን ቀን ጀምሮ ፋናም ዝም፣ ፍቅርተም ዝም ! እማማ አመለ ብቻ እንዲሁ የልጆቻቸውን ዝምታ ለመስበር የባጥ የቆጡን ያወራሉ:: የማታ ማታ ቡናችን እንደወትሮው አይደምቅም ነበር:: የፍቅርተን ሱሪ የወሰደው ሌባ የፍቅርተን ምላስ የወሰደው እስኪመስለኝ ፍቅርተ ከዛ በኋላ እንደበፊቱ ስታወራ ሰምቻት አላውቅም::

"አብርሽ ሰላም ነው" ቢቃ የምታናግረኝ እችን ብቻ ነበር:: እንደ በፊቱም እቤቴ አትመጣም:: ከትምህርት ቤት ስትመለስ የእማማ አመለን ነጠላ በደንብ ልብሷ ላይ ጣል ታደርግና ቤተክርስቲያን ትሄዳለች:: አንዳንዴ በጣም አምሽታ ስለምትመለስ እና ጧት ስለምትወጣ ለሁለት ለሶስት

ቀን አንኳኳርም:: በሰሱ መጋረጃ ዓይኖቼን ልኬ በደበዘዘው ብርሃን የሰለቸውና ከውትሮው የባሰ አስፈሪ የሆነ ፊቷን አየለሁ::

ፋና ጋር የነበረን ግንኙነት ግን ቀስ በቀስ እንደነበረው ተመለሰ ፤እንደውም ከበፊቱ የበለጣ አብረን መዋል ጀመርን:: ፋናም የበፊቷ አፍቃሪ ፋና ሆነች:: ዓለምን ረስተን በዛች ደሳሳ ጓዳ ውስጥ የራሳችን ፀሐይ፣ የራሳችን ጨረቃ፣ የራሳችን ከዋከብት ያሉባት ዓለም ፈጠርን ፤ ፋናን ያፈቀርኳት ሳይሆን እኔን ራሴን የሆነች እስኪመስለኝ ሁሉ ነገሬ ሆነች::

የሶስተኛ ዓመት ትምህርት እንዳለቀ ለእረፍት ወደ ቤተሰቦቼ ለመሄድ ምን ያህል እንደተጨነቅኩ መግለፅ አልችልም:: ፋናን ትቼ መሄድ ራሴን ትቼ ከመሄድ በምንም አይተናነስም:: ግን የግድ መሄድ ነበረብኝና ወደ ቤተሰቦቼ ጋር ከፍለ ሐገር ለሁለት ወር እረፍት ሄድኩ:: ለተከታታይ ሁለት ሳምንታት ፋና በህዝብ ስልክ እየደወለችልኝ እናወራ ነበረ፣ ከዛ በኋላ ግን ድምፅዋ ጠፋ፤ ለአስራ አምስት ቀናት ጠበቅኩ ፤ ፋና አልደወለችም:: የማውቀው ስልክ አልነበረኝም፣ ፋናም ስልክ አልነበራትም - ናፍቆቷን መቋቋም ለእኔ ሰቃይ ነበር ::

በመጨረሻ ወሰንኩ:: ቤተሰቦቼን የምማርበት ኮሌጅ እንደጠራኝ በመንገር ማቄን ጨርቄን ሳልል በአንድ ወሬ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ:: አዲስ አበባ ስደርስ ልቤ ፈርቶ ነበር:: እቤት ስደርስ እማማ አመለ አንገቴ ላይ ተጠምጥመው ሳሙኝ:: እንባቸው አንገቴ ስር ሲረጥበኝ ነበር እያለቀሱ መሆኑን ያወቅኩት::

ወደ ቤት ሰገባ ቤቱ ካለወትሮው ጭር ብሏል:: እማማ አመለ ጉድ ጉድ ብለው ቡና አፈሉ፣ "ድንገት መጣህብኝ" ብለው ቁራሽ እንጀራ በበርበሬ አቀረቡልኝ እና የመጀመሪያውን ቡና ቀድተው ሲያቀብሉኝ እጃቸው ሲንቀጠቀጥና ሲኒው ከማስቀመጫው ጋር በእጃቸው እንቅጥቃጤ ምክንያት ሲንቀጫቀጭ ተመለከትኩ:: ልቤ የባሰ ፈራ::

"አቡዬ ይሄውልህ ፋኒዬ ድንገት ሳላሰበው ብድግ ብላ አረብ አገር ሄደችብኝ" አሉና እንባቸውን ዘረገፉት ! የያዝኩት ቡና ሳላሰበው ከእጄ ላይ ወድቆ ተከነበለ::

"እንዴት ማዘር?...ማን ወሰዳት?...እርስዎ እንዴት ዝም ይላሉ?..." የጥያቄ መዓት ዘረገፍኩባቸው፤ ራሴን መቆጣጠር አልቻልኩም ፤ እማማ አመለ ግን አንገታቸውን ደፍተው አንዲት የቄጤማ ዘለላ እያፍተለተሉ ሰቅሰቅ ብለው ከማልቀስ ውጭ ቃል አልተነፈሱም:: ሽበት የወረረው ፀጉራቸው፣ ቆዳቸው፣ በእርጅና ብዛት የተጨማደዱ እጆቻቸውና አስር ቦታ ላይ በከር የተሰፋ ኮንጎ ጫማ ያጠለቀ እግራቸውን ስመለከት ከፋና ናፍቆት ጋር ተደማምሮ እንባዬ ከውስጤ ገነፈለ ::እማማ አመለ ማልቀሴ አስደንግጧቸው ከፍራሻቸው ተነስተው መጥተው ጎኔ ተቀመጡና እንደ ልጅ አጥንታም ደረታቸው ላይ ራሴን አስጠግተው አቀፉኝ:: ሁለታችንም በዛች ልትፈርስ አንድ ሃሙስ በቀራት ደሳሳ ጎጆ ሰቅሰቅ ብለን ተላቀስን::

ወደ ማታ ላይ ፍቅርተ መጣች:: ገና ሲታየኝ አቅፋኝ መነፋረቅ ጀመረች:: በቀጣዩ ቀን የማደርገው ነገር ግራ ገብቶኝ ፍራሽ ላይ ተቀምጬ ሰቆዝም ፍቅርተ ወደ ከፍሌ ገብታ የተጣጠፈ ወረቀት ሰጠችኝ እና ወደ ከፍሏ ተመለሰች:: ፋና የፃፈችልኝ ደብዳቤ ነበር ፤ የፋኒ ትንንሽና ቁልጭ ያሉ ፅሁፎች:-...

"አብርሽዬ መቼም እንደምታዝንብኝ አውቃለሁ:: ጨካኝ ትለኛለህ አውቃለሁ:: ግን...በሌለህበት እዚህች ብዙ ነገር ያሳለፍንባት ጓዳ እየገባሁ ሰንት ቀን አለቀስኩ መሰለህ...ችግራችን ገፋኝ... በየቀኑ የማየው ነገር አንገሸገሸኝ:: ከአንተ በላይ የቤታችንን ችግር የሚያውቅ ማን አለ አብርሽ? በእርግጥ የዛን ጊዜ ለመሄድ ማሰቤን ሰነግርህ የሆንከውን ነገር አይቼ ሐሳቤን ቀይሬ ነበር፤ ግን የፍቅርዬ ሱሪ የጠፋ ቀን በቃ ወሰንኩ:: እንዳትቆጣኝ ሃሳቤንም እንዳታስቀይረኝ ፈርቼ ተደብቄ ደላላው ሰውዬ ጋር አስፈላጊውን ሁሉ ጨረስኩ፣ አንተ ለአረፍት እስከምትሄድ ነበር የምጠብቀው:: ፍቅርዬ በውሰጧ የሞተውን ፍቅር፣ የከሰመውን ተስፋ ማዳን የምችልበት ሌላ ነገር የለኝም::

አፈቅርሃለሁ አብርሽ - አከብርሃለሁ እና እመለሳለሁ::እግዚአብሄር እንዲረዳኝ ፀልይልኝ:: ስለምታፈቅረኝ ከልብህ እግዚአብሄርን እንደምትለምንልኝ አውቃለሁ:: አብርሽ እዛ ትልቁ ዲከሽነሪ ውስጥ የነበረውን ጉርድ ፎቶግራፍህን ሳላስፈቅድህ ወስጀዋለሁ:: ሁልጊዜም ላይህ አፈልጋለሁ - ሁልጊዜም አብርሽዬ...ግን እንዳትረሳኝ ሁልጊዜም አፍቅረኝ::

አብርሽ ትወደኝ የለ ? እማማን ትወዳት የለ ? ፍቅርን ትወዳት የለ ? እኔ እና አንተ በፍቅር ልናሳልፋቸው ከምንችላቸው ውድ የፍቅር ጊዜያት ሁለት ዓመት ለምንወዳቸው ሰዎች ብንሰጥ ሁሉንም ነገር ታውቀዋለህና ይቅር ትለኛለህ ብዬ አሰቤ ነው:: እንኳን እንዲህ ርቄህ መሄድ ከዚህች መጋረጃ አልፌ ከከፍልህ ሰወጣ አልቅሽ አልቅሽ እኮ ነው የሚለኝ:: አብርሽ እፈራለሁ፤ ኪፊቴ ምን እንደሚጠብቀኝ አላውቅም - ግን ምናባቴ ላድርግ...እመብረሃን ትርዳኝ !"

ደብዳቤውን አንብቤ ሰጨርስ አቅመቢስነት ተሰማኝ:: በቃ ! ከአሁን በኋላ እድሜ ልኬን ለማንም ለምንም የማልጠቅም ከንቱ መሆኔ ገዘፈብኝ:: ፍራሽ ላይ በደረቴ ተኝቼ ወደ ዛኛው ክፍል በትካዜ መመልከት ጀመርኩ::

ከመጋረጃዬ ባሻገር ድህነት የነገሰበት ዓለም ይታየኛል - የተራቡ ባልቴቶች ቅንጦት ባሰከራት ከተማ ሰር ተቀብረው ይታዩኛል:: ሊሰደዱ የሚያኮበኩቡ ወጣቶች ታዳጊ አጥተው ይታዩኛል... ትምህርታቸውን ትተው ለጉልበት ሰራ የተሰለፉ ወጣቶች ይታዩኛል:: ለእለት ጉርስ ለዓመት ጉርስ የተቸገረ ቤተሰብ ይታየኛል:: ከመጋረጃው ወዲህ ከፍሌ ውስጥ ሬዲዮው ያወራል - ስለ ሙዚቃ ያወራል፣ ስለ ልብስ ያወራል፣ ስለ ፅዳት ያወራል፣ ስለ እድገት ያወራል፣ ስለ ፖለቲከኞች ምርጫ ያወራል፣ የአገር መሪዎችን ያሞካሻል:: ሬዲዮው አጠገብ በልቼ የተረፈኝ ዳቦ በወረቀት ተጠቅልሎ ተቀምጧል:: ከጎኑ እንቁላል የተጠበሰበት መጥበሻ ከነተረፈ የእንቁላል ጥብሱ ይታየኛል:: አኔ ያለሁበት ሆነው የእማማ አመለን ቤተሰብ ሲመለከቱት ይህ ቤት "ከሰሃራ በታች" ነው::

ችግሩ ፣ተስፋ ማጣቱ ፣ስደቱ የተጧጧፈበት፣ ሰው በአይነውሃው የሚጠላበት፣ በተፈጥሮ መልኩ ደረጃው ከፍና ዝቅ የሚልበት፣ ይሄ ቤት "ከሰሃራ በታች" ነው ! እኔ ቤታቸውን ተከራይቼ የምኖረው ስደተኛ ባለቤቶቹ ተወልደው ባደጉበት ጓዳ በችግር ሲሰቃዩ እየታዘብኩ ነውና ይሄ ቤት "ከሰሃራ በታች" ነው:: አዲሳባ እንዲህ ናት ! አገሬ ከነጭ ልብሷ፣ አገሬ ከጠጅና ጮማ ግርጌ እቾትና:: በስስ መጋረጃ ድንበር የተካለሉ ጎረቤቶች አንዱ ብሩን መጣያ አጥቶ በጥጋብ ሽቅብ ሲሸና' ከመጋረጃው ጀርባ በረሀብ ከንብል የሚሉ እልፎች የሚኖሩባት አገሬ እቾትና !

*** *** ***

ከተመረቅኩ በኋላ አዲስ አበባን ለቅቄ ወደ ቤተሰቦቼ ሄድኩ:: እዛው ሰራ ሰላገኘሁ አዲስ አበባን ለአራት ዓመታት ተመልሼ አላየኋትም:: ፋናም በውሰጤ ደበዘዘች::ቀስ በቀስ ያች የፍቅር ጀምበር በመለያየት አድማስ ጠለቀች:: ሌላ ህይወት፣ ሌላ ታሪክ ውስጥ ገባሁ :: ከአራት ዓመት በኋላ የማስተርስ ትምህርቴን ለመቀጠል ወደ አዲስ አበባ መጣሁ ::

"ሂድ! ሂድ!" እያለኝ ከስድስት ወራት በላይ እነ እማማ አመለ ሰፈር ሳልደርስ ቆየሁ:: ምን እንዳስፈራኝ ባላውቅም ውስጤ በፍርሃት ይታመስ ነበር:: አንድ ቀን ግን ወሰንኩ:: ታክሲ ይዤ ወደ ወሎ ሰፈር ሄድኩ:: ከታክሲ ስወርድ የገጠመኝ ነገር አስደንጋጭ ነበር:: የእነፋና ቤት ይቅርና ሰፈሩ ራሱ ምልክቱ ጠፍቷል:: ሰፈሩ የለም መንገድ ሆኗል - ቀለበት መንገድ ሆኗል - በረሀ ሆኗል:: ወገቤን ይዤ ቆምኩ፤ ግራ ገባኝ፤ እንደ አዲስ ፋና ናፈቀችኝ:: እማማ አመለን ማየት ፈለግኩ ! ሁሉም የሉም:: ተስፋ ቆርጬ ተመለስኩ::

ከብዙ ጊዜ በኋላ የማስተርስ ትምህርቴን አጠናቅቄ በምርቃቴ ማግስት ለምርቃት የተነሳሁትን ፎቶዬን ለመውሰድ ካዛንችስ ወዳለ አንድ ፎቶ ቤት ሄድኩ:: ሮዳስ የምትባል ልጅ አብራኝ ነበረች:: ሮዳስ ፍቅረኛዬ ናት:: ፍቅር ከጀመርን ዓመት አልፎናል:: እርሷም እንደኔው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማስተርሷን ስትሰራ ነው የተገናኘነው:: ፎቶ ቤቱ እንደደረስን ፎቶ ያነሳንን ልጅ አገኘነው:: የምርቃት ኮሚቴ ሆኜ ስሰራ ፎቶ የሚያነሳው ልጅ ጋር በደንብ ተግባብተናል::

ፎቷችንን እስኪሰጠን ለእኔና ለሮዳስ ሻይ አስመጥቶልን ስለምርቃት ፎቷችን የባጥ የቆጡን እያወራልን ሰንጠብቅ፣ ድንገት ፎቶ ቤቱ መስተዋት ላይ የተለጠፈ አንድ ሰላሳ በአርባ ሴንቲሜትር ሰፋት ያለው ፎቶ ተመለከትኩ:: ምን አስፈንጥሮ እንዳስነሳኝ አላውቅም:: ወደ መስተዋቱ ተንደርድሬ ሄድኩና ቆምኩ - ፋና ! ራሷ ናት...የራሷ የፋና ፎቶ ነው::

የለበሰችው አጭር ቀሚስ ፍም የመሰለ ቀይ ታፋዋን አጋልጧታል - ቢሆንም ፋና ናት ! ዓይኖቿን ጨፍና ወደ ሰማይ አንጋጥጣለች:: ቀይ የከንፈር ቀለም የተቀቡ ከንፈሮቿ በመጠኑ ከፈት ብለዋል:: ፀጉሯ ባጭር ተቆርጦ ወርቃማ ቀለም ተቀብቷል:: ቢሆንም ፋና ራሷ ናት! አፍንጫዋ ተበስቶ ቀለበት ተንጠልጥሎበታል:: ጡቶቿ ደረቷ ላይ በሰፊው እስከ ሆዷ ድረስ ቅድ ባለው ቀሚሷ ምክንያት ግራና ቀኝ በግማሽ ብቅ ብለው ይታያሉ:: ራቁቷን ናት ማለት

ይቀላል:: ተረበሽኩ:: ጩህ...ጩህ አለኝ::

ጓደኛዬን ሮዳስን ረስቻት ጉርድ ፎቶ በመቀስ እየቆራረጠ ከመደርደሪያው ጎላ ወደ ቆመው ፎቶ አንሺ ተመለስኩና ወደ ፋና ፎቶ በእጄ እየጠቆምኩ፣

"ይህችን ልጅ ታውቃታለህ?" ብዬ ጠየቅኩት::

ለአመል ያህል ወዳመለከትኩት ፎቶ ዓይኑን ላከና በፍጥነት መለሰልኝ፣ "ከዚህ ቀጥሎ፣ ቀጥሎ ያለው ሶስተኛው ቤት ውስጥ ትሰራለች:: ከአረብ አገር ነው የመጣችው፣ አዕምሮዋ ትንሽ ትንሽ ችግር አለበት:: ተጠፍራ ነው የመጣችው:: ደግሞ አረቦች ደፍረዋት የወለደቻት አንዲት ልጅ አለቻት" አለኝ::

"ምንድን ነው ቤቱ ?ማለቴ የምትሰራበት..."

"ቡና ቤት" ብሎኝ ወደ ሰራው ተመለሰ !

"እ...ና ቡና ቤቱ ውስጥ ምንድን ነው የምትሰራው?" አልኩት ባለማመን::

ቀና ብሎ በመገረም ተመለከተኝና፣ "ሴት ልጅ ቡና ቤት ውስጥ ምን ልትሰራ ትችላለች አብርሽ ?" ብሎኝ ጥያቄዬን በጥያቄ መለሰልኝ:: ቀስ ብዬ ስዞር ሮዳስ ጎኔ ቆማ ልጁ የተናገረውን ሁሉ ሲታዳምጥ አገኘኋት:: ፎቷችንን ተቀብለን ስንወጣ ሮዳስ እንደ ቀልድ እንዲህ አለችኝ፣

"ደግሞ ብለህ ብለህ የሴተኛ አዳሪ አድራሻ መጠየቅ ጀመርከልኝ ?" አልመለስኩላትም:: ሮዳስ ዛሬ ካለችበት የትምህርት እና የኑሮ ደረጃ ላይ ቆመው ቁልቁል ወደ ፋና ከተመለከቱ፣ ፋና...ከሰሃራ በታች ናት::

4 ትንሽ ወደግራ ዘምበል...

አባቴ ሲራመድ ትንሽ አንከስ ይላል:: ያን ያህል አንኳን አይደለም:: ወታደር ስለነበር ታፋው አካባቢ ጥይት ጨረፍ አድርጋው ነው:: ('ለጡረታ ሰበብ ትሆን ዘንድ ከእግዜር የተተኮሰች ጥይት' ይላታል አባቴ ራሱ) !! አንድ አራት እርምጃዎቹ 'ኖርማል' ይሆኑና አምስተኛዋ ላይ ትንሽ ወደግራ ዘምበል ይላል - እንደ እኛ ታሪክ !! የራሳችን ፊደል፣ የራሳችን ቋንቋ፣ አድዋ፣ መቅድላ፣ 'ድርቅ' አንከስ ወደ ግራ !! ይሄው ነው !

ታዲያ አባቴን ጥምድ አድርጎ የያዘው የግራ እግሩን በፈንጅ ያጣ ወታደር ጎረቤት አለን ፤ "ለዚች በየአምስት እርምጃው ለምትከሰት እንከሻው 'የአካል ጉዳተኛ' ተብሎ ጡረታ ይበላል:: ይሄ ለጂግሜ ከመሰከረም እኩል ደመወዝ ከመክፈል አይተናነስም - አይ እች አገር ! አይ ታሪክ !" እያለ ያሸሙረዋል - በከራንቹ መሬት እየቆረቆረ....!!

የአባቴን እግር የጨረፈችው ጥይት ለአባቴ ግንባር የተተኮሰች መሆኗን ዘንግቶ:: የተጫረ እግር ከተቆረጠ እግር እያወዳደረ በጉድለት ቁና የታሪክ ገለባውን ሊሰፍር ይዳዳዋል :: ጡረታን የጉዳት ዳረጎት አድርጎ የሚያስብ ከንቱ !! ሰው አንገቱን ተቆርጦ ጡረታ እየተቀበለ መኖር ቢችል ኖሮ፣ "ለአገራቸው ክብር" አንገታቸውን የተቆረጡቱ "ግራ እግር ምን አላት" ብለው በተቆረጠው ግራ እግሩ በሳቁበት ነበር ፤ "አንዱ ባንዱ ሲስቅ ጀምበሯ ጥልቅ" (በጨለማ መሳቅ የለመደ ሆዘብ ስለጀምበር መጥለቅ ምን ገዶት:: ለምን እንጦሮጦስ አትወርድም:: ኮኮቦችን ወላ ጨረቃዋን አስከትላ::)

ቀን ቀን ትሁት፣ የተከበረ፣ የተጣላ የሚያስታርቅ የመንደሩ ዋልታ ነው አባቴ :: ማታ... አቤት ቀንና ማታ በአባቴ ባህሪ ሲለኩ ያላቸው ልዩነት:: ጧት የነበረው አባቴ ሌላ ክፍለ ዘመን፣ ማታ የሚከሰተው ደግሞ ሌላ ላይ የተፈጠረ ፤ ሁለት አባት ያለኝ እስኪመስለኝ !! አባቴ ማታ ማታ ከራሱና ከእነዛ ሁለት ሥዕሎች ጋር ይጣላል ::

ጠጭ ነው። በየቀኑ ይጠጣል። ሲጠጣ ቤተሰብ አያረብሽም። እናቴን አይናገርም። ቤታችን ግድግዳ ላይ የተለጠፉት ሁለት ሥዕሎች ጋር ነው ዱላ ቀረሽ ግብ ግብ የሚፈጥረው - በቃል !!

"አባትህ ስራው ምንድን ነው ?" ብባል፣ "አባቴ ስራው ምን እንደሆነ አላውቅም" ነው መልሴ። ማረያምን አላውቅም !! ትምህርት ቤትም እንደዚሁ ብዬ መልሼ ሁሉም ሳቁብኝ። እኔ ግን ለምን እንደሳቁ አልገባኝም !! የተማሪዎቹ አሸ ይሁን - ምድረ ኩታራ። ቲቸር ምን አሳቀው ? (ከሳቁ በፊት እጉ ነበር የምለው።) የቲቸር ሳቅ ስላበሳጨኝ ሆነ ብዬ እንዲህ ስል ሳቁን ተረጎምኩት፣ "አባትህ ቢያጣ ቢያጣ መምህር መሆን ያቅተዋል ?" ማለቱ ነው።" ባይስማኝም አንጀቴ ራሰ። ይሄን አስቀያሚ መላጣ፣ ኮቱ የተዛነፈ ሂሳብ አስተማሪ ተውትና ስላባቴ ልንገራችሁ...(ሲጀመር ሂሳብ አስተማሪ ስለአባቴ ሥራ ምን አገባው - ደሞ ይሰቃል እንዴ!)

ስለአባቴ ሥራ እንዴት ልበላችሁ? አባቴ አሁን ሹፌር ነው ተብሎ አንድ ፈርማታ ሳያልፍ ራፖርት ጸሐፊ ይሆናል፣ "እሳቸው የሚጽፉት ማመልከቻ መሬት ጠብ አይልም" ተብሎ ባለጉዳይ ቤታችን ሲመጣ፣ አባቴ መጋዝና ሜርቴሎውን ይዞ ገና ድሮ አናፂ ሆኗል። እንግዲህ በከረምት ጣራችሁ አፍስሶ ወይ የእንጨት አጥራችሁ ወድቆ ትላንት ግንቦት ላይ አናፂ የነበረ አባቴን ሰኔ አንድ "ጠግንልን" ብላችሁ ብትመጡ አባቴ ከተከመረ የከሰል ጆንያ ኋላ ቆሞ 'የከሰል ነጋዴ' ሆኖ ታገኙታላችሁ ("ዱቤ ከልከል ነው" ከሚል ፅሁፍ ጋር)...እና አባቴ ሥራው ምንድን ነው ልበል ? ብዙ ሥራ ያለውና ምንም ብር የሌለው አባት !

ብር ከአንዱ ይበደራል፣ የተበደረውን ከሌላ ሰው ተበድሮ ይከፍላል። ለሌላው ሰው ደግሞ ከሌላ ሌላ ሰው ተበድሮ ይከፍላል። ሕፃን እንደነበርኩ ታዲያ ይሄ የአባቴ 'የመበደርና ብድር የመክፈል ሳይከል' መጨረሻ ያለው ስለማይመስለኝ አባቴ እስከዘላለሙ በብድር የሚከሰስ፣ የሚታሰር አይመስለኝም ነበር። ብድር ይከፍላል። እጁ ላይ ምንም ብር አይኖረውም። ብር ለምን ይጠቅማል ቢሉኝ፣ ብድር ለመክፈል። 'ደመወዝ ለምን ይጠቅማል?' ቢባል ብድር ለመክፈል፣ ታዲያ ለምንድነው ሰዎች 'በባንክ ብድር ቤታቸው ተሸጠ' የሚባለው? - እንደኔ አባት ብልህ ስላልሆኑ ነዋ !!

ሥዕሎቹ፣

1. አባቴ በመጠኑ ሲሰክር (ሞቅ ብቻ ሲለው) ፊት ለፊቱ ቆሞ "ሳተናው ደህና አመሸህ!" የሚላቸው የአፄ ቴዎድሮስ ሥዕል የሸጉጣቸውን አፈሙዝ አፋቸው ውስጥ አስገብተው መቅደላ ጫፍ ላይ ሬሳና ቁስለኛ ከሰራቸው ተለሸልሾ የሚታይበት ሥዕል፣ በቀኝ በኩል ከዕቃ መደርደሪያዋ በላይ ግድግዳው ላይ ተለጥፎ ይገኛል። (አባቴ ከዚህኛው ስዕል ጋር የመረረ ጥል የለውም፣ አልፎ አልፎ ካልሆነ...።)

2. አባቴ ስካሩ ከመደበኛው ስካር ከፍ ሲልና፣ ቀን ከገጠመው የሕይወት ስንክሳር ጌሾ ጋር ሲቀየጥ ደግሞ ከማይጋጩት ባላጋራ ጋር ይጋጫል፣ "...የጌታ እየሱስ ክርስቶስ" ምሥል ጋር!!

እየሱስ ቀይ መጎናፀፊያ ለብሶ፣ ረዥም ምርኩዙን በብብቱ ስር ይዞ፣ በር ሊያንኳኳ...በግራ በኩል!! አባቴ ከዚህ ሥዕል ጋር ይጣላል (ድፍረቱ ሊይገርምም ?)

*** *** ***

አባቴ ገና በር ሲያንኳኳ እናቴ ስካሩ እንደኛ ደረጃው ይሁን ወይም ሁለተኛው ደረጃ ታውቀዋለች፣ 'እንዴት ታውቃለች ?' እግዜር ይወቅ !! እነዚህ እናቶች በየድራፍት ቤቱ ስለማይደሰኩሩ እንጂ በየራዲዮና በየቴሌቪዥኑ ስለማይቀባጥሩ እንጂ ስንት ጉድ ተዓምር አለ በውስጣቸው:: ስንት ጉድ፣ መላ...:: እንኳን ባላቸው በር ሲያንኳኳ ቀርቶ ዙፋን ላይ ቂብ ሊል ያቆብቆበ ባለተራ ዓይነ ውሀውን እንብበው ከፉ ይሁን ደግ ያውቃሉ - ዘመን ምስከር ነው !!

ሁለተኛው ዓይነት ስካር ከሆነ እናቴ ተንደርድራ ከርሰቶስ ሥዕል ፊት ትሄዳለች - በፈጣን አነጋገር፣ "ጌታ ሆይ አባከህ የተናገረውን ቢናገር አትቁጠርበት ይቅር በለው" ብላ የንስሃ ቀብድ ታስይዛለች ! (ሙሉውን አባቴ ራሱ ስካሩ ሲበርድለት ያወራርዳል !!) ከዛ በሩን ትከፍትለታለች...!!

ፊቱ ወዝቶ አይኑ በአስፈሪ ሁኔታ ጉሸርጥ መስሎ ይገባል:: "ሰላም አመሻችሁ!" የለ ምን የለ፣ "የአባትህ ገዳይ እዛ ቤት ተደብቋል፣ በግራ በኩል ከአልጋው በላይ ታገኘዋለህ" ብለው የላኩት ይመስል ዝም ብሎ ይገባና በቀጥታ ወደግራ ታጥፎ ከአልጋው በላይ የተሰቀለው የከርሰቶስ ስዕል ፊት ይቆማል ::

ፂሙን እያሻሸ ለረዥም ደቂቃዎች በዝምታ ሥዕሉ ጋር አፍጥጦ ይቆይና ድንገት፣ ..."አንከፍትም!!" ብሎ ይጮሃል:: እናቴ ሽምቅቅ ትላለች::

"ለስንቱ እንከፈት፣ ሲያንኳኩ ስንከፍት ገብተው እኛን ሲያስወጡን:: በጣታቸው ሲያንኳኩ 'ቤት ለእንግዳ' ብለን ስንከፍት በከንዳቸው ሲደቁሱን ከመከፈት ጋር ተጣልተናል ፤ አንከፍትም...!!"

እናቴ ወደ ጣራው ዓይኗን ልካ በለሆሳስ ታነበንባለች:: ለከርሰቶስ "ቅድም ያልኩህን እንዳትረሳው አደራ!" የምትል ይመስለኛል:: አባቴ ይንጎማለላል:: ረዥም ነው ቁመቱ:: ብን ተደርጎ የተበጠረ ጥቁር ከርዳዳ ፀጉሩ ላይ ወደፊት አካባቢ ትንሽ ሸበት ጣል ያደረገበት :: የጨርቅ ሱሪው የተኩሰ መስመር ቀጥ ማለት፣ "ሱሪውን ከለበሰው ጀምሮ ተቀምጦ አያውቅም እንዴ" የሚያስብል፣ በሚገባ የተወለወለ አሮጌ የወታደር ቦት ጫማ :: ይንጎማለላል ...

"አንከፍትም ! አድሜ ልኬን በርህን ሳንኳኳ የከረቸምከብኝ፣ እንዴት ነው የኔን ልብ ዛሬ የምከፍትልህ:: የገቡትንም ማስወጫ አጥተናል እንኳን አዲስ ለሚያንኳኳ ልንከፍት - አንከፍትም!!" ይንጎራደዳል:: አንዳንዴ ፊቱ ላይ የሚንቀለቀለውን ቁጣ ሳይ፣ "በቃ ፓንጥሎ ጣለው ከርሰቶሰዬ ጉዱ ፈላ" እላለሁ:: ይሄ ሥዕል ከድሮ ጀምሮ ግድግዳችን ላይ ስለተሰጠፈ ነው መሰለኝ ከርሰቶስ ከአኛ ቤት ሌላ መሄጃ ያለው አይመስለኝም ነበር:: እናቴና ከርሰቶስ የአባቴን ባህሪ ችለው

ሶኖሩት ሌላ መሄጃ ስለሌላቸው ይመስለኝ ነበር::እኔ፣ ከርስቶስና እናቴ የአባቴን ባህሪ ችለን የተቀመጥነው ሌላ መሄጃ ስለሌለን ይመስለኝ ነበር...

"እንከፍትልህም...ይህቺ ሚስኪን (ወደናቴ እየጠቆመ) ለሰንቱ ሃብታም፣ ለሰንቱ ጀግና፣ ለስንቱ ባለ ሥልጣን የከረቸመችውን ልቧን ለኔ ከፈተች:: ምን ተጠቀመች ? ምንም !! እድሜ ልኳን ጡረታ የወጣ ወታደር ባሏ ሰክሮ ሲመጣ በር ከፋች ሆና ቀረች..." (ስለሌላ ባል እንጂ ስለራሱ የሚያወራ አይመስልም::) "እሷን ተዋት...እቺ አገር ራሷ...እቺ እጇን ወደአንተ ትዘረጋለች የተባለችው... ሃሃሃ ...እች ኢትዮጵያ ...ጓደኞቼን ዋጥ ስልቅጥ ያደረገችው አገር ራሷ...ለንጉሥ ልቧን ስትከፍት፣ ለወታደር ልቧን ስትከፍት፣ ለወንበዴ ልቧን ስትከፍት፣ ለሶሻሊዝም፣ ለምናምኒዝም ልቧን ስትከፍት - ይሄው መከፈት መዘጋት የሰለቸው በሯ ተገንጥሎ ከፍቷን ቀረች::እናስ ? ምናችን ጅል ነው የምንከፍትልህ ?...እንከፍትም !! እንከፍትም !! በከፈትን ቁጥር እየገባ የታጨቀብንን ጣጣ ባስወጣህልን ይልቅ ! ...ላንተም አይመችህ...ውስጣችን ነድዷል፣ ከስሏል - የተቃጠለ ቤት ውስጥ ለመኖር ይሄን ያህል ስታንኳኳ መኖር...ኤዲያ" እናቴ እንባዋ ጠብ ሲል ይታየኛል::

ልቤ ይታፈናል:: ልብ ድካም የሚባለው ይሄ ይሆን ? ቤታችን ይታፈናል:: በጣም ብዙ መላዕክት ቤታችን ውስጥ ታጭቀው፣ "እረ ጌታ ሆይ ይሄ ሰውዬ አበዛው፣ ፍቀድልንና ወደዛ ቦጫጭቀን ሲአል እንወርውረው..." እያሉ እየሱስን የሚያስፈቅዱ ይመስለኛል::

"እስቲ ተዉት...እሱ ያለፈውን መከራ ማን አለፈ ? ...የዚህን ሚስኪን ልጇን ቀንበር ማን ተሸከመ? እስከመጨረሻው አለምነዋለሁ...!" የሚላቸው ይመስለኛል በሩን ማንኳኳቱን ሳያቋርጥ፤ ከርስቶስ የኔ ልብ አዋቂ ! አባቴ እያነሰ ከርስቶስ እየገዘፈ ይሄድብኛል - አሁን ደግሞ ለአባቴ እሰጋለሁ::

ጎምለል ጎምለል..."እንከፍትም !! አናውቅም እንዴ...ወላ መስኮት ወላ በሩ በተዘጋ ቤት ሰተት ብለህ ገብተህ 'ሰላም ለአናንተ' ስትል? አሁን ምን ያዘህ?...ግባ...ይሄው በግድግዳው ግባ:: መቼም ዓይናችን እያየ አንከፍትልህም..." እያጉተመተመ ልብሱን ያወላልቃል:: መጀመሪያ ኮቱን - ገበሩ ተቀዳደ:: እያጣጠፈ ያጉተመትማል - "ወይ መክፈት..." ሱሪውን በሥርዓት አልጋው ላይ ዘርግቶ በእጁ እየተኮሰ ያጣጥፋል:: ቢሰክርም ባይሰክርም ልብሱን በመስመሩ ማጠፍና በሥርዓት ማስቀመጥ አይረሳም:: ሊተኛ ሲል ያየኛል:: ልክ የአልጋ ልብሱን ገለብ ሲያደርግ ኩርምት ብዬ እናቴ ስር...:: "አይዞህ አንበሳዬ...ምነው ከኔ ከምትፈጠር በቀረብህ... የማይረባ አባት ለአንድ ልጁ አንኳን የማይሆን - ወይ አባት - አላየንም አባት - እንደለማዳ ውሻ ሰምህን ተከትሎ ከሚጮህ ስሜ ሌላ ምን አወርስሃለሁ - ቤሳቤስቲን..." እየተናገረ አልጋ ልብሱ ውስጥ ገብቷል:: በብርድ ልብሱ የታፈነ እንቅልፍ የተጫጫነው ድምፁ ያጉተመትማል፣ '...ከንቱ...ለራሴ ከንቱ ሆኜ የሰው ሰው ከንቱ አድርጌያት ቀረሁ...ግራ ገብቶኝ ግራ...' ረዥም ዝምታ፣ የተኛ እስኪመስለን :: ድንገት፣ "አለሜ...እራት በልታችኋል..." ይላታል እናቴን::

"እም" ወይም "አልበላንም" አትልም:: ሁልጊዜ መልሷ ይገርመኛል፣

"ቆንጆ ወጥ ሰርቻለሁ ፤ ትንሽ ልስጥህ አሰቲ..." ትለዋለች:: ገና ቅድም ተነሰታ ጓዳው በር ላይ ደርሳለች፣

"አ...ይ..." ይላል ስልል ባለ ድምፅ:: አንዳንዴ "አይ..." ብሏትም ታቀርብለታለች፣ ተነስቶ ይበላል፣ አንዳንዴ "አይ..." ካለ ትመለሳለች:: በሁለቱ 'አይ'ዎች መሃል ያለውን ልዩነት ብዙ ጊዜ ለማጥናት ሞክርኩ:: በድምፅ ርዝመት፣ በቅላፄ ተመሳሳይ ናቸው:: እናቴ ግን በሁለቱ 'አይ'ዎች መሃል የአባቴን መሻት በቀላሉ ታውቃለች፣ አለመሻቱንም:: (አለመሻቱ እንኳን አይ ካለ አይ ነው :: ግን እንዴት አይ ያለ ሰው አይ ያለበትን ጉዳይ እንደፈለገው ማወቅ ቻለች ??????)

አማርኛ አስተማሪያችን "ልጆች ቋንቋን ከቤተሰብ ከማኅበረሰብ ይማራሉ" አሉኝ እንጂ ቋንቋን የምንማረው ከሕይወት፣ ለዛውም መተሳሰብ፣ መከባበረ እና መፈቃቀር ካለበት የሕይወት ልምዳችን ብቻ ነው:: አማርኛ አስተማሪያችን ራሳቸው፣ አባባ "አይ" ቢል እራት "አቅርቢልኝ" ማለት መሆኑን በጭራሽ አያውቁም:: ከማህበረሰቡ ይሄን አልተማሩማ !! ስሜትና ስዋሰው ለየቅል ናቸው !!

ጧት ከእንቅልፌ ስነቃ ታዲያ ብቻዬን ነኝ:: እናትና አባቴ ቤተ-ክርስቲያን ሄደዋል:: የክርስቶስ ሥዕል ግን አሁንም አለ:: ቆይ አባቴ ከሌለ ማን እንዲከፍትለት ነው የሚያንኳኳው ? በብርድ ልብሴ ተጠቅልዬ ሥዕሉን እያየሁ አስባለሁ፣ "አባታችሁን ታዘዙ፣ ቤተሰቦቻችሁ የማይወዱትን በመሥራት አታሳዝኗቸው" ይሉን የለ የሰንበት አስተማሪያችን ? ስለዚህ...

"አልከፍትም !!" እላለሁ ቀስ ብዬ...

እ ገ ዛ ላ ታ ለ ሁ . . . !! 5

ቆንጆ ማለት ለዓይን የሚማርከ፣ ለጆሮ የሚጥም፣ የሚያምር፣ የሚያስደስት፣ የሚያማልል፣ ሰው፣ እንስሳ፣ ሳር፣ ቅጠል፣ አየር፣ ውሃ፣ ቃል፣ ሁኔታ፣ ድርጊት ሌላም መዓት ትርጉም ይኖረዋል። አሻሚ ነው ቃሉ። 'ውብ' የሚለው ቃል ግን አያሻማም አያደናግርም፣ "ውብ" ማለት "እናቴ" ማለት ናት ! የእኔ እማማ ብቻ !!

አዎ እናቴ ውብ ናት !! በችግር የማይፈታ ውበት። ማንም በአድናቆት ቃል በእንቶፈንቶ ድለላ ውሉን እጁ አስገብቶ የማይተረትረው ነጭ ቱባ ናት እማማ ፤ ፈገግ ስትል ከጥርሶቿ ድል ማድረግ በአካባቢው ይነዛል። እንደ እናቴ ፈገግታ ልብ የሚሰነጥቅ ሳቅ አላየሁም፣ የእናቴ ፈገግታ ብርታቴ ነው። ሰውነቴ በፈገግታዋ ይታደሳል። የተፈጥሮ ፍልውሃ ነው ፈገግታዋ !!

ሕይወት ወገቧን አስራ ልታስለቅሳት ድንጋይ ስትፈነቅል እናቴ...እማምዬ...የኔ ፀሐይ...በአንዲት የአሸሙር ፈገግታ ትደቁሳታለች ፤ ሕይወት የጨለማ አረሟን በቤታችን ላይ ስትዘራ እናቴ በፈገግታዋ ትመነጋግለውና የደስታ እና የሐሴት አዝመራ ቤታችን ይዘናፈላል።እዛ ማሳ ውስጥ እኔ አቦርቃለሁ።አውቆም ይሁን ሳያውቅ አባቴ ቤታችንን የምድር ዋልታ ላይ በበረዶ ገነባው፤ እናቴ በፈገግታ ገመድ ጎትታ መሃል አዲስ አበባ፣ አራት ኪሎ፣ ፀሐይ የሞላበት አመጣችው ቤቱን ከነግቢው ከነዛፉ !! እንደዛ ነው የሚሰማኝ።

አባቴ በውትድርና ኤርትራ ሄደ። "እነከሌ አገር ሊገነጥሉ፣ መሬት ሊሸርፉ ነውና ሄደህ ልክ አግባቸው!" በሚል ትዕዛዝ ከእኔ ከአንድ ልጁና ከሚወዳት ሚስቱ ተነጥሎ ሄደ ። "...እቤት ቁመና ! አቤት የትጥቅ ማማገር !" እያለ ጎረቤቱ ሸኘው። አምሮ ሊገድል፣ አምሮ ሊሞት አባቴ። ሕፃን ነበርኩ፤ ብዥ ያለ ነው ትዝታዬ። አባቴ ሄደ፤ (ዘመተ ይሉታል)። ሰልከ የለም፣ ደብዳቤ የለም፣ ሄደና ጠፉ።

እናቴ ታዲያ በፍፁም ንፅህና ለድስት ዓመት ጠበቀችው። ያውም በደጃችን፣ በእናቴ ውበት

መቶ ጆኔራል እየሸለለ፣ ሺ ካድሬ እየቋመጠ፣ ሚሊዬን አብዮት ጠባቂ ምራቁን እየዋጠ !! "ንፅህናዋን በምን አወቅከ ?" ስድስት ዓመት ሙሉ ማታ ማታ አንዲት ቀን ሳታቋርጥ ፎቶው ፊት ተንበርክካ ምን እያለች ትፀልይ እንደነበር እናንተ ታውቃላችሁ ? የአባቴን ፎቶ አቧራ ዝር እንዳይልበት በቀን ስንት ጊዜ ትወለውለው እንደነበርስ...? ከቤታችን ዕቃዎች ውድ የተባለው መደርደሪያ ላይ ምን ይቀመጥ እንደነበርስ ? የአባቴ ፎቶ !! በዛ ናፍቆት በረበበበት፣ ምስኪን እናትና ልጅ ምዕመን በሆኑበት፣ የብቸኝነት ቤተ መቅደስ ውስጥ የአባቴ ፎቶ ፅላት ነበር::

አባቴ ፎቶ ጎን ተሳስቼ ደብተሬን ባስቀምጥ ሳታስደነግጠኝ ቀሰ ብላ ታነሳዋለች :: ቤት ለማዘጋጀት እንዳይመስላችሁ፣ አባቴ ፎቶ አጠገብ ምንም እንዳይቀመጥ እንጂ !! እማማ የቃል ኪዳን ቀለበቷን ሽጣ ምን ገዛች...? ለኔ ቆንጆ ጫማና ልብስ ፣ ምድረ የትምህርት ቤት ማቲ የቀናበት የደብተር መያዣ ቦርሳ ፣ ለአባቴ ፎቶ ወርቃማ የብረት ከፈፍ ያለው ባለመስታዋት የፎቶ ማስቀመጫ፣ በተረፈችው የቃል ኪዳን ቀለቧን የምትመስል 'አርቴፊሻል' ቀለበት :: በእንቁ ልብና በአርቴፊሻል ቀለበት ቃል ኪዳኗን አጠረች፣ከእኔ በስተቀር ይሄንን ማንም አያውቅም:: ለራሷስ ምን ገዛች?...ምንም !! እች ናት እናቴ!!

ስድስት ዓመት አባቴን ጠበቀችው::ይሄ ሊመጣ ይችላል ተብሎ እዛም እዚህም እየተባለ የሚጠበቀው ዓይነት ጥበቃ ሳይሆን 'መቼ ሄደና' ብሎ ከችች የሚሉት አይነት የመንፈስ አብሮነት፣ በሌሉበት ማከበር !! ...ይሄ የመጀመሪያው ዓመት ላይ "ሄደብኝ የኔ ጌታ የልቤ ቁራሽ የደሜ ጭላፊ..." እያሉ ጎረቤት እንዲያባብል ድራማ መስራት፣ ዓመት በጨመረ ቁጥር 'እሁን ተፅናናች ሰው መቅረብ ጀመረች' የሚባለው አይነት መጠበቅ ሳይሆን፣ ትላንትም ዛሬም ዓመታት ጉልበቱን በማይሰልቡት ጥልቅ መሻት ጠበቀችው:: ይህች ናት እናቴ!!

ስለ ኤርትራ በተወራ ቁጥር ኪሎ ሲጋ ከአካሏ እየተገነጠለ ጠበቀች :: "ከኤርትራ የመጣ ሰው በኮተቤ አለፈ" ቢሏት ነጠላዋን አንጠልጥላ ኮተቤ ትገኛለች::" አንዲት ኤርትራዊት ተፈናቃይ አቃቂ ኪዬስክ ከፈተች" ቢባል ከአራት ኪሎ እየተመላለሰች የስሙኒ ሻይ ቅጠል ለመግዛት ደንበኛ የምትሆን ሴት ካለች እናቴ ብቻ ነበረች:: እች ናት እማማ!!

እርጋታዋ የእኔ እማማ በ"እልፍ ሲሉ አልፍ ይገኛል" ተረት አልፍኛቸው ውስጥ ተላላፊ እንደሚያበዙ ሴቶች አይደለችም ፤ ማንም የቃል ኪዳን መስመሯን አያልፍም፣ አገር ያውቃል፣ ቤታችን ቤተ መቅደስ ነው:: የፍቅር ፅላት በቅዱስ ቅዱሳን እማማ ልብ ውስጥ አለ:: እርጋታዋ ታማኝነቷን ይነግረናል:: ዓይኗ ከአባቴ ፎቶ ላይ ከተነቀለ ቀጥሎ ማረፊያው እኔ ላይ ነው:: ጆሮዋ ወደ ውጭ አይቀሰርም:: የኔን አርቲ ቡርቲ ወሬ እንደወንጌል በጥሞና መስማት የነፍሷ እርካታ ነው:: አባባ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እኔ ዮሐንስ ራዕይዋ...ታነበኛለች፣ ሰባት ቀንድ፣ አስራ ሰድስት ምላስ፣ ምንም ጆሮ የሌላቸው ልዩ ፍጥረቶች መሐል እናቴ ጆሮ ብቻ ሆና ትሰማኛለች....!!

ጥቁር ፀጉሯ ሲዘናፈል፣ እንደማር የለሰለሰ ቆዳዋ አላፊ አግዳሚ ሲጠራ፣ ረጋ ባለ እርምጃ እንደ ደመና ሰትንሳፈፍ፣ "ፈዛዛ ውበቷን አቀለጠችው" ይሏታል:: "ንታታ...እንደ ኤሊ ስትንቀሪቀፍ

አድሜዋን ፈጀች" ይሏታል። በሌጣ ልባቸው ሮጠው ምናምንቴ ሰለቃረሙ የፈጠኑ የመሰላቸው የመንደራችን ከንቱ ሐሜተኞች። የፍቅር መሰቀል ተሸከማ ዳገት የምትወጣ እናቴን ኤሊ ይሏታል፤ እፍ አውጥተው ኤሊ ይሏታል። የድንጋይ ልባሷ አንደነሱ ቀሚስ የትም ለማንም አለመገለቡ እያበሳጫቸው፣ ተኳኩለው የሚጠብቋቸው ወታደር ውሽሞቻቸው ያልተኳኳለች እናቴን እያዩ "ማናት ይህች ቆንጆ ?" ሲሏቸው እየበሸቁ...።

እማምዬ ሲድስት ዓመት ጠበቀችው አባቴን። "ይኼኔ ባሷ ከአስመራ ቆንጆዎች ጋር አሸሼ ገዳሜ ሂዶ አዲስ አበባ የገቡ ይመስል። "ለታመነልህ ታመን" የቆሸሸ ዲስኩራቸው "በአልታመኑልንም" ሰበብ ባሎቻቸውን እንዲከዱ፣ ፍቅረኞቻቸውን እንዲቀጥፉ መንገድ እየጠረገላቸው፣ ለውሰጣቸው ግልሙትና ጥቅስ እየሆነላቸው፣ "የአስመራን ግልሙትና በአዲስ አበባ ግልሙትና መበቀል ፅድቅ ነው" የተባለ ይመስል እማምዬን "ባልሽ ወንድ ነው አትመኝው" ይሏታል።

አንድ ማለዳ በራችን ተንኳኳ። እማማ ከፈተች። ጎረቤቶቻችን አንድ የተጎሳቆለ ወታደር አስከትለው መጡና "ባልሽ ሞቷል" አሏት ። "በዚህ ወርዶበዚያ ሂዶ፣ መድፍ ተኩሶ፣ ታንክ ማርኮ፣ በጀግንነት ሞተ !" አሏት። ዝም ብላ ሰማቻቸው። "ሰው ቀጥ ብሎ የማያይ ጨዋ፣ ለትዳሩ ታማኝ፣ ወታደሩ ሁሉ አዛና እዚህ ሲል ባልሽ ግን የአንቺን ፎቶ ከደረት ኪሱ ሳይለይ በየበረሃው ለአገሩ ሲፋለም ኖሮ ሞተ" አሏት። ዝም ብላ ሰማቻቸው።

አባቴ ሲሞት "ከጎኑ ነበርኩ" ያለው ጎስቋላ ወታደር ከአባቴ ሬሳ ኪስ ውስጥ አገኘሁት ያለውን ፎቶ ሰጣት። እናቴና አባቴ ጎን ለጎን ሆነው የተነሱት ጉርድ ፎቶ ግራፍ ነበር። ልከ መሀላቸው ላይ በጥይት የተቦደሰ ፎቶ እማማ እጅ ላይ እንዳለ በትከሻዋ ተንጠራርቼ ፎቶውን አየሁት። እን...ዴ ! በመድፍ ጥይት ነው እንዴ ፎቶውን የበሱት? እና እንዴት እንዲት ጥይት በቤተሰብ መካከል ይሄን የሚያህል በደም ነጠብጣብም የተከበበ ሽንቁር ትፈጥራለች? ገረመኝ።

"ባለቤትሽ ደረቱ ኪስ ነበር ፎቶውን የያዘው። ከጠላት የተተኮሰ ጥይት ፎቶ ባስቀመጠበት ኪሱ በኩል ደረቱን መታችው" አለ ድምፁ የሰለለው ወታደር። እማማ ፎቶውን በትኩረት አየችው፤ ረዥዥዥም ሰዓት ዝም ብላ አየችው፤ አላለቀሰችም። ፊቷም ላይ ምንም ለውጥ አልታየም። ከፎቶው ይልቅ ሽንቁሩን የምታይ መሰለኝ። አንዴ በረዥሙ ተነፈሰችና ፊት ለፊት መደርደሪያው ላይ የተቀመጠውን የአባባን ፎቶ ተመለከተች ።

አሁን ውሻ ሞት በከፈተው ቀዳዳ ጅብ ወንዶች ዘው ሊሉ አሰፈሰፉ።"አይዞሽ ሰው መቼስ ዘላለም አይኖር ምናምን..." ብለው በማስተዛዘን ሰም ወደ ቤተ መቅደሳችን ዘው ሊሉ። እናቴ "ማንም ለቅሶ እንዳይደርሰኝ" አለች። መንደሩ "ለየላት አበደች..." ብሎ አወራ።

እማማ የእኔ መልአክ እኔንም ግራ አጋባችኝ ። አባቴ ሞቷል ወይስ አልሞተም ? ቢሞትም እማማ "አልሞተም" ካለች አልሞተም።

ቀኑ የአባባ መርዶ የመጣበት ሰኞ ነበር:: ረጋ ብላ ቁርስ ሰራችልኝ፤ የሚጣፍጥ ጨጨብሳ፤ ስኳሩ በዛ ካለ ሻይ ጋር :: እሷ አልበላችም::

በእጇ የያዘቻትን የሻይ ማንኪያ እየነቀነቀች በጥልቀት ታየኛለች:: ዓይን ዓይኔን እያየችኝ ጥርግ አድርጌ በላሁ::

ጉንጩን ስማኝ ወደ ትምህርት ቤት ሸኘችኝ:: ጉንጩን ነው ያልኩት ? በልምድ ብዙ ወላጆች "የልጆቻቸውን ጉንጭ ይስማሉ" እንላለን እንጂ እንደ እኔ እናት ከሆነ ግን ወላጆች የልጆቻቸውን ነፍስ ነው የሚስሙት :: አዎ እማምዬ ነፍሴን ስማ ነው የምትሸኘኝ!! ብዙ ከሄድኩ በኋላ ወደ ቤታችን ዞር ስል አረንጓዴ ቢጃማዋን ለብሳ የበሩን ጣውላ ተደግፋ ቆማ እያየችኝ ነበር፤ የደከማት ትመስላለች:: እማማን እንዲህ ከሩቁ ሳያት "ተመለስ ተመለስ... እቅፍ አድርጋት... ከጎኗ አትለይ..." ይለኛል:: ሁለት ሰው እሆናለሁ፤ እግሬ ወደፊት እየሄደ ልቤ ወደ እማማ ወደኋላ ይሮጣል ::

ዓይኖቿ ብርታቶቼ ናቸው:: ከኋላዬ ስትቆም አልፍ አለላፍ መላዕከት ከነሰይፋቸው፤ ከነለላት ሰረገላቸው እኔን ሊጠብቁ የቆሙ ይመስለኛል:: በምድር ላይ ያለ የጦር ሰራዊት ከነመሳሪያው ያጀበኝ... እናትዬ ከኋላዬ ስትቆም ሰማይ ይቀርበኛል፤ ደመና ባጭር የተቆረጠ ፀጉሬን ሲዳስሰኝ ይሰማኛል፤ የእግዜር እግር ስር የቆምኩ ይመስለኛል:: የምረግጠው ምድር በእግሮቼ ብርታት የሚናጥ፣ ድንጋዮቹ የሚፈነቃቀሉ ይመስለኛል:: የእማማን የዕይታ ጥሩር ከለበስኩ ማንንም አልፈራም ::ተራሮች ምንድናቸው? በእግሬ እንደማንከባልለው የጨርቅ ኳስ ናቸዋ !! ጨጨብሳ ባልበላም በጠረኗ ሺ ዓመት እኖራለሁ፤ በፈገግታዋ ዘላለም!!

እማምዬ የፍቅር ጥግ፣ የእናትነት አልፋና አሜጋዬ:: እናንተ "ሴት እናት ናት! ሴት እህት ናት!" የምትሉ 'በደፈናው ኃይማኖተኛ ሁሉ መነኩሴ ነው' እያላችሁ ነውና ይቅር ይበላችሁ፤ ሴትነት እናትነት አይደለም:: "ሴት ከውስጧ የወጣ ገዳም ውስጥ ስትመንን እናት ትሆናለች" ሴት..."ልጅ" የሚባል መሰቀል ተሸክማ የሕይወትን ቀራንዬ ስትወጣ 'እናት' ትባላለች ፤ ሴት ልጅ የራሷን ዘመን ይቅርብኝ ብላ የልጆቿ የዘመን መስቀል ላይ በፍቅር ስትቸነከር ወደ እናትነት ከፍታ ታርጋለች::

እማማን ዞሬ አየኋት:: የምትወደው ባሏን መርዶ ቅድም የሰማች ሴት በር ላይ ቆማለች፤ አይገርምም ? እናት የላትም፤...አባት የላትም፤...ዘመድ የላትም፤ እኔ ብቻ ነኝ ያለኋት:: የማላውቀው ሰሜት ወረረኝ:: በአንድ ጊዜ ጀግናም ፈሪም ሆንኩ - እኩል! "ማንም የላት" እና "እኔ አለሁላት" የሚሉ ኃሳቦች ተጋጩብኝ::

ትምህርት ቤቴ እስከምደርስ እንባዬ ጉንጮቼ ላይ እየፈሰሰ እንዲህ እያልኩ ለብቻዬ አነበንብ ነበር...

"ሳድግ ለእማማ አዲስ አበባ ሱቆች ውስጥ ያሉትን ቀሚሶች ሁሉ እገዛላታለሁ:: ፒያሳ ወርቅ

ቤቶች ውስጥ የተደረደሩትን ያልተደረደሩትንም የወርቅ ቀለበቶች፣ ሃብሎች፣ ጉትቻዎች...ሁሉንም ለእማምዬ እገዛላታለሁ። ለእናትዬ ትልቅ ቤት እገዛላታለሁ። ትልቅ ግቢ እገዛላታለሁ...።

ባለ ሚሊዮን ፎቅ፣ ሜቆ ጨረቃን የሚነካ ሕንፃ እገዛላታለሁ። በመጨረሻው መስኮት ብቅ ብላ የአባቴን ፎቶ ከነ ወርቃማ 'ፍሬሙ' ጨረቃ ላይ ታስቀምጠዋለች። ማንም እንዳይደርስበት !! ላድግ ለእማምዬ ሰፈራችንን አራት ኪሎን እንዳለ እገዛላታለሁ። ከነሐውልቱ፣ ከነዩኒቨርስቲው፣ ከነቤተመንግስቱ...!!

ላድግ ለእማማ፣ ለእኔ ደግ፣ ለእኔ ሩህሩህ አዲስ አበባን እገዛላታለሁ። ሳድግ...ለኔ ትሁት፣ ለኔ ቃልኪዳን አከባሪ ኢትዮጵያን እገዛላታለሁ !! ከነሕዝቡ፣ ከነኃይማኖቱ፣ ከነቤተ ክርስቲያኑ፣ ከነ መስጊዱ እገዛላታለሁ...።

ላድግ ኢትዮጵያን...ከነተራራው፣ ከነራስ ዳሽኑ፣ ከነሸለቆው፣ ከነጫካው፣ ከነዋልያና ጭላዳው፣ ከነአዋሹ፣ ከነጫሞ እና አብያታው፣ ከነሶፍዑመሩ፣ ከነላሊበላው፣ ከነፋሲለደሱ፣ ከነጣናው፣ ከነአባዩ፣ ከነአከሱሙ... እ ገ ዛ ላ ታ ለ ሁ!!

እዎ እገዛላታለሁ !! "አልፈልግም የኔ እንቦቀቅላ ይሄ ሁሉ ምን ያደርግልኛል ?" ብትልም አልሰማትም፣ እገዛላታለሁ...!!!

ላድግ...ትልቁ የልቧ ስባሪ፣ የነፍሷ ቀንዲል፣ የፍቅሯ በር፣ የእኔም አለኝታ እንደቀልድ የወደቀባትን ምድር...

ኤ

C

ት

ራ

ን

እገዛላታለሁ ! ለ እ ማ ም ዬ !!

6 የፍርምባ ጦርነት

በንቃት ድንበር እየጠበቅኩ ነው ፤ ጠላት ፊት ለፊቴ አፍጥጧል:: በማንኛውም ሰዓት ወደ እኔ ሊንደረደር ይችላል:: በመጠኑ ያደፈች ጅንሰ ቁምጣዬን ከጉርድ ቀይ ካኒቴራ ጋር ለብሼ ነጠላ ጫማዬ ከእግሬ ላይ ትበር ይመስል በእግሮቼ ጣቶች በመንከስ ከቤታችን በር ላይ ነው ያለሁት፤ በእጄ ከአቅሜ በላይ የሆነ ብትር ይዣለሁ...የአያቴ የተሰበረ መቋሚያ ነው...መቋሚያውም የተሰበረው እዚሁ በዓይነ ቁራኛ የምጠብቀው ጠላት ጀርባ ላይ ነበር :: አባቶቻችን ያወረሱንን ጠላት አያቶቻችን ባወረሱን ሰባራ መቋሚያ እየተከላከልሁ ነው::

ነገ በዓል ነው:: ቤታችን ትንሽ ጠቦት ታርዶ ቤቱ ሲጋ ሲጋ ይሸታል:: እናቴ ቤቱን እና ሲጋውን አንድጠብቅ ጥብቅ ትዕዛዝ ሰጥታኝ ገበያ ሄዳለች:: በዋናነት የተሰጠኝ ተልዕኮ፣

1. ዶሮዎች የተሰጣውን የሽሮ ክክ እንዳይበትኑ

2. ሌባ ወደቤታችን እንዳይገባ

3ኛው እና ዋናው..."ገንባው እዚህች ግድም ድርሽ እንዳይል..." ነው:: (እዚህች ግድም ድርሽ አንዳይል ? ማን ? ገንባው !!)

ዶሮዎች ሰጡ አካባቢ መለቃቀም ይችላሉ:: ሰጡን መብላትም ሆነ መበተን ግን የለባቸውም፤... ሌባ በአጥራችን ጥግ መሄድ ይችላል፣ "ደህና አደራችሁ" ብሎም ማለፍ አይከለከልም:: ሰላምታ የአግዜር ነው ትላለች እናቴ...በዕርግጥ ሲደጋግሙባት 'ሦስት ጊዜ እንዴት አደራችሁ አንዱ ለነገር ነው' ትልና የአግዜር ሰላምታ ሲደጋገም ባለቤትነቱ የሰይጣን ሊሆን እንደሚችል በተዘዋዋሪ ትናገራለች:: እና ሌባው አሰካልደጋገመ ድረስ ሰላም ብሎ ማለፍ ይችላል:: ...ገንባው ግን... እዚህች ግድም ድርሽ ማለት የለበትም :: ወላ ሰላም ማለት ሁሉ አይችልም:: ሰላምታውን ደገመም አልደገመም ፤ ቢቃ የበላይ ትዕዛዝ ነው !!

ግንባው በመንደራችን የሚኖር ባለቤት የሌለው ትልቅ ድመት ነው ። የበግ ግልገል የሚያክል ዥጉርጉር ድመት ! እኔ ከተቀመጥኩበት አንድ አስራ አምስት ሜትር ራቅ ብሎ ከኋላው ሸብረክ በማለት ሁለት የፊት እግሮቹን ቀጥ አድርጎና ደረቱን ነፍቶ ጉርድ ፎቶ ሊነሳ ፎቶ አንሺ ፊት የተቀመጠ ጎረምሳ መስሎ...ቁሟል ።

ተራ ድመት እንዳይመስላችሁ...በሰፈራችን ውስጥ ያልገለበጠው ድስት፣ ያልከፈተው መሶብ፣ የመንጠቅ ሙከራ ያላደረገበት የስጋ ዘር የለም። መንደራችን ውስጥ ዶሮም ይሁን በግ ሲታረድ ግንባውን ጠባቂ ቃፊር ማቆም ቸል የማይባል ጉዳይ ነው። "ግንባው ቢመቸው ቆሞ ከሚሄድ በግ ላንባ ይመነትፋል" ይሉታል...ሞኝ ሰፈርተኞች...!! ታሪክ የሚተነፍሱበትን፣ የተዓማኝነት ላንባቸውን በቁማቸው እንደመነተፉቸው ማን በነገራቸው።

ግንባው ግዙፍ ቢሆንም የተጎሳቆለና በእድሜ የገፋ ድመት ነው። ትንሽ ያነከሳል። በዛ ላይ ዓንድ አይን የለውም። ጅራቱም ቆራጣ ነው። ሲጮኽ ድምፁ ያስፈራራል። እማማ ብርዘገን ለፋሲካ የገነጣጠሏትን ዶሮ ላጥ አድርጎባቸው ሲሮጥ ጉሮሮውን በቢለዋ ወግተውት ነው ድምፁ ተበላሽቶ የቀረው። የዛሬን አያድርገውና 'ሚያውውውው' ሲል የአይጥ ሰራዊትን የሚያርድ፣ ሴት ድመቶችን የሚያማልል ድምፀ መረዋ ድመት ነበር ።

ድሮ የጋሽ ታምሩ ድመት ነበረ። አንድ ቀን ታዲያ ፍርምባ የሚባል ነገር ሰረቀ ብለው አባ ታምሩ በአንካሴ ወጉት። ከዛ በኋላ እሳቸው ቤት መኖር አቆመ። ጨካኝ ናቸው። ፍርምባ ለምታክል ሲጋ ብለው...ተወልዶ ካደገበት ቤት አባረሩት ፣ ያውም በአንካሴ ወግተው። እሳቸው ግን፣ "ድመቱን ለፍርምባ ብዬ አልወጋሁትም" ብለው ዋሹ። ትልቅ ሰው ይዋሻል ? ደግሞ እኮ ያኔ የሆነውን ሁሉ በዓይኔ በብረቱ አይቻለሁ...ማሪያምን አይቻለሁ !

ድመቱ ፍርምባውን በአፉ አንጠልጥሎ መሬት ለመሬት እየጎተተ እኛ ቤት ፊት ለፊት ወዳለው የውሃ መውረጃ ቱቦ ሲሮጥ አባ ታምሩ ልክ እንደኦሎምፒክ ተወዳዳሪ ግራ እጃቸውን ወደፊት ቀስረውና ጦር የጨበጠ ቀኝ እጃቸውን አስከቻሉት ድረስ ወደኋላ ለጥጠው በሰፋፊ ርምጃዎች ተንደረደሩ ...1...2...3...ጦሩን ኧ....ው ....አደረጉት። ድመቱ ሲሮጥ ጦሩ ሲከተለው፣ ጦሩ ህይወት ያለው ይመስል ነበር። ልክ ቱቦው ጫፍ ላይ ሲደርስ የድመቱ የኋላ እግር ታፋ ላይ ጦሩ ተቀበቀበ...አቤ...ት ገንባው እንዴት አሰቃቂ ጩኸት እንደጮኸ። ...እንዳንቡላንስ ነው የጮኸው...ሚያያያያያያያያያያያ...! ሲጮህ በአፉ የያዘው ፍርምባ ወደቀ። አንድ ነጭ ያልቆሰለም ያልተወጋም ድመት ቀልቦት ወደቱቦው ውስጥ ጥልቅ አለ...!!

ጎረቤቱ ሁሉ፣ "አቤት አጨካከን እናትዬ የአግዜር ፍጡር ነው...ምን በደለ ?" እያለ ሲያጉረመርም አባ ታምሩ ታሪክ ፈጠሩ። "የልጅ ልጄን ዓይኗን ሊያወጣት ነበር እኮ፣ ግዴላችሁም ይሄ ድመት አውሬ ሆኗል..." በማለት የፍርምባውን ፀብ 'ትውልድ ለማዳን' የተደረገ ጦርነት አስመሰሉት።

የሚገርመኝ ታዲያ የመንደሩ ሰው ነው። በወሬ ወሬ " ይሄ ድመት ምን ሆኖ ነው የሚያነከሰው?"

ሲባል ፤ ..."ይሄ 'አውሬ' ነው...የጋሸ ታምሩን የልጅ ልጅ ዓይኗን ሊያወጣት ሲል አያታ የደፈሙ በአንካሴ ወጉት" ይላል :: ሞራሽ አይጦቻቸውን አያሳያደ አንዳልፈጀላቸው 'አውሬ' የሚሬ ስም ሰጡት ለዚህ ሚስኪን ገንባው !!

ትልልቆቹ ሰዎች ሁሉ፣ ፀጉራቸው የሸበተው አስተማሪው ሰውዬ (ትልቁ ግቢ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሳይቀሩ ይሄን የፈጠራ ታሪክ ያወራሉ::ታዲያ ስለአገር ታሪክ እናውራ ሲሉ አላምናቸውም ትላንት አፍንጫቸው ስር ያውም በጠራራ ፀሐይ የተፈፀመ የድመት ታሪክ ወጊው ቢፈጠርስ መንገድ የተረኩ ሁሉ ስለአገሬ ታሪክ እናውራህ ሲሉኝ እንዴት ልመናቸው ?በመንደራችው የድመት ታሪክ ያልታመኑ ሁሉ ስለአገራቸው አንበሶች ጀብዱ ሲደሰኩሩ እንዴት ልቢ አሺ ብሎ ይቀበል ?ታሪክ ማውራት ታሪክ ከመስራት እኩል ጀግንነት እንደሚጠይቅ የገባኝ ያኔ ነው ::

ከዛን ቀን ጀምሮ ጦርነቶች ሁሉ የእደባባይ ምክንያታቸው ምንም ይሁን ምን ከኋላቸው ፍርሃ የሚባል ስጋ ያለ ይመስለኛል:: ገንባው አውሬ አይደለም:: ገንባው የከለከሉትን የዕለት እንጀራ ነጥቆ "ተመስገን" የሚል ሚስኪን ድመት ነው:: የዕለት እንጀራውን ሲነጥቃቸው የዘላለም ስሙን ነጠቁት:: "ያኔ ባንካሴ ባንወጋው ኖሮ ትውልዱ ሁሉ አውር በሆነ_" እያሉ ከደመቁ ጥፍር በባሰ የውሸት ጥፍራም ታሪክ ሞፍን ትውልድ ይፈጥራሉ::

በታሳብ ካቀረቀርኩበት ቀና ስል ገንባው የለም:: "በሰማም የት ሄደ ሮ ሰባራ መቋሚያዬን ወድሬ ወደ ጓዳ ሮጥኩ:: መስኮቱ ገርበብ ብሏል:: የጠቦቱ ታፋም ተሰቅሎ በነበረበት ቦታ የለም:: ...ወይኔ ጉዴ ዛሬ እናቴ ገደለችኝ ቢቃ::

ሮጬ ወደ ውጭ ስወጣ ገንባው ታፋውን እየጎተተ ወደ ቱቦው ጥልቅ ሲል አየሁት::

"ወይኔ አንካሴ ኖሮኝ በነበር...ይሄን አውሬ አልለቀውም ነበር" አልኩ ለራሴ...::

ተ ሸ ከ መ ና ታ ል !! 7

እናቴ ሁልጊዜ እንድናጠና ስትመክረን እንዲህ ትላለች፡-

"እናንተ ልጆች አጥኑ፣ ተማሩ እባካችሁ ! ...እኔ ባለመማሬ ነው ጉዴን ተሸከሜ የዋልኩት፤" ማንበብም መፃፍም ስለማትችል ንግግሯ በቁጭት ነበር። አንድ ቀን ታዲያ ይሄ ተሸክማ የዋለችው ጉድ ምን እንደሆነ ለማወቅ ጓጉቼ ጠየቅኳት፣

"ማሚ የምን ጉድ ነው ተሸከመሽ የዋልሽው ?"

አወራችኝ...

**** **** ****

በደርግ ጊዜ መስከረም ሁለት ቀን ሕዝቡ በግድም ሆነ በውድ የድጋፍ ሰልፍ ይወጣ ነበር። መስከረም ሁለት ደርግ ንጉሱን ገልብጦ ሥልጣን የያዘበት ቀን ነው። በአጭር አገላለፅ መስከረም ሁለት የደርግ ግንቦት ሃያ ነበር። ታዲያ እናቴ በወቅቱ የነበረውን የግዳጅ ውትድርና በመፍራት የመጀመሪያ ልጇን ወታደር ቤት እንዳይወስዱባት ከከተማው ወጣ ያለ አከሰታችን ቤት ደብቃ፣ ሁለተኛ ልጇንም ገጠር አናቷ ጋር ልካ፣ ሦስተኛውን ልጇን አልጋ ስር አስቀምጣ፣ አባቴንም "ታምሜያለሁ በል!" ብላው፣ እሷ ግን ነጭ ልብስ ለብሳ ሰልፍ ወጣች። ግዴታ ነዋ!

ቀበሌ ስትደርስ ሴት ወንዱ ያለውን ለብሶ ተሸቀርቅሮ፣ ቀበሌውም በተለያዩ መፈከሮችና በባለ ቀለም መብራቶች አጊጦ ጠበቃት። የቀበሌው የኢ.ሴ.ማ ኃላፊ የነበረች ሴት በባለእጀታ የጣውላ ሰሌዳ ላይ ተፅፈው የተዘጋጁ በመቶ የሚቆጠሩ መፈከሮችን ለእናቴ እያሳየቻት፣"ምረጭና አንዱን ያዥ" አለቻት።

እናቴ ቀለል ያለችና በደማቅ ቀይ ቀለም የተሸሞነሞነች መፈከር መርጣ እነሳችና ወደ ሰልፉ ተቀላቀለች። ከለበሰችው የሚያምር የአበሻ ቀሚስ እና ከራሷም ቁንጅና ጋር ተዳምሮ የኦሎምፒክ መክፈቻ ላይ 'ኢትዮጲያ' የሚል ምልክት ይዛ ሰልፉን የምትመራ ቆንጆ የአበሻ ሴት ትመስል ነበር።

በዕለቱ መስቀል አደባባይ እናቴን በርካታ ሰዎች በግርምትና በአድናቆት ሲመለከቷት ዋሉ።

ታዲያ በዚያ ሰሞን ማታ በቴሌቪዥን ደጋግመው እናቴን ከነመፈክሯ ያሳይዋት ጀመረ። ምን ይሄ ብቻ፣ ዓመቱን ሙሉ ፎከረውም እናቴን ማሳየት፣ ኢህአፓ ብለውም እናቴን፣ መኢሶን ብለውም እናቴን፣ ቀይ ሽብር ብለውም እናቴን፣ ጓድ ሊቀመንበር ተናግረው ሲያበቁም እናቴን ማሳየት።

ጭራሽ ብሔራዊ ውትድርና ተብሎ ምድረ ወጣት ሲጓፈፍ ፣ የብሔራዊ ውትድርና አገር አቀፍ ዓርማ የእናቴ ፎቶ ሆኖ በየቦታው ተለጠፈ። በነጭ ልብስ ተውባ መፈክር ይዛ የቆመች እናቴ የብሔራዊ ውትድርና አገር አቀፍ አርማ ሆነች። አንድ ጋዜጣ ላይ የእናቴ ፎቶ ስር እንዲህ የሚል ጽሑፍ ሰፍሮ ነበር፤

"አብዮታዊት ሶሻሊስት ኢትዮጵያ ነጭ ቀሚስ ለብሳ"

እናቴ ታዲያ መጀመሪያ አካባቢ በቴሌቪዥን በታየች ቁጥር በቁንጅናዋ የተመረጠች መስሏት አባቴ ላይ በኩራት ትነሰነስበት ነበር፣

"ጓዳ ለጓዳ ስውል ቀላል ሰው አድርገሽኝ፣ እግሬ ወጣ ካለ አገር ነው የሚሰግድልኝ!" ትለዋለች ኮራ ብላ። አባቴ አፉን ሸርመም አድርጎ፣ "እዩኝ እዩኝ ማለት ደብቁኝ ደብቁኝ ያመጣል !" ይላታል።

"የቅናት ወሬ ነው ይሄ" ትልና ሆነ ብላ ለማበሳጨት በቴሌቪዥን ደጋግሞ የሚታየውን ምስሏን አተኩራ እየተመለከተች፣

"እንዲት ፍሬ ልጅ እኮ ነኝ" ትላለች። አባባ ታዲያ "ሃሃሃሃሃሃሃሃ..." ብሎ በረዥሙ ይስቅና "ሰልፍ ላይማ መንግስትም አንድ ፍሬ ነኝ ነው የሚለው" ይላል።

"ኤዲያ እንግዲህ ቦለቲካህን ልትጀምር ነው..." ብላ ወደ ጓዳዋ ትገባለች።

ይሁንና እናቴ እየቆየች በቴሌቪዥን መታየቱ እና ስለ እርሷ መወራቱም ሲደጋገምባት ፈራች።

በተለይም ጓድ መንግስቱ ኃይለማሪያም መስቀል አደባባይ በትልቁ የተሰቀለውን የእናቴን ፎቶ ለተሰበሰበው ሕዝብ እያሳዩ በደም ፍላት፣

"እንደነዚህ ዓይነት ጀግና እናቶች ያሉባት አገር በማንም ወመኔ ከሃዲ ስትወረር እንዴት ወንዶቿ አልጋ ስር ይደበቃሉ? እነዚህን ቦቅቧቃ ወንዳገረዶች ቂጣቸውን በሳንጃ..." እያሉ ንግግር ካደረጉ በኋላ እናቴ ሲጋቷ ከፍ አለ።

ሲጋቷን ለማስታገስ፣ "ኧረ ይሄ መፈክር ምንድን ነው የሚለው?" ብላ የተማረ ሰው ጠየቀች። መስከረም ሁለት ሰልፍ ላይ ይዛ ስለወጣችው መፈክር ተሸክማው ስለነበረው ጽሑፍ ሚያዚያ ላይ "ምንድን ነው?" ብላ ጠየቀች።

ሲነበብላት አመዷ ቡን አለ ፤ ብርክ ያዛት።

መፈክሩ እንዲህ ነበር የሚለው...

"የአብዮት ጠላቶችን ለማደባየት እኛ እናቶች ልጆቻችንን፣ ካስፈለገም ባሎቻችንን በደስታ እናዘምታለን!!"

ደወል !! 8

የእካባቢ ሳይንስ መምህርታችን እትዬ ሐረጓ ከሰራ ተባረረች። ምናለበት ሂሳብ አስተማሪያችን ጋሽ ቢጋለ ቢባረር፤ ምናለበት እንግሊዝኛ አስተማሪያችን እትዬ ፀሐይ ብትባረር። ርዕሰ መምህራችን እቶ ተከሉ ራሳቸው ቢባረሩ ምን ነበረበት። ኤዲያ እንደው እዚች አገር ደግ አይበረከትም።

ይሄ ዜና ለእኛ ለሦስተኛ 'ሲ' ክፍል ተማሪዎች ትልቅ መርዶ ነበር። ልክ ሁላችንም በጅምላ ከትምህርት ቤት አንደተባረርን ዓይነት ስሜት ነው የተሰማን። እትዬ ሐረጓ የተባረረችው "ሰው በማጎበር የተደራጀ እንስሳ ነው" ብላ በማስተማሯ ቢሆንም ርዕሰ መምህራችን አቶ ተከሉ ግን "መምህርት ሐረጓ የተባረረችው 'ሰው በማጎበር ከተደራጀ እንስሳ ነው' ብላ ፀረ ልማት ትምህርት በሕፃናት አእምሮ ውስጥ በመዝራቷ ነው" ብለው መምህራን ስብሰባ ላይ ተናገሩ አሉ። ይሄን ወሬ የነገረችን የሂሳብ አስተማሪያችን ልጅ ገነት ናት፤ አባቷ ሲያወራ ሰምታ !

አስቲ ለአንዲት 'ዮ' ብለው እትዬን ያባርሯታል...? አንዲት 'ከ' ምርጥ መምህራችንን ታስባርራለች ? አግዚአአአአአአ...ርዕሰ መምህራችን ራሳቸው ሰልፍ ሜዳ ላይ 'ነፍ' ጊዜ አይደል እንዴ የሚሳሳቱት ? ባለፈው እንዲያውም ማስታወቂያ ሲለጥፉ "ማንም ተማሪ 'ከአጥር' ከዘለለ እና ግቢ ውስጥም ይሁን ከግቢ ውጭ ከተያዘ የእኛ ተማሪ አይሆንም" ለማለት "ማንም ተማሪ 'ከጥር' ከዘለለና ግቢ ውስጥም ሆነ ከግቢ ውጭ ከተያዘ የእኛ ተማሪ አይሆንም" ብለው ማስታወቂያውን አሳስተው በመፃፋቸው ወላጅ ሁሉ ልጆቻችንን ጥር ወር ሲገባ ሊጨርሱብን ነው ብሎ ተንጋግቶ አልመጣም ? ...እና እትዬ ሐረጓ ላይ ሲሆን 'ዮ'ን ያካብዳሉ ? ወይኔ! አለቀሰኩ፤ ስቅስቅ ብዬ አለቀሰኩ ::

ለእናቴ ይሄንኑ አሳዛኝ ጉዳይ ስነግራት "ጉድ !...ዛሬም ተባረረች?" አለች እዝን ብላ። በኋላ አባቴ ጋር ሲያወሩ የሰማሁት ነገር የባሰ አሳዘነኝ። እትዬ ሐረጓ ለካ መባረር ብርቋ አልነበረም፤ መምህርታ ነገር የሚመርባት፤ ችግር ዘሎ የሚለጠፍባት፤ ነገር ከየትም ተሰቦ የሚሰበሰብባት ሚስኪን የመከራ ማግኔት ነበረች።

በጃንሆይ ጊዜ አማርኛ አስተማሪ ነበረች አሉ። አንድ ቀን ታድያ ተማሪዎቿን ተረትና ምሳሌ

ስታስተምር "አንበሳ ሲያረጅ የዝንብ መጫወቻ ይሆናል" ብላ ጥቁር ሰሌዳው ላይ በትልቁ በመፃፏ ተከሰሰች። በወቅቱ የንጉሡ ዙፋን በተማሪዎች መነቃነቅ ጀምሮ ነበር። ደርጎችም ወታደራዊ ነጠላቸውን አሸርጠው የአብዮታዊ ዘፈን ዳርዳርታ እስክስታቸውን አራተኛ ላይ እያስነኩት ነበር፤ አብዮታዊ ዋንጫ ልቅለቃ፣ ወታደራዊ ሶራ ሶራ...ህዝቡ እያጨበጨበላቸው...።

እቺ ሚስኪን መምህርት ታዲያ እየተዋከበች ራሳቸው ንጉሡ ዙፋን ፊት ቀርባ ጃንሆይ ገሰጿት "ስሚ! ከላይ ናት ዙፋናችን፣ ከግዜር የተሰጠች...፣ ከእዮብ ትዕግስት የተቆነጠረች...፣ ከዳዊት እምነት የተጨለፈች...፣ ከሰለሞን ጥበብ የተዘገነች...፤ እንኳን ዝንብ ተማሪና ዝንብ ደርግ ቀርቶ ማንም አይጫወትብን።" አሏትና በዚህችው ምክንያት ከርቸሌ ተወረወረች! እንደሚወራው የንጉሡ እስር ቤት ያን ያህል ባያስከፋም የእስር ጥሩ የለውምና መምህርት ሐረጓ ክፉኛ አዝና ነበረ።

"ሳይደግስ አይጣላም" እንዲሉ መምህርቷ በእስር ላይ እያለች ደርግ ንጉሡን ገልብጦ ሥልጣን በመያዙ ተፈታችና "ሳይንስ አስተማሪ" ሆና ተመደበች። "ኧረ እኔ አማርኛ አስተማሪ ነኝ" ብትል ማን ይሰማት ! "አብዮት ተረትና ምሳሌ ሰልችቷታል፤ ሰርዓተ ነጥብ ምናምን አትሻም፤ ሳይንሳዊ ወታደር፣ ሳይንሳዊ መደብ....ቀጥይ"

"እሺ!" ብላ ማስተማር ጀመረች...ሳይንስ ! በአማርኛ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለምዶባት "እጅን ከምግብ በኋላ መታጠብ ከዓረፍተ ነገር በኋላ አራት ነጥብ እንደማሰቀመጥ ነው" እያለች ሳይንስ ትምህርት ማስተማሯን ቀጠለች።

የሳይንስ ትምህርት እያስተማረች ተማሪዎችም ወደዋት ሰትኖር በአንድ የተረገመ ቀን "ዝንቦች ከቆሻሻ ይፈለፈላሉ" ብላ በማስተማሯ ተይዛ ታሰረች። የፖሊስ ጣቢያው ኃላፊ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ በፊቷ እየተንጎራደደ "ትላንት በአረጀ አንበሳ የሚጫወቱ ዝንቦች አልሽን፣ ለአንበሳው ማርጀት ቅድሚያ ሰጥተን ታገስን። ጭራሽ ዛሬ ከቆሻሻ ተፈለፈላችሁ ትይናለሽ !? እኛ የተፈለፈልነው ከአብዮት ነው..." ብሎ ራሱን በዝንብ ወከሎ በመበሳጨት አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድባት አዘዘ ። ያው በወቅቱ ሰላምታም ቅኔ ነው ተብሎ ሰምና ወርቁ ይፈለግ ነበርና መናገር ሲጋት ነበር።

መምህርት ሐረጓ ነገ ዛሬ ገደሉኝ እያለች ልጧ ተርሶ፣ መቃብሯ ተምሶ ስትጠብቅ ሞት የፈረደባት ካድሬ ልጁ ርሷ የምታስተምረው ኖሮ አባቱን አልቅሶ በመለመኑ ተፈታች።

"ትንሽ ሕፃን ይዛ ቋማ ከወደቡ
ላምላክ ብትነግረው ፀጥ አለ ወጀቡ" እንዳለው ድምፃዊው ...

ካድሬው ቢሮው ጠራትና ቁርጥ ያለ ማስጠንቀቂያ ሰጣት። "ስሚ አንቺ ሴትዮ፤ አሁን በልጄ ልመና ምሬሻለሁ። ከአሁን በኋላ፣

" ነኛ. አንበሳ የሚባል ሰም፤

ጋኛ. ዝንብ የምትባል ቃል...ከአፍሽ ቢወጣ ውርድ ከራሴ፤ ሂጂ ውጭ...ምን ትመስላለች አች! ለኮስማናውም ለምኑም በብድር የተገዛ ጥይት እንጨርስ እንዴ...!" ብሎ ለቀቃት:: መከላፊት ከሞት ጋር ሲወዳደር እዚህ ግባ አይባልምና በመከላፈቷ ሳይከፋት በምህረቱ ደስ ብሏት ወደ ጓላዋ እየተገላመጠች ወደቤቷ በረረች::

*** *** ***

አንድ ሌላ ቀን መምህርቷ ተማሪዎችን 'እንበሳ ግቢ' ወስዳ አንድታስጎበኝ በርዕሰ መምህሩ ታዘዘችና ለተማሪዎች ምን ብላ እንደምትነግራቸው ሲታሰብ ቆይታ እንዲህ አለች፤

"ልጆችዬ ! ቅዳሜ ጠዋት የ"እንስሳት ንጉሥ" የታሰረበት ሄደን ስለምንጎበኝ ከወላጆቻችሁ ስሙኒ ስሙኒ ተቀብላችሁ እንድትመጡ !" በቀጣዩ ቀን ግን ሌላ ጣጣ መጣባት:: አሰጠንቅቆ የፈታት ካድሬ ከአራት አጃቢዎቹ ጋር ከተፍ አለ:: ደም ሰሩ ተገታትሮ...

"እንች ሴትዮ ችግርሽ ምንድን ነው ? የአስለፍልፍ ይዞሻል ወይስ ሁለት ነፍስ ነው ያለሽ?"

"ምን አጠፋሁ ደግሞ ጌታዬ !" አለች እየተንቀጠቀጠች::

"የእንስሳት ንጉሥ የታሰረበት ሄደን እንጎበኛለን" ብለሽ ተማሪ አሰልፈሽ ቤተ-መንግሥት ልትሄጅ ነው:: እንኳን አንቺ ሰንቱ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ነኝ ባይ እየጠየቀ አልቻለም:: ደግሞስ የአብዮታዊት ኢትዮጵያን ሕዝብ ነው እንስሳ የምትይው?"

በወቅቱ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቤተመንግስት በቁም እስር ላይ ናቸው እየተባለ በርካታ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ ድርጅቶች እንጎብኛቸው የሚል ጥያቄ እያቀረቡ ነበር:: ያችን ቀን በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር አማላጅነት ምህረት ተደረገላት:: አብዮታዊ ሽምግልና ነፍሷን አተረፈው::

ይሄው አሁንም እንደኛና ከምትወደውና ከምታከብረው የመምህርነት ሰራዋ አመድ አፋሽ እድሏ አፋፍሶ አስባረራት፤ ያውም በአንዲት 'ዮ' እና በአንዲት 'ከ'...፤ በእንበሳም፤...በዝንብም፤ ...በ'ዮ'ም..በ'ከ'ም... ፍዳዋን የበላች ሚስኪን መምህርት በተማሪዎቿ ዐይን ግን ፍፁም ሌላ ሰው ነበረች ::

*** *** ***

የእትዬ ሐረጓ ከፍለ ጊዜ ሲደርስ ሰኞ በሦስተኛው 'ፔሬድ' ሁላችንም ደስ ብሎን በር በሩን እናያለን፤ ብቅ ስትል ግር ብለን ከወንበራችን እንነሳለን፤ ወንበሮች ይንኳኳሉ፤ ይንሳጠጣሉ፤ ወረቀቶች ይንከሻከሻሉ...ከዐይኖቿ ስር በሰሱ ማዳያት ጣል ያደረገባት፤ ሁልጊዜም ፀጉሯን በሻሽ የምትሸፍን፤ ከሻሹ ያፈነገጡ ነጭና ጥቁር ጠቃጠቆ የፀጉር ዘለላዎች ግንባሯ ላይ የሚታዩ፤ የተንሳቆለች መልአከ ረጋ ባለ እርምጃ ትገባለች...::

"የእባትሽ ሥራ"

"ጎንጥላ ሠሪ"

ያሬድ ...ሹፌር

ሳራ ...ዛፍ ቆራጭ

ታምሩ ...አባቴ ሞቷል እናቴ ልብስ ታጥባለች፤

ሽብሩ ...አባቴን አላውቀውም...

ከሁላችንም ፊቱ ወዛ ያለውን ኡስማንን ጠየቀችው፤

"ኡስማን አባትህ ስራቸው ምንድን ነው?"

"ቅቤ ነጋዴ" አለ ኡስማን ቀስ ብሎ፤ አይናፋር ነው::

እትዬ ተስፋ በመቁረጥ በረዥሙ ተነፈሰች:: እንደድሮው የሕዝብ ትምህርት ቤት የሚማር የባለስልጣን ልጅ የለም...በዝምታ ዕቃዋን ሰብስባ ድከም ባለ አርምጃ ከከፍላችን ወጣች::

"ደህና ሁኑ ልጆች!" አላለችም::

"የቤት ሥራችሁን ሳትሰሩ እንዳትመጡ!" አላለችም::

...ሄደች ደጓ መምህርታችን::

ከሁለት ወር በኋላ ርዕሰ መምህራችን አቶ ተከሉ ሰልፍ ሜዳ ላይ ቆመው እንዲህ አሉ...፤

"በታላቅ ትጋት እና የሙያ ፍቅር ላለፉት 28 ዓመታት ደከመኝ ሰለቸኝ ልረፍ ሳትል በመምህርነት ሲታገለግል የቆየችው መምህርት ሐረጓ ባደረባት ህመም ምክንያት በሕክምና ስትረዳ ቆይታ ትላንት ማታ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች፤...የአንድ ደቂቃ የህሊና ጸሎት !" አሉና አቀረቀሩ::

ሁሉም ሲያንነብስ ቀጥ ብዬ ርዕሰ መምህሩን እየኋቸው:: እጃቸውን ወደ ኋላ አጣምረው ፊት የተሰለፈውን ተማሪ አፍንጫ ሊነካ የደረሰ ቦርጫቸውን ቀስረው ሳያቸው እትዬ ሐረጓን በጭካኔ የዋጧት መስሎ ተሰማኝ:: ከነማጥፊያዋ፣ ከነጠመኔዋ፣ ከነጎንጥላዋ::

ገድሎ አንገት ማቀርቀር፣ የህሊና ፀሎት የሚባል የማስመሰል ካባ ለብሶ እነሆ ሰልፍ ሜዳችን ላይ...

የሆነ ነገር ቀጭ ሲል ሰምቼ ቀስ ብዬ እንደገና ወደፊት ተመለከትኩ:: ተደገመ:: እትዬ ሐረጓን ተከታ የገባችልን ውብለም የምትባል ወጣት መምህርት ማስቲካ ነበር:: የቀጣዩ ዘመን ሌላ ግዴለሽ ደወል::

9 የአባዬ ስልክ እና ባዮሎጂ

እንዲህ እንደዛሬው በየሰዉ ኪስ ሳይልከሰከስ በፊት ስልክ ተዓምራዊ የሀብት መለኪያ ነበር። አቤ...ት ስልክ እንዴት እንደሚከበር ! እንደሚፈራ...! ያኔ ኔትወርክ እንጂ ስልክ አልነበረም። ዛሬ ግን ስልክ እንጂ ኔትወርክ የለም ።

እንግዲህ በሰፈራችን አንድ የቤት ስልክ ብቻ ነበረ ያለው፤ ስሙ ደግሞ "የአባዬ ስልክ"፤ ብዙው የሰፈር ሰው የእኔን እናት ጨምሮ በዚህ ስልክ ነበር የሚጠቀመው፤ ደግሞ ድምፁ የትናየት እንደሚሰማ...ኪሊሊሊሊሊሊሊሊ ሲል የመንደሩ ሰው ሁሉ ሥራ ያቆማል። ወጣቶች ፍቅረኞቻቸው የደወሉ መስሏቸው የያዙትን ሥራ እርግፍ አድርገው ጆሮና ልባቸውን ያቆማሉ፤ እናቶች ሊጥም እያቦኩ ከሆነ ነጭ የቦክስ ጓንት ያጠለቁ መስለው ብቅ ይላሉ። የአባዬ የስልክ ድምጽ መቼም አይረሳኝም። አሁን የመጡ ስልኮች ቢዘፍኑ ቢንቀጠቀጡ የአባዬን ስልክ ድምፅ ከአዕምሮዬ ሊፍቁት አልቻሉም።

ስልኩ ሲጮኽ ልጆቻቸው አረብ አገር ያሉ እናቶች ልባቸው ይሰቀላል...፤ እናቴ ራሷ " አቡቹ ! እስቲ እሱን ቆርቆሮ ቀንሰው" ትላለች፤ ቴፑን ማለቷ ነው። እንግዲህ ይሄ ሁሉ ሰው እንዳቆበቆበ የአባዬ ልጅ ቡጡጡ በራቸው ላይ ትቆምና "እማማ ፋጤ ስ...ልክ ! ከውጭ ነው ቶሎ በሉ!" ብላ ትጮሀለች። እማማ ፋጤ ወደ አባዬ ቤት ሲሮጡ ሌላው ጎረቤት ወደየስራው ይመለሳል፤ ስልኩ በተደጋጋሚ የሚጮኸው ለበዓል አካባቢ ነው፤ በተለይ ለአዲስ ዓመት!

ቀላል ስልክ እንዳይመስላችሁ፤ በዚህ ስልክ ስንቱ ከውዱ ጋር አውግቷል፤ ስንቱ የውዱን መርዶ ተረድቶ በድንጋጤ ስልኩ የተቀመጠበት ጠረንጴዛ ሰር ተጠቅልሏል፤ ስንቱ ከጠፋ ዘመዱ ተገናኝቷል፤ ስንቱስ ብር እንደተላከለት ሰምቶ ፈንጥዟል ! ...እሪ ስንቱ ! ወደ አባዬ ቤት ሲንደረደር እንቅፋት አንግሎት ባፍጢሙም የተተከለ፤ ጥፍሩ የተነቀለ...አለ።

ለምሳሌ የአረጋሽ ጥፍር ተጣምሞ የቀረው ወደ አባዬ ቤት ስትሮጥ እንቅፋት አንግሏት ነው። አረጋሽ

ሀመሙን ቻል አድርጋው ስልኳን እናገረችና ልክ ስልኩን ስትዘጋው፣ "ኡኡኡኡኡኡኡኡኡ" ብላ ጮኸች። መርዶ የሰማች ነበር የምትመስለው፣ በኋላ ሲጣራ ከሰልኩ በፊት ለመታት እንቅፋት ነው ያለቀሰችው። ጥፍሯ ግን ተጣምሞ ቀረ።

ይሄ ስልክ ስልክ ብቻ አይደለም፣ ጩኸቱ የምሰራች ነው፣...ጩኸቱ መርዶ ነው። ከመንደራችን በላይ ያለው የጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ደውል ድምፅ የአባዬን ስልክ ጩኸት ያህል ግርማ ሞገስ የለውም - ለመንደርተኛው። የኛን መንደር ሰዎች ወፍራም እንጀራ፣ ደንዳና ናፍቆትና ፍቅር በቀጭን የስልክ ሽቦ ውስጥ ተጉዞ የሚያርፍበት ኬላ የት ነው ቢሉን "የአባዬ ቤት" እንል ነበር ።

ይህን ስልክ በጉጉት ከሚጠብቁ ቤተሰቦች መሃል የእኛ ቤተሰብ አንዱ ነበር። አባቴ ለሥራ ከእኛ ርቆ ይኖር ስለነበር እኛ ልጆቹን የሚመክረው ለሚስቱም የሆድ የሆዱን የሚናገረው በአባዬ ስልክ ነበር። አንደውም ግንባር ቀደሙ የአባዬ ስልክ ተጠቃሚ ቤተሰብ የእኛ ቤተሰብ ነበር ማለት ይቻላል። ታዲያ አባቴ ለበዓል ሲመጣ ለአባዬ የሆነ ነገር ይዞ ስለሚመጣ ስልክ ስንጠራ ቤተሰባዊ ቃና ባለው መንገድ ነው። "ስልክ !" ብቻ አንባልም፤ "እንዳይቆጥርበት ፍጠኑ ጋሼ ነው !" የሚል ማስጠንቀቂያም ይጨመርበታል።

ለምሳሌ አባቴ ሲደውል እናቴ ከፊት፣ አህቴ ከኋላ፣ ወንድሜ ቀጥሎ፣ እኔ፣ ትንሸዋ አህቴ ተግተልትለን እንሄዳለን። መጀመሪያ እናቴ ናት የምታናግረው፤ ድምጿን ቀንሳ ፊቷ በሃፍረት፣ በናፍቆትና በፍቅር ተጥለቅልቆ ብዙ "እም" እና "አይይ!" የበዛበት ንግግር ታደርጋለች።

እም!

እም!

እም!

አይይይይይ!

የአባዬ ስልክ ደግሞ ለከፋቱ ይጮሃል፤ በአሁኖቹ የእጅ ስልኮች ቋንቋ 'ላውድ ስፒከር' ላይ ያደረጉት ይመስላል።

"እንደምነሽ ! ...ምነው ድምፅሽ ጎረነነ ? አመመሽ እንዴ የኔ እናት ?" ይላል አባባ፤

"አይይይይ! ደህና ነኝ! " ትለለች እናቴ፤ አንዳንድ የፍቅር ነገርም ስለሚናገር ቶሎ መበናበት ትፈልጋለች።

ቀጣይ ተረኛ ትልቅ አህቴ ናት።

"ምን ልላከልሽ"

"ስኒከር ሜማ"

"አሽ!"

"ነው ..."

"አሺ የኔ ማር!" ድምፁ ውስጥ መናፈቅ አለ፣

"እንደባለፈው ሰፈ እንዳታመጣ ባባ"

"አሺ የኔ ቆንጆ!"

ወንድሜ ይቀጥላል...

"ታኪታ ሜማ ባለ ብሎኑን"

"ባለ ቡሎን ሜማ አለ እንዴ ?" ይላል አባቴ በግርምት፣

"እንከት!"

"አሽ አፈልጋለሁ ፤ አንተ ብቻ እናትህን እንዳታስቸግር፣ በደንብ ተማር!"

እኔ አባትህን አናግር ስባል አላናግርም፣ አብሬ ሮጬ አባዬ ቤት ድረስ ሄጀ ግን ብሞት አላናግርም፣ እናቴ ትበሳጫለች።

"አሺ ምን ላምጣልህ ይልሃል" ትላለች በብስጭት፣

"ም ን ም!" እንባዬ ይመጣብኛል፣ አባቴን እወደዋለሁ፣ ግን በስልክ አላናግረውም። ለምን ቢባል መልሰ የለኝም። የተባለው ነገር ሁሉ ሲመጣ ግን እሁቴ ያንን ሁሉ ማብራሪያ ሰጥታ ጫማዋ ይሰፋል ወይ ይጠባታል። ወንድሜ ባለብሎን ታኪታ አይመጣለትም፣ "ኧረ እንዲያ የሚባል ጫማ የለም!" ይለዋል አባባ። እኔ ግን ምንም ሳልናገር ምርጥ ነገር ይመጣልኛል፣ አባቴ እኔን ራሴን እስኪመስለኝ ምርጫው ልክ ነው።

*** *** ***

እኛ ሰፈር እንዲት ሴት ጎረመሰች የምትባለው በአባዬ ስልክ ቤተሰብ ወይም ዘመድ ያልሆነ ወንድ ከደወለላት ነው። ሁሉም ሴቶች ለፍቅረኞቻቸው የአባዬን ስልክ ነው የሚሰጡት። ወንዶችም አልፎ አልፎ ይሰጣሉ ። ታዲያ አባዬ ቤት የተወራችው ነገር ስልኩ እንደ ሚጋፍን እየጮኸ ምስጢሩን ስለሚዘራው ጎረቤቱ ጋር ወዲያው ይደርሳል።

"ሮማን የያዘችው ልጅ ሹፌር ነው መሰል ሁልጊዜ ከተለያየ አገር ነው የሚደውለው፣

"እትይኝም!"

"ሙች!...እንዴ ከጅቡቲ፣ እንዴ ከሞያሌ፣ ቢጡ ሲያወራ ሰምታ ነው የነገረችኝ"። ቢጡ የአባቼ ልጅ ናት፣ ማን ከማን ጋር ምን አወራ የሚለውን ለመንደሩ የምታዳርሰው እሷ ናት።

እንዲህ እየተባለ ቢቃ የተወራው የተደረገው ሁሉ ሰፈሩ ውስጥ ይናኛል። አንዲት ሴት ወይም ወንድ በአባዬ ስልክ ካልተደወለለት ጉርምስናው እውቅና አያገኝም።

አንዲት ሴት ስልክ ማናገር እና አለማናገሯ የፀባይ መለኪያ ሆኖ በመንደርተኛው ያስወቅሳታል። አልያም ያስመሰግናታል። "ውይ እሷ አንገቷን የደፋች፣ አባዬ ቤት አንድ ቀን ረግጣ አታውቅም " ይባላል። ወይም "እች ልጅ የአባዬን ቤት እዘወተረች፣ መዘዟን እንዳትመዝ" ይባላል። ታዲያ የአባዬን ቤት ከማይረግጡ 'ጨዋ' ጎረምሶች መሃል አንዱ እኔ ነበርኩ። ስምንተኛ ክፍል ስደርስ ግን ጨዋነቴ ተገሰሰ።

*** *** ***

የስምንተኛ ክፍል የባዮሎጂ አስተማሪያችን አትዬ መከሊት በጣም አይናፋር ሴት ነበረች። 'ምእራፍ ዘጠኝ' የስነተዋልዶ አካላት የሚል ርእስ ላይ ስንደርስ ፊቷ ቀልቶ እያፈረች ሲታስተምረን ትዝ ይለኛል።

"የስነ ተዋልዶ አካላት እንግዲህ...ያው...ወንድ እና ሴት ...ያው..." ጭንቅ ይላታል አትዬ መከሊት፣ እኛ ደግሞ ጆሮ ብቻ እንሆናለን። ስልሳ የምንሆን የአንድ ከፍል አጉል ኢድሜ ላይ ለምንገኝ ተማሪዎች ይሄ ጉዳይ የነፍስ ጉዳይ ነበር - የምንጓጓለት፣ ለመስማት የምንሰስትለት፣ የስነተዋልዶ አካል ነገር ልባችንን ሰቅሎት፣ ትንፋሻችንን ውጠን እንቁለጨለጫለን። በከፍለ ጊዜው መርፌ ቢወድቅ ይሰማል ፀጥታው።

"ውይ...ምነው ሁልጊዜ እንዲህ በትኩረት በተከታተላችሁ...! አያችሁ መማር ለራስ ነው፣ ትምህርት አገርን ይቀይራል። ያደጉት አገሮች ዝም ብለው አላደጉም። ...ትምህርት..." ኤጭጭ እኛ ስለ ስነተዋልዶ አካላት ለመስማት ጓጉተን አትዬ ምከር...መከራ፣ መከራ ምከሯ ሲያልቅባት...

"ወንድ ልጅ ሲጎረምስ ፂም ማውጣት የተለያየ የሰውነት ከፍሉ ላይ ፀጉር ማብቀል...እና ድምፅ መጎርነን ይጀምራል...ገባችሁ ?"

ሰምረት እጇን ታወጣለች፣ "ፀጉር የሚወጣባቸው የተለያዩ አካላት የትኞቹ ናቸው ቲቸር?"

"ውይ አንች ደግሞ ፈተና ላይ የማይመጣ ነገር ምን አጠያየቀሽ ?" ትልና ታፍራለች አትዬ፣ ሁላችንም እንስቃለን።

መስፍን እጁን ያወጣል በተራው፤ የመስፍን እጅ ማውጣት ይገርመናል፤ በገመድ አስረውም ቢጎትቱት እጁ የማይዘረጋ ልጅ ዛሬ እጁን ሲያወጣ ይገርመናል:: ሽባ የተተረተረ ያህል በግርምት እንመለከተዋለን::

"ሴት ስትጎረምስስ ምን ምልክት ይታይባታል ?" ብሎ ይጠይቃል፤ ከፍሉ በሳቅና በጩኸት ይደበላለቃል:: እትዬ ታፍራለች::

"ዝም በሉ ልክ ነው ጥያቄው፤ የምን መገልፈጥ ነው:: እስቲ ከእናንተ ይህን ጥያቄ የሚመልስ" ትልና እኛኑ ታጋፍጠናለች:: ቶማስ እጁን ያወጣል "ሴት ስትጎረምስ ያው...አለ አይደል..." ብሎ ደረቱ ላይ እጆቹን ያሳርፍና እንደ ጡት ያጎብጣቸዋል:: የከፍሉ ተማሪ በሳቅ ያውካካል::

እትዬ በሃፍረት መግቢያው ይጠፋባታል፤ ድንገት አንድኛችንን ትጣራለች::

"አብርሃም !"

"አቤት!" እላለሁ በድንጋጤ፤

"የሴት ልጅ ጉርምስና ምልክቶች ምን ምን ናቸው?"

በፍርሃት ላብ ላብ እያለኝ እየፈራሁ ሞከርኩ "ስ.....ስልክ!"

"ምን ?"

"ስልክ...ማለት የአባዬ ስልክ" ከፍሉ በሳቅ ተንጫጫ፤

"ጥያቄው አልገባህም..." ብላ እንድቀመጥ ምልክት አሳየችኝ:: "መልሱ ስላልገባት ጥያቄው አልገባህም ትላለች እንዴ!"ብዬ አኮረፍኩ::

አጎጠጎጤ፤ የድምፅ መስረቅረቅ፤ የዳሌ መስፋት እና የወር አበባ ማየት የሴት ልጅ ጉርምስና ምልክቶች መሆናቸውን ባዮሎጂው ነገረን::

*** *** ***

ትዕግስት የምትባል የከላስ ልጅ የወደድኩት በዛው ሰሞን ነበር:: ትዕግስት ቆንጆ፤ በነፃነት ያደገች የሃብታም ልጅ ናት:: ቤታቸው ስልክ አላቸው :: ብቸኛ ችግሯ አውርታ የማትጠግብ፤ ሳታቋርጥ ሙሉ ቀን የምታወራ ወሬኛ መሆኗ ነበር:: ስታወራ በጣም ትጮሃለች:: በቃ ቀስ ብሎ ማውራት አትችልም ::

ሁሉን ነገር ለመሞከር የቸኮለች ከመሆኗ ብዛት ጓደኛ እንሁን ብዬ በጠየቅኳት በቀጣዩ ቀን

ከከፍላቸን ጎላ ተቀምጠን ጉንፉዙን ሶማ ኦሰነበረቶኝ። ከምር ነዘረኝ። በቅጣዛ ሳምንት ነንሩ። ሶማ ጉዘረዙን ነዛ አይረጉቸው። በሳም ሰለወሃይጎኒት ከተምነዘርት ቤት ውሚ ላቀራት ፈመኙ አኒም የአባዙን ሰልከ ቁጥር ሰጠኝት።

*** *** ***

አንደ ቀን ከወደ አባዬ ቤት ሶሚ ተጠራ !

"አብርሽ ሰ...ል...ከ!"

"እቤት ! መጣሁ !" አለች አኒቴ!

"ነሽ አይደለም አብርሽን የሚፈልግ ሌላ ሰው ነው" አለች ሚጣ። "ሌላ ሰው የታወቀ ነዉ ትርጉሙ።

አባዬ ቤት ሰደርስ የገጠመኝ ነገር አሰደንጋጭ ነበር። ቀኑ የኪዳነምህረት ቀን ነበር፤ አባዬ ቤት ዝከር ተደርጎ ፀበል ጸዲቅ ሰለነበር ከሩቅም ከቅርብም የተሰበሰበው ጎረቤትና ዘመድ እዝግኔ ግጥም ብሎ ያውካካል። መሪመጀ እንኳን አልነበረም። ግጥም ብሎ በሰው ተሞልቷል ቤቱ ደግሞ ለከፋቱ ሰልኩ ስር ያለች ኩርሲ ላይ አግግ በላይነሽ የሚባሉት የሰፈራችን ነገረኛ ባልቴት ተቀምጠዋል። ኖ ከመግባቴ ለከፋኝ።

"አቡዛ አንተም መጣህ...ና አለፍ በዚህ!" አሉኝ፤

የደወለችው ትዕግስት ነበረች። በሆነ ነገር ተደባብረን ሰለነበር አትደውልም ብዬ ነበር። ትዕግስት በባህሪዋ ፈጯሂ ናት። እንከዋን የሚርመህ ሰልከ ጋር ተዳምራ! የሰልከ ጉግግር ሳይሆን ለዛ ሁሉ ሰው አዋጅ የምታውጅ ነበር የምትመስለው።

"አብርሽዬ!"

"እቤትየ" አልኩ ኮሰተር ብዬ። ፀበል ቀማሹ ሁሉ ወሬ ቅመስ ተብሎ የተጠራ ይመስል ጭጭ ብሎ ጆሮውን ቀሰረ።

"አብርሽ ምነው ጨዋ ሆንከ?" አለችኝ ትዕግስት። ልከ እንደ ሬዲዮ ድራማ ፀበልተኛው ይሰማል።

"እ!"

"አብርሽ ችግር አለ...? ትላንት ከንፈርህን ሰለሳምኩህ ደበርኩህ?"

አማዚኦኦኦኦኦኦኦ! ሰልኩ አጠገብ የኪዳነ ምህረት ሰዕል ተቀምጧል፤

"ኪዳነምህረት የዚችን ልጅ አፍ ወይም የፀበልተኛውን ጆሮ ከዘጋሽልኝ የዛሬ ወር አንድ ፓኮ ሻማ"ብዬ ተሳልኩ:: ስልኩን በጆሮዬ ለማፈን ወደ ጆሮዬ ጥብቅ አድርጌ አስጠጋሁት::

ትዕግስት ትቀባጥራለች::

"...አብርሽ እኔኮ ሴከስ እናድርግ ስትለኝ እንቢ ያልኩህ ፈርቼ ነው፤ በናትህ አብርሽ...እሽ በቃ አርብ አከስቴ ቤት አድሬያለሁ ልበልና አንተም አመቻችተህ..."

እማማ በላይነሽ ወሬ እያዳመጡ ፉት ያሉት ጠላ ሰርናቸው ውስጥ ገብቶ ትን አላቸው:: ከኩርሲያቸው ላይ አስኪፈነገሉ ተንፈራፈሩ:: "...ውሃ ውሃ ስጧቸው ! ጀርባቸውን ምቷቸው!" ይል ጀመረ ፀበልተኛው:: እኔም የአባዬን ስልክ ዘግቼ ቀስ ብዬ ወጥቼ ተፈተለኩ፤ ወደ ቤቴ::

ወዲያው ሰፈሩ ውስጥ ዝናዬ በመወራቱ እናቴ አበደች...

"እንዴት ታዋርደኛለህ! እንዲህ ላገር መሳቂያ ታደርገኛለህ፣ አብረሃም?! ... አባቱ ባይኖር ሴት ቢያሳድገው ልታስብለኝ ....!" እያለች እንባ እየተናነቃት ስትገስፀኝ በመሐሉ ቢጣ ተጣራች::

"ሶስና...ሶሲ ...ስ...ል...ክ ጋሼ አይደለም ! ሌላ ሰው ነው !":: እናቴ ቢድንጋጤ ውሃ ሆነች፤ ሶስና ትንሿ አህቴ ናት:: የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ፤ ሶሲ ጎረመሰች ፤ በአህቴ መጎርመስ እኔ እና እናቴ መደፈር ተሰማን:: አናግራ ስትመለስ ልንወርድባት ተዘጋጀን!

10 ሁለት ብር ስንት ዶላር ነው ? (አንዷን ወንዝ ሁለት ጊዜ ስንሻገራት)

ከአስራ አንድ ዓመታት በፊት ደሀ ነበርን:: ያጣን የነጣን፣ ሙልጭ ያልን ነጭ ድሆች:: ከድህነታችን ከብደት የተነሳ ሰንት ሰዓት ላይ እንደምንበላ ሳይሆን ሰንት ሰዓት ላይ ርሀቡን ጋብ እንደሚል ነበር ዘወትር የምናስበው:: እኔና እህቴ ትምህርት ቤት፣ "እበበ በሶ ባላ" የሚል ምሳሌ 'ቲቸር' ሲናገሩ በመሳምጀት ምራቃችንን እንውጥ ነበር::

ቤታችን ውስጥ አንድ የረገበ የሸበ አልጋ፣ ሁለት የሳር ፍራሾችና አራት የተወላገዱ ኩርሲ ወንበሮች ብቻ እንደነበሩን ዛሬም ድረስ እናቴ ሳጥን ውስጥ ያሉት ታሪካዊ ፎቶዎች ያሳብቃሉ :: ግድግዳ ላይ ሾና እንደተረጨዙ የሞተ አባቴ ፎቶግራፍ የዘመን ጥቀርሻ እንዳወየበው በላስቲክ ተለብዶ ተሰቅሏል::

እንግዲህ ቤታችን ሁለት ክፍል ነበረች:: አሁን የነገርኳችሁ የሳሎናችንን (ወጡ እንዳይቀር) ይዞታ ነው:: ወደጓዳ ስትገቡ ውስጣቸው የእንጀራ ላስቲክ ብቻ ያለባቸው ሁለት ትልልቅና አሮጌ የእንጀራ መሶቦች ታገኛላችሁ:: ጠርዛቸውን በደሀና ቀን አይጥ የቸረቸፈው !!

ሁለቱም ሁልጊዜ ባዶ ነበሩ (አይጦች ከልጆቻቸው ጋር በእነዚህ መሶቦች አጠገብ ሲያልፉ ለልጆቻቸው እንዲህ እያሉ ታሪክ የሚያወሩላቸው ይመስለኛል:: "በድሮ ጊዜ በአያቶቻችን ዘመን፣ እነዚህ መሶቦች ውስጥ ተበልቶ የማያልቅ እንጀራ ነበር:: የዛሬን አያድርገውና ለሰንቱ የአይጥ ሰርግ ድግስ የበቃ - ወይ ጊዜ መሶብም እንደ ዓለማያ ሀይቅ ይደርቃል !"

እናቴ ታዲያ አማኝ ናት:: በየሦስት ቀኑ መሶቡ ውስጥ የሚቀመጡትን የእንጀራ ላስቲኮች እያጠበች እድርቃ ወደ መሶቡ ትመልሳቸዋለች:: "በረከት ሲመጣ አዋጅ አያስነግርም፣ ድንገት ከተፍ ቢል ተዘጋጅተን መጠበቁ ደግ ነው" ትላለች:: ይሄን መራር ስብከቷን አልወደውም - ግን ትንቢቷ ሰመረ::

እናቴ ኦብይ ነበረች:: ደሀ ነብይ በቤቱ አይከበርም፣ እናትም ብትሆን !! አከበርናትም አላከበርናትም ትንቢቷ ሰመረና በረከት እንደመብረቅ ወረደብን:: (ምናባቴ ልበል ታዲያ) በሰድስት ወር ውስጥ

መከለኛ ገቢ ካላቸው ጎረቤቶች ተርታ ተሰለፍን። ጎረቤቱ ጉድ ብሎ ሳያባራ፣ በዓመቱ ምን የመሰለ ቤት ሰራን - ባለ አምስት ከፍል ዙሪያውን በግንብ የታጠረ። አጥሩ፣ ሰው እንዳይመጣብን ሳይሆን፣ በለመደ እግራችን ልንቀላውጥ እንዳንሄድ ራሳችንን ከነበረ ልምዳችን መከለያ ይመስላል።

ቡሀላይ ገና ሀብታም እንደሆንን አካባቢ አናኗሩን አንላመደው ብለን ተቸግረን ነበር። እንግዲህ የዚህ ድንኮኖኛ ለውጥ ምክንያቱ እህቴ ፈረንጅ ማግባቷ ነበር (ደግ ፈረንጅ)። እንዴት እንዳገባችው (ይቅርታ እንዳገባት) ላውራችሁ። ከትምህርት ቤት እየመጣች፣ ልክ ኡስማን ሱቅ አካባቢ ስትደርስ፣ ፈረንጁ መኪናውን ቆሞ ቆሞ ሄዶ አድርጎ አቆመና "አ...ማይ...ጋድ" በማለት የእህቴን ውበት አደነቀ።

በበኩሌ የእህቴ ውበት የፈረንጅ መኪና ማስቆም ቀርቶ የራሷን ሳንቲም 'ሆጭ' አድርጋ ከፍላ የምትሳፈርበት ታከሲ እንኳን እጁን ብትዘረጋ የሚቆምላት አይመስለኝም ነበር። ግን ምን ይደረግ፣ ፈረንጆች ነገራቸው ሁሉ ግራ ነው። መኪናውን እዛው ጥሎት እህቴን ተከትሎ ቤታችን ድረስ መጣ።

እናቴ ለዕርዳታ የመጣ መስሏት፣ ከዓይኖቿ 'ትራጄዲ' ብርሀን ለቀቀች። የመንደራችን እንግሊዝኛ አዋቂ (የእህቴም ወዳጅ ብጤ) ሲራጅ ተጠርቶ መጣና ፈረንጁ ምን እንደሚል ተረጎመልን። "እሷን ማግባት አፈልጋለሁ" ነው የሚለው አለ ቅር ብሎት - ወደ እህቴ እየጠቆመ።

እናቴ ባለማመን፣ "ማንን እጅጋየሁን" አለች። (እህቴ እጅጋየሁ ነው ስሟ)

"አዎ...ሌላ ማን አለ ታዲያ እማማ አረጋሽ" ሲራጅ ተነጫነጨ (እህቴ ጋር ማታ ማታ እዛ እንጀራዋ ዛፍ ስር ይቆሙ ነበር) እናቴ፣ አንዴ ፈረንጁን፣ አንዴ እህቴን ስታይ ቆየችና፣

"ሲራጅ...ግን...እንግሊዘኛ በደንብ ታውቃለህ ?" ስትል ባለማመን ጠየቀች። ፈረንጁ ግን ወደ እህቴ እየጠቆመ በተኮላተፈ አማረኛ "ኮንጆ...ኮንጆ.." በማለቱ "ይሄ ሰው አምርሯል" አለች እናቴ። ያው ጉዳዩ የፈጀውን ጊዜ ፈጅቶ በአንድ ወር ውስጥ ተጋቡ።

ይሄ ፈረንጅ (ይቅርታ የእህቴ ባለቤት) ታዋቂ የታሪክ ተመራማሪም ነበር።ይሄን የሰማሁ ቀን፣ "እህቴ ከመከሳቷ የተነሳ ሉሲን መስላው ይሆን" ብዬ አሰብኩ፣ ወይስ እህቴ ይሄን ሚስኪን ፒተር ማንትስ ምናምን አሰነካችው...።ከተማውን የሞሉት ቆነጃጅት ሁሉ ፒተርን ሲያዩ ተበድረው የሚስቁ፣ መቀመጫቸውን እንደባንዲራ የሚያውለበልቡ፣ እንደ አቦሸማኔ ሽንጣቸውን እየመዘዙ እማላይ ሊሆኑ የሚደከሙ ስለምን ለዓይኑ አልሞሉም ? ግዴላችሁም ይሄ ፒተር ጤነኛ አይደለም፣ ገዳይ ዘመን የሌለው አፅም ሲያገላብጥ፣ ተዘግቶ የኖረ ዋሻ ሲበረብር አንዳች ነገር ተጣልቶታል።

እንዲት የከርዳዳ ፀጉሯ ቱማታ አዳማ ድረስ የሚሰማ፣ በመረገጥ ብዛት ሶሉ ተረከዙ ላይ የተሸነቆረ ነጠላ ጫማ የምትጎትት ሴት በልዕልት ሂሳብ የሚያሳይ፣ ሰይጣን መነፅር ዓይኑ ላይ የተሸነቆረ ነጠላ ጫማ የምትጎትት ሴት በልዕልት ሂሳብ የሚያሳይ፣ ሰይጣን መነፅር ዓይኑ ላይ የለጠፈበት ነገር አለ፣ እንጂ እህቴ ላይ እንዲህ ሙጭጭ ባላለ። ሚስኪን ፒተር ቤት መጥቶ

እዛች ጠማማ ዱካ ላይ ቁጭ ብሎ እሁቴን ዓይን ዓይናን ሲያይ፡ በእውነት እንደሰጋ ዘመኗ እንጀቴ ይንሰፈሰፋል።

እንግዲህ ይሄ ፈረንጅ እሁቴን ጠቅልሎ ከመውሰዱ በፊት፣ ትምህርቷን እንድትጨርስ ተባሎ ለሁለት ዓመት እዚሁ ተቀመጠች። ፒተር ታዲያ በየሰድስት ወሩ እየመጣ ቤታችንን ጥምቀተ ከማድረጉም በላይ፣ ይሄን ዶላር ልኬ ልሙት አለ ! ይልካል፣ ይመነዘራል። ይልካል፣ ይመነዘራል። ወላ በጥቁር፣ ወላ በኑሮ ዝበያ እየተመነዘረ ዓለማችንን አየን። ስልካቸን ከፌሙሽ ጎረቤት "እሁን አብርሃም ወደ ባንክ ሊሮጥ ነው" ይላል። ቤታችን እማር የጣለው ሰው ሁሉ በሞቴ፣ እፈር ስሆን ተብሎ ተጋብዞ ነው የሚሄደው። የእንግዳ ማረፊያ፣ የአብርሃም ድንኳን !! በየቀኑ ብቅ እያሉ የሚመፀውቱ የኔ ብጤዎችም ብዙ ነበሩ። እንዳንዱማ ደንበኛ ከመሆናቸው ብዛት፣ "ስለመብርሃን" አይሉም። ሶባቢያችንን በር ያንኳኳሉ፣ ቢቃ በልተው ጠጥተው ይሄዳሉ።

እንደውም እንዱ የኔ ብጤ መመፅወቱን መብት እድርጉት፣ "ምነው ዛሬ ፈኪጢን አላነሳችሁት" ብሎ አስከመቆጣት ደረሰ። ይሄው ሰውዬ ሌላ ቀን የጎድን አጥንት ስለተሰጠው እኩርፎ ሳያመሸት ሄደ። እናቴ እንደገና ጠርታ፣ ወዙ የሚፍለቀለቅ ቅልጥም ሰጠችው። ደስ ብሎት፣ "በዚህ የሚያይሽ ቅልጥሙ ይሰበር" ብሎ መረቃት።

ይሄ ሁሉ ርዝቅ ሲመጣ፣ ግቢያችንን በሞላው የበረከት ውሀ ድሎት ሲዋኝ፣ "ደሀ ብር እያማኝ ሲቆጥር ይጥላል" እንደሚባለው የእሁቴ ፀባይ ይቀያየር ጀመረ። ልብሷን ለባብሳ፣ ቦርሳዋን አንጠልጥላ ጧት የውጣች ማታ ትመለሳለች። ድሮ ከሰው የማይቆጥሯት ጎረምሶች ሁሉ እንደጥላ ከሰሯ አንጠፉ አሉ። አሷን ብለው ሳይሆን የፈረንጅ ሚስት ጋር ዋልን ለማለት።

እጅግዬ፣ እጅግሻ፣ ጂጂ፣ ጃ፣ ጆ፣ ጅን፣ ጅንሊድ (ካፒታሊን ይሆን?) ቢቃ ስሚ ፍጻውን አየ። በዚህ ዘመቻ ፈታውራሪው 'ሲራጅ' ነበር (ተከተለኝ ወደ እጅጋየሁ ልዘምት ነው...)። የእሁቴ ድፍረት ገደቡን ጣሰና ጭራሽ አርግዛ ቁጭ። ደግነቱ በዚያ ዓመት የአናቴ አምላክ የፒተርን አማር ያዘው።

እናቴ መጀመሪያ አርግዘናው ከፒተር መስሏት ነገር ሊታበላሽ ነበር። "ለፒተር ንገሩልኝ ደስ ይበለው፣ 'ዓይንህን ባይንህ ልታይ ነው' በሉልኝ" ምናምን...! ልጅቱ ስትወለድ ከዶታዋ በስተቀር ቁርጥ 'ሲራጅን' !! (የመንደራችን ነገረኛ ሴቶች ግር ብለው 'ላንግዌጅ' ትምህርት ቤት ተመዘገቡ ይሄን ጉድ ለፒተር ለመንገር !!) ጉዳዩ ተሸፋፍኖ፣ ተደባብሶ 'ሾላ በድፍን' - የስድስት ወር ልጇን ለእኛ ጥላ አሀቴ አሜሪካ ገባች።

ሕፃኗን አልም ያለ ገጠር የምትኖር አከስታችን ጋር ላከናት። ሲራጅ "የገጠራቱ ኢትዮጵያ ሕፃናት የትምህርትና የጤና ዕድል የማግኘት ዕድላቸው አናሳ ነው" አለ...ሃሃሃሃ (ሰውየው አሉ፣ ከሚሰቱ ውጭ ፋጤ ከምትባል ሴት በድብቅ ወልዶ ልጁ ሞተ ብለው አረዱት። ሚስቱ ፊት አያለቅስ ነገር ቸገረው። ዝም አይል ነገር ልጁ ሆኖበት እና ምን አለ፣ "እጅብ አላህ የፋጤን ልጅ ትገልባት") ሲራጅም ልጇን ገጠር አትላኩብኝ አይል ነገር ቸግሮት፣ ዝም አይል ነገር የአባት

እንጀት ሆነና፣ "አጀብ አላህ የገጠሪቱን ኢትዮጵያ ሕፃናት..." ብሎ አረፈው::

"ሄሎ አብርሽዬ ደርሻለሁ:: ለሲራጅ ደርሻለሁ በልልኝ::" አይዋት እንግዲህ እህቴ ከነስንከሳሯ አሜሪካ ላይ:: እንደነገ ልትበር እንደ ዛሬ ማታ፣ በጓሮ በኩል እንጀሪው ዛፍ ስር ሲራጅ ጋር ቁጭ ብለው አያወሩ:: ሲራጅ እንባውን ሲጠርግ አየሁት:: አሳዘነኝ:: ለሰንቱ ልዘን ?!

ሲራጅ ጋራጅ እየሰራ እናቱን ይረዳል፣ እህቱን ያስተምራል:: በፊት ደሰ የሚል ቀይ ልጅ ነበር - መልከ መልካም:: ጥቁርቁር ብሏል አሁን:: በየበረሃው ተበላሽቶ የቆመ መኪና ተከትሎ ሲባዝን !!

እዚህ እንጀሪ ዛፍ ስር ሕፃን ሆነን ፣ እኔ፣ እህቴና ሲራጅ አቃቃ እንጫወት ነበር - ሲራጅ እና እህቴ ባል እና ሚስት ሆነው:: ደግሞ ሲራጅ ከመብሰሉ ብዛት ወደ ጥቁርነት የሚያደላ ያሞከሞከ የእንጀሪ ፍሬ ለእህቴ ይሰጣት ነበር:: ከፍ ስንል እህቴና ሲራጅ እይነ ውሀቸው አላምርህ ሲለኝ ብቻቸውን ተውኳቸው:: ይሄው አሁንም አዛው ቦታ ላይ እህቴ ቢጋራጅ ስራ የፈረጠመው የሲራጅ ትከሻ ላይ ራሷን ጣል አድርጋዋለች - የሆነ ህልም ነገር ነበር የሚመስለው::

በፊት በፊት፣ እናቴ ሳንቲም ይቸግራትና የዘወትሩን ቡና እንኳን ሳታፈላ በር ላይ ቁጭ ብላ ትተከዛለች:: እህቴ ወጣ ትልና ቡና ዳቦ ምናምን ይዛ ትመጣለች:: ቤታችን ትንሽ ፋሲካ ይሆናል፣ ደስ ብሎን እናድራለን:: ይሄ ነገር አንዴ፣ ሁለቴ ሳይሆን ለዓመታት የተደጋገመ ነገር ነበር::

ሲራጅ ብር እየሰጣት እንደሆነ እኔ አውቃለሁ:: እናቴም ታውቃለች:: ግን "ከየት አመጣሽው?" ብላ እህቴን አትጠይቃትም:: ድህነት ልጁን የመገሰፅ ድፍረቷን ሰልቦት !! ሲራጅ ለእኛ ቤተሰብ፣ በትላንትና እና በዛሬ መካከል የነበረ ድልድያችን ነበር:: እዩት እንግዲህ የእንጨት ድልድዩን አፍርሰን የብረት ድልድይ ስንዘረጋ:: ተመልከቱ እንዱን ወንዝ፣ ሁለት ጊዜ ስንሻገር:: ሳንደፈር የኖርን ማለት ምንድን ነው:: ምድራችንን ፎከረን ለተቀበልናቸው ባዕዳን ሚስቶቻችንን አልቅሰን እናስረከባቸዋለን:: ኡፍፍፍ...ይሄ የነማን ጦርነት ነው - የሲራጅና የፒተር፣ የአበሻና የፈረንጅ፣ የጥቅምና የፍቅር፣ የብረት መዝጊያና የጭራሮ መዝጊያ፣ የሀሊናና የሆድ፣ የነፍስና የሰጋ ወይስ የሰውና የፈጣሪ?

*** *** ***

ከአራት ዓመት በኋላ እህቴ መጣች አምሮባት (ፈረንጅ መስላ፣ 'ሰው ማንን ይመስላል ቢሉ ኑሮውን'):: አገር ምድሩን ጉድ ያሰባለ መኪና:: አንድ ቸኮሌት የመሰለ የሁለት ዓመት ሕፃን ልጅ - ይዛ መጣች::

ባለ ምናምን ኮከብ ሆቴል ፒተር፣ እኔ፣ እሷ እና የሁለት ዓመት ከልሰ ልጁ ምላ እየበላን፣ ፒተር የራሱን ጨርሶ እጁን ሊታጠብ ሲሄድ:: ልጁ ድክ ድክ እያለ አባቱን ተከትሎ ከዓይናችን እንደተሰወሩ፣ እህቴ ወደኔ ሰገግ ብላ፣ "አብርሽ ሲራጅ አሁንም ሰፈር ነው የሚኖረው?" አለችኝ

እፍረት በተቀላቀለበት ጉጉት:: ያስታውቃል በሆዴ አፍናው የኖረችውን እሳት በሰው ላገር ስታምስለስለው የኖረችውን ህመም ዛሬ ከእኔ ከወንድሟ ጋር ልትካፈለው እንደተነፈሰችው ሰው መሰያት !!

እውነቱን ለመናገር ሲራጅን ረስቸው ነበር፣ "እኔንጃ ካየሁት ቆየሁ:: የሆነ ሰዓት ላይ ግን ጀዝበ ነበር" አልኳት በግዴለሽነት:: ዩኒቨርስቲ ገብቼ ስለነበር በእርግጥም ካየሁት ሁለት ዓመት አልፎኝ ነበር:: ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁት ሰፈር ድንገት ከሥራ ሲገባ ነበር:: ጅዝብ ብሎ ኮሌታዋ የነተበ ሸሚዝ ጉልበቱ እና መቀመጫው ላይ የሳሳ ጅንስ ሱሪ በጥቁር ተረከዟ በተጣመመ ጫማ፣ በእጁ ባንጠለጠላት ፌስታል ሦስት ዳቦዎች ይዞ፣ "እሽ አብርሽ ሥራ ጥሩ ነው" አለኝ ተማሪ መሆኔን ረስቶታል:: ደግሞ አይኔን ማየት አልፈለገም:: እህቴ ያዘጋጀችውን ጉርሻ ወደ ሰሀኑ መልሳ ፍዝዝ ብላ ቀረች::

ፒተር ያመጣልኝን ስልክ እየጎረጎርኩ እህቴን ከትካዜዋ ጋር ረሳኋት:: ፓ እንዴት ቀውጢ ስልክ ነው...!!

"እኔ የምልሽ ይሄ ስልክ ዋጋው ውድ ነው አይደል ?" አልኳት በማዳነቅ:: እህቴ በትዝብት እያየችኝ፣ "ሰባት መቶ ዶላር..." አለችኝ ድምፅዋ ሻከሮ ነበር::

"ወደኛ ብር ሲመነዘር..." ብዬ ሳሰላ...::

"ወደ እኛ ብር ሲመነዘር ሲራጅ ለአማማ ቡና ብሎ ከሚሰጠኝ ሁለት ብር አይበልጥም:: ሲራጅ ለአብርሽ ብሎ ይሰጠኝ ከነበረው አስከርቢቶ አይበልጥም" ብላኝ ወደ መታጠቢያ ቤቱ ሄደች፣ ፒተርና ልጁ ታጥበው ሲወጡ እሷ ልትታጠብ ሰትሄድ መንገድ ላይ ተላለፉ:: ፒተር ፈገግ አለላት፣ እህቴ እንደማታውቃቸው ዝም ብላ አልፋቸው ሄደች::

ሲራጅ አስከርቢቶ ይልከልኝ እንደነበር ትዝ አለኝ:: ያኔ በልብስ፣ በጫማ፣ በደብተር መያዣ ቦርሳ ይበልጡኝ የነበሩ ሕፃናትን የማስቀናበት ብቸኛ ንብረቴ ሲራጅ ያመጣልኝ የነበረው ቀይ አስከርቢቶ ብቻ ነበር:: ሙሉ ቀይ ቢክ አስከርቢቶ::

ስልኩን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጬ ወደ መታጠቢያ ቤቱ በትካዜ አመራሁ:: እህቴ እያለቀሰች ነበር:: ከአሜሪካ በመጣልኝ ስኒከር ጫማ ሲራጅ የሚባል አራት ዓመት ተቀብሮ የኖረ ፈንጅ ረገጥኩ:: ሲመቸን የምንረግጠውን አናውቅ ! ረገጥኩት - ቡምምምምምምምምምምምምምም... ቁስለኛ እህቴ፣ ሙት እህቴ!

እፍረት በተቀላቀለበት ጉጉት። ያስታውቃል በሆዷ አፍናው የኖረችውን አሳት በሰው አገር ስታምሰለስለው የኖረችውን ህመም ዛሬ ከእኔ ከወንድሟ ጋር ልትካፈለው እንደተነፈሰችው ሰው መሰየት !!

እውነቱን ለመናገር ሲራጅን ረስቸው ነበር፣ "እኔንጃ ካየሁት ቆየሁ። የሆነ ሰዓት ላይ ግን ጀዝበ ነበር" አልኳት በግዴለሽነት። ዩኒቨርስቲ ገብቼ ስለነበር በእርግጥም ካየሁት ሁለት ዓመት አልፎኝ ነበር። ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁት ሰፈር ድንገት ከሥራ ሲገባ ነበር። ጅዝብ ብሎ ኮሌታዋ የነተበ ሸሚዝ ጉልበቱ እና መቀመጫው ላይ የሳሳ ጅንስ ሱሪ በጥቁር ተረከዟ በተጣመመ ጫማ፣ በአጭ ባንጠለጠላት ፌስታል ሦስት ዳቦዎች ይዞ፣ "እሽ አብርሽ ሥራ ጥሩ ነው" አለኝ ተማሪ መሆኔን ረስቶታል። ደግሞ እይኔን ማየት አልፈለገም። እህቴ ያዘጋጀቸውን ጉርሻ ወደ ሰሀኑ መልሳ ፍዝዝ ብላ ቀረች።

ፒተር ያመጣልኝን ስልክ እየጎረጎርኩ እህቴን ከትካዜዋ ጋር ረሳኋት። ፓ እንዴት ቀውጢ ስልክ ነው...!!

"እኔ የምልሽ ይሄ ስልክ ዋጋው ውድ ነው አይደል ?" አልኳት በማዳነቅ። እህቴ በትዝብት እያየቸኝ፣ "ሰባት መቶ ዶላር..." አለችኝ ድምፅዋ ሻከሮ ነበር።

"ወደኛ ብር ሲመነዘር..." ብዬ ሳሰላ...።

"ወደ እኛ ብር ሲመነዘር ሲራጅ ለእማማ ቡና ብሎ ከሚሰጠኝ ሁለት ብር አይበልጥም። ሲራጅ ለአብርሽ ብሎ ይሰጠኝ ከነበረው አስክርቢቶ አይበልጥም" ብላኝ ወደ መታጠቢያ ቤቱ ሄደች። ፒተርና ልጁ ታጥበው ሲወጡ እሷ ልትታጠብ ስትሄድ መንገድ ላይ ተላለፉ። ፒተር ፈገግ አለላት፣ እህቴ እንደማታውቃቸው ዝም ብላ አልፋቸው ሄደች።

ሲራጅ አስክርቢቶ ይልክልኝ እንደነበር ትዝ አለኝ። ያኔ በልብስ፣ በጫማ፣ በደብተር መያዣ ቦርሳ ይበልጡኝ የነበሩ ሕፃናትን የማስቀናበት ብቸኛ ንብረቴ ሲራጅ ያመጣልኝ የነበረው ቀይ አስክርቢቶ ብቻ ነበር። ሙሉ ቀይ ቢክ አስክርቢቶ።

ስልኩን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጬ ወደ መታጠቢያ ቤቱ በትካዜ አመራሁ። እህቴ እያለቀሰች ነበር። ከአሜሪካ በመጣልኝ ስኒከር ጫማ ሲራጅ የሚባል አራት ዓመት ተቀብሮ የኖረ ፈንጅ ረገጥኩ። ሲመቸን የምንረግጠውን አናውቅ ! ረገጥኩት - ቡምምምምምምምምምምምምምም ቁስለኛ እህቴ፣ ሙት እህቴ!

እግዚኦኦኦኦኦኦኦኦ 11

እማማ የውብዳር ጓደኛዬን ያሬድን ልጅ ልከው አስጠሩት እና እንዲህ አሉት፡-

"ያሬድ ምንስ ባልወልድህ እናትህ አልነበርኩም ? አሳድጌ አሳድጌ እንዲህ ከሰው በታች ታደርገኛለህ...?"

"ምን አደረኩ እማማ የውብዳር..?"

"እሄሄ...! የምትከፍለው የላትም፣ ያጣች የነጣች ደሃ ናት ብለህ ነው...!?"

"ኧረ እኔ ለማንም እንደዚህ አላልኩም !" አለ ግራ ገብቶት እኔን እየተመለከተ፡፡ አላለም እንድልለት ፈልጓል፡፡

"ነው እንጂ !! ምን የመሳሰለ የመልአከ፣ የፃድቃን ሰማእታት ሥአል በየሰዉ ቤት ስትሰል፣ የኔን የየውብዳርን ቤት ሰይጣን ይፈንጭበት፣ ዲያቢሎስ ከነሠራዊቱ ይፈንጭበት፣ ሌጌዎን እስከሰታ ሲያወርድበት ውሎ ይደር ብለህ ነው የእኔን ቤት ለይተህ የተውከው?!" አሉት በትዝብት እያዩት፡፡ እንደሚጠቀሟቸው ቃላት ከብደት ግን ድምፃቸው አያስፈራም ነበር፡፡ እንደውም የሆነ የሚያስቅ ዜማ ነበረው፡፡

"እእእ...ለዚህ ነው እንዴ ...ኧረ ጣጣ የለውም ከፈለጉ ከማንም አስበልጬ የፈለጉትን አሥልሎታለሁ!" አለ ፀጉሩን እያፍተለተለ በፈገግታ፡፡

"ተባረክ የኔ ልጅ...! ብሩክ ሁን !!"

"አሜን" አለ ያሬድ፡፡

"እኔ ደሞ እንዲህ ትልቅ ባለሙያ መሆንህን የት አባቴ አውቄ ! መንደር ለመንድር አዚህ ቦዘኔ ጋር ተያይዘህ ስትዞር (እኔን በአገጫቸው እየጠቆሙ) 'አይ መባከን !' አላለሁ፡፡ ለካ አንተ

እንዲህ እጅ ወርቅ ነህ። ገና ትላንት አይደለም እንዴ የሰማሁት...፤ እች ማናት ኮማሪዋ...እዚህ ታከሲ መቆሚያው ጋ ድራፍት ቤት ያላት...ሌዲያ ስሚ አይያዝልኝም..." አያሉ አንዴ መሬት አንዴ ሰማይ ሲመለከቱ፤

"ናርዶስ !" አልኩ ሳይጠይቁኝ።

ፈገግ ብለው "አ...ዎ ናርዶስ" አሉና ወሬያቸውን ሊቀጥሉ ካሉ በኋላ የሆነ ነገር ትዝ እንዳለው ሰው ኮስተር ብለው ወደኔ በመዞር "ደህና ሰው ቢጠይቅህ አታውቅም እንጅ ኮማሪና ጫት ነጋዴማ አይጠፋህም" አሉኝ።

ያሬድ አቀርቅሮ በሳቅ ፍርስርስርስ !! ኮማሪና ጫት ነጋዴ ደህና ሰው አይደለም ያለው ማነው?

"... እናልህ እሷ ቤት የሳልከውን የጊዮርጊስ ሥዕል በቀደም መሃበርተኛው ሁሉ እያየ ጉድ ሲል...'ማነው የሳለው ?' ብላቸው የጉልላት ልጅ አሉኝ...እሃ ጉልላት እች የኔ ጉልላት? ...አሱማ ምን የጉልላት ልጅ ነው? የኔው የራሴው ልጅ አይደለም እንዴ ? ብዬ መጣሁልህ። ሞቸስ ባልወልድህም ልጄ ነህ፤ ንፍጥህን ጠርጌ ያሳደኩህ" አሉ።

"ልክ ነው" አለ ያሬድ እየተቅለሰለሰ።

"እሁ እሁ እሁ እሁ እ ሁ..." ብለው ሳል የሚመስል ሳቅ ሳቁና ቀጠሉ፤

"...መቸስ ያ...ጊወርጊስ ማንም ቤት የለ !! የፈረሱ ግርማ ሞገስ...የዘንዶው ርዝማኔ_ነብሰ ያለው እኮ ነው የሚመስለው ! ተባረክ ! ...መሃበርተኛው ሁሉ ነው የመረቀህ። ሞቸስ የእኛ መሃበርተኞች ምርቃት ብቻ የት እና የ....ት እንደሚያደርስህ...!! ቀላል ማኅበር እንዳይመስልህ! የዚች የ....አስተማሪዋ ልጅ ማነው ስሙ?" ስሙ ጠፋቸው፤

"ኢድማሱ" አልኩና አስታወስኳቸው።

"እንቶ ሌላም ሥራ የለህ የመንደርተኛ ስም አጥና" ብለው ከወረቆኝ በኋላ ወሬያቸውን ቀጠሉ፤ "እናልህ እሱ የዛሬ ሦስት ዓመት እኛ ማኅበር ላይ ምን የመሰለ የፅዋ ልብስ አምጥቶ ሰጠ - ስእለት ነበረበት። ታዲያ መኅበርተኛው አንድ ባንድ መረቀው። እሁን አማሪካ ነው ያለው። አንቱ የተባለ ሃብታም ሁኗል አሉ። በሦስት ዓመት! ሰው በሰላሳ ዓመት የማይደርስበትን ቂብ ብሏል።" አሉና ስለ ማኅበራቸው ምርቃት ከፍ ያለ ዋጋ በዝርዝር ማስረጃ አያጣቀሱ አወጉ።

"አሁን እንኳን የጠራሁህ እ..." ስሙ ጠፋባቸው።

"ያሬድ" ብዬ አስታወስኳቸው።

በብስጭት እየተመለከቱኝ "ወቸ ጉድ ! ባለቤቱ እያለ አንተ ቱሩጁማን ነህ ?..." ያሬድ አሁንም

በላቀ ፍርስስስ - አንዳቀረቀረ !

ከዚህ ጊዜ በኋላ ለረኽም ጊዜ 'ቱረጁማን' እያለ ይጠራኝ ነበር።

"...አሁን ሚመጣው ታህሳስ በ27 የኔም የመድኃኒያለም ዝክር አለች። እንደው የመደኃኒዓለምን ሥዕል...ይሄ...ቤት የሚያንኳኳበትን እንድትሥልልኝ ነበር..." አሉት።

"ፒስ !" አለ ያሬድ።

"ምናልከኝ ?"

"ጭጣ የለውም !" አላቸው ፈጠን ብሎ።

ያሬድ ሥዕል ሳልልን ሲሉት ሲነጫነጭ ነበር የማውቀው። አሁን ፈጠን ብሎ መስማማቱ ገርሞኝ ቀጥ ብዬ ተመለከትኩት። ፊቱ በፈገግታ ተጥለቅልቆ ነበር። "እችን ሴትዮ ቀልቡ ወዷቸዋል ማለት ነው" ስል አሰብኩ። በሥዕሉ ተስማሙና ለያሬድ ቀብድ መቶ ብር ሰጡት።

*** *** ***

ያሬድ ጓደኛዬ በጣም ጎበዝ ሠዓሊ ነው። "ሞናሊዛን በግራ እጇ አስላታለሁ" ይላል ችሎታው ላይ ጉራ መርቆበት ሲያወራ። ሥዕል አልተማረ፣ ሠዓሊ ዘመድ የለው፣ ሥዕል ሲሳል አይቶ አያውቅ - ከመሬት ተነስቶ ሠዓሊ ሆነ። ከመሬት የተነሳነው እንኳን አብረን ነበር። እርሳስ ይዘን የሴት ምስል መሣል ጀመርን። እኔ የምስላቸው ሴቶች እግራቸው እያርፍም፤ አንዴ ወደግራ ይንሻፈፋሉ፤ አንዴ ወደቀኝ ይወላገዳሉ...ሌላ ጊዜ ቀኝ እግራቸው አሪፍ ይሆንና ግራው ይዛነፋል - በተለይ የሱሪ ለባሽ ሴቶችን ሥሥል አልሆንልህ አለኝ።

ያሬድ ታዲያ "አንተ አርፈህ ቀሚስ ለባሽ አትስልም እንዴ...ቀሚስ እንኳን ያንተን ቀሽም የሥዕል ችሎታ የስንቶቹን ደጋን እግር ሸፍኗል" ሲለኝ ከዚህ ሁሉ ከወገብ በላይ ብስላቸውስ ብዬ ስሞከር አሁንም እኔ የምሥላቸው ሴቶች አይናቸው አያርፍም፤ ይንሸዋረራሉ፤ ይጠናገራሉ። ፊት ለፊታቸው የልብ ቅርፅ አሥልና ወደልቡ እንዲያዩ ላደርጋቸው ስሞከር አይናቸው የእኔን ልብ ትቶ ያሬድ ከጎን ወደሳለው መኪና ይመለከታል። ሰለቸኝና አርግፍ አድርጌ ተውኩት። ያሬድ "መኪሊትህ አይደለም በቃ!" ሲለኝ ጭራሽ ተስፋ መቁረጤ ጉልበት አገኘ።

ያሬድ ግን ከሴቶቹ ሥዕል ወደ ሞናሊዛ አደገ። ይባስ ብሎ ቅድስት አርሴማን ሁሉ ቁልጭ አድርጎ ሳላት።እንደውም በእጇ የያዘችውን ፅዋ ረስቶት እኔ አስታውሼው ነው የሣለው። ከዛ ድንግል ማሪያምን ልጇን እንዳቀፈች ሣላትና መንደርተኛው ሁሉ "...ይሄ ልጅ የት ይደርሳል" እያለ ሲጠብቀው ሰላማዊት ለምትባል ሰምንተኛ ከፍል አራት አመት ሊደገመች ልጅ "ወደ ዘጠነኛ ከፍል ተዘዋውራለች" የሚል 'ፎርጅድ' ካርድ ሲሰራ ተይዞ ሁለት ዓመት ታሰረ።

በዕርግጥ ያሬድ በጣም ነበዝ ከመሆኑ የተነሳ ሰላማዊት ራሷ የእውነት ወደ ዘጠነኛ ከፍሎ ያለፈች መስሏት እኔና ያሬድን ምሳ ጋብዛናለች:: "ወጣ ወጣና እንደሸንበቆ ተንከባለለ እንጂ መቀጫ" እንዲሉ ያሬድ ማረሚያ ቤት ሰነበተ::

ከአስር ቤት ሲወጣ ፍልስፍና ጀምሮ ነበር:: በተለይ ከአግዚያብሔር ጋር 'መሳፈጥ' አበዛ:: እረ እንደውም ከሥዕሉ ወደ ፍልስፍናው አዘነበለ:: አገር የሚያከል ሽራ ይወጥርና ምን ተዓምር ሊሥል ነው ብዬ ስጠብቅ መሐል ላይ አንዲት በዓይን አንኳን ለማየት የምታስቸግር ጥቁር ነጥብ ብቻ ጠብ አድርጎ "ጨረስኩ" ይላል::ብስጭት ብዬ "ምንድን ነው ይሄ ?" አለዋለሁ:: ራቅ ብሎ ሸራውን በትኩረት ሲመለከት ይቆይና "...በዚህ ግዙፍ ዓለም ላይ የሰራኸውን ብትሰራ ነጥብ ነህ...፤ ሌሎች ነጥቦች ጋር ካልተደመርክና ካልተሰለፍክ መስመር የለም ሥዕል የለም...፤ ሁለት ዓመት ስታሰር እኔ ማለት እች ነጥብ ነበርኩ" ይላል:: ብሩሹን አነሳና ከነጥቧ ጎን አንዲት ሌላ ነጥብ አስቀምጥና "እኔ ነኝ" አለዋለሁ፤ እንሳሳቃለን:: ወጣ ብዬ ስመለስ ግን እኔ ሸራው ላይ የለሁም:: መስመር መሆን ካልፈለገ የራሱ ጉዳይ ብዬ አተወዋለሁ !

እየቆየ ያሬድ የሚሥላቸው ነገሮች ሁሉ ግራ አጋቢ ሆኑ:: አንደኛው ዓይኗ ሰፈድ፤ ሌላኛው አይኗ አስር ሳንቲም የሚያከል፤ ቁመቷ ከመርዘሙ ብዛት ዛፍ የመሰለች ሴት ይሥልና "ሰው አድሜው በጨመረ ቁጥር ዕይታውም ይሄው ነው፤ አንድ ዓይንህ ከዘመንህ ጋር ያድጋል፤ አንድ ዓይንህ ግን የማያድግ፤ የማይቀየር፤ ትላንትህን ብቻ እየተመለከተ እስከ ዕለተ ሞትህ ይኖራል" ይለኛል፤ ምኑም አይገባኝ::

ይቀጥላል የያሬድ ሥዕል:: አንድ ቀን ማሲንቆ ሣለ:: ቋሚው ላይ የቆመችው አንዲት መለሎ ሴት ስትሆን እንደጭራ ቋሚው ጋር ተቋጥራለች:: ከጎኗ ወገቡ የጎበጠ ወንድ ልክ እንደ ማሲንቆ መምቻ ደጋን ተሰሏል::

"ይሄ ደግሞ ምንድን ነው?" አልኩት በማናናቅ::

"ይሄስ ምንድን ነው ?" ብሎ መልሶ ጠየቀኝ የእኔን ጭንቅላት በሁለት እጁ ይዞ እየወዘወዘ::

"እናትን ልቀቀኝ ወደዛ" አልኩና ገፋሁት::

እሱ ግን የበለጠ አጥብቆ ይዞኝ "ሁልጊዜ ማብራሪያ አትጠይቅ፤ ሥዕል የሠአሊው ብቻ አይደለም፤ እንደውም የተመልካቹ ነው:: እንደመሰለህ ተርጉመው፤ እንደገባህ ተንትነው" ብሎ ወደ ጎለዬ ገፋኝ፤ ተንገዳግጄ ቆምኩ::

ያሬድ አልጨከነም፤ ስለሥዕሉ እንዲህ አለኝ:-

"ስለፍቅር አንዱ ይቃና ዘንድ አንዱ እንዲንበጥ ግድ ይላል:: ፍቅር ዝቅ ማለትን ይጠይቃል:: በአንዱ ዝቅታና በሌላው ከፍታ የፍቅር ዜማ ይደምቃል" አለኝ:: ማሲንቆና የማሲንቆ መምቻ፤

ሰውና ሰው ሁኖ እንዴት እንደታየው አማዜር ይወቅለት። እንዲሁ ልከራከረው ብዬ "ሻኮሊንና የሻኮሊን መሟወቻ ዘንጉ ሁለቱም ቀጥ ያሉ ናቸው ግን አራፍ ዜማ ይፈጥራሉ የግድ መንበጥ ለምን አስፈለገ ?" ብዬ በንግግሬ በብልሃት ትከሻዬን ነቀነቅ አደረኩ።

"ተሳስተሃል ! የሻኮሊን ሳጥኑ ትከሻ ላይ ዘና ብሎ አርፎ መሟወቻው ሲንከራተት ነው ዜማ የሚፈጠረው፤ ሁለቱም ሰው ትከሻ ላይ ቁጭ ቢሉ ምንም አይፈጠር ነበር፤ ምንም !" አለና ተነስቶ ወጣ።

••• ••• •••

ጓደኛዬ ያሬድ ታህሳስ 23 የአማማ የውብዳርን የክርስቶስ ሥዕል ስሎ እንደጨረሰ አብረን ወደ ቤታቸው ሄድንና አሰረከብናቸው !! ደስ ብሏቸው ፈታቸው በፈጣሪያ ደምቆ ሁላታችንንም ከመረቁን በኋላ ሥዕሉን የተሸፈነበትን ወረቀት ቀስ አድረገው ገለጡት። ገልጠው ሲያዩት ቤትዮዋ ግራ ገባቸው !! ራቅ ቀረብ፡ ቀረብ ራቅ እያደረጉ ለዩትና ፈጣሪያቸው ከፈታቸው ላይ ከሰሞ እንዴ ያሬድን፡ እንዴ እኔን፡ እንዴ ሥዕሉን እያፈራረቁ ቃኙን። ልቤ በፍርሃት ተውጦ ሲዘል ይሰማኛል።

"ያሬድ!" አሉት

"እቤት ማዘር!" አላቸው በፍፁም መረጋጋት ፀጉሩን እያፍተለተለ።

"ክርስቶስ በር እያንኳኳ አልነበርም የተባባልነው ?"

"ነበር" መለሰ ያሬድ አሁንም ረጋ ብሎ።

ቀረብ...በጣም ቀረብ አድርገው ሥዕሉን በትኩረት ተመለከቱትና_

"እንዲህ ያለ መድሃኒዓለም አይቼም ሰምቼም አላውቅም" አሉ ግራ ተጋብተው።

ያሬድ መለሰላቸው፤ "እሱማ መድሃኒዓለምን ማን አየው ብለው_ያው ቢቆሉ መሰረት እንስለዋለን አንጂ" አለና ያሬድ አስር ቤት የጀመረችውን ፍልስፍና መስኮት ከፈተላት። በዕርግጥ ያሬድ ሥዕል ሲስል አስተያየት መቀበል አይወድም። "ማመልከቻ የምፅፍ መሰለህ እንዴ እየነገርከኝ የምስለው?" ይላል። ቢሆንም ይሄን የአማማ የውብዳርን ከርስቶስ ሲስል "ኧረ ይሄ ነገር አችን ሴትዮ ያሳብዳቸዋል" ብዬው ነበር። ያሬድ ግን ከሥዕሉ ላይ አይኑን ሳይነቅል_"ጉቢቷቸው ካበዱ አንድ ነገር ነው" ብሎ አስተያየቴን አጣጣለው። ከዛም "የሥዕልም ይሁን የሌላ ኪነጥበባዊ ፈጠራ አላማው ሰዎችን በሰሩት መንገድ ላይ ሲረግጡ እንዲኖሩ ጫማ ማቀበል አይደለም፤ አዳዲስ ጫካዎችን መንጥሮ አዲስ መንገድ መፍጠር ነው፡ ነገሮችን ከተለየ አቅጣጫ ማሳየት ነው። አዲስ የሕይወት ቅመም፡ አዲስ ጠብ የሚል ቱይዳ ያለው እውነት..."

"እረ ባክህ አንተ ልጅ! ለአንዲት ባልቴት የአንተ ፍልሰፍና አይገባም፤ ያውም በአምላት ሃ ነገሮች ዙሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ ብትፈላሰፍ 'እብድ !' የሚል ካባ ነው የሚያስደርብልህ፤ ለዛውም ከዱላ ከተረፍክ ነው" አልኩት።

"ፍልሰፍና ዋጋ ያስከፍላል። ዓለማችንን የቀየሩ ፈላስፎች ዋንጫ አይደለም የተሸለሙት፤ መርዝ የተሞላ ፅዋ እንጂ። አንዲያውም አልሸሹም፤ በድፍረት ጨለጡት እንጂ። ስለ አውነት ማፈግፈግ ወደ ምንም መድረስ ነው፤ ደፋር መሆን አለብህ።" እያለ የማያባራ ዲስኩሩን ሲግሞጎ 'የራስህ ጉዳይ!' ብዬው ዝም አልኩ። ይሄው አሁን አማማ የውብዳር ጋር ተፋጠጠ፤ ፈላስፋው ከነተፈላሰፊበት ስዕሉ።

ሥዕሉ እንዲት ከፍል ቤት ውስጥ ያልተነጠፈ አልጋ፣ ግማሽ ብርድ ልብሱ መሬት ላይ ተንዘላዞ አዛው መሬቱ ላይ ግማሽ ገፆቹ የተገነጠሉ መጽሐፍ ቅዱስ ወድቋል። የቆሸሹ ካልሲዎች በየቦታው ተበታትነዋል። በጣም ብዙ የቢራ ጠርሙሶች በስዕሉ ግራ በኩል ይታያሉ። የቢራ ጠርሙሱ አጠገብ አንድ አግር የሴት ጫማና የጡት ማስያዣ ወድቋል። የምታበራ የቃል ኪዳን ቀለበት ደግሞ በጎኑ ከወደቀ የወንድ ጫማ ስር ትታያለች። የተራቆተች ሴት ሥዕል ከተዘበራረቀው አልጋ በላይ ተለጥፏል። አልጋው ላይ ከአንሶላ አፈትልኮ የወጣ የሴትና የወንድ አግር ይታያል። ኮሚዲኖ ላይ በርከት ያለ የአሜሪካ ዶላር ዝርከርከ ብሏል። ከዚህ ሁሉ መዝረክረክ ፊት ለፊት መሐል ወለሉ ላይ ኢየሱስ ከርስቶስ በሁለት እጁ አራሱን ይዞ ቆሟል። ...ይሄ ነው ሥዕሉ!

"ጌታ ራሱን ይዞ ታይቶም ተሰምቶም አያውቅ !" አሉ አማማ የውብዳር ባለማመን። ቀጠል አደረጉና "ለመሆኑ በሩ የት አለ ? የሚንኳኳው በር የት አለ ?" ሲሉ ጠየቁ በቁጣ።

ያሬድ ጓደኛዬን እስር ቤት የለከፈችው ፍልሰፍና ታስለፈልፈው ጀመረች:

"እ...ከርስቶስ በየቤታችን ከገባ ቆየ። አሁን ይሄን ሁሉ ዘመን ቤታችንን ዘግተን ስናደርግ የቆየነውን ጉድ፤ እንዲሁም የኖርንበትን መዝረክረክ፤ መጨማለቅ፤ ማስመሰል እና መታበይ አይቶ ራሱን ይዞ እግዚዚዚ

ግድግዳው ጋር ከተጋፈጠ በኋላ ነበር በሩን አግኝቶት የወጣው፤ ወደ ታች ወደ ወጡ ቤት ተፈተለከ::

ፈላስፋ የቀረበለትን መርዝ በድፍረት ሲጨልጥ እንጂ እንዲህ እንደ አቦሸማኔ ሲሮጥ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም:: ያዘው ! ...አረሰቶትል ሮጠ፡ ሶቅራጥስ የነሳራን የልብስ ማጠቢያ ጎማ ዘለለ፡ ኮንፊሽየስ የአማማ ዙሪያሽን ስጥ ረጋግጦ አለፈ፡ ዲዮጋን በአባ እጅጉ ቤት ወደ ወንዙ ታጠፈ፡ አሶ አንዱን መንገደኛ ቁስ ጫትሯቸው ፈረጠጠ ...እኔም ተከተልኩ_

"ባሞር ቅር !" እማማ የውብዳር ተራገሙ...

"በመሣበር የመረቁትን በየግላቸው እየረገሙ መሣበራቸው እንዴት ፀንታ ትቆማለች ?" አለ ያሬድ::

"ባከሀ አርፈሀ ሩጥ:: የፀበሉ ቀን በመሣበር ይረግሙሃል" አልኩት፡ አበሳጭቶኝ ነበር:: እየሸሸ አቃቂር ያውጣል እንዴ?!

12 ንፋስ ወዴት ነህ ቢሉት ማርና ወተት ወዳለበት

እማማ አረጋሽ ቤት ሩጫ ልናይ ተሰብስበናል:: ልጃቸው ከውጭ አገር ትልቅ ቴሌቪዥን ስላመጣችላቸው በሳቸው ቴሌቪዥን ማየት የሩጫ ጥም ይቆርጣል:: መቸስ ቴሌቪዥኑን ግድግዳ በሉት:: የእማማ አረጋሽ ቤት ከሦስት ግድግዳና ከአንድ ቴሌቪዥን ነው የተዋቀረው ቢባል ማጋነን አይሆንም:: ባለቤታቸው አቶ ፈንታው ነፍሳቸውን ይማራቸው ዜና ለማየ በየቀበሌው እንደዞሩ ይሄን ዓለም ሳያዩ ሞቱ፤ ሳያልፍላቸው ሞቱ:: "ቁጭ ብለው ቴሌቪዥ በማያ ጊዜያቸው ሞቱ" ይላል ጎረቤቱ::

ጀመረ ሩጫው - ገንዘቤ ዲባባ፣ አበባ አረጋዊ ቴሌቪዥኑን እየሞሉ ደግሞ ራቅ እያሉ...

እኛም "ገንዘብ...ገንዘብዬ...ገንዘባችን...ሩጭ አሳያቸው...አይዞሽ" እያልን፣ ያው አበባ አረጋዊ ፈትለ ብላ ወርቁን ወሰደችው:: ያውም የስዊዲን ማልያ ለብሳ በስዊዲን ባንዲራ ተውባ ! ብዙዎቻች ቀዝቀዝ ሰንል እማማ ወለላ "እልልልልልልልልልልልልልል አሰይ አሰይ" አሉ (ጎረቤት ናቸ

"እንዴ ለስዊዲን እኮ ነው የሮጠችው" ብንላቸው፣

"ይሁና ልጃችን ናት" አሉ::

እማማ አረጋሽ ታዲያ፣ "አይ ወለላዬ አሁንስ እማማ ፅጌን መሰልሽኝ" አሉ::

ስለ እማማ ፅጌ ለመስማት ጆሯችን ቆመ::

"ማናቸው እማማ ፅጌ ?"

እማማ አረጋሽ ስላነሷቸው ሴት ታሪክ አወጉን...

*** *** ***

በድሮ ጊዜ እኛ ሰፈር እች አሁን ጋሽ አቁባይ ገፋ አድርገው ያጠሯት ቦታ ላይ አንዲት የእማማ ፅጌ ድንጋይ የምትባል ጥቁር ድንጋይ ነበረች - አጠገቧ ደግሞ የላስቲክ ቤት:: አሁንም አጥሩ ውስጥ ድንጋዩ አለ:: ታሪክን ቢያጥሩት ያው አጥሩ ውስጥም ሁኖ ቢሆን ይጮሃል::

እማማ ፅጌ አንዲት ልጅ ነበረቻቸው:: መቼስ ቁንጅናዋ አይወራም:: መልአክ፣ መልአክ በሏት:: አንዲት ልጃቸው ናት፣ አባቷ አይታወቅም:: እችው ባልቴት እናቷ አዚህች ድንጋይ ላይ ተቀምጠው ድንቾም ቲማቲምም እየቸረቸሩ አሳደጓት:: በኋላ ህመሙም አርጅናውም ሲጫጫናቸው ግማሽ ችርቻራ፣ ግማሽ ልመና በሆነ ሕይወት ይውተረተሩ ጀመር ::

መቼስ ልጅቱ መንገድ ዳር እየኖረች ልዕልት መሰለች:: የመንደሩ ሴቶች ጠርሙስ ሙሉ ቅባት ጨርሰው፣ ያማረ ለብሰው፣ ትኩስ በልተው ጠብ ያላለላቸው መልክ አዚህች መንገድ ዳር ላስቲክ ከልላ በምፅዋት የምትኖር ልጅ ላይ ፈሰሰ:: ፀጉሯ ተዘናፈለ፣ ዳሌዋ ሞላ ወንዱ ሁሉ ዓይኑ ይቀላውጣት ጀመረ::

አንድ ምሽት እማማ ፅጌ ኡኡ አሉ:: መንደርተኛው ወደ ላስቲኳ ቤታቸው ተሰበሰበ:: ልጅቱ የለችም ጠፋች:: መንደርተኛው እማማ ፅጌ ጋር በመሆን ሳምንት ሙሉ ፈለገ:: የለችም:: ቆንጆዋ፣ ባልቴት እናቷን ትታ ምጥ ትግባ ሰምጥ አልም ድርግም አለች:: ጎረቤቱ ተሰፋ ቆርጦ ወደ የራሱ ጉዳይ ቢመለስም ሚስኪኗ ባልቴት ግን ከዛች ቀን ጀምሮ ለአስራ አንድ ዓመታት ታየች በተባለበት ተንከራተቱ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የቀራቸው ከተማ የተረፋቸው መንደር የለም::

በየደረሱበት የዕለት ጉርሳቸውን እየለመኑ ፅንፍ የለሽ በሆነ የእናት ፍቅር ልጃቸውን ፈለጉ::

በአስራ አንደኛው ዓመት ልጃቸው ውጭ አገር ኖራ እንደተመለሰችና አንድ ባለፀጋ ልታገባ ሰርጉ እየተደገሰ መሆኑን ከሁነኛ ሰው ሰሙ:: "አይ ልጄ ፈልጋ አጥታኝ ነው" አሉና ወደ አዲሳባ አቀኑ:: አዲሳባ እንደገቡ አንድ ጥግ ላይ ከያዟት ፌስታል ለከት ቀን ብለው ያስቀመጧትንና ላለፉት አስራ አንድ ዓመታት ለብሰዋት የማያውቋትን ቀሚስ አውጥተው ለበሱ:: ራሳቸውን አየት አደረጉና፣ "እመቤት መሰልኩ አይደለም እንዴ፣ ልጄንማ አላዋርዳትም" አሉና ፈገግ አሉ::

ልጃቸው 'አለች' ወደተባለበት ቤት ሳያርፉ ጉዞ ጀመሩ:: ቤተ መንግሥት የመሰለው ቤት በሁለት ዘበኞች ይጠበቃል:: "የልጄ ቤት" አሉ በኩራት ፊት ለፊት ቆመው፤ ከዛም ጠጋ ሲሉ "እግዜር ይስጥሽ" አለ አንዱ ዘበኛ፣ እማ ፅጌ ይሄን ቃል ሺ ጊዜ ሰምተውታል የዛሬው ግን ለየት አለባቸው::

ሳቅ ሳቅ አላቸው:: ይሄ ጥበቃ ከደቂቃዎች በኋላ ጎንበስ ቀና ሲልላቸው ታያቸው፣

"ልጄዋ እኔ እንኳን የመጣሁት ቢጣዬን ብዬ ነው"

"ቢጣ ማናት?"

"ልጄ ናታ እዚህ ቤት እንደምትኖር ነግረውኛል"

"እንደዛ የምትባል ሴት የለችም እዚህ እማማ"

ጢጋ አሉትና፣ "ሙሽራይቱ ማነው ስሟ"

"እሜቴ ስማቸው ብሩክታዊት ነው"

ግራ ተጋብተው ከግቢው በር እንደቆሙ ቢጣ ከሸበላ ባለቤቷ ጋር ውሃ በመሰለ መኪና ጣ አለች። ራሷ ናት፣ እናትና ልጅ ፊት ለፊት ተፋጠጡ። እናት ችለው መቆም አልቻሉም ጉልበታቸው ተብረከረከ፣ "ቢጣዬ ያይኔ አበባ..." ብለው ወደ መኪናው በእንብርክክ ቀረቡ። ልጅ ኮስተር አለች፣ የመኪናውን መስተዋት ዝቅ አደረገች፣ ጥቁር መነፅሯን ወደ ፀጉሯ ኪ ራሷን መታ አድርጋ ውብ ፀጉሯን ወደ ጎን አለችና፣

"ምንድነው?" አለች ፊቷን አጨፍግጋ።

"ቢጣዬ...እናትሽ ስንከራተት ኖሬ ይሄው መጣሁልሽ። ሄድኩ አይባልም? ሚዳ ላይ ጣል አድርገሽ ማን አላት ብለሽ..."

"ማነህ ወደዛ ውሰዳት! የማንም ወፈፌ እየመጣ...እንሂድ ሃኒ" አለች ቢጣ መኪናውን ወደ ሚያሽከረክረው ሰው ዞር ብላ...።

"ሃሃሃሃሃሃ ሃኒዬ አትበሳጭ አዲሳባ በነዚህ ዓይነት ፈጣጣዎች ነው የተሞላው" ነዳጁን ሰጡ ፈትለከ። እማማ ፅጌ ተንበርከከው ቀሩ። ራሳቸውን አይተው "ልጄ አስከተረሳኝ ተጎሳቁያለሁ ማለት ነው?" አሉ - በልጃቸው አልፈረዱም።

አስከሰርጉ ቀን ከግቢው ፊት ለፊት ካለች በረንዳ ላይ ዝናብና ፀሐይ እየተፈራረቀባቸው ልጃቸው መኪና እንደልብሰ እየቀያየረች ስትገባና ስትወጣ እየተመለከቱ በልጃቸው ምቾትና ታላቅ ደረጃ መድረስ የራሳቸውን መከራ ረስተው ቆዩ። አንድ ቀን እናቴ ብላ አጇን እንደምትዘረጋላቸው ተስፋ በማድረግ። (ልጅ ያላየቻቸው እየመሰለች ሲታልፍ ቆየች ከአንድ ወር በላይ !!)

የሰርጉ ቀን፣ እናት ያችን ቀሚስ ከፈስታላቸው አወጡና ለበሱ፣ የኖሩባትን በረንዳ ጠራረጉ ፈስታላቸው ውስጥ ያስቀመጧትን ትንሽ ብልቃጥ አወጡና በረንዳው ላይ ባለ መስታወት ዓይናቸውን ተኳሉ።

ከሰዓት ሙሽራዋ በነጭ ቀሚስ ተውባ በከፍት መኪና ሱትደርስ ጎረቤቱ፣ ሰርገኛው ሲተረማመስ መሃል መንገድ ላይ ከሰርጉ መኪና ፊት ለፊት እማማ ፅጌ አስከሰታቸውን አወረዱት። ሰው ሁሉ አብድ መስለውት ለአፍታ ትኩረቱን ወደ ባልቴቷ አዞረ። ከሚጫታው ከሙዚቃው በላይ

የዘፈረ ድምፅ ከባልቴቷ ውጣ።

"መጥቶም ሄደችም ደሟ ከደሜ ሲጣፍ ከሲጫ የተፈለፈለ ልጇ ቢጣፍ እኾት - እንኳን ደስ ያለሽ በሉኝ፣ ሙሽራው ልጇን እደራ" አሉና ፈታቸውን እዙረው ወደ በረንዳቸው ሄዱ - ከኋላቸው የእድምተኛው ሳቅና ፈዝ እየተከተላቸው።

ሌሊቱን ሲጨፈር፣ ሲደለቅ ታድሮ ጧት ያደረው ሰርገኛ ሲውጣ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የአስከሬን ማንሻ መኪና ከሰርጉ ቤት ፊት ለፊት ካለ ሱቅ በረንዳ ላይ የእንዲት ባልቴት ሬሳ ሊያነሳ ታየ። ሬሳው ከተነሳበት በረንዳ ንፋስ እየገፋ ወደ ሰርግ ቤቱ በር የወሰደው እንድ ጥቁርና ነጭ ፎቶ ዘበኛው እግር ስር ደረሰ። እናትና ልጅ የተነሱት ፎቶ ነበር።

"ወይ የሰው መመላሰል...ልጅቱ እትዬን እትመስልም...?" አለ ዘበኛው ለጓደኛው፣

"ኤዲያ እሱን ወዲያ ጥለህ ይሄን ያዝ" ብሎ ከሰርጉ የተረፈ ቢራ ሰጠው። ዘበኛው ፎቶውን ጥሎ ወደ ቢራው ዞረ። ነፋስ ጥቁርና ነጩን ፎቶ ወዳልታወቀ ቦታ እየገፋ ወሰደው።

"እኛ ያሳደግናት በማር በወተት..." የሰርግ ዘፈን ከግቢው ይሰማል።

13 'ቆጠራ ላይ ስለሆንን መግባት ከልከል ነው' ኮሚቴው !!

"ይሄ የተከበረና የታፈረ ቤተሰብ ተዋርዷል ! ተቃልሏል ! አገር ከመቃጠሉ በፊት አሁኑኑ ይሄን ጉድ አጣርታችሁ ንገሩኝ" አለ አባቴ እኔንና እህቶቼን ሰብስቦ:: ፊቱ ላይ የሚንቀለቀለው ብስጭት አቤት ሲያስፈራ:: አባባ እንዲህ ሲሆን አይቼው አላውቅም:: ጉዳዩን ከሰማን በኋላ ወዲያው ኮሚቴ ተቋቋመ...::

የኮሚቴው አባላት፤

አብርሃም (ቅፅል ስም የለውም)... ትልቅ ወንድም፣ የቤተሰቡ ብቸኛ ወንድ ልጅና የኮሚቴው ሰብሳቢ::

ናአሚን (ቹቹ)...የቤተሰቡ የመጀመሪያ ልጅ ለአረፍት ከአሜሪካ የመጣች፣ የኮሚቴው ጸሐፊ::

ሮዛ (ቢጢቃ)...የአብርሃም ታናሽ እህት የሁለተኛ ዓመት የዩኒቨርሰቲ ተማሪ፣ ገንዘብ ያዥ::

መቅደስ(ባርቾ)...የአከሰት ልጅ፣ በአባቴ ጥሪ ለዚሁ ጉዳይ ከናዝሬት የመጣች..."ሙድ" ያዥ እና አባል::

ኮሚቴው በቀጥታ ተጠሪነቱ ለአባቴ ሲሆን፣ የስራ ዘመኑም ይህ ጉዳይ እስኪጣራ ብቻ ይሆናል::

አገር ሊያቃጥል የተፎከረበት ጉዳይ...፣

አባቴ አሁድን የሚያሳልፈው በማንበብና በመፃፍ ነው:: ሁልጊዜ የሚያነበው፣ 'የደጃዝማች ወንዱ በቀለ የጦር ውሎ' የሚል መጽሐፍ ሲሆን የሚፅፈው ደግሞ ማመልከቻ !! ለቀበሌ ለከፍለ ከተማ...ለዕድር...ለጡረታ ሚንስቴር...

አንድ ቀን ታዲያ ማመልከቻው ጻፈና ልከ ፈርማው ላይ ሲደርስ እስክሪብቶው አቋረጠ።
"እብረሃም አስቲ እስክሪብቶ እምጣ?" አለኝ እየተጣደፈ።
"ኧረ አልሆንክም አባባ"
"ኤዲያ...የተማረ ሰው እንዴት እስክሪብቶ ከኪሱ ይጠፋል? ጠመንጃ የሌለው ወታደር ማለት ነው..." ብሎ ከተማረረ በኋላ ሀፍረን አሀቴን፣
(ራሴን እምኝ ስለነበር የአባባ ንዝንዝ አልተመቸኝም።)
"ቢጡ እስክሪብቶ እምጭልኝ!" አላት።
"እሺ..."ብላ አሻንጉሊቷን ለእኔ አላቅፋኝ ሮጠች(ፈጣን የኪጂ ተማሪ ነች)።
"እሰይ የኔ እንበሳ፣ ካንተ ትሻላለች" አለ ወደኔ እያየ።
ቆይታ ቆይታ ተመለሰችና፣ "አባባ ቀይ እስክሪብቶ ነው"
"ምነው ይሁን..." አላት ሰስቅ ወደኔ በብስጭት እያየ።
ቆይታ ቆይታ መጣች፣ "ይሄው..." ያመጣችው እርሳስ ነበር።
"እይ...ይሄ ምን ያደርግልኛል? እስክሪብቶ ነው ያልኩሽ" አለ አሁን እሱም ሳቁ መጥቶ ነበር።

"ከተሳሳተህ ታጠፋዋለህ ብዬ ነዋ ! ላጲስ አለው አየኸው።"

"ሂጅ ሆኖ መኝታ ቤት ፈልጊና እምጪ...እይ ቢጣዬ ፈርማ በላጲስ ቢጠፋ...የብድር ሰነድ ላይ የፈረምነውን ስንት ጉድ ፈርማ ባጠፋነውና አገር አፎይ ባለች።"

ቢጡ ወደ ሆኖ መኝታ ቤት ሮጠች (ሀና የ2ኛ ክፍል ተማሪ አህቴ ነች። ጨዋ፣ ጎበዝ ተማሪ...)
አቤት አባባ ሲወዳት፣"ሀና ትሙት" ካለ አቢቃ !!
ቢጡ የሀናን ቦርሳ ተሸከማ መጣች።

"እልከፈትም አለኝ አባባ።"

አባባ ቀስ ብሎ ቦርሳውን ከፈተና እስክሪብቶውን ፍለጋ ጀመረ። ድንገት ትንሽ ፓኬት ነገር አጁ ላይ ዱብ አለች። ወደ ዓይኑ ጠጋ አድርጎ አያት። ራቅ...ቀረብ...እንደገና ራቅ...
"እሃ...አብርሃም !" አጠራሩ ከመጥበቁ የተነሳ ስሜ የሚሰበር እስከሚመስለኝ።
"አቤት አባባ..."
"ሂድ መነፅሬን አምጣልኝ...ቶሎ በል"
"እ" አልኩ ግራ ገብቶኝ።
"መነፅሬን አምጣ አኮ ነው የምለው..." ጩኸቱ አስበረገገኝ።
"አባባ...መነፅርህን አኮ አድርገሽዋል" አልኩ። እጁን ወደ ዓይኑ ልኮ መነፅሩ ዓይኑ ላይ መኖሩን

አረጋገጠና፣
"እንቺ ወደ ውስጥ ግቢ..." አላት ቢጡን በቁጣ
"እሺ" ብላ ሮጠች::
"ይሄ ምንድን ነው...?"
እኔም ደነገጥኩ፣ የድንገተኛ አርማዝና መከላከያ ፖስት ፒል፣ አባባ አውቆታል::
"እ...እንጂ ምንድን ነው ?"
"ምን ትጠይቀኛለህ አንብበዋ"

አየት አድርጌ፣ "መድኃኒት ነው...ያው ራሷን አሟት ምናምን ሊሆን ይችላል::"

"ዝም በል:: እንካኝ...እንካ ራሴን አመመኝ ስትል አልነበረም፣ እንካ ዋጠው የራስ ምታት ከሆነ:: ሂድ እህቶችህን ጥራ" አለ በጩኸት:: ሁሉም ተሰባሰቡ:: ሀና የለችም ነበር፣ 'ላይብረሪ' ብላ ሄዳለች::

አባባ አጭርና ታሪካዊ ንግግር አደረገ (የሁላችንም ልብ በሐዘን ተነከቶ ነበር::) ይሄን ሁሉ ሴት ሲያሳድግ የዚህ ዓይነት ውርደት ደርሶበት እንደማያውቅ:: በተለይ ይሄን ጉዳይ ራሷ የሚያደርገው፣ መድኃኒቱ ትልቅ ተስፋ በሚጥልባትና በሚኮራባት ልጁ ሀና ቦርሳ ውስጥ በመገኘቱ መሆኑን በተጎዳ ድምፅ ከገለፀ በኋላ፣ 'በጥብቅ' የሀና መኝታ ቤት እንዲበረበር ትዕዛዝ ሰጠን::

"አብርሃም እህቶችህ ባሉበት ይሄን ጉዳይ አንተ ራስህ እየመራህ መርምር፣ ባይልልህ ነው እንጂ ቤተሰብ መሪ መሆኛህ ነበር...ወይ ውርደት !!" ብሎ ጠረጴዛውን ደቃው፣ እንደ ፍርድ ቤት መዶሻ የዕለቱ ስብሰባ መዝጊያ ተደርጎ ተወሰደ::

የምርመራ ቡድኑ ከላይ በጠቀስኩት ኮሚቴ በመዋቀር (አባቴ ደውሎ የጠራት የአክሰታችንን ልጅ በማካተት) ወደ ሀና መኝታ ቤት ዘመተ:: እናቴ የኮሚቴው አባል ልትሆን ብትጠይቅም 'የእናት አንጀት...' በማዘንም ይሁን በሌላ ምክንያት ሊያዳላና የኮሚቴውን ስራ ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል በማለት ሳትካተት ቀረች::

ኮሚቴው ገና ከጅምሩ ፀብ ጀምሮ ነበር:: ምክንያቱ ደግሞ እኔ እንደቀልድ የወረወርኳት ጥያቄ ነበረች፣ "ምናልባት ሀኒ ቦርሳ ውስጥ ከእናንተ አንድኛችሁ አስቀምጣችሁባት ይሆን?" ሁሉም ተንጫጩ:: እንደምንም አረጋግቻቸው (የሕዝብና የመንግስት ኃላፊነት ስላለብኝ) ስራችንን ቀጠልን::

የሀኒ መኝታ ቤት ሲፈተሽ መሳቢያዋ ውስጥ ለቁጥር የሚያዳግቱ የወንድ ፎቶዎች ማግኘታችን አስደነገጠን:: ጨዋዋ ሀኒ እየዞረች ፎቶ ማንሳት ጀምራ ይሆን ? ሲቀጥል የባሰው መጣ:: ወረ በጡት ማስያዣ፣ ወላ ከወንዶች ጋር:: ብቻዋን...ሀይቅ ዳርቻ ላይ:: ...ቆይ አዲስ አበባ ሀይቅ አለ እንዴ...ታዲያ የት ሄዳ ተነስታ ነው ? በጀልባ (ታይታኒከኛ ፎቶ):: ከቤት ወጥታ የማታውቀ

ልጅ ሙሉን ከንፍ በራ ሀይቅ ዳር ተገኘች ? ኧረ ጉድ...ጭፈራ ቤት...ማታ በሚኒስከርት...ሀና ሚኒስከርት (ሀናን በሚኒስከርት አየናት ከሚሉኝ፣ አንተን በሚኒስከርት አየንህ ቢሉኝ አምን አላ) ጓደኔ ይሆን 'መነፅሬን አምጣ' አለ አባባ። እውነቱን ነው፣ 'ኧረ መነፅሬን አምጡ' አለ ያልኩ፣ ሲጠቁ ልየብት ሆኖ አረፈው። እኛ ሳሎን ተቀምጠን፣ ዘራፍ የነሉሲ፣ የእነ ማንትሰ ልጅ_ሶመሪአሙ ደም_እባይን ገደብነው ስንል_መኝታ ቤታችን፣ የታሪክ የወግና ባህል ግድባችን ፈርሶ እኛ ተኮላቅልቋል። ነበዝ መነፅራችንን ሰጡን። 11:30 ቤቷ የምትከተት ልጅ ጭፈራ ቤት !!

የኛ ላፕቶፕ ተከፈተ ('ብልግና ተከፈተ' ቢባል ይሻላል።) የወሲብ ፊልም ከአፍ አስከገደፉ፣ ቢቆ አባባን ካሁኑ መሰናበት አለብን - ደም ግፊቱ... ታላቅ ታሪካዊ አደራ የተጣለብኝ ሰው ባልሆን ኖሮ ባለቀስኩ ነበር፣ ግን ስራዬን ቀጠልኩ፣ የወንዶቹ ፎቶ እጅግ ከመብዛቱ የተነሳ ለፈታሪት እንዲመች ይቆጠር ብለን መቁጠር ጀመርን። መኝታ ቤቱ በር ላይ፣ "ቆጠራ ላይ ስለሆንን መግባት ክልክል ነው ኮሚቴው !!" የሚል ጽሑፍ ለጠፍን። ከፎቶዎቹ ኋላ ስማቸው ተጽፏል። 43 ዘሩ...44 ሚኪ...44 ፒተር(ፈረንጅ ነው)(የአከስቴ ልጅ ምራቋን ስትውጥ ጉሮሮዋ ሲነራጭ ሰማሁት። ፈረንጁን የዋጠችው ነው የምትመስለው።) 45 ሽምሰዲን (የሰፈራችን ባለሱቅ) 'ደንበኛዬ ነው' ትላለች ሀኒ። እይ ሀኒ እዚህ ሚስኪን ቤተሰብ ላይ ቅኔ ስትዘርፍበት ነው ኖሮችው። ግዴለም !...46 ሀውቹባን (ቻይናዊ)። እቺ ልጅ ዓለም አቀፍ ስብሰባ ጠርታ ነበር እንዴ?

"ዊ መስት ኮል 911 ኢሚዲየትሊ" አለች ለዕረፍት ከአሜሪካ የመጣችው ትልቋ እህታችን ፊቷ በድንጋጤ አመድ መስሎ፣ እንባዋ በዓይኗ ሞልቶ። ...ኮሚቴው በሳቅ ፍርስስስስስ። ከሳቂታ ኮሚቴ ጋር አብሬ በመስራቴ ኩራት ተሰማኝ።

ቢጡ ስንስቅ ሰምታን በሩን አንኳኳችና፣ "እብልሽ ኮሚቴው ውስጥ አስገባኝ" አለችኝ። ሳቅ ሁሉ ደሲታ የሚመስላቸው ሚስኪኖች ስንቱ ኮሚቴ ውስጥ ገብተው እንደቀለጡ ባወቀች...

"ቢጣ ተመለሽ ! ማንበብ ትችይ የለ...የተለጠፈውን ሊታነቢም ?" አልኳት።

እየጮኸች ማንበብ ጀመረች፣ "ቆ...ጠ...ራ...ላ...ይ...ስ...ለ...ሆ...ን...ን.....አብልሽ እኔም እኮ ቁጥር አስከ መቶ እችላለሁ። ልቁጠርልህ ? ስማኝ...ዋን...ቱ...ሰሪ...ፎር...ፋይፍ....." የፈረንጁን ፎቶ እያየሁ የቢጣን እንግሊዝኛ ሳዳምጥ፣ "ተከብበናል..." አልኩ ለራሴ።

"ምናልክ አብልሽ...ከልገባህም በአምሀሪክ ልቁጠርልህ ? አንድ...ሁለት...ሾሽት..."

ለምሳ ስንወጣ ቢጣ በሩ ስር እንቅልፍ ወስዷት በእንቅልፍ ልቧ ትቆጥራለች፣ "አርባ ሾሽት ባላት...ባ አምስት..." እንደገና ኮሚቴው ባሳቅ ፍርስስስስስ። የራበው ኮሚቴ ሲስቅ ይደብራል...!!

14 የመግቢያ ፈተና

አስራ ሁለተኛ ከፍል ተፈትኜ ዩኒቨርስቲ የሚያስገባ ውጤት በማምጣቴ መንደሩ በደስታ አበደ የበለጠ ወሬውን ያሞቀው ደግሞ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መመደቤ ነበር::

'እሳቷ ኸዋና ከተማው ከባህሩ ዘላ ጥርቅም አለች' ተባለልኝ:: ወሬው ሁሉ ስለኔ ሆነ_::

"...የአቶ ዘለቀ ልጅ ይንበርስቲ በጠሰ..."

"የትኛው_"

"ይሄ ባለፈው በሬ ወግቶት የነበረው"

"...እረረረረረረረ ...ሰው ሁሉ ሞኛሞኝ መስሎ፣ ለካስ እንዲህ ጥይት ነው ጃል"

"ቀለም ዘልቆት ነው ፈዘዝ ያለው እይ...ጎበዝ ነው ከድሮውም...እረ::" ወሬው ከመንደር መንደር ተሰራጨ፣ በዛን ሰሞን የመንደሩ ሕፃናት አጥንቶን እንሙት አሉ:: ለወትሮው በቅስቀላ ትምህርት ቤት የሚሄደው ውሪ ሁሉ፣ ሰዓቱ ሳይደርስ ደብተሩን እንጠልጥሎ ቱርርር እያለ ይበር ጀመር::

ሁሉ ነገር ተሰናድቶ ድል ያለ የመሸኛ ግብዣ ተደረገና ቤተሰብ፣ ወዳጅ ዘመድ ሁሉ ተሰባስቦ ጨዋታው እንደደራ፣ ከከተማ የመጣው አጎቴ ስለሁኔታው ያወጋኝ ጀመረ፣

"መላኩ"

"አቤት አጎቴ"

ከሆንክ ሆንና የትኛው ስርቆ ነው የደለደልከው ሲድስት ኪሎ የሚባለው ነው የነበት ሆስፒታል አጠገብ"

"አይ አይደለም አትቴ"

"እምስት ኪሎ የሚባለው ነው ቢቃ አዛ የአከሰቱ ቤት ነን። ከይንበርስቲው ጋር ኩታ ገጠም ናቸው እንዲህ አጥር ነው የሚለያቸው" አለች ከመንደራችን በሶስተኛ አዲሳባን ሁለተ ጊዜ ሂዳቢታለች የምትባለው አረጋሽ፣ በዕርግጥም ወደ እምስት ወር አዲስ አበባ ቆይታ ተመልሳለች አትቴ ቀጠለ፣ "እምስት ኪሎ የት ነው፣ ወደ ጥቁር እንበሳ ሆስፒታል ይቀርባል መላኩ የሚባለው እውነት ነው?"

"ኧረ አትቴ አይደለም"

"ተዉት በቃ አራት ኪሎ ነው" አለች አረጋሽ፣ ቀጠል አድርጋም፣ "አዛው ዝቅ ብሎ እኮ ነው! ከዚህ እንደ አቶ አስራት ቤት ቢሆን ነው፣ አትቴ ጉግሳ ቤተ አዛው ሰፈር ነው" "መላኩ፣ ለመሆኑ አራት ኪሎ በመሆኑ ከፍቶሽል?" አለ አትቴ ፊቴን እያየ።

እናቴ ፊቴ ላይ ያለውን ቅሬታ እንብባ እንዲህ አለች፣

"አይዞህ የኔ እንበሳ፣ እግርህ አዲሳባን ይርገጥ እንጂ ግደለም...ከአራት ጀምረህ አምስትም፣ ሲድስትም ሰባትም ኪሎ ትገባለህ። ስንቅ ነው፣ እኔ እናትህ አያለሁ አትቸገርም" አለች። "እናትህ እውነቷን ነው፣ የትም ብትሆን እንዳትሰጋ!" አለ አባቴ ቀከራ በሚመስል ድምፅ።

አትቴ ቀላል ሰው አይደለም፣ ጊዜው ራቅ ይበል እንጂ አዲሳባ አንድ ወር ከአሰራ አምስት ቀን ሰንብቶ መጥቷል። እናም ባለችው እውቀት ስለ አራት ኪሎ እንዲህ አለ፣ "ኧረረረ ሞኘው ጭንቅላቱ ላይ ነሀና፣ ቤተ መንግስቱ ውስጥ በለው ቢቃ" አለ ጋቢውን ወደ ትከሻው ከፍ አያደረገ።

ማመንታቱ ምርር ስላደረገኝ እንዲህ አልኩ፣ "እኔ የተደለደልኩት ኮሜርስ የሚባል ቦታ ነው።"

"አአአአ" አጉረመረሙ።

"እሱ ደሞ ወዴት ነው? አዲስ አባ ነው...ሲባልም አልሰማሁ" አለ አትቴ።

"እኔም የት እንደሆነ አላውቅም አትቴ፣ ብቻ አዛው አዲሳባ እንዱ ግድም ነው" አልኩ። በዕርግጥም አራት ኪሎ፣ አምስት ኪሎ፣ ሲድስት ኪሎ ካልተባለ ዩኒቨርስቲ ስለማያመስለኝ ኮሜርስ ባሉት ነገር ከፍቶኝ ነበር።

"ከሆነስ ሆነና የትኛው ሰርፋ ነው የደለደሉህ...ሲድስት ኪሎ የሚባለው ነው_የካቲት ሆስፒታል አጠገብ..."

"እይ አይደለም አጎቴ"

"እምስት ኪሎ የሚባለው ነው በቃ...እዛ የአክስቴ ቤት ጎን:: ከይንበርስቲው ጋር ኩታ ገጠም ናቸው...እንዲህ አጥር ነው የሚለያቸው" አለች ከመንደራችን ብቸኛዋ 'አዲሳባን ሁለት ጊዜ ሂዳበታለች' የምትባለው አረጋሽ፣ በዕርግጥም ወደ አምስት ወር አዲስ አበባ ቆይታ ተመልሳለች_ አጎቴ ቀጠለ፣ "አምስት ኪሎ የት ነው?...ወደ ጥቁር እንበሳ ሆስፒታል ይቀርባል_መላኩ_የሚባለው አውነት ነው?"

"ኧረ አጎቴ አይደለም"

"ተዉት በቃ አራት ኪሎ ነው" አለች አረጋሽ፣ ቀጠል አድርጋም፣"እዛው ዝቅ ብሎ እኮ ነው! ከዚህ እንደ አቶ አስራት ቤት ቢሆን ነው፤ አጎቴ ጉግሳ ቤቱ እዛው ሰር ነው" "መላኩ፣ ለመሆኑ አራት ኪሎ በመሆኑ ከፍቶኽል?" አለ አጎቴ ፊቴን እያየ::

እናቴ ፊቴ ላይ ያለውን ቅሬታ አንብባ እንዲህ አለች፣

"አይዞህ የኔ አንበሳ፣ እግርህ አዲሳባን ይርገጥ እንጂ ግዴለም_ከአራት ጀምረህ አምስትም፣ ስድስትም ሰባትም ኪሎ ትገባለህ:: ስንቅ ነው? እኔ እናትህ አያለሁ አትቸገርም" አለች:: "እናትህ እውነቷን ነው፣ የትም ብትሆን እንዳትሰጋ!" አለ አባቴ ቃኪራ በሚመስል ድምፅ::

አጎቴ ቀላል ሰው አይደለም፣ ጊዜው ራቅ ይበል እንጂ አዲሳባ አንድ ወር ከአስራ አምስት ቀን ሰንብቶ መጥቷል:: ...እናም ባለችው አውቀት ስለ አራት ኪሎ እንዲህ አለ፣ "ኧረረረ ዋናው ጭንቅላቱ ላይ ነህና፣ ቤተ መንግስቱ ውስጥ በለው ቢቃ" አለ ጋቢውን ወደ ትካሻው ከፍ አያደረገ::

ግምታቸው ምርር ስላደረገኝ እንዲህ አልኩ፣ "እኔ የተደለደልኩት ኮሜርስ የሚባል ቦታ ነው::"

"እእእእ" አጉረመረሙ::

"እሱ ደሞ ወዴት ነው? አዲስ አባ ነው...ሲባልም አልሰማሁ" አለ አጎቴ::

"እኔም የት እንደሆነ አላውቅም አጎቴ፣ ብቻ እዛው አዲሳባ እንዱ ግድም ነው" አልኩ:: በዕርግጥም አራት ኪሎ፣ አምስት ኪሎ፣ ሲድስት ኪሎ ካልተባለ ዩኒቨርስቲ ስለማይመስለኝ 'ኮሜርስ' ባሉት ነገር ከፍቶኝ ነበር::

"ምንድነውሳ የሚያስተምሩት?" አለ አባቴ::

"'የንግድ ስራ' ይላል ወረቀቱ ላይ" አልኩ::

"መድሃኒዓለም! ንግድ ምን ትምህርት ይላል? ይሄው እኛ ዝም ብለን እያቀላጠፍነው እይደለም?!" አለ አባቴ፣ ታዋቂ የአሀል ነጋዴ ነው::

"እንዴዴዴዴዴ ባንክ የምትሰራው የአከሰቴ ልጅ የተማረችበት ነው፣ ኧረ ጥሩ ተማሪ ቤት ነው ሲሉ ሰምቻለሁ:: ሞት ይርሳኝ! ያ በሪሁን፣ የእናቴ የአሀት ልጅ፣ ቤቱ እዛው ነው" አለች አረጋሽ::

ጋሽ ዘለቀ የመንደራችን አስቂኝ ሽማግሌ፣ "አረጋሽ እንደው ያንች ዘመዶች ሁሉ ዩኒቨርሰቲ ላጥር ሰር ብቻ ነው እንዴ ቤት የሚሰሩት?!" አሉና ሰዉን አሳቁት::

ሁሉም እንደየአቅሙ የሰማውንም ያየውንም ስለአዲስ አበባ ይመከረኝ ጀመረ::

የመጀመሪያው አጎቴ ነው፣ "መላኩ...አዲሳባ እንዲህ ቀላል አገር እንዳይመስልህ ባህር ነው... በህር...በዛ ላይ ሌባው አይጣል፣ ሴት ወንዱ ሞላ፣ ነው:: ሱፉን ግጥም አድርጎ መኪንት የመሰለው ሰው፣ ጠጋ ብሎ ከኪስህ ገንዘብህን ይከተልብኻል:: ሴቷ ስትውረገረግ ልብህን ትሰልበዋለች:: አንዳች አፍዝ አደንግዝ አላቸው:: ጠንቀቅ ብለህ እንደወታደር ነው መኖር፣ የአዲሳባ ሕዝብ ፈዛዛ አይወድም"

አጎቴ አዲስ አበባ የሄደው ለሕክምና ነበር:: ታዲያ ከቆየባቸው አርባ አምስት ቀናት ሰላሳ ዘጠኙን ጥቁር አንበሳ ተኝቶ ነው ያሳለፈው፣ ሁለት ቀን የካቲት ሆስፒታል...አንድ ቀን ጦር ኃይሎች...ከህመሙ ጋር እየታገለ ስለአዲሳባ ይሄን ሁሉ ማወቁ ግሩም ነው::

ዙሪያሽ ነበረች ቀጣይ መካሪ፣ "ወይ አዲስ አበባ...ሂሂሂሂ...የጉድ አገር እኮ ናት፣ መንገድ ስትሻገር ነጭ ነጪን እየረገጥክ ነው፣ ሳት ካለህ መኪናው አያፈናፍንም..."

"ይሄ አዲስአባ ሰፊ አገር ነው አልተባለም እንዴ? የምን የማሪያም መንገድ ነው! ነጩን ጥቁሩን እንዳሻው ይራመድ እንጂ" አለች እናቴ::

"ሂሂሂሂ ሕግ ነው፤ እንደኛ አገር ያገኙበት መርገጥ የለም እናቴ፣" ብላ አረጋሽ ቀጠለች፣ "እና...መላኩ ዋናው ነገር...ዋናው የአዲስአባ ሴቶች አሳሳቾች ናቸው፤ ያንተ ዓይነቱን ሸበላማ ካዩ ተከትለውህ ነው የሚመጡት:: ኮስተር በል፣ ፊት አትስጣቸው! ኧረ በድንግሏ...ሃፍረት የሚባል አያቃቸውም..."

"ምንድነውሳ የሚያስተምሩት?" አለ አባቴ::

"'የንግድ ስራ' ይላል ወረቀቱ ላይ" አልኩ::

"መድሃኒዓለም! ንግድ ምን ትምህርት ይላል? ይሄው እኛ ዝም ብለን እያቀላጠፍነው እይደለም?!" አለ አባቴ፣ ታዋቂ የአሀል ነጋዴ ነው::

"እንዴዴዴዴዴ ባንክ የምትሰራው የአከሰቴ ልጅ የተማረችበት ነው፣ ኧረ ጥሩ ተማሪ ቤት ነው ሲሉ ሰምቻለሁ:: ሞት ይርሳኝ! ያ በሪሁን፣ የእናቴ የአሀት ልጅ፣ ቤቱ እዛው ነው" አለች አረጋሽ::

ጋሽ ዘለቀ የመንደራችን አስቂኝ ሽማግሌ፣ "አረጋሽ እንደው ያንች ዘመዶች ሁሉ ዩኒቨርሰቲ ላጥር ሰር ብቻ ነው እንዴ ቤት የሚሰሩት?!" አሉና ሰዉን አሳቁት::

ሁሉም እንደየአቅሙ የሰማውንም ያየውንም ስለአዲስ አበባ ይመከረኝ ጀመረ::

የመጀመሪያው አጎቴ ነው፣ "መላኩ...አዲሳባ እንዲህ ቀላል አገር እንዳይመስልህ ባህር ነው... በህር...በዛ ላይ ሌባው አይጣል፣ ሴት ወንዱ ሞላ፣ ነው:: ሱፉን ግጥም አድርጎ መኪንት የመሰለው ሰው፣ ጠጋ ብሎ ከኪስህ ገንዘብህን ይከተልብኻል:: ሴቷ ስትውረገረግ ልብህን ትሰልበዋለች:: አንዳች አፍዝ አደንግዝ አላቸው:: ጠንቀቅ ብለህ እንደወታደር ነው መኖር፣ የአዲሳባ ሕዝብ ፈዛዛ አይወድም"

አጎቴ አዲስ አበባ የሄደው ለሕክምና ነበር:: ታዲያ ከቆየባቸው አርባ አምስት ቀናት ሰላሳ ዘጠኙን ጥቁር አንበሳ ተኝቶ ነው ያሳለፈው፣ ሁለት ቀን የካቲት ሆስፒታል...አንድ ቀን ጦር ኃይሎች...ከህመሙ ጋር እየታገለ ስለአዲሳባ ይሄን ሁሉ ማወቁ ግሩም ነው::

ዙሪያሽ ነበረች ቀጣይ መካሪ፣ "ወይ አዲስ አበባ...ሂሂሂሂ...የጉድ አገር እኮ ናት፣ መንገድ ስትሻገር ነጭ ነጪን እየረገጥክ ነው፣ ሳት ካለህ መኪናው አያፈናፍንም..."

"ይሄ አዲስአባ ሰፊ አገር ነው አልተባለም እንዴ? የምን የማሪያም መንገድ ነው! ነጩን ጥቁሩን እንዳሻው ይራመድ እንጂ" አለች እናቴ::

"ሂሂሂሂ ሕግ ነው፤ እንደኛ አገር ያገኙበት መርገጥ የለም እናቴ፣" ብላ አረጋሽ ቀጠለች፣ "እና...መላኩ ዋናው ነገር...ዋናው የአዲስአባ ሴቶች አሳሳቾች ናቸው፤ ያንተ ዓይነቱን ሸበላማ ካዩ ተከትለውህ ነው የሚመጡት:: ኮስተር በል፣ ፊት አትስጣቸው! ኧረ በድንግሏ...ሃፍረት የሚባል አያቃቸውም..."

"አንድ ቀን የአከሰቴ ልጆች ካማሪካ መጡና አራት እንብላ ብለው ሰብስበው ወሰዱን:: ጉድ እየሁ...ጉድ...ሴት አና ወንድ፣ ሴትና ወንድ ሁነው ነው የሚቀመጡት:: አንድ ብቻሀን ቁሪር ብሎ መቀመጥ ነውር ነው የተባለ ይመስል...:: ሃዲያ አንድ ጊዜ ይጎርሱና መሳሳም፣ ደሞ ይጎርሱና መሳሳም...እማምላከን አሀሉን በውሃ ሳይሆን በመሳሳም የሚያወራርዱት ነው እኮ የሚመስሉት...ሁሁሁሁ" ብላ በአፍረት ሳቀች::
"ወላዲት አምላከ!ኸምግብ ቤቱ ነው የሚሳሳሙት?
ፈረሰኛው ጊወርጊስ!"

ሁሉም በወሬው ተገርመው ተንጫጩ::

ቀጠለች አረጋሽ፣ "ደሞ ሴቶቹ እንዲቹ እርቃናቸውን ቁራጭ ልብስ ጣል አርገው እንዲቹ እንደፈጠራቸው ነው የሚመናቀሩት...የቆዳቸው ልስላሴ...መስተዋት ነው የሚመሳስሉት... 'አይበርዳቸውም ወይ?' እላለሁ እኔማ" አለች:: ...ገረመኝ!!

"እና መላኩ፣ በሌላ ሌላው እንኳን አንተ አትመከርም፣ በሴቶቹ እንዳትፈተን አደራ!" ብላ ምክሯን ጨረሰች::.

እንደጧት አዲሳባ ልሳፈር ሌሊቱን ሲያቃዥኝ አደረ:: አራት እየበላሁ ይመስለኛል፣ የቆዳዋ ጥራት መስተዋት የመሰለ ሴት አርቃኗን ጎኔ ተቀምጣ አንዴ በጎረስኩ ቁጥር የምትስመኝ ይመስለኛል፣ ልክ እንደማወራረጃ:: ከዚሁ ፈተናው ጀመረኝ::

15 እብድ እና ዘመናይ

ጓደኛችን አመሃ አበደ !!

ድንገት ነው እንደ ትንታ፣ እንደ ሳል፣ እንደ ንጥሻ አብደቱ ያመለጠው:: እቺ አይምሯችን ግን ከንቱ ናት ለካ! ደርሰን እናሞካሻታለን አንጂ አንዳንዴ እንዲህ ሜዳ ላይ ጣጥላን ትወፍፋለች ለካ:: ሰው ከንቱ !! አይምሯችንን ልንጠብቃት ይገባል፣ አለች ስንላት ገደል ገብታ ገደል ታስገባናለች፣ ወይኔ አምሽ! ምነው ሴት ሆኖ ተፈጥሮ በነበር !?...ይሻለው ነበር ! ባንዴ ከማበድ በየቀኑ ትንሽ ትንሽ ማበድ !

የስነ አሉምሮ ጠበብት "ሴቶች የማበድ እድላቸው ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር በጣም እነስተኛ ነው፣ ምክንያቱም ሴቶች ብስጭታቸውን፣ መከፋታቸውን በአንባ ይሸኙታል፣ በጩኸት ይሸውዱታል፣ ወንዶች ግን አፍነው ስለሚይዙት ውስጣቸው ይጠራቀምና ድንገት ገንፍሎ ጉድ ያደርጋቸዋል" ይላሉ:: በነጋዴ ቋንቋ ስንለፀው ሴቶች የሚያብዱት በችርቻሮ ሲሆን ወንዶች ግን በጅምላ ነው እንደማለት::

ጓደኛችን አመሃ ኮሌጃችን ውስጥ ወላ ባለባበስ፣ ወላ በትምህርት የሚደነቅ ሲበዛ ዝምተኛ ልጅ ነበር:: 'ሃይ፣ ባይ' ነው ቅፅል ስሙ:: ቢቃ ስንገናኝ 'ሃይ' ይላል:: እንዲት ቃል ሳይተነፍስ ስንለያይ፣ 'ባይ' !! አምሻ ልዩ ልጅ ነበር:: ምድረ ኩታራ ከየዶርማችን ሱክ ሱክ እያልን ወደ 'ክላስ' ስንጣደፍ አምሃ ፀዳ ባለ ፓጃሮ መኪናው ከተፍ ይላል:: እንግዲህ እኛ ባየነው ነገር ሰላምን የምንለካ የዋህ ከተሜዎች የአመሃ ተድላ እና ሀብት ተደማምሮ እንኳን አብደት ድብርት በአመሃ አጠገብ ያልፋል ብለን በምን አባታችን ጠርጥረን:: "ፀጉራም ውሻ አለ ሲባል ይሞታል" እንዲሉ አበው በሀብት ፀጉር የደለበ የመሰለን አመሃ 'አለ' ስንለው 'ለቀቀ' !!

አመሃ እና እኔ ጓደኞች ነን:: እንደውም አመሃ ሁለት ጓደኛ ብቻ ነው ያለው፣ እኔና ናትናኤል የሚባል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አብረው ሳንፎርድ የተማሩ ልጅ:: በቃ ሌላ ጓደኛ

የለውም::ያው ፍቅረኛው እንዳለች ሆና !! ቤቱ ሁሉ ወስዶ ከሞልቃቃ እናቱ ጋር አስተዋውቆኛል::

እንደ አመሃ እናት በጣም አጭር ጅንስ ቁምጣ የለበሰች ወጣት እናት ከዛ በፊትም ከዛ በኋላም አይቼ አላውቅም:: የእግሮቿ አረዛዘም፣ ሰበር ሰካ አረማመዷ ወጣት ይፈትናል:: ከላይ ጣል ያደረገችው ስስ ቦዲ ነገር የጡት መያዣዋን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል:: አመሃ ሁሊታችንን ትቶን ወደ ውስጥ ሲገባ፣ "የዛሬ ልጆች ቆንጆዎች ናችሁ" አለችኝ:: አነጋገሯ እንደ ማስቲካ ይለጠጣል፤ ከአስተያየቷ ጋር ተዳምሮ አድናቆቷ እናታዊ አድናቆት ሳልመስልህ አለኝ:: የለም የለም እቺ ሴት የእናት ቀለም የላትም::

ፊት ለፊቴ ተቀምጣ አንድ እግሯን ሶፋው ላይ አውጥታ በረዣዥም የእጇ ጣቶች ጉልበቷን በስሱ እንደማከከ አደረገችው:: ቁምጣዋ ተሰብስቦ የተላጠ ብርቱካን የመሰለ የደላው ሰውነቷን አጋለጠው:: ጥርት ያለ የታፋዋ ቆዳ ላይና የሚያማምሩ የእግሯ ጣቶች ላይ ዓይኔን አለማሳረፍ አልቻልኩም:: በዛ ላይ ውስጥን ሰርስሮ የሚያይ የሚመስል አስተያየቷ "ምነው ባልመጣሁ!" አስባለኝ::

በምድር ላይ ያሉ እናቶች ሁሉ ሽንሽን ቀሚስ 'ዩኒፎርማቸው' ይመስለኝ ነበር:: ያደግኩበት መንደር ሁሉም የሚለብሱት እንደዛ ስለነበረ ሲቀመጡ እንኳን ዘርፋፋ ቀሚሳቸውን እንዴት ሰብሰብ አድርገው እንደሚቀመጡ ሳስብ የዚች "እናት" ነገር ግራ ገባኝ:: መቼም "እናት ምን መምሰል አለባት?" የሚል ጥያቄ ቢነሳ ያው "እናት መምሰል አለባት" ነው መልሱ:: እቺ ሴት ግን ምኗም እናት አይመስልም:: የእናት ለዛ የላትም፤ የእናት የዋህነት፣ ደግነት ፊቷ ላይ ከነአካቴው የለም:: ዘላ ያልጠገበች የአሰረኛ ከፍል ተማሪ ነው የምትመስለው::

የአመሃ አባት ውጭ አገር በሚገኝ ዩኒቨርስቲ መምህር ናቸው:: እናቱ አብራቸው ሄዳ እዛ እንዲኖሩ ብትለመን፣ ብትመከር "በአንገቴ ገመድ ቢገባ አልሄድም!" ቦግለቷ ሁላቱ ብሯቸውን እዚህ በቅንጦት የተምነሸነሸ ቪላ ውስጥ ይኖራሉ:: አባቱ በስድስት ወር እንዴ ብቅ እያሉ ይጎበኟቸዋል - ራሱ አመሃ ነው የነገረኝ:: ሁልጊዜም አባቱ ሲመጡ ታዲያ እናትና አባት ዱላ ቀረሽ ንትርክ ውስጥ ናቸው:: አባት የሚስታቸውን ባህሪ ያውቁታል:: ሚስትም የባሏን ባልነት ባትረሳም የትዳሩ ነገር እጅ እጅ ብሏታል::

የሆነው ሆኖ አምሃ አበደ:: ከማበዱ በፊት የሚጠረጥር ዘመድ፣ በጊዜ አፋፍሶ ፀበል የሚወስድ ወዳጅ ዘመድ አጥቶ እንጂ አምሃ ግልፅ የሆኑ ምልክቶች ሲያሳይ ነበር - በተለይ ለእኔ::

ምልክት አንድ:- ሀዳር ላይ የሚያብድ፣ መስከረም ላይ ሱሪውን ከፍ ከፍ ያደርጋል ይሉሉ እማማ ሩቂያ፣

አንድ ቀን አመሃ (ለይቶለት ከማበዱ አንድ ወር በፊት) ሱሪውን አስር ጊዜ ከፍ ከፍ ያደርጋል:: "ሰፍቶሀል እንዴ ይሄ ሱሪ ?" አልኩት:: "አይ ቀበቶዬን ረስቼ ሳላረገው ነው የመጣሁት" አለኝ፣ እንዲህ የምንባባለው ወደ ላይብረሪ እየሄድን ነበር:: ላይብረሪ ውስጥ ጎን ለጎን ለመቀመጥ ቦታ

ስላልነበር በያገኘነው ወንበር ተራርቀን ተቀመጥን። ድንገት አመሃ ቁሞ ሲል ሸሚዙ ከኋላው ሰብሰብ አለና ቀበቶ ማድረጉን አየሁ። ያውም ጥቁር የቆዳ ቀበቶ። "ቀበቶ አላደረግኩም" ማለቱ ዝርግኝ ስንወጣ አጠያቀሞለሁ ብዬ በዛው ረሳሁት።

ምልከት ሁለት፡- "አላህ ሲቆጣ ብትር አይቆርጥም፣ ያደርጋል እንጂ ነገር እንዳይጥሙ" ይላሉ አሞሃ ፍቅያ፣ የሰፈራችን አድባር፤

እኔና አመሃ አንድ ታዋቂ ሬስቶራንት ውስጥ ገባንና ምግብ አዘዝን - 'ፒዛ'። አመሃ ቀመስ አደረገና አስተናጋጁን ጠርቶ፣ "ምንድን ነው ይሄ ሁሉ ጨው ! ቤቱ ውስጥ ያለውን ጨው ሁሉ ነው የሞጅራችሁት ?" ብሎ ፎክቦት። እንደ እውነቱ ከሆነ አመሃ ሲፎህም ሆነ በቁጣ ሲናገር ሰምቼ ስለማላውቅ ከምላሴ ይልቅ አመሃን አምኜው ነበር። አስተናጋጁ ግን በትህትና፣ "ይቅርታ እኛ ፒዛ ስናዘጋጅ ጨው አንጠቀምም፣ ደንበኛው ራሱ በሚፈልገው መጠን እንዲጠቀም ለብቻ ነው የምናቀርበው" አለች ፈታችን የተቀመጠውን የጨው አቃ አያሳየችን።

"ሂጂ ወደዛ !! ይሄን ልመን አንችን ?" አላት ምላሱን በአስፈሪ ሁኔታ ጎልጉሎ በግራ እጁ ጫፉን በመያዝ በሹካው ጫፍ ለአስተናጋጁ አያሳያት። ፒዛውን ትተነው ሌላ ቤት ገባን። አመሃ ለስላሳ አዘዘ። አንድ ጊዜ ተንገሞቶ ፊቱን አጨፈገገና፣ "ቱ !" ብሎ ወለሉ ላይ ተፋው። ፊት ለፊት ተቀምጠው የነበሩ ወንድና ሴት ፍቅረኛሞች ፊታቸውን አጨፈገጉና ተመለከቱት። "እንዴት ሚሪንዳ ውስጥ ሎሚ ትጨምራላችሁ ?" ብሎ አዛም ግብ ግብ ፈጠረ። በቃ ይሄ ልጅ ነገር ሁሉ አልጥመው አለው። (ሊያብድ አስር ቀናት ብቻ ነበሩ የቀሩት)

ሦስተኛ ምልከት፡-...አብድ

ሌላ ቀን መኪናውን እያሽከረከረ ወደ ማቆሚያው አመራና የዶክተር ታደሰን አሮጌ ዲኤክስ መኪና አርፋ በቆመችበት ከኋላዋ ገጫት። ድሮም ሆድ የባሳት ነበረች። ከዛም ሰው ተሰብስቦ ወሬ ሲያይ አመሃ ረጋ ብሎ ወረደና ልክ እንደ ትራፊክ ፖሊስ ኮስተር ብሎ ግጭቱን ከተለያየ አቅጣጫ አይኑን እያጨነቆረና አንገቱን እየሰበቀ ከተመለከተ በኋላ (ፎቶ የሚያነሳ ነበር የሚመስለው) ወደ ዶክተር ታደሰ ቢሮ ሄደ። ሳያንኳኳ በሩን በርግዶ ገባና ዶክተሩ ላይ አፍጥጦ፣ "አንተን ብሎ ዶክተር... መኪና እንኳን በስርዓት ማቆም የማትችል..." ብሎ ሙልጭ አድርጎ ሰድቧቸው ወጣ፤

"ይሄ ልጅ አብድ ነው እንዴ !" አሉ ዶክተሩ።

አራተኛው ምልከት፡- ዘመናይ

ሄለን የምትባል 'ዘመናዊ' የዲፓርትመንታችን ልጅ አለች። ምንም ነገር ስትናገር ለነገ የማትል፤ "ውይ አሷ ጣጣ የላትም፣ 'ፍሪ' አኮ ነች" እያለ ለአብደት የቀረበ ዘመናዊነቷን ተማሪው ያባባሰባት። አመሃ ጋር አንድ ሰፈር ናቸው። እንደውም ቤተሰብ ናቸው ማለት ይቀላል።

አንድ ቀን አመሃ፣ እኔ፣ እሷ ሆነን ዩኒቨርስቲው መናፈሻ ውስጥ እንደተቀመጥን አንዱ አስተማሪ ቤታችን ሲያልፍ፣ "ይሄ ሲድ የሆነ ሰውዬ ባለፈው ቢሮው አስገብቶ ቀሚሴን ሊገልበው..." አለች።

"ምን !? ያንቺን ቀሚስ ሊገልብ ይሄ ቆሻሻ" ብሎ አመሃ ወደ ሰውዬው ሊንደረደር ሲነሳ እንቅ አድርጌ ያዝኩት። መጠርጠር ጀምሬ ነበር - አምሽ ለቀቅ እያደረገ እንደነበር።

"ምን ነካህ አመሃ ስትቀልድ እኮ ነው እሷ !" አልኩት።

"እየቀለድሽ ነው ?" አላት አመሃ ወደ ሄለን ዞሮ። 'እም' እንድትል ጠቀስኳት፣

"እም" ከማለቷ፣ አመሃ በጥፊ አፍጫላት። አስደንጋጭ ነገር ነበር። ሰድድብ ጀመሩ፤

"ፂዝባ !" አለችው። ሰው ስትሳደብ አይቻት አላውቅም። መናፈሻው ውስጥ ያለ ተማሪ ሁሉ ወደ እኛ ዞረ።

"ሽርሙጣ !" አላት። ከአመሃ ይሄ ቃል ይወጣል ብሎ ማንም አይገምትም።

"ቆሻሻ !" አለችው።

"ማማታም!" አላት።

"ስማ አባትህ ቾክ እያቦነነ ባመጣው ገንዘብ ስትሞላቀቅ ጠገብከ !"

"እና እንዳንቺ እናት በመሸርሞጥ ሃብታም መሆን ይሻላል ?" ተማሪ በተሰበሰበበት እብድና ዘመናይ ልክ ልካቸውን ተነጋገሩ። አመሃ ሊለይለት ሶስት ቀን ቀርቶት ነበር።

ሲድስተኛው ምልክት፡- ልበቢስ

የመጀመሪያውን ሴሚስተር ጨርሰን ሁለተኛውን መጀመራችን ነበር።አዲስ ኮርስ የሚሰጡን መምህር ወደ 'ክላስ' ገቡ። ፀጉራቸው ወደ ኋላ የተደለሰ ህንዳዊ ናቸው። ሰታትስቲክስ የሚባል ኮርስ ነው የሚያስተምሩት። ይሄ መምህር ከአንድ የመንግስት የኒቨርስቲ በተማሪዎቹ የ'አንፈልጋቸውም' ተቃውሞ የተባረሩ ህንዳዊ ቢሆኑም አሁን የምንማርበት ኮሌጅ ግን፣ "ከውጭ በመጡ ታዋቂ መምህራን..." እያለ የቴሌቪዥን ማስታወቂያ የሚሰራባቸው የሰንፍና ጥግ ናቸው። ያው እንግዳ ተቀባይ ነንና አከብረን ተቀበልናቸው።

በተኮላተፈ እንግሊዝኛቸው ማስተማር ጀመሩ፤

"ሰታትስቲክስ ከሌሎች የጥናት መስኮች የሚለየው አንዲት አገር 'የልብ ምታን' የምታዳምጥበት መሳሪያ በመሆኑ ነው" አሉ በኩራት።

አመሃ ድንጉት ብድግ ብሎ "ዝም በል !" አላቸው።

'ቲቸርን' ከራማቸውን ነው የገፈፈው። እኛንም እንጂ !

አመሃ በብስጭት ዲስኩሩን ቀጠለ:: "ሁሉም አስተማሪ እየመጣ 'የልብ ምት፤ የልብ ምት' ይልብናል:: 'ኢኮኖሚክስ' የእንዲት አገር የልብ ምት የሚለካበት የጥናት መስክ ነው፤ 'ሕግ' የአንዲት አገር የልብ ምት የሚለካበት...'ፖለቲካል ሳይንስ' ሁለንተናዊ የአገር የልብ ትርታን የሚያዳምጥ የጥናት ዘርፍ ነው... ቆይ የዚች አገር ልብ በስንቱ ነው የሚለካው? ሲጀመር አገራችን ልብ ቢኖራት እንዳንተ ኢይነቱ ፊት ታስቀምጠን ነበር?

አገራችን 'ልብ አላት ወይስ የላትም?' የሚለውን ሃቅ የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ ያስፈልገናል፤ የልብ ትርታ ከመለካታችን በፊት ልብ መለኪያውን ይዞ ከየዩንቨርስቲው በየዓመቱ ወደ ሕዝብ የሚጎርፈው ሁሉ 'እዚህ ልብ የለም፤ የምትሄድበት ሄደህ ፈልግ፤ ካልሆነም ልብ ፍጠር' እየተባለ ስለ የትኛው ልብ፤ ስለየትኛው ትርታ ነው የምትቀባጥረው ? ሳልፈልግ ብዙ አታስወራኝ... ሃሃሃሃሃሃ"

አመሃ ለየለት !! አፋፍሰን አማኑኤል ወሰድነው:: እዛው ቀረ !! እናቱ ተጠርታ መጣች:: ሰውነቷ ላይ ጥብቅ ያለች አጭር ሚኒስከርት ለብሳ ከመኪናዋ ወረደችና ሰበር ሰካ እያለች ወደ እኔ መጣች::

"ምን ሆኖ ነው ?" አለችኝ፤

ነገርኳት::

"ድሮም የአባቱ ልጅ ነው፤ ሴታ ሴት፤ ለየለት" አለች በብስጭት:: ምን እንዳበሳጫት አላወቅኩም፤ ከብዙ ጊዜ በኋላ ሄለን አመሃ በእናቱ ምክንያት አዕምሮው እንደተናጋ አወጋችኝ::

"አንድ ቀን አመሃ ሶደሬ ሊሄድ ከሴት ጓደኛው ጋር ቀጠሮ ያዙ:: ታውቃት የለ ያች ሚዳቆ የመሰለች ጓደኛው:: እናልህ ለእናቱም ይሄንኑ ነግሯት መንገድ እንደ ጀመሩ የጓደኛው እናት የደም ግፊታቸው ከፍ ብሎ ጉዟቸው ተሰናከለ:: ሆስፒታል ቆይቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ እናቱ ናትናኤል ከሚባለው ከራሱ ከአመሃ ጓደኛ ጋር ያውም አባቱ አልጋ ላይ...ሂሂሂሂሂ"

ሄለን 'ፍሪ' ስለሆነች በሚያሳብድ ቃል ነው የነገረችኝ፤ መሳቂ አበሳጨኝ::

"እብርሽ" አለችኝ እየሳቀች::

"ምን ሆንሽ !" አወራሯ አበሳጭቶኝ ነበር::

"ተረኛው አንተ ነህ...ሂሂሂሂሂ"

ተራዬ ለእብደቱ ይሁን ለ.... አልገባኝም፤ ግን አልጠየቅኳትም:: ምክንያቱም ሄለንም በጅምላ አብዳ ሳይንሱን ጉድ ልታደርገው እየተዘጋጀች ስለመሰለኝ ነበር::

ከፍሪጅ የተጫረ እሳት 16

አዲሳባ ውስጥ ከሚኖሩ ሃምሳ ዱርዬ ሴቶች መካከል የሰላሳ ዘጠኙ ስም ሜሮን ይመስለኝ ነበር፤ አምስቱ ሄለን፣ አምስቱ ሃያት፣ አንዷ ግን አንድ ነጥብ አምስት ሚሊየን ስም እየቀያየረች የምታጭበረብርና ስሟ የማይታወቅ፤ ቦሌ ቢባል ካዛንችስ፣ ፒያሳ ቢባል አራት ኪሎ፣ ነርስ ብትሆን ሱቅ ጠባቂ፣ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ብትሆን ሴተኛ አዳሪ...ብቻ ስሟን የምትቀያይር ሴት ነበረች የምትመስለኝ::

አዎ ስሟን እየቀያየረች በአንድ ነጥብ አምስት ሚሊየን ስም የምትዶርር (ዱርዬ የምትሆን)... ትዕግስት፣ ሳባ፣ ገነት፣ ማርታ፣ መቅደስ፣ ትርሃስ፣ ሐረገወይን፣ ወላንላ፣ ዙሪያሽ፣ ፍሬ፣ ቃልኪዳን፣ ቲቲ፣ መዓዛ፣ ራሄል፣ ሚሚ፣ ሙና፣ አስናቁ፣ ዘሪቱ፣ መንበረ፣ አለምነሽ፣ ያኔት፣ ሊና፣ ሳራ፣ ሃና...አንድ ነጥብ አምስተኛው ላይ ሜሮን ትሆናለች:: እች አስስት !!

አስስት ብያለሁ አዎ !! ስም እኮ ቀለም ነው፤ ሰው ስሙን ሲቀያይር ቀለሙን ለመቀየር መሞከሩ ነው:: እና ጥሩወርቅ ጎጃምኛ ቀለሟን ቀይራ 'ሊያ' ነኝ ስትል ምን እየሆነች ነው? አካባቢዋን እየመሰለች፤ አዲሳበባን እየመሰለች:: እስስትስ ከዚህ የተለየ ምን አደረገች ? ያው አካባቢዋን ለመምሰል ቀለሟን ነው የቀየረችው:: አነጋገርን ለመቀየር የሚደረግ ድካም ምንን ለመቀየር ነው ? ቀለምን !! እናም ሰውና አስስት ከሚመሳሰሉበት ባህሪ ዋናው የተጠጉትን መምሰላቸው ይመስለኛል::

ስምንተኛ ክፍል እንደነበርኩ ፍቅር ያዘኝ:: ሜሮን ከምትባል፣ ሁልጊዜ በብዙ ሴት ጓደኞቿ ከምትከበብ ልጅ:: ደግሞ ስትስቅ ታምራለች:: ስትኩሳተር ግን ታምራለች፤ አነጋገሬ ተምታታ

አይደል ? አንዲህ ነበር የተምታታብኝ !! ቀይ ናት፡ ከቢጫነት ጋር የሚዋሰን ቅላት:: አፏ ሰፋ ያለ...ከንፈሯ ቀይና ወይታች ወረድ ብሎ የሆነ "ከምታፈጥ መጥተህ አትሰመኝም!" ብሎ የሚግራ ነገረኛ ከንፈር፤ ሕፃን ሆነን አባ ገመቹ አጥር ላይ ተንጠልጥሎ የሚያሰጎመዠንን ፕሪም የመሰለ::

የላይ እና የታች ከንፈሮቿ በአንድ ላይ ሲታዩ የሆነ ልብ የሚሰውሩ የልብ ቅርፅ:: ሜሮንን በአይኒ ሳይሆን በልቤ ነበር የማያት:: ሳያት 'የልቤ ሽፋሽፍት ይርገበገባል' ! በሰንት መከራ ያውም ወደ ዘጠነኛ ከፍል ስናልፍ "ሳይሽ የልቤ ሽፋሽፍት ይርገበገባል..." ብዬ ደብዳቤ ፃፍኩላት:: 'ሄለን እና 'ሃያት' የሚባሉት ጋጠወጥ ጓደኞቿ ጋር በመሆን በዚች ዓረፍተ ነገር ምክንያት ዓመቱን ሙሉ መሳቂያ መሳለቂያ አደረጉኝ:: መሪያቸው አንዲት ስሟን የማላውቃት አይጠ መሳጥ የመሰለች ልጅ ነበረች::ልክ እኔ ሳልፍ ደረታቸውን በእጆቻቸው አያራገቡ በሳቅ ያውካካሉ:: አይጠ መሳጢ በአካፋ ዓይኗ አሸዋ ወንድ ስትግፍ የምትውል ከንቱ !! ስሟን አላውቀውም፤ ስሟን አስር ጊዜ ትቀያይራለች፤...ስሟ ብዙ ነው:: ሁሉንም ስሞቿን የኢትዮጵያ ቄሶች ሁሉ እየተጋገዙ ይጥሩት !!

የእርሷ ሳቅ ሳቄን ገድሎታል:: የእርሷ የፌዝ ዕይታ ሩቅ እንዳላይ እንገቴን አስደፍቶኛል:: 'የልብ ሽፋሽፍት' የሚል ግጥም ፅፋ ለፀረ ምንትስ ከበብ ዓመታዊ ዝግጅት ሰልፍ ሜዳ ላይ አንብባ 843 ተማሪ ወደ እኔ ዞሮ ገልፍጧል:: 843 ተማሪ × 32 ጥርስ = 26 976 ጥርሳቸው ይርገፍና !! ቆይ የአስተማሪዎቹን ረስቼው ነበር:: + 23 × 32 = 736 − 32 (ቲቸር ሙሴ አንድም ጊዜ አልሳቁም)::

የፍቅር "እፒታይቴን" ምድረ ጥርሳም በሳቃቸው ቆልፈውት አሰራ ሁለተኛ ከፍል ጨርሼ ዩኒቨርስቲ አስከምገባ ድረስ ሴት የምትባል ፍጥረት አጠገብ ድርሽ ብዬ አላውቅም:: እና ምን ተባልኩ ? ጨዋ !! እንኳንም ያልቀረብኩ !! ምናቸው ይቀራል?! ያች አይጠ መሳጥ፤ አስቀያሚ፡ ጥርሳም፡ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊየን ስማም !! ዛሬ የራሷ አንድ ስም እንኳን ጠፍቶ ማንም 'እንቺ' የሚላት የካፍቴሪያ አስተናጋጅ ሆናለች:: ሻይ አዞ ስሙኒ ጉርሻ ለተወላት ሰብለ፡ ቡና ጠጥቶ ለገለፈጠላት ናኒ እየሆነች አስስቷ የስሟን ቀለም እየቀያየረች አለች:: ብር ዛፍ ቁርስ ቤት ሳልፍ ሳገድም ከነቀይ ሽርጧ እያታለሁ::

ዩኒቨርስቲ የተመደብኩት እዚሁ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ነበር:: ደስ አላለኝም:: ምክንያቱም ከአዲስ አበባ ውጭ ከወላጅ ራቅ ብዬ የመኖር የቆየ ፍላጎቴ ተሰናክሏልና:: አስከፊው ነገር ደግሞ ዩኒቨርስቲው "የአዲስ አበባ ልጆች እየተመላለሳችሁ ተማሩ በቂ መኝታ የለኝም" አለ፤ ይሄ ደግሞ ዩኒቨርስቲና 'ሃይ ስኩል' የሚለያዩበትን አንድ ድንበር አፈራረሰው:: ዩኒቨርስቲ ውስጥ የገባሁ አልመሰልህ አለኝ:: ወደ አስራ ሶስተኛ ከፍል ያለፍኩና እዛው የነበርኩበት ትምህርት ቤት የቀጠልኩ አይነት ስሜት ነበር የተሰማኝ:: ያ ሁሉ የተወራለት፡ በፊልም እና በሰመመን መጽሐፍ ብዙ የተባለለት የዩኒቨርስቲ ሕይወት፡ ላየው የጓጓሁለት "የግቢ ላይፍ" ውሃ በላው !! ወይ ነዶ!

አንድ አራት ወር እየተመላለስኩ እንደተማርኩ እዛው ዩኒቨርስቲው አካባቢ ቤት ተከራይቼ ለመማር ወሰንኩ:: ምንም አስቤ ሳይሆን የአዲስ አበባ ታክሲ ጊዜዬን እየበላብኝ ስለተቸገርኩ ነበር:: ማንም አልተከራከረኝም፤ ዩኒቨርስቲው ከሚወረውርልኝ ሳንቲም ላይ ቤተሰብ በየወሩ ድጎማ አየመረቀበት ቤት ተከራየሁ::...ድከም ያለች ቤት አንድ ሰፈር ውስጥ....:: እንግዲህ የእኔ ቤትና ከጎኔ ያሉት ጭርንቁስ ቤቶች በመደዳ የተሰለፉ ነበሩ:: ፊት ለፊት ደግሞ ፊታቸውን ወደ እኔ ቤት ያዞሩ በስሪትም፣ በመጠንም ከእኔ ቤት ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ሌላ መደዳ ቤቶች አሉ:: መስኮቴን ስከፍት ፊት ለፊት ያለው ቤት መስኮት ጋር እፋጠጣለሁ:: በሬን ስከፍት ፊት ለፊት ካለ በር ጋር !! በሁለቱ መደዳ ቤቶች መካከል ቀጭን የእግር መንገድ አለች:: የእኔ ቤትና ፊትለፊቴ ያለው ቤት ጣራቸው ሊገጣጠም ምንም ያህል ስለማይቀረው በመካከላችን በቀጭኗ የእግር መንገድ የሚያልፍ ሰው ረዥም ኮሪደር ውስጥ የሚያልፍ ሊመስለው ይችላል:: ከበሬ ላይ አንድ ጠቀም ያለ ርምጃ ወደፊት ብራመድ ፊት ለፊት ያለው ቤት በር ላይ አርፋለሁ:: ይሄ ነው የተከራየሁት ቤት...::

ሜሮንን ተሻግሮ ሜሮን አለች ወይ...

በአንድ ርምጃ ርቀት ጣራዬ፣ ከጣራው የሚነካካው ቤት ውስጥ ፊት ለፊቴ 'ሜሮን' የምትባል ልጅ መኖሯን ያወቅኩት ቤቱን በተከራየሁ በሁለተኛው ቀን ነበር:: በጊዜና ቦታ ርቀት ትቼው የመጣሁት "ሜሮን" የሚባል እንደ ጥላ የሚከተል ስም እዚህም መጣ:: ሜሮን...ሜሪ...ሜሪቾ... ሜሪዬ...ይላታል የመንደሩ ሰው:: ጥቁር ትሁን ቀይ አይቻት አላውቅም ነበር:: ለሰባት ወራት ያህል ጧት እየወጣሁ፣ ማታ እየገባሁ በሰላም ኖርኩ::

በአንድ ጠራራ የግንቦት ቀን ከ'ከላስ' ወደ ቤቴ እየገባሁ ነበር:: የፀሐዩ ቃጠሎ ከንፈሬን ሁሉ አድርቆታል፤ ሰውነቴ ሁሉ የተነነ ነው የመሰለኝ:: ድርቅ የመታኝ !! ቀዝቃዛ ውሃ ለመግዛት ጫፍ ላይ ወዳለች ኪዮስክ ሄድኩና "ቀዝቃዛ ውሃ ስጭኝ እስቲ" ብዬ አስር ብር ባለሰሃኑ ሚዛን ላይ ጣል አደረግኩላት:: አስር ብሩ ሚዛኑ ላይ ሲያርፍ ሚዛኑን ዝቅ አላደረገው ከፍ...

"ቀዝቃዛ የለም !" አለች አስር ብሩን በእጇ ይዛ፣

"እሽ ቀዝቃዛ ኮካ"

"ቀዝቃዛ ኮካም የለም ከውጭ ልስጥህ ?" አለች፤

"ቀዝቃዛ ነገር ምንድን ነው ያለሽ ?"

"ፍሪጅ የለኝም ከውጭ ነው ሁሉም !"

"ተይው በቃ !" ብዬ ብሬን ልቀበል እጇን ዘረጋሁ:: ቅር እያላት ብሬን መለሰችልኝ:: ፊቴን ኮሰኮስኩ: : በጣም ነበር የተበሳጨሁት:: ኤጭ!!

ቤቴ ገብቼ ቱታ ቀየርኩና ፍራሹ ላይ በጀርባዬ ተንጋልዬ በአፎይታ ተነፈስኩ:: ወዲያው በር

ሲንኳኳ በግርምት ወደበሩ ተመለከትኩ:: ጆሮዬን አቁሜ ብጠብቅም ምንም ድመፅ አልነበረም፤ መልሼ ጋደም ልል ስል በድጋሜ ተንኳኳ፤ በቀስታ ! ላለፉት ሰባት ወራት አንድም ጊዜ ቢሬ ተንኳኩቶ ስለማያውቅ ተገረምኩ:: "ማነው?" አላልኩም:: በቀጥታ ሄጄ ከፈትኩት:: እንዲት ቆንጆ ጠይም ልጅ በሬ ላይ በትልቅ የጠርሙስ ጆግ ውሃ ይዛ ቆማለች:: ጆጉ ላይ የገገረው በረዶ ስለሚታይ ቅዝቃዜው ያስጎመዣል:: ምራቄን ዋጥኩ እና ልጅቱን አየኋት:: አሷም ታስጎመዣለች፤ አሷን እንደመድኃኒት ውጦ በያዘችው ውሃ ማወራረድ ነበር!!

እየፈራች "ሱቅ ውሃ ጠይቀህ ስላጣህ ከቤት አምጥቼልህ ነው"አለችኝና ውሃውን ዘረጋችልኝ:: ሳላንገራግር ተቀበልኳት:: 'ቴንኪው' የለ ! ምን የለ !

ቆንጆ ነች ! በጣም ቆንጆ ነች ! በተለይ ዓይኗ፣ በተለይ ጥቁር የሚያብረቀርቅ ፀጉሯ ከቁጥጥሩ ገና የተፈታ እንደሆነ ያስታውቃል:: በተለይ ደግሞ ጡቷ ! የለበሰችውን ሸሰ በዲ በሸካከቶ ሊተኮስ የተሰናዳ የሆነ ተተኳሽ ነገር !! በተለይ ደግሞ ሁሉም ነገሯ::

የተጋለጠ ደረቷ ማር የተንጣለለበት ሜዳ ይመስላል:: ቆንጆ ነበረች፣ ግን ልጅ ነበረች፤ ቢበዛ አስራ ሰድስት ቢሆናት ነው:: ዞር ስትል መቀመጫዋንም አይቻለሁ...(ለምን ይደበቃል?):: ለአስራ ሰድስት ዓመት ልጅ ይበዛል፤ ግን ቆንጆ...ቆንጆ እና ልጅ፣ ቆንጆ ልጅ !! እንትፍ ትፍ ትፍ እደጊ !! መቼም አዲሳባ ቆንጆ እያጣመመ ነው የሚያሳድገው !! ለማንኛውም እደጊ !!

ከእኔ በር ወደ ራሷ ቤት ስትሄድ እኔም ውብ ሰውነቷን ቆሜ ስገመግም አንድ መንገደኛ..."ታዲያስ ሜሪ !" አላት፤ እርፍ !! ሜሮን ናት ለካ !! በፍቅር ውሃ ጥም ለዓመታት ያደረቀችኝን ሜሮን የምትባል ደረቅ ወንዝ ተሻግሬ በቀዝቃዛ ውሃ ጥሜን የምታስታግስ ሜሮን የምትባል ጅረት ላይ ደረስኩ::

ሜሮንን ተሻግሮ ሜሮን ለለቸ ወይ...

ምትና ውሃ ጥም ለንድ ለይደለም ወይ::

'እየጠጣህ አብርሽ !' ብዬ ራሴን ጋበዝኩት:: ቀዝቃዛውን ላንደቀድቀው ነበር፤ ግን ገና እንዴ ሰጎነጭለት ጥርሶቼ ሁሉ ጠፉኝ፤ ቦታቸው ላይ ደነዘዙ፤ ምን እዳ ነው ! ልብም ጥርስም ደንዝዞ የት ይደረሳል !? ጥርስ የሌለው ልበ ቢስ አንበሳ የሆንኩ መሰለኝ፣ ቢሆንም አንድ የተለኮሰ ነገር ነበር::

ፍሪጅ እና ቦኖ ውሃ በምን ይለያያል !?

ሜሮን ትላንት ያመጣችልኝን ጆግ ልትወስድ ስትመጣ ፈገግ ብዬ ተቀበልኳት:: ባዶዋን አልነበረችም:: ሌላ ጆግ ሙሉ ቀዝቃዛ ውሃ ሰጥታኝ ባዶ ጆግ ወሰደች:: ...ጆግ ውሃ ...ጆግ ...ውሃ ...፤ ከብዙ የጆግና ውሃ ምልልስ በኋላ ተቀራረብን::

"የት ነው የምትማሪው ?"

"ሚኒሊክ..." ጆግ ውሃ ...ጆግ ውሃ...

"አሳይመንት ተሰጥቶኝ ነበር ጊዜ ካለህ ትሰራልኛለህ ?"

"አምጭው ኧረ !" ብጥርጥር አድርጌ ሰራሁላት፤ አስረዳኋት፤...እንዴዴዴዴ! እንዲህ አይነት አደገኛ አስተማሪ ነበርኩ እንዴ ለካ !

ጆግ...ውሃ ...ጆግ...ዉሃ... እና አንድ ቀን ለስላሳ ቅዝቅዝ ያለ ሚሪንዳ !!

"የምን ለስላሳ ነው ሜሮን ?"

"ታዘብኩህ ዛሬ ልደቴ ነበር፤ 16 አመቴ፤ 'ሃፒ በርዝደይ!' ሳትለኝ" ፈገግ ብላ::

"በቃ ቅዳሜ ራሴ አከብርልሻለሁ"

"ፕሮሚስ ?!" ብላ የሚያምር መዳፏን በጉጉት ዘረጋችልኝ፤ ፊቷ በፈገግታ ተጥለቅልቆ ነበር::

"ፕሮሚስ !" ብዬ መዳፌን መዳፏ ላይ አስቀመጥኩ:: ለመጀመሪያ ጊዜ መነካካታችን ነበር !! እጇን አልሰበሰበችም፤ እኔም እጇን አላነሳሁም:: እግዜር "መሃላውን እስካፀድቀው እጃችሁን እንዳለ ሳይለያይ አቆዩት!" ያለን ነበር የምንመስለው:: ዓይኗ ውስጥ ፀሐይ አየሁ፤ ሁለት ፀሐይ! አማረችኝ:: የሆነ የሚያምር መናፈሻ መሰለችኝ:: ውስጧ አረፍት የተዘራ:: ሲደክም ለኖረ አንድ አኔ ሰፊ አልጋና አረፍት ያለባት አገር::

ጆግ ውሃ ...ጆግ ውሃ ...ቅዳሜ ሆነ !!

ከማክሰኞ እስከ አርብ ያላሰብኩትን ቅዳሜ ጧት ተጨነቅኩ:: የአስራ ስድስት ዓመት ልጅ ይገፍ የት አባቴ ነው የምጋብዛት ? ...ቤተሰቦቿስ ምን ይላሉ? (ለነገሩ ሴት አያቷ እና እሷ ብቻ ናቸው የሚኖሩት) ... ቢሆንም ጎረቤቱስ ምን ይላል?...ወይ ጉድ !

ሜሮን በጧት መጣች፤ ተኝታም ያደረች አልመሰለኝም::

"እንተ እስካሁን ተኝተሃል !?" አለችኝና የተኛሁበት ፍራሹ ጫፍ ላይ ተቀመጠች:: ቤቴ መግባት ፍራሽም ላይ መቀመጥ ጀምራለች:: ጧት ስትመጣ ደስ አይለኝም፤ ስስ ፒጃማ ቁምጣና ባለማንገቻ ጉርድ ቦዲ ስለምትለብስ እፈተናለሁ:: በዛ ላይ በጣም ተጠጋግተን ስለምንቀመጥ ጠረኗ አፍንጫዬን ይዞ ወደ ጡቶቿ መሃል ይጎትተኛል:: ፈተና ነው በቃ !...እርሷ ደግሞ በፍፁም 'ንጹህ' ልብ እንደፈለገች ትሆናለች::

በቃሌ መሰረት ልደቷን ልናከብር ተቀጣጠርን:: ከሰፈር አብረን መውጣቱ ለጎረቤት ሃሜት ስለሚዳርግ የሆነ አሷ የመረጠችው ሬስቶራንት ስምንት ሰዓት ላይ እንገናኝ ተባባልን...::

እኔ በበኩሌ የዚህ ዓይነት ቤት አይቼ አላውቅም፤ ቀድሚያት ነበር የደረስኩት:: ቀይ የለበሱት ጠረጴዛዎች የአገር ሹካና ማንኪያ፣ ቢላዋና የጨው የምናምን እቃ ዙሪያቸውን ተደርድሮባቸው፣ ፈዘዝ ያለ ብርሃን ያለበት አዳራሽ ውስጥ በሰፊው ተንጣለዋል::

ምኞት አይመቸኝም፤ ቅንጦት አያቀናጣኝም፤

ጨነቀኝ !

ሜሮን ስትደርስ ልቤ በድንጋጤ ልትቆም ምንም አልቀራትም:: የሚያምር አጭር ጉልበቷ ላይ የቆመ ቡና ዓይነት ቀሚስ ለብሳለች:: ውብ እግሮቿን ለማሳየት ሆን ተብሎ የተሰራ የሚመስል ረዥም ተረከዝ ያለው ጫማ፣ ጥልፍልፉ ፍርጥም ያለ ባቷ ላይ እንደሃረግ እየተጠመጠመ ወጥቶ ጉልበቷ ላይ የደረሰ...፣ ጡቶቿ ደረቱ ላይ ከፍት በሆነው ቀሚሷ ታቅፈውና ተሳስመው የሲኦል ሸለቆ እንደሰሩ...፣ ፀጉሯ ወደ አንድ በኩል ተሰብስቦ በማስያዣ ተይዟል፤ ዓይኗ በኩል ተከቧል፣ ...አህህህህህ ሰታምር! የአዲስ አበባ እናቶች አድሜ አቆጣጠር አይችሉም ይሆናል አንጂ ይህቺ ልጅ አስራ ሰድስት ዓመቷ ብቻ አይመስለኝም:: በዚህ አድሜ ቀጠሮን የመከሸን ሳይንስ እንዴት ነው መካን የሚቻለው? እኔ እኮ በዚህ አድሜም አልችልበትም::

ቆሜ ተቀበልኳት፤ ጉንጯችንን አነካካነው፤ መሳሳም መሆኑ ነው:: ...አቤት ሽቶዋ! ...ፊቴ ዝም ብላ ቆመች ! ...ቆምኩ ...አሃ ለካ ወንበር ይሳባል ! ሳብኩላት፤

"ቴንኪው !" ብላ ተቀመጠች፤

"በጣም ቆንጆ ሆነሻል"

"እመሰግናለሁ" የተጠና ምልልስ መሰለብኝ እንጂ ከልቤ ነበር የተናገርኩት:: በዚህ ቀን ከሜሮን ጋር ከዘፍጥረት እስከ ራእይ አወራን:: ሜሮን ካለ አድሜዋ የበሰለች ጉድ ነበረች፤ ...እናም እንዲህ አልኩ፣

" 'አዲስ አበባ ውስጥ ከሚኖሩ ሃምሳ ዱርዬ ሴቶች ውስጥ ሰላሳ ዘጠኙ ስማቸው ሜሮን ይመስለኛል' ግን ማናባቱ ነው ይሄን ቆጠራ ያካሄደው ደደብ...!"ሜሮን ጋር ተዋድደን ነበር በቃ ! እኔ ጋር በመሆኗ ነፍሷን እስከትስት ተደስታ ነበር::...እኔማ ነፍሴን ከሳትኩ ሰንብቻለሁ:: ልዩ ሰው አድርጋ እንደምታስበኝ ነገረችኝ፤ ሰፈር ውስጥ ዝምታዬ መስጧታል::

ደግሞ ወሬው ሁሉ ከየት መጣልኝ ? የሰው ሰው በሳቅ ልገድል !! እግዜር ሲያስወድድህ ብዙ ሳቅ የወደደህ ሰው ልብ ውስጥ ያስቀምጣል፤ ከዛም የውድህ ሳቅ መውጫ በር፣ መተንፈሻ መስኮት ያደርግሃል:: አንተ በፈለግከው መንገድ አፍህን ከፈት፣ ቃላትን አውጣ፤ ሜሪዬ የኔ ውብ አቤት ሳቋ ሲያምር ! እዛ ዩኒቨርስቲ "ሄይይ ምን አዲስ ነገር አለ ?" እያሉ ሳቅ ፍለጋ እንደሚባዝኑ ሕይወታቸውን በጊዜ ያሟጠጡ ደነዝ ሴቶች አይደለችም:: ቻፕስቲካም ከንፈራቸውን እስከጆሮ ግንዳቸው ለቀው በ 'ዊትኒ ሆስተንኛ' ለመሳቅ ቆርቆሮ ድምፃቸውን እንደሚያንኳኩ ኳኳታሞች

አይደለችም፤ ሜሪ ራሷ ሳቅ ነበረች፤ ፍንትው ሰትል ከአግር ጥፍሯ እስከ ራስ ፀጉሯ በሳቅ የምትጥለቀለቅ ! አንደእኔ አይነቱ ሰው 'ተሳቀልኝ' ቢል ያምርበታል፤ ተስቆለታላ...!!

ልብ ነበራት፤ የፍቅር የሰላም ያልተነካካ:: 'ውይ ወንዶች!' እያሉ ያለፈ እንኩሮ ሕይወታቸውን አዲስ የፍቅረኛ ምጣድ ላይ በትዝታ ሰም እንደሚጠፈጥፉ ሴቶች አልነበረችም:: ብታውቀውም ባታውቀውም ነገ ይናፍቃታል:: ማንንም አልጎዳች፤ ማንም አልጎዳትም:: ተረት የላትም !! ተረት አይደለችም:: "እነእከሌ ተፋቀሩ" ስትባል አትቀናም:: "ተለያዩ" ሲባል አትፈርድም፤ ከተማውን የሞላው ፈራጅኮ ግማሽ ፍርዱ በቀል ነው:: የደረሰበትን ሊበቀል፤ ያደረሰውን ሊያስተባብል...! ሜሪ ግን ብቻዋን ናት:: ብቻዋን ወደ ሕይወቴ መጣች፤ አልከበደችኝም::

ከዛን ቀን ጀምሮ ሁልጊዜ ማታ ማታ በር ላይ እንቆምና ስናወራ እናመሻለን:: ውሃ ልትደፋ ወጥታ ሊሆን ይችላል:: "ቻው በቃ መሸ !" ትለኝና ቆም ትላለች:: ከቻው በኋላ አንድ የሆነ ነገር የማድረግ ፍላጎት ሁለታችንም ልብ ውስጥ አለ:: ግን ማን ይድፈር ? ከቻው በኋላ አንድ ሰዓት እናወራለን:: "ምን አወራችሁ ?" ቢባል እንጃ !! ብዙ ጊዜ ቤቴ እንዳትገባ ሆነ ብዬ እከላከላለሁ፤ ፈተናው ይከብደኛል፤ ስለዚህ በር ላይ ቆመን እናወራለን:: ወሬኛ ነኝ:: የማላወራላት ነገር የለም !! ባወራሁበት የምከፈለው ደመወዝ ሳቋ ነው:: የጠገበ ደመወዝ:: እግዜርዬ የፍቅር ዩኒቨርስቲ አስመርቆ የሰጠኝ ምርጥ ስራ - "ሃሌ ሉያ !" አስመርቆ 'ስራ ፍጠር' ቢለኝ ምን ይውጠኝ ነበር ? ሳቋ ደመወዜ ነው::...አስቃታለሁ፤ የማወራላት ምንም የማይጠቅም ነገር ቢሆንም የሳቅ ደመወዜን አስቀርታብኝ አታውቅም::

ታዲያ አንዳንዴ ማታ ቆመን ስናወራ ከሩቅ የጅብ ድምፅ ይሰማል:: አውውውው...! ወደ እኔ ጠጋ ትላለች፤ ሜሪዬ የመጨረሻ ፈሪ ናት:: ጠረኗ ይጠርነኛል:: ከምሽቱ አየር ጋር ወደ ሳንባዬ ተሰገብግቤ እሰበዋለሁ፤ ጠረኗን !! አሷን ራሷን እንደአየር ስቤ ውስጤ ያስገባኋት እስኪመስለኝ፤ ጅቡን እድሜውን ያርዝምልኝና በጣም ትጠጋኛለች::

ስለጅብ አወራላታለሁ:: "የጅብ ጥፍር አንገትሽ ላይ ካሰርሽ በቃ የሄድሽበት ሁሉ ሲበሉ ነው የሚያደርስሽ"

"ውሸትህን ነው ! ሂሂሂሂሂሂ..."

"ለምን እዋሸሻለሁ በሳይንስ የተረጋገጠ ነው"

"አላምንህም ! ሃሃሃሃሃ..."

"እይውልሽ የአሜሪካ ሳይንቲስቶች ናቸው እኮ ያጠኑት"

"ው....ይ ውሸት አላምንልህም ! እንዴት አድርገው ያጠኑታል ? ... ታየኝ እኮ ስንት ሰራ ትተው አንገታቸው ላይ የጅብ ጥፍር አሰረው ሲዞሩ ! ሂሂሂሂሂሂሂሂ..." ፍልቅልቅ ትላለች::

"ቀላል ነው፤ አንድ ጊዜ ይህን ጥናት እናጥና ብለው አለቃቸውን ሊያስፈቅዱት የጅብ ጥፍር አንገታቸው

ላይ ልከ እንደዚህ እንደማተብ (እንገቷ ላይ ያሰረችውን ማተብ እየነካካሁ) አሰረው ሳይንቲስቶቹ ወደ ኃላፊያቸው ከፍል ሲገቡ ኃላፊው ምን እያደረገ አገኙት መሰለሽ...? በርገሩን እየገመጠ::"

"ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ....ውሸት ! ውሸት !"

"...ከዛ ጥናቱ ተፈቀደላቸውና ወደ አፍሪካ መጡ፤ የሆነ ሰው የማይኖርበት ጫካ አካባቢ አውሮፕላናቸው ተከሰከሰ"

"አ ማይ ጋድ ! እውነትህን ነው ?" አለች ደንገጥ ብላ::

"ያ ! ግን ማንም አልሞተም:: በተዓምር ተረፉ:: ሁሉም አንገታቸው ላይ የጅብ ጥፍር አሰረዋል፤ ከዛ የሆነ ነገር ሸትቷቸው ዞር ሲሉ ጫካው ውስጥ የሚኖሩ አዳኞች ምን የመሰለች ጥንቸል ለምሳቸው እየጠበሱ..."

"ወ...ይኔ ውሸትህ ሂሂሂሂ...አልሰማህም !"

"እስኪ ጥናቱን የበለጠ ለማረጋገጥ ወደ ሌላ ዓለም እንውሰደው አሉና ናሳ ጋር ተነጋግረው ወደ ጨረቃ የሚጓዙ ጠፈርተኞች አንገት ላይ የጅቡን ጥፍር አሰሩላቸው::"

"አሁንስ አበዛኸው ሕፃን ልጅ መሰልኩህ እንዴ ?" ብላ የውሸት ተቆጣች:: ሜሪ ከዚህ ቁጣዋ ቀጥሎ የሚፈነዳውን ሳቅ ስለማውቅ ውሸቴን ቀጠልኩበት::

"ልከ ጠፈርተኞቹ ጨረቃ ላይ ሲያርፉ ከእነሱ ቀድመው ጨረቃ ላይ ያረፉ የሩሲያ ጠፈርተኞች ራት ሊበሉ ሲዘገጃጁ ደረሱ አልሻለሁ"

"ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ ሁለተኛ አላዋራህም እሺ ! ሰታሰጠላ ! እኔ ቁም ነገር የምታወራ መሰሎኝ ! ሂሂሂሂ..." ሳቋ መቆሚያ የለውም:: እኔም በሳቋ ልቤ ሃሴት ያደርጋል::

እስካሁን ስሚያት አላውቅም:: 'ሳማት ሳማት...ከንፈሯን ጉረሰው ጉረሰው' ይለኛል፤ ጨለማ የሆነ ሰይጣን ነገር ሳይኖረው አይቀርም ! ቀን እዚሁ ቦታ ላይ ቆመን በጭራሽ የማይሰማኝ ስሜት ማታ የሚገፋፋ አንዳች ነገር አለው:: ወደ ደረቴ ስትጠጋኝ የጡቱቿ ጫፎች ደረቴን ሸንቁረው በጀርባዬ በኩል ብቅ ያሉ ይመስለኛል:: ...ፈተና ነው !

ጅብ ሲጮህ ስለጅብ አወራታለሁ:: ድመት ከጮኸ ስለድመት፤ አበባ ካለች ስለአበባ...:: ስናወራ ስናወራ ሰካራሙ ጎረቤታችን ጉግሳ እየተወላገደ፣ እየዘፈነ ይመጣል::

"አንተ ጉግሳ መጣ አራት ሰዓት..." ትላለች ሜሪ:: ጉግሳ አራት ሰዓት ላይ እንደሚመጣ የታወቀ ነው፤ የመንደሩ ሰዓት ነው ጉግሳ:: ወሬ ሲወራ ሁሉ '...ልከ ጉግሳ ሲመጣ...' ይባላል:: ልከ አራት ሰዓት እንደማለት:: እየዘፈነ፣ እየገጠመ (አያዝናና እና አያስተማረ ይሉታል ሲፎግሩ) ከተፍ ይላል፤ ጉግሳ::

ለአማሩ ሜማ የለው ለራሱ ባርኔጣ፤
የቅጣቸው አባት አሁን ገና መጣ::

ይላል ጉግሳ (ቅጣቸው ልጁ ነው):: ወተር ወተር እያለ በጨለማው ውስጥ ሲራመድ የእማማ ትሩፋት ቡችላ ትጮህበታለች:: ው ው ው ው ው ው ው ው...!!!

ጉግሳ ቆም ብሎ ቡችላዋ ወዳለችበት ግቢ በንቀት እየተመለከተ፤

"ቡችላ...! ወንድ ከሆንሽ...የአመቤትሽ ውሽሞች አጥር ሲዘሉ አትጮሂም ? በአገልግል ዶሮው ተቋጥሮ በጓሮ በር ለውሽሞች ሲላክ አትጮሂም ? ...ውሻ ...የውሻ ልጅ !! ...ይቅርታ ! ደግ እናትሽን አሰደብሽኝ...! ነፍሷን ይማርና እናትሽ ጥሩሩሩሩሩ ውሻ ነበረች:: ቤቴ ድረስ ሸኝታኝ ነበር ቤቷ የምትገባው:: ...የልጅ ዘመድ የለውም አንች..." አይጨርሰውም::

ጉግሳ እኔና ሜሪን ያየናል:: ከእርሱ በፊት ቀድሞ አጠገባችን የሚደርሰው የአረቄና ጠጅ ሽታው ነው:: ቆም ብሎ ንፋስ እንደገፋው ዛፍ እየተወዛወዘ ኮፍያውን ያወልቅና በአከብሮት ጎንበስ ብሎ (በግንባሩ እንዳይደፋ አሰጋለሁ) "ወጣቶች ልጆቻችን...የነገ አገር ተረካቢ እንደምን አመሻችሁ...! ሃሃሃሃ...!! እኛንም እንዲህ ነበር ድሮሮሮሮሮ የሚሉን፤ ኪኪኪኪ...:: የአገር ርከክቡ ሲዘገይ እየጠጣን እንጠብቀው ብለን ሰካራም ሆንን ! ሃሃሃ..." ይላል በስካር ድምፅ::

"ደህና አመሹ ጋሽ ጉግሳ!" እንለዋለን::

ትከ ብሎ ያየንና፣ "መፋቀር ጥሩ ነው፤ እጅግ በጣም በጣም...ጥሩ ነው !! ይሄ ቡዳ ሰፈር! ቡዳ እንዳይበላችሁ ቤት ግቡ!" ይለናል:: ሜሪ ሳቋን አፍና ዝም ትላለች::

"መጽሐፉ...ጋብቻ ቅዱስ ነው ይላል፤ ደግሞ ፍቅር ከሌለ ቆርቆሮ...ቁራሌ ቆረቆንዳ ነህ ይላል፤ እኔ አሁን አምሳልን አፈቅራታለሁ:: አስራ ሶስት ዓመት ስንኖር ተጣልተን አናውቅም:: ለምን ?...ፍቅር ይሻላላ !! መጽሐፉ ተፋቀሩ ይላል !...ጎበዞች ! አይዟችሁ ደህና እደሩ !" ይልና እየተወላገደ ያልፋል:: ሜሪ ደረቴ ላይ ድፍት ብላ በሳቅ ፍርስስስስ ትላለች::

ጉግሳ ትንሽ አለፍ እንዳለ፤ "እያንዳንድሽ ወየውልሽ ! ...በየጥጋጥጉ እየቆምሽ የምትባልጊ ሁሉ! ...ወየውልሽ !" ይላል እጁን ወደ ሰማይ ዘርግቶ፤ አመልካች ጣቱን እየነቀነቀ:: "መጽሐፉ... በጨለማ የሰራሽውን ሁሉ በፀሐይ እገልፀዋለሁ፤ ስራሽን እንደ በርበሬ ዛላ፣ እንደታጠበ ልብስ፣ ለወፍጮ እንደተዘጋጀ የሽሮ ክክ ፀሐይ ላይ አሰጣዋለሁ ይላል መጽሐፉ!...ወዮልሽ...! አርፈሽ አትማሪና ኮከብ ስትቆጥሪ አምሽ...!" ካለ በኋላ በዜማ ይቀጥላል፤

አንኳን ቤትና የለችም አጥር፣
ሊደጅ ላድራለሁ ኮከብ ሰቆጥር...

"...ኮከብ ቆጣሪ አስማተኛ ሁሉ...!!" ሌላ ርዕስ ውስጥ ይገባል፤ ጉግሳ እንዲህ ነው::

ሜሪ ጋር አንዳንዴ 'ወክ' እናደርጋለን:: ንፁህና ፀጥ ያለ ኤምባሲ አለ:: በሱ በኩል ማታ ከጎኗን ደገፍ ብላኝ በጣም ተነካከተን ብርዱ ለስላሳ ቆዳችን ላይ የፈጠራቸው መንደብደቦች - የእኔ እንድብድቦችና የሜሪ እንድብድቦች እየተነካኩ፣ ሽቶዋ እየተቀላቀለብኝ ደስ ብሎን እንዝናናለን:: ስንሄድም ሆነ ስንመለስ አገር ቢያየን ግድ አልነበረንም:: አሁን አውርተናል:: 'ውስጤ ውስጥ ነሽ' ብያታለሁ፤ 'ወድጄሻለሁ!' ብያታለሁ፤ ምንም አላለችኝም፤ ግን እንባዋ መጥቶ ነበር::

አንድ ቀን ከ'ወክ' ስንመለስ እኔ ቤት ገባን:: ፍራሽ ላይ እግሯን አነባብራ ዘርግታ ተቀመጠች:: ቀሚሷ ስላጠራት ትንሽ ተጨናንቃ ነበር:: አጠገቧ ተቀመጥኩ:: ሁለታችንም የሆነ ነገር በጣም በጣም ፈልገናል፤ ግን...፤ አየኋት ቀሚሷ ላይ ባለች ቁልፍ ትጫወታለች:: ፈራሁ ! ... አዕምሮዬ በሀሳብ ተራወጠ፤

1. የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንዲት ሴት አሰራ ስምንት ዓመት ሳይሞላት ወዳና ፈቅዳም ሆነ ሳትወድና ሳትፈቅድ ወሲብ ብትፈፅም፣ ወሲብ የፈፀመባትን ሰው ዘብጥያ ...ከርቸሌ... ወላ ጀሜ አስገባው ይላል!!

2. ሕገ አግዜር ወዳ ፈቅዳ ሴት ወንድ ምናምን አይልም፤ "አታመንዝር!" በቃ !! ከፈለግክ የከጀልካትን ሴት አግብተህ አንዳሻህ ሁን:: አለበለዚያ አምሮትህን 'ሲያምርህ ይቅር!' ብለህ ገስፀው:: ከዚህ በተረፈ ሲአል ወላ ጀሀነም ትወረወራታለህ ! ይላል::

3. የእኔ ይዞ ሚች ልብ የሜሪን የሚያምር ባት፣ የፈረጠመ ዳሌና ጫፋቸው የሚጣራ ጠይም ጡቶች እያየ ከምድራዊውም ከሰማያዊውም ሕግ ሊያጋጨኝ በደም ፍላት ደም ይረጫል:: ልቤ ሲደልቅ ግግም ግግም...ግግም ሲል አንድ ታዋቂ ትግረኛ ዘፋኝ ከነከበሮ ደላቂው በልቤ አዳራሽ የሙዚቃ ስራውን የሚያቀርብ ይመስለኛል::

የልቤ ምክር፣ "አብርሽ ሜሪ ትወድሃለች:: ያደረጋችሁትን ለማንም አትናገርም:: ደግሞ እያት ከንፈሯ እንዴት እንደሚንቀጠቀጥ...ስትንከረፈፍ አንዱ እንዳይልፍህ !...እጆችህን ጡቶቿ ላይ አሳርፋቸው - አይዞህ ጠጋ በላት...:: ኤጭጭጭ የምን መጨናነቅ ነው...የወንጀል ሕጉ አንጀባ ነው ባክህ !...እግዜር ደግሞ እንኳን አንተን ስንቱን ይቅር ብሎ የለ !? ...ኧረ ሳይመሽ ፍጠን ! ነገ በዚህ ስሜት አታገኛትም:: እንደውም ያልፈለካት መስሏት በዛው ነው የምትቀረው...ቱ..." ብሎ ደም ይተፋል ልቤ፤

እነሆ በህገ እግዜር፣ በወንጀለኛ መቅጫ ህግና በግልፍተኛ ልብ መሃል ሚስኪኑ አብረሃም...

ሜሪ አንድ እግሯን ሰብሰብ ስታደርገው ከጠይምነቷ የቀላ ለስላሳ ታፋዋ ተጋለጠ:: ቀሚሷን ሳብ አደረገችው፤ ግን አልሸፈናትም:: ቀጥ ብላ አየችኝ:: አይኗ ቡዝዝ ብሎ ነበር:: ትከሻዬ ላይ ራሷን ደገፍ አደረገችው:: ...ኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡ ጠረኗ አመንዝር ይለኛል::

ውቢቷ አመንዝር ይለኛል...:: ልቤ አመንዝር ይለኛል...:: ቤቱ አመንዝር ይለኛል...:: ሁኔታው አመንዝር ይለኛል...::ፍራሹ "ኑ እንጂ እየጠበቅኳችሁ አይደለም እንዴ! የምን መጎለት ነው!' ይለኛል:: እርግጠኛ ነኝ ሰይጣንም እንደአምፊ ቲያትር ከነጅሪው ተሰብስቦ እያየን ነው::

ሜሪ በቀኝ እጇ ጣቶች እየተጫወተች ነበር:: አቤት እጇ አለሳለሱ !! ደግሞ ይሞቃል ! ...ቆይ ምናባቴ ነው የማደርገው ? ... ሕግ ይሄን ያያል ? አያይም ! ?

ሕግ የሜሪ ጡቶች ማማራቸውን እንደቅጣት ማቅለያ ያያል...?

እናቴ አበባ ይዛ ምርቃቴ ላይ ለመገኘት ካሁኑ ስታወራ ምን ያህል በደስታ እንደምትምነሸነሽ እያወቅኩ...ምርቃት በቴሌቪዥን ባየች ቁጥር "አሁን የኔ ልጅ..." እያለች በደስታ እና በተስፋ ፊቷ ላይ የምትለኩሰውን ብርሃን እፍ ብዬ ላጥፋው ? "ልጅሽስ ?" ስትባል (ኧረ ሳትባልም::) በኩራት "ዩኒበርስቲ ገባኮ" እያለች በሳቅ የምትምነሸነሽ እናቴን በሐዘን አንገቷን ደፍታ አሰር ቤት ሰሃን ይዛ እድሜ ልኳን እንድትመላለስ ልፍረድ ? ... ከሁሉም በላይ እግዚያብሄር ይቅር ባይ ነው፤ ልከ ነው ! የንስሃ ቀብድ ግን አይቀበልም:: "ላጥፋ እንዴ፣ ይቅር ትለኝ እንደሆን ?" እንደማለት !!

የሜሪን እጅ ከእጇ ላይ አነሳሁ:: ከፍራሹ ላይ ተነስቼ ቆምኩ፤ ከዛም "መሸ አይደል ?!" አልኳት፤ "ውጪ" ነበር የሚመስለው አነጋገሬ - ገብቷታል:: ተነስታ ልብሷን አስተካከለችና "አንተ ፍሪጅ አያስፈልግህም፤ ራስህ ማቀዝቀዣ ነገር ነህ" አለችኝ:: "ደህና እደር!" ሳትለኝ ወጣች፤ አልተመለሰችም!! የፍሪጅ ውሃውም በዛው ቆመ !!

እግዚያብሔር ታዲያ እንዲህ ሲል በታላቅ ድምፅ ያወጀ መሰለኝ፣

"ልጄ አብረሃም ሆይ ! ህግጋቴን ላከበሩ፣ በፈተና ሰዓትም የቃሌን ጭላንጭል ሊመለከቱ ለተፍገመገሙ ሁሉ፤ አንድ ጆግ ቀዝቃዛ ውሃ ቢከለከሉ እንኳን ስለነሱ ዓለምን በቀዝቃዛ ውሃ አረሰርሳታለሁ !!!"

ከረምት ገባ !!

ዝናብ፣ ውሽንፍሩ፤ ደመናው ... አዲስ አበባ ቀዝቀዝ አለች !! ከረምቱ የእኔ ከረምት መሰለኝ::

አዲሳባ ውስጥ ፍሪጅ ካላቸው ሃምሳ ሴቶች መካከል ሃምሳውም ስማቸው ሜሮን ይመስለኛል፤ የፍሪጆቹ ዓይነትና ስም ቢለያይም ባህሪያቸው አንድ ነው፤ "አመድ በዱቄት መለወጥ" በሰጣት ጠብታ ውሃ ጎርፍ ማንነትን በውለታ መልከ መቀበል ያምረዋል - ፍሪጁ !! ፍሪጁን ከነስጦታው የሚሹ ይሄ ታላቅ ከረምት የእነርሱ አይደለም !!

ፍራሼን ተመለከትኩት፤ ሰፊና ንፁህ ነው:: ብቸኝነት ሰላም፤ ፍራሹም ሰፊ ነው::

17 የታረሙ ነፍሶች

እጅጋየሁ ማታ ሦስት ሰዓት ላይ በቤታችን ስልክ ደወለች... 'ማዘር' ጋር አሰራ አምስት ደቂቃ የሚሆን ሲያወሩ ቆዩና ጥግብ ሲሉ ማዘር እንዲህ አለች፣ "አብርሽ ስልኩ ያንተ ነው ና አናግራት...ቶሎ በል እንዳይቆጥርባት እጅግዬ ናት::"

እጅጋየሁ ሰባትና ስምንተኛ ክፍል አብረን የተማርን ጓደኛዬ ናት:: ይሄው እስካሁንም እንኳን ከኔ ጋር፣ ከቤተሰብ ጋርም ጥብቅ ወዳጅ ሆና ቀጥላለች:: በተለይ ማዘር ጋር በከፉ ቢደጉ ይጠያየቃሉ፤ እንደውም እውነቱን ለመናገር እጅጋየሁ ከእኔ ይልቅ የእናቴ ጓደኛ ነው የምትመስለኝ:: ከልቧ ጥሩ ልጅ ናት:: የታመመ አሳዳ የምትጠይቅ፣ ሃዘን ካለ ከሃዘንተኛው ሳትለይ የምታፅናና (ጊዜው እንዴት ይበቃታል?) ሰርግም ካለ የጥሪ ካርድ ከማዘጋጀቱ ጀምሮ እስከቤተሰብ ቅልቅል ጎንበስ ቀና ብላ የምታዳድር ሌሎችን የማገልገል ፀጋ ያትረፈረፈላት ልጅ ናት:: እች ናት እጅጋየሁ !!

እኔ ታዲያ ወሬዋ ይሰለቸኛል:: ይንዛዛል:: ማቋረጫ የለውም (ስለእጅጋየሁ ወሬ ለእናቴ ስነግራት ግን 'ይንዛዛል' አልልም፣ የምለው "ትንሽ ወሬዋ ዘለግ ይላል" ነው:: እናቴ ታዲያ እንዲህ አሳምሬም ነግሬያት ትበሳጭብኛለች፣ "ሂድ እባክህ ወሬኛ ! ዝም ብለህ ወረቴ አለቀ አትልም... ዘለግ....አጠር !! ሆዲ ከፋት የለውም፤ ውስጧ ያለውን ሁሉ ስለምታወራ ነው፣ 'እንደሌሎቹ' ነገር በሆዲ የምታብላላ 'ማሽንክ' አይደለችም::"

እንግዲህ "ሌሎቹ" እና "ማሽንክ" የሚሉት ቃላት ዝምተኛዋንና የአሁኗን ፍቅረኛዬን 'ቤዛ'ን ኢላማ ያደረጉ የእናቴ ጥይቶች ናቸው፤ እናቴ ቤዛን አትወዳትም:: ከእጅጋየሁ ጋር እንድንጋባ ነበር ፍላጎቷ:: ምን ያደርጋል፣ እጅጋየሁም አይታኝ አይታኝ አገባች:: (እረ እንዲያውም የዛሬ ስድስት ወር አካባቢ 'ወለድኩ' ብላ ማዘር ሄዳ አይታታለች::) እኔም ከቤዛ ጋር ፍቅር ጀመርኩ::

ከስምንተኛ ክፍል ወደ ዘጠኝ አልፌ ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ስዘዋወር እጅጋየሁ ደገሙችና

እዛው ስምንተኛ ከፍል የተማርንበት ትምህርት ቤት ቀረች:: ታዲያ ልክ መስከረም ገብቶ ትምህርት ስንጀምር ደብዳቤ ፃፈችልኝ:: ደብዳቤዋ ላይ መቼም የማልረሳው ግጥም ነበር::

የባህርዳር ቅጠል ዳርዳሩ ለስላሳ፣

ተለያየን ብለህ እንዳንረሳሳ::

እኔም ያለሁ አዲስ አበባ እሷም ያለች አዲስ አበባ፣ "ባህርዳር ድረስ ሄዶ ቅጠል የሚያስበጥስ፣ ሙሾ የሚያስወርድ ምን ጉድ ተፈጠረ?" አልኩና ተገረምኩ:: እጅጋየሁ ነገረ ሰራዋ ሁሉ የትልቅ ሰው ነበር ፤ ያኔ ትልቅ ሰው ማለት ዛሬ ላይ አካባጅ የሚለውን ቃል ይተካል::

ይሄው ዛሬ ደግሞ ደወለች:: መቼም የደወለችበት ምክንያት ወይ የታመመ አልያም የሞተ ሰው ቢኖር ነው:: ሁለቱም ግምቶቼ ልክ ካልሆኑ ግን የሚያገባ ጓደኛችን አለ ማለት ነው::

"ሄሎ"

"እንተ...ወይ የሰው ነገር:: በቃ እንዲህ በዋል ፈሰስ ሆነህ ቀረህ ? ምን ይሻልሃል ? ወሊድኩ ብዬ እፍ አውጥቼ ተናግሬ 'ማሪያም ትማርሽ!' ማንን ገደለ ?"

"አይ...ኧ..." አፍሬ ነበር::

"ተወው ተወው... ደህና ነህ ግን ? ስራ ጥሩ ነው ? ቤዚዬስ እንዴት ናት ? ባለፈው መንገድ ላይ አግኝቻት ጉንፋን ያዘኝ ብላ፣ ተሸላት ? ውይ የሷ ነገር በሽታ አትችልም እኮ ሂሂሂሂ" የትኛውን ልመልስ ? ትቀጥላለች:: "አብርሽ ልጄ አለቀሰችብኝ፣ ቶሎ ጉዳዬን ልንገርህ...ቲቸር በለጠ እኮ ሞቱ..."

"ምን...?"

"ይሄውልህ ዛሬ አረፉ:: ነገ ሥላሴ ነው ቀብራቸው፣ ልንገርህ ብዬ ነው፣ ከተመቸህ ብቅ በል - አብርሽ ...አባከህ ከሰው አትለይ..."

"ትቀልጃለሽ በዚህማ አይቀለድም:: ...ለቲቸር በለጠ ቀበር ...ብሞት አልቀርም ለምን ሺ ስራ ጥንቅር አይልም" አልኩ::

"ግን ምን አገኛቸው በናትሽ...?"

"ሚስታቸው...አንገብግባ ገደለቻቸው::"

"አትቀልጅ ባክሽ"

"እመቤቴን ! በስተርጅና እንዲት እሳት አግብተው፣ ቀን ምድረ ውሪ ጋር ሲዳረቁ ውለው ሲገቡ እሷ ደግሞ ማታ ከቤት በምላሷ ትጠብሳቸዋለች:: ቢቃ ሳይደላቸው ድፍት አሉትና አረፉ ከንፈሯን መጠጠች::

"የሚስት ምላስ ቢደፋ ኖሮ ቢኒ ገና ድሮ..." ቢኒ ባሷ ነው::

"አትሞጣሞጥ አንተ! እኔይቱ ልጅት!" ሳቋ ይቀድማታል:: ነገ መምህር በለጠ ቀብር ላይ ልንገናኝ ተቀጣጥረን ተለያየን::

*** *** ***

ምንጊዜም የአማርኛ ክፍለጊዜ ሊጠናቀቅ ሲል አሮጌ የሸራ ቦርሳቸውን ከፍተው በስርዓት ከተሰደሩ ወረቀቶች መሐል አንድ በካኪ ወረቀት የተሸፈነ ትልቅ መፅሐፍ የሚያወጡ፣ ከወገባቸው በመጣ ጎበጥ ያሉና ትንሽ ዘርፈፍ ያለ ቅጠልማ ሹራብ የሚለብሱ አድሜያቸው ወደ ሃምሳ ዓመት የሚሆን ሰው - መምህር በለጠ !!

ተማሪዎቻቸው መልስ ስንመልስ ትናንሽ ዓይኖቻቸውን ጠበብ አድርገው በጥሞና ሲመለከቱን በዓይናቸው የሚያዳምጡን ይመስለን ነበር:: መምህር በለጠ !! በመምህር በለጠ ከፍለ ጊዜ ደስታችን ፊታችን ላይ ይንበለበላል:: የማይወዳቸው ተማሪ አልነበረም:: መስፍን እንኳን አምስት 'ፔሬድ ዘግቶ' በእሳቸው ከፍለ ጊዜ ቢሞት አይቀርም::

እንደውም አንድ ቀን በቲቸር በለጠ ከፍለ ጊዜ ለመታደም በአጥር ዘሎ ሲገባ ተይዞ ወላጅ ጠራ፤ የመስፍን አባት፣ "ይሄ የልጄን የትምህርት ፍቅር ነው የሚያሳየው፣ ዘሎ ሲወጣ አልተያዘም ዘሎ ሲገባ እንጂ" አሉ:: መስፍን ከግቢ ውጭ የበላው ፓስቲ የዘይት መሃተሙን ከንፈሩ ላይ እንዳተመበት በቲቸር በለጠ ከፍለ ጊዜ ከተፍ ይላል - ያውም ፊት ወንበር ላይ !! በሐሰብ ከፍለ ጊዜ መስፍን 'ፊት ወንበር ሂድ!' ከሚባል ሞያሌ ድረስ በባዶ እግሩ ቢሄድ ይሻለዋል።

...በካኪ ወረቀት የተሸፈነው መጸሐፍ ይከፈታል፣ "ፍቅር እስከ መቃብር" ነው !!

በመምህር በለጠ ሊተረከ ተከፈተ:: ምድረ ማቲ አይናችን፣ አፋችን አብሮ ተከፈተ:: ፍቅር እስከ መቃብር ተነስቶ መምህር በለጠን አለማንሳት፣ ከመጸሐፉ ላይ በዛብህን ከመርሳት አይተናነስም፣ እንደውም ፍቅር እስከ መቃብር ገለጥ ገለጥ ቢደረግ፣ በዛብህ...ሰብለ ወንጌል...ጉዱ ካሳ...መምህር በለጠና...ፊታውራሪ መሸሻ አኩል የመጸሐፉ ገፀ-ባህሪያት ሆነው የሚገኙ ይመስለኛል::

በሚያምር ድምፃቸው ትረካውን ይጀምራሉ:: ከዝምታችን ብዛት የልብሳችን ቱማታ ይሰማል፣ ጭጭ...መምህር በለጠ በትረካቸው መሐል የግል አስተያየታቸውን ይጨምራሉ:: አንዳንዴ አስተያየቱን ጣል የሚያደርጉት በሚተርኩበት ድምፅና ፍጥነት ስለሆነ አስተያየቱን ከታሪኩ መለየት ያዳግተናል ፤ ቢሆንም አስተያየቱን የታሪኩን ያህል እንወድደዋለን::

እንደ ፊታውራሪ እየጎደሩ፣ እንደ በዛብህ እየተቅለሰለሱ፣ እንደ ሰብለ ረጋ ብለው፣ እንደ ጉዱ ካሳ እያፈዙ እና እያሸሞሩ፣ እንደ ሃብትሽ ይመር እየተቆናጠሩ፣ እንደ ቄስ ሞገሴ እየተሸቆጠቆጡ በግርምት አስጥመውን...እያለ ኪሊሊሊሊሊሊሊሊ ይላል ከፍለ ጊዜው ማብቃቱን የሚያረዳው ደወል:: ኡኡኡኡኡኡኡኡኡ...ኤጭጭ...! በየአፋችን እንንጫጫለን::

'ቲቸር' መጻሐፉን ደጋግመው ደጋግመው ሰላነበቡት የሚበልጠውን በቃላቸው ነበር የሚወጡት፤ እያነበቡ ድንገት በመሐል አንዱን ወይም አንዷን ተማሪ ይጠራሉ፣

"ሃና!"

"አቤት ቲቸር!" ድንገት በመጠራቷ ደንግጣ ታፈጣለች:: የከፍላችን ጎበዝ ተማሪ ናት ሃና...

"የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎት ምንድን ነው ?" ይጠይቋታል::

"ምግብ...ልብስ...መጠለያ..." መለሰችው እንላለን እኛ በሹክሹክታ:: ገና ትላንት ነው አካባቢ ሳይንስ መምህርታችን ያስተማረችን::

"አይደለም ! በጭራሽ አይደለም ! ሳይንሱ እውነታውን ጋርዶብናል:: እንጀራን ማን ሀሊና ውስጥ ቦታ ሰጠው ? 'የምድር ፍሬ፣ የወንዝ ውሃ ይሙላህ' የተባለን ሆድ ማነው የሰው መሰረት ያደረገው? የለም! በየጫካው በየዱሩ ርቃናቸውን የሚኖሩ ወገኖቻችን ርቃናቸው ጌጣቸው ነው፤ ቤትስ ቢሆን - የሰው ልጅ ተንኮሉን ሊከልል፣ ማካፈሉን ሊጋርድ ግድግዳ አቆመና 'ስለታም' እንዳይባል 'ቤት መሰረታዊ ፍላጎት ነው' አለ - ለግርዶሹ ስም አወጣ:: ልጆች ልብ በሉ...የሰው መሰረታዊ ፍላጎት አንድ ነው፣ እሱም ፍቅር ነው:: ካለፍቅር ሰው የቁም ሙት ነው:: ሰው ሰውን ሲያፈቅር፣ ሰው አምላኩን ሲያፈቅር፣ ሰው አገሩን ሲያፈቅር፣ ሰው እውነትን ሲያፈቅር፣ ሰው ነፃነትን ሲያፈቅር ነው ህያው የሚሆነው:: ሰው ነገውን ሲወድ፣ ነገውን ሲያፈቅር ነው ነገ ለሚፈጠር ትውልድ ፍቅር የሚያወርሰው ... አስትንፋሱ የሚቀጥለው:: በሉ መልሱልኝ፣

"በዛብህ እንጀራ አጣ?" ይጠይቁናል::

"አላጣም!" በአንድ ላይ እንመልሳለን::

"ልብስ አጣ?"

"አላጣም"

"ቤትስ?"

"አላጣም"

"እያችሁ! ፍቅርን ብሎ፣ ፍቅርን ተርቦ፣ ፍቅርን ተራቁቶ ሲንከራተት አባይ በረሃ የሸፍታ ሲሳይ ሆኖ ቀረ!" እዝን ብለው በመስኮት ወደ ውጭ እየተመለከቱ ከቆዩ በኋላ፣ "ፍቅር ነው የሰው መሐሉ" ይሉና ሁላችንንም ያዩናል...

መምህር በለጠ ይሄው ሞቱ ! እጅጋየሁ እንዳለችው በሚስታቸው ብስጭት ሞተው ከሆነ የሰበኩትን ፍቅር አጥተው ሞቱ !!

ሃና የከፍላችን ንበዝ ተማሪ ታዲያ ያሏትን 'ለቀም' አደረገችና የአካባቢ ሳይንስ ፈተና ላይ የሰው መሰረታዊ ፍላጎት 'ፍቅር' ነው ብላ በመመለሷ 'ኤከስ' ገባባት::

ቲቸር በለጠ ይሄን ሰምተው ሳቅ አሉ፤ ከዛም ረጋ ብለው መከሩን፣

"ልጆች! በሉ የተባልነውን ሰንላችሁ ብቻ ነው ትምህርት ተማራችሁ የሚባለው:: የነፍስ ሃቅ ትምህርት መስሏችሁ ተቀብላችሁ አትሩጡ!! ነፍስ ያመነው እና ወረቀት የሚያምነው የተለያየ ነው:: ይሄን አትርሱ:: የነፍስን እምነት የሚሸከም ትከሻ ያለው ወረቀት እምብዛም ነው:: ሰንቱ ነብሱ ሹክ ያለውን ለወረቀት ሹክ ብሎ እንጦሮጦስ ወርዷል !!" ብለው በዝምታ ከዳር አስከ ዳር የተኮለኮልነውን ተማሪዎች ይቃኙንና ድንገት፣

"ሃና !" ብለው ይጣራሉ፣

"አቤት ቲቸር!"

"...አስተማሪሽ ነፍስሽን ማረም አትችልም፣ ለዛ ነው 'ኤከስ' የገባብሽ" ካሉ በኋላ የሃናን አማርኛ ደብተር ወስደው በቀይ አስከርቢቶ ፈረሙበት:: "አማርኛ ፈተና ላይ ሁለት ነጥብ ጉርሻ ሰጥቼሻለሁ::" የሃና ነፍስ ታረመ !! (ሃኒን ከብዙ ዓመት በኋላ አንድ ዓለም አቀፍ ስብሰባ ላይ በጦርነት ስለሚጎዱ ህፃናትና እናቶች የምርምር ወረቀት አቅርባ በቴሌቪዥን አየኋት:: ያቀረበችውን ወረቀት አፈላልጌ አነበብኩት:: አውነትም ሃኒ ነፍሷ ታርሟል::)

መምህር በለጠ...ትረካቸውን ቀጥለው እንደፈዘዝን...ድንገት፣

"አንተ አሳት ትውልድ ዝሙትና ፍቅር የየቅል ነው:: ሰብለ ዝሙት ብትሻ እንደ ውሻ እግሯን የሚከተል መኳንንት ነበረላት:: ልብ በሉ ... ትዳር አያስጨፍርም:: 'ብቻዬን ከመውደቅ ሁለት ሆኜ ልውደቅ' የሚሉም ጅሎች ናቸው ፤ አብሮ መሆን እና አንድ መሆን የየቅል ነው:: ትዳር አንድ መሆን ነው !! በጥቅም በሰከረ ትዳርና በፍቅር በሰከረች ሰብለ መሐል አንድ የሰከረ እርምጃ ሲቀር ፍቅር በመሐል ገባ::

...በላይ ዘለቀ ከነተከታዮቹ ቤልጅግ ይዞ የናኘበትን ጫካ ሰብለ ፍቅር ታጥቃ ብቻዋን ዘመተችበት:: በላይም ለአገሩ ፍቅር፣ ሰብለም ለበዛብህ ፍቅር ... አያችሁ ... የአባይን በረሃ

የሚያሸግር ድልድይ ምንድን ነው ... ፍቅር !! ያልተበረዘ ያልተከለሰ ሃቅን ወደ ትውልድ ማስተላለፊያው መንገድ ምንድን ነው ? ፍቅር!! ሰብለ እንበሳና ነብሩን ፊት ለፊት ተጋፈጠች ...!"

"መስፍን!"

"እቤት ቲቸር!"

"...እንተ ዱርዬ ፓስቲ ቤት ለፓስቲ ቤት ልጃገረድ ይዞ መዞር ፍቅር አይደለም..." የከፍሉ ልጅ በሳቅ ያውካካል:: መስፍን ሁልጊዜም ከሴቶች ጋር ሻይ ቤት መታየቱ የታወቀ ነው::

"እበባ!"

"እቤት!"

(ወደ አበባ በመጸሐፉ እየጠቆሙ) "ከማንም ጎረምሳ ጋር ሲገቡና ሲወጡ መላፋትና መጓተት ፍቅር አይደለም:: ፍቅር ራሰን ያስከፍላል:: ፍቅር ብታገኘውም ያስከፍልሃል፣ ብታጣውም ያስከፍላል ... ክፍያው የየቅል ቢሆንም !!"

መምህር በለጠ በአማርኛ ከፍለ ጊዜ የፍቅር ሰዋሰው የሚያስተምሩ፣ የነፍሳችን ስንኝ ከፍቅር ስንኝ ጋር ቤት እንዲመታ የግሰውን መምህር ይሄው እንደተባለው ከሆነ 'ፍቅር ተርቢው' ሞቱ !!

"...እሳት ትውልድ ንቃ፣ ዘመኑ የእነ ቁስ ሞገሴ ዘመን ነው:: ተመሳስሎ፣ ተለጥፎ የመኖር ዘመን:: ሆድን እናት ላይ እስቀምጦ እዩኝ ማለት:: ፊት ለፊት 'ለምን?' ከማለት ፊት እያዩ፣ ፊትን የመምሰል አስለትነት አዋቂ የሚያስብልበት ዘመን ነው:: አባብነት ዝና የሆነበት:: አንጉዱ ካሳን የማውጣዘ ዘመን..." ይላሉ ሲናገሩ አንዳንዱ ከተረከዘቸው ብድግ ብለው በጥፍራቸው እየቆሙ መፅሐፉን በአመልካች ጣታቸው አልባትነት ከፍለው ይዘው ከፍ ዝቅ እያደረጉ ስለሆነ፣ የሙዚቃ አኬለትራ መሪ ይመስሉ ነበር::

ሞቱ መምህሩ !!

አንድ ቀን 'አበበ በሶ በላ' ብለው ፃፉና፣ "አበበ አንተ ነህ፣ አበበ አኔ ነኝ፣ አበበ በዛብህ ... አበበ ሰብለ ናት:: ... አበበ ጉዱ ካሳ፣ አበበ ቁስ ሞገሴ፣ አበበ ፊታውራሪ መሸሻ ... አበበ ወዛደሩ፣ አበበ ምሁሩ":: አነጋገራቸው ስብከት ይመስል ነበር::

" ... አበበ ሰብለ ስትሆን፣ በሶው ... የታሰርክበትን የባህል ሰንሰለት በፍቅር ቢላዋ መበጣጠስ ነው:: ... የጥቅም ጣኦትህን አሽቀንጥረህ የፍቅር ፅላትህን ማንገስ ነው:: አበበ በዛብህ ሲሆን፣ በሶው መርገምትና ማሰፈራራያን የናቀ ፍቅር ነው:: ሌሎች ሰራላቸው ደስታ የሚጉብህን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሰእለት ማሸቀንጠር ነው::ላልተሳልከው ስእለት ህይወትህን

አለመስጠት !! አበበ ፊታውራሪ መሸሻ ሲሆን በሶው ቅራሪ ርዝራሽ የዘር ማንዘር ከብር ነዉ ... በዘር መኮፈስ ... ትዕቢት:: አበበ ጉዱ ካሳ ሲሆን፣ በሶው በጨለመ ዘመን በአብደት ደመና የተሸፈነ መብረቃዊ መገለጥ ነው..." አሉና ከስተር ብለው ቃጭን::

ይሄው 'ቲቸር በሰጠ' ሞቱ !!

*** *** ***

የቲቸር በለጠን አስከሬን ከተሸከሙት ሰዎች መካከል አንዱ እኔ ነበርኩ:: ከፊቴ መስፍን ሳለ፣ አስከሬኑ ከበደኝ:: የተሸከምኩት የመምህሬን ኮሰማና አካል መሆኑን አስከጠራጠር አስከሬኑ ከበደኝ... !!

በአብረቅራቂ ልብስ ተሸፍኖ በእሳት ትውልድ ታጅቦ ወደ መቃብር የሚጓደፈው አስከሬን ጋር ...ሰብለ ...በዛብህ ...ጉዱ ካሳ ...ፊታውራሪ መሸሻ ...የኢትዮጵያ ሰነ ጽሁፍ ...ታላላቆቹ የጥበብ ሰዎች ...ፍቅር ራሱ አብረው ወደ መቃብር እየተወሰዱ መሰለኝ:: ካለነገሩ አልከበደኝም ይኔ አስከሬን !! አህሳ ...ማን ተረፈ፣ ...እነ ቄስ ሞገሴ አልቃሽ ሆነው፣ ቀበር ቆፋሪ ሆነው፣ አሽቢ ሆነው ምድርን ሞልተው...

አበበ መምህር በለጠ ሲሆን፣ በሶው ነፍሱ የታረመ ትውልድ ነበር!!

ይሄን ያለ ግን አልነበረም:: ሁሉም ሰው የሚያወራው ስለሚለታቸው አቃጣይነት ብቻ ነበር ከሚቹ ይልቅ የሞቱ ምክንያት መግነኑ የሞተን ሰው ሥራ ህያው ከማድረግ ይልቅ የቋሚን መቆም በምክንያት መዘለፍ ስለሚቀል ይሄንኑ ተራ መንገድ የመከተል አምልኮ መሰለኝ::

በብረትና ቻፕስቲክ በተከበበ ከተማ እነሆ የመልአክ ድምጽ ተሰማ 18

እንዲት ፍቅረኛ ነበረችኝ:: ይሄን አደረገኝ ሳትል ርግፍ አድርጋ ተወችኝ:: የተወችኝ ሰሞን አዕምሮዬ ነገር አየቀሳቀለ አስቸግሮኝ ነበር:: የምይዝ የምጨብጠውን አጥቼ ነበር:: ብዙ ነገር ነበር:: በተለይ ደግሞ ከተለያየን ከአምስት ወር በኋላ እንደወለደች ሰሰማ "አንዲት ሴት የምታረግዘው ስንት ወር ነው?" ብዬ አሰብኩ:: መቼም ከእኔ አለማርገዟ ጥያቄ አልነበረውም፤ ምክንያቱም "ከጋብቻ በፊት ዝንቤን እሽ እንዳትል!" ብላኝ ስለነበር ቃሏን አክብሬ ከመሳም ዘልዬ አላውቅም::

ለዛውም ከንፈሯን እየሳደድኩ ነበር የምስማት:: በደቡብ በኩል ከንፈሬን ሳምጠሙጥ ወደሰሜን እየዞረች፤ ከሰሜን ስንደረደር ወደ ምስራቅ እየሸሸች ፍዳዬን አብልታኝ ነበር የኖርነው:: ስንትና ስንቴ ከንፈሯን የሳተ ከንፈሬ ባዶ አየር ሰሚል:: አየር ስታስመኝ ከርማ በመጨረሻ አየር ላይ ትታኝ ሄደች:: ደግሞ እኮ የአካሄዷ ከፋት "ቻው" ማለት ሃሳንን ገደለ ? "አልፈልግህም!" ማለት ምን ችግር አለው ? አንድ ቅዳሜ ደውዬ "ዛሬ እንገናኝም እንዴ ፍቅር?" ስላት "ለምንድን ነው የምንገናኘው ?" ብላ ግራ የገባው ጥያቄ ጠየቀችኝ:: በቃ በዛው ቀረች::

እና ይሄው በተለያየን በአምስት ወሯ ወልዳ አረፈችው:: ነርስ ነበረች፤ በኋላ ስሰማ አንድ ዶክተር ነው አሉ ያገባት:: እኔ ሳድግ "ዶክተር አሆናለሁ" እንዳልኩት ፍቅረኛዬ "ሳድግ ዶክተር አገባለሁ" ብላ ላትመኝ አልቀረችም:: ከዛ በኋላ የሴት ዘር ጠላሁ:: በተለይ ነርስ የሚባሉ ሴቶች፤ ዶክተሮች ራሳቸው በሽታ ፈዋሽ ሳይሆኑ በሽታ መስለው ታዩኝ:: ለዛ ነው ሆስፒታሎች ሲአል የሚመስሉኝ:: ለእኔ በሽታ ማለት ወደሞት ሳይሆን ከሞት የባሰ ወደምጠላቸው ነርስና ዶክተሮች የሚወስደኝ የሲአል መንገድ ነው::

*** *** ***

ሰሞኑን ታዲያ ወደ አንድ የግል ሆስፒታል ጎራ ብዬ ነበር:: በሕይወታችን ውስጥ የጠላታችንን ደጅ የሚያስጠበኙን የባሱ ጠላቶች ይገጥሙን የለ ! በቃ አመመኝና ወደምጠላው ሆስፒታል ሄድኩ:: ሆስፒታሉ ውስጥ ለቁጥር የሚያዳግቱ 'ሴት' ነርሶችን ስመለከት "ይህ ነገር የግል ክሊጅ ነው ? ወይስ የግል ሆስፒታል ?" ብዬ አሰብኩ::

ገና በሩ ላይ ስደርስ አንዲት በተናገረች ቁጥር ከንፈሯ ጆሮዋ ጥግ እና ጥግ እየደረሰ የሚመለስ አዚያው ሃዲድ ከንፈሯ ላይ የደፈደፈችው ቻፕስቲክ እቷን ፀሐይ ላይ የተቀመጠ የቅቤ ቅል ያስመሰለው ነርስ ወደኔ መጣችና በቁሙ የሞተ ፈገግታ እያሳየችኝ፣ "ምን ልርዳከ ?" አለችኝ፣ ስትናገር ቃላቶቹ ያዳልጣቸዋል - ቻፕስቲኩ ይሆን ?! ጥርሷ በብረት ታስሯል:: እስኪ እሱን እስኪፈታላት ብትታገስ ምን ትሆናለች ? 'ካልሳቅሽ ወየልሽ!' ያላት አለ ? መቼም የዚህች ነርስ ጓደኛ ብሆን (እይበልብኝና) ከንፈሯን እንድታሳስረው ነበር የምመክራት::

"እኔ እንኳን የመጣሁት እናንተን ለመርዳት ነው" አልኩ ሰለ ከፍያቸው ውድነት ማሸሞሬ ነበር፤ እርሷ ግን ፊቷ በፈገግታ ተጥለቀለቀ፤ አቁነጠነጣት:: 'የተናገርኩት ይሄን ያህል ያስደስታል ወይንስ የእውነት የእርዳታ ድርጅት ልኮኝ የመጣሁ መስሏት ነው?' እያልኩ ስገረም "አ..ው...ኬ..! አዲስ የተመደበት ዶክተር እርስዎ መሆን አለብዎት?" ብላኝ እርፍ:: አቤት 'ኢ.ኬ..!' ላይ ከንፈሯን እንዴት እንደምታደርገው ! አንዳንድ የከተማችን ዘመነኛ ሴቶች በእንግሊዝኛ የከንፈር ቀመር አማርኛ ካለወራን እያሉ ከንፈራቸውን ለጥጠውት ሊምቱ ነው::

ልጅቱ በደስታ ተጥለቀለቀች:: "ክርስቶስ ሊፈውስህ መጣ" የተባለ የአድሜ ልክ በሽተኛ እንኳን እንደሷ አይፍነከነከም:: የቃልኪዳን ቀለበቷን አውልቃ ሳትደብቀው በፊት (ማን ይሆን ያገባት?) ፈጠን ብዬ "እኔ እንኳን ልታከም የመጣሁ በሽተኛ ነኝ" አልኳት:: ወዲያው ፊቷ ላይ የተጥለቀለቀው የሳቅ ማዕበል ድራሹ ጠፍቶ፣ "ተከተለኝ" አለችና ወደ ካርድ ከፍል መራችኝ፣ እየተቆናጠረች፣ የሆነ ሰበር ሰካ የማለት ሙከራ ዓይነት:: እች አረማመድ ለአዲሱ ዶክተር ተቀምራ የተቀመጠች ሳትሆን አትቀርም::

ካርድ ከፍሉ ውስጥ አንድ አማሯን አጥፋ ተሸክረካሪ ወንበር ላይ የተጎለቶች ሴላ "ቻፕስቲካም ሴት፣

"ስምህ" አለችኝ፣

"ስሜ ምን ሆነ ?" ስል ጠየቅኳት:: ልከ አማርኛ ዘጠነኛ ቋንቋዬ ሳይመስላት አልቀረም::

"አይ ስምህ ማነው ማለቴ ነው"

"አ...አብረሃም !"

"አድሜህ ስንት ነው ?" (ማስቲካዋን ቁጭ)...

"250 ብር ከፈል!"አለችኝ፤ከፈልኩ::

ካርዱን አቀበለችኝ:: አየሁት ስሜን አሳስታ ነው የፃፈችው::

"ስሜን አሳስተሽዋል" አልኳት፣ በመስተዋቱ ሽንቁር ጎንበስ ብዬ::

"ሶ_ሪ! አስኪ...አብርሃም...አይደል ስምህ?" አለች ስህተቷ አልገባትም::

"እም አንቺ ማን 'አርሃም' ብለሽ ነው የፃፍሽው 'ቢ'ን ረስተሻታል::"

ኮስተር ብላ አዲስ ካርድ አወጣችና አያቀበለችኝ፣ "ስምህን ሞልተህ ትሰጠኝ?" አለችኝ፣ የቅሬታ ፈገግታ አያሳየችኝ:: የዚህችም ጥርስ በብረት ታስሯል:: ደሞዛቸውን ቻፕስቲክና የጥርስ ማሰሪያ ብረት የሚከፍሏቸው ነው የሚመስሉት፤ ወይስ "ሆዴን ከመቻል ተርፎ ጥርሴን የሚያሳስር ባል ወላ ጓደኛ አለኝ" መልዕክት ነው ?!! መቼስ የአዲስ አበባ ወንድ ብሩ ተረግሟል::

ስሜን ሞልቼ ሳበቃ "እድሜዬንም ልሙላልሽ?" አልኳት፤ ሆነ ብዬ ለማበሳጨት ነበር:: የመጋጠቅ ያህል ካርዱን ከእጄ ላይ ወሰደችና የምትሞላውን ነገር ሞልታ፣ "ዶ/ር ሰናይት ጋር ነህ:: ከፊትህ አምስት ሰው ይቀድምሃል" አለችኝ:: በጣም ተበሳጭታለች::

"ይቅርታ ወንድ ዶክተር የላችሁም ?" አልኳት:: በረኸሙ ተንፍሳ ካርዴን ተቀበለችኝና "ዶክተር አምሃ" ብላ ፃፈችበት::

"አመሰግናለሁ!" አልኳት በሚያበሳጭ ድምፅ፤ ከዛም ካርዱን አየሁትና ተመልሼ..."ይቅርታ የዶክተሩን ስም ማን ነበረ ያልሽኝ?" አልኳት::

በማርምት አየችኝና "ዶ/ር አምሃ 3 ቁጥር ላይ" አለች ታሉን ረገጥ አድርጋ::

"'አማ' ነው የሚለው፤ 'ኤች' የለችም" አልኳት ካርዱን አያሳየኋት:: (የእውነትም የለችም ነበር):: ስልችት ብያት አንገሽግሻት በመጨረሻ ትዕግስቷ አስተካከሰቻት::

ወረፋ ስጠብቅ ከፊቴ የሚቀድሙኝ አራት የሚሆኑ ሴት ታካሚዎች እየገቡ በጣም ከቆዩ በኋላ በጣም እየሳቁ ይወጣሉ:: አረማመዳቸው ራሱ ይቀየራል:: እየተንኳተቱ ነበተው እንደ ሞዴል እየተወረገረጉ ይወጣሉ:: "ውስጥ የተቀመጠው ዶክተር ነው ወይስ 'ኮሜዲያን'?" እያልኩ ሳስብ ተራዬ ደረሰና ለመላቅ ተዘጋጅቼ ገባሁ:: ወይ መሳቅ !

ጎልማሳ፣ መላጣ ዶክተር ኮስተር ብሎ በአስከፊ ቦው ወንበር ጠቆመኝ:: ስታይሉ ነው መጨረሻ ላይ ያስቀኖል...

"እሽ አብርሃም፤ እንዴት ነው የሚያደርግህ?" አለኝ ከበፊቱ በባሰ ኮስተር ብሎ፤ የመጨረሻዋን ሴት እኔ ያባረርኳት ሳይመስለው አይቀርም...መላጣ፤ ምናባቱ ያኮሳትረዋል?!

በሩ ተንኳኳ::

"ይግቡ!" አለ:: የመጨረሻዋ ታካሚ ነበረች ተመልሳ የገባችው:: ስልኳን ረሲታ ልትወስድ ነበር:: (በሽታዋ አልዛይመር ነበር እንዴ?) ዶክተሩ ፈገግታው ፈነዳ:: "አኬ !" ብሎ ተነስቶ በሁለት እጁ አቀበላት:: ዳሌዋ ሰፋ ያለ መልከመልካም የሃብታም ሚስት ነገር ናት:: ልክ ስልኳን ሲሰጣት የሆነ ዓይነት ለየት ያለ መተያየት ያየሁባቸው መሰለኝ::

"ቴንኪው ዶክተርዬ !" ብላው በተረከዘ ረጅም ጫማዋ ወለሉን እየደቃችው እና እየኮመረገገች ወጣች:: የሽቶዋ ጠረን ግን ከፍሉን ሞላው:: ዶክተሩ ከተዘጋው በር ላይ ዓይኑን መለሰ ፈገግታውን አከሰመው:: ልክ 'እፍ' እንዳሏት ሻማ ወደ እኔ ሲዞር ፈገግታው ድርግም ብሎ ጠፋች::

"ይቅርታ...(ካርዴን እየት አድርጎ) አብርሃም ! እንዴት ነው የሚያደርግህ ?"

ነገርኩት::

"ያስቀምጥሃል?"

"አያስቀምጠኝም"

"ያስመልስሃል?"

"አያስመልሰኝም"

('ስልኪን ብረሳም አያስመልሰኝም' ብለው አሪፍ ነበር:: 'በሽተኛ ቅኔ አያምርበትም' ብዬ ተውኩት::)

"ምግብ ይዘጋሃል?"

"አይዘጋኝም!"

"የመቆረጣጠም ስሜት አለው?"

"የለውም !!"

ታይፎይድ ለማለት ቋምጦ ነበር::

ስላበሳጨኝ ባጭሩ ነበር የምመልሰለት:: 250 ብሬን ከፍዬ ይገላምጠኛል እንዴ ደሞ ? ይሄን የሕፃናት ምኞት የሆነ ስራውን ሊኮራበት ይፈልጋል:: ደግሞ ምን ያጣድፈዋል? ከእኔ በፊ የገቡት ሴቶች በሌላ በር የወጡ እስኪመስለኝ ነበር የቆዩት::

"እጅጌህን ሰብስብ" አለኝ ማዳመጫውን ጀሮው ላይ እየሰካ:: ኧረ ይሄን ሰው እንድ በሉት ጉርድ ሸሚዝ ለብሼ እጅጌህን ሰብስብ ይላል:: ለምን ከቀልቡ አይሆንም ?!

ቀጥሎ ደረቱ ላይ ማዳመጫዋን ለጠፋትና (እቤት መቀዝቀዟ!) "ተንፍስ!" (ትንሽ ወደፊ ዘመ

አለ እንዳልተነፍስበት) እንጀቴን አሳረረው። አጥንታም ደረቴ ላይ ቀዝቃዛ ማዳመጫውን ሰጥፎ "ተንፍስ!" ይለኛል። ከእኔ በፊት ያከማትን ሴት ደረት እያሰበ መሆን አለበት። (ታዲያ ምን እቆየው ? ወይስ የተንዳ ልቤ ዶክተር መሆኑን አውቆ ሲጮህበት ሰምቶ ይሆን?) ወረቀት ላይ ምልከት አደረገና ወደ ላብራቶሪ ላከኝ። ላብራቶሪ ማለት በተለይ የግል ሆስፒታሎች ቫይረስ፣ ባክቴሪያ፣ ጀርም እና የታካሚውን ብር ፈልገው የሚያገኙበት ቦታ ነው!!

ወደ ላብራቶሪው ስገባ 'መልዓክ' ጠበቀኝ። ቤቃ መልዓክ ነጭ ጋውን ለብሶ !! ውብ የሆነች ልጅ ከመቀመጫዋ ተነስታ ተቀበለችኝ። ያውም በፈገግታ!! እቤት ፈገግታዋ ሲያምር! ልክ የህንድ ፊልም ላይ እከተሩ ያፈቀራትን ሴት ሲያይ እንደሚፈዘው ፈዘዝኩ...። እቤት ፈገግታ! ምን የተባረከ በሽታ ነው ዛሬ እዚህ የጣለኝ ? ጥርሷ በብረት አልታሰረም። (ከአሰራቱ ነፃ ወጥቶ ይሆን?) ቁመቷ ደግሞ ሲገርም...! እኔ እንኳን ሪዥም የምባለው ትከሻዋ ላይ ቀረሁ!! በዛ ላይ የድምፅዋ መለስለስ ! ወላ መስረቅረቅ...! ቆዳዋ ጥርት ከማለቱ ብዛት አንዢ ስር ያለው ደም ስር ጥቁር አረንጓዴ ሆኖ ይታያል። ወረቀቱን አየችና "ምን ገጠመህ አብርሽ?" አሉኝ። አፌ ቁርጥ ይበል ! መኪና ሙሉ ብርቱካን፣ ተሳቢ መኪና ሙሉ ሙዝ፣ ቡቴ መኪና ሙሉ የማንጎ ጭማቂ ይዞ ሌላ ሰው ከሚጠይቀኝ አሷ በሳምንት አንዴ "ምነው አብርሽ?" ብትለኝ አመኑኝ አፈወሰለሁ!!

"ትንሽ አመመኝ" አልኳት። ካለውትሮው የራሴ ድምፅ ጨዋ ሆኖ ተሰማኝ። እንድታዝንልኝ ሳልፈልግ አልቀረሁም።

"ቆየብህ ?" ጥያቄዋን ቀጠሉት። መርፌና ሰሪንጅ እያዘጋጀች። ጋዜጠኞች ጥያቄና አጠያየቅን ከዚህች ልጅ ቢማሩ ምናለበት?

"እይይ ትላንት ነው የጀመረኝ" አልኳት። ወደዛ ወደዚህ ስትል ዓይኔ አብሯት ይንከራተታል። እቤት ዓይኔ ሲያሳዝን...! ደግሞ መቀመጫዋ ሲያምር! ጨከና እዚህ መቀመጫ ላይ መቀመጢ ገረመኝ።

"እ! ጥንቁቅ ልጅ መሆን አለብህ ፤ ቦሂዚ ነው የመጣኸው።እስቲ እጅህን እዚህ ጋር አድርገው! ጨብጠው ! ከንዴ ላይ ያረፉት ውብ ጣቶቿን ተመለከተ አያለሁ።ጣቶቿ የእኔ ደም ስሮች መሰሉኝ፣ ጥፍር ቀለም አልተቀባችም። ቀይ እና ረዣዥም ጣቶቿ ተወዳዳሪ የላቸውም።

የላስቲክ ጓንት ስታጠልቅ ክፍት አለኝ። በጣቶቿ ውበት ብቻ ለፈውስ ተቃርቤ ነበር። ይልቅ የገረመኝ አለንጋ ጣቶቿ ላስቲክ ለብሰውም ውበታቸው አለመደብዘዙ። ደሜ ወደ ሰሪንጁ ሲገባ አየሁት። ልንገራችሁ አይደል...! "አብርሽ እግረመንገዴን ለቀይ መስቀል ደም ልሙሰድ እንዴ?" ብትለኝ እንስራ ሙሉ ደም በደስታ አለማስ ነበር። እይ ቀይ መስቀል...! ምን አለ ይህችን መልዓክ ቀመስ ልጅ በቴሌቪዥን ብቅ አድርጎ "ደም ስጡ !" ቢልና ህልሙን ቢያሳካ፣ እንዴ ፈገግ ብትል ለኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ከፈሰሰው ደም በላይ፣ አይተነውም ሰናየውም ከፈሰሰው

ደም በላይ አንለማስ ነበር።

"አላመምኩህ እንዴ?" አለችኝ ድንገት ፈገግ ብላ። ለኔ ግን ፈገግግግግግግግግግ ሆነ! የላብራቶሪው ቅሪቅንብሮች ሁሉ የሳቁ መሰለኝ። አጉሊ መነፅሩ እግሩን አንስቶ የሳቀ መሰለኝ።እጋነንኩት? ደግ አደረግኩ !!

"እረ አላመመኝም !" አልኩ ፈገግታዋን በፈገግታ እየመለስኩ። እሷን የሆንኩ መሰለኝ። በሷ ላቋ ግድግዳውም ላይ፣ መደርደሪያውም ላይ፤ እኔም ላይ ነጥሮ ይመለሳል። "ዓለም የገደል ማሚቱ ይሁንልሽ!" ብሎ የመረቃት ሰው አለ።

ይህችን የመሰለች ቆንጆ አዚህች ቀዝቃዛ ከፍል ውስጥ መገኘቷ ገረመኝ። ቁራጭ ቁንጅና ይዘው ከተማውን የሞሉት ምድረወልጋዳ፣ ወልካፋ፣ ጉረኛ፣ ቻፕስቲካም፣ 'ሂዩማንሄራም፣ ከሃላ ሁሉ ታይፈስ እየያዛቸው አዚህ በመጡና በቅናት ደም ግፊት ጨምረው በሄዱ!!

ትንሽ የፕላስቲክ ብልቃጥ እየሰጠችኝ "መፀዳጃ ቤት ትሄድና በዚህች ትንሽ...ታመጣለህ" አለችኝ ፤ ደበረኝ፣ ለምን አንደሆነ አኔንኛ፣ በዕርግጥ አቺን ለመሰለች ልጅ፣ ቆንጆ አንቡጥ አበባ ይዞ መሄድ እንጂ ከመፀዳጃ ቤት በብልቃጥ "..." ይዞ መሄድ ደስታ ሊፈጥር አይችልም። ምን ይደረግ ሰኔና ሰኞ ገጠመብኝ። ቢሆንም "በዚህች ትንሽ...ታመጣለህ" ስትለኝ "..." ራሱ አቧ ስትጠራው ሲያምር! 'ይሄ ነገር ከዚህ በፊት ስሙ እንዲህ ያምር ነበር እንዴ!' አልኩ ለራሴ ፣

ወጥቼ ወደ መፀዳጃ ቤቱ ሰሄድ እንዲት ጠረንባሎ ነርስ ቆማ በስልክ እያወራች ትገለፍጣለች ማስቲካ እያላመጠች ፀጉሯን ስልክ ባልያዘው እጇ እያፍተለተለች በስልክ የሞቀ ወሬ ይዛለች፤ "ይቅርታ ሽንት ቤቱ በየቱ ጋር ነው?" አልኳት ሆን ብዬ 'መፀዳጃ ቤት' የሚለውን ቃል አልተጠቀምኩም::ስልክ እንደያዘች ያላየሁ በመምሰል ነበር ፉከ ብዬ የጠየቅኳት። በምልከት ጠቆመችኝ..የስልኩ ወግ ያጓጓት ትመስላለች:: አሁን ከዘጋው የደወለላት ሰው መቼም የማይደውልላት ይመስል::

"ይቅርታ ወደ ግራ ነው?" ያልገባኝ መስዬ ጠየቅኳት::

ስልኩን በእጇ መዳፍ አፈነችና "ወደ ቀኝ በዛጋ ስትታጠፍ" አለችኝ በትህትና ድምጽዋን ዝቅ አድርጋ ዓይኗን አያስለመለመች:: ትህትና አያምርባትም:: የተጠና ትህትና መሆኑ ያስታውቅባታል አንዳንድ ሴቶች ትህትና አያምርባቸውም:: እንደሰፊ ሹራብ ፊታቸው ላይ ሲንዘላዘል ከልባቸው እንዳልሆነ ያስታውቅባቸዋል:: ትህትና በቀመር አያምርም:: ትህትና ከእውነተኛ ማንነት ሌሎችን ሳይሆን ራስን ከማከበር ፈንቅሎ የሚወጣ ባህሪ ነው:: ብዙ ቦታ ያጋጥመኛል ያልፈጠረባቸውን ባህሪ ዓይናቸውን እያስለመለሙና ድምፃቸውን ለመስማት አስከሚያስቸግር ዝቅ አድርገው "ጨዋ" ለመባል የሚሞክሩ ለዛ ቢሶች:: አንዷ የእኔ ፍቅረኛ የነበረችው ነርስ ነበረች።

ፊቴ ቁማ መንገድ የጠቆመችኝን ነርስ "ታዲያ በምልከት ያሳየሽኝ እኮ ወደ ግራ ነው...ግራና ቀጠልኩ:: ስልኩን በመዳፏ እንዳፈኑት በግርምትና በብስጭት አፈጠጠችብኝ:: "ሳልሰማ የአዕምሮ ህክምና ጀመርን እንዴ?" ሳትል አትቀርም::

መፀዳጃ ቤቱ እየተፀዳ ስለነበር የፅዳት ሰራተኛዋ "ይቅርታ አሣ ተጠቀም ለጊዜው" አለችኝ በትህትና:: የሴቶችን መፀዳጃ ቤት እያሳየችኝ:: "አይይይ! ከተፀዳ ሲሉል ያልተፀዳ መፀዳጃ ቤት ይሻላል" አልኳት:: አልገበትም:: ምን ይገባታል? ከመኖር ብዛት ሴትነት ገነት መስሏት!!

የላብራቶሪ ውጤቴ ጋር የወሰድኩት ነገር አስደሳች ነበር:: የላብራቶሪ ቴክኒሻኗን ሰልኪ !! ሃሣሃ "በደማችን ያመጣነውን ሰልኪ ማንም አይቀማንም ማለት ዳድቶኝ ነበር:: ደግሞ ስሟ ሲገርም "መና" - ጠበቅ አድርጋችሁ አንብቡት !! ይሄን ስም ሌሎች ሴቶች ላይ ከሰማችሁት ስትፈልጉ ላላ አድርጋችሁ ማንበብ ትችላላችሁ::

ለመና ግጥም የፍኩላት፤

አይንሽን ለማየት ሁልጊዜ ለንድመጣ፤

ከሰኞ አስከ ሰኞ ምናል ጤና ባጣ!!

"...አብርሽ ተሻለህ_?" በቀጣዩ ቀን ደውላ መና ደህንነቴን ጠየቀችኝ:: 'የሰው መውደድ ይስጥህ' ከተባላችሁ መልዓክንም እንደሚያጠቃልል እንዳትረሱ!!

"አብርሽ እንዳልጠይቅህ ቤትህን ደበቅከ..." ከ 3 ቀን በኋላ ደውላ...

ጉድ በል ጎጃም...አለ !

"...እኔ የምልሽ መናዬ ደም ስትወስጅ በስህተት ልቤን ወስደሽው ይሆን እንዴ....?" ያልኳት ፊቷ ላይ የይለፍ ምልከት ካየሁባትና ተቀጣጥረን አራት ኪሎ አካባቢ ቡና ከጠጣን በኋላ ነበር::

ሳቀችልኝ...! በሳቅ ፍርስስስስ አለችልኝ:: 'ያወራኸው ይጣፍጥልህ' ተብላችሁ ከተመረቃችሁ መልዓክትም ይስቁላችኋል:: ሌላ ቀን የፅሁፍ መልዕክት ላክችልኝ - hi Arish...:: 'ь' ተረስታለች፤ "ቢ" ፊደልን ድሮም አልወዳት - እንኳን ረሳቻት!!

19 ዝግመተ ለውጥ

ረሾም ነገር አልወድም። ረሾም ቁመት አንደ ሰብለ፣ ረሾም መንገድ በአኔና በአነሰብሰ ቤት መካከል አንዳለው፣ ረሾም ወሬ ሰብለ አኔን አስቀምጣ በሰልከ አንደምታወራው፣ ረሾም ፅድሜ እንደሰብለ አያት አና ረሾም ቀን እንደዛሬው... ዛሬ አሁድ ነው !

አሁድ ከመርዘሙ የተነሳ የሚመሸው ከነገ ወዲያ ይመስለኛል። አሁድ ለአኔ መጀመሪያና መጨረሻ ያለው ዘላለም ነው። "ለምን?" እንዳትሉኝ፣ ታሪኩ ረሾም ነው። ረሾም ታሪክ አልወድም፣ አንደ አኔና እንደሰብለ የፍቅር ታሪክ።

ሰብለ ፍቅረኛዬ ነበረች። ሰብለ የሚለው ስም በዝግመተ ለውጥ የተገኘ ይመስለኛል። ሰላቢ... ሰለበ...ሰብለ.... እያለ የተሻሻለ ዓይነት። አሁድም ከ24 ሰዓት ተነሰቶ ዘላለም የሆነ....

ዛሬ አሁድ ነው፣ 'ይሄ ጋግርታም ሕፃን አሁድ፣ አርጅቶ መካነ ሰኞ ውስጥ አሰኪከተት ምናባቱ እየሰራሁ...የት አባቴ ሄጂ ላሳልፈው ይሆን?' እያልኩ አሰባለሁ። አንድ ሀሳብ መጣልኝ። ቤቱ በር ላይ ተቀምፎው ፀሐይ እየሞቅኩ የሆነ ነገር ማንበብ...በቃ !

ኩርሲ ነገር አወጣሁና ተመልሼ ከጠረጴዛዬ ላይ የሚነበብ ነገር ሰፈልግ አንድ ጋዜጣ አገኘሁ፣ መልሼ አስቀመጥኩት -ረሾም ጋዜጣ ነው ! የሰብለ አባት ይሄን ጋዜጣ ይወዱት ነበር... ነብሳቸውን ይማረውና... አሳቸው የሞቱ ቀን የቀብር ሥነ ሥርዓቱ አረዛዘም መቼም አይረሳኝ...። ከሰው የተለየ ጋጢያት የተበተባቸው ይመስል ፍትሀቱ ረሾም ነበር። ለነገሩ አራጣ አበዳሪ ነበሩ።

ሀሳቤን ቀየርኩና ጋዜጣውን ይዤ ውጣሁ፣ ፀሐዩ ሲጠነክር አናቴ ላይ ጣል አደርገዋለሁ።

በር ላይ ቁጭ ብዬ አላፊ አግዳሚውን መመልከት ጀመርኩ። አማማ ትሁኔ የሸሮ እህል

ያስጣጣሉ፤ የሚገርሙ ሴትዮ - ሁልጊዜ የሚያስጡት ነገር እያጡም። የሚሰጣ ነገር ቢጠፋ፣ የማስጫውን ሰማያዊ ፕላስቲክ ብቻውን ያሰጡታል። ታዲያ ያሰጡትን ቢያሰጡ፣ ስጡ ላይ እንድ ሁለት ከሰል ጣል ማድረጋቸው አይቀርም። እንድ ቀን ጠየቅኳቸው።

"እማማ ትሁኔ!"

"ወዬ አብርሽ"

"ይሄ ከሰሉ ምንድን ነው ?"

"ዋቱ ?"

"ይሄ ስጡ ላይ ያለው"

"ኧረ...ይሄን እስከዛሬ አታውቅም? ሆሆ..." ካሉ በኋላ ባለማወቄ ተገርመው አጭር ማብራሪያ ሰጡኝ።

"ይሄ እንግዲህ...ስጥ ሰታሰጣ አንድ ሁለት ከሰል ጣል ካደረግክበት ሰላቢ አጠገቡ አይደርስም፤ መዳኒት ነው" አሉ ወደ አልማዝ ቤት እያዩ - ፀበኛ ናቸው።

"ሰላቢ ምንድን ነው ?"

"የሚሰልብ ነዋ...አንተ ይንበርስቲ በጥሰህ ሰላቢ ይጠፋሃል....ሰላቢ ባይኑ የሚሰልብ ነው - ያየውን ነገር ሁሉ ላጥ የሚያደርግ። አህል አይል፣ ዘይት አይል፣ ሊጥ አይል...የተጋገረ እንጀራ - በቃ እየት ሲያደርጋት ሽው ነው...ወደቤቱ ያጋባታል ..." አሉ አልማዝ አንድትሰማ ፍጭክ ብለው።

ከሰል ከሰላቢ ቢያድን እኔ ኩንታል ከሰል ተሸክሜ ሰብለን ስከተላት በዋልኩ ነበር። አንድ ሰላቢ ባለጋራጅ ነው የሰለበኝ። ለነገሩ ሰብለ አንኳን ከሰል ጣል ማድረግ፣ ከሰል ጉድጓድ ውስጥ ቢያስጥትም መስለቧ አይቀርም። ሲፈጥራት ሰላቢ ነገር ነበረች። ከፍቅር የበለጠ ምን ከሰል አለ? ሲያቀጣጥሉት የሚንቀለቀል አሳት። የከሀደት እመድ ሲያለብሱት፣ የተዳፈነ ረመጥ፤ ሲያጠፉት ጥቁር ታሪክ ! ከፍቅር የባሰ ምን ከሰል አለ?!

አንድ ባለጋራጅ ነው ከአጀ ኑጥቆ ሰብለን የወሰዳት። ምን ይወለዳታል፣ ሄደች አንጂ። አንዳንዴ ከሥራ ሰወጣ፣ በምታምር ቀይ መኪና ሲሸኙት አንጣጠማለን። ጋቢና ተቀምጣ በኩራት ታየኛለች፣ 'አየህ ያለሁበትን ዓይነት መኮፈስ። ሰው ከሰው ልብ ላይ ወርዶ፣ ቆርቆሮ ውስጥ ስለተቀመጠ ይሄን ያህል መኮፈስ ነበረበት?

በ'ሬ ላይ ተቀምጬ አላፊ አግዳሚውን መመልከቴን ቀጠልኩ። ኤሜሬ...መምሬ ታምሩ ሳር ቅጠሉን ሰላም እያሉና እያሳለሙ መጡብኝ!! ምክራቸው ረኽም ስለሆነ ሳያቸው ገና ይደክመኛል። እንግዲህ "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም"

ሊሉኝ ነው፤ ታዲያ ለእሳቸው ሰል ከማን አባቴ ጋር ልሁን? የእናቴ ንሰሀ አባት ነበሩ፣ እሳቸው ግን ራሳቸውን የእኔም ንሰሀ አባት አድርገው ቁሜ አሉ፣ ንሰሀ አያቴ::

አጠገቤ ሲደርሱ፣ "አብረሃም እንደምን አደርከ?"

"ደህና እደሩ አባ"

"አይ የእንተ ነፃር:: ሰው ሲያኑበ መነጥሩን ነው የሚወለውለው:: አንተ ሁልጊዜም ስታነብ ጥርስህን ትፍቃለህ፣ በጥርስህ ታነብ ይመስል" አሉኝ፣ አሁን ይሄ ከንሰሃ አባት የሚጠበቅ ንግግር ነው ? በዕርግጥ የወይራ መፋቂያ በአጄ ይዤ ነበር:: በአከብሮት ቆምኩና ሁለት እጆቼን አንሰፈ እንደተሸከሙች ሴት ከኋላዬ አነባብሬ ማንባሬን ወደ አባ አሰገግኩ::

ወደ ሰማይ ዓይናቸውን ተክለው ጋቢና ካቦርታቸውን በቀኝ እጃቸው አየሰረሰሩ ከኮታቸው የውስጥ ኪስ መስቀላቸውን ሊያወጡ ሲታገሉ በትዕግስት ጠበቅኳቸው:: ሁልጊዜም እንዲህ ሲያደርጉ መስቀላቸውን ከውስጥ ኪሳቸው ሳይሆን ከልባቸው ውስጥ የሚያወጡ ነው የሚመስለኝ:: አሳለሙኝ:: አዚህ ሁሉ ልብስ ውስጥ ተቀምጣ መስቀላቸው ግንባሬን ስትነካኝ ለምን እንደምትቀዘቅዘኝ ይገርመኛል !!

"አብረሃም!" አሉኝ ድምፃቸውን አለስልሰው:: (እንግዲህ ሊጀምሩ ነው)

"አቤት አባ"

"እንደው ቢመክሩህ አልሰማ አልከ...ሽረ ተው...ተው አብረሃም ተው:: እኔ ወድጀ አይደለም የምነዘንዘህ የናትህ አደራ ከብዶኝ ነው:: ምናለ አንዲን ጥሩ ከርስቲያን አግብተህ ብታርፍ:: ሰነኩ የት ታገኛታለህ፣ ቤተሰኪያን መምጣቱንም ትተኸዋል....!! አስቲ ምን ትደለህ? የጠገበ ደመወዝ ትበላለህ፣ ምን የመሰለ ሰፊ አልጋ አለህ..." አሉ በአገጫቸው ወደ ቤቴ ውስጥ እያመለከቱ:: እንዴ አባ...አልጋና ትዳር ምን ያገናኘዋል፣ ያላገባሁት አልጋ ይጠበኛል ብዬ መሰላቸው እንዴ... ወይስ በትዳር ውጦመድ ውስጥ እንድገባ አልጋዬ ላይ ቁራጭ ሲጋ አየጣሉልኝ ነው::

"ሁልጊዜ ልጅነት የለም...አየው..." አሉና ምስጢር እንደሚያወራ ሰው ጠጋ አሉኝና ጋቢያቸውን ወደ ላይ ወደ ትካሻቸው አስተካከሉ:: ከዛም ድምፃቸውን ቀነስ አድርገው፣ "...እንደውም እንዲት ትሁት እማዜር የባረካት ልጅ አቃለሁ፣ ከዚህ...ማነው...ይሄ ሲኖቹ ከሚሄዱበት አገር ማነው..."

"አረብ አገር" አልኩ ቶሎ እንዲላቀቁኝ:: አረብ አገር የሚሄዱት ሴቶች ብቻ ናቸው የተባለ ይመስል!

"አለአ ተባረከ አረብ አገር...አና እዛ ሄዳ ትንሽ አመም አድርጓት ነው የመጣችው ...ጨ...ዋ ድምፅ ሲወጣት የማትሰማ፣ ከቤቷ ቤተሰኪያን ከቤተሰኪያን አቢቷ ነው - እርግት ያሉች የጨዋ ልጅ - ላንተ የምትሆን ናት ግዴለህም አያት ! ሳምንት እኔው ራሴ አስተዋውቅሃለሁ:: እንተማ ዞሮብሃል እንኳን የትዳር አጋር ልትፈልግ ራስህም ጠፍቶሃል...ምን ታረግ...ቤትህ ጠበል አይረፍብት፣

ጳዊት እንኳን አትደግም" ልቃወም አፌን ከፍቼ ተውኩት።

"አይደለማ አይደለም..." ብለው እንደገና ሴላ ረዥም ምክር እንዳይጀምሩ ፈርቼ ዝም አልኩ። ብቻቸውን በግዕዝ እያንበነቡ ወደታች ወረዱ።

እንዲሁ ስለመምሬ አና ለትዳር ስላሰቡልኝ ልጅ እያሰብኩ የያዝኩትን ጋዜጣ መቃኘት ጀመርኩ።

በደማቅ ጥቁር ቀለም፣ "በማኅበር ተደራጅተው ጫት የሚያመርቱ አርሶ አደሮች ኑሯችን ተለውጧል አሉ..." ይላል።

ወረድ ብሎ፣ "አንዳንድ የማኅበሩ አባላት ጫት በመሸጥ አይሱዙ መኪና ገዝተናል፣ ልጆቻችንንም ከተማ ልከን እያስተማርን ነው ሲሉ ገልፀዋል" ከጽሑፉ ስር አይሱዙ መኪና ተደግፈው ፎቶ የተነሱ አርሶ አደር ምስል ይታያል።

ወረድ ብሎ ሌላ አርዕስት፣

"አንድ አይሱዙ መኪና ሃያ ሜትር ጥልቀት ያለው ገደል ውስጥ ገብቶ ከላይ ጭኗቸው የነበሩ ሰባት ሰዎች ሞቱ። ከሚቾቹ አራቱ ከገጠር ከተማ እየተመላለሱ የሚማሩ ተማሪዎች ሲሆኑ ፖሊስ የአደጋው መንስዔ 'ሹፌሩ ጫት እየቃመ ማሽከርከሩ ነው' ብሏል !"

ጋዜጣውን አጥፌ ሰፈራችንን ማየት ጀመርኩ። ቅድስት ቀይ የአራት ልብስ ለብሳ አቃ ታጥባለች፤ እያንጎራጎረች፣ "በሰባራ ፎሌ ውሀ አይጠለቅም..." አይ ቅድስት ! አንደኛ ሰፈር ሴት የባከነበት መንደር ያለ አይመስለኝም። ቆንጆ ናት 'ሞዴል' የመሆን ፅኑ ፍላጎት ነበራት። አንደውም የሰፈር ልጆች ሲፎግሯት፣ "'ውበት ውጪያዊና ውስጣዊ ነው' ሲሉ ሰምታ ውስጣዊ ውበቷን ለማየት ጓልትራሳውንድ' ተነሳች" ይሏታል። ስታንጎራጉር እየሰማኋት ሰደምጿ ማማር ተገረምኩ፤ "ወይ ይህቺ አገር ዘፋኞቿ በየማጀቱ አቃ እያጠቡ አቃ አጣቢዎቿ በየአደባባዩ እንዝፈን እያሉ ያደነቁሩናል" አልኩ ለራሴ። የቄሳርን ለእግዜር፣ የእግዜርን ለእግዚሃር።

*** *** ***

የመንደራችን የአንድ አሁድ ውሎ ከሞላ ጎደል እንደሚከተለው ነው። ከጧቱ 12፡00 ሰዓት አልማዝ የምትባለው ጎረቤታችን በሯ ላይ ስለተጣለው ድግምት ታማርራለች፣ ትራገማለች፣ ጠበል ታርከፈክፋለች። ድግምት በመጣል የሚጠረጠሩ ጎረቤቶቿን ታሸሙራለች፣ "እችኑ ኑሮ ብለዋት..." አያለች፣ ብዙ ጊዜ የሞተ አይጥ ነው በሯ ላይ ተጥሎ የሚገኘው።

ከ 12፡30 አለክ ጧቱ 2፡00 ሰዓት አማማ ዘብይደሩ ሞንቅሎ የተባለውን የልጅ ልጃቸውን የረግማሉ፣ ይሳደባሉ፣ ይወግራሉ። እንዳንዴ ወገራው ሲበዛ ገላጋዮች ይገባሉ። "ባጭር ቅር..." ይሉትና ሲታመም ሆስፒታል ለሆስፒታል አዝለው ይዞራሉ።

ከሁለት ሰዓት አስከ አራት ሰዓት የመንደሩ ልጆች አጌ ቤት ፊት ለፊት ያለች (ሰርቪስ ቤት እንኳን የማታቆም) ቢጤ ሜዳ ላይ ኳስ ይራገጣሉ። የሚያስነሱት አቧራ ልጆቹን ሰለሚሸፍናቸው አንደ ህልም ነው ብሎ ብሎ ብለው የሚታዩት።

ከሚጫወቱት ልጆች መሃል ጭንቅሎ (የአማማ ዘብይደሩ የልጅ ልጅ)፤ ሃይለሚካኤል 'አረቡ (የአማማ የውብዳር የልጅ ልጅ)፤ ሙስጠፋ (የአማማ ዘሃራ የልጅ ልጅ)፤ ሊቲና 'ወንዳወንድ ስለሆነች ከቤ' ይሏታል (የአማማ ትርሃስ የልጅ ልጅ ናት)፤ ከላይ ከተዘረዘረው የዘር ሃረግ እንደሚታየው መንደራችን አንድ 'እናት' የሚባል ትውልድ ገድፏል፤ 'አባት' የሚባል ሃረግ ዘሏል። ሕፃናቱ ከአያቶቻቸው ጋር ነው ያደጉት። ያውም አቅም ከሌላቸው ደሃና አቅመ ደካማ ባልቴት አያቶቻቸው ጋር! 'እናቶቻቸው የት ሄዱ? አባቶቻቸውን ምን በላቸው?' ቢባል መልሱ ከሁሉት ጉዳዮች አያልፍም። አንድም ወልደው ለእናቶቻቸው እየሰጡ አረብ አገር ሄደዋል፤ አልያም በኤችአይቪ አልቀዋል። የመንደራችን እውነታ ነው ይሄ !! ደግሞ ሕፃናቱ የተመካከሩ ይመስል በየምክንያቱ ሲጣሉና ሲነታረኩ የሁሉም መሃላ አንድ ዓይነት፤ "እናቴ ትሙት !!" የሚል ነው።

ልክ ከአራት ሰዓት አስከ አምስት ሰዓት፤ ሁለቱ የመንደራችን እንጀራ ሻጮች ሙሉና ዝናሽ ዱላ ቀረሽ ስድድብ ይጀምራሉ። በደንበኛ መቀማማት ነው የሚጣሉት፤

"ለማያውቅሽ ታጠኚ...ደግሞ ሙያ እንዳለው ሰው። ማየት የተሳነው እንጀራ እየጠፈጠፍሽ... አኩል ታወሪያለሽ..."

"ኤጅ አባክሽ...እኔ ሙሉ በወፍጮ ቤት ጥራጊ አይደለም ደንበኞቼን የማስተናግደው፤ ጥርት ባለ ጤፍ ጥር...ት"

"ሂሂሂሂሂ 'መጣፊጡ ቀርቶ እጇን በለቀቀኝ አሉ አትዬ አሰለፍ፤ ጥራቱ ቀርቶብሽ ቡሃቃሽን በወር አንዴ እንኳን ባጠብሽው። ሰዉን ሁሉ በሆድ ቁርጠት ፈኬረሽው' ትላለች ዝናሽ። የሙሉ ደንበኛ ስለሆንኩ በዚህ አባባሷ ሆዴ ይጮሃል፤ ...ኡ.... ወር ሙሉ የማይታጠብ ቡሃቃ ...እቺ ስድደብ ደንበኛን ለማስከዳት ወሳኝ የቃላት ጦርነታቸው ናት።

ልክ አምስት ሰዓት ሲሆን እማማ መጣፈጥና ስንቅነሽ ቡና ይጠራራሉ። ወደ ስድስት ሰዓት ጀሚላ የቅንድቧን ኩል ጀሮና ጀሯዋ ጥግ ድረስ ተኩላ በሰልኳ እያወራች ወደላይ ትጣደፋለች፡ "ሃቢቢ መጣሁ_ወጥቻለሁ" አያለች። አፍንጫ የሚሰነፍጥ ሽቶዋ መንደሩን ያውደዋል። ጀሚላ ስታልፍ ጥርኝ ያለፈች ነው የሚመስለው። የታከከችው ነገር ሁሉ ሽቶ ሽቶ፣ መቼም ሃቢቢዋ የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ያደረገ ሰው መሆን አለበት።

ይሄን ሁሉ ሳይ ይከፋኛል። በጭንነት ይጫጫነኛል። ከወንዙ ተገንጥሎ ከራሬ ውስጥ እንደተኳተረ ውሃ አዛው የምሽግት አልያም የተቀመጥኩበት በትነት የማልቅ ነገር መስሎ ነው የሚሰማኝ

ይሄ...የተረገመ እሁድ ወደዛ አልቆ ሥራዬ በገባሁ ! ለነገሩ ከእሁድ ይሻላል ብዬ አንጂ ሥራዬም ሠልችቶኛል:: የባንክ ሠራተኛ ነኝ:: ብዙ ሰዎች የባንክ ሠራተኛ መሆኔን እንደትልቅ እና አስደሳች ሥራ አድርገው ሲያወሩ ይገርመኛል:: ለእኔ የባንክ ሥራ በምድር ላይ ካሉ አስከፊ ሥራዎች ሁሉ አስከፊው ይመስለኛል:: እንደውም ላለው ሳይሆን ለሮቦቶች የሚሰማማ ሥራ ቢኖር የባንክ ሥራ ነው አያልኩ አስባለሁ::

አንድ አይነት ቅርፅ ያላቸው 'ብር' የሚባሉ መርገምቶችን መቁጠር:: አራት ዓመት ሙሉ ቆጠርኳቸው...ሌጭ...ድፍን አገር የሚራኮትለት ብር ለእኔ አንዳች ቆሻሻ ነገር መስሎ ነው የሚታየኝ:: ብር ይሸታል:: ካላመናችሁ ወደ አፍንጫችሁ አስጠጉና ሞክሩት:: እንደ ብር መጥፎ ሽታ ያለው ነገር ምን አለ ? ለነገሩ የዘንድሮ ብር ላሸትተውም ብትሉ አፍንጫችሁ ላይ ላይደርስ ያልቃል - ሰላቢ ነገር ነው::

ምስላቸው ብር ኖት ላይ ያሉት ሰዎች ከመኖር ብዛት የቢሮ ባልደረባ መስለውኛል:: ደግሞ አልወዳቸውም:: ሰምሳሌ አንድ ብር ኖት ላይ ምስሉ ያለውን ሰው መንገድ ላይ ባገኘው ነበሚምጭው የማልፍ ይመስለኛል:: አስር ብር ላይ ያለችው ሴትማ በለማም ስታበሳጨኝ፤ የሆነች ነገረኛ ነገር:: በደንብ አይታችኋታል? ስፌት የምትሰፋ ትመስላለች እንጂ ጆሮዋን አቁማ ነገር የምትሰማ እኮ ነው የምትመስለው:: ደግሞ ፊቷ ላይ የአሽሙር ፈገግታ አለ:: ከሁሉም ከሁሉም የሚያበሳጨኝ ነገር ደግሞ ከንፈሯ !! የከንፈሯ ማማር የሰብለን ከንፈር እኮ ነው የሚመስለው !! ከነስፈቷ አጎኗ ላለው አንበሳ ነበር መስጠት !!

ባንክ ቤት ስትሰሩ ስጋችሁ በሱፍ ተጀቡኖ ወሩ መጨረሻ ላይ የሱፍ ቆሎ መግዣ እንኳን የማይተርፋችሁ መናጢ ደሃ መሆናችሁን ብዙ ሰው አይረዳም:: ቁጥርና ስጋት ባንድ ላይ የሚኖሩት ባንክ ቤት ውስጥ ነው:: ብር ስትቆጥሩ በስጋት ነው:: እንዱን የብር ኖት ሌላ የተደረበበት እየመሰላችሁ በፍትጊያ ፍዳውን ታበሉታላችሁ:: በዛ ላይ ሰው ለብር ያለውን ሚችነት፣ ስግብግብነት፣ ደግነትም ጭምር ትታዘባላችሁ::

ሃሃሃ የሆነ ነገር ትዝ አለኝ:: አንድ ቀን እንዲ እኔ ወዳለሁበት መስኮት ጠጋ አለችና ትልልቅና የተራቆቱ ጡቶቿን መስታወቱ ጋር ጨፍልቃቸው በሽንቁሩ ታናግረኝ ጀመረ:: ደረቷና ጡቷን የወረራት ብጉር መሰል ነጠብጣብ ያስቅቃል፡ መቶ ሺ ቁጫጮች የሚርመሰመሱበት ደረት ነው የሚመስለው:: እንደው አንዳንድ ሴቶች ምን ማሳየት እና ምን መደበቅ እንዳለባቸው አያውቁም::

እኔ ደግሞ ከኋላዋ ቱራ የሚጠብቁ ደንበኞች ወደሷ ሲያፈጡ፣ "እቺ ሴት ታዋቂ ትሆን?" ብዬ አሰብኩ:: ለካስ ወደኔ ስታነብስ በጣም አጭር ጉርድ ቀሚሷ ከኋላዋ ታፋዋ ድረስ በመራቆቱ ነበር ያ ሁሉ ዕይታ፤

"ምን ልታዘዝ የኔ እመቤት" አልኳት:: በሚያበሳጭ መሞላቀቅ ቻፕስቲክ አውጥታ ደዘደዝ ከንፈሯን ቀባችና ቀጭ አድርጋ ዘግታ ወደ ቦርሳዋ መለሰች:: በትዕግሰት ጠበቅኳት::

"ዶላር ተልኮልኝ ነበር"

"ከየት ነው?"

"ከዲሲ ...አሜሪካ"

"የላኪው ስም?"

"ዳኒዬ" አለች በፈገግታ::

"ዳንኤል ነው?"

"ያ"

"ስንት ነው የላከልሽ?"

"ስሪ አር ፎር ሃንድረድ ዶላ..ር" ስታወራ እንባቷን ትሰብቀዋለች::

ዳንኤል የላከላት ግን አንድ መቶ ዶላር ለዛውም መላኪያው ከዛው ላይ የሚቆረጥ ነበር::ይሄንኑ ስነግራት...ደዘይሂ..ሞልቃቃዋ እና ቋጫጫሚ ሞልቃቃ - ፊቷ ተቀያየረ:: ስልኳን አውጥታ ደወለችና ጥርት ባለ አማርኛ፡ "አንቶ ያ ችጋራም መቶ ዶላር ብቻ ነው የላከልኝ - ዳንኤል አርገጤ ነሞ" ብላ አርፍ:: ወዲያው አንድ ቁሽሽ ያለ ቱታ የለበሰ ጎልማሳ ሰው መጣና፣ ደብተሩን እያቀበለኝ:: ልጅቱ የቱታው መቆሸሽ ደብሯት ፊቷን አፍጨፈገገች::

"ወደየት ነው?" አልኩት::

"ወደ ጅማ"

"መጠኑ..."

"አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊየን":: ሞልቃቃዋ ሰውየውን ቀጥ ብላ እየችውና ፈገግ ብላ በአክብሮት ቦታውን ለቀቀችለት:: ወዲያው የሚያደርጋትን አላጣት፡ "ወደዚህ ጠጋ ብለህ አናግረው፡ ሶሪ ቦታ ያዝኩብህ" አለችው በፈገግታ:: ዞሮ እንኳን አላያትም:: (የውሸት አክብሮቷና ፈገግታዋ ከሰረ::) ሰውዬው አናትዬ ስራ ልቡን ያወለቀው ላብ እደር ነገር ነው ሲሏን ለማየት ጊዜውም የለው...!! "ሚስኪን ዳኒዬ!" አልኩ በሆዴ::

በቃ ይሄ ነው ስራዬ ብር መቁጠር መሰጠት:: ብር ማስገባት፡ ማስወጣት...ኤጭጭ !! ቢሆንም ከአሁድ ይሻላል::

አማማ መጣፈጥ ስንቅነሽን ቡና ሊጣሩ ስማሁ ገና አምስት ሰዓት...ወይ እዳ!

ቅድስት አሁንም እያንገራገረች ነው፡ "የቤቴ ወለሉ ጣራ እና ግድግዳው..." የቤታቸውን ግድግዳና

ጣራ ከውጭ በኩል በረሸም መጥረጊያ እያፀዳች ነበር። ቆንጆ ናት፣ ፀይም ቆዳዋ ጥርት ያለ፤ በተለይ አንዲህ ከኋላዋ ሁኖ ስትንጠራራ ላያት የአቦሸማኔ ሽንጥ። ቅድስት ቆንጆ ናት። አንደው ተፈራርተን እንጂ አኔና ቅድስት ሳንከጃጀልም አልቀረን። ባየኋት ቁጥር አቅፌህ ሳማት ሳማት ይለኛል። ...አሷም በሰበብ አስባቡ አቤቴ ጎራ ማለት ታበዛለች ግን - እንፈራራለን።

ቅድስት፣ አርሴማ፣ ሃያት፣ ጀሚላ፣ ሜሮን፣ ሂሩት እና ሄለን አረብ አገር ሰሰራ ሄደው የተመለሱ የመንደራችን ሴቶች ናቸው። ያልተመለሱትንማ አረብ አገር አዛው ይቁጠራቸው...።

መጀመሪያ አረብ አገር የሄደችው አርሴማ ነበረች፣ አንዳሁኑ ባልተለመደበት ጊዜ። ታዲያ አርሴማ ብዙ አልቆየችም፣ ባልታወቀ ምክንያት በሦስት ወሯ ተመለሰች። ዘጠኝ ወር ሲሞላት ግን ምክንያቱ ታወቀ፣ ወንድ ልጅ ተገላገለች ! የመንደሩ ሰው አርጉዝ መሆኗን ካወቀበት ቀን ጀምሮ፣ "የሚወለደው ልጅ አረብ ይመስላል...አይመስልም" እያለ ሲነታረክ፣ ሲወራረድና ብር ሲያሲዝ ከረመ። አርሴማ የሚያምር ከልሰ ልጅ ወለደች። ጉና ከአራሰ ቤት ሳትወጣ ደግሞ መነሻው ያልታወቀ ወሬ ይናፈስ ጀመረ።

"አርሴማ የወለደችው ትሰራበት የነበረ ቤት ተቀጥሮ ከሚሰራ ፓኪስታናዊ ዘበኛ ነው" ይሄ ወሬ ለጉድ ተናፈሰ።

"ቱ! ለምላ ወንድ!" ተባለ። "አንገት ደፊ አገር አጥፊ" ተባለ።

ይሄ ወሬ አድሜው ከሳምንት አላለፈም። የመልስ ምት በሚመስል ሌላ ወሬ ተተካ። "አርሴማ ያረገዘችው ከኪዌቱ አሚር ሁለተኛ ልጅ አብደል ናስር ነስረዲን ነው...አነሱ ቤት ነበር የምትሰራው..." ይሄንኛው ወሬ ከመጀመሪያው የበለጠ ገነነ። አንደውም በቅርቡ መጥቶ ለፊራችንን በሊዝ ሊገዛውና ለአርሴማ በኢትዮጵያ አንደኛ የሆነ ሕንፃ ሊገነባላት እንደሚችል ሁሉ ተወራ።

"ሊወዳት መቸስ ለብቻው ነው፣ አቧን ሲያይ ጥምጣሙ እስኪበር ነው ቢደሰታ የሚምነሸነሸው" እየተባለ ወሬው ደመቀ። ጥምጣሙ እስኪበር የሚያፈቅር የአሚር ልጅ አዚህ ጭርንቁስ መንደራችን ውስጥ መጥቶ ለማየት አኔ ራሱ ጓጓሁ፣ የፍቅርን ኃያልነት ለመታዘብ አሰፈሰፍኩ።

ሕፃኑን ልጅ አያቱ "ኃይለሚካኤል" አሉት፤ ኃይለሚካኤል አብደል ናስር ነስረዲን በዚህ ሁኔታ የመንደራችን አባል ሆነ። (አረቡ ይሉታል በቅፅል ስም፣ በኢትዮጵያና ኩዌት መካከል ወደፊት ለሚኖረው ወዳጅነት ይህ 'ታሪካዊ አንበቃቅላ ታሳቅ ሚና ሳይኖረው አይቀርም... ሂሂሂ)። አድጎ አስር ዓመት እስኪሆነው ግን አባቱ ነኝ ያለ የአሚር ልጅ አልታየም። አንድ ቀን ታዲያ አያቱ፣ "አሚሩ ቀርቶበት ዘበኛውም በመጣና የአባትን ጣዕም ባወቀው" አሉ በቁጭት።

ከአርሴማ በኋላ ሜሮንና ጀሚላ አረብ አገር በመሄድ ሁለት ዓመት ቆይተው ተመለሱ። አነጀሚላ

ቤት አዲስ ምንጣፍ ስለተነጠፈ ጫማ ሳያወልቁ መግባት ተከልክሎ ነበር። በአንድ አጣ ምንጣፉን የረገጠ እንግዳ በጀሚላ ልዩ ቤት ሁለተኛ አጣሩን በአየር ላይ አንዳንጠለጠለ ደርቆ ይቆማል። እማማ ሐዋ (የጀሚላ እናት) ታዲያ "ይሄን ምንጣፍ ወዲያ አንሽልኝ ሲታመም ጣያቂ፡ ሲቸግረኝ ደራሽ ጎረቤቶቼን አላቀቀብኝ" አሉ። ሲቆይ ግን ምንጣፉም ቆሸሸ መጓቀቡም ተነሳ፡ መጀመሪያ ቤተሰቡ ከዛም ሁላችንም መንደርተኞች ከነጫማችን መግባት ጀመርን።

ሜሮን እንደመጣች አካባቢ ደግሞ የተረፈ ምግብ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ አየደፋች አስቸግራ ነበር። "እረ ለልጆቹ መከሰስ ይሆናል አህሉን አትድፊ ጡር ነው" ብትባል፣ "ላላ ላላ" እያለች መገልበጥ ሆነ። ከወሮች በኋላ እንኳን ሊተርፍ ዋናውም እያነሰ ቤተሰቡ መነጫነጭ ስለጀመረ አህል መድፋቱ በዛው ቆመ።

አረብ አገር የሄዱት ሁሉ ኮንትራታቸውን ጨርሰው ባንዴ ወደ መንደራችን በመጡበት ወቅት የሚገርም የባህል፣ የኢኮኖሚ፣ የቋንቋ መቀየጥ ተከሰተ። ፓስፖርት፣ ቪዛ፣ ኮንትራት፣ በርሜል፣ ካርን፣ ጉምሩክ፣ ሃቢቢ...ሃቢብቴ የሚሉ ቃላት ተዘወተሩ። በመንደራችን ሻይ አብዝቶ መጠጣትና ሩዝን ከአንጀራ እኩል ገበታ ላይ ማቅረብም ተለመደ። በሳተላይት ዲሽ የአረብኛ ፊልሞችና ተክታታይ ድራማዎችን ማየትም አንዱ ለውጥ ነበር።

አርሰ በአርስ መንደርተኞች ሲጣሉ አረብኛ ሰድቦችን መቀላቀል ሁሉ ተጀመረ። እንደውም አንድ አረብኛ ሰድብ ለእኔም ደርሶኛል። ቅድስት የአስቴርን ሲዲ ልትዋስ ቤቴ ስትመጣ በቃሌ የሸመደድኩትን ግጥም ብቻዬን ሳነበንብ ደረሰችና "መጅኑን!" አለችኝ። በኋላ ሜሮን እንደተረጎመችልኝ ከሆነ "ወፈፌ" ማለት ነው አሉ።

በዚህ ወቅት ሂሩት አረብ አገር እሄዳለሁ ብላ ተነሳች። "እንዴ ደግሞ አንቺ ምን አጣሽ ኑሯችሁ ጥሩ፣ ትምህርትሽን እየተማርሽ ነው" ብትባል

"እንዴት ነው ምን አጣሽ...ተውኝ...ተውኝ አባክችሁ ሆድ አታስብሱኝ። ያጣሁትን እኔ ነኝ የማውቀው። የመንደሩ ሴት ሁሉ በአረብኛ ሲሰዳደብ እኔ አሰከመቼ በአማርኛ ስሳደብ እኖራለሁ - ማን ከማን ያንሳል?!" አለች አንባ እየተናነቃት። ሄደችና ሁለት ዓመት ቆይታ ብዙ አረብኛ ስድቦችና አንድ በርሜል ልብስ ይዛ ተመለሰች።

አሰገራሚ በሆነ ሁኔታ በርሜሉ ውስጥ ሙሉ የቤይሩት መቶ አለቃ ዩኒፎርም ተገኘ። የሂሩት አባት ያንን ግጥም አድርገው ለብሰው አንዳንድ ቤይሩት ኖረው የመጡ ሴት እህቶቻችንን በሰላም አገር ሲያስደነግጡ ከረሙ። ሂሩትም ሃሜት አልቀረላትም፤ "ፖሊስ ቤት ተቀጥራ ነበር የምትሰራው ልብሱን ሰርቃ አምጥታ ነው" አሏት።

ሂሩት ግን አንድ ቀን ቁጭ ብለን ስናወራ ስለ'ዩኒፎርሙ' ይሄን ታሪክ ነገረችኝ። አንድ መቶ አለቃ ሂሩትን ድንገት አያትና በፍቅሯ ተነደፈ። መጀመሪያ በሃር የተጠለፈ መሃረቡን ላከለት

(የፍቅር መግለጫ መሆኑ ነው) ዝም ስትለው 'አሃ እንሶብሽ ነው!' በማለት የፖሊስ ኮቱን ከሙሉ ሙሳረጉ ላከላት። በመጨረሻ መልስ ሲያጣ ሱሪውን ላከላት። በሱሪው ተጠቅልሎ ደግም ክላሽንኮቭ ጠመንጃው አብሮ ነበር። እንግዲህ ወንድ ልጅ ሱሪና ጠመንጃውን ከሰጠ ምን ቃሪው? ይሄ ሚስኪን አፍቃሪ ፖሊስ እስካሁን በፓኪ አውትና በግልገል ሱሪ በቤይሩት ጎዳናዎች ላይ ግዳጁን እየተወጣ ይገኛል። (አያድርስ ነው...አይሳቅም ! እኔስ እለሁ አይደል ለዚች ሰላቢ ስብለ ነፍሴን ሰጥቼ እርቃኔን የቀረሁ።)

ሂሩት የኒፎርሙንም ክላሽንኮቭ ጠመንጃውንም ይዛ ወደ ኢትዮጵያ ስትገባ ኤርፖርት ፍተሻ ላይ ተያዘች።

"ሥለሪያው እያልፍም ይወረሳል፣ ዩኒፎርሙን ችግር የለም ማስገባት ትችያለሽ" አሏት ፈታሾቹ።

"ኧረ የለው ስጠታ ነው በናታችሁ!" ብትላቸው፣

"አማ ነው" ብለው ግግም አሉባት። ወደ ሀላፊው ቢሮ ገብታ ጉዳዩን ነገረችው። ኖና 'ክላሽ' ስትለው፣ "እያልፍም" አላት በቁጣ።

"ምናለበት ባታካብዱ...ባንድ ጠመንጃ መንግሥት አይገለበጥ!" አለችው ግልፍ ብሏት።

"ዋይ...ተይ ባከሽ እኛም ደርግን ስንገለብጠው ባንድ ክላሽንኮቭ ነው የጀመርነው..." ብሎ ሸኛት።

ሂሩትና ጀሚላ "ዩኒፎርም ሰርቃለች" በሚለው ሐሜት አቧራ ያስነሳ ፀብ ገጠሙ። በአረብኛ እና በአማርኛ ነበረ ሰድድቡ። ቅድስት መሀል ገብታ እየገላገለች አግረ መንገዷን አረብኛ ሰድቦችን ለእኛ ለመንደርተኞች ትተረጉምልን ነበር።

"ከልብ!" አለች ሂሩት ጀሚላን። ቅድስት፣ "ኧረ እንዲህ አይባልም አግዜር አይወደውም ሂሩት" በማለት ነገሩ ለማብረድ እየሞከረች ወደ እኛ ዞር ብላ፣

"'ከልብ' ማለት ውሻ ማለት ነው።" ትለንና ወደ መገላገሏ ትመለሳለች።

አልልልልልልልልልልልልልልልልልልልልል አሁድ መሸ ! ድንገት ቅድስት ዝንጥ ብላ አቤቱ መጣች፣ ከሰዓት ሰርግ ነበራት። ኡፍፍፍ የለበሰችው ረዥም ቀሚስ እንዴት አንዳማረባት።

"ባለጌ!" ስትለኝ ላለመስማት ጆሮዬን ልይዝ ነበር።

"እና ካሁን በኋላ ልሄድልህ ነው?" ስትለኝ ማመን አልቻልኩም። ዞር ብዬ አልጋዬን አየሁት። አስከዛሬ አዚህ ባህር ላይ ብቻዬን የምንሳፈፍ ሚስኪን ጀልባ መሆኔ ተሰማኝ። ዘልዬ አቀፍኳትና ግጥም አድርጌ ከንፈሯን ሳምኳት።

"ሂድ መጅኑን!" አለችኝ። እንደዚህ ቃል አሪፍ የፍቅር ቃል ሰምቼ አላውቅም። ራሴ ስተረጉመው፣ "በፍቅር የወደፈ" ማለት ሳይሆን አይቀርም ዘ "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም አደግመዋለሁ...አባ ልክ ናቸው።

የአሁድ ሌሊት እንዴት አጭር ነው - ለዚህ ጊዜማ ይጣደፋል !

ፊንዲሻ ሲቆሉት ድምፅ ሲበሉት ድምፅ 20

የአንድ ደቂቃ የህሊና ጸሎት አድርገን እንደተቀመጥን፣ ፕሮግራሙ ቶሎ እንዲያበቃ ሌላ የህሊና ጸሎት ጀመርኩ። ዓለም ዓቀፍ የሴቶች ቀንን ለማክበር የከፍለ ከተማው የሴቶች ሊግ ባዘጋጀው ፕሮግራም ላይ ተገኝቻለሁ።

ሊጉ በመሥሪያ ቤታችን በኩል ግዳጅ የተቀላቀለበት ጥሪ አቅርቦልን አለቃዬ "ሂድ !" ስላለኝ የቀበሌው አዳራሽ ውስጥ ተገኝቻለሁ። ያውም ቅዳሜን በሚያክል ቀን - ከሰዓት!! ሰኔና ሰኞ ገጥሞብኝ።

"...አሁን ደግሞ የከፍለ ከተማችን የሕፃናትና ሴቶች ፑል ምክትል ኃላፊ ወ/ሮ ደርባቤ በላቸው እንስራውን ሰብሮ ወሰዳት ልጅቱን' የሚል ምርጥ ግጥም ያቀርቡልናል..." አለ ጉጉት የመሰለው መድረክ አስተዋዋቂ። አፉ ላይ የደቀነውን ማይክሮፎን ድምፅ ማጉላቱን የተጠራጠረ ይመስል በጣም እየጮኸ ነው የሚናገረው።

ቀጠለ "ወ/ሮ ደርባቤ ለከፍለ ከተማችን፣ ብሎም ለከተማችን፣ ብሎም ለኢትዮጵያ ሴቶች፣ ብሎም ለአፍሪካ ሴቶች ታላቅ ምሳሌ የሚሆኑ የዘርፈ ብዙ ሙያዎች፣ ተሰጥኦዎች፣ ትምህርቶች፣ ሰልጣኖች ባለቤት ናቸው" አለና፣ "...አሰቲ ወ/ሮ ደርባቤን ወደ መድረክ..."

...ጀ...ጀ.....ጀ

ጥልፍ ቀሚስ የለበሱትና አንዳንድ ልማታዊ ዝማጅቶች ላይ ልማታዊ ግጥም በማቅረብ የሚታወቁት ወ/ሮ ደርባቤ መድረክ ላይ ቆመው በፈገግታ ለሕዝቡ ጎንበስ ቀና እያሉ ምስጋና ይሁን ሰላምታ ያለየለት ግማሽ ስግደት አቀረቡ። ግጥሙን ሊያቀርቡ ነው ብለን ፀጥ ስንል አስተዋዋቂው ማዋደዱን ቀጠለ፣ "...ቢታምኑም ባታምኑም ወ/ሮ ደርባቤ ይሄን ዝማጅት አስመልክቶ ግጥም እንድትፅፍልን የነገርናት (እንች አላት) ትላንት ዘጠኝ ሰዓት ነው። ይገርማችኋል ሌሊቱን ስትፅፍ

አድራ ዊት ስደውልላት በስልክ ማጥመን አነበበችልኝ...'ወይ መባረክ' ነው ያልኩት...::"(በሕዝባ ስልክ ስምንት ገፅ ማጥም እያነበቡ አላየንም ባርኩት)::

"...የግጥሙን ጥልቀት እና ውበት ራሳችሁ ታዘቡት...እስቲ ለዚህች ብርቱ ሴት ሞቅ ያለ ጭብጨባ..." ብሎ ጭብጨባውን ራሱ ጀመረው:: ማይኩን በሌላኛው እጁ ሊጠፈጥፈው አዳራሹ ጓ...ጓ...ጓ... በሚል ለጀሮ የሚቱፍ አስቀያሚ ድምፅ ተሞላ:: ከታዳሚው የተንበገረቀ ደካማ ጭብጨባ ጋር ተዳምሮ ጓጓታው በቀላል የነፍስ ወከፍ መሳሪያዎች የታጀበ የከባድ መሳሪያ ድምፅ ነበር የሚመስለው::

ብዙው ታዳሚ በየእጁ ፈንዲሻ እና ለስላሳ ይዞ ስለነበረ ማጨብጨብ አልቻለም አንጂ ለጭብጨባማ የእኛን ከፍለ ከተማ የሴቶች ሊግ ጽሕፈት ቤት ሰራተኞች ማን ብሏቸው:: ...በተለይ እጃቸው ባዶ ሲሆን የሚያጨበጭቡት ጭብጨባ ቢሾፍቱ ይሰማል:: እጃቸው ባዶ ሲሆን ለዜና ያጨበጭባሉ፣ ለሪፖርት ያጨበጭባሉ፣ የቀበሌው ሊቀመንበር ሲያስነጥሱ ሁሉ ያጨበጭባሉ፤ እጃቸው ሞላ ካለች ግን ጠቅላይ ሚንስትራችን ቢዘፍኑም እያጨበጭቡም:: አንዳንዴ ታዲያ ጭብጨባዎች ሲቀንሱ ኢኮኖሚያችን ያደገ ይመስለኛል::

ቀጠለ አስተዋዋቂው (ወ...ይ ዛሬ) "ወ/ሮ ደርባቤ...ገጣሚ ብቻ አይደሉም፤ የታሪክ ተመራማሪም ናቸው:: (ወ/ሮ ደርባቤ ቆመው በቁማቸው ገድላቸው ሲለፈፍ በፈገግታ ያዳምጣሉ)...ከፍተኛ ለድናቆት ያተረፈውንና...የከፍለ ከተማችን የኢድነት ማራቶን ሩጫ ከዘመነ ደርግ ውድቀት በኋላ' የሚለውን መጽሐፍ ጨምሮ አራት የግጥም መጻሕፍትን አሳትመዋል፤ ይሄን ያህል ካልኩ እንዳላሰለቻችሁ ወደ ወ/ሮ ደርባቤ ልምራችሁ..." ብሎ ማይኩን በአክብሮት ለሴትዬዋ አቀበላት:: ('እፎይ! አንድ አዛ ለቀቀ' ይላሉ አማሳ ሩቅያ ሲተርቱ)

...ማይኩን ተቀብላ ጓ...ጓ... እደረጎችና (የፊረደበት ማይክ ተጠፍጥፎም፣ ያወሩትን ሁሉ ተሳበሎ አጉልቶም አሳዘነኝ):: "እ...እኔ አንኳን የተባለውን ያህል ነኝ ብዬ አላምንም...፣ ምክንያቱም እንደ እኔ ዕድሉን ቢያገኙ...አንኳን ኢትዮጵያን ዓለምን 'ጉ...ድ' የሚያስብሉ ሴቶች ከእናንተ መሀል አሉ ብዬ ስለማምን ነው..." አለች ወይዘሮ ደርባቤ::

ጭብጨባ...!! ቼቼቼቼቼቼቼ (ፈንዲሻው አለቀ እንዴ ጭብጨባው ደመቀከ)

ከንኔ የተቀመጠች ሴት "እውነት ነው" ብላ ጮኸች:: (ዓለምን 'ጉድ' ከሚያስብሉት ሴቶች መሐል እንዲ ሳትሆን አትቀርም:: ዞር ብዬ ላያት በግራ እጁ 'ሞባይል' ስልኳን፣ በቀኟ፣ መዳፏ አስኪወጣጠር የዘንጉችውን ፈንዲሻ ይዛ በለሜት ወደ መድረኩ እያየች ቁጭ ብድግ ትላለች:: ...ከፈንዲሻው ኮርሸም አደረገችለት::)

ሴትዮዋ ግጥሟን ከማቅረቧ በፊት ለላሳ ደቂቃ አወራች::...እንዴት የወንዶችን ተፅዕኖ ተቋቁማ 'ታላቅ ገጣሚ' ለመሆን እንደበቃች፣ ሴቶች የርሷን ፈለግ ይዘው እንዲከተሏት፣ (ብትወዱስ እኔን

ምስሉ ጸርዳርታ)...ይሄን ሁሉ አወራችና "እንዳላሰለቻችሁ" በማለት ወደ ግጥሟ ተሸጋገረች !!
(ሃሃ ድሮ የሰለቸነውን !?)

ወደ መድረክ ስትወጣ መነፅሯን በታዋ ላይ ረሳታው ሰለነበር፣ "እቀብሉኝ!" ስትሳቸው የእጅ ቦርሳዋን አራት ሰዎች ግራና ቀኝ ይዘው (ማሸርገዳቸው ሰላበሳጫኝ የጨመርኩት ነው) አቀበሏት...።:ቦርሳዋ ውስጥ አስር ደቂቃ ፈልጋ መነፅሯን ቤቷ መርሳቷን አረጋገጠች።:...እናም ወደ ብርሃኑ ቀርባ ግጥሟን ማንበብ ጀመረች።:

አንቱራውን ሰብሮ መሰዳት ልጅቷን (ርዕስ)

ሸረ አያ ደገፉው ለንታ ትልቅ ሰው፣

አንዲት ፍሬዋን ልጅ ማስቸገርህን ተው፣

ውሃ ልትቀዳ መንዝ ሰትሄድ፣

ቁመሽ አውሪኝ አልካት በግድ...፣

ይሄ አልበቃ ብሎህ ለው ሞር ሲልህ፣

ሕፃኗን ደፈርካት አማዙር ይይልህ !! ('ውይ መንዶች፣ አለች ከጎኔ ያለችዋ ባለ ፈንዲሻ)

ደሟን አያዘራች አቢቷ ሰትደርስ፣

አንቱራ ሰበርሽ ብለው ገረቷት አያድርስ...

ደሞ በሌላ ቀን አንደሽ አድብተህ...፣

አሁንም ደፈርካት አንተ ግን ምን ሳይንት ለው ነህ...።። ('በስማም ጭከኔ ..ሌለዋ ሴት)

አዳራሹ ፀጥ ብሎ 'ግጥሙን' እያዳመጥን ድንገት ጎኔ ያለችው ሴት ጎርደምደምደም..ከሸሸሸ... ሰታደርግ ደንግፌዉ ዞሬ ተመለከትኳት።: ተመስገን ፈንዲሻ እየበላች ነው።:...እኔማ በግጥሙ ተመስጣ በስህተት ሰልኳን ቀረጣጠመቻት ብዬ ነበር።:

ግጥሙ ለድፍን ሀያ ሰባት ደቂቃ ተነበበ።: የግጥሙ የመጨረሻ ስንኞች...

ፈስቱላ ተይዘ ሰትንከራተት፣

ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ አማኝታት፣

ለዲሳባ በመኪና ለመጣቻት...

መንግሥታችን በሠራው ዘመናዊ አሊፓልት...!

አመሰግናለሁ !!

ጀኧጀጀጀጀጀጀጀጀጀጀጀ...(ታዳሚው ፈንዲሻውን ጨርሶ ነበር)

ለመውጣት ሳቆበቁብ አስተዋዋቂው አንዲህ አለ...

"ለሴቶች ቀን ያልሆነ ግጥም ለመቼ ይሆናል' በማለት ወይዘሪት ዘቢደር የወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ለማንበት ሃያ አንብባው የተደነቀላትን 'ታታሪዋ ሥራ ፈጣሪ' የሚለውን ግጥሜን ሳቅርብ ብላለችና አስቲ ወደ መድረክ..."

ጀጀጀጀጀጀ...

ተነስቼ ወጣሁ:: ወደ ቤቴ ሰሄድ ከኋላዬ የአስተዋዋቂው ድምፅ ይሰማኛል::

"...ወጣት ዘቢደር 'የእንስቷ ጣጣ' የሚል በቅርቡ በታተመ የግጥም መድብሏ ከፍተኛ እውቅና ያተረፈች ብርቱ ሴት ስትሆን..." እያለ ቀጠለ::

ይሄ ቀበሌ ነዋሪው ሳይሰማ ማተሚያ ቤት ከፈተ እንዴ?...እንዴት ነው ይሄ መድብል ማለትም አንዲህ የቀለለው ነበዝ ?!

21 “ሸረኛ” “እና” “ደህና” በአንድ ላይ ሲሄዱ በሸረኛው በኩል ተናደ መንገዱ

ሸረኛ፣

የዶክተር ደበሜ እርገጤ መዝገበ ቃላት ‘ሸረኛ’ የሚለውን ቃል ሲያብራራው እንዲህ ይላል፤ ሸረኛ – ስም፣ እንዳገባቡ ‘ተውላጠ ስም’፤ እንዳወጣጡ ‘ግስ’፤ ሳይገባም ሳይወጣም ራሱን ችሎ ፃረፍተ ነገር !!

ትርጉሙ፡- (በተንኮል የሰው ማንነት፣ መልካም ስም፣ መልካም ሥራ፣ መልካም ማንኙነት የሚሸረሽር፣ የሚሰረስር፣ የሚቦረቡር፣ የሚደረምስ፣ የሚያጠለሽ...) ይለዋል። መዝገበ ቃላቱ ይሄን ሁሉ ነገር ከሚያንዛዛ በቀላሉ መግለፅ ይችል ነበር ልክ እንደዚህ፣

ሸረኛ፡- ሰው - አቶ እጅጉ !! በቃ!! አጭር ግልፅና ወቅታዊ ፍቺ !!

ምላሌ፣ አቶ እጅጉ ሸረኛ ነው። ትክክል !! ይሄ ምሳሌ አይደለም፣ እጅጉ (እጅ እግሩን አስሮ ሊሰል ይወርውረውና) ‘ሸረኛ’ ነው። ሸረኛ ብቻ አይደለም፣ ምቀኛም ነው። የሚቀናበት ነገር ቢያጣ እኩል በተሰጠን 24 ሰዓት ይቀናል። (“እንደው በየትኛው ጊዜ ብትማሩት ነው ይሄን ሁሉ ነገር ያወቃችሁት?” ይላል የማያውቀውን ነገር አውቀን ካገኘን። ለነገሩ እሱ ምንም አያውቅም።) ምን ይሄ ብቻ! አማዜር በፈጠረው አየር ሳይቀር ይቀናል፣ የቢሯችን መስኮት ተከፍቶ እንደልብ አየር ሲገባ ብቅ ይልና፣ "ይሄን አየር በነፃ ትሉታላችሁ" ይላል። አንከፈል? ሸረኛም ምቀኛም ብቻ አይደለም መሰሪ ተንኮለኛም ነው።‘አሜልቶ አይሰጥም ይባላል አንጂ ይሄው የተሟላ ክፉ ሰው።

እንግዲህ ሸረኛ፣ ምቀኛ፣ መሰሪ ሆኖ ደግሞ አለቃዬም ነው። ጥሎበት አይወደኝም። እኔም ‘ለምወደው ሰው ስለማልወደው ‘ተመሰገን ቢወደኝ ምን ይውጠኝ ነበር?’ እላለሁ ሁልጊዜ፤ ለምወደው ሰው

ነው የምጨነቀው። አሁን በዚች ቅፅበት በሆነ አጋጣሚ ነገር ሎተሪ ምናምን አይነት እድል ገጥሞኝ በድንገት የብዙ ብር ባለቤት ብሆን (እሪ የትንሽም ቢሆን) የመጀመሪያ ሥራዬ ሁለት እጆቼን ኪስና ኪሴ ከትቼ በቀዳዳ ኪሴ ውስጥ በሾለኩ ጣቶቼ ራቁት ታፋዬን በማኳጠጫ ሙዚቃ 'ሪትም' እየተመተምኩ ጀነን ብዬ ወደ አለቃዬ ቢሮ ሄድና አንኳኳለሁ፣ ኖ...ኖ... አላንኳኳም፤ በሩን በእግሬ ገፋ አድርጌው እገባለሁ። (ካፈቀሩ ከነፍስ፣ ከጠሉም ከነፍስ ነው የምን ማስመሰል) ፊት ለፊት፣ ጉማሬ ፊቱ አለቃዬ ሁልጊዜ በሚደፈርሱ አስቀያሚ ደመና አይኖቹ ያፈጥብኛል። ቀጥሎ ኪሶቼ ውስጥ የወሸቅኳቸውን እጆቼን በቁጣ ያያል፣ (ደንግጬ ከኪሴ እንዳወጣቸው እንድርበተበት።) ፀጥ ብዬ በትዕቢት ሳየው የኢትዮጵያን ሲጋራ ሁሉ ብቻውን ያጨሰ ከሚያስመስሉት አስቀያሚና ገጣባ ከንፈሮቹ ቃላት ይፈለፈላሉ፤ ሰው ሰው የማይሸቱ አብሪተኛ ቃላት።

ምናልባትም፣ "ብላችሁ ብላችሁ ማንኳኳቱንም ተዋችሁት..." ይል ይሆናል። (እግዜርና ሰይጣን ለዚህች ቅፅበት አርቅ አውርደው ይሄን ድንጋይ ራስ አለቃዬን በመጾሻ ያንኳኩትና።) ወይም፣ "ኪስህ የወሸቅከውን እጅህን አውጣ!" ሊልም ይችላል፣ አላወጣም ! (ኪሴ ቀዳዳ ቢሆንም ቀዳዳውን ተሻግሮ ያለውም ወንድነት የራሴ ርስት ነው - ዘራፍ ! በቀዳዳ እኚነታችን ውስጥ አያለቃ ወንድነታችንን ያከላሹን ከፉዎች ሁሉ ከዛሬ ጀምሮ አድርጉ ያሉትን አናደርግም።)

ኮራ ብዬ "እእእኣ አቶ አጅጉ" አለዋለሁ። ("አቶ" በማሾፍ ሲጠራ እንዴት ያለ አሪፍ ስድብ ነው።) ለምሳሌ፣ እኔ "አቶ" ከሚለው ቅፅል ይልቅ ከስሜ በፊት ሰሃራን የሚያህል ባዶ ምድረ በዳ ቢዘረጋ ይሻለኛል። በተለይ አለቃዬ "አቶ" ከሚለኝ !! ...አም ! አቡ "አቶ" ሲለኝ በውስጡ "መቼም ለአቶነት አትበቃም በቸርነቴ 'አቶ'ነት ልስጥህ እስቲ" የሚል ይመስልበታል። 'አቷሞ!!

አና "አቶ አጅጉ ከዛሬ ጀምሮ ሥራ ለቅቄያለሁ" አለዋለሁ - በኩራት። 'እእእኣ' የምትለዋን ዘገምተኛ ቃል ማሰቀደም አልረሳም። አራት ዓመት ሙሉ የሱን አስቀያሚ 'እእእኣ' ችዬ ኖሬ የለ - ሰለዚህ የምለው እንደዚህ ነው። "እእእኣ...አቶ አጅጉ ከዛሬ ጀምሮ...እእእኣ ሥራ ለቅቄያለሁ !!"

ይደነግጣል፣ አያምንም። እኔ ሰፈጋ የዋልኩበትን ሥራ ሁሉ ለአለቆቹ እንዲህ ሠርቼው እንዲህ አድርጌው አያለ በሰልክ መወሸክቱ ሊቆም ስለሆነ ይደነግጣል - አሰይ ! ወሸካቶች መደንገጥ አለባቸው።

ወዲያው የበሰበሰ የማኔጅመንት 'ሲስተሙን' እኔ ላይ ሊምከራት ይፍገመገማል፣ "አትደንግጥ የበታች ሠራተኛህ ፊት አዋቂ፣ ልበ ሙሉ ምንትሰ ሆነህ ቅረብ፣ ባትሆንም ሁን..." የምትለዋን ያስብና ጉሮሮውን ጠራርጎ፣ "እእእ...እዚህ መሥራቱ ራስህን ለማሳደግም ሆነ ቢተሰብህን ለመርዳት አይሻልህም?" ይላል። ሥራ ብለቅ ቤተሰቦቼ በረሃብ ዛሬውኑ የሚያልቁ በሚያስመስል ሁኔታ 'ቤተሰብ' የምትለዋ ቃል ላይ አፅንኦት ሰጥቶ።

ከፉዎች መሳሪያ ልጅህ ላይ ባይደግኑም፣ እናትና አባትህን አፍነው ባይወስዱም፣ የነሃን ጨለማነት እየነገሩ ያግቱሀል። ስንቱ መሰለህ ቁራጭ ዳቦ እንዳይነሱት ፈርቶ ለማንም አጋሰስ ጉልበቱን

የሚገፈግፈው፣ ስንቱስ ነው 'ከሥራ መባረር' የሚባል የታንክ አፈ ሙዝ ልቡ ላይ ተደግኖበት ዘመናዊ ባሪያ የሆነው !! ስንቷን ሚስኪን በፀሃፊነት ስም የጭን ገረዱ ያደረጋት ጋንጩር አለ ቢሮ ይቁጠረው !!

ሀላፊ ሲባል አርቲስት ነው። ወንበሩን መድረክ ያደረገ ተዋናይ። ያውም ድብን ያለ ትራጀዲ የሚተውን። እና እኔ ምን አለዋለሁ... ሃላቤ ደስ ብሎኝ ሳምለለስል፣ ዙፋን ዘው ብላ ወደ ቢሮዬ ገባች። ጥሎባት ማንኳኳት አትወድም። 'አንኳኪ!' ብሏት የሚያውቅም የለም።

"አብርሽዬ" ትለኛለች። (ስሟን ከነአያቷ ቁስ ይጥራትና) ! ሁልጊዜ ስትጠራኝ እንዲሁ ነው። ታዲያ አጠራርዋ ከማማሩ ብዛት እኔን ለጠራችኝ ሌሎቹ 'ወይዬ' ሊሏት ይዳዳቸዋል።

"እንዲህ በሀሳብ ሞልጥ ያልከው ወዴት ሄደህብኝ ነው?" ወዴትስ ብሄድ ምን አገባት። ጭራሽ የምሄደውስ የምቀረውስ ለሷ ነው እንዴ? ('ሄደህብኝ !!' ጥርግ ብል እንትናዬ እያለች አንዱ ቢሮ ልትንኳተት።)

"አ...ምነው ጠፋሽ?" አልኩ እንደመጣልኝ። የምለው እጥቼ እንጂ ዙፋን ደግሞ መቼ ጠፍታ ታውቅና። በአንድ ጊዜ ሰባት ቢሮ ውስጥ የምትገኘውን ዙፋንን ጠፋሽ ማለት መሬትን "ምነው በዚህ ሳምንት መዞርሽን አቆምሽ?" ብሎ ከመጠየቅ አይተናነስም።

"ሆሆ ከየት ተገኘሽ፣ አሁን እንኳን ስመጣ አራተኛዬ ነው" አለችና ከጠረጴዛዬ ፊት ለፊት ወንበር ስባ ተቀመጠች። ወንበሩ ተንጫጫ። ጉርድ ቀሚሷ ቀይ ታፋዋን ወለል አድርጎ ያሳያል.... ኤጭጭጭጭጭጭጭ!!

"ቆንጆ ናት" ይባላል። "ትሁት ናትም" ይሏታል። "የሰለጠነች፣ ሰው አከባሪ" የሚሏትም ብዙ ናቸው፣ እንደው ባጠቃላይ አዚህ ቢሮ ዙፋንን ለማናገር፣ ለማቅረብ፣ ቢመቸው ወደ አልጋው ጎትቶ አብሯት ለመጋደም የማይመኝ ያለ አይመስለኝም።

ዙፋን እኛ ቢሮ ሥራ ስትጀምር ከሥራ ልምዷ ጋር ከአግዜር የተላከ "ከዛሬ ጀምሮ 'ያየ አመነዘረ' የሚለው ጥቅስ ተሰርዟል" የሚል ደብዳቤ ይዛ የመጣች ይመስል፣ እዛ ቆይናንስ ከሚሠራው ዲያቆን ወልዱ ጀምሮ ሰው ሰላም ሲል አገፍጩ መሬት እስኪነካ የሚያጎነብሰው ጴንጤው ምክትል ኃላፊያችን የዙፋንን እግርና መቀመጫ አይተን እንሙት አሉ። ዙፋንም ታዲያ የፅለት አንጀራዋ የሰው አይን ይመስል ነገረ ሥራዋ ሁሉ የታይታ ነው። አቤት መታየት ስትወድ። ሰው ከኋላዋ እንደሚያያት ከጠረጠረች ለከፋ ቁን ያስቀመጠችውን መቆናጠር ሁሉ ትጠቀምበታለች።

ጥሎብኝ አልወዳትም፣ እሷም ታውቀዋለች፣ ምንም ትልበስ፣ እንዴትም ትራመድ እንደገለባ ትቀልብኛለች። ብትሞት ቢሮዬን ሳትረገጥ አትውልም - 'ዛሬስ እንዴት ነኝ?' አይነት። የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ፀሃፊ ናት። ቅርብ ጊዜ ነው የተቀጠረችው - ሃሃሃ ወይ መቀጠር፣ ቅጥር ነፍሰ ገዳይ።

የአለቃዬ አለቃ ፀሃፊ ናት። የተመቻት የሃብታም ልጅ፣ ቤት ከመዋል ብላ ፀሃፊ የሆነች። አሷ 'ፀሃፊ' ሲሏት አትወድም፣ 'ሴክሬታሪ' ነኝ ነው የምትለው። ውድ ልብሶችን የምትለብሰ፣ በተረከዘ ረጅም ጫማ ከቢሮ ቢሮ 'ሰታውደለድል' የምትውል ቆንጆ እንዴት ፀሃፊ ትባላለች? የሚያማልሉ ቀያይ አግሮች ያሏት፣ የከረመና የታጀለ የወረቀት ጠረን የሞላውን ቢሮ በሽቶዋ የምትፈውስ ዙፋን እንዴት 'ፀሃፊ' ትባላለች? ጥና ሳያት እንደረሽምና እንደማያልቅ መንገድ ትደከመኛለች፤ አንደ ረዥም ሰዓ ቢሰ ወሬ ትሰለቸኛለች። ከልቤ ትሰለቸኛለች። ባትመጣብኝ ደስታዬ ነው። ይሄንን ነገር ማመን አልቻለችም። በሕይወት ዘመኗ እንደኔ ፊት ነስቷት የሚያውቅ ወንድ ያለም አይመስለኝም።

...ትለዋለች በተዘዋዋሪ፣ "...እከሌ እኮ ጨዋ ነው፣ የኔ ጌታ እሱን ያገባች የታደለች። ቢሮው ስሄድ ከወንበሩ ብድግ ብሎ ሥራውን አርግፍ አድርጎ ትቶ እኮ ነው የሚያዋራኝ..." እንኳን ተነሳላት ! ለምን ከመነሳት አልፎ ዘሎ ኮርኒሱ ጋር አይጋጭም። እንኳን ለደቂቃ ሥራ ማቆም፣ ለምን የሥራ መልቀቂያ አያስገባላትም። እዝግ፣ ታዝገኛለች። ኮተታም ከብር አሳዳጅ።

የጠላሁባት ምክንያት እንደ አንዳንድ ወንዶች ከራሳቸው ጋር ፈተና ሲገቡ መሻታቸውን ሊሸሹ ሴት እንደሚያንቋሸሹት አይነት አይደለም። ቁልጭ ያለ አገር ያወቀው ፀሐይ ያገረረው፣ በአምባገነን አግሯ ምንም በሆነ ሲትነቷ፣ ፍትህ ትረግጣለች፣ ያማረችው በሚስኪኖች እንባ ታጥባ ነው። ንፅህናዋ ንውህ ነፍሳትን ትቢያ አድርጋ ነው። ያውም ራሳቸውን መከላከል የማይችሉ ሚስኪኖችን። ሽረኛ ናት። ዙፋን ሽረኛ ናት። አለቃዬ ሽረኛ ነው። እዚህ የተሰበሰቡ ወተፈናም ኃላፊ ተብዬዎች ሁሉ ሽረኞች ናቸው። እና፣

መዝገበ ቃላቱ፣ 'እና' የምትለዋን ቃል አያያዥ፣ ብቻዋን የማትቆም ቁንፅል ይላታል። በአጭር ምሰሌ 'እና' እኔ ነኝ። በሽረኞቹ እና በደህነኞቹ መሀል ያለሁ ወይ አልሸርር ወይ አልደህንን "እና" እኔ ነኝ። ምንም ታሪክ፣ ምንም ትርጉም የለኝም።ሥራዬም ባህሪዬም በሆኑ ነገሮች መሐል መደበቅ ይበዛበታል "እና" ነኝ !! እና ምን ይጠበሰ።

ደህና፣ አማማ መለኮት መዝገበ ቃላቱ ሳይሆን መዝገበ አማዚሃር "ደህና" ብሎ የሚላቸው አይነት ናቸው። አማማ መለኮት እድሜያቸው ሃምሳ ሁለት ወይም ሃምሳ ሰባት (እራሳቸው እንደሚሉት)፣ ትህት፣ በዚህ እድሜያቸው ሰሁሉም ሰው ታዛዥ እና የሁላችንም መካሪ። አማማ መለኮትን የማይወድ ማንም የለም - መሰፈሪያው ቢለያይም። በምንም ይሰፈር በምን፣ እንደኔ የሚወዳቸው ግን የለም።

የዛሬ ዓመት አካባቢ አማማ መለኮት ቢሮዬ መጥተው ከጠረጴዛዬ አንድ ሁለት አርምጃ ራቅ ብለው ቆመና ከወገባቸው ጎንበስ በማለት ሰላምታ አቀረቡ። ያረጁ ይመስላሉ። ፊታቸው በሀዘን እኮፍኩፎ በአድሜ እናቴን ይበልጣሉ። ከወንበሬ ተነስቼ ለሰላምታ እጄን ዘረጋሁላቸው፣ በሁለት እጆቻቸው አሁንም ጎንበስ ብለው ሰላም አሉኝ፣ እጃቸው ይሻከራል፣ ልክ እንደ እናቴ

እጅ:: አነዚህ ሞረድ አጀች የስንቶቻችንን ባለ ለሰላሳ አጀች ህይወት እንደሞረዱ ፈጣሪ ይወቅ !

እንዲቀመጡ ወዳመለከትኳቸው ወንበር ቀስ ብለው ተቀመጡና የመጡበትን ጉዳይ ቀስ ብለው አስረዱኝ፣ "አቶ አብረሃም (አቤት 'አቶ' በአላቸው አንደበት እንዴት ከብር እንዳለው !) ያው እንደምታውቀው እዚህ ቤት ነገረ ሥራቸው ሁሉ ውስጥ ለውስጥ ነው:: ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሰልል በሠራሁ ለትንሽ ትልቁ 'እሺ!' ብዬ ባደርኩ ድንገት ከሥራዬ ነቀሉኝ::" አሉና እንባቸው ተዘረገፈ! እድሜ በሸነተረው የቆዳቸው አጥፋት ሽብሽብ ውስጥ እንባቸው ጎረፈ:: በነጠላቸው ጫፍ አይናቸውን ጠረጉ:: (አዚህች ባልቴት ውስጥ ይሄ ሁሉ እንባ እንዴት ሊኖር ቻለ? እድሜ ልካቸውን ያጠራቀሙት ይሆን?) እማማ መለኮት ከፅዳት የሥራ መደብ ተነስተው በሀያ ዓመት የቢሮክራሲ ባቡር ተጉዘው ፀሃፊ ለመሆን የበቁ ፅኑ ሴት ናቸው:: ከልምድ አንዳየሁት ብዙ ታላላቅ ድርጅቶች ሱፍ ለብሰው በሚኮፈሱት አለቆቻቸው ሳይሆን በሚሰኪኖች ትከሻ ላይ ተጭነው ነው የቆሙት:: እማማ መለኮት የድርጅታችን ዋልታ ይሄው ተባረሩ::

ከዛ በፊት፣ ከመባረራቸው በፊት፣ አሸሙር የሚመስል ስብሰባ ተደረገ:: አንዲት ረዳት የሌላቸው ሚስኪን ባልቴት ለማባረር ቱባ ቱባ ባለስልጣን፣ ከቱባው የተኮረተሩ ከር ኢቃጣሪዎች እና "እናዎች" ውሃ ቡና ቀርቦ ስብሰባ ተደረገ::የስብሰባው መሪ፣ "ሸረኛው" እጅጉ፣ ፀሃፊው "ሸረኛው" አለሙ፣ ተላላኪው፣ ወሬ አቀባዩ (እንደ ሰው አልባ አውሮፕላን አያንጣበበ ሰላኩት አለቆቹ ወሬ ይቃርማል:: "መታዘዝ ፅድቅ ነው" ሲባል የመታዘዝ ፅድቅነትን የማያመዛዝን አዕምሮ ተሸከም የሌሎች ባሪያ መሆን ማለት አይደለም:: ሰብዓዊ ትዕዛዝ፣ ሰው መሆን 'ይቅርብህ ተበለህ ሳይሆን፣ 'ለእኔ ማለት ይቆየኝ፣ ቅድሚያ ለሌሎች' ከሚል በጎነት መነሳት ነው:: በጎነት በትዕዛዝ አይመጣም::)

ስብሰባው ተጀመረ:: ለአንዲት ባልቴት ተሰበሰቡ እንዳይባል የማይረባ አርሲ ኩርሲ አጀንዳ ጋር ተደምሮ የእማማ መለኮት መባረር "መቀነስ" የሚል የዳቦ ስም ተሰጥቶት አጀንዳ ሆነ::

"ባንድ ላይ ሲሄዱ" መዝገበ ቃላቱ በአንድ ላይ መሄድን በአንድ ላይ ከመታየት ነጥሎ አለማየቱ ትልቅ ኮድለት ነው::

ሸረኛ"፣ "እና" ና "ደህና" ስብሰባው ላይ በአንድ ላይ ተገናኝን፣ በማንኛችን በኩል መንገዱ እንደሚናድ ልናይ - ቀድሞ የተናደውን::

"ተናደ"

ስብሰባውን የጀመረው አለቃችን አቶ እጅጉ ነበር:: ኩፍስ ብሎ የኮቱ አጥፋት ሸብዳዳ ትከሻው ላይ ተከምሮ (ከኮቱ ውስጥ ትንሽ የሰፋ ትራስ ያስቀመጠ ይመስለኛል):: ጨዋ ለመሣሰል በሚዳዳው ድምፅ ስብሰባው መጀመሩን አረዳ ('አበሰረ' የሚሉም አሉ "ከሸረኞች መሃን ናቸው") "አ..ያው እንደምታውቁት..." አለ (ምንም በማናውቀው ነገር) "...መሥሪያ ቤታችን ያለውን

መልካም ስምና ዝና ለማስቀጠል (ሂሂሂሂ ጉድ ፈላ በቀን የሚመጣው ባለጉዳይ ሁሉ እዬዱ እያለ ተራግሞ የሚሄድበት መሥሪያ ቤት 'መልካም ስምና ዝና' ይሁና...) ዘመናዊ የአሠራር ሲስተምና ዘመን አፈራሽ መሳሪያዎች እንደሚያስፈልጉ በማመን የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ወስደን እየተንቀሳቀስን 'ያለበት ሁኔታ ነው ያለው'...

እነዚህ ዘመናዊ መሳሪያዎች ደግሞ ብቻቸውን 'ጠብ' የሚል ለውጥ እንደማያመጡ 'እሙን' ነው፤ ስለዚህ ቢሯችንን 'በአመለካከት' 'በአውቀት' 'እና' 'በተግባር' ከመሳሪያዎቹ ጋር አብሮ በሚሄድ 'ወጣት' የሰው ኃይል ማደራጀቱ ለነገ የማይባል አንገብጋቢ ተግባር ነው... !!"

በእማማ መለኮት በኩል መንገዱ "ቱናደ"። ጨዋነትን የጫነው መኪና ገደል ገባ። ትህትና ተሽቀነጠረ። መንገድ ስለሌለ ወደኋላ ተመለሰን። መንገድ አፍራሽ ሸረኞች ራአይ እንደሀልም ያያሉ። ከመድረሰም ተጣልተዋል። መንገድ የለማ ...!! ከአባይ ወዲያ ማዶ ያለ ዘመድ ሆነ የእማማ መለኮት ሥራ፤ እንባቸው በአይናቸው የሞላ አለት ዋይ ብለው ቀሩ።

እንዲት በእድሜ የገፉ ሚስኪን አባሮ በየቢሮው እየዘረች ምስጋና የምትቀላውጥ ገልቱ ለመቅጠር ምድረ ጉማሬ ሚስኪኑን ላብ አደር ሰብስቦ አላዘነ። ደግሞ ስለዘመናዊነት ያወራሉ፣ እማዚኦ አለቆቻችን ስለዘመናዊነት አወሩ።ስልካቸው ባትሪ ሲጨርስ ተበላሸ ብለው ሠሪ ቤት የሚሮጡ አለቆቻችን ዘመናዊነትን ሰበኩ። ከፕሪንተር የሚወጣ ወረቀት ደመና ሰንጥቆ እንደሚወጣ መልአክ በግርምት የሚመለከቱ። ('እይ ፈረንጅ ነፍስ መፍጠር አኮ ነው የቀረው!' እየተባባሉ።) አለቆቻችን ዘመናዊ እንሁን አሉ።

እማማ መለኮት በጡረታ ስም ተባረሩ። ('ተቀነሱ በል እቶ አብረሃም' ተብያለሁ።) ዙፋን ተቀጠረች - እሁን ድርጅቱ ዘመናዊ ሆነ። "እንደምን ዋላችሁ..."፣ "ሃይ ጋይስ" በሚል ሰላምታ በመተካቱ አልልል ቢሯችን ዘመናዊ ሆነ።

ዙፋን የዘመናዊነት ፋና ወጊ፤ አንድ ገፅ ደብዳቤ ስትፅፍ አንድ ከግማሽ ገፅ ስህተት የምትዘራ ጉድ። ወሬ ብቻ፤መሸኮርመም ብቻ፣ በየሰሙ ላይ 'ዬ' መጨመር ብቻ (አብርሽዬ...ቶማስዬ... ጋሽ ሰይድዬ...ተፈራዬ...ሐንስዬ...ገኔዬ...አማዚያብሄርዬ...ጂሰስዬ_) እንደ 'ዮ' ፊደል ትልቅ አፍ ብቻ ያላት መርገምት።ደህና ነገር ሲናገር ከንፈሩ እንደደረቀ ሰው በየደቂቃው ቻፕስቲክ እየተለቀለቀች በየቢሮው ማውራት !! ('ውይ ጥርስ አታስኪድንም፤ ተጫዋች ምናምን ይሏታል - የሸረኛው መንታ።)

ቆንጆ ብቻ መሆን እንዴት ይቃጫል። ሴት ብቻ በመሆን ከወንድ የሚቸር ወሲባዊ ኩበር ምኞ ውድቀት ነው?! ዕድሜ ከፍ ባለ ቁጥር የሚናድ የእንቧይ ካብ። እንዴት ሰውን ያህል ፍጥረት ያውም እናትነትን ያህል አደራ ትቀበል ዘንድ ተፈጥሮ የጠከሰቻት 'ሴት' ስለጥፍር እንድ ሰዓት ሙሉ ታወራለች? ስለፀጉር ሁለት ሰአት፣ ስለጥፍር ቀለም ሙሉ ቀን፣ስለ ልብስ..

የመታየት ልክፍት (ኤግዝቪሽኒዚም ይለዋል በሬቻ)። በፋሽን ስም ነጋቸው ላይ ውበት ሊዘሩበት

ምሽሎትን ዘፌ አርሲ ኩርሲ የውበት ኮተት እያወሩ ይፈጁታል። ይሄ የሴት ውበት ነው የሴት ብከነት። ስለውበት የሚደሰኩር ሚዲያ ላይ አፍጥጣ የምትውል ዙፋን፣ ቆዳዋን በምናምን አደንድና ፍቅር እንዳይሰርጻት ራሷን ሲታዋድድ ትኖራለች። ሴት ከመልክ የተሻለ መወዳደሪያ ዘሌላት ውድድሩ ውሰጥም የምትኖረው ቢበዛ ሰጥቂት ዓመታት ነው። ባካና ! ዙፋን ባካና ናት፣ ስሟ ራሱ እሷ ላይ ሲደርስ 'ዙፋን' የሆነ፣ የመወዘፍ አይነት ደውል ነው። (ውዝፍ ከሚለው ስርወ ቃል የመጣ...)

ከአለቃዬ ጋር በአይኗ ስትዳራ ስንት ጊዜ ታዘብኩ። እማማ መለኮትን ነቅላ ላትፀድቅ ነገር ራሷን የተከለችበትን ቆሻሻ መንገዷን አይቻለሁ። ለፀሃፊነት ሥራ ውድድር መሰለፍ የማይችል ባለጩት ጨንቅላቷ ላይ ሰው ሰራሽ ፀጉር ጎዝጉዛ ከቡር ሴትነቷን በየቢሮው ስትነዘንዝ ሳናይ አለወራንም፤ "ጭስ ካለ እሳት አለ" ብለንም አይደለም። ቆይቶ የተደረገ ግምግማ ላይ የተገደደች አበመስላ ቀባጠረችው አንጂ። ("የሸረኞች መንገድ የተናደች" አለት)

ባለቤት የለሽ ሰጥ ማንም አላፊ አግዳሚ የሚዘማናት። ወንዶች በምናምንቸው እየተመሩ የሚደርሱባት ጥግ። የሴትነት ባንዲራ ዝቅ ብሎ የሚውለበለብባት ፀያፍ ምስሶ። ለወረደ የሴትነት ባንዲራ ሴሰኛ ወንዶች ሲዘምሩ ምስሶው አንዴት 'ቴንኪው' አያለ ይሽኮረመማል?

የእድሜ ጉዳይ ነው፣ ያች የሴትነት ባንዲራ ትወርዳለች። ያኔ ዘማሪ ሲጠፋ ሴትነት የተጎጠለው "ሰው መሆን ብቻውን" ሲቆም ይሄ ከተማውን የሞላው አላፊ አግዳሚውን በቅናት ግልምጫ የሚጎነትል፣ "ምከሩ ላይ ሰቆ የመከራ ዱላ መድረሻ ያሳጣው፣ ፍቅር አልባ የሴት ፊት ሁሉ" ዙፋን የተባለች መህበርተኛ ይመረቅለታል።

አቀባበል ይደረግላት ተባለ - ዙፋን። ሰው እንዴት ምንም ይቀበላል? በማ ታርዶ፣ ቢራ ቀርቦ "አንዲት ፀሃፊ ለመቀበል ይሄ ሁሉ ድግስ" አንዳይባል፣ ለአቀባበሉ ህዝባዊ ስም ወጣለት - "የሩብ ዓመቱ የማምሻማ ማጠቃለያ"። ሲበላ፣ ሲጠጣ ሸረኞች የሸረኛ ልዕልታቸውን ከብበው እያውካኩ ጥሬ ከብስል ሲሰለቅጡ እማማ መለኮት ናፈቁኝ። እንዲህ ዝማጅት ሲኖር አሳቸው ሴሊት ሁሉ እያደሩ ወጥ ይሰሩ ነበር - አምስት ሳይከፈላቸው። ነጭ ልብሳቸውን ለብሰው፣ ምድረ ሆዳም ሲያስተናግዱ ይውሉ ነበር።

መንገዱ...

ከማብሯው ሹልክ ብየ ወጣሁና፣ አጠያይቄ እማማ መለኮት ቤት ሄድኩ። በራቸው ላይ ቁጭ ብለው የምስር ክክ እየለቀሙ ነበር። ሲያዩኝ በድንጋጤና በግርምት ተርበተበቱ። የምስር ክክ የያዘውን ትሪ ወደቀኞቸው ካለች መደብ ነገር ላይ ሲያስቀምጡ -የተለቀመው ካልተለቀመው ቀፋሳቀለ_። አንደእኛ ቢሮ፣ እንደእኛ ሃላብ፣ እንደእኛ ፖለቲካ፣እንደእኛ እኛነት ተመልሶ መልቀም። አዲስ እንግዳ ሃሳብ፣ እንግዳ አሰራር፣ እንግዳ ርዕዮተ ዓለም ሲመጣ ያከበርን መስሎን የሰራነውን ማፍረስ።

ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው በአክብሮት ቆሙ፤ "ውይ በሞትኩት አዚህ ድረስ ምን አለፋህ

አቶ አብረሃም - እጄ ቆሻሻ ነው ቆይ" ብለው ቀሚሳቸው ጋር ጠራረጉና በተሰፋ አያዩኝ ጨቡጥኳቸው፣ ምናልባት ወደሥራ ልመልሳቸው የሄድኩ ይመስላቸው ይሆን? ግባ አሉኝ፣ ገባሁ፣ ንውህና ጠባብ ናት ክፍላቸው:: ወደጓዳ መግቢያ ላይ ባለጥልፍ ነጭ መጋረጃ:: ባለመደገፊያ የቀርከሃ ሶፋ:: ግድግዳ ላይ አንድ ጥቁርና ነጭ የትልቅ ሰው ፎቶ አለ (ባላቸው ይሆኑ?):: ከነኑ ባለድግሪ ወጣት ባለቀለም ፎቶ:: አማማ መለኮት መጋረጃዋን ገለጥ አድርገው ወደ ጓዳ ገቡ::

*** *** ***

ቡና እንደምወድ ያውቃሉ:: ላፍላልህ ሳይሉ ቡናውን አቀራረቡ:: አወሩኝ ስለነበረው፣

"ማራ ገብቶኛል፣ እንቅልፍም አልወስድሽ ብሎኝ ነው ያደርኩት:: አንግዲህ በዚህ ዕድሜ ሰው ቤት ልብስ ላጥብ ነው ? አንጀራ ልጋግር ? እኔኮ ሌላው አይደለም ያሳዘነኝ፣ ይሄን ያህል ባመት ያገለገልኩበት ቤት ነው:: ምናለ ለወጉ ጠርተው እንግዲህ በቃሽ ቢሉኝ:: አቶ እጅጉ መጥቶ፣ ሰሜን አንኳን አልጠራኝም፣ ይሄን ኮምፒተር አፀዳጅው፣ እንግዲህ ጡረታ መውጫሽም እየደረሰ ነው' ቢቃ እንዲህ ነው ያለኝ:: የዛሬን ቀን አያምሽልኝ፣ እንዲሁ አለኝ...ይባላል ? አቶ አብርሃም አስቲ ፍረድ፣ ፍርድ ለራስ ነው መቸም..."

አለቀሱ አማማ መለኮት:: የማደርገው ነገር ጠፋብኝ:: "ብዙ ያየሁ ሰው ነኝ፣ ይከፋኛል፣ ማግኘትም ማጣትም ማጀቴን የጎበኘው ሰው ነኝ::ባሌ የሞተብኝ ሴት ነኝ-አርጅቻለሁ:: ልጄ ምጥ ይግባ ስምጥ የጠፋብኝ ብሎተኛ ነኝ:: ለትንሽ ትልቁ ደፋ ቀና የምለው ቀባሪ የለኝም፣ 'የአገሬ ሰው ነው ቀባሪዬ' ብዬ ነው:: እንዴት እንዲህ ያመንኩት ህዝብ ይተፋኛል? እንዴት ባዕድ እሆናለሁ? አይዞሽ ማንን ገደለ? ፀሃፊነቱን ይተዉት እናትነት ይመረመራል ? አንድ ሰው በሬ ዝር አይልም ? በሃዘን በደስታው ከሥራዬ አልፎ ተርፎ ለድግሳቸው ጉልበቴን ገብሬ ቤታቸውን አሳቀናሁም ? ፍረድ አቶ አብረሃም - ፍርድ እንደራስ ነው" ስኳር ወደ ስኒዎቹ ጨመሩ:: በዝምታቸን ውስጥ ቡናው ሲቀዳ ደስ የሚል ድምፁ ጠባቧን ቤት ሞላት:: አንዲት ከሰት ያለች ጥቁር ድመት ንበታ ረከበቱ አጠገብ ቆመች:: ለቡና ቁርስ ከተቆራረሰው ዳቦ ቆንጥረው ሰጧት::

"አማማ መለኮት!" አልኩ ቀሰ ብዬ፣

"ወይዬ!" አሉ ቡናውን እያቀበሉኝ::

"ልጄ ጠፋ ነው ያሉኝ...?" ወይ ወሬ መውደድ አሁን የሰው ብሶት ከመቀሰቀስ ውጭ ምንም ላልፈይድ ምን አጠያየቁኝ_::

"አዎ...ይሄ ፎቶ የሱ ነው" አሉ ወደ ባለድግሪው ወጣት እየጠቆሙኝ:: ጭራሽ ተነስተው ፎቶውን ከተሰቀለበት አወረዱና ሰጡኝ:: መልከ መልክም ወጣት ነው፣ ሳቂታ::

ልጄ ነው - አንድ ልጄ። ስድስት ኪሎ በድግሪ ተመርቆ ወር ላይቆይ 'ወደ ውጭ አገር ልሂድ' ብሎ ተነሳ። 'ኬኒያ የሚባል አገር ደረስኩ' ብሎ ደወለልኝ። ይሄውልህ ከዛ በኋላ ይኑርም ይሙትም ወሬው የለ" ብለው አንባቸውን ዘረገፉት።

"ከሄደ ቆየ ?..." በሃሳቤ ኬኒያ ያሉ ጓደኞቼን 'ይሄን ልጅ ካላገኛችሁ ወዮላችሁ!' ልል ተዘጋጅቼ። "እንግዲህ ወደ አስራ አምስት ዓመት አይሆነውም ብለህ ነው...?" ፎቶው ላይ አፍጥጬ ቀረሁ።

"ቡናው ቀዘቀዘብህ፣ የኔ ነገር" ብለው ፎቶውን ከእጄ ተቀበሉና ቦታው መለሱት።

ስናወራ ቆይተን እንደምጠይቃቸው ነግሬያቸው ስወጣ፣ "አቶ አብረሃም፣ ካላስቸገርኩህ በቀደም ተጣድፌ እኔ መሳቢያ ውስጥ፣ መሃረቤን ረስቸው መጣሁ። አንደው ላቶ ሽበሩ ብትሰጥልኝ በዚሁ ሲያልፍ ያቀብለኛል" አሉ። አቶ ሽብሩ የመስሪያ ቤታቸን ሹፌር ነው።

ያችን ተዓምረኛ መሃረብ የቢሮው ሰው ያውቃታል። አማማ መለኮት ፀበል ቤት ይሄዱና ወይም ቤታቸው ዝክር ብጤ ትኖራቸውና ሰምንቀርባቸው ባልደረቦቻቸው የፀበል ቤት ዳቦ በመሃረባቸው ጠቅልለው ያመጡልናል - በቀይ ክር የሀረግ ጥልፍ ዙሪያውን የተጠለፈበት መሃረብ።

*** *** ***

በቀጣዩ ቀን ቢሮ ስገባ አቶ እጅጉ ደረጃው ላይ አገኘኝና፣ "አቶ አብረሃም፣ ምነው ድግሰ ረግጠህ ወጣህ?" አለኝ። "አጋሰስ!" አላልኩትም።

የአማማ መለኮትን መሃረብ ለማምጣት ወደ ዙፋን ቢሮ ሄድኩ። ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር አማማ መለኮት ከለቀቁ በኋላ ወደዚህ ቢሮ የመጣሁት። ዙፋን እሷን ከፈተቻው፣ "አ...ንተ በመጨረሻ መጣህ። ዝም ብለህ ትንቀባረራለህ መምጣትህ ላይቀር" አለች ፊቷ አንበሳ ጉዳይ አይነት ቆንጆ ሰፍሮበት - ደነዝ!! እታንብሳ እግሯን የሆነ ነገር አያደረገች ነበር የምታወራኝ - ጠረጴዛው እግሯን ጋርዶኛል።

"ምን እዚህ ይሄ መንገዳችሁ አባራ ብቻ ነው ኤጭ"። ተሸከርካሪ ወንበሯን ወደእኔ ስታዞረው የተራቆተ ቀኝ ታፋዋ ስለተቀመጠች በጣም ገዘፍ ታየኝ። አይኔን ወደታች ሰልከ ባለተረከዝ ጫማዋን አየወለወለች እንደነበር ገባኝ። በእጄ፣ በቀይ ክር ሃረግ የተጠለፈበት የአማማ መለኮት መሃረብ በከፊል አባራ ለብሶ...

22 የመጀርደሪያው ጫፍ

"አብርሃም !"

"አቤት"

"ስምህ ማነው ?" አለኝ ፊቴ የተቀመጠው ደማ ፖሊስ። ፊቱን ሰየው ማቋጨት ጀምሮ መሐል ላይ ሊደርስ ሊያቋጭ የፈለገው ዜማ የጠፋበት ጎረምሳ ይመስላል። ስሜን ጠርቶ 'ስምህ ማነው?' ሲለኝ ቢገርመኝም በትህትና ቱናገርኩ።

"አብረሃም"

"አ_ብ_ር_ሃ_ም" ፊደል እየቆጠረ ፃፈ።

"የአባትህ ስም" ነገርኩት - ጻፈ።

"አብረሃም ! ለምንድነው የሰው ባል ጭካኔ በተሞላበት መንገድ በሚዛን ስህን የፈነከትከው?" አለኝ። አጠያየቁ 'ባትመልስልኝም ግድ የለም' የሚመስል ስሜት ነበረበት።

"ሸረ ሰላበሳጨኝ ነው እንጂ እኔ ሰው ጋር ተሰዳድቤ እንኳን አላውቅም፤ እንኳን በጭካኔ" ዓረፍተ ነገሬ እየተወለጋገደ መለስኩ።

"እሱማ ታስታውቃለህ። ጨዋ ልጅ ነህ። ጨዋ ባትሆን ኖሮ ሰዠኑ ላይ የተቀመጠውን እንድ ኪሎ መመዘኛ ብረት ትተህ በሰሃኑ ብቻ አትፈነክተውም ነበር። ጎበዝ ! ራስህን መማዛትህ ትልቅ ነገር ነው። 'ራሱን የሚገዛ አገር ከሚገዛ ይበልጣል' ይባላል። ቢሆንም ግን አብረሃም ዋስ ትጠራለህ።"

"እሺ !" አልኩና ትዝ ሲለኝ የሚዋስ ሰው የለኝም።

"አንካ ደውልና ዋራ !" ብሎ ቅድም ወደ ማረፊያ ቤት ስገባ የተቀበለኝን ስልኬን ወደ ፊቴ ገፋልኝ።

ወደ አለምሮዬ የመጣችው ሂሉ ነበረች።; ግን ሀሳቡ በራሱ ሳቄን አመጣብኝና ተውኩት። ባሏን ፈንክቼ ሚስቱን ዋስ ሁነኝ ማለት በእርግጥ ያስቃል። ዝም ብዬ ዋስ የሚሆነኝ ሰው ሳወጣና ላወርድ ቆየሁና "ዋስ የለኝም !" አልኩት ለደጉ ፖሊስ።

"እንዴት ዋስ አይኖርህም? ከሰው አልተወለድክም...? ጓደኛ የለህም? ወይም ጎረቤት ?" አለ ፖሊሱ። እንዲህ ሲለኝ ዘመድም ጓደኛም የምለው ሰው እንደሌለኝ ትዝ አለኝና አንባዬ በዐይኔ

"ደህና እስቲ የአንድ ሰው ስም ንገረኝ!" አለ ለመፃፍ እየተመቻቸ።

"የአንድ ሰው ማለትን?"

"በቃ ዝም ብለህ የአንድ ሰው ስም ንገረኝ!" አለ።

"አበራ !" ማረፊያ ቢቷ ውስጥ 'አበራ አንበሳው !' የሚል ስም በተወለጋገደ የአጅ ጽሁፍ አይቼ ሰለነበር እፌ ላይ ድንገት መጣልኝ።

"የአባቱ ስም ማነው ?"

"አኔ ንጃ !"ተገርሞ አየኝና ፊገግ ብሎ አጉተመተመ።

"በቃ 'አበራ በለጠ' ብዬዋለሁ - ዋስህ ነው። አብረሃም አምንሃለሁ፤ ጥሩ ልጅ ነህ፤ ይሄ መቼም የፅለት ግጭት ነው። ከአሁን በኋላ እዛ ሱቅ አካባቢ ብትደርስ ግን ዋስህን እቀፊድደዋለሁ፤ ንግሬያለሁ!" አለ እየሳቀ።

እዚች ምድር ላይ ይኑር አይኑር በማይታወቅ ዋስ ከእስር የወጣሁ ሚስኪን ሰው። ቀበቶዬን ተቀብዬ ከታጠቅኩ በኋላ ወደ ቤቴ አዘገምኩ። ፖሊሱ ያሳየኝ እምነት በጣም ነው የገረመኝ። ለምን እንደሆነ ባላውቅም ሰው ከመሬት ተነስቶ ያምነኛል። ሌባ ብሆን መቼም ባንዴ ሃብታም ነበር የምሆነው፤ ለዎች እንዲያምኑህ አና እንዲዘናጉ ማድረግ ትልቁ የሌብነት ጥበብ ነውና።

ሰፈሬ ሰደርስ ወደ ሀሊና ሱቅ መንገድ ጀመርኩና ትዝ ሲለኝ ደንግጬ መንገዴን ቀየርኩ። ሱቁ አካባቢ እንዳልደርስ ማለጠንቀቂያ ተሰጥቶኛል። ወይኔ ከሁሉም ከሁሉም ሀሊናን ሳላይ መዋል እንዴት ያስጠላል?! ሀሊናን እንዳላይ በህግ ተከልክያለሁ። ያ ፖሊስ በሕግ አላስፈራራኝም፤ ሕጉን ነው አዕምሮዬ ውስጥ ተክሎ በፍቅር ያጠረው።

ሂሉ አስካሁን በዱቄት የተበከለ ጋውኗን ለብሳ ፊቷ በሚነድ ሻማ የሆነ ነገር እያደረገች ይሆናል፤

ወይም የለስላሳ ሳጥን ላይ ቆማ እንደ ነብር ሽንጧ ተመዛ የላይኞቹ መደርደሪያዎች ላይ ሳሙና እየደረደረች ይሆናል። ስትንጠራራ እኮ ስታምር! ሰማይ ላይ በተቀመጠ ገበታ በሚያማምሩ ጣቶቿ እግዜር ጋር ቼዝ የምትጫወት ነው የሚመስለኝ። ሂሱ የኔ ውበ ! የኔ ቆንጆ ! የማርማ ሚስት ! ሰው እንዴት ግርማን ያገባል በእግዚአብሔር...!

*** *** ***

ብቸኛ ነኝ ! ሁሉም ነገር የሰለቸኝ የሃያ ሰባት ዓመት ወጣት። ቤቴ አገባለሁ፤ አወጣለሁ፡ ፡ ሦስት ዓመት ሙሉ እዚህ ሰፈር ሰኖር የማውቃት ህሊናን ብቻ ነው። መንገዴ ላይ ሱቅ አላት፤ድምቅ ያለ ሱቅ። የሱቁ ድምቀት ህሊና ራሷ ሳትሆን አትቀርም።

ህሊና ጨዋ ሴት ነበረች። እኔም ጨዋ ልጅ ነበርኩኝ። የህሊና ባል ግን ጨዋ ስላልነበረ ሊያሳስተን ሞከረ። ይሄ አባላች ደሰ ይበለው፤ ተሳክቶለት ተሳሳትን። በዕርግጥ ስህተታችን ጣፋጭ ነበር።

ለሚስቱ ሱቅ ከፍቶ ወንድ ደንበኛ በመጣ ቁጥር ዐይኑን ማጉረጥረጥ ተገቢ ነው? ገበያተኛ በመጣ ቁጥር የሚስቱን ፈገግታ መለካት እና ማታ ማታ በልከ ፈገግ በይ እያለ መነትረክ እግዜር ይወደዋል? እሽ ይሄ ይሁን ግዴለም...ግን "አብረሃም የሚባል ልጅ እዚህ ሱቅ ለምን ይመጣል ለሞላ ሱቅ?!" ብሎ መጠየቅ ከአንድ ባለ ሱቅ ይጠበቃል? ...መንግስት ሳያዳላ ሕዝብ እንዲያገለግልበት በሰጠው ንግድ ፈቃድ አከሌ ይምጣ አከሌ ይሂድ ብሎ ሰው ይመርጣል? እሺ (ሂሂሂሂ...ሽረ ይሄስ ያሳፍራል) ግን ሚስቱ ጋር፤ ቆንጅዬ ሚስቱ ጋር እቅፍቅፍ ብሎ_ ከመተቃቀፍም አልፎ መርፌና ክር ሆነው ሌላ ዓለም ውስጥ ሲዋኙ ድንገት የማይቋረጥ ነገር አቋርጦ፤ "ለምንድን ነው አብረሃም ቲማቲም የሚገዛው? ማን ሊያበስልለት?" ብሎ ሚስቱን ይጠይቃል፤ እንዲህ ይደረጋል ?

ሂሱዬ ብስጭት ብላ "ራሱ ይሰራላ" ስትለው፤ "ራሱ እንደሚሰራ በምን አወቅሽ ?" ይባላል ? ለጥያቄና መልስ ይሄ ቦታው ነው ? ለዓቱስ ነው ?

ባሏ ቀልቡ አይወደኝም፤ አቀፈዋለሁ። እኔ ሱቁ በር ላይ ስቆም ዐይኔን ላለማየት የሚያየው ነገር የለም። የተደረደረውን ሳሙና፤ የተሰቀለውን ሙገ፡ የተሰጠፈውን ዳቦ ክልክል ነው የሚል ማስታወቂያ...ብቻ ማየት የቻለውን ሁሉ ፊቱን አጨፍግጎ ይቃኛል። እናቴን ሊፈነክተኝ ፈልጎ ደህና መፈንከቻ ያጣ ነው የሚመስለው። በዛ ላይ ሆነ ብሎ ህሊናን በወሬ ያጨናንቃታል። እንዳናወራ መከላከሉ እኮ ነው።

"አጃክስ አለቀ እንዴ ?" ይላታል፤

"ኧረ አለ!"

"ለሰላሳ ዘሬ አላወረድሽም ?"

"ግና ትላንት እኮ ነው ያወረድኩት !"

በቃ የማይቀጣጥረው ነገር የለም።

እንግዲህ ስገባና ስወጣ ሰላም የምላት ብቸኛ ሴት ባለ ሱቋ ሀሊና ነች። ሱቋ መንገዴ ላይ ስለሆነች አስቤዛዬም የሚሸመተው ከሷው ነው። ታዲያ ሀሊና ጥሩ ልጅ ስለሆነች ነው መሰል ከደንበኝነት ከፍ ያለ ቅርርብ ነው ያለን።

ዛሬም ልክ ደመወዝ እንደተቀበልኩ ሄድኩ፣ ባሷ የለም። ሁላታችንም ደሰ አለን።

"እንቱ!" ትለኛለች፣

በቃ ስሜን ጠርታኝ አታውቅም። 'እንቶ' ነው የምትለኝ። እውነቱን ለመናገር ሀሊና 'እንቶ' ስትለኝ ስሜን ያቀናጣችው ነው የሚመስለኝ። አብርሃም ሲቀናጣ 'እንቶ' ! በእኔ ጆሮ ብትሰሙት በጣም ይገጣጠማል !!

"ሰላም ሂዱ!" ባሷ ከሌለ ሂዱ ነው የምላት፣ በእርግጥ አንዳንዴ እሱም እያለ ያመልጠኛል።

"ምን ሆነህ ነው ዐይንህ የቦዘዘው?" ትላለች በትልልቅ ዐይኗ እያየችኝ። ዐይኖቿ ዐይኔን ይስሙኛል።

"ጸቢ ልከፍል ስለሆነ ይሆናላ !"

በዚህ ሁኔታ መቀለድ መቻሌ ግዴላችሁም ብርቱ ሰው ብሆን ነው!

"ሂሂሂሂሂሂሂ...ውይ አታስቀኝ ከምሬ ነው!" ትላለች፣ ሰቃ ከወጣላት በኋላ እኮ ነው። ከዛም የወሩ አዳዬን እንተሳሰባለን።

"ጸቢ ከልከል ነው!" ከሚለው ጽሑፍ ሰር ያስቀመጠችውን የጸቤ መጻፊያ ደብተር ታወጣና ቁልቁል በአስከርቢቶዋ እየጠቆመች "ካርድ የነዐዐ ብር...ግን ሙቶ ብር ካርድ ምን ያደርግልሃል? ወሬ እንኳን አታበዛ" ትላለች፣

"ዳቦ...

ዳቦ

ዳቦ ...ሰነፍ ስለሆንክ እኮ ነው ዳቦ የምትበላው ! ...ብቻ እንጀትህ እንዳይደርቅ ፤ ምናለ እንደ ወንዶቹ እንቁላል እንኳን ብትጠብስ ?..." ትቀጥላለች።

"...የተፈጨ ቡና...!

ሻይ ቅጠል...!

ኮካ !

እምቦ ውሃ ሂሂሂሂሂሂሂ አስኪ ለው ዳቦ እየበላ አምቦ ውሃ ሆሆ" ስትስቅ ደሰ ስለምትለኝ ገዘም ብዬ እያታለሁ፣ ሰታምር !

"እ...እ...እና አንድ ሊትሯን ውሃ በድምሩ...መቶ ለላሳ ሁለት ብር"

"እምሳ ብሩን ረስተሻል !" አላታለሁ::

"የምን ሃምሳ ብር?" ትለኛለች::

"አንድ ቀን ተበድሬሽ ለታከሲ አንኳ..."

"አላስታውስም"

"እኔ አስታውሳለሁ" አላትና ሁለት መቶ ብር አዘረጋላታለሁ:: አንዱን ብቻ አንስታ አንዱን እጇ ላይ ትተወዋለች::

"ብር አለህ ግን?" ትለኛለች፣ደግሞ ከልቧ መሆኑን ዐይኗ ያስታውቃል::

"ዛሬማ ሃብታም ነኝ"

"ያንተ ሀብታምነት እንደሁ ኢድሜው ሦስት ቀን ነው" ታየኛለች፣ በዐይኗ የነካችኝ ነው የሚመስለኝ::

እለምሮዬ ባለትዳር መሆኗን እንዳያምን ጣቷን ላለማየት አጥራለሁ:: የሆነች ለስላሳ ነገር ነች፣ አንጣቷን በዐይኔ ሰነካው ይለሰልሰኛል:: ባሏ ግርማ ሲያቅፋት የሚኮሰኩሳት ነው የሚመስለኝ፣ የሆነ ሰውነቷ የሚንደበደብ::

ሂሉን ሱቅ ውስጥ ቆማ ሳያት መደርደሪያው ሁሉ የተሞላው በፍቅር ይመስለኛል:: ማነሽ ሁሉንም በጅምላ ገዝቼዋለሁ፣ ከነመደርደሪያው፣ ከነሚዛኑ፣ ከነመዛኟ !!

በትልቅ ጥቁር ፌስታል ቋጥሮ አእንም አዛው ውስጥ መጨመር፣ ወደ ውጭ ማየት የለ፣ ወደ ውስጥ የሚመለከት የለ፣ አርፍ !

ኤጭጭ! ከኋላዬ ጥላው ሲከብደኝ ታወቀኝ...ግርማ መጣ...፤ ባሏ መጣ ! የተደገፍኩትን መደርደሪያ ከፍቶ ሲገባ ወድቄ ነበር::

"ይቅርታ ልገባ ነው አይባልም ?" ሂሉ በባሏ ብልግና ስትሳቀቅ ይታወቀኛል:: ይሄ ውሻ የሆነ ሰው፤...ቢቃ የሂሉም ፊት ኮስተር የእኔም ፊት ኮስተር !! መደርደሪያው ይንኳተትብኛል:: ማካሮኒ፤ ፓስታ፤ ሳሙና፣ ምንትስ...ያ ሁሉ ፍቅር አልም ! ይሄ ሰሐራ ባሏ ሲገባ ፍቅር ይተናል::

በለፈው ከስራ ወጥቼ ወደ ቤቴ አዘግማለሁ:: ድከም ብሎኝ ስለነበር ሂሉን ረስቻት ነበር:: ልከ በሱቋ ሳልፍ "አንተ" ብላ ጮኸች:: የሂሉን ድምፅ ሲሰሙ ድካም፣ ድንዛዜ ሁሉ ጠጠር አንደተወረወረበት የወፍ መንጋ 'እኔ' ከምባል ዛፋቸው ላይ ግርር ብለው ሲበሩ ታወቀኝ::ከንፈሬ ላላዘው ግራና ቀኝ ሸሸ፤ ፈገግ አልኩ:: እናም ወደ ሱቋ ሄደኩ፤ ከድካሜ ብዛት ደረጃውን ለወጣ ገድገድ ብዬ ነበር::

"እኔን!" አለች ሂሉ፤

ሱቁ ላይ ስደርስ ግርማ ተቀምጧል:: ድካሞቼ ሁሉ ተጠራርተው ድብርትን ጨምረው ሰፈሩብኝ፤"ሰላም ዋላችሁ!" አልኩ፤

"እግዚያብሄር ይመስገን!" አለች ሂሉ፣ እግዜር ቀኑን የሰጠው ላቧ ብቻ ይመስል:: ያ ጋግርታም ባሏ ዘጋኝ! ይዝጋው !

ምን እንደማወራ ጠፍቶብኝ እንዴ መደርደሪያው ላይ ያሉትን እቃዎች፣ እንዴ ሂሉን ሰቃኝ ቆየሁና..."ሳሙና ስጭኝ!" አልኩ:: ሂሉ ሳቋ መጥቷል፤ ድንገት እንደዘባረቅኩ አውቃለች:: ቢሆንም ከመጨረሻው መደርደሪያ ላይ ልታወርድ የለሰላሳ ሳጥኑን አስጠጋችና ጫማዋን አውልቃ ኩርሲዋ ላይ ቆመች:: አግሯ እንዴት ነው የሚያምረው ! ተረከዟ ነጣ ብሏል፤ ተንጠራራች፤ ተመዘዘ ሽንቧ ...!

"ሽንቧ የሚመስለው...የምንትስ ሃረግ..." አያልኩ በሃሳቤ ስዘፍን እና ምራቄን ስውጥ ቆይቼ ዞር ስል ግርማ ዐይኑ ቀልቶ እኔ ላይ አፍጥጧል:: "ነብር አየኝ በል!" አይነት ዛቻ ቀመስ ዕይታ...! የሚጮህ ዐይን ያየሁት ግርማ ላይ ነው:: ዐይኔን ከዚህ ፈጣጣ ላይ ነቅዬ በጥግ በኩል ስልክ የኮንደም ካርቶኑ ላይ አረፈ:: የግርማም ዐይን ዐይኔን ተከትሎ ይሁን ወይም የዐይኑ አግር ፕሎት አዛው ላይ አረፈ፤ ወይም ያረፈ መሰለኝ::

ሂሉ የቆመችበት ኩርሲ ነቅነቅ ሲል "እኔን!" ብዬ በድንገጤ ጮህኩ፤ አደነጋገጤ ለራሴም ገርሞኛል:: ውሃ ጠንብ ባሏ ምንም ያልመሰለሙን እኔን ምን ቆርጦኝ ነው የደነገጥኩት? ምን አስበረገገኝ? "የምጣዱ ሳለ የእንቅቡ ተንጣጣ" አሉ! እንደውም የግርማ አስተያየት 'ምነው በፈረጥሽ!' የሚል ያስመሰልበታል::

ሳሙናዬን ተቀብዬ ወደ ቤቴ አዘገምኩ:: በቀጣዩ ቀን ቅዳሜ ሂሉ እንባዋ ጠብ አስኪል እየሳቀች ሳሙናውን ገዝቼ ከሄድኩ በኋላ ከግርማ ጋር የተባባሉትን እንዲህ ስትል ነገረችኝ:: አወራሯ

ድራማ ነው የሚመስለኝ። ሂሱ ሲበዛ ነፃ ነች።

"አንተ !" በሳቅ ፍርስርስ አለች፤

"ምን ያስቅሻል?"

"እይውልህማ...ብታይ...ትላንት ሳሙና ስጭኝ ስትለኝ ሰጥቼህ (ረሽሮም ሳቅ)...ሰጥቼህ... ከሄድክ በኋላ ግርምሽ ብሰጭት ብሎ ሲነዘንዘኝ አላመሸ መሰለህ! ሆሆ!!"

"ምን አነዛነዘው ?"

ነገረችኝ፤ ልክ እኔ እንደወጣሁ ግርማ ሂሱን ጠየቃት፤

"...እኔ የምልሽ፣ አብረሃም 'ሳሙና ስጭኝ' ነው ያለሽ አይደለም እንዴ?"

"እዎ፣ እና እኔስ ሌላ ምን ሰጠሁት?"

"ምን እንደሰጠሽውማ እንችው ታውቂያለሽ"

"እንዴ! ግርምሽ ምን ማለትህ ነው?"

"የሳሙናውን ዓይነት አልተናገረም። እንዴት ዘለሽ አዛ ትንጠላጠያለሽ? አዚህ የገላ ሳሙና አለ፣ አዛጋ እጃክስ አለ፤ አ...ላርን ፊሳሽ ሳሙና አለ፤ ምን እንደፊለገ በምን አወቅሽ ?"

ሂሱ ደነገጠች። ቢሆንም ኮስተር ብላ መለሰችለት።

"ሁልጊዜ የሚወስደው ይሄንን ነዋ!"

"እስኪ አሱን የዱቤ ደብተር አቀብይኝ" አለ፤ አቀበለችው። የወሰድኩትን ዝርዝር እየና "የታሰ ሳሙና ወስዶ የሚያውቀው?" አላት በብስጭት።

"እየከፈለ ነው የሚወስደው"

"ያሁኑን መቼ ከፈለ ?"

"ኤጭ እንግዲህ አትጨቅጭቀኝ ! ወይ 'ሱቁን ዝጊና ቤት ተቀመጭ!' በለኝ" አለች ብስጩት ብላ፣

በዱቤ ደብተሩ ወርውሮ ሳታት። ከፀያፍ ስድብ ጋር "ሸርሙጣ!"

ይህን ስትነግረኝ ሁለታችንም ከልባችን ሳቅን። ስቃ ስቃ ሲወጣላት "እንተ ምናለብህ ላቭ

ነውና ሰውየ በሰላም ሰጥ ትላለህ፤ የሰው ትዳር እየበጠበጥክ" ልክ ስለሌላ ሰው ትዳር የምታወራ ነገር የምትመስለው::

በሷ ግርማ ከሌለ ወሬያችን መቆሚያ የለውም:: እንደማልወደው ታውቃለች:: እሱም እንደሚያውደኝ ታውቃለች:: ይሄ ነገር ሳያስቃት አይቀርም:: "ሰው ከመሬት ተነስቶ ይጠማመዳል ? ሂሂ !!" ትላለች:: ከዛም ልክ የመጀመሪያው ወሬ አካል አስኪመስለኝ ሌላ ርዕስ ውስጥ ትነቧለች::

"እንተ..ዶች ሽሚዝ አውንም አለች?" አለችኝ ድንጉት የለበስኳትን ሸሚዝ በግርምት እየተመለከተች::

"ላም የት ትሄዳለች ?"

"መጀመሪያ ቀን አዚህ ሱቅ ስትመጣ እችን ነበር የለበስከው...ፀጉርህ ጨብረር ብሎ እዚች ጋ ቆመህ..ወረፋ ነበር፤ ሰው ሁሉ ሊያለፈህ ገዝቶ ሊሄድ አንተ ዝም ብለህ ቆመህ...ሂሂሂሂ...ሌባ መስለሽኝ፤ ስልኬን አንስቼ መሳቢያዬ ውስጥ አስቀመጥኩት..ሃሃሃ...ከዛ በአንድ ዐይኔ አንተን አያየሁ፤ በአንድ ዐይኔ ደንበኞቼን ላስተናግድ ነበር::...ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ !" አወራሯ ያስቃል:: 'ሌባ ትመስላለህ' አያለች እንኳን ታስቀኛለች::...ደግሞ የሚገርመኝ አሳሳቋ 'ሳቁ እንኳ ዓይነት ግብዣ' ነው በቃ !

"...ግርምሽም ሌባ ነበር የምትመስለው...አሁንም ሐሳቡን የቀየረ አይመስለኝም:: ሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂ..." ሁለተኛዋን አረፍተ ነገር ስራዬ ብላ እኔን ለማብሸቅ የጨመረቻት ብትሆንም አያወቅኩም ተበሳጨሁ::

"እናትክን በይው አሺ!"

"ሃሃሃ እንተ ባለጌ ሲድ...ባሌ እኮ ነው! ሂሂሂሂሂሂሂ..."

"እኮ ባልሽን እናትክን በይው ! ...ማታ እቅፍ አድርገሽ ጉንጩን እየሳምሽ ፣ ሙቼም ይሄ ማቀፍም መሳምም አይገባው..'የኔ ቆንጆ አብርሃም እናትክን ብሎሃል አሽ !' በይው"

"ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ" የሚያልፈው ሰው አየዞረ እስኪመለከት ሳቋን ለቀቀችው፤ አየሰቀች እንባዋ ሲፈስ ገርሞኝ ነበር:: በቀጥታ እየሳቀች ማልቀስ መጀመሯን ያወቅኩት ወዲያው ነበር::

"እንዴት እንደመረረኝ!" አለችኝ:: ደነገጥኩ:: ብሶቷን ዘረገፈችው::

የሕረር ልጅ ናት:: ዘጠነኛ ክፍል እያለች ይሄ ያሁኑ ባሏ ግርማ ወታደር ሆኖ ሰፈራቸው የነበረ ካምፕ ውስጥ ይኖር ነበር:: ያኔ ተጫዋች፣ ወንዳወንድ፣ ቤቃ የሚፈቀር ሰው ነበር:: ለጓደኝነት ሊጠይቃት አላንገራገረችም:: "ይገርሽ ልጥፋ!" ሲላት አምናዋለች:: ካሰ እናት ያሳደጋትን አንድ

አባቷን ጣጥላ ይሄን መዶሻ ራስ ተከትላ ኤዲስ አበባ ገባች። እናቱ፣ አህቶቹ፣ ወንድሞቹ ሳይቀሩ አተከኗት። በጎብረት ያገቧት ይመስል በትዳሯ እየገቡ መፈትፈት ጀመሩ። ነፃ መሆኗን አለሌነት፣ ላጭን የሸርሙጥና ደውል አድርገው ዐይንሽን ላፈር አሏት፣ እንደ አዲሳባ ሰው በሯንም ጥርሷንም በልኩ መክፈት ያላደገባትን። ሚስኪን ! ልለማመድህ ብትለውም አልሆነላትም።

"ኤጭጭ እቦ እንደፈለጉ ይሁኑ!" ብላ ላጭንም ነፃነቷንም ተያያዘችው። ይባስ ብሎ ላቂ ማርከት እንዳልወደዳት "ላቅሽን አቁሚ!" አላትና አረፈው!! ብዙ ባሎች የባል ድንበሩ የት ድረስ እንደሆነ አያውቁም። ትንሽ ባሎች ደግሞ ድንበራቸው ላይ ላይደርሱ ይቆማሉ።

እባቷ እሷን ፍለጋ ተንከራትቶ ተንከራትቶ ሲሞት አፈር አላለበሰችውም። የሐረር ሰው ውሉ ይግባ አልቅሶ ቀበረው። በምድር ላይ የነበራት አንድ መሸሻ ዋሻ ተደፈነ። አሁን ግርማ መድረሻ የሌላት ከንቷ የተሰበረ ወፍ አደረጋት። "በየመንገዱ ስታገጭ ነው ያገኘሁሽ" አላት ፤ እንደ ሚስት ላይሆን እንደ ሰራተኛ ክፍ ዝቅ አድርጎ ያዝዛት ጀመረ። ያኔ ካስቀመጠባት መንበር ጎትቶ አወረዳት። ለሴት ልጅ ትልቁ ከብሯ ቤተሰቧ መሆኑን አመነች። ለምን አፈር ጠርጎ የሚተኛ ደሃ አይሆንም ቤተሰብ አለኝታ ነው ! ፍቅር ይወጣል፣ ይጠልቃል። አም ! የሰው ፍቅር እንዲ ፀሐይ ምሰራቅና ምዕራብ አለው። እየጣፈጠ ወጥቶ፣ እያቃጠለ ይጠልቃል! ቤተሰብ ግን ሰማይ ነው። የሕይወት ፀሐይና ጨረቃ ሲፈራረቅ የማይቀያየር፣ የማይጠልቅ፣ የማይጠቀለል ቦታውንም የማይቀይር ሰፊ ሰማይ ማለት ቤተሰብ ነው። ሂሱ ቤተሰብ የሉትም። ሰማይ የሰም። ቀጥ ለትል አና ነው - ባዶ ነው ! ኮክብ የሰም፣ ጨረቃ የለችም፣ ፀሐይም የለችም። ሰማይ በሌለበት ምንም የለም። እግዜር የት ይሆን መቀመጫው ? የት ሆኖ ይሆን ይህን ጉድ የሚመለከተው?!

የአዲስ አበባ ኑሮ አንገሽግሻት። ለምሬቷ ጣዕም ኮሶ የጨመረው ባሏ ነው። "ታምናለህ... ከሳመኝ ሰንት ጊዜው !" አለችኝ። "ግን አወደዋለሁ ! ሰድቡ፣ ማቃለሉ አያቃጠለኝ አንኳን አወደዋለሁ !"

"ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ አንተ አስለፈለፍከኝ !" አለችና ላጭን ለቀቀችው። የኔ ሚስኪን !!

ባለፈው ሐሙስ ደግሞ ሂሱ ወደኔ ጠጋ ብላ ፊት ለፊቴ ቆመች።መሐላችን ላይ ሚዛኑ አለ። ራቷ ልክ አልነበረም። ቶሎ አንድሄድላት መፈለጓ በግልፅ ያስታውቃል።

አንድ ትንሽ ልጅ መጥቶ "ሳሙና ስሜኝ ! ቢጫውን" አላት፤

"የለም !" አለች፤ ግን ፊት ለፊት ተደርድሮ ነበር።

ሌላ ሴት መጣችና "ስኳር ስጭኝ ሕሊና" አለቻት።

"የለም !" ፊት ለፊት ኩንታል ስኳር ተቀምጧል። ዝርሞኝ ጠየቅኳት።

"ሂሂሂ...እንተ ካልሄድከልኝ በስተቀር ምንም ነገር አልሸጥም ዛሬ" እየቀለደች መስሎኝ ነበር።

"ማሪያምን !" ስትለኝ የላጥኖ ቦርሳዬን አንስቼ፣ "በይ ቻው !" አልኳት።

"ቻው አብርሽ !" አለችኝ በቅሬታ ፈገግታ። "አብርሽ" ብላኝ አታውቅም፤ ግራ ገባኝ።

በቅጣቱ ቀን ሂሉ የለችም ነበር፤ ባሷ ተገትሯል።

"ለለም ማርማ"

"ምን ልስጥህ?" አለኝ ኮስተር ብሎ፤

"ክዚ"

"ለምን"

"እቪ ቀዚቃዛ ስፕራይት አድርገው"

"ለምን"

"እንጂን ውሃ ስጠኝ እቪ !" ውሃውን ሊሰጠኝ ዘወር ሲል ፊት ለፊት ሰማያዊ መደብ ላይ በነጭ የተጻፈ ማስታወቂያ መለጠፉን ተመለከትኩ። "የኔ ብጤና ዱቤ ፈላጊ አማዜር ይሰጥልን" ይላል። የብልግና ጥግ !! ሂሉዬ ይሄን ለመጋረድ ነበር ትላንት ፊቴ እንደ ጨው አምድ ተጥሬ የነበረው።

"ይሄን ብትነጥይ እገነጥልሻለሁ" ብሎ ፎከረባት። ማርማ እንደሰጠፈው ቆይቶ ሰማሁ። እኔን ሊማኝ! ለማለት ፒያሳ ሂዶ ማስታወቂያ ያጽፉል !?...ጓጉንቸር!!

ሀሊና ከሰዓት ኢቷን በስካርቭ ሸፍና ቆማ አገኘኋት።

"ምነው ሂሉ?"

"ትንሽ ጥርሴን አሞኝ !" ፊቷ ሞቶ ነበር። ዐይኖቿ ባዶ ቀፎ፤ እንድ የሕይወት ምዕራፍ በሆነ ምክንያት የተዘጋ አይነት። ሀሊና የትላንቷ አልነበረችም። ባላወቅኩት ምክንያት ተቆጣሁ።

"እሰኪ ስካርቭሽን አንሺው" አልኳት።

"ሂድ ቤቃ አብርሽ !" ብላ እንባዋ ተዘረገፈ። ከዛ በኋላ ሀሊናን ለአንድ ሳምንት አላየኋትም። ለውለት ለሦስት...ለሰድስት ወር !!

ለአንድ ሳምንት በኋላ ወደ ሱቁ ስሄድ ማርማ ከአንዲት የማልወዳት ሴት ጋር ቆሞ እያወራ ነበር። በንቀት እያየኝ፤ "አሁን ደግሞ ምን ቀረህ? ከሚስቴ ጋር አጣላኸን !" አለኝ። ዞር ብዬ ሴላ ሰው መኖሩን ተመለከትኩ፤ እኔን አልመሰለኝም ነበር።

"እስቲ ነው ባክህ ምን ታስመስላለህ!" አለኝ እያመናጨቀ። አንዲት የሀሊናን እግር መጡጣት ተከትላ ማርማን እንደ ሞልፊት ለመንጠቅ ያሰበች የምትመስል ማዲያታም ሴት "ሆሆ...የልብን ስርቆ እንደገና ዐይንን በጨው አጥቦ መምጣት አለ እንዴ?" አለች። ይህቺ ሴት ካሁንም በፊት እኔና ሀሊናን ስትመለከት ሀይኗ ደም የሚለብስ፤ በተሳሳቅን ቁጥር በርሷ እየመሰላት የምትመናቀር፤

ለማርማም ነገር የምታመላልስ ነገረኛ ነበረች።

"በሰላም ነው?" አልኩት።

"ወደዛ ሂድ ባክህ ! ሁለተኛ ሱቄ በር እንዳትደርስ። አዚህ አካባቢ ባይህ ጥርስህን ነው የማራግፈው!" አለ አያመናጨቀኝ። አሁን የኔፎርሙ ብቻ ሲቀር ወታደርነቱ ተመለሰበት። አብራው ያለችው ሴት "ማርምዬ በአመቤቴ ተረጋጋ ! የማይረባ ሰው ጋር አትጋጭ ! እጅህ ላይ አንድ ነገር ይሆንብሃል !" አለች።

እንዲህ ስትለው ጭራሽ ለያዥ ለገናዥ አስቸግሮ ቁጭ አለ። አውነቱን ለመናገር ማርማንም ሆነ ሴትዮዋን ከቁም ነገር አልፃፍኳቸውም። እንደው ነገሩ ገረመኝ እንጂ !

"አንተ ልከስከስ የሸርሙጣ ልጅ !" ብሎኝ ቁጭ ! ቀኝ እጁን ጌታ ይባርከው !! ከቁጥጥሬ ውጭ ተወንጭፎ ግርማ ጉንጭ ላይ በብርሃን ፍጥነት ሲያርፍ ከመደርደሪያው ስር ተንገዳግዶ ወደቀና ወዲያው አፈፍ ብሎ ተነሳ። ፊት ለፊቴ የነበረውን የሚዛን ሰሀን አነሳሁት። በአንድ በኩል አንድ ኪሎ ግራም ብረት ነበር። እኔ ግን ሰሀኑን እንስቼ በቀጥታ ግርማ ማንባር ላይ በጠርዙ በኩል አሳረፍኩት። ባባቴ ወንድ ነኝ።

አልወጣልኝም። አሪታዋን የምታቀልጠውን አቃጣሪ በጥፊ አቃጠልኳት! ከዛ አገር ምድሩ ተሰብስቦ ገላጋይ ሆነ። ግርማ ደሙን እያዘራ ይፎክራል። ወደፊት "ደሜን አፍስሼ ባቆምኩት ሱቅ" አያለ ታሪክ ያዛባ ይሆናል፤ ይሄ የማይረባ ! ታሰርኩ። እናም ደግ ፖሊስ ገጥሞኝ ተፈታሁ፤ "ሂሉ ጋ እንዳትደርስ!" ብባልም ከዛ በኋላ አሷም ራሷ እንደጠፋች ሰማሁ። ስልክ እንኳን አልነበራትም - ሂሉ። ከዛ ሰፈር ቤት የቀየርኩበት ምክንያት ያንን የመቃበር ቦታ የመሰለ ሱቅ ላለማየት ነበር።

አንድ ምሽት ከስድስት ወር ይሁን ሰባት ወር በኋላ ሰልኪ ሲጮህ አነሳሁት።

"እንቲ!"

ዝም...! ደንግጬ ነበር።

"አብርሽ !"

"ሂሉ !"

"ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ...ትኝትህ ነው ? እንቅልፋም !" ልክ ትላንት የተገናኘን ነበር የሚመስለው አነጋገሯ። ልታገኘኝ ቀጠረችኝ። ነገ ቅዳሜ ነው፤ እንኳን የሂሉ ቀጠሮ ተጨምሮበት !

ሂሉዬ አምሮባታል፤ አወራን።

ዋዛን ጊዜ ግርማ የሚያስጠላ ማስታወቂያ ለጥፎ እንዳትገነጥይ አለኝ፤ እኔ ግን በብስጭት ገንጥዬ አየለው በቦክስ ጥርሴን መታኝ። ሰማይ ምድሩ ነበር የዞረብኝ። ቤት በቦክስ ይመታል?...ያውም አፏን "ፊልምጫ የሚበቃኝ ሂሂሂሂ!" አለች። በጣቷ ንጭ ጥርሶቿ መሐል በማራ በኩል የተተካች ሰው ሰራሽ ጥርስ እያሳየችኝ። እነጋገሯ ልብ ይሰብር ነበር፤ አጋዥ የሌለው አቅመቢስ ሰው ዓይነት። "በቃ ስካርፍ አድርጌ ያየኸኝ ቀን ማታ በሚኒባስ ተሳፍሬ ወደ ሐረር...ሃሃሃሃሃሃሃሃ" ትንሽ እንደ መተከዝ አለች።

"እባቴ ሲሞት ሐረርም የሞተች መስሎኝ ነበር። ዓዋደኞቼ፣ የእባቴ ጓደኞች፣ ጎረቤቱ እንደ አዲስ ለቅሶ ተቀምጦ የአባቴን ሞት አዲስ አደረገው። 'አይዞሽ!' አሉኝ። ሰው ሁሉ የአባቴን ሞት ያፀናኑ መስሏቸው እኔን ከሞት ቀሰቀሱኝ። ሐረር ፍቅር ናት ! ሰው ሰው ይሸታሉ ሰዎቹ..." አንባዋና የደስታ ፈገግታዋ ተቀላቀለ። ሰው በሰው ሲረካ እንደዛን ቀን ተመልከቼ አላውቅም።

"ሂሉ እቤትትትት እንዴት ስወድሽ እንደነበር አኮ !" አልኳት።

"እንተ_ሊንድ ጥርስ አለብህ ላንተ የከፈልኩት ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ"

እየተንጠራራን ነበር ከሕይወት መደርደሪያ ላይ አሰከፊ ትላንታችንን የምናጥበበት ሳሙና ልናወርድ !!

"ሂሉ ባልሽን በሚዛን ፈነከትኩት አኮ..." አልኳት። አኒገሬ "ተበቀልኩልሽ" ይሁን፣ አልያም "ጅማና ነኝ" ማለት ለራሴም አልገባኝ !!

"ሃሃሃሃሃሃ ሰማሁ አኮ...! አቦ ጌታ ይባርከህ...! ሃሃሃሃሃ ባለጌ ነህ ግን_ገና ስማኒያችን አልተቀደድም አኮ ! አሁን የመጣሁት ለዛ ነው..."

እየተንጠራራን ነበር። ከአዲስ አበባ ሐረር፣ ከሐረር አዲስ አበባ መደርደሪያው ቢርቅም የቆምንበት የመፈላለግ ኩርሲ እንደምንም አያደራረሰን። ሂሉዬ አዲስ አበባ ዘመድ የላትም። እኔም ሐረር የማውቀው ሰው የለም። ግ...ን እኔንም ሐረር ! ሂሉንም አዲስ አበባ ደጋግሞ ያስረገጠን ጉዳይ ምንድን ነው ? "ከምር ግን ምንድን ነው ?" የሚሉ ጠያቂዎች ቢከሰቱ መልሳችን አንድ ነው። ምንድን ነው ? "ከምር ግን ምንድን ነው ?" የሚሉ ጠያቂዎች ቢከሰቱ መልሳችን አንድ ነው።

"...ለቦ አትነዝንዙና !!"

23 አለሁላት...!!

አናቴ ሁልጊዜ ሁለት እጆቿን ወደ ሰማይ ዘርግታ እግዜርን እንዲህ ትለዋለች፣
"አብርሽዬ የሚያዝለትን ሴት ሳታሳየኝ እንዳትገለኝ::"

.

.

አንባሁ !!
አናቴ ሁለት እጆቿን ወደ ሰማይ ዘርግታ እግዜርን እንዲህ አለችው፣

"ምነው ይሄንንስ ከሚያሳየኝ በገደለኝ..."

ሀና ምንተሰኖት ትባላለች የምኮራበት ሚስቴ:: እወዳታለሁ፣ አፈቅራታለሁ:: ክቡ ነገር በስፈሯ እንዲያልፍ አልፈልግም:: ሀኒዬ የአኔ ጥሩ ሱስ፣ 'ካላየኋት ያዛጋኛል' ስል ሰዎች አያምኑኝም፤ ሀኒ የእኔ ልብ፣ የጠላችው ጠላቴ ነው:: "ይሄ አባማ የሚባል ሰውዬ በቴሌቪዥን ያደረገው ንግግር አስጠላኝ" ብትለኝ፣ ሲ አይ ኤን ሳልፈራ፣ ኤፍ.ቢ.አይን ከቁብም ሳልቆጥረው አባማ ላይ የግድያ ሙከራ ባደርግ ደስታዬ ነው:: አንቅ አድርጌ አይኑን ለፍጥጦ፣ "ኧረ አብርሽ በእናትህ የዛሬን ማረኝ...ሁለተኛ በየትኛውም ሚዲያ ከመቅረቤ በፊት ንግግሬን ለሀና ምንተሰኖት አሳውቃታሰሁ... ካልፈቀደችልኝ አላደርገውም" ቢለኝ አልምረውም:: እማምላከን አልምረውም !!

ሀናዬ የኑብሴ ፍራሽ...ላያት ድሎቴ ናት:: ሀና ካዘዘችኝ...እቤት ፍጥነቴ ፤ ገና ልትናገር ስትጀምር እኔ ሮጫለሁ:: አልጋ ላይ ጋደም ብላ ቴሌቪዥን እያየች እኔ ቆንጆ ቡና እያፈላሁላት...የሆነ ነገር ብትፈልግ...ልትናገር ስትጀምረው ነገሩን አምጥቼዋለሁ :: ለምን ትጨርሰዋለች...ቃሏ ፍቅር ነው...ፈደሎቿ እንደ ረሀብ ቀን እህል ያላሉኛል::

"አብርሽ..." ስትለኝ 'በቦታህ!' እንዳሉት ሯጭ እዘጋጃለሁ:: ወደ መሻቷ ተፈትልኬ በምደር ላይ ያሉ ወንዶች ሁሉ የሚሰቶቻቸውን ፍላጎት ካሟሉበት ሰዓት የተሻለውን ለማስመዝገብ::

'ድ' ብላ ስትጀምር ፈትለክ ብዬ ድስት...ድራፍት...ደንች...ድልህ...ድፍድፍ (ከአማማ ፈጠኑ ቤት)...ድመት...ድንጋይ ...ድራማ (በሲዲ) ይዤላት እያለከለኩ ከተፍ ሰል፣ "ውይ አብርሽዬ...በቲቪ ድሮ አይቼ 'ድቡን እየው' ልልህ ነበር አኮ" ትለኛለች በፍቅር ዓይን እያየችኝ...!! አይከፋኝም፣ ለምን አከፋለሁ:: እንደገና ድብ ብየችና 'ድ' ብላ ስትጀምር፣ አሁን ባመጣኋቸው ነገሮች ላይ ድብ ጨምሬ ባመጣሁላት...የእኔ ሀኒ...መከሲት ብያታለሁ:: እሷ ናት ቀኝም ግራም ጎኔ::

ሀኖን እናቴ አትወዳትም:: "እንዳች አስነከታው ነው ልጄን እቺ የሰው ጉድ!" ትላታለች:: አባቴማ ኖ ሲያያት የእናቱ፣ የአባቱ፣ የሁለት አህቶቹና የአንድ አህቱ ገዳይ ነው የምትመስለው፣ አቤት ሲጠላት:: በወሬ ወሬ "መንገድ ላይ አጠረሃም እና..." ሲሉት፣ "በቃ !" ብሎ ይጮሀል:: "አጠርሃም ካላችሁ አይበቃም...እናን ምን አመጣው?" ይላል:: ያውቃል ማንም ጋር እንደማልታይ፣ ሀኒ ጋር ነኝ ቤት ውስጥ - የምትበላውን እየሰራሁላት:: ሀኒ ጋር ነኝ በመንገድ - ቦርሳዋን ይዤላት፣ ጫንጥላዋን ይዤላት፣ ሰቃ ከገዛን አስቤዛም ቢሆን እኔ ይዤላት...ሀኒ ጋር ነኝ የትም !!

ሀኒን አህቴ አትወዳትም:: ከዘመናዊ ጓደኞቿ ጋር ሆና ከሩቅ ካየችኝ በሬ እንዳሯሯጠው ሰው መንገድ አሳብራ የጓደኞቿን እጅ አየጎተተች ትሸሻለች:: "ወንድሜ በሬ እገባ" እያለች ነው የምታወራው አሉ !

ወንድሜ ሀናን አይወዳትም:: "ለስንት ሰንጠብቅህ እዚህች አዚፋ ጋር ትወዛፋለህ" ይለኛል፣ አዚፋ ምን እንደሆነ አላውቅም:: ግዴለም ሀኒዬ 'እዚፋ' ከሆነች፣ አዚፋ ይባረክ !! ስድብ ሰውን ካረከሰው፣ ሰው ስድቡን ስለምን አያከብረውም? ሀኒዬ እዚፋን አከበረች...አወዳታለሁ::

ሀኒ ቆንጆ አይደለችም:: የኔ ቆንጆ፣ ቆንጆ አይደለችም:: "ኪንኪ ፀጉሯ ጠዋት ስትነሳ ያስፈራል" ይሉሉ፣ አዎ አውነት ነው:: "አፍንጫዋ በአይኗና በላይኛው ከንፈሯ መካከል ያለ ሁለት የሽንቁር ኮረብ ነው" አያሉ ያሚታል...አውነት ነው !!

ከንፈሯ ወጣ ወጣ ባሉ ጥርሶቿ (በገጣጣ ነው እነሱ የሚሉት) ከርሰቱ ተገፍቷል:: በዛ ላይ ብትስቅ ዙሮ ማጅራቷ ላይ ይዘያየራል ይላሉ:: አዎ አውነት ነው !!

"የጣቶቿ መዶልዶም ከዘጠኝ ዓመቷ አስከ አስራ ዘጠኝ ዓመቷ ነ0000000000000000000000 ከንቃል ገብስ ሳታቋርጥ የወቀጠች ያስመስላታል" ቢሉም (ተጋነነ አንጂ) አውነት ነው !! "እግሯ ከየትኛውም ሜማ ጋር አንዲጣላ ተደርጎ ነው የተፈጠረው" ያሉትም አልዋሹም::

በዚህ ሁሉ መናቅ፣ በዚህ ሁሉ መገፋት ተገፍታ እኔ የምባል ጥግ ላይ ደረሰች - የሀኒዬ ዓለም መጨረሻ::የት ትሂድላቸው? አለሁላት ወንድሟ ነኝ:: ፍቅረኛዋ ነኝ::ባሏም ነኝ!! አላፍርባትም:: አኮራባታለሁ !! ሀኒዬ የኔ ናት:: ማነው እኔን አልፎ የሚዘልፋት ወንድ ?! የኤሌክትሪክ አጥሯ ጠባቂ ውሻዋ ነኝ:: ከአግሯ ሰር የማልጠፋ:: ባለቤቱ ያላከበረው አምሌ፣ ወላ መልኩ ወላ ዘመናዊነቱ አያስከብረውም:: አንዱ የወረወራቸው አይደሉ ሌላኛው መኪና ላይ የሚኮፈሱት!

የተናቁ አምሌዎች !! ሀኒዬን አከብራታለሁ !! እግዜር ያውቃል ልቤን !!

"ጥርስሽ አያምርም" ቢሏት ከሳቅ ተጣላችላቸው:: ሰው ፊት አትስቅም ሀኒ:: የመጻፍ መብታችን፣ የመሰለፍ መብታችን ተነካ የሚሉ የአገሬ ልጆች፣ የሀኒዬን የመሳቅ መብት በአደባባይ ነጠቁ:: እስካሁን ሻይ ቡና ለማለት ክፍቴሪያ መግባት ያስፈራታል:: ራሷ ቤት ውስጥ ስትቀመጥ እንኳን አግሮቿን ሶፋ ስር ልትደብቅ ይከጅላታል:: በመንገድ ዳር ዘለፋ መሳቀቅን ሸልመዋታል:: ሰው ለሰላምታ ስትጨብጥ ትሳቀቃለች:: የመዳፏን ሻካራነት በየጭብጨባው የሚጮኽ አዋጅ አድርገው ልቧ ውስጥ ተከለውባት::

ሀኒዬን "ቆንጆ ካልሆንሽ ሰው ከመሆን መንበር ተንኮታኩተሻል" ብለዋታልና ቆንጆዎች አምላክ ይመስሏታል:: የሴት ልጅ የክብር ጥጉ በየሆቴሉ ወንበር ተጎትቶላት መቀመጧ ነውን ? በአደባባይ መታቀፍስ የፍቅር አሜኃ ሆኖ የታወጀው መቼ ነው ? እየተውረገረጉ የወንድ ጭብጨባ ያደነቆራቸው ሀኒዬን ቃል ሳያወጡ በድርጊት ቀበሯት::

እነሆ ለእንዲት ደሀ...ለእንዲት መልከ ጥፉ ደሀ ተልኬ የምታስተናግድበት ተራ ሻይ ቤት ተከለትኩ፣ ያውም 'አዩኝ' ብሎ የሚቆሸሽ ነጭ ሸሚዝ ባማረ ጂንስ ሱሪ ለብሼ፣ ጥቁር መነፅሬን ሰክቼ አየተቆነንኩ በረንዳው ላይ ካሉት ወንበሮች በአንዱ ላይ ሰፈርኩ::

"ምን ልታዘዝ!" አለች ሀኒዬ እየተሸቆጠቆጠች:: ሳያት ላማትብ ቃጥቶኝ ነበር:: እግዜር ለውኃ የት ድረስ ውብ እንደሚያደርግ አውቃለሁ:: የት ድረስ መልከ ጥፉ እድርጎ እንደሚፈጥር አነሆ የአጁን ውጤት ፊቴ አቁሞ አሳየኝ:: "አቤት ችሎታው ምን ይሳነዋል!" አልኩ ::

ስራዬ በዛው ግድም ነበርና ደጋግሜ ሳያት ከቀን ወደቀን እየባሰ የሚሄድ ይሄ ጎደለው የማይባል ፍፁም የሆነ አስቀያሚነት እንዳሸከማት እየተገረምኩ ታዘብኩ:: ግና የገረመኝ፣ "አቤት ስታሸጠላ!" አያልኩ ሳያት መፈለጌ - ደንበኛ ሆንኩ::

"ምን ልታዘዝ!"

"ቡና"

"ምን ላምጣልህ?"

"ቡና"

"ሰላም! ምን ላምጣልህ?"

"ቡና"

"ቡና ነው ዛሬም!" (ፈገግ ለማለት አየሞከረች)

አዎ (በፈገግታ)

ከዛ ሳላዘት ቡና አመጣችልኝ...ቡና...ቡና...ቡና...ሰላምታ...ሀና ነው ስሚ፣ አንድ ቀን ጠየቅኳት... ነገረችኝ:: ስራ ከሌላት አጠገቤ ትመጣለች...እናወራለን...እንዴት ደስ እንደምትል:: ትልልቅ ጡቶቿን አልፎ ልቧ ይታያል - ንጹህ ነው !!

አንድ ቀን ከሃኔ የተቀመጡ ተስተናጋጆች "የሰው ጅብ!" ሲሏት ጆሮዬ ጥልቅ አለ - ያዘዝነው ዘግይቦን ብለው !! በመሰደቧ ሳይሆን እኔ ፊት በመሰደቧ የቅስሟ መስተዋት ክፍት እፍ በወረወረው የዘለፋ ጠጠር ሲንኮታኮት ፊቷ ላይ እንዴት አንጀት የሚበላ መሳቀቅ አየሁ:: ተሳዳቢዎቹ ጋር የነበረች አንዲት ሴትም ላንቃዋ አስኪላቀቅ ሳቁች:: አዘንኩ:: ለምን አዘንኩ - አንጎጃ !!

የውበት ጥርሳቸውን ሰለው ወንዱን ሊከረትፉት ከተማውን በቀን የወረሩት ሴቶች..ያውም የጉም ጅቦች ላይ አፋቸውን ለአድናቆት ሲበረግዱ የሚውሉ ዘመናዊ ተብዬ ቅርፊት የከተማ ወንዶች፣ እንዲት ደሀ ሚስኪን "የሰው ጅብ!" ብለው ተሳላቁ::ሰርታ በኖረች...በጅብ አፋቸው ጅብ አሏት::

በቀጣዩ ቀን እንገቷን ደፍታ፣ "ምን ልታዘዝ!" አለችኝ_በመከራ እንገቷን ብቅ ካደረገችበት ግንጉንት በዘለሉ ኩርኩም ወደ ትንሽነት መልሰዋት ከ ሀ አስጀመሯት::

"ስልክ አለሽ?" አልኳት፣

"ቡና" የምል መስሏት ልትመለስ ካለች በኋላ ያልኩትን ባለማመን፣

"እ" አለችኝ

"ስልክ ቁጥርሽን ስጪኝ!"

"የድርጅቱን ነው?" ስትል ጠየቀችኝ፣

"ኖ ! ያንቺን የራስሽን!"

ዝም አለች:: ቆይታ...ቆይታ

"09..." አለች

"09..." አልኳት ስልኬ ላይ እየየፍኩ

"እ...09..." ፈራች:: ማመን ከበዳት ፤ የኔ ሚስኪን! ጀግናው ወገኗ፣ ዘላፊ ወገኗ፣ ሃይማኖተኛ ሀዘቧ የገደላት...ሙት መቃብሯን ለመፈንቀል ሁሉም በየአቋሙ የወረወረባትን ድንጋይ፣ በአሸሙር አካፋው በለበጣ መጋፈያው የመለሰባትን የቀበር አፈር መፈንቀል ከበዳት::

"በዚህ ምልክት አድርጊልኝ አጠብቅሻለሁ" ብዬ ቁጥሬን ያመጣችው ደረሰኝ ላይ ፅፌ ሰጠኋት...

የሴት ከብር መሳም ነው ? መታቀፍ ነው ? ተስመው የተወረወሩ፣ ታቅፈው የተሸቀነጠሩ ይናንሩ፤ ሴት ልጅ ያመነችው ወንድ፣ 'ጣላት!' 'ተዋት!' ከሚል አሸሙር ሊታደጋት፣ ያኔ ነው ከብር በታዋ ላይ የምትቀመጠው:: ሴት ልጅ ስታፈቅር አድሜዋን ነው ሸርፋ የምትሰጠው::

ሽራርፈው ሽራርፈው ሴቶቹን ከአድሜያቸውም ከውበታቸውም አጣልተው ገሸሽ ያሉ ወንዶች ይሰሙ! እኔ ሽቅርቅሩ ሀናን ወደድኳት፣ መረተኛ አይደለሁም። ምንም ቢመጣ አልተዋትም። አዝኜ አይደለም። ሰማኋት፣ አይኔን ሳልወድ በግድ አስጨፈኑኝ።

መንገድ ላይ ሀኒዬን በኩራት ሳቅፋት፣ "የሚታቀፍ ጠፍቶ..." ይላሉ ሊታቀፉ ከየቤታቸው የወጡ አቅፍ ናፋቂዎች ሁሉ...

ስሰማት የሚያቅለሸልሻቸው አይናቸውን አዞሩ። ሀኒዬን አበድኩላት !! ሀና ሴት ናት !! እግዜር "ሴትነትን" መደበቂያ ቢያጣ ባልረባ ስጋ ጠቅልሎ ያኖረባት የከብር መዝገብ። ወንዶች አማር ላይ ሴትነትን ሲፈልጉ። ያማረ አፍንጫና ጥርስ ላይ ሴትነትን ሊያጠምዱ መንጠቆ ሲወረውሩ... እግዜር እንቁውን የት እንዳስቀመጠው ተመልከቱ።

አገባታለሁ...ሀናን "አገባታለሁ!" ያልኩ ቀን ሙሽ ባይነት ባይነት ወረደ። ሀና ራሷ ደነገጠች። ከዛ በፊት "እንዲሁ ከምቀር ፍቅር የሚባለውን ነገር ልሞክረው ቢያንስ ከትዝታው ጋር እኖራለሁ" ብላ አንጂ፣ ያገባኛል ብላ በምን ጠርጥራ(በጎላ እንደነገረችኝ)።

ተወራ በመንደሩ፣ "አብርሀም ቡጡቃ ሻይ ቤት ያለችውን 'ሆረር' ሊያገባ ነው..."

"አትቀልድ ባክህ"

"ማርያምን!"

"ከርሰቶስ ምስክሬ..."

"ወላሂ!"

"አበደ እንዴ?!መካሪ የለውም?"

ተቀባበሉ ወሬውን...

ለከብሩ...ለወኑ ሲመጓረጉ፣ "ሀኒን ላገባት ነው ፤ ዳሩኝ!" አልኩ ቤተሰቦቼን፣

"እያገባንም !!" አሉ።

'የራሳችሁ ጉዳይ!' ብያቸው ከሀኒ ጋር አብረን መኖር ጀመርን። ወላ ቤተሰብ፣ ወላ ጓደኛ ድራሹ ጠፋ። ሀኒዬን ወደድኳት። ከዚህ ሁሉ አሰቃቂ መልክ ጥፉነት መሀል የተረፉት ጡቶቿ መስውሰውኝ በስሜት እንዳይሆን የወደድኳት ብዬ ጀማው ሲንጫጫ ፈራሁ...ኧረ ሀቂቃው ፍቅር ነው !!

አራት ዓመት አሳት በሆነ ፍቅር ኖርን፣ ባለብኝ ወደድኳት። ይሄው እርጉዝ ናት፣ ያውም የስምንት ወር። ሀኒ እኔ ጋር ትስቃለች። እኔ ጋር አግሯን አትደብቅም። በነበረው ግዝፈት ላይ እርግዝና ያሳበጠው አስቀያሚ እግሯን ጉልበቴ ላይ አስቀምጬው ሳሸላት እንዴት ደስ እንደሚለኝ...

"አብርሽዬ"

"ደ_" አላታሰሁ

"አንትን ፈልጌ ነበር"

"ምን_" በቦታህ አብርሽ! ተዘጋጅ !

"ሽ_" ሂድ_ዲዲዲዲዲ ስጋ_ሰዕል (ከሰዓሊ ጓደኛዬ)_ስሰ ፒጃማ_ለንግ_ስራስር ነገር(ድንች፣ ቀይ ስር፣ ካሮት) ስእለት(ለማሪያም ሀኒ በሰላም ትገላገል ብዬ)_እያለከለኩ ስመለስ፣ "ውይ አብርሽዬ_'ስልኪን አቀብለኝ!' ለማለት ነበርኮ፣ ሮጥኩብኝ_ሃሃሃሃሃሃሃሃሃ"_እኔ ፊት ስትስቅ አትላቀቅም ሀኒዬ !!

24 ትንቢት...

በዚህች 'ቅድስት' ምድር

ትንቢት ነው መሰቡ፣ ትንቢት ነው ሰፈዱ

ትንቢት ነው ቡሀቃው፣ ትንቢት ነው ምጣዱ

ትንቢት ነው ሰሳቱ፣ ትንቢት ነው ኦመዱ...

በይበለሳል ትንቢት ለየተሸወዱ

ሚስኪን ድሰታቸውን ኦመድ ላይ የጣዱ

ሸሯቸው ሳይፈላ ከኦመድ ተዋሀዱ...

"አመዳም !! በትንቢታችን አሹፈህ ሞተኸል..." (ለጻፍኩት ግጥም የጓደኛዬ አስተያየት)

ሕፃን እንደነበርኩ አማርኛ አስተማሪያችን፣ "ሲታድግ ምን መሆን ትፈልጋለህ ?" ብለው ጠየቁኝ፣

"አሳድግም !!" አልኳቸው::

ንዝረቱ ሱዳን ድረስ በሚሰማ ኩርኩም አጋጨኝ:: ገጭ !! ቮሬክተር ስኬል' ምናምን ቁጥር የተመዘገበ ኩርኩም በሸመልስ ሐብቱ ትምህርት ቤት ሁለተኛ 'ዲ' ከፍል ስነፍ መደዳ ስለተኛው ዴስክ ላይ...ጥቁር ሰሌዳው እያደገ እያደገ ሄዶ ግድግዳውን የሸፈነው አስኪመስለኝ ሬት ለፊቴ የሚታየኝ ነገር ሁሉ ጨለማ ብቻ ሆነ:: የቀኔ ማብሪያ ማጥፊያ እናቴ ላይ ተገጥሞ በኩርኩም የሚበራና የሚጠፋ ዓይነት...'ገጭ' ሲል አልም !! ቀኑ ጨለመብኝ:: ማክሰኞ ቀን ነበር...ማክሰኞ ጨለመ_!!

ይሄ ኩርኩም የሚ'ገባው ለአማማ ዙሪያሽ ነበር...(የሰው ሀቅ ነው የወሲድኩት) አላቸው ናቸው መሰለኮታቸውን መሰተዋት ለወፍ በወረወርኩት ድንጋይ የሰበርኩባቸው ቀን መንደሩ ሁሉ አየሰማ! "ይሄ ያስታውቃል አያድግም" ያሉኝ:: ደግሞ የባህል መድኃኒት አዋቂ ናቸው:: ትንቢት ቃመስ የህኪም ትዕዛዝ ብናገር ይሄን የሚያክል ኩርኩም...?

በኩርኩም ሾኢታድግም!' ትንቢቱን አከሸፈውት ነው መሰል አደግኩ!! ፀረ ትንቢት ኩርኩም:: "ልጅህን በኩርኩም አጋፊጨው ፤ ሲያድግ ዶክተር ለመሆን ይመኛልና::"

ሦስተኛ ከፍል አባቴ፤ "ምን ለመሆን ትመኛለህ?" አለኝ::

ከኩርኩም ቀጠና ነፃ የሆነ ቦታ ላይ ቆሜ፤ 'ጠቅላይ ሚንስትር' አልኩ

"አዘዝዝዝ የኔ ልጅ! ጎሸሸሸሽ!" አለ በጣም ፈሞ:: ጩኸቱ አራት ኪሎ አስኪሰማ !!

"ምናለ ?" አለች እናቴ ጓዳ ሆና የአባቴን 'ጎሸሸሸ' እንጂ የእኔን የ'ጠቅላይ ሚንስትርነት' ምኞት አልሰማችም ነበር::

"ቆይ ራሱ ይንገርሽ... 'ስታድግ ምን ትሆናለህ በይው!'...አፈር ስሆንልሽ ፀሐይዬ ጠይቂው... ሃሃሃሃ ሂድ ንገራት!" አለና ወደ ጓዳው ገፋ አደረገኝ...ወደ ጓዳ እየተገፉ ጠቅላይ ሚንስትር ይኮን ይመስል...::

"ና አሉቲ አጉተ...ምን ታፍራለህ...ና ወደዚህ...ንገረኝ! ምንድነው የምትሆነው ስታድግ?" አለች 'ምኞቴ' እንዳያመልጣት እቃ ማንኳኳቷን አቁማ::

"ጠቅላይ ሚንስትር"

"ጎሸሸሸሸሸሸሸሸሸሽ...የኔ ልጅ!" እቅፍ አድርጋ ሳመችኝ:: ፊቷ ሁሉ በፈገግታ ተሞላ::

4ኛ ከፍል አንደኛ ወጣሁና የወላጆች ቀን ላይ፤ "ሲድግ ጠቅላይ ሚንስትር እሆናለሁ" አልኩ፣ ተጨበጨበልኝ:: የጮብጨባው ድምቀት ሀዝቡ ከተፈጠረ ጀምሮ ጠቅላይ ሚንስትር አይቶ የማያውቅ አስኪመስለኝ አስገረመኝ::

6ኛ ከፍል... "ምን መሆን ትፈልጋለህ ?" "ጠቅላይ ሚኒስትር" እጅግ በጣም ብልህ...ንበዝ...!!

ሾኛ ከፍል... "ምን መሆን ትፈልጋለህ ?" "ጠቅላይ ሚኒስትር" በጣም ንበዝ...!! (ብልሆን የት ጣሏት)

ዘኛ ክፍል... 'ምን መሆን ትፈልጋለህ ?' ሳልባል "ጠቅላይ ሚኒስትር እሆናለሁ" ብዬ ተናገርኩ... "ይሻላል አብርሽ...?" አለች አናቴ ቅር ብሏት::

12ኛ ክፍል... በወሬ ወሬ 'ጠቅላይ ሚንስትር' እንደምሆን ገለፅኩ... ዝበዝ የለ ፤ ሰነፍ የለ (ድምፀ ተአቅቦ)

ዩኒቨርስቲ ልገባ ውጤት መጣልኝ !! አናቷ ላይ 4 ነጥብ !! (አሳት እኮ ነኝ) ማታ አባቴ ጋር እያወራን አናቴ አራት እያቀራረበች ጥያቄው ተነሳ፤ "አ...ሽ ጎረምሳው! ታዲያ ምን ልታጠና ወሰንክ...?" አለኝ በኩራት እያየኝ::

"ያው ፖለቲካል ሳይንስ ነዋ አባባ" አልኩት ልክ እንደሱ ኮራ ብዬ::

"ምን ለመሆን ?" ተገርሞ ጠየቀኝ::

"ጠቅላይ ሚንስትር ነዋ !!" በመገረሙ ተገርሜ መለስኩለት::

እናቴ የያዘችውን ሰሀን በቁሟ ለቀቀችውና እንባ እየተናነቃት አባቴ ላይ ጮኸችበት፤ "ሲያብድ ዝም ብለህ ታየዋለህ እንዴ ? አስከዛሬ 'ልጅ ነው ንብስ ሲያውቅ ይሻለዋል' እያልን ዝም አልን..." አለች ሳግ እየተናነቃት ፤ እንባዋ በአይኗ ሞልቶ ነበር::

አባቴ ሲያስብ ቆየና...ረጋ ብሎ፤

"አብርሃም" አለኝ፤

"አቤት አባባ"

"አርፈህ ዶክተር ሁን !!"

ሕክምና ፋክልቲ ገባሁ:: የሁለተኛ ዓመት የሕክምና ተማሪ አስከምሆን ተስፋ አለኝ (ከተሞከረ)... እያልኩ ሳምስለስል 'አሳይመንቱም' ምኑም እየያዘኝ አልሞላልህ አለኝና 3...4...5...6...7.....አርፌ ዶክተር ሆንኩ !! ጨመርኩበት..."ዶክተር አብርሀም የመሀፀን እስፔሺያሊስት !!"

አገር ከመምራት ሰውን ከመነሻው ወደ መድረሻው መምራት ስራዬ ሆነ:: አገር አቅጣጫውን የሳተ ፖለቲካ ወልዳ ራሷም አቅጣጫዋን እንዳትስት ከመከላከል፤ አቅጣጫውን የሳተ ፅነሰ አንዲት ሚስኪን እናት አጥፍቶ ራሱም አንዳይጠፋ መከላከል ስራዬ ሆነ:: የተዘነፈ፤ መቀመጫው ያልተመቸው ኢኮኖሚ በጨነገፈ ቁጥር የሞንገፋውን ምክንያት ለሕዝብ ከማብራራት ስለጨነገፈ ፅንስ ሳይንሳዊ ምክንያት መደርደር ስራዬ ሆነ:: 'ብዙ አልራቅኩም...' አለዋለሁ ለራሴ::

ማን ያውቃል? በእጇ ካዋለድኳቸው አንዱ ጠቅላይ ሚንስትር ቢሆን...ናኖኖኖእለለለለለለ...

እኖናት ግና ተመልደው አጀ ላይ ሲያለቅሱ ከት ከት ብለው የሳቁብኝ ይመስለኛል..."አብርሽ... አቢሀ ምን ትሰራለህ...?" የሚሉ ዓይነት...ፈርምልን...አመዳም ሁሉ...!!

ማታ አዝማሪ ቤት ሄጀ እየጠጣሁ...አላለሁ ተቀበል...

ለያቸሀለኝ ወይ ይሀንን አንክፍ፣

ሲሪንጁን ወደሮ በአራት ኪሎ ሊያልፍ...

"የተማሩ አኮ ናቸው አቶ አብርሃም..." ሹክሹክታ...

"አሜሪካ...ናሳ...አጃቸውን ስሞ ሊቀጥራቸው ሲል፣ 'እንቢ...ህዝቤ...ብለው...ዶላር ከወገኔ አይበልጥም ብለው..." ይባልልኝ ጀመር በመሸተኞቹ...

አሜሪካን በስም ካልሆነ አላውቃትም !! ስንት የጨነገፈ የዲቪ ፎርም አለ መሳቢያዬ ውስጥ...

25 ዶክተር አሸብር

ቦምብ እንዲኖረኝ አፈልግ ነበር...!! አንደ እጅ ስልኬ በፈለግኩበት ሰዓት ቁልፎቹን የምጫነው የራሴ፣ የግሌ ቦምብ። ቦምብ ሲባል ግን ይሄ ሰባት ሰው አቁስሎ፣ ሁለት ሰው ገደለ...መስተቀት ሰባበረ፣ ግድግዳ ደረመሰ የሚባለው ዓይነት ቦንብ ሳይሆን በጅምላ ፊቴን ያጠቆረብንን፣ በጅምላ የበደለንን፣ በጅምላ የጎፋንን ሕዝብ በጅምላ ድራሹን የሚያጠፋ ኒውክሌር ቦምብ።

ቡምምምምምምምምም ሰፈራችንን የዶግ አመድ_አዲሳባን ከነስሟ ድራሿን የሚያጠፋ...

ወይ ለዲስ ለበባ ለወይ ሸገር ሆይ፣

ከተማ እንደጤዛ ለልም ይላል ወይ...

እየተባለ አስኪዘፈን ወላ ሙሾ አስኪወርድ ድረስ ቢቃ አዲስ አበባን ባዶ የሚያደርግ_እንጦጦን ሳይቀር ከሰሩ ነቅሎ ሀንድ ውቅያኖስ የሚጥል_"አዲሳባ የምትባል ከተማ አዚህ ነበረች። ምክንያቱ ባልታወቀ ፍንዳታ ጠፋች" እንዲሉ ባለታሪኮች፤ ምክንያት ነጋሪ ባለታሪክ አይተርፍማ።

ኒውክሌር ቦምብ እንዲኖረኝ አፈልግ ነበር። ሰዎች 'የግል ቤትና መኪና ቢኖረኝ' ብለው እንደሚመኙት ቦምብ ቢኖረኝ አያልኩ አመኝ ነበር። እዚህ መሐል አዲስ አበባ ሲፈነዳ ንዝረቱ የሩሲያን የበረዶ ግግር የሚሰነጣጥቅ... ካናዳ ሊታጨድ የደረሰውን የስንዴ አዝመራ የሚያረግፍ - ኒውክሌር ቦምብ።

ይሄ የተመኘሁት ቦምብ ቢኖረኝ ለመጥፎ ነገር አልጠቀምበትም። እንደ ቤት ዕቃ እንደ ፍሪጅ ቁምሳጥን በቀጥታ ወስጄ አቶ ቀለመ ወርቅ ግቢ ውስጥ መሐሉ ላይ አስቀምጠውና እንዲፈነዳ ቁልፉን እጫነዋለሁ። ቡምምምምምምምምም_ከእኛ ሰፈር ጀምሮ እፈር ነሽ ድንጋይ፣ ዛፍ ነሽ ተራራ ነሽ እየጠራረገ...ወደታች ወደ ሚዜሰሲኮ ሕንፃውን ሁሉ አመድ እያደረገ መንገዱን ሁሉ እየነለባበጠ ይወርድና ወደ ጦር ኃይሎች (አቶ ቀለመወርቅ አዛ ወንድም አላቸው)...ከዛ ወደ አየር ጤና፣ ዓለም ባንክ ('አዲስ ቤት እያስገነቡ ነው' ተብሏል ዓለም ባንክ አካባቢ)

በዚህ በኩል ደግሞ በመስቀል አደባባይ አድርጎ ካዛንችስ ነሽ ሀያ ሁለት፣ መገናኛ፣ መሪ፣ ሲ ኤም ሲን እየጠራረገ በኮተቤ በኩል ሲቪል ሰርቪስ (እዛ የአቶ ቀለመወርቅ ትልቁ ልጃቸው ይማራል...ይሄ ደነዝ ተምሮ ላይገባው የመንግሥት አህል ይፈጃል !) ፍንዳታው ወደ ቦሌ፣ ኤምፍሪያል፣ ገርጂም መሄድ አለበት በቃ...!! ማነው የሚከለከለኝ? የፈለግኩትን ማሰብ መብቴ ነው ! ማንም ሰው በሀሳቡ በአንድ ጀምበር ዓለምን ማጥፋት ይችላል - እንኳን ይህቺን ቢጢቃ ከላቅኝ የምትንጠራራ በውራጅ የምትንደላቀቅ አዲስ አበባን ቀርቶ::

አዲስ አበባ አቅፋ ደብቃ ጠጅ አያጠጣች ፍሟማ እያስቀረጠች 'እጉ' ብላ ባኖረችው፣ 'ቀለመወርቅ' በሚባል ሰው በላ ሞራቅ ሽሞማሌ ምክንያት አሸብር የሚባል ቂሙን የማይረሳ ጠላት አፍርታለች:: እኔ ነኝ አሸብር:: አዲስ አበባ አዲስነቷን ሳትወድ ተነጥቃ 'አዲስ ፍራሽ' ትሆናታለች የታባቷ !!

መብቴ ነው...በሀሳቤ ሕንፃዎቿን የፍርስራሽ ክምር ማድረግ_ታሪክ ማድረግ:: "እዚህ ላይ እኮ ቀለበት መንገድ ነበር" እያለ ድሮ የሚያውቃት አስኪያዝንላት(ለወሬ ነጋሪ የሚተርፍ ካለ) እመድ ማድረግ ይህቺን አመዳም፣ የሰው ፊት እያየች የምታዳላን ወረተኛ ከተማ ንፋስ ያየው ዱቄት ማድረግ:: ደግሞ ከሷም ብሶ አዱ ገነት...ኡኡቴ!!

እንዲህ እያልኩ ሳስብ ነፍሴ ትረካለች...ውስጤ ይረጋጋል:: አዲስ አበባን የተበቀልኳት ይመስለኛል...ደስ ይለኛል:· በቁጣ የጋለ ሰውነቴ ይቀዘቅዛል:: አዕምሮዬም ተረጋግቶ ወደ ማሰቡ ይመለሳል፤ አበቦች አበባ ሊመስሉኝ ይጀምራሉ:: ኢይኔም በጎ በጎውን ማየት ይጀምራል፣ ውርውር የሚለውን ሰው እና መኪና...ቆንጆዎቹን ሴቶች፣ ባጠቃላይ ሕዝቡን ማየት እጀምራለሁ... ግን ሁሉንም አጠላቸዋለሁ፣ አልወዳቸውም::

ጥላቻ የዘወትር ጸሎቴ ነው:: የጥፋት ምኞት አባታችን ሆይ የዕለት ድኃሜ !! ምነው "በደፈናው ጥላቻ" የሚል የእርጎ ዝንብ ቢንጋጋም አዲስ አበባን ከነሕዝቧ አልወዳትም:: ደግሞ "አዲስ... አዳዱ...አዱ ገነት" እያሉ ይመፃደቁላታል:: ኡኡቴ...አዱ ሲኦል !! የአፍሪካ ዋና ጀሀነም፣ የሰይጣን ዝርት መሰብሰቢያቸውን !!

አልወዳትም አዲስ አበባን:: አልወደውም ሕዝቡን:: እንዲህ ነበር የማስበው ሁልጊዜም:: ጧት የአዲስ አበባ ቅዳሴ ከአፅናፍ አስከ አፅናፍ ሲናኝ መስጊዶቿ በአዛን የማለዳ አየሯን ሲሞሉት፣ 'እናንተ ከቱ ሕዝቦች ደግሞ ነጋላችሁ፣ ለከፋት ተነሱ' የሚሉ ይመስለኝ ነበር:: ማታ ሕዝቡ በየበረንዳው ተኮልኩሎ ድራፍቱን ሲገለብጥ፣ ቢራውን ሲያጋባ ውስጡ የተከለውን ከፋት እንዳይደርቅበት ውኃ የሚያጠጣ ይመስለኝ ነበር:: ሕዝቡ ራሱ ስለራሱ ደግነት፣ ስለራሱ ቸርነት፣ ስለራሱ እንግዳ ተቀባይነትና አማኝነት ለራሱ ሲያወራ ይገርመኛል:: ለእኔ የአዲስ አበባ ህዝብ በዙ አይደለም፣ አንድ አምላል አንድ አካል ያለው፣ 'ቀለመወርቅ' የሚባል አንድ ሰው ነው !!

ክፍል ሁለት

አሸብር ነው ስሜ - ዶክተር አሸብር በአምላክ! 'በአምላክ' አባቴ አይደለም፣ እያቴም አይደለም፣ ማን እንደሆነ አላውቅም...እናቴም አታውቅም። ልክ ለእኔ አሸብር የሚል ስም እንደወጣልኝ 'አባት' ሰሚለውም ቃል በአምላክ የሚል ስም ወጣለት። የእኔን ስም ያወጣችው ብዙ ላሞቿ ያሏት ከፋትን እንደ ላም የምታረባ እና ባወራች ቁጥር ከንፈሯን በአውራ ጣቷና በአመልካች ጣቷ በቄንጥ የምትጠርግ ከፉ ባልቴት ነበረች።የአባቴን ስም ያወጣችልኝ ግን እናቴ ናት። እናቴ አፀደ ! አቲዬ ነው የምላት (በዚህች ምድር ላይ ስሟ ላይ 'ዮ' ጨምሬ አቆላምጬው የምጠራት ብቸኛ ሰው እኔ ልጇ አሸብር ብቻ ነበርኩ።)

እንደኛ ከፍል አሰከመዘገብ የአባት ስም አልነበረኝም። ልክ ትምህርት ቤት አቲዬ ወሰዳኝ ስመዘገብ ጉጉት የመሰለው መዝጋቢ እናቴን እያጣደፈ ጠየቃት። ድሪቶ ቀሚሷ ለዓይኑ ቀፎት እያመናጨቀ የእኔን ስም ጠየቃት። ዮኦት አስተያየቱን፣ እናቴን ዝቅ የሚያደርግ የፊቱን ገፅታ አይቼዋለሁ፣ በዚያው ድሪቶ ቀሚስ ስር በፍርሃት ተከልዬ...አይቼዋለሁ ቅንድብና ቅንድቡ አሰኪነካኩ ሲጠጋ እናቴ ላይ ሲኮሳተር። ሰራሷ ኑሮ የነሳመጣት እናቴን ሲገላምጣት አይቼዋለሁ።

አቲዬ አስመዘግባኝ ከፊቱ ዞር ስትል ፊቱን አጨፍግጎ መጥፎ ጠረን እንደሚያባርር ሰው በግራ እጁ እየሩን አያራገበ ሲያባርር አይቼዋለሁ። በአርግጥ አቲዬ አማማ የብርጓል ቤት አንኩሮ እያነኮረች ነበር። "ምነገባው ዛሬ ነው የሚያልቀው" ሲሏት ነው ብድግ ብላ ሳትሊቃለቅ የመጣችው። ቢሆንስ ልክ ቆሻሻ አንደሸተተው ሰው ሁሉ አንዲያየው አድርጎ እጁን ያራግባል ? የአማማ የብርጓል ቁጥር አንድ የጠላ ደንበኛ እንዳልሆነ ሁሉ፣ 'አሻሮ ሸተተኝ' ብሎ ያዙኝ ልቀቁኝ ይላል ? ኑበር አየው !! አንኳን ይህቺን አይቼ አንዲሁም ጥሏቻ ጥላቻ ይለናል። ያንን የውሻ ልጅ አስተማሪ እንደ ጠመድኩት ጡረታ ወጣ !! ደግሞኮ አያፍርም መንገድ ላይ ሲያገኘኝ "የእኔ ተማሪ ነው!" እያለ በኩራት ያወራል።

"ስም ?" አላት አቲዬን።

"የእኔን ነው ?" አለች እየፈራች። ፈሪ ነበረች እናቴ። ፈሪው የአዲስ አበባ ሕዝብ እንደያቅሙ ደሀ ማስፈራራትን ተክኖበታል። በትዕቢት ማከላፈቱ፣ በክፋት፣ ስድብና ዘለፋው እናቴን ፈሪ በርጋጊ አድርጓታል።

"እንቺ ነሽ አንደኛ ክፍል የምትመዘገቢው ?" አላት። አጠገባችን ያሉት ሁሉ ሳቁለት። አቲዬ ተሳቀቀች። ሰውነቷ ሽምቅቅ ሲል ቀሚሷን አንቄ ተሰምቶኛል፣ የመሸማቀቋ ንዝረት እንደ ታላቅ የመሬት ርዕደት ለእኔ ለልጇ ተሰምቶኛል። የሰዎቹ ሳቅ በፍርሀት ሲያንቀጠቅጣት ተሰምቶኛል፣ የአንድን ታዳጊ የፍቅር ሕንፃ የሚያፈርስ የመሬት መንቀጥቀጥ እናት የምትባል ሚስኪን ምድር ላይ ሲነሳ በሳቅ የሚያጅቡ ጅሎች ዙሪያችንን እያላዘኑ ነበር ::

ዋልድሽን ስም ንገሪኝ ሌትዮ!" አላት ከከበበው ሰው የተበረከተለትን ላቅ ካጣጣመ በኋላ::
ዮአሉ...አ..ሸብር....አሸብር ነው ስሙ" አለች ራሴን እያሻሸች::

"የአባት ስም ?"

"አባ...ት" ብላ ዝም አለች:: አባቴን መንደርተኛው ሁሉ ጠንቅቆ ያውቀዋል:: ወኔ ቢኖረው ኖር ሁሉም በጎብረት እንደ መፈከር በአንድ ላይ የአባቴን ስም ሊጠራው ይችል ነበር:: ግን እንደማያውቅ ሁሉ የአቲዬን አፍ በጉጉት ይመለከት ጀመረ::

"የአባቱ ስም ማነው?"

"ቀ..." መጨረስ አልቻለችም... 'ቀለመወርቅ!' ልትል ፈልጋ እንደነበር የገባኝ ካደግኩ በኋላ ነው፤ "የዛሬዋ ደግሞ የጉድ ናት የልጇም አባት የሚጠፋት..." ብሎ እንደጮኸ እንዲሰቁለት ሰዎቹን ለየ:: ያልደመቀ ሳቅ ተሳቀለት:: "በይ ወደዛ ሁኝ ስታሲታውሽ ትመለሻለሽ ተረኛ ቀጥል!" አለ አስከራብቶውን እያወናጨፈ:: እናቴ ከእንቅልፉ እንደባነነ ሰው፣ 'በአምላክ...በአምላክ ነው የአባቱ ስም' አለች:: ጎረቤቱ እርስ በእርሱ ተያያ፣ አንሾካሾከ:: መዘጋቢው ራሱን ግራና ቀኝ በብስጪት እያወዛወዘ መዘገበኝ:: ራሴ የሚያስወዘውዝ ስንት ጉዳይ አያለ፣ አቲዬ የእኔን አባት ስም አሰበች ብሎ ይሄን በአድሎዎ የተሞላ ራሱን ይንጣል:: ብዙ ሰዎች አንድን ነገር በቀላሉ ስለሚያገኙት ማንም ሰው በቀላሉ የሚያገኘው ይመስላቸዋል፤ ለምሳሌ አባት !

ከመዘገባ ስንመለስ አቲዬን ጠየቅኳት፣ "አባቴ ማነው?":: ደንግጣ አየችኝና አጥብቃ በያዘችኝ እጇ ወደ መንገዱ ዳር ሳብ አደረገችኝ:: ከሩቅ የሚመጣ እኛ ካለንበት ነገም የሚደርስ የማይመስል የሚጮኽ መኪና እንዳይገጨኝ:: አቲዬ መኪና መንገድ ላይ ስሄድ መኪናው በአካል ባይደርስ እንኳን ድምፁ የሚገጨኝ ነው የሚመስላት:: ትሳሳልኛለች !!

"እባትህማ በአምላክ ነው...በአምላክ" አለችኝ:: አነጋገሯ የገጠር ተፅእኖ ይሚነዋል:: 'በአምላክ' የሚለው ስም ለራሷም ሳይገርማት አልቀረም ::

"የት ነው ያለው?"

"ሁሉም ቦታ "

"የታለ ?" ብዬ ዞር ዞር አልኩ::

"አይታይም ...አሱ ግን እኔና አንተን ያየናል፣ ችግር ካጋጠመን ከየት መጣ ሳይባል ከተፍ ይላል"

"ከተፍ"

"አዎ ከተፍ ድንገት!" አለችኝ አቲዬ አልሀ በተሞላበት ድምፅ:: እንዲህ ስትለኝ አባቴ ፖሊስ መሰለኝ:: ብዙ ጊዜ ሰዎች ሲያወሩ "ፖሊስ ከተፍ ብሎ" ሲሉ አሰማ ነበር::

"አቲዬ!"

"ወይዬ!"

"አባቴ ልክ እንደ አማዚያቤር ነው?"

"አዎ ቁርጥ እንደ አማዚያብሄር።" በአባቴ ዝና ትንሽ ልቤ ይምላል።

"አቲዬ!"

"ወይ" ትንሽ ያለለቸኳት ትመስላለች።

"ከአማዚያብሔርና ከአባቴ ማን ይበልጣል ?"

"እኩል ናቸው...እኩል" ትለኛለች።

ክፍል ሦስት

አሸብር ብላ ስም ያወጣችልኝ ከቤታችን በላይ ብዙ ላም የምታረባ ቅሌታም ባልቴት ናት። ሰሙ ከእኔ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ከአቲዬም ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። እኔ ልወለድ አቲዬ ምጥ የተያዘች ቀን የዚህች አቃጣሪ ባልቴት የአሜሪካ ላም ያልታወቀ ነገር በልታ ሆዷ ተቆዝሮና አረፋ ደፍቃ እየጓጎረች ነበር አሉ።

የመንደሩ ሰው ከእኔ እናት ምጥ ይልቅ የዚህች የመንደራችን ሀብታም ላም ነፍስ አስጨንቆት አዋላጇ አልማዝ ሳትቀር ወደዛው ሂደው ነበርና አቲዬ ብቻዋን እኔን ተገላገለች። ብቻዋን !! የቀን ሥራ ያጠነከራት ብርቱ ሴት ባትሆን ኖሮ ሟች ነበረች። ብቻዋን ወለደችኝ !!

አንድ የአንሰሳት ሀኪም ተጠርቶ የእቃጣሪዋን ዘርፌ ላም ሆድ አስከሪብቶ በሚመስል ነገር ወግቶ ሲያስተነፍሰላትና ላሟ መጓጎሯን ሲታቆም መንደርተኛው አልልታውን አቀለጠው፤ አልልልልልልልልልል... አቲዬ አልልታውን ከሩቅ ሰምታለች። በዚህ መሀል አዋላጇ፤ "በሞትኩት ያሟ ሚስኪን ምን ደርሳ ይሆን?" ብላ ወደ ቤታችን ተጣደፈች። አቲዬን የተፈለቀቀ ወርቅ የመሰለ ወንድ ልጅ አቅፋ አገኘቻት። ያ የተፈለቀቀ ወርቅ እኔ ነበርኩ ያውም ገና በአሳት ሊፈተን የተዘጋጀ ወርቅ።

ዘርፌ የሚሏት ሀብታም ባለላም የላሟን ደኅንነት ሊጠይቃት ቤቷ ሲጎርፍ የዋለውን ቅቤ እንጓኝ ሁሉ ስታስተናግድ ውላ ወደ ማታ አስር አንጀራና ከከ ወጥ ይዛ ቤታችን መጣችና "መንደርተኛው በእኔ ላም በተሸበረበት ቀን ተወልዷልና 'አሸብር' ብዬዋለሁ" አለች። አሸብር ሆኜ ቀረሁ!! ነገ አድጌ ብረብሽ፤ 'ስምን መልዓክ ያወጣዋል' በሚል ሒሳብ 'መልዓክ ነኝ' ልትል። እች...ስድብ የማይገልፃት...!! ሰ 'አንቁታ' የደረሰች ሴትዮ ናት፣ 'አንች' የምላት ባትሰማኝም ስንቃት ደስ ስለሚለኝ ነው።

እንግዲህ አሸብር የተባልኩት እንዲት ተራ...አጋሰስ...የአሜሪካ ላም ባጋበለችው ፌሲታል ታምማ መንደርተኖውን ባሸበረችበት ቀን በመወለዴ ነው - ቢቃ !! ደግሞ ምኔም የማያሸብር እንደውም ቅበል ሲንከሻከሽ አቲዬ አሮጌ ቀሚስ ስር የምደበቅ ፈሪ ነበርኩ...ሰሜን ያወጣው መልዓክ አይደለም፤ ዘርፌ የምትባል ቀንዳም ሰይጣን ናት!!

አኦኮ የሚያበሳጨኝ...የዛን ጊዜ ዘመኑ ስላልሰለጠነ ነው ብዬ ውስጤ ከተመረዘበት ጥላቻ አንዳይሸር፣ ዛሬም ድረስ ጎረቤቶቻችን ስለዛ ጊዜ ሲያወሩ ፊታቸው የተቀመጠችውን አቲዬን... ብቻዋን መውሊዷን ከቁምነገር ሳይቆጥሩት ማለፋቸው ሳይበቃ፣ ከሞተች የቆየችውን የአሜሪካ ላም ደግነት፣ ባልዲ ሙሉ መታለብ...ፌሲታል በልታ ስታቃስት እንጀታቸው መንሰፍሰፉን እየተቀባበሉ ማውራታቸው ነው። ደግሞ የሚንሰፈሰፍ እንጀት አንዳለው ሰው።ጎማ እንጀት ሁሉ !!

እቤት ስጠላቸው! ልቤ ተሸንቁሮ የቋጠረው ፍቅር ፈሶ ያለቀበት ይመስል የተረፈኝ እፅናፍ የለሽ ጥላቻ ብቻ ነው። ማንንም አልወድም ሁሉንም እጠላለሁ !! ዘርፌ መልዓክ ብትሆን ጥሩ ነበር - ስሜን እንድሆን፤ ይሄን ከመሬት ተነስቶ የሚሸበርና የሚያሸብር አውራና ምንዝር ፣ረቤት ሁሉ እንዳሸብረው !! ወይ ነዶ...ሰሞላ ቦንብ ምናለ እንዲት ኒውክሌር በምብ ብትኖረኝ !! ለክፉ ነገር አልጠቀምባትም፣ ቀለመወርቅ ግቢ እወስድና ...!!

ክፍል ለራት

አቲዬ ከገጠር ወደ አዲስ አበባ ስትገባ ገና 14 ዓመት እንኳን አላምሮ አልሞላትም ነበር። ገጠር የሚኖሩ ቤተሰቦቿ ምናምኒት የሌላቸው ያጡ የነጡ ድሆች ስለነበሩ ኾነ በልጅነቷ ነው ልፋት ፅጣ ፋንታዋ የሆነው - ገጠር ስልችት አላት። ባል አልነበረም የስደቷ መነሻ። ያላቻ ጋብቻ ምንትስ ብላ አልነበረም ወደ ከተማ መኮብለሏ። 'የከተማ ሰው ከድህነት የሚያላቅቅ ዓመድሽን የሚያራግፍ ደግ ነው' ብለዋት እንጂ ባል ሽሽት አልነበረም።

ከተሜው ያላቻ ጋብቻ እያለ የሚወተውተው ሲያስመስል እኮ ነው። በሀብት፣ በዘር፣ በእምነት ሉቻ በማሳደድ ሰብ ስለተለከፈ፣ የመነፋፈልና የማግለል ንቅዘቱ ነው የሚያስለፈልፈው። ተራራ ተሻግሮ የሚጮኸው ከተሜ ስንት የነቀዘ ባህል፣ የገማ ዓመል ጉያው ውስጥ ሸጉቧል። አሱን ብሎ የመብት ተከራካሪ፣ አሱን ብሎ ታዳጊ። 'ምን በወጣሽ ካለ አድሜሽ ማግቦትሽ' እያለ የገጠሯን ሴት በአዞ እንባ ሙሾ የሚያስወርድ ከተሜ በየጓዳው ከከፉ ባል ይከፋል።

የልጅነት አግሮቿ ወደ አዲስ አበባ መሯት። ዘርፌ የምትባል ባለ ብዙ ላም ሴት በደህ መንደር 'ከአኔ ወዲያ ሀብታም ላሳር' የምትል ከብረ ቢስ ባልቴት ላይ ሰዎች አምጥተው ጣሏት። ሴትዮዋ ብዙ የአሜሪካ ላሞች ስለነበሯት አቲዬን በሰራተኝነት ቀጠረቻት።

ገጠር ትታው የመጣችው አዛባ መዛቅና ላም ማለብ እዚህም መህል አዲሳባ ጠበቃት:: ሳቁ እየመሰለው ይሮጣል አንጂ አጣ ፋንታውን በመሸሽ አያመልጠውም:: እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል ብሂል ጋር ስንተላለፍ አጣ ፋንታችንም አብሮን አያለፈ ከፊታችን ይጠብቀናል:: እንዲያ ነው አቲዬን የገጠማት፤ ከአበሻ ላም ወደ አሜሪካ ላም!! አዲሳባ ራሷ የአሜሪካ ላም ናት:: ብዙ ላበላት ብዙ የምትታለብ:: አላቢም ታላቢም በግፍ የሞላባት፤ ውጪዋ አብረቅራቂ ቀለም የተቀባ ሰፊ በረት !!

አንዳንድ የአሜሪካ ላሞች ከሰው ልጆች የበለጠ ከብር ይሰጣቸዋል:: የአሜሪካ ላም ስለሆኑ ወይም ላም ብቻ ስለሆኑ አይደለም - ወተት ስለሚታለቡ:: ስጋቸው ስለሚበላና ሌላ የምትታለብ ላም፣ የሚታረድ በሬ ስለሚወልዱ:: ይሄ የዓለማችን የደነዘ የምጣኔ ሀብት ቀመር ነው - 'የበለጠ የሚታለበውን የበለጠ ተንከባከበው !!' ይልቫል በአደባባይ በክራቫት በታነቀ ተወካዩ:: በተወካዩ መሪነት የሰግብግብነትና የክፉት ኪራላይሶ የሚደግም አህዛብ 'ከተሜ' ይባላል::

አገር ይሁን ሰው ምንም ከሌለው ምናምቴ ነው:: ይገፋል፤ ይረገጣል:: ለጠብታ ነዳጅ እንድ አገር ሰው ሲፈጅ ዓለም ጭጭ የሚለው ለዕድቅ የሚሆንን መንገድ በግፍ ለመቀየስ ነው ካለወት !! 'ሰብዓዊነት ገደል ይግባ!' ብለው ሰው መሆንህን ሊከዱ የሚዳዳቸው ሁሉ፤ በዕድልም ይሁን በችሎታህ አምልጠህ ሰው ስትሆንባቸው ገደል ያስገቢትን ሰብዓዊነት ጎትተው የሚያወጡበትን ገመድ እንድትሰጣቸው ፊትህ ቁመው ጅራታቸውን ይቆላሉ:: ደግነቱ ጭራቅ ለጭራቅ አስኪበላላ አይጨካከንም - የጭራቅ ሕግ አለ፤ የጭራቅ መህላ በየወንዙ የሚማማሉት ዓይነት:: እንደ አቲዬ አይነት ሚስኪን ለልፋት የፈጠራት እንደ አህያ ያሻቸውን የሚጭኑባት ፍጥረት የሚማማሉበት ወንዝ ዳር ከተገኘች፤ 'አደፈረሽብኝ' ከማለት አይመለሱም ::

ክፍል አምስት

እንደሰው ባልቆጠሯት እናቴ ጉልበት ሰው የሆኑ ብዙዎች 'ሰው ብቻ' እንዳልሆኑ፤ ይልቅ 'በጣም ሰው' እንደሆኑ ሲሰማቸው ('ከጣት ጣት ይበላለጣል' የሚል ተረት ሁሉ አላቸው::) የአቲዬ ወጣት ሰውነት ላይ አይናቸውን ያቁለጨለጩ ጀመረ:: ቀለመወርቅ የሚባል ካፖርትና ከብ ኮፍያ የማይለየው ባለ ትልቅ ቤትና ባለ መኪና ሰው 'ነበር':: አሱስ አሁንም አለ፤ እኔ ውስጥ ከሞተ ቆየ እንጂ ! በውስጤ ሚሊየን ጊዜ ገድየው፣ ሚሊየን ጊዜ ተነስቷል - የክፉ ሰው ነፍስ ጣር ይበዛበታል::

ሁሉም ሰው 'ጋሽ ቀለሙ' ነው የሚለው እና ይሄ ካፖርታም ቤታም እና መኪናም አጋሰስ በእናቴ ቁንጅናና ወጣትነት ቋመጠ:: ትልልቅ ልጆች አሉት:: ሚስቱ ጋር ተፋትቷል (ባይፋታ ነበር የሚገርመው):: ይሄ የአምሳ ምናምን ዓመት 'ሰው' እንዲት ፍሬ ልጅ ሊያጠምድ ዘርፌ የምትባል አቃጣሪ ያረጀች አሮጌ መረብ ሰፈሩ ላይ ወረወረ:: "ዘርፍዬ እንዴት ያለችውን ልጅ አመጣሽት ደሞ! ,, ሲል ይታየኛል በዓይነ ህሊናዬ::

አቲዬ የምትባል ሚስኪን አሳ የህይወትን ዋና ልትለማመድ ስትፍገመገም መረቡ ውስጥ ገቢች፤ ዘርፌ የምትባል ቁራጭ የአሳማ ሲጋ የክፋት መንጠቆ ላይ ተሰክታ አቲዬን አታለለቻት።

'ለፀደ!"

'አመት አትዬ!"

"ኤዲያ እንደ ባላገር 'እመት!' አትበይ፣ 'አቤት!' ነው የሚባል። ነይ አስቲ ሲጋሽ ቀለሙ ወተት አድርሽለት!" አለች ዘርፌ።

'እሽ!' ብላ የወተት ጠርሙሱን አንስታ ልትሄድ መንገድ ጀመረች - የእኔ ታዛኝ አቲዬ። በልቴቷ ተቆጣች።

'ግይ ወዲህ የምን መንኳተት ነው አቴ...ማንም መደዴ ቤት የምትሄድ መሰላት እንዴ...እንዲህ ተንቢተሽ ትልቅ ሰው ቤት ...ምኗ ገልቱ ነሽ አንችዬ...በይ ፊትሽን ታጠቢ አግርሽንም እዛ ድንጋዩ ላይ ፈግፍገሽ ታጠቢው።"

አቲዬ ሰውነቷ ነክቶት የማያውቀውን ልብስ፣ አግሯ ተጫምቶት የማያውቀውን ጫማ ከአመቤቷ ተቸራት። በደስታ ሰከረች። ሰለከተማ ሰዎች ቸርነት የሰማችው ቃል ሲጋ ለብሶ ፊቷ ሲሣቀር አየቻው። አበባ መሰለች። ድሮም አበባ ነበርች !! እንኳን ያኔ አሁንም ውብ ናት የእኔ እናት !!

በዚህ ዓይነት 'ቀለሙ' ለሚባለው ውሻ ወተት አደረሰች። ደጋገመችው። ስትመላለስ ቆየች።

የቀለመወርቅ ቤት ቤተመቅደስ መሰላት፣ ካልታጠቡ የማይረግጡት። አንድ ሴላ ቀን ዘርፌ አቲዬን ጠራቻት።

"እፀደ!"

'እመ....አቤት እትዬ!" ('እመት አትበይ የባላገር ነው' ተብላለቻ።)

"ጋሽ ቀለሙ አመም አድርጎታል። ቤት ሰውም የለ፣ ሂጂ አስቲ አሀል ውሃ ስሪለት። እኛ እያለን በረሀብ እይሞት መቸስ ጡር ነው።"

'ምን አገኛቸው?!" አለች አቲዬ የኔ የዋህ በአባቦች ጨዋታ መሃል ንፁህ ልጂን በአደራ እያስቀመጠች፣

'ምን እንደነካውማ አሱኑ ጠይቂው፣ አኔ ሠች ሞልቶልኝ አየሁት ብለሽ" አለች ዘርፌ።

አቲዬ ወደ አቶ ቀለሙ ሄደች፣ ዋለች፣ አደረች። ልታሰታምመም ሄዳ ኢድሜ ልኳን ህሊናዋ ውስጥ

የሚመረቅዝ በሽታ ይዛ ተመለሰች:: አቲዬ ከዛን ቀን ጀምሮ ቅስሟ ተሰበረ፣ ፈጣታዋ ጠፋ፣ አንገቷን ደፋች:: ቀለመወርቅ ይሉት መሸገር ማን ወጣትነቷን የመጠጠው ይመስል አማረበት አረማመዱ ሳይቀር እንደወጣት ሆነ:: ማዬላችሁም እድሜም እንደገንዘብ ይነጠቃል:: ይሄ ሰው የአናቴን እድሜ በግፍ ነጥቋታል::

አቲዬ በዚህ ልክ የሌለው መከፋት፣ መማለጫ አልባ በሆነ ቅሰም መሰበር ውስጥ እንዳለች፣ "አፀደ!" አለች አሰሪዋ ዘርፌ::

አቲዬ "አቤት!" አላለችም፣ ዝም ብላ አቃጣሪዋ ፊት ሄዳ ቆመች:: 'እመትን' በሰልጣኔ ሰም 'አቤትን' ከከብሯ ጋር ቀምተዋት ምኑን አቤት ትበል...:: ዘርፌ ትአዛዟን እንዲህ ስትል ጀመረች፣

"ጋሽ ቀለሙ ቤት ሂጂና..."

"አልሄድም !!" አለች እንባ ተናንቋት::

"ምናልሽ እንች..እከክከከከ ጭቅቅትሽን ሳላቅቅልሽ እንዲህ አፍሽን ሞልተሽ ትሰድቢኝ! " ባልቴቷ በያዘችው የኒኬል ሰሀን አቲዬን ፊቷ ላይ ደረገመቻትና፣ "እች ደነዝ እጇን አላመመችኝ" አለች::

ሰሀኑ የሰሚንቶው መለስ ላይ ወድቆ ተቅጨለጨለ:: አቲዬ በቀኝ እጇ ሰሀኑ ያረፈበትን ፊቷን ሸፍና፣ አግሯ እንደመራት ወደ መኪና መንገዱ በረረች:: ትንሽ እንደሄደች እዚህ አሁን ትልቁ ዳቦ ቤት የተሰራበት ቦታ ላይ አንዲት ኪዮስክ ነበረች፣ አንዳንዴ አቲዬ አየተላከች እቃ የምትገዛባት፣ ባለቤቷ የአቲዬን ወጣትነት ሰታይ ሁሌ ምራቋን የምትውጥ (ለለራተኝነት)...ጠራቻት::

"አፀደ..እንችን እኮ ነው!"

ዝም::

"ምን ሆነሻል ?"

ዝም...እርምጃዋን ቀንሳ አየቆመች::

"እንችን እኮ ነው!"

ዝም::

"እንዴ ደግሞ ፊትሽ ምን ጉድ ነው? ኧረ ጉዴ፣ ምንድነው ይሄ ሁሉ ደም?!"

አቲዬ ደነገጠች:: እጇን ከፊቷ ላይ አንስታ ተመለከተችው፣ በደም ተሸፍኖ ነበር::

አሁን ያፈነችው እንባ ፈነዳ:: ከልጅነቷ ጀምሮ ውስጧ የተጠራቀመው ጩኸት እና እዬዬ፣ መንደሩን የሚያሸብር ዋይታ ሆነ:: መንደርተኛው ተሰበሰበ::

ምንድን ነው?"

"እንዴ የአትዬ ዘርፌ ሰራተኛ አይደለችም እንዴ ምን አገኛት?"

ማናባቱ ነው የዘርፍዬን ልጅ እንዲህ ያደረጋት? ...ዘርፌ...ዘርፍዬ...ወይዘሮ ዘርፌ...እማዬ ዘርፌ"

የዘርፌ ሰራተኛ ለው በመሆኗ ሳይሆን፣ በዘርፌ ንብረትነቷ መንደሩ ዘራፍ አለ::

እኮ ማናባቱ ነው የነካት?

ሩናሪ ማነው የመታሽ?"

"ዘርፌ ራቧ !!"

ዝም ሰፈሩ !! ዝምምም

አምራና ተውባ በየመንገዱ ሰበር ሰካ የምትል ወይዛዝርት፣ የሚንሳለል ሸበላ ሁሉ፣ 'የሰው ላብ ገንዘቤ ውስጥ የለም ብለሀ ማል' ቢባል አግሬ እውጭኝ በሚል ሯጭ መንገዱ በተሞላ - ታላቁ የሽሽት ሩጫ !!

ክፍል ሲድስት

አቲዬ ለስድስት ወር ክለውነት ተራ እስከትወጣ ለባለኪዮስኳ ስትሰራ ከከረመች በኋላ ከረምት ገባ። ባለኪዮስኳ አቲዬን በንሰር ዓይን ስትከታተላት ነበር። ከአያንዳንዷ ቀን ጋር እየተሸቀዳደመች ነበር። አንድ ማለዳ የአቲዬን ድሪቶ ልብሶች በፌስታል ቋጥራ ከድፍን ሃምሳ ብር ጋር ሰጠቻትና፣ "በይ እግዜር ይከተልሽ!" ብላ ከቤቷ አሰወጥታ ወረወረቻት። የአቲዬ ሆድ ገፍቶ ነበር። የቀለመወርቅ ፅንስ ከውስጥ፣ የመንደሩ ሰው ከውጭ አየገፋ ሰው በሞላው አገር አናቴን ምድረ በዳ ላይ አቆሟት።

አቲዬ ስትፈጭ እና ስታነፍስ የዋለችው የምስር ክክ ብናኝ ፊቷና ፀጉሯ ላይ ተነስንሶ ነበር። ከሰድስት ወር በፊት የነበረችው ልጅ አግር ቆንጆ ልጃገረድ ናት ቢባል 'ቀለሙ' ራሱ አያምንም። መንገድ ዳር ቆመች። የከረምት ዝናብ ያካፋል። አንድ የመኪና ፅቃ መለዋወጫ ሱቅ በር ላይ ፍዝዝ ብላ ቆመች። ምንም አያየች...ምንም ሰው፣ ምንም መኪና ምንም ቤት። ህይወት ዝም የምትልበት፣ አዕምሮ ዝም የሚልበት፣ የሰው ልጅ ለሆነች ቅፅበት በቁሙ የሚሞትበት ቅፅበት አለ አይደል። አቲ በቁሟ ሞተች።

አላዛርን ከሞት ያስነሳ ራሱም ከሞት የተነሳ ክርስቶስ 'አቲዬ!' ብሎ ልክ እኔ እንደምጠራት ጠራት። ዞር አለች ወደ ኋላዋ። ከርስቶስ ላይሆን አንዲት ምቾት መድረሻ ያሳጣት ቆንጆ ወጣት ነበረች..."ወደ ውስጥ ግቢ! ዝናብ መታሽ እኮ" አለቻት አቲዬን። ገና ሲያንረመርም እግሬ አውጭኝ ብሎ ሰው የሚሸሸው ዝናብ እንኳን፣ እንዳሻው ሰው ላይ ይጨፍር ዘንድ ሰው በቁሙ የሚጠፋበት ቀን አለ። አቲዬ ጠፍታ ነበር።

ወጣቷ ከፍ ያለ ወንበር ላይ ተቀምጣ እንፋሎቱ ወደ ላይ የሚመዘዝ ትኩስ ሻይ እየጠጣች ነበር።

አቲዬ ወደ ውስጥ ገባችና ኩርምት ብላ አንዱ ጥግ ቆመች። አንደ ቆመች ዝናቡ አባራ። ሰዉ በያቅጣጫው ሩጫውን ጀመረ። አቲዬ ግን አልተንቀሳቀሰችም። የአርሷ ዝናብ አላባራም፣ መጠጊያ ላጣ ሰው የሕይወት ዶፍ አባርቶ አያውቅም። ሰው የፍቅር ጉንጥላ፣ የዝምድና ጉንጥላ፣ የጓደኝነት ጉንጥላ፣ የትዳር ጉንጥላ፣ የአውቀት ጉጉንጥላ፣ የስራ ጉንጥላ፣ የተስፋ ጉንጥላ፣ የአምነት ጉንጥላ ይዞ ስለሚኖር እንጂ ከሕይወት ሰማይ ላይ ነፍሰን የሚያበሰብስ መንፈስን እንደ ወረቀት የሚያላሽቅ የብቸኝነት እና የተስፋ መቁረጥ ዝናብ አባርቶ አያውቅም።

የአቲዬ ዝናብ አላባራም። ይሄን ሁሉ የነፍስ ጉንጥላ ጨካኝ ንፋስ ከእጇ ነጥቋታል። ንፋሱ ቀሚቧን በግድ ገልቦ ውስጧ ቅዝቃዜ አስቀምጧል። ንፋሱ የሕይወት አቧራ አንስቶ ፊቷና

ሥሯን ለልብሷል። ንፋሱ የተሰፋ ጎጆዋን አፈራርሶ አዚህ አቁሟታል። አቲዬ የእሷ እናት መሆኗ የለትም ።

መሆኖች ተንኳኩ። ቆንጆዋ ልጅ ጃኬቷን ደረበች። ውጭ የተደረደሩ አቃዎችን አስገባች፤ እናም ቁልፉን በሚያሣምሩ ጣቶቿ እንዳንጠለጠለች አቲዬን ግራ በመጋባት አየቻት፣ 'ውጪ!' ማለት ብለሣኖ ነው። ቀደሞ ወጥቶ፣ ውጪ ጋር መቆም ግን ያው ውጪ ማለት ነው።

አቲዬ ዝናብ አስኪያባራ ከተጠለለችበት ሱቅ በቀስታ አርምጃ ወጣችና በረንዳው ላይ ቆመች፤ ባለሱቋ ቆንጆ ሴት ሱቋን ቆላለፈች። የአቲዬ ንገር ሳያሳዝናት አልቀረም፣ "እ...ምን ሆነሽ ነው አያትዬ?" አለቻት። አቲዬ ዝም። ዓይኗ እንባ አቅርሮ ዝም...ወደ ሞቅ ቤቷ አልያም ወደ ቀጠራት ፍቅረኛዋ ልትሄድ ያኮበኮበች ወጣት የአቲዬን የአርባ ቀን ዕጣ ከየት ጀምሮ ቢነገራት ይገባታል? አቲዬ ዝም አለች። አልለመደባትም 'እንዲህ ሆንኩ' ብሎ ማውራት፣ አልለመደባትም ምሬት መዘብዘብ - ልማዷ አይደለም።

ውጣቷ ጥቂት ብሮች ከቦርሳዋ አውጥታ ለአቲዬ ዘረጋችላትና "አይዞሽ! ይሄን ያኸ በቃ" አለቻት። አቲዬ ግን ለማትባ ከተዘረጋው የወጣቷ እጅ በድንጋጤ አፈገፈገች። ልክ ጩቤ እንደተሰነዘረበት ሰው ነበር የበረገገችው። 'ለማኝ ልሆን?' ብላ በውስጧ አሰበች። እንባዋን እያዘራች ሽቅብ አፃሯን ተከትላ ትጓዝ ጀመር።

ሰትም የማያደርሱ የሚመስሉ አርምጃዎች አንዳንዴ አዕምሮ አስቦ ከሚደርስበት የተሻለ መፍትሄ ላይ ያደርሳሉ። ሰዎች የፈጣሪ መንገድ ይሏቸዋል። አቲዬ ዝም ብላ ብዙ ርቀት ተጓዘች። መታጠፊያ ስታገኝ እየታጠፈች፣ መንገድ ስታገኝ እየተሻገረች ዝም ብላ ወደፊት። ከሰጣ ፋንታዋ ትሸሽ ይመስል መንዴ ባያልቅ ብላ ተመኘች። ቢቃ አስከዓለም ጥግ ዝም ብሎ ቀሪ እድሜዋን መጓዝ ።

ቀጥ ብላ ተመለከተች። ፀጥ ያለ ቤተክርስቲያን ከነታላቅ ጉልላቱ ፊት ለፊቷ መንገዱን ተሻግሮ ይታያል። የልብሰ ፈሰታዋን አንጠልጥላ አሮጌ ሃምሳ ብሯን በእጇ እንደጨበጠች፣ ዓለምን ያመዳው የጨበጠ አግዚአብሔር ጋር የተፋጠጠች መሰላት።

ዚህ ሁሉ በደል...የዘ.ህ ሁሉ ግፍና ስቃይ ጠንሳሽ 'አግዚአብሔር'ን ፊትለፊት ያገኘችው መሰላት። ግዚአብሔር ለይቷት ሳያፈገፍግ፣ የበደላት ሁሉ አሳፍሮት ሳይሸሽ በፊት ልትደርስበት መንገዱን ቋርጣ ወደ ቤተክርስቲያኑ ገሰገሰች።

ግዚር ፈርቷት አግሬ አውጫኝ የሚል መሰላት አቲዬ። መኪናዎች አምባረቁ፣ ሹፌሮች መኪናቸው መስኮት ብቅ ብለው ፀያፍ ስድብ ወረወሩባት። አንበሳ ጋር ልትፋለም ታላቁን ግሬ 'በላ ልበልሃ' ልትለው በድፍረት የምትገሰግስ ጀግና በውሸዎች ጩኸት የምትበረግግ ሚሰኟት።

አቲዬ ቤተክርስቲያኑ በር ላይ ደረሰች። አግዜር ያኔ ለያት። ከሰማየ ሰማያት ዙፋኑ ላይ አንደተቀመጠ ድምፅ ከወደ ምድር ሰማ። "ቅዱስ...ቅዱስ..." እያሉ በታላቅ ድምፅ የሚሰግዱና የሚያሸበሽቡ አልፍ አሊላፍ መላኩትን "ዝም በሉ አንድ ሰየት ያለ ድምፅ ከምድር ሰምቻለሁ" አለ።

"ጌታ ሆይ ሞልቃቆች በስሱ እያማታቡ መኪናቸው ውስጥ ሆነው ሽው የሚሉት አይነት ድምፅ ይሆናል" አሉት መላዕክቱ።

"አይደለም" አለ አግዚአብሔር።

"የኮተታሞች የኮተት ጥያቄ ይሆናል" አሉት በምድራዊ ትርኪምርኪ የስጋ ጥያቄ የተማረሩት መላዕክት።

"አይደለም አልኩ አኮ" አለ አግዚአብሔር በታላቅ ድምፅ።

"ጌታ ሆይ! ምናልባት የሀብታሞች 'ከስካር፣ ከደም ግፊት ከፈወስከኝ መጋረጃ...ግሎንጥላ' የሚሉት አይነት የተለመደው ስእለት ይሆን?" ጠየቁ መላዕክቱ።

ዝም አለ አግዚአብሔር !! ዝምታው እንዳች አስፈሪ ነገር አለው። በዝምታው ውስጥ ፅንፍ የለሽ ሀዘንና ፍቅር ነበር።

ከልጅ ስጠኝ ንዝንዝ፣ ከስራ ስጠኝ ንትርክም የተለየ ድምፅ ነበር። ድምፄ ካማረልኝ ብላ የምትዘምር ሴትም አልነበረችም። 'በታላቅ ግርማ ሞገስህ በአሳት ሰረገላ ደርሰህ ጠላቴን አፈር ድሜ የምታስበላ የነገስታት ንጉስ። ከፀሐይ አስራ ዘጠኝ እጅ የምታብራ...' እያለች በተጠና መንፈሳዊ ፉከራ መንፈሳዊ ዘራፍ የምታደነቁር ሴትም አልነበረችም። ከተሰበረ ልቧ በወጣ ማቃተት ዙፋኑን የነቀነቃችው አዚህ ግቢ የማትባል ሴት ናት። አንዲት ሴት በሩ ላይ ሰትቆም፣ "ማነው የልብሴን ጫፍ በዕምነት የነካው" ብሏል እግዚአብሔር!!

አቲዬ የአኔ ጀግና ማንንም ደጅ አልጠናችም። በልበሷ መቆሸሸ ይናቋት እንጂ የአኔ አናት ከአዲስ አበባ የሕዝብ ጎርፍ ቁራሽ አልለመነችም። ለማን ሰምታ እንደምትናገር አውቃለች። አጥሩን በድንጋይ ቢያጥር፣ ባማረ መኪና ቢንፈላሰስ፣ ሴቱ በወርቅ ቢሸቆጠቆጥ...የአዲስ አበባ ሰውና አቲዬ ልብ ለልብ ተነጋግረዋል።

አይታዋለች ሕዝቡን የሀሊናውን ዓይን ጨፍኖ ጎዳና የፈሰሱትን የራሱን ጉዶች እንቁልልጭ አያለ በየስጋ ቤቱ በረንዳ ላይ ጥሬ ስጋውን ሲያጋበስ፣ ቢራና ውስኪውን ሲገለብጥ - አይታዋለች።

በረሀብ የተቆራመቱ፣ ልብሳቸው ላያቸው ላይ ያለቀ ሚስኪን ሕፃናት በምጽት ብዛት ገና በሕፃንነታቸው የስጋ ከምር ከተሸከሙ ብጤዎቻቸው የሚሆኑ ሕፃናት የተረፋቸውን እንዲሰጧቸው አጃቸውን በልመና ሲዘረጉ - አይታለች። የደህ ልጆች የሀብታም ልጆችን መኪና እየተከተሉ

ሊሆን አይታለች። የተረፈውን ሳንቲም በምፅዋት ሰም ሲወረውር ደግ ይመስላል ሕዝቡ፣ ሥላሜ የደግነት ከበሮ እየደለቀ "ደግነት ባህሌ ነው" የሚለው ህዝብ !!

የልብ ሬቢታሷን ከሻኔ አስቀምጣ በሞንባሯ ተደፍታ ሰቅሰቅ ብላ አለቀሰች። ቃል አልተነፈሰችም፣ ከሰዉ ተነስታ ቀጥ ብላ ወደ ምፅዋት ማሰባሰቢያ ሳጥኑ ሄደችና በእጇ የጨበጠችውን ድፍን ሃምሳ ብር አሳጥፋ በጠባቧ የምጽዋት ሽንቁር አስገብታ ፊቷን አዙራ አርምጃዋን ቀጠለች - ባደዋን !!

አላሚአብሔር በምድር ላይ ከባዱን ብድር ጥላበት የሄደችውን ቤት እንዲህ አላት።

"ጌዲሽ አልፍ አጥፍ ብድርሽን አከፍልሻለሁ።" አቲዬ መሀፀን ውስጥ በፅንሰነቴ ከተጣላበጥኩ፣ ቢቃ በዚህ ቀን መሆን አለበት!! አስከዛሬ ድረስ ትልልቅና ውብ ቤተክርስቲያኖችን ሳይ በአቲዬ ምክ ብር የተገነቡ ነው የሚመስለኝ።

ኖ ስትል ፊት ለፊቷ ማንን አገኘች? አባ እስጢፋኖስን !! በተዓምር ማመን የጸዳኝ አቲዬ ይሄንን ስትነግረኝ ነው። አባ እስጢፋኖስ አቲዬን አያዩ፣ "አንች ዘርፈ ቤት የነበርሽው ልጅ አደይሽም እንዴ ?" አሉና ጠየቋት መነፅራቸውን አያስተካከሉ። አባ እንኳን በዚህ ድንግዝግዝ ደመና አመሻሽ ቀርቶ በጠራራ ፀሐይ የቢተክርስቲያኑን ዋና በር የሚስቱ ፅኑ የዐይታ ችግር ያለባቸው አባት ነበሩ። አቲዬን ግን ተመለከቷት_በመነፅራቸው ሳይሆን በአግዚር ዓይናች !!

ያ ቀን አባ እስጢፋኖስ ቢተክርስቲያን ውስጥ እንዲት እናት መነኩሲት የሚኖሩባት የመቃብር ቤት አቲዬን ወሰደው አኖሯት። ሆዷ ውስጥ ወደዚች ምድር ሊቀላቀል የተዘጋጀ ፅንስ_ከረገጠችው ቪቱ ወለል ስር ይህቺን ዓለም ጥግብ አሰኚል ናሮባት የተሰናበታት የሀብታም ሽማግሌ አፅም.. አቲዬ መሐል ላይ።

ሰባተኛ ክፍል

አቲዬ ያረፈችባቸው መነኩሲት "የኔ ልጅ አይዞሽ የበላነውን እየበላሽ ልብሽ እስከፈቀደው ጊዜ ሙዳየ ትችያለሽ የአግዚር ቤት ነው..ቤትሽ ነው" አሉና ድርብ የሰሌን ምንጣፍ ብዙ ቦታ ላይ ዘርግተ ትችያለሽ የአግዚር ቤት ነው..ቤትሽ ነው" አሉና ድርብ የሰሌን ምንጣፍ ብዙ ቦታ ላይ ዘርግተው ከሰው ዓይነት ከርና መጣፊያ ከተጠቀመ ብርድ ልብስ ጋር ሰዉቷትና አንጁጥማ ላይ ራሳቸው ከሰው ዓይነት ከርና መጣፊያ ከተጠቀመ ብርድ ልብስ ጋር ሰዉቷትና አንጁጥማ ላይ ራሳቸው አነጣጠፉላት።

ኝም ላይ ጭካኔ ሲፈነጩ፣ ማን አለብኝነት በሀሴት ዋጉጫ ልቅሊቃውን ሲያስነካው፣ ሰብዓዊነት መቃብር ቤት ውስጥ በፍፁም ፀጥታ ከአትዬ ጋር ተሾነጉ። አቲዬ ከደጓ መነኩሲት ጋር በመቃብር ሴት ውስጥ ተቀመጠች። 'ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል' ቢባልም ቅሉ ኑሮው አልሞቃትም። አንቷ ድረስ ዘልቆ የሚያንዘፈዝፍ የፍርሀት ብርድ ሰላም ነሳት። 'መሄጃ የለኝም' ከሚል ስጋት ሳሀፈውም ቢሆን አርፋለች። ግን መቃብር ቤቱ ውስጥ የነበራት ቆይታ የቢቃይና የፍርሀት ነበር።

ሰው የተቀበረበት ቤት ውስጥ መቶኛቷ ፍርሃት ለቀቀባት። ከተኛችበት ሰሌን ስር በሰብሰ አፅሙ የቀረ ሬሳ ተኝቷል። በአፈ ታሪክ እንደሰማችው (አሁንም ድረስ እንደምታምነው) ደግሞ መታን እካላቸው ቢጋደምም መንፈሳቸው አርፎ አይቀመጥም...። መነኩሲቷ ወጣ ካሉ ተከትላ ደጅ ትቆማለች። እንቅልፍ ሽለብ ሲያደርጋት አንድ ሰጋው ሁሉ ረግፎ ጭራሮ የመሰሉ ጣቶቹ ብቻ የቀሩ አጥንታም አጅ የተኛችበትን መሬት ፈነቃቅሎ አንገቷን ሲያንቃት ይታያትና ኡኡታዋን ታቀልጠዋለች...ቅዠት!! መነኩሲቷ አቲዬን ማረጋጋት ለአቲዬ መፀለይ ብቻ ሆነ ስራቸው።

በፍርሀት ሁለት ቀንና ሌሊት እንቅልፍ ሰላልወሰዳት በሦስተኛው ቀን ምሽት እንቅልፍ አሸክራትና ሰሌኗ ላይ ኩርምት ብላ ተኛች – ዓለም ገፍቶ ገፍቶ የመገነገ ሰሌኗ ላይ የጣላት ሚስኪን ሴት፤ መነኩሲቷ በሀዘን ግንባሯን እንደ ትንሽ ልጅ አያሻሹና አተነፋፈሏ የተስተካከለ መሆኑን አያዳመጡ እንደ መልካም ወላጅ ቀስ ብለው ድራቡን አልብሰዋት ወደ ፀሎታቸው ተመለሱ።

ብዙ ሳይቆይ ትንሽዋ የመቃብር ቤት በአስደንጋጭ ጩኸት ተሞላች። አቲዬ "ልጄን...ልጄን" አያለች እንደ አብድ ከመኝታዋ በርግጋ በመነሳት ራሷን ይዛ መጮህ ጀመረች። አቅመ ደካማዋ መነኩሲት አቲዬን ሊያቆሟት አልቻሉም። የሷ ባልሆነ ጉልበት ገፈታትራቸው በማገርም ፍጥነት ሰሌኑን ጠቅልላ የቤቱን ወለል በጥፍሯ ትቧጥጥ ጀመረች፤ "ልጄ...ን...ልጄን ወስዱብኝ..." እያለች በመረገጥ ብዛት የደደረውን አፈር ትመነጭር ጀመረ።

እንባዋ በጉንጮቿ ላይ ለጉድ እየፈሰሰ፤ በላብ ተነክራ እየቃተተች ከትንንሾቹ መቃብር ቤቶች ጩኸቷን ሰምተው የወጡ መነኮሳት ወደ እማሆይ ቤት መጥተው ተረባርበው አስኪያስቆሟት ድረስ አቲዬ በአስሩም ጥፍሯ መሬቱን አየቧጠጠችና አየቆፈረች ኡኡታዋን ማቅለጥ አላቆመችም ነበር።

ክፉ ቅዠት...የዘወትር ቅዠቷ የሆነው ጭራሮ አጅ ዛሬም ከፊነቀለው መቃብር ውስጥ እጁን ብቻ ሳይሆን ከትከሻው በላይ ነበር ተመዝዞ የወጣው - አፈር እንደለበሰ...!! ከዛም በአስፈሪ ዓይኖቹ አቲዬ ላይ አፈጠጠባት፤ አየችው ቀለመወርቅ ነበር። ያውም አፈር ከነለበሰ ባርኔጣና ካፖርታው !! "ልጄን አምጪ!" ብሎ አጥንታም እጁን ወደ ሆዷ ላከና በቅፅበት አንድ ቀይ የሚያምር ሕፃን ይዞ ተመለሰ። ሆዷ ባዶ ሲሆን ታያት፤ ቀሰላት። ልጁን በደስታ ተመለከተውና ወደ ውስጥ ወደ መሬት ይዞት ሰረገ...። ልከ ጫጩት ነጭቆ ወደ ጉድጓዱ እንደሚገባ ሽለምጥጣጥ !!መሬቱን ከፍቶ ሲገባ፣ መጋረጃ ገልጦ የገባ ነበር የሚመሰለው።

በቀጣዩ ቀን አባ አስጢፋኖስ ሁኔታው ሲነገራቸው ድሮም ለአቲዬ ቋሚ መኖሪያ ሲያፈላልጉ ነበርና ፍለጋውን አቆጥነው ከሁለት ቀን በኋላ በፊት ትኖርበት ወደ ነበረው መንደር ወሰደው አንዲት ከዋናው የቀበሌ አጥር ጋር ተያይዛ የተሰራች የቆርቆሮ ቤት ውስጥ አስገቧት። የመንደሩ አድር አቃ ማስቀመጫ ነበረች። የእቃ ማስቀመጫዋ ቤት ጣራና ግድግዳዋ በድንብ ስላልገጠመ፣ ሌሊት ብርዱ፣ ቀን ፀሐዩ በክፍተቱ ውስጥ አያለፈ ይገባ ነበር። አባ አስጢፋኖስ ከንሰሀ ልጆቻቸው ለምነውም ተለማምጠውም ያገኟቸውን አሮጌ ፍራሽ፣ ብርድ ልብስና የውሀ መያዣ ጎማ ለአቲ እያሳቡ

ሙሮ እንግዲህ አቶ አንደምታውቂው ቤሳ ቤሰቲን የሌለኝ የአግዜር አገልጋይ ነኝ። ከዚህ የተሻለ
ነ እለተሁልሽም። ባይሆን ጎንሽን ማሳረፊያ ካገኘሽ ሌላው ሌላው በረጣሪ ፈቃድ ቀስ እያለ
ይመለል። አኔም አየመጣሁ አይሻለሁ።" ብለዋት ሄዱ።

ክፍል ሰምንት

ሰሎሱ ድንኳን፣ እንጨቶች፣ መንበሮችና ስጋጃ ምንጣፎች በአንድ በኩል ተሰድረው ገባ ብሎ
ዘ ውስጥ ባለችው ትርፍ ቦታ ላይ ደግሞ የአቲዬ ፍራሽ ተዘርግታለች። ብዙ ጊዜ ሞት
ወይም መርዶ ስለሚኖር የእድሩ አቃ አይኖርም። ስለዚህ ሰፋ ትላለች ቤቷ። አንዳንዴ ደግሞ
ለድርታኖው አቃውን ሊመልስ በግዴለሽነት ወንበሩን፣ እንጨቱን ከባባዶቹን ምንጣፎች አቲዬ
ወታ ላይ ጥለውት ይሄዱ ስለነበር ያንን ሁሉ ጓዝ ጎትቶ ቦታ ማስያዙ ለእንዲት ነፍስ ጡር
ሰት ፈተና ነበር።

አቲዬ ግን ታደርገዋለች፣ "እንዲህ አታድርጉ" እትል ነገር ሆሆ...ወደዛ ውጪ ቢሏትስ።

ሳ አስጢፋኖስ ብዙ ቤት ሊያስቀጥሯት ደክመው ነበር። ይሁንና ቀጣሪዎቹ ነፍሰ ጡር
ሙናን ሲሰሙ ሁሉም አቲዬን ቤታቸው ማስገባት አልፈለጉም። እባ ቢጨንቃቸው የአቲዬ
ኛ ሰላም ቢነሳቸው አቲዬን ለዚህ ሁሉ መከራ የዳረገቻት ዘርፌ ቤት ሳይቀር ሄዱና፣ "እችን
ዘ ይቅር በያት ባከሸ" ብለው ተማፀኑ።

"ሂይይይይ እባ ምነው እያወቁት... እንደ ልጅቼ እንከብከቤ በያዘኩ አይደለም እንዴ ጥጋብ
ርቅሏት ለመንደሩ ሁሉ ስሜን አጥፍታው የሄደች..." አለች አቃጣሪዋ። እባን በአፍ መሸንገል
ባዘርን መሸንገል ይመስል የአቲዬን በደለኝነት ስትዘረዝር ደስ እያላት ነበር።

ዝድ አይደለችም እንዴ መለተማሪያም...ደግሞስ አንች ቤት ከመቼ ወዲህ ነው ይቅርታ የጠፈው
ቷ..እንጂ" አሉ አባ።

ዝብኛ አባ በዛብኝ ...ምን በደልኩ እናት በሆንኳት...የበላሁትን ባበላስኩትን ባለበስኩ
ው ሁኝ! ሰልጥኝ!' ባልኩ - ይሄ ይገባኝ ነበር?" እንባ እየተናነቃት አባ ፊት በደሏን ዘረዘረች...
ኮ አስመሳይ!!

'ይሄው የትም ስትንዘላዘል ዲቃላዋን ይዛ አረፈችው" አለች ዘርፌ። "ከእኔ የተጣላ እጣ ፋንታው
ውድቀት ነው..." ልትል እየዳዳት...።

አ እንደሆኑ የአቲዬን ነፍስ መታደግ ይቅደም ብለው እንጂ የቀለመወርቅንና የዘርፌን ቤራ
ውሳጣቸው ያውቀዋል። አንዳንዴ 'የአግዜር አገልጋይ ከመሆን' ሽፍታ በሆንኩ፣ ነፍስ ጎዳይ
ሸንኩ' የሚያስብሉ እንደ ዘርፌ ዓይነት ገርፈው የሚጨቡ ጅራፎች ሲያጋጥሙ የንስሀ አባቶች

ልብ ምን ያህል ይሰበር ይሆን?! ቢቻል ጥምጣምና መስቀልን ለነዴ አስቀምጦ ምንሽር መታጠቅና አንዲህ አይነቶቹን እድሜ ጠገብ አባቦች ማንባር ማንባራቸውን ማሉት ነበር።

ዘርፌ ከዚህ ሀሉ ፉከራና ማስመሰል በኋላ አቲዬን ቤቷ እንደማትመልሳትና ከፈለገች በቱመላሳሽ ላሞቹን የመንከባከብ ልብስ የማጠብ ስራ እንድትሰራ በወር ፲0 ብር ልትከፍላት ለአባ ቃል ገባች።

"ያው ለነፍሴ ብዬ እንጂ የደረሰች አርጉዝ ምኗ..." አለቻቸው ለአባ።

"ማዴለም ወለተማሪያም መቼስ ሰው አንዳረገዘ አይኖር...ሁሉ ነገር ሲወለድ ጊዜ አለው። ደግሞ ይሁን ከቶ ተረግዞ አይቀርም፣ ነገን ነው ማየት" አሉ አባ። የቄስ ምንሽሩ ቅኔ ነው - ተከሱባት አባ!!

የቅኔ ጥይት ከተኳሹ እስከ ኢላማው ለመድረስ ጊዜ ይወስዳል። ለዛ ነው ዘርፌ አባ አግር ሰር ድፍት ያላለችው - ይድፋትና!! አባ አውነት ነበራቸው፣ እንደ ተረገዘ የሚኖር በደል የለም - ይወለዳል አንድ ቀን።

አቲዬ በዙሪያ ገጠም አጣፋንታዋ ዙራ ዘርፌ ቤት ገባች (ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ እያለ መንደሩ... አውር ቢሸፍት ጓሮ ድረስ ነው እያለ አሽሟጣጩ...) አንደገና ወተት ማለብ፣ አንደገና አዛባ መዛቅ፣ አንደገና ጉልበቷን መገፍገፍ...ያውም ቁጥ ብላ አመቤቷን በማታይበት የሞራል መዳሸቅ ተተብትባ - የበደሏትን ይቅርታ ጠይቃ። የዘርፌ ደግነት ግን በመንደሩ ተወራ። "መልሳ ተቀበለቻት እኮ ዘርፌ ሆዷ ቂም አይቋጥር..." እየተባለ።

አቲ አባባ ያገኙላት የቆርቆሮ ቤት ውስጥ እየኖረች፣ ለመንደሩ ሰው ሁሉ የቀን ሥራ እየሰራች ኑሮዋን ጀመረች። ዘርፌን በድላ በመመለሷ አንደተሣገረከ ባሪያ ጉልበቷን ትገፈገፍ ጀመረ። የመንደሩ ሰው ሁሉ ዳኛ...ወንጀለኛው ሁሉ ፊራጅ ሆነ አናቴ ላይ!! የማያሰሯት ነገር አልነበረም።

እነዚህ ባሎቻቸው ከየመሸታ ቤቱ እያነሱ፣ ከየመንገዱ እየሲቃቀሙ፣ ከየገጠሩ እያመጡ ሰው ያደረጓቸው...ጊዜ ያነሳቸው ቅሎች ለፍቶ በመኖር፣ አምላክን በማመን በእጅጅ ንፁህ ፍሬ የምትኖር አናቴን ብረት መንፈስ ሰበሩ።

ጊዜ ያነሳው ቅል እንኳን ድንጋይ ብረት ይሰብራል!!

አጠላቸዋለሁ...!!

በባሎቻቸው ገንዘብ እድሚያቸውን የሚገፉ፣ ሰማኒያ በሚባል ህጋዊ ፈቃድ የባሎቻቸውን ዳረጎት እየተቀበሉ የሚዘባነኑ የሰማኒያ ለማኞች። ሰማኒያ የሚሉት፣ ፍቅር ሲያልፍ ያልነካው የልመና ንግድ ፈቃዳቸው ቢቀደድ ከአቲዬ የባሰ አዘቅት ውስጥ የሚወድቁ ሁሉ ሚስኪን አናቴ ላይ ተዘባነኑባት።

"ምነው ይሄ ምንጣፍ እንዳልረባ ነገር አዚህ ተጣለ?" ይላል አንዱ ጎረቤት ወደ አንዱ ጥግ የዘመን ቆሻሻውን ተሸክሞ ወደ ተጣለ አሮጌ ምንጣፍ እያሳየ።

"አየ...አፈር ተሸከም በስብሶ ማን አሱን ይታገላል?" ትላለች ባለቤት ተብዬዋ...ትላንት የከሰል ጀንያ ሳይቀር የምታጥብ የነበረች...ከሰራተኝነት ወደ ሚስትነት በአንድ ሌሊት የአልጋ ወለምታ የተሸጋገረች መሆኗን አገር አያወቀ።

"ግዴለሽም አፀደ ማማሽ ቀን ብትውልበት አበባ ይመስላል" ይላል መካሪው።

አቲን ይጠሩና ያዟታል። ማማሽ ቀን ጭቃ ታጥባለች። እንዳሉትም አበባ ይመስላል ምንጣፉ...፤ "አቤት ቤት አያያዝ ! የምንጣፏ ንጣት ብቻ ለመርገጥ ያሳዝናል እኮ እከሊት ! የአሷ ባል ሚስት አገባሁ ይበል..." ይባልላታል። ተወዝፉ አቲዬን ቁራሽ በማይገዝ ብር መንደር የሚያለብስ ምንጣፍ ያሳጠበች እከሊትን፣ በእናቴ ጉልበት የምሲጋና ካባ ይደርቡላታል።

"አፀደ በይ አችን ያዥ" ትልና ሶስት ብር ትሰጣታለች። አቲዬ ተቀብላ ወደ ማደሪያዋ ትመለሳለች - አትከራከርም። ይሄንንም እንደብልጠት ይወስዱታል። በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የደሀን ጉልበት ከነፃ በሚጠጋጋ ከፍያ መበዝበዝን እንደብልጠት ያዩታል።

ቀናቸው የተዳረሰ አርጉዝ አሰሪዎች ሰላሳ ትራስ ደልድለው በረንዳቸው ላይ ይቀመጡና ቀኗ የደረሰ እናቴን፣ "በደንብ አሺው እንጂ" እያሉ ልብስ ያሳጥቧታል። ለዘመናት በስንፍናቸው ቤታቸው የከመሩትን ቆሻሻ ሲያስፀዷት ይውላሉ። 'እንኳን ማሪያም ማረችሽ!' የሚል ጠያቂ ቤታቸውን እንዳይታዘብ...የበከተ ቤታቸውን...ከቅዱስ ዮሐንስ አሰክ ቅዱስ ዮሐንስ ውሀ ነክቶት የማያውቅ መጋረጃቸውን ያሳጥቧታል !! ወይስ ከአርጉዝ አርጉዝ ይሰያል...። የደሀ እርግዝና ቢጨነግፍም እዳው ገብስ ነው ዓይነት ፍዳዋን ያበሏት ነበር እናቴን...።

ለምን ለፋች አይደለም የምለው ! ግን የለፋችበትን የላቧን ዋጋ ከልከለዋታል። አፈር ያብላቸውና የደም ገንዘብ የበሉ ናቸው። ዳሌያቸውን እያገማሸሩ ወንድ የሚያሳድዱ ሴት ልጆቻቸው አቲዬ ከአርግዝና ህመም ጋር አየታገለች ያጠበችውን ልብስ የለበሱ አርኩሳን ናቸው...። ሕፃናት ልጆቻቸው በየሜዳው ሲንከባለሉ እናቶቹ በሳምንቱ መፅጪረሻ ስለሚደክመው የአቲዬ ጉልበት ሳይሆን ስለሳሙናቸው ነበር የሚጨነቁት፣ 'አጉተ ልጅ ኧረ የሳሙና ጡር አለው' እያሉ። አቲዬ ቃል ሳትተነፍስ ማንንም ሳታማርር አስክ ወለደችበት ቀን ድረስ ስትሰራ ነበር...።

ክፍል ዘጠኝ

አኔ የተወለድኩ ቀን ጠዋት አቲዬ 'አቃጣሪዋ ዘርፌ' ቤት ወተት ስታልብ ነበር። ረፋዱ ላይ የአንዲት ጎረቤት በርበሬ ስትቀነጥስ ዋለች። ውጋት ሲጀምራትና ምጡ ሲጫናት ከበርበሬ ቅንጠሳው በኋላ ልብስ ወደምታጥብበት ቤት ለመሄድ እየተዘጋጀች ነበር። ህመሙ ሲጀምራት

ግን መንገዷን ቀይራ ወደ መንደር አዋላጇ አልማዝ ቤት ሄዳ እየፈራች፣ "እትዬ አልማዝ እያመመኝ ነው። ምጥ ነው መሰለኝ..." አለቻት።

"ውይ በሞትኩት...መጣሁ ሂጂና ቤትሽ አረፍ በይ..." አለቻት።

አቲዬ እንደታዘዘችው አደረገች። አዛች አሮጌ ፍራሽ ላይ ተኝታ ምጥ እየናጣት በር በሩን ማየት ጀመረች። አልማዝ ግን ወደ አቲዬ አልሄደችላትም። ምክንያቱም አቲዬ ምጥ የተያዘች ቁን፣ ዘርፌ የምትባለዋ አቃጣሪ ባልቴት የአሜሪካ ላሟ ያልታወቀ ነገር በልታ ሆዷ ተቆዝሮና አረፋ ደፍቃ እየጓጎረች ስለነበር፣ መንደርተኛው ሁሉ ወደዚያው ሄዶ ነበር። አዋላጇ አልማዝም ቅድሚያ ለዘርፌ ላም ሰጥታ ነበር።

አንድ ግብርና የሚሰራ የአንስላት ህክምና ባለሙያ ተጠርቶ አስከራብቶ በሚመስል ነገር የላሟን ሆድ ወግቶ ካስተነፈሳት በኋላ ላሟ ነፍሷ መለስ በማለቱ የመንደሩ ሰው ደስታውን በእልልታ ገለፀ።

በዚህ መሐል አዋላጇ አልማዝ፣ "በሞትኩት ያች ሚስኪን ምን ደርሳ ይሆን?" ብላ ወደ ቤታችን ተጣድፋ ብትደርስ አቲዬ እኔን አቅፋ አገኘቻት። 'የወርቅ ፍልቃቂ' የመሰልኩ እኔ፣ በአሳት የተፈተንኩና የጥላቻ እሳት የምተፋ እኔ፣ አላፊ አግዳሚውን የምራገም እኔ በእናቴ እቅፍ ላይ!!

ታሪክ ይወቀኝም አይወቀኝም፣ እናት የተባሉች ታላቅ ሀገር ከስግብግብ፣ ከአስመሳይ፣ ከራስ ወዳድ፣ ከአሸቃባጭ፣ ደሀ ከማይወድ፣ እምነት ከሌለው፣ ሆድ አምላኩ ከሆነ አመንዝራ እና ጨካኝ ጎረቤት ቅኝ ግዛት የወጣሁ ጀግና እኔ ተወለድኩ !! አገሬ እናቴ አፀደ ናት ! ባንዲራዬም የእናቴ ቀለም አልባ አሮጌ ቀሚስ !! ድምጿ መዝሙሬ ነው፣ ትዕዛዟ ሕገ መንግስቴ !! እናቴ አፀደ ወይንም ሞት!! አቲዬ ትቅደም !! አቲዬ ለዘላለም ትኑር!

መዝሙሬ...፣

ተንቃሽ የናርሽው ድሮ ከዚህ ቀደም፣

ለናቴ ለፀደ የደፈረሽ ይውደም !!

በሰሜን ሰግብግብ የደሀ ደም መጣጭ ጎረቤቶች፣ በደቡብ ራስ ወዳድ በደሀ አምባ የሚኖሩ አጋሰሶች፣ በምስራቅ የእናቴን ፀሐይ እንዳትወጣ የሚጋርዱ አስመሳይና ሆዳሞች፣ በምዕራብ ሚስኪን ሴት ደፋሪዎች አና ትውልድ የሚከዱ ካፖርታሞች...። ከታች በባዶ እግሯ የምትረግጠው ምድር፣ ከላይ እግዚአብሔር (የባህር በሯ) የሚያዋስናት ሀገር አፀደ ትባላለች - የእኔ አገር አሏ ናት !!

አፀደ ከሰማይ ዱብ እንዳለ ጉድ ዘመድ የላትም። እናት፣ አባት፣ አክስት፣ አጎት የላትም።

አልተማረችም፤ ገንዘብም የላትም። ግን ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ ላለሆነ ባለፀጋ አግዚያብሔር እንበና ድፍን የኢትዮጲያ ሃምሳ ብር ያበደረች ልበ ሙሉ ሴት ናት። አግዚያብሔርም የማንም ብድር በአጁ ይቆይ ዘንድ አይወድምና ብድሩን ይከፍል ዘንድ አኔን መንገድ አደረገ። ለድፍን ሠዓ ለምስት ዓመታትም አነፀኝ - ደለደለኝ።

አግዚአብሔር ፈጠነም ዘገየም ወደ አያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውስጥ ይመጣል። ሲመጣ የአግዜርን አርምጃ የአግሩንም ዳና የሚቋቋም መንገድ የሚሰራው 'መከራ' በሚባል ኮንክሪት ነው ። ዙሪያህን የከበበህን ችግርና አልህ አሰጨራሽ የሕይወት ፈተና ስታልፍ፣ የአግዜር የመጀመሪያ አርምጃ ትጀመራለች። ያኔ ታዲያ ርህብን ብቻ ሳይሆን ጥጋብንም የምትችል አድርጎ አንዳነፀህ ይገባሀል።

አሰራሩ እንደዛ ነው፤ ባይሆንም እኔ እንደዛ ነው አላለሁ። አንተን ከድህነት ማውጣት ብቻ ሳይሆን መጫውን የጥጋብ ዘመንም የሚሸከም ትከሻ እንዲኖርህ አድርጎ ይሰራሀል። ካለመንክ እንደየዕምነትህ መጽሀፍህን ግለጥ፣ አዱኒያን እንደ ምናምንቴ ንቀው ፈጣሪን ያመኑ፣ የተከተሉ ሁሉ ሰፈርህ ሕንፃ አቁሞ እንደሚሸልለው አብራተኛ ሃብታም ባንዴ ሰማይ ጥግ አልደረሱም።

ፈጣሪ ሲሰራህ ቀስ ብሎ ነው፣ ግን መቼም እንዳትፈርስ አድርጎ። ያኔ ደስ ይልሃል - ወደህ ነው፤ ገንበስ ብለህ ታመሰግናለህ - በግድህ !! አንተ ሳለማመሰገን ብትጥር እንኳን ስጋህ ያማረ ፍራሽ ላይ ለሽ ሲል፣ በርህብ የተንሰፈሰፈ አንጀትህ ውስጥ የጣመ ምግብ ሲንዘንዝ፣ በላዩ ላይ ጥሩ ቡና ስትጨምርበት፣ ከምንም በላይ ደግሞ ራስህን ስትገዛና ልብህ በሰላም ሲሞላ፣ "አግዚያብሔር ይመስገን" ይልብሀል አፍህ ከአንተ ትዕዛዝ ውጭ!!

ክፍል አሰር

አቲዬ አኔን ከወለደች በኋላ ትንሽ ተስፋ ልቧ ውስጥ አደረ። 'አባቱ በልጁ አይጨክንም መቼም' ብላ። ግን አባት በልጁ ጨከነ። 'ቀለመ ወርቅ' አባት የመሆን ሞራሉም ብቃቱም የሌለው ሴሰኛ ሽማግሌ መሆኑን የአቲዬ ልብ ያወቀው ብዙ ቆይቶ ነበር። ወንዶች ለአገር ዳር ድንበር ለየፎከሩና እየሸለሉ የመዝመታቸውን ያህል አባትነትን ለመቀበል፣ ትዳርንም 'አሜን!' ብሎ ለመኖር፣ ከነፍሳቸው ጋር የሚገጥሙት ጦርነት ቀላል አይደለም። ለመውለድ ወንድ መሆን በቂ ነው፣አባት መሆን ግን ታላቅ ጀግንነትን ይጠይቃል። ቀለመወርቅ ደግሞ ጀግና አልነበረም። ከሰዚህ አኔን ልጁን ዶሮ ሳይፈጭህ ሦስቴ ካደኝ።

አቲዬ የአኔ ብርቱ ግን በሰባት ቀኗ ከአራስ ቤቷ ተነስታ ምንም አንዳልተፈጠረ ሁሉ ስራዋን ጀመረች። "ኧረ ወገብሽ ይጥና" ያላት አልነበረም። የበሰበሰ ድሪቷቸውን ከምረው ጠበቃት አንጂ !! 'የምትገርሚ ጠንካራ ልጅ' አያሉ። አርባ ቀን ሙሉ ተዘፍዝፈው ሊጣቸውን ሊያሻምዱ ኑረው ሲወጡ አንኳን አራስነት ምን ያህል ከባድ መሆኑን እንደማያውቁ ሁሉ፣ አቲዬን በሥራ

ሲያጣድፏት ምንም አልከበዳቸው።

ልጅ ይዛ ሥራ መሥራት ከባድ ነበር ለኢቲዬ። በየቤቱ በረንዳ ላይ እያስተኛች ሳለቅስባት እያጠባችኝ(ምናባቴ እንደሚያስለቅሰኝ አንገፃ !)። ኢቲዬ እናቴ ብርቱ ሰው ከህይወት ጋር ትግሏን ቀጠለች...አንድ...ሁለት...ሦስት...አራት ወር ላሉቃጣሪዋ ዘርፌ ኢቲ እየፈራች እንዲህ አለቻት፤

"አትዬ...አኔ እንግዲህ እስካሁን ለልጁ አንድ ነገር ያደርጋሉ ብዬ ጠበቅኳቸው አሳቸው ግን..."

"ማናቸው ልጄ..." አለች ዘርፌ ለካሄዱ አላምር ብሏት ፊቷን አጨፍግጋ።

"ጋሽ ቀለመወርቅ" አለች ኢቲ።

"እሀ...ደሞ እሱ ምን ቤት ነው ባንቺ ልጅ..."

"እትዬ...ፈርቼ አልነገርኮትም እንጂ፣ አኔ ሌላም ወንድ ነክቶኝ እያውቅ ተሳቸው ነው..."

"ወዲያ ዝም በይ...ምን ትላለች አቺ...የተከበረ ሰው አናት ዘሎ ፊጥ ማለት ምን ይሉት ብልግና ነው?! ሁለተኛ እንዲህ ያለ ነውር ስትተነፍሽ ብሰማ ውርድ ከራሴ...። ሂጂ እሁን ወዲያ ያው ደሞዝሽ!"

ብላ አስር ብር ወረወረችላት። ስራዋ አስደንግጧት እንጂ ሳምንት ነው ገና ደሞዝ ለኢቲ ከከፈለቻት።

ቀለመወርቅ ይህችን ጭምጭምታ ሲሰማ ተንኮሉን ጀመረው። ኢቲዬን ከመንደሩ ሊነቅል እንቅልፍ አጣ። ኢቲዬ ለአባ አስጢፋኖስ ሽምግልና ላከችበት።

"ቀለመወርቅ መቼስ ዘር አይጠላም። ነገ የት እንደሚደርስ አንድ ፈጣሪ ነው የሚያውቀው። ሌላው ቢቀር የወተት መማጋ እንኳን ስጣት መቼስ አቧ ጋር አንዲህ ሠራህ፣ አንዲህ አደረግክ ለማለት ባልደፍርም ልጁ ቆርጠው የጣሉት አንተን ነው..."

"ምን ማለተዎ ነው አባ...አኔን በአንዲህ ያለው ቅሌት አንዴት ይገምቱኛል?" ብሎ በአባ ከፉኛ ተቆጣ። ቀለመወርቅ ሽምጥጥ አድርጎ ካደ !! መቸም ቁርጥ አድርገው የጣሉት ሰይጣን ነው፤ ይባሰ ብሎ ከዘርፌ ጀምሮ መንደርተኛው ሁሉ ኢቲዬን ሥራ ማሠራቱን እንዲያቆም ተንኮል ይሸርብ ጀመረ - ተሳካለት። አንድ መንደር ሕዝብ አንዲት ደሀ ላይ አመፀ። ቀለመወርቅ እና ዘርፌ ነበሩ የተንኮል ድሩ ፈታዮች።

"ነገ ባልሽን ስሙን ብታጠፋውስ...ሰው አንደሆነ አንች ቤት ልብስ ማጠቢን፣ ገባ ወጣ ማለቷን ነው የሚያየው" ይሏታል ለአንዷ አሰሪ።

'እውነትዎትን ነው እትዬ ዘርፌ ለአቶ ቀለመወርቅ ያልተመለሰች እች...' ትላለች:: በቃ አቲዬን በለበጣ አስባብ ታብርራታለች፤ "ውይ ትላንት ልጅቷ አጠቡት ልብሱን" በቃ !!

አቲዬ ግራ ገባት:: እኔን አዝላ ስትንከራተት ትውልና የሚሠራ ሥራ አጥታ ማታ ቤት ትመለሳለች:: ቤት ውስጥ የነበረችው ርጋፌ በለ ብቻ ነበረች:: ወደማታውቀው መንደር እየሄደች፤ "የሚታጠብ ልብስ አላችሁ?" ትላለች::

'የለንም::"

'ወፍጮ የሚሄድ አህል በርበሬ ካለ..."

"የለም...የለም" ይላሉ ያዘለችውን ልጅ አያዩ::

አቲዬ ተንከራተተች:: በመጨረሻም ያላት አማራጭ ልጇ በርሀብ ከሚሞት ቀለመወርቅ እግር ላይ ወድቃ "ይማሩኝ!" ማለት ነው:: ቀለመወርቅ - ቀጣፊው ነብይ አሱ በመንደሩ "ይታሰር" ያለውን ሥራ ሰይጣን በድፍን አዲስአበባ ያሰረዋል:: አቲዬ "ይቅር ይበሉኝ ልጄ የአርሰዎ አይደለም ቢቸግረኝ ነው ከፉ የተናገርኩት" ልትል ወደ ቀለመወርቅ ቤት ገሰገሰች::

ለክፋቱ ደግሞ ዓይን የለ እፍንጫ፣ ፀጉር የለ ጆሮ እኔ ቁርጥ ቀለመወርቅን ነበር የምመስለው:: ለክህደት የማልመች ጉድ:: ቀለመወርቅ ብቻውን የወለደኝ ይመስል አቲዬን የሚመስል እንዴት ነገር የለኝም:: የቀለመወርቅን የልጅነት ፎቶ ቁጭ!! ቢሆንም "ይቅር በለኝ ልጅህ አይደለሁም" ልል በለናቴ ጀርባ ላይ ወደ አባቴ እየሄድኩ ነው - አባት ያሳጣውና:: ይሄ የውሻ ልጅ !!

ቀለመወርቅ የእድር ዳኛው ጋር ተነጋግሮ አቲዬን ከማደሪያዋ ሊያፈናቅላት ሲዶልት እንዳመሸ የዘርፌ ሠራተኛ ለአቲዬ ሹክ ብላት ነበር:: ለይቅርታ የባስ ያሮጣት አንዱ ጉዳይም ይሄ ነው:: ደግነት ጥግ እንደሌለው ሁሉ ከፋትም መጨረሻ የለውም:: ይሄ ከፉ አቲዬን ማሳደዱን በትጋት ተያይዙት ነበር:: እናም አቲዬ ይቅርታ ልትጠይቅ፤ "ማረኝ ጌታዬ" ልትለው ወደ ቤቱ ሄደች::

ወዳጄ...እግዜር ይቅርታ ይወዳል ማለት 'ማንም ጥጋበኛ አግር ስር እየሄድክ አንድትደፋ ይሻል' ማለት አይደለም:: አቲዬ የአኔን የልጇን ነፍስ ለማትረፍ ራሱን በፈጣሪ ቦታ አስቀምጦ ይቅርታ ሊጠየቅ የተዘጋጀው ካፖርታሙ ቀለመወርቅ ቤት ልከ በሩ ላይ ስትደርስ እና የግቢውን በር ሲታንኳኳ እጇን ስታነሳ፤ እግዜር "ተመለሽ" አላት:: ያው እንግዲህ እግዜር ሲናገር በሰው አይደል...::

የእድር ለፋፊው ጉልማው እሳት ጎርሶ እሳት ለብሶ አቲዬን ከኋላዋ በቁጣ ጠራት:: በሰሚ አይደለም፤ "እንች...አንችን አኮ ነው:: ምን ያለችው ናት ጃል" አያለ:: አቲ እየተጣደፈ ወደ አርቧ የሚመጣውን ለፋሪ ቁማ ጠበቀችው:: አጠገቧ ሲደርስ፤ "ምን መሆንሽ ነው እንች ሴትዮ የአሙሪት ቅጠል ረግጠሻል እንዴ?" አለ::

"ምነው?" አለች ግራ ገብቷት።

"ምነው ትለኛለች እንዴ፣ በይ ነይ አሁን፡ እቃ ማስቀመጫ ቤቱን ከፈችላችው። ሰው ሞቶ ድንኳን ልናወጣ ብንል ቁልፍ ይዘሽ ጠፋሽ። እገር ተረፈ እንዴ፣ ያልኳተንኩበት የለም እንትን ፍለጋ" አለ በማማረር። አቲዬ ቁልፍ ልትሰጠው አስባ እንድ እቃ ቢጠፋስ ብላ ሰለፈራች የሰውየውን የማያቋርጥ ድንፋታ እየሰማች ይቅርታው ይቆየኝ ብላ ወደ አድሩ እቃ ማስቀመጫ ቤት ተመለሱ፤ ለፋፊው መንዱን ሙሉ እየነተረከት ነበር አቲዬን።

"እገር ተረፈኝ እንዴ...ዘርፌ ቤት፣ ከዘርፌ ቤት ጆሚላ ቤት፣ ጆሚላ ወደ ላይ ሄደች ብትሰኝ ዝናሽ ቤት፣ ዝናሽ..." እንዳንዱ ሰው እያባራም። ከአሱ ያነሰ ሰው ያገኘ ሲመስለው ሌሎች ያሉትን ሁሉ ይዘረግፋል። ሌሎች በናቁት ልክ ሊንቅ ይፍገመገማል።

እቃ ቤቱ ሲደርሱ ብዙ ሰዎች ተሰብስበው ነበር። ነጭ የእቃ መጫኛ መኪናም ቆማለች። መኪናዋ ሳን ነጠላዋን ያዘቀዘቀች ሲት፣ ጀርባዋ ላይ ፎጣ ጣል ያደረገች ፀጉሯን በሻሽ አስራ ከቀሚሷ ስር ቱታ ሱሪ፣ የቱታውን ጫፍ ካልሲዋ ውስጥ ጠቅጥቃ ነጭ ሸራ ጫማ የተጫማች ደልደል ያለች ቀይ ወይዘሮ ቆማለች። (የአዲስ አበባ ሴቶች ሀዘን ማካበድ ይችሉበታል። ትጥቃቸው ሲታይ ዘመቻ የሚሄዱ አክ ነው የሚመስሉት፣ የሚችን ነፍስ ሊያስመልሱ ያሰቡ የከተማ አርበኞች_)

እች ከራስ ሻሽዋ አስከ እግር ካልሲዋ የነገርኳችሁ ወይዘሮ አጥፍ ወርቅ ትባላለች። ዋናው መንገድ ላይ ወደ ግራ ታጥፎ ከሹልቃ ክትፎ ቤት አጠገብ ያለው ባለ ሁለት ፎቅ ሆቴል የእርሳ ነበር። ጋሪ መቆሚያው አጠገብ ነዳጅ ማደያው ኋላ ያለው ሰፊ ግቢ መኖሪያ ቤቷ ነው። እና እች ሀብታም ሴት፣ አቲዬ ተጠርታ ከመድረሷ በፊት በወሬ ወሬ፣

"ዘበኛው ነው የጠፋው ?" ትላለች።

"እይ እዚህ የምትኖረው ልጅ ናት" አላት የአድሩ ሊቀመንበር።

"እዚህ መጋዘን ውስጥ ሰው ይኖራል ያውም ሴት ልጅ?" አለች ከልቧ ደንግጣ።

በቆርቆሮ ቤቱ ዙሪያ የሽንት መሽኛ፣ ቆጥሻ መድፊያ ቦታ ሲሆን፣ እዛ አካባቢ ለደቂቃ መቆም እንኳን ከርፋቱ አይጣል ነበር። በቤቱ ጥግጥግ ሳርና ቅጠላቅጠል አብቅሎበት መቃብር በ አስመስሎታል። ጣሪያውም ላይ ሀረግ ተንዠርዥሏል። በቀንም የሚያስፈራ ቤት ነበር እንኳ በሌሊት።

አቲዬ ስትደርስ የሴትዬዋ ድንጋጤ እና ሀዘን ጨመረ። ከንፏ ለቆመው ሰው፣ "ጭራሽ ሕፃ ልጅም ይዛ ነው እዚህ የምትኖረው?" አለችው።

"አዚሁ ነው እኮ የወለደችው" አሳት የእድር ሊቀመንበሩ። ሴትዬዋ አንጀቷ ተንሰፈሰፈ። ቤቱ ለከፈት እቾ ሴት ጉዱን ልየው ብላ ወደ ውስጥ ተራመደች።

"አትዬ አጥፍወርቅ ሽረ አቧራ ነው ጉንፋን ያስይዝሻል" አያሉ ተንጫጩ የእድሩ ሰዎች። እፍንጫ ያላት ፍጥረት እቾ ሴት ብቻ ትመስል። ወይዘሮ አጥፍወርቅ ግን ወደ ውስጥ ገብታ የአቴን መኝታ ተመለከተች። የተበላሳውን የቤቱን ግድግዳና ጣሪያ በታላቅ ሀዘን ቃኘች። በራሷ ዓይን ሳይሆን በእግዜር ዓይን። አናም ሁለት ጊዜ አስነጠሰችና አቲዬን እንዲህ አለቻት፣

"እሁኑኑ የምትፈልጊውን አቃሽን መኪና ላይ ጫኝ። እኔ ቤት ትኖሪያለሽ። ማነህ ና እግዛትሞ አንጂ) የእድር ለቶፊው ማውራቱን አላቋረጠም፡ "ያንች ዕጣ ፋንታ አንደ ሙበራት ሊበራ እኔ ከላምስት ላንቲም አንዲህ መኳተን...ነገ ሰው ብትሆኝ እንድ ዋንጫ ጠላ አትይኝም። አውቀዋለሁ እጀ አመድ አፋሽ ነው። አገር ቀረኝ እንዴ፣ ዘርፌ ቤት የለችም ሲሉኝ..." አንደ አዲስ ጀመረ...።

ክፍል ሰለራ ለንድ

አቲዬ ለመርገጥ የሚያስፈራው የወይዘሮ አጥፍወርቅ ግቢ ውስጥ እንዲት ቆንጆ ሠርቪስ ቤት ተሰጠቻት። ያውም ከነሙሉ ዕቃው።

"ማነው ስምሽ አናቱ?" አለቻት አቲዬን ወይዘሮ አጥፍወርቅ።

"አጠደ"

"ውይ የኔ ድንቡሽቡሽ! ስንት ወሩ ነው?" አለች እኔን እያየች።

"አሁን የፊታችን ገብሬል መንፈቅ ይሞላዋል" አጂን ወደኔ ዘረጋች። ፈገግ ብዬ እጂን ለቀም። 'ሕፃናትን መለይከው ይመራቸዋል' የሚባለው እውነት ሳይሆን አይቀርም። ወይም ሴትዬዋ እጅ ላይ የተገጠገጠው የወርቅ ቀለበትና ጌጣጌጥ መጫወቻ መስሎኝ። ወይዘሮ አጥፍወርቅ አቲዬን እንዲህ አለቻት፣

"ላንችና ለልጅሽ ሆድ አታስቢ! እዚህ ተርፎ ለሚደፋ አህል የበላነውን ትበያለሽ። ብትወጅ እኛ ጋር አየሰራሽ፣ ከፈለግሽም ያሻብሽ አየዋልሽ እዚሁ ኑሪ - ቤትሽ ነው።"

ኑሪ...ኑሪ...ኑሪ...ኑሪ...ኑሪ.....በሕይወት ኑሪ። ሌሊት ኮሽ ባለ ቁጥር ሳትለጊ ኑሪ። ልጅሽን አንደፈለግሽ የምታጥቢበት፣ የሽንት ጨርቅ የምታጥቢበት ውሀ ሳያለስብሽ ኑሪ። ልጅሽ የሚበላው ካር ሳይቸግረው ኑሪ...ኑሪ...። አግዚርም ሲናገር ልክ እንዲህ ነበር፡ "ያውላችሁ ምድር ኑሩበት፣ ውሀው ያው፣ ምግቡ ያው፣ መኖሪያው ያው..." ይሄው ወይዘሮ አጥፍወርቅ ግቢ ዘፍጥረት ራሱን ሲደግም።

"በመጀመሪያ ምድር ባዶ ነበረ። ባዶው ላይ አንዲት የጨለማባት ሚስኪን ሴት ልጅ እዝላ ቆማ ነበረ። እግዜር ብርሃን ይሁን አለ። ቦማ !!" ከአግዜር ብርሃን ጋር ሲውዳደር ቀለመወርቅ አብሬ ትል ማለት ነው። ዘርፌ ሀይሏን የጨረሰች የኢድ ባትሪ። ወይዘሮ እጥፍወርቅ ጨረቃ - የእግዜርን ብርሃን የምታንፀባርቅ። እግዜር ግን ፀሐይ - ከአድማስ አስከ አድማስ በብርሃን የሚያጥለቀልቅ አናም የሚሞቅ !!

አቲዬ በተሰጣት ምርጫ መሠረት እዛው ቤት ልትሰራ ወሰነች። በዕርግጥም የተሻለ ምርጫ ነበረ። የማንንም ፊት ከማየት በአጅጉ የተሻለ። ለእኔ በተለይ ግቢው መቦረቂያዬ፣ የወይዘሮ እጥፍወርቅ ፈጣሪታ ምቾቴ ሆነልኝ። በዛ ሰፊ ግቢ ውስጥ ወይዘሮ እጥፍወርቅ፣ ወጣት ተማሪ ልጃቸውና እኛ ብቻ ነበርን የምንኖረው። የወይዘሮ እጥፍወርቅ አምስት ልጆች ኑሯቸው በውጭ ሀገር ነበር።

ወይዘሮ እጥፍወረቅ አስገራሚ ሴት ነበረች። እንኳን አቲዬ የድሮ እመቤቷ ዘርፌ ራሷ የማታልመውን ከውጭ ሀገር የመጣ አንድ ሻንጣ ልብስ ለአቲዬ ሰጠቻት። ለእኔም ቆንጆ ቆንጆ ልብስ ገዛችልኝ - ዘነጥን !! እኔና አቲዬ ቂቅ ብለን ዘነጥን - ደግሞ ስናምር!!

አቲዬ ከወይዘሮ እጥፍወርቅ የተሰጣትን ልብስ ለብሳ አበባ መስላ ብቅ ስትል ዘርፌ ዓይኗ ደም ለበሰ፣ ቀለመወርቅ ደም ማፈቁ ከፍ አለ። ከራ አሳቢዎች ምን ሀብት ቢተርፋቸው የያዙት ነገር ዓያስደስታቸውም። ይልቅ የሚጠሉት ሰው ጥቃቅን ለውጥ ያንገበግባቸዋል። ዘርፌና ቀለመወርቅ የምቀኛ ግንባር ፈጥረው ተንገበገቡ። የግንባሩ ጸሐፊ ሰይጣን!! እናም ሰይጣን ከቀለመወርቅ እና ዘርፌ ጓላ እግዜርም ከአቲዬ ፊት ቆመው ጦርነቱ ተጀመረ !! አሁን በኑሮ ማስፈራራት በክብር መንጠባረር የለም። ማንም ሆዱ ከሞላ ጅግና ነው። ማንም ቢመታ የሚወድቅበት፣ ቢቆስል የሚታከምበት ካለው ጅግና ነው። ማንም የሚያከብረው ሰው ከጎኑ ካለ በሌሎች ንቀት ሞራሉ እንደደረቀ እንጨት አይሰበርም። ዋናው ሰንቅና ትጥቅ ግን ማንም አግዚያብሄር ከጓላው አንዳለ ካመነ ልበ ሙሉ ነው !!

አቲዬ ይሄን ሁሉ ሆና ነው ወደ ጦርነቱ የገባችው !! እናም ጦርነቱ በታሪክ 'ወርቃማው ጦርነት' በመባል ይታወቃል በእኔ በነፍሴ ዘገባ !! ወደፊት ልጆቼ "ለምን ወርቃማው ጦርነት ተባለ ?" ብለው ቢጠይቁኝ መልሴ አንድ እና አንድ ነው፣ "በቀለመወርቅ እና በእጥፍወርቅ መካከል በተደረገ ሰብዓዊ ጦርነት በእሳት የተፈተኑ ወርቆች ወደ ምጾት አገር ስለተሰደዱ" አላቸዋለሁ።

ክፍል አሰራ ሁለት

የባርነት አስከፊ ገፅታ ያለው በባርነት መገዛቱ ላይ ሳይሆን በባርነት የተገዙበት መንገድ ላይ ነው። በፍላጎት ለሌሎች ባሪያ መሆን ለራስ ህሊና የጌትነት ማዕረግ ስለሚያጎናፅፍ፣ ለነፃነት ትግል ሳይሆን ለምሲጋና ራስህን እንድታዘጋጅ ነው የሚያደርግህ። 'አሰይ፣ እንኳንም ባሪያ

ሆኑ' የሚባልለት ባርነት አለኮ:: ሰዎች በፍቅር ለሀገራቸው ባሪያ ይሆናሉ:: ለፈጣሪያቸው ይገዛሉ:: ለሚወዱቸው ያገለግላሉ:: ግን ደስተኞች ናቸው:: ለምን ? መንገዱ ፍቅር ነዋ !!

አቲዬ ዙሪያውን በረሻም የግንብ አጥር ወደተከበበው ግቢ ገብታ ብትከትምም ዕጣፋንታዋን ግን ለሳመለጠችውም:: ዕጣፋንታ እኮ ጥላ ነው:: በዙሪያህ ያለውን ችግርና መከራ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ብርሃን ሲጠፋ፣ አብሮ የጠፋ ይመስለሃል እንጂ፣ ቀን የሚሉት ፀሐይ ወጋገኑን ሲቃድ ከትላንቱ በላይ ደምቆ ካንተ በላይ ገዝፎ ከፊትህ ይመራሀል - ከኋላህም ይከተልሀል::

አቲዬም ዕጣ ፋንታዋን ስንዝር አላመለጠችውም:: ከባርነት ወደ ፍቅር ባርነት ተቀይሮ በትልቁ ግቢ ውስጥ ጠበቃት እንጂ::ሰው አጥቶ፣ ውርማ ውጠት የነበረውን የወይዘሮ አጥፍወርቅ ግቢ ነፍስ ዘራችበት:: ሰፈውን ግቢ ከጧት አስከ ማታ አፅድታ ትልቁን ቤት ውበት ትደፋበታለች፤ የወይዘሮ አጥፍወርቅን ሆቴልም ቀጥ አድርጋ የያዘችው አቲዬ ራሷ ነበረች::

የሆቴሉን አንጀራ ሙሉ በሙሉ ትጋግራለች:: የአልቤረጎዎቹን አንሶላዎች ታጥባለች:: እንደዛም ሆኖ በጣም ደስተኛ ነበረች:: ወይዘሮ አጥፍወርቅ ደግ ሴት ነበረችና ምንም ቢደረግላት ይገባታል፤ የአቲዬ ባርነት ጣፋጭ ነበር:: መሀተመ ጋንዲ ወደ ወይዘሮ አጥፍወርቅ ግቢ ጎራ ቢሉ ኖሮ፣ "ነመስቴ...እኛም የታገልነው ለዚህች አይነቷ ባርነት ነበር በርቱ!" ብለው የሚሄዱ ይመስለኛል!!

በእርግጥ ወይዘሮ አጥፍወርቅ አቲዬን አንጀራ 'ጋግሪ' አላለቻትም:: ራሷ አቲዬ ለሆቴሉ አንጀራ ግዥ አየተባለ በቀን የሚወጣውን ብር ስትመለከት፤ "ምጣድ ግዙልኝ ራሴ አጋግራለሁ" አለች ለንጂ:: የሆቴሉን አንሶላ፣ "አጠቢ" ያላት ማንም አልነበረም:: አጣቢዋ ሰትጨማለቅ ስታያት አቲዬ የኔ የልብ ሰው፣ "ምነው እቴ ሰው የሚተኛበት አይደለም እንዴ" አለችና እጇን ሰቅሰቃ ገባችበት::"እቦ የአጥፍወርቅ ቤርጎ አንሶላው ብትል ፎጣው አንዴት ይጸዳል" አስኪባል:: የወይዘሮ አጥፍወርቅ ልብ አቲን በልጅነት መንበር ላይ ወስዶ አስቀመጣት፤ አኔንም በልጅ ልጅነት !!

ግቢው የአኔ ነበር:: እንዳሻኝ የምሆንበት ግዛቴ:: የሳሎኑ ዕቃ የእኔ ነበር:: ጆሮ ጭው የሚያደርግ ዋጋ የተከሰከሰበት ሶፋ ላይ ሸንቼበታለሁ፤ ወተት ደፍቼበታለሁ፤ አቀርሽቼበታለሁ:: ሰዓይን የሚያሳሳውን የቡፌ ዕቃ አንኮታኩቼዋለሁ:: የወይዘሮ አጥፍወርቅን ባለ አልማዝ ፊርጥ የአንገት ሀብል ከአንገቷ ላይ በጣጥሼዋለሁ:: (የዚህ ሀገር ወርቅ አንጥረኛ አይሰራውም ተብሎ ተቀምጦ ቀረ...) የፋናዬን (እህቴ ማለት ናት - የወይዘሮ አጥፍወርቅ ልጅ) ቀይና ውብ ፊት በ•ሜጭራዋለሁ፤ ፉነዴን እንደ ሀፃን ልጅ ነበር የማስለቅሳት::

አቲዬ ስትነግረኝ ፋናዬ ከትምህርት ቤት ስትመጣ ቦርሳዋን አንዳዘለች እኔ ላይ ትጠመጠምና ድብድብ ነው:: ሱቅ የተሰቀለ አሻንጉሊት ካየች፤ የሕፃን ልብስና መጫወቻ ሳይኗ ውስጥ ከገባ፤ ለእኔ ለመግዛት ከእናቷ ጋር "ብር ስጭኝ አልሰጥም" ጦርነት ነው::

የእናቴ ንፁህ ልብ አንደስፖንጅ ፍራሽ በሕይወቴ መንገድ ላይ ተነጥፎ በዛች ቅፅበት የነበረ

ልጅነቴን እንከን አልባ አድርጎልኛል። ጥፋቴን የሳቅ ምንጭ፣ ሰቅሶዬ ለማባበል ለሚራወጡ ቤተሰቦቼ፣ "የማባበል ሰራ ጀምሩ" የሚል ደወል ነበር። የፍቅር እና የቤተሰብ ቅንጦት ቶምበላ በጠዋቱ የውጣልኝ ጩቅላ !!

ሦስተኛ ዓመቴን ልይዝ ሁለት ወራት ብቻ ሲቀሩ በእኔና በአቲዬ ሕይወት ላይ ድንገት ፀሐይ ጠለቀች። ያች ፍልቅልቅ ፀሐይ ጠለቀች። ምንም ተራራ በሌለበት፣ ምንም ደመና በማይታይበት ንፁህ ሰማይ ፀሐይ ለወትሮው በአናት ትይዬ በምትሆንበት አኩለ ቀን ድንገት ድርግም አለችና እኔና አቲዬ ድቅድቅ ጨለማ ላይ ቆምን። ብርሃን ይሁን ያለ አምላክ በቋጣ "ጨለማ ይሁን" ብሎ ያዘዘ ይመስል የዚህን ሁሉ ጊዜ ውብ ብርሃናችን በአንዲት ቅፅበት ድርግም አለ !! አንደማብራያ ማጥፊያ ቀጭ አድርጎ ድርግም !!

ድቅድቅ ጨለማ ከቀኑ ሰባት ሰዓት ላይ በጠራራ ፀሐይ አይከሰትም ያለው ማን ነው? - የፀሐይ ግርዶሽ። ማለትም ሳይንሱ ያሻውን ይበል እንጂ፣ እውነታው ወዲህ ነው። በምንወዳቸው ሰዎችና በአኛ መካከል ሞት የሚባል ግርዶሽ ሲጋረጥ፣ 'የፀሐይ ግርዶሽ' ይባላል !!

ወይዘሮ እጥፍወርቅ ለጓደኛዋ ልጅ ምርቃት ተጠርታ ወደ አዳማ ስትሄድ መንገድ ላይ እንድ ከባድ መኪና ትንሽ ዲኤከስ መኪናዋ ላይ ወጣባት። ደግ አይበረከትም !! ተረት አውሪዎች ደፋሮች ናቸው። ቀለል አድርገው፣ "ሲኖሩ ሲኖሩ ሞቱ" ይላሉ። ሞት ከተረትም ከታሪክም፣ ከዛሬና ነገም በላይ የገዘፈ ሰቆቃ መሆኑን ማን በነገራቸው። "ወይዘሮ እጥፍወርቅ ደግ ሰው ነበረች፣ ስትኖር ስትኖር በተወለደች በምናምን ዓመቷ በድንገተኛ ኤደጋ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች" ተባለ። ቢቃ!!

ስለ ወይዘሮ እጥፍወርቅ ሞት አቲዬ ለማንም ምንም ስታወራ ሰምቻት አላውቅም። እማዜር ስትደገፈው የሚወድቅ ምርኩዝ ለአቲዬ በማዋሉ ብዙ ዓመታት ቤተክስቲያን እየሄደች ወቅሳዋለች ፣ "ሰለምን ደግ ኑሮን አንቁልልጭ ትለኛለህ፣ ለተራበ ውሻ ቁራጭ ስጋ ይዞ ሲያጓጓ እንደቆየ ሰው ከጠላቶቼ ዓይን በላይ ሰቅለህ አኖርከኝ። እንዲበጫጭቁኝ ወደነሱ መልሰህ ጣልከኝ" አያለች።

እኔም ነፍስ ካወቅኩ በኋላ እማዜርን ወቅሼዋለሁ። "ዘርፌ ለመኪና ሞት ምን ይጎድላታል? አዳማ መንገድ ላይ በእሰቃቂ ሁኔታ ተጨፍልቆ ለመሞት ቀለመወርቅ ምን ያንሰው ነበር?"

ዘፋኞቹ እየተቀባበሉ፣

"መንገድ ዓይኑ ይፍሰስ አይባልም ደርሶ፣

የመሰደውን ሰው ያመጣል መልሶ" ይላሉ።

የታለ የአዳማ መንገድ ወይዘሮ እጥፍወርቅን የመለሰው? ቢሆንም እማዜር የለም አላልኩም። አቲዬ እማዜር አለ ካለች፣ ማንም ፈላስፋ ሀሳቤን ሰንዝር አያናውጣትም። እማዜርን በድፍረት

ለናፈቀው፤ ልነተርከው፤ ልነዘንዘውና ልነጫነጭበት እችላለሁ። በምድር ላይ ሰው ሁሉ ከነእናቴ ሞቶኝ እኔ፣ "እማዬር የለም" ብዬ ማን ላይ ልነጫነጭ፣ ማን ላይ ልመናቸከ፣ ማንንስ ልነዘንዝ...፤

ዘውርግጥ አይኑ ይፍለስ የተባለው መንግድ ዘርፈንና ቀለመወርቅን ወስዶ ባይመልስም ባልከፋ፤ እማዬርስ ምኑ ሞኝ እነዚህን ጥራጊ ፍጥረቶች ወደ ሰማይ ቤት የሚጠራ። እዚሁ ይጨማለቁ እንጂ፤ ይህ ላይ አፋቸውን ይከፈቱ። አስመሳይ መንደርተኛ፣ ግቆቸውን በአናቱ፣ ሰማቸውን በምላሱ ተሸክሞ ሲኖር እማዬር ሰሲኦላቸው የሚሆን ማገዶ ይሰበስቡ ዘንድ እድሜ ይጨምርላቸው። በምሳሙቱ ልደታቸውን በፌሽታ ያከብሩ !!አንድ ቀን እንደልደት ሻማ 'እፍ!' ተብለው አስኪጠፉ ! የአዳማ መንገድ አበጠላኝ። የአዳማ መንገድ ላይ ቀለመወርቅ ቀብረር ብሎ ሲራመድ ይታየኛል ልክ እንደቤቱ ኮሪደር። ቀለመወርቅ የጣረሞትን ገጸ ባህሪ ወክሎ ድራማ የሚሰራ መሰለኝ። አንዴት ነው የሚዋጣለት።

ደስ የሚለው ሃገር አዳማ መንገድ ላይም ባይሆን በመኪና አደጋም ባይሆን ዘርፌና ቀለመወርቅ ይሞታሉ !!!! (ሀሌሉያ) ያች አቃጣሪ ባልቴት ሽንሽን ቀሚሷን ጥላ አርቃኗን ትነነዛታለች። የአሜሪካ ላሞቿ አማላጅ ሆነው ገነት ያስገቧት እንደሆነ እናያለን !!

ይሄ ባለጌ ሽማግሌ ቀለመወርቅ ካፖርትና ኮፍያውን መልዐክት በር ላይ በክብር ይቀበሉትና፣ "እዚህም በክብር ልናር ነው" እያለ ሲያስብ፣ ማጅራቱን ይዘው ወደ አሳት ጉድጓድ ውስጥ በአርማጭ ይገፈትሩታል። ታዮኝ በአየር ላይ እየተምዘገዘገ ሲወርድና ቦጭረቅ ብሎ ሲያርፍ፣ አሳቱ አንደውሀ ዙሪያውን ሽቅብ ሲረጭ !! ያኔ "እሽብር ልጂ ነው" አያለ ቢቃጣጥር አሳቱ ይበርድ እንደሆነ እናያለን !! አንዴ ፊላስፋዎች ምን ነካቸው 'ሲኦል' የለም የሚሉት? ሰለቱ ካለ አፎቱን እንዴት የለም ይላሉ? ሲኦል መኖር አለበት። ቀለመወርቅና ዘርፌ አያሉ አንዴት ሲኦል አይኖርም !!

ከፍል አስራ ሦስት

ቁጥር ስፍር የሌለው ሕዝብ ለቅሶ ለመድረስ የወይዘሮ አጥፍወርቅን ግቢ አጥሰቀለቀው። ቀስ በቀስ አስተዛዛኙ አየተመናመነ መጥቶ በመጨረሻ ግቢው ወደነበረው ገምታ ተመለሰ። ከሀዘኑ በኋላ ነገሮች ሀልም በሚመስል ሁኔታ ተቀያየሩ። ሀዘኑ ባበቃ በጥቂት ወራት ውስጥ ፋናዬን ወንድሞቿ ስዊዲን ወደሚባል ሀገር ወሰዷት።

ራኒ የእኔ እህት አቲዬን ስማ በተሰበረ ልብ ግቢውን ለቀቀች። አቲ በምድር ላይ ያሷትን ሁለት ዘመዶች አጣች። ዘሬም ይሄን ስታወራኝ ዓይኗ ውስጥ ሀዘም ይንቀለቀላል። ነፍሷ ይቃትታል፤ ዝም ብላ ትቆይና፤

"እሹዋ!" ትለኛለች።

"ሱዲን የሚሉት ሀገር ወዴት ነው?"። ስዊዲን ሀገር ቤትና ሕዝብ ተቆጥሮ የሕገበ- ቁጥር ምንትስ ሚሊየን ደረሰ ቢባል አቲዬ አታምንም። የስዊዲን ህዝብ ቁጥር 'አንድ ብቻ' ነው ፋናዬ ብቻ !! አቲዬ የዛችን ደግ ሴትዬ ልጅ ፋናዬን እንደ አየሩሳሌም አንድ ቀን ልታያት ፀኑ መሻት ፊቷ ላይ ይንቀለቀላል።

አንዲት እድሜዋ አርባ የሚሆን ሽቅርቅር፣ ሲበዛ ቆንጆ የሆነች ሴትዬ (የወይዘሮ አጥፍወርቅ አህት ናት ይላሉ።) ከሁለት ጨምላቃ ሴት ልጆቿ ጋር፣ ወር ሳይሆን ጠብቂ ተብላ እግዜር ይወቅ ብቻ ግቢውን ትኖርበት ጀመረ። ሆቴሉ ተሸጠ። እች ሴት አስቴር ትባላለች። ምኗም የማይጨበጥ ተልካሻ ሴት ! ከዕድሜዋ ጋር ጦርነት የገጠመች 'ማቶ' !

አንዳንዴ በተረት የሚታወቀው አስማተኛ መስተዋት መኝታ ቤቷ ውስጥ የተቀመጠ ይመስል ጉብታ በወጣች ቁጥር ልብስ የምትቀይር፣ "የሆነ ቦታ በመልክ የምትበልጥሽ ውብ ሴት አለች" እያላት መስተዋቱ፣ ፊቷ ላይ የትራስ ሰንበር ከሚወጣ ኢትዮጲያ ላይ ከሰሜን እስክ ደቡብ ጫፍ አዲስ ስምጥ ሸለቆ ቢፈጠር የምትመርጥ የውበት ሰሲታም !! የዕለት እንጀራዋ የሰው ዓይን የሆነ ከንቱ፣ የአጥፍወርቅን ግቢ በባለቤትነት ታስተዳድር ጀመር።

አቲዬን አንደ ሰራተኛ ስለምታስባት ማመናጨቅ የጀመረቻት ሾ የሀዘንተኛው እግር ጨርሶ ሳይጠፋ ነበር። እኔንማ ግልገል ሰይጣን አድርጋ ነው የምታየኝ። በወይዘሮ አጥፍወርቅ የለመድኩትን መዘባነን ታጥቄ ወደ ሳሎን ዘው ስል በቲሸርቴ አንጠልጥላ መሬት ለመሬት እየጎተተች በረንዳው ላይ የመወርወር ያህል ትጎትተኝና፣ "ማነሽ አንች ልጅ ነይ ወደዛ ውሰጅ ይሄን ልጅሽን ! አንዴ የምን መጨማለቅ ነው አሱ...ሁለተኛ አዚህ ምንጣፍ ላይ ሲወጣ እንዳላይ!" ብላ እጇን ታራግፋለች።

አቲዬ ነፍስና ሰጋዋ አየተሟገቱ መወልወያ ይዘ ትገባና ያበላሸሁት ነገር ካለ ትፈልጋለች። ብዙ ጊዜ ግን የዚህች ከንቱ ጩኸት ምክንያት አልነበረውም። ምክንያቷ ሰው አለመፈለግ ነው። ሰውን በማራቅ ሰላም ይገኝ ይመስል ! ሁካታ ነፍሷን ሀቅ አጉርሳ ዝም እንደማሰባል የቀረባትን ሁሉ ታፍናለች።

በዚያ ከወራት በፊት ምግብ ይልከሰከሰበት በነበረ ግቢ ውስጥ ጣረሞት ረሀብ ያንዣብብ ጀመረ፤ በፊት ወተት የምትገዛልኝ አጥፍወርቅ ነበረች። መሰቧ መሰባችን፣ ድስቷም ድስታችን ነበረ። አንዲህ ባጭር ጊዜ ከጓዳችን ቁራሽ ዳቦ፣ ንጣይ አንጀራ ይነጥፋል ብሎ ማን አሰበ !!

አንዳንዴ ምኞት ያዘናጋል። ምኞት ስትኖርበት ዘላለማዊ ይመስላል። ሜዳ ላይ ጥሎህ እንደ ጉም ሲተን ነው ፊቱ ላይ ቀዝቃዛ ውሀ እንደቸለሱበት ሰው የምትበረግገው። ስንቱ ቤተሰብ ድንገት ከምኞቱ በችግር ተኮርኩሞ ነቅቷል። ስንቱ ባለስራ ስራውን ተደግፎ፣ ድጋፉ ሲከዳው ወድቆ ቀርቷል። ስንቷ ባለትዳር፣ የባሏ እጅ ሲነጥፍ አብሮ ቅስሟ ተሰብሯል። አማኙቶ ማጣት ብሎ ህዝቡ የሚጠራው ይሄንን አይደል - ተገኝቶ መጥፋት ቢሉት ይሻል ነበር !!

አስቴር አቲየን ታዝዛታለች፣ ታመናጭቃታለች፣ ትልካታለች፣ ግን ብርም ሆነ ምግብ አትሰጣትም፤ የሚገርመው ደግሞ ቤቱ ውስጥ አንጀራ አይጋገርም ወጥም አይሰራም። እናትና ቦዘኔ ልጅቷ የታሸገ ነገር ይገዙና መኪናውም ውስጥ መንገድም ላይ ይበላሉ፣ ማሸጊያውን ወዳገኙበት ይወረውሩታል። እነዛን ደማቅ ጽሑፍ ያላቸው የቸኮሌት ላስቲኮች በርሀብ እየተንሰፈሰፍኩ ቀድጄ የላስኩባቸው ጊዜያት ብዙ ነበሩ - ዛሬ ቸኮሌት እንደ መርዝ አጠላለሁ !! እነዛ ባዶ የፍራፍሬ ሜመሚቂ ዕቃዎች ስይት ነበሩ ለኔ። ዘመናዊነት ያደነዘዛቸው እናትና ልጆች - ምኞት ውስጥ የመነኑ የስንፍናና የከፋት ቆብ የጫኑ ርኩሶች ነበሩ። እንኳን ግቢያቸው ውስጥ ለተጠጉ ሚስኪኖች፣ አርስ በርሳቸውም የተለያዩ የሰው ክብቶች።

መኝታ ቤታቸውን በየፈናቸው ዘግተው፣ ማንም አራት እግሩን ቢበላ አልሰማንም አላየንም ብሎ የሚፈክህ ጋግርታም የግለኝነት ባሕር ውስጥ የተጠመቁ። የምዕራባዊያኑን ቆሻሻ ግለኝነት የስልጣኔ አልፋ፣ የዕውቀት አሜጋ ያደረጉ ፉዞዎች። በእንግሊዝኛ እየተለፋደዱ፣ በአማርኛ የአዕምሮ መቃወስ ውስጥ የተዘፈቁ የቤት ዕቃዎች። የሞራልም ይሁን የሀይማኖት፣ አልያም ከነፍስ ስልጣኔ የሚመነጭ ጠንካራ ስብዕና የሌለው ኢትዮጲያዊ። ውጭ ሀገር ደርሶ ሲመለስ ምን አይነት አስቃቂ 'ማቶ'ነት ውስጥ እንደሚነከር የታዘብኩት በእነዚህ ከንቱዎች ነበር። አናታቸው ሀያ ዓመት፣ ልጆቹ እየሄዱ እየመጡ ከአስር ዓመት በላይ አሜሪካ ኖረዋል። አስቴር ታዲያ ለዓመታት ከኖረችበት አሜሪካ ምን ይዛ መጣች? ሰምቻታለሁ ለመጣ ለሄደው፣

"እበሻ ሰራ አይወድም፣ ነጮቹ እኮ ለሰዓት ያላቸው ከብር ለሰራ ያላቸው..."

"እበሻ የተመጣጠነ ምግብ አያውቅም - ማድፋፋት፣ ጥሬ ከብሰል ማጋበስ..."

"እበሻ ሙች ንፅህና ይወዳል ነጮቹ እኮ..."

"ኤዲያ የሀበሻ ወንድ ሙች ሴት ያከብራል - ነጮቹኮ"

"የእበሻ ልጅ አስተዳደግ..."

"የእበሻ ሕክምና ደግሞ ራሱ በሽታ ነው። ነጮቹ እኮ"

"እበሻ ገንዘብ ከመሬት የሚታፈስ ነው የሚመስለው። ዓይኑን በጨው አጥቦ፣ 'ዶላር ላኩ ነው፣ ነጮቹ እኮ አስራ ሰምንት ዓመት ከሞላቸው..."

ኮሮ የባርነት ቀንበር ጫንቃዋ ላይ ተሸክማ የምትደሰኩር ቱልቱላ። ከየትም የፈለፈለቻቸው ልጆቿ በአስተዳደግ ይሁን በግል ባህሪ ምን ዓይነት እናት እንደሆነች ጮክው አያወጁ፣ "ዓይናቸሁን ጨፍኑ ላምናችሁ" ትለናለች።

የነጮቹ ፅንፍ የለሽ ውክቢያ ዕድሜዋን ሙሉ ያጨቀባት የታላቅነት አባዜ 'እበሻን በበጎ እንዳታይ

እንደ ጋሪ ፈረስ ቀይዷት፣ ለእግዜር ሰላምታ የቀረባት ሁሉ የፈጋችበትን ዶላር የሚነጥቃት እየመሰላት ስጋዋ ያልቃል። ልጆቿም በየአጥሩ ጥግ ከሚያናጋቹት የለበሻ ወንድ ጋር ሲሳሳሙ እና በየመሸታ ቤቱ ሲዳሩ ከማምሸት ውጭ የፈየዱት ተዓምር የለም። በነፃይቱ ሀገር ኖረው ለመጡ የሰልጣኔ ጥጎች፣ የከንፈር ዋጋው የዶላሩን ያህል ውድ አይደለም። እነዛ ወንበር ሰበው በከብር ሴትን ልጅ የሚያስቀምጡ 'ነጫጭ ወንዶች' የሴትነትን ከብር እየሰበኩ ሰብዓዊነታቸውን ከአግራቸው ስር እንደጨፈላለቁት ለመረዳት የጋረዳቸው ነጭ ይመና አይፈቅድላቸውም !!

ለእነዚህ የሰልጣኔ ርዝራዦች የሰው ልጅ ስለከብሩ መኖር፣ ስለማተቡ ዓለማዊነትን 'በልከ ይሁን' ማለቱ 'ተራ መኮፈስ' ነው። በርሳቸውን ከመከፈት፣ ለማንም አላፊ አግዳሚ እግራቸውን መከፈት ይቀላቸዋል። ምክንያቱም "ዶላር - የተከበሩት የነጮች ውድ ቅርስ" ሲሆን ሰውነታቸው ግን የርካሾቹ፣ የሰነፎቹ፣ ያልተማሩት፣ ሥራ የማይወዱት፣ ብር ከመሬት የሚታፈስ የሚመስላቸው አበሾች ርካሽ ንብረት ነው።

በዚህ ፍልስፍና እገሩን አጥምቀውት አገሬው ፈረንጅ ባል ፍለጋ ሲራኮት ቢታይ ምን ይገርማል !!

አቲዬ አንድ ቀን እየፈራች ሴትየዋን አናገረቻት፤ "እትዬ ወጥቼ አንዳንድ ስራ ልሰራ ነበረ ምናልባት ከፈለጉኝ ብዬ ነው..."

"ስራሽ ምንድን ነው?" አለች ሴትዬዋ አቲዬን ከታች አስከ ላይ እያየቻት።

"እኔ እትዬ እጥፍወርቅ ጋር እንጀራም አጋግራለሁ ያው ለሆቴሉ፣ አዚሁ ነው ስራዬ ሌላ ምን ስራ አለኝ"

"እኔ የማሰራሽ ነገር የለም። ውጭ ነው የምንበላው። ልትሄጂ ትችያለሽ።" አቲዬ ደነገጠች።

"ቀን ቀን ስራ ሌላ ሰፍራ እየሠራሁ፣ ለማደሪያዬ አዚሁ ቢፈቅዱልኝ። መሄጃም የለኝም፣ ከነልጄ ለነፍሴ ብለው እትዬ እጥፍወርቅ አስጠግተውኝ ነው..."

"ኤጭ አበሻ ሲባል 'የነፃ ራት' ካልበላ አንቅልፍ አይወስደውም። ጤነኛ ነሽ፣ አግር እጅ አለሽ፣ ሰርተሽ ሳትሳቀቂ ቤት ተከራይተሽ መኖር ሰትችይ አስጠግተውኝ ቅብርጥሶ ማለት ምን አመጣው፣ ነጮቹ ቢሆኑ..." ደሰኮረች። አቲዬን አዛ መቆየቷ ብዙም ደስ አላላትም፣ ቢሆንም አንዳንድ ሥራ ማሠራቱ አንዳለ ልቧ አውቆታል። 'የነፃ ጉልበት' የማይፈልግ የነጭ አድናቂ ማን አለና። አናም አቲዬን እንዲህ አለቻት፣ "እንግዲህ ያው ፀባይሽን አሳምረሽ ኑሪ፣ እኔ ጫጫታ ምናምን አልወድም። ቤቱን ከፈለግኩት በማንኛውም ጊዜ ትለቂያለሽ..."

አቲዬ እኔን አዝላ ወደረሳቸው መንከራተት ተመለሰች። አዲሳባ ውስጥ የምታውቀው መንደር አንድ ነው ፣ አዛም ቀለመወርቅና ዘርፌ አሉ..! አሳ ነባሪዎቹ ሦስት ዓመት ፀሐይ ሳይነካት ብርቱካን መስላ የወጣችውን አቲዬን ሲያዩ ጥርሳቸውን አፏጩ። ቀለመወርቅ ደቆሩ ምራቁን

አየዋጠ እንደገና ተመኖት። ሰላማረባት መንደርተኛው በሙሉ ጠላት። ዘርፌ የክቱት ልምጯን አዘጋጅታ ነበር የጠበቀቻት።

ከከፍታ እንደመውረድ ውርደት፣ ረግጠው ወዳለቆት ነገር እንደመመለስ ታላቅ ሰቆቃ የለም፤ የራስህ ወገኖች መብረር ስትጀምር 'አሰይ' ከማለት ይልቅ ክንፍህ ተሰባብሮ አግራቸው ስር ወድቀህ ስትፈጠፈጥ ለማየት ይጓጓሉ። እናም ስትወድቅ ይረካሉ። 'ብዬ ነበር፣ እያችሁ እየተባባሉ የምቀኝነት ትንቢታቸው የሰመረላቸው ምቀኛ ኅብያት ይንጫጫሉ። ብሔራዊ ምቀኝነት የተጠናወተው ሕዝብ እንደኛ ይኖር ይሆን? "ለምን በደፈናው አንሰደባለን?" ይለሀል 'ምቀኛ ስትለው የተዳፈነበት አመክንዮ እየደረደረ፣ 'ሁሉም አንድ አይደለም' ይልሀል፤ ግን ሁሉም አንድ ነው። ጠጥቶታል እንደ ውሃ፣ በልቶታል እንደ እንጀራና ጥሬ ሰጋው !! ቢማርም፣ ቢያገኝም፣ ምቀኝነቱን ያዘምናታል እንጂ ቢሞት አይጥላትም፤ ማተቡ ናት።

ከዚህ በኋላ የሆነውን ዝርዝር ነገር ስናገር ማንንም ሳይሆን ራሴን እጠላለሁ። አቲዬ በሲጋም በነፍስም የቀለመወርቅ መጫወቻ፣ የዘርፌ ገረድ ሆና ኖረች። ለሰንት ዓመት...። ዘርፌ ቤት የመይሀኒያለም ዝክር፣ አከሊት ቤት የኪዳነምህረት ዝክር፣ አሻሮ፣ የጠላ ቂጣ፣ ድፎ ዳቦ። የአከሊት ልጅ ልታገባ ነው - ወጥ ሰሪ፣ ጠላ ጠማቂ። ሲወልዱ - ልደት፣ ከርሰትና - አሳት በላት አናቴን።

ውበቷን ጤናዋን ወጣትነቷን አሳት በላው። አቲዬ እንደብረት ምጣድ አሳት ላይ ተጥዳ እኔ የምባል ጣፋጭ ኬክ በላይዋ ላይ በሰልኩ። ይሄ ሁሉ ሥራ በዚህች ሚስኪን ሴት ላይ ተጫኖ፣ ማታ ወደ ማደሪያዋ ስትመለስ የአስቴር ጨምላቃ ሴት ልጆች የውስጥ ልብስ ሳይቀር በየቦታው ተወርውሮ ይጠብቃታል። ቀን አናትና ልጆች ሲወጡ ወንድ የሚራኮትላቸው ዘናጮች፣ ሽቷቸው ከራቅ የሚጣራ ሽቅርቅሮች፣ የቤታቸውን ጉድ ወላድ አይየው! እነዚህ በየአደባባዩ ሽቅርቅር የሚሉ ሰዎች ቤታቸው የዝርክርክነት ጥግ የሚሆነው ለምንድን ነው ግን ? ብዙ ሰው አየሁ - ብዙ ሽቅርቅር !!

ሴት ልጅ ቢያንስ የውስጥ ልብሷን የራሷን ገመና አንዴት ሌላ ሰው እንዲያጥብላት ትፈልጋለች - ለዛውም በየካፍቴሪያው ተጎልተው ሲገለፍጡ የሚውሉ ስራፊት ሴቶች። አይቻለሁ በአስቴር ልጆች ! እናታቸውም ያው ናት። የዘር ነው መቆሸሸ። ከማን ይማራሉ? ያኔ ነው ረጅም ጫማ አድርጎ ከመቆነን በፊት፣ ፀጉር እየነሰነሱ 'አገር ይየን!' ከማለት በፊት፣ 'ሴት' ሲባል ፊቴ የሚደቀነው ይሄው ፅንፍ አልባ ስንፍና ነው። የሴት ልጅ ስንፍና እንዴት ይቀፋል? መንገድ ላይ ሰበር ሰካ የሚሉ ሴቶች ሁሉ ከውበታቸው በፊት መታጠቢያ ቤታቸው ነው ዓይኔ ላይ የሚደቀነው።

ድንገተኛ ፍተሻ ይደረግ ቢባል፣ ከዝርክርኩ ወንደላጤ፣ ካልሲ በየቦታው ከሚጥለው ወንድ የባሰ ሰንሰ ጉድ ሴቶች አሉ፣ ስንትና ስንት ወር ሙሉ ሰው ሰራሽ ፀጉር አናታቸው ላይ ጀልቶ መሬት አይነካን የሚሉ። በዛ የልጅነት አድሜዬ ተላላኪነትን በተማርኩባት፣ ለሙናር ስል የመሸቆጥቆጥን እርምጃ ዳዴ ባልኩባት በህይወት ውጣ ውረዴ ነበር "ሴትነት ደራሽ ንፋስ የሚከምረው፣ ደራሽ

ንፋስ የሚበትነው የምድረ በዳ የአሸዋ ከምር ነው" ብዬ በሴት ተስፋ የቆረጥኩት:: የአስቴር ልጆች፣ 'ሴት' መሰለውኝ !! መቼስ በሕይወት ውስጥ ሕይወትን አጠናግረን እንድንመዝናት የሚያደርጉን አባይ ሚዛኖች አይጠፉ::

ክፍል አስራ አራት

መማርን ጌታ ይባርከው !! 'መማር መቃጠል ነው' ይላሉ ተምሮ ማቃጠል ለአኔ ዓለሜ ሆነች !! ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት እንደኛ ከፍል አስከመዘገብ የአባት ስም አልነበረኝም:: አሸብር ብቻ ነበርኩ:: ልክ ትምህርት ቤት አቲዬ ወስዳኝ ስመዘገብ ጉጉት የመሰለው መዝጋቢ የእናቴ ድሪቶ ቀሚስ ለዓይኑ ቀፎት አያመናጨቃት አይቼዋለሁ:: ተመዘግቤ ስንመለስ አቲዬ ከፊቱ ዞር ስትል፣ ፊቱን አጨፍግጎ መጥፎ ጠረን እንደሚያባርር ሰው በግራ እጁ አየሩን እያራገበ ሲያባርር አይቼዋለሁ::

በአርግጥ አቲዬ እማማ የብርጓል ቤት እንኩሮ እያነኮረች ነበር:: "ምዝገባው ዛሬ ነው የሚያልቀው ሲሏት ብድግ ብላ ነው የመጣችው:: ቢሆንስ ልክ ቆሻሻ እንደሸተተው ሰው ሰው እንዲያየው አድርጎ አጁን ያራግባል እንዴ...:: የእማማ የብርጓል ቁጥር አንድ የጠላ ደንበኛ እንዳልሆነ ሁሉ:: ሊያስተምረን ከፍል ውስጥ ሲገባ እንደባቡር ሀዲድ የረዘመ የጠላ ትንፋግ ተከትሎት እንደማይገባ ሁሉ - ኑበር አየው ያንን የውሻ ልጅ:: አስተማሪውን እንደጠመድኩት ጡረታ ወጣ !! ደግሞኮ አያፍርም መንገድ ላይ ላገኘው ሁሉ፣ "እኔ ነኝ ያስተማርኩት" እያለ በኩራት ያወራል:: በርሱ የትምህርት ዓይነት ብቻ ዶክተር የሆንኩ ይመስል!!

"ስም ?" አላት አቲዬን ድሮ::

"የአኔን ነው ?" አለች እየፊራች::

ፊሪ ነበረች እናቴ:: ፊሪው የአዲስ አበባ ሕዝብ እንደያቅሙ ደሀ ማስፈራራትን ተከናበታል::

"አጉኮ ነሽ እንደኛ ከፍል የምትመዘገቢው?" አላት:: አጠገባችን ያሉት ሁሉ ሳቁለት:: አቲዬ ተሳቀቀች:: ሰውነቷ ሽምቅቅ ሊል ቀሚሷን አንቄ ተሰምቶኛል መሸማቀቋ::

"የልጅሽን ስም ንገሪኝ ሴትዮ" አላት እያከላፈታት::

"የእሱ አ..ሸብር...አሸብር ነው ስሙ" አለች ራሴን እያሻሸች::

"የአባት ስም ?"

"አባ...ት" ብላ ዝም አለች::

"የአባቱ ስም ማነው..."

ሳቅ። "መጨረስ አልቻለችም። ቀለመወርቅ ልትል ፈልጋ እንደነበር የነባኝ ካደግኩ በኋላ ነው።
ግዘራም ደግሞ የጉድ ናት። የልጇም አባት የሚጠፋት..." ብሎ እንደኖና እንዲስቁለት ሰምቼን
አየ። ያልደመቀ ሳቅ ተሳቀለት።

"ብይ ወደዛ ሁኝ! ስታስታውሽ ትመለሻለሽ፤ ተረኛ ቀጥል!" አለ አስከርቢቶውን እያወናጨፈ።
(አልረለትም ግማሽ ድረስ ቀለሟ ያለቀ ሰሚያዊ ቢከ አስከርቢቶ።)

አናቴ ከእንቅልፉ እንደባነነ ሰው፤ "በአምላከ...በአምላክ ነው የአባቱ ስም።" አለች።

መዝጋቢው ራሱን ግራና ቀኝ በብስጭት እያወዛወዘ መዘገበኝ።

የአባት ስም - በአምላከ (በእምላከ አባቴ አይደለም። አቲዬ ለአምላክ ሰጠችኝ።) የሃምሳ ብሩ
ቢገርመው፤ ለአግዜር ሰው አበደረችው አቲዬ። የእኔ እናት በሕይወት ባንክ ውስጥ ብድር
ለሚመልስ ብድር በመስጠት የተካነች ባለሙያ ነበረች - ነገን የምታይ !! አግዜር የተበደረው
ትውልድ፤ ወለዱ የተባረከ ዘር ማንዘር ነው። "አስክ ሺ ትውልድ ዘርህን እባርካለሁ።" ብሏል
ራሱ አግዜር !!

ትምህርት ቤት ገባሁ...!!

ከፍላችን ልጆች የኑሮ ደረጃ በዳግማዊትና በእኔ መካከል የተወሰነ ነበር። ዳግማዊት የሚታዘል
ባለዚፕ ቦርሳ ያላት ቆንጆ አንደኛ የሀብታም ልጅ ስትሆን፤ እኔ ከሸራብ የተሰራች ኮሮጆ የነበረኝ
አንደኛ የደሀ ልጅ። ይሁን እንጂ በንፅህና አልታማም። ልብሶቼ ሁልጊዜም ንፁዎች ነበሩ -
ንፁህና አሮጌ። ሰኞ ሰኞ ሰልፍ ሜዳ ላይ የእጅ ጥፍሮቻችን ሲታዩ ንፁህ ጥፍሮቼን በኩራት
ነበር የምዘረጋው። የዳግማዊትን ያህል በፈገግታ "ጎበዝ" ባልባልም፤ ከቆሻሻና ከስንፍና የተጣላች
ቆራጥ ደሀ እናት አለችኝና ስንፍናና ቆሻሻ አጠገቤ ዝር አይሉም !! (ሰው ወዶ አይደለም ለካ
ዘራፍ የሚለው።)

አንድ ቀን ግን በሕይወቴ ሰላቀቅበት የኖርኩበት ነገር ተፈጠረ።

አንዳዱ አስቴር ከዋናው ቤት አሮጌ ፍራሽ (የሆቴሉ አልቤርጎ ውስጥ የነበሩ።) እና ሌሎችም
ዕቃዎችን ከዕቃ ቤቷ አስወጥታ እኔና አቲዬ የምንኖርበት ከፍል ውስጥ አስቀመጠች - እንደዕቃ
ቤት። አናም ቤታችን ውስጥ በታጨቀው ዕቃ ምክንያት ቤቱን እንደ ልብ ማፅዳት በለመቻሉ
ቁንጫ እንደጉድ ይፈነጭ ጀመረ።

ጋሽ መሀሪ አካባቢ ሳይንስ መምህራችን ነበር። ሲያስተምር ስወደው። የርሱን ትምህረት አስር
ካስር ነው ሁልጊዜም የምደፍነው። እኔ ስለምወደው፤ የሚወደኝ ይመስለኝ ነበር ። እንድ ቀን

ግን ዘላለማዊ ጠላቴ ያደረገውን የማይረባ ነገር አደረገ ::

ሰለ ጓሮ አትክልት ጥቅም እያሰተማረ ነበር:: ድንገት ዳግማዊት፣ "ዋ...ይ" ብላ ጮኸች:: ቦርሳዋ ላይ ሁለት እሳት የመሳሰሉ ቁንጫዎች ዘለውባት ነበር:: የከፍሉ ልጅ ሁሉ በድንጋጤ ወደ ዳግማዊት ዞረ:: መምህሩ ሁኔታውን ሊያጣራ ከምኔው አጠገባችን እንደደረሰ አንጃለት::

"ምንድን ነው?"

"ቁ..ን...ጫ" አለች ለቅሶ በሚመስል ሞልቃቃ ድምፅ::

እኔ ከዳግማዊት ጎን ነበር የምቀመጠው:: ባልገባኝ ምክንያት ተቆጣ::

"እስቲ ቦርሳህ" አለኝ:: በቃ እንዲህ ነው ያለኝ:: ከወንበሩ ስር ከተሰራው የደብተር ማስቀመጫ፣ የሹራብ ኮሮጆዬን አወጣሁ:: በዚህች ቅፅበት የተከሰተው ነገር አሰደንጋጭ ነገር ነበር:: በርካታ ቁንጫች ከእኔ ኮሮጆ ላይ ተፈናጠሩ::

መምህር መሀሪ ፊቱን አጨፍግጎ ኮሮጆዬን አነሳና ወደፊት ወደ ጥቁር ሰሌዳው ወረወረው:: ደብተሮቼ በአየር ላይ ወረቀታቸውን እያርገበገቡ ተበታተኑ:: (አስከዛሬም ደብተሮቼ በአየር ላይ እየተንሳፈፉ ይታዩኛል - አላረፉም::)

"ውጣ ጆሮህን ያዝ!" ብሎ በኩርኩም አፈለሰኝ:: ወጥቼ ጆሮዬን ያዝኩ:: ከኩርኩሙ በላይ ሀፍረቱ ጠዝጥዞኝ ነበር::

የታፈነ የጓደኞቼ ሳቅ:: በትምህርት አልችለኝ ሲሉ እችን እንደውድቅት፣ እችን ከአነሱ እንዳነስኩባት አጋጣሚ ሊጠቅሙባት:: የእቃኝነት ልጆች...ስንቱን ትምህርት ስደፍን ለጭብጨባ በመከራ የሚነሳ እጃቸው፣ ዛሬ ሳቃቸውን ሊያፍን ወደ አፋቸው ተወነጨፈ::

ቡፍ...ቡፍ...ሂሂሂ...

መምህሩ መሀሪ (ስሙን ቄስ ይጥራውና!) ሰለጓሮ አትክልት የፃፈውን አጥፍቶ ጥቁር ሰሌዳው ላይ፣

"ተሰቦ" ብሎ በትልቁ ፃፈና ከሰሩ በድርቡ አሰመረበት:: ያውም አረንጓዴ ቀለም ባለውና እንደ ብርቅ በምናየው ጠመኔ !!

ከዛም ሰለተሰቦ ሙሉ ከፍለጊዜውን ሲለፈልፍ ዋለ::

"አያችሁ...ልክ እናንተ ወደ ትምህርት ቤት ወይም ዘመድ ለመጠየቅ በታክሲ፣ በአውቶብስ ተሳፍራችሁ እንደምትሄዱት፣ ቁንጫዎችም በአይጦች ተሳፍረው ንፅህናው ወዳልተጠበቀ ቤት ይሄዳሉ:: አሁን እሱ ደብተር መያዣ ላይ እንዳያችሁት (እኔን አየጠቆመ)፣ ንፅህናው ባልተጠበቀ

የልበስ ሻንጣ፣ የደብተር መያዣ፣ በሴላም ቁሳቁሶች አማካይነት እየተንጠላጠሉና እየተደበቁ ከቦታ ወደ ቦታ በመንቀሳቀስ፣ እንደ ዳግማዊት ዓይነት ንፁህ ልጆች በተሰበ ይያዛሉ..." በማለት አስቶማረ፡፡ ምን ያስተምራል አስተማሪ የሚባለው ነገር የጠላት ሰም እንዲመስለኝ አደረገ አንጂ !! ለረዥም ጊዜ 'ተሰቦ' እያሉ ጓደኞቼ ያበሽቁኝ ነበር፡፡ ከአርባው ስንፈተን ግን ሰለተሰበ ተጠይቀን የደፈነኩት እኔ ብቻ ነበርኩ፡፡ ሰው ሰድቡን አይረሳማ !! በተሰይ እኔ ስድቤን አልረሳም !! መሰቱን አልረሳም !!

ስድበና መሳቱት እንደ አረግራጊ ሳንቃ ሽቅብ ተኩሰው በቀል የሚባል ጨረቃ ላይ የሚያሳርፉኝ ሮኬቶቼ ነበሩ፡፡ እንዲያ ካልሆነ በቀል መቼ አምሮ !! የሰደበኝን ሁሉ አልለቀውም !! ለምን ዘላለም አይኖርም፣ አልረሳም፣ የአዲስ አበባ ሕዝብ ሂትለሩን አቅፎ አያሳደገ መሆኑን መች ጠርጥሮ? ለፋሽስቱ እድገት ኩርኩምና እርግማን እያዋጣ እንደሆነ መቼ ቀልቡ ነግሮት? ሬዲዮና ቴሌቪዥኑ ኢድንቁሮት፣ ፊልምና ድራማው አሳውሮት፣ ሽቅርቅሮቹ ልቡን አጥፍተውት፣ ሕዝቡ ምን አያሰደገ እንደሆነ አያስተውልም !! በኢያንዳንዱ መንደር አለ የተገፋ ሕፃን ሂትለር - የሕዝብ ንቀትና ጥላቻ በከፋት ያፈረጠመው፡፡ በቀጥታ ሳይሆን ሲያውቁ ለልጆቻቸው በሚያለብሱት ልብስ፣ በሚያገምጡት ኬክ፣ እንቁልልጭ እያሉ አርፎ የተኛ ረሀቡን ቀስቅሰው ያስነኩት - የቆሰለ አቦሸማኔ አለ፡፡ ሕዝብ ጠላቱን የሚጠብቀው ድንበሩ ላይ ወታደር አሰልፎ ነው፡፡ አገርና ሕዝብ ንፋስ እንደገረሰሰው ዛፍ ከስራቸው ተነቅሰው የሚወድቁት ግን ውስጣቸው ባሳደጉት ጭቆና፣ ባፈረጠሙት የጥላቻ ከንድ በተደቆሱ ግለሰቦች ነው፡፡

ሕዝቤ ያሳረፈብኝን የጥላቻ ኩርኩም ነገ በጅምላ አልቂት አከፍለዋለሁ - ብቻ ልደግ !! ማሪያምን አልለቀውም ይሄን ሕዝብ፡፡ ደግሞ ብቻዬን አይደለሁም - ይሄ ሁሉ ተገፍቶ ጎዳና የሚንከራተት ሕፃን፣ ነገ ተንደላቅው የሚማሩትን ቆንጆ የለበሱትን ልጆችህን ሕይወት ያመሳቅለዋል፡፡ የዘራኸትን የጥላቻ ፍሬ ታፍሳታለህ፡፡ ነገ የበደልከው፣ ያከላፈትከው፣ የረገምከው ሕፃን አጅ ላይ ትወድቃታለህ፡፡ ያኔ በቀሉን በሀ-ለት እጅህ ትቀበላለህ፡፡ ድፍን አገር ይሰማ ተቀምጠችሁ የሰቀላችሁትን ቆማችሁ ማውረድ የሚያቅትባችሁ ቀን ይመጣል፡፡ ...ቱ !! እሸብር አይደለሁማ !! እንዲህ ነበር ሁሌም የምለው፡፡

እኔ ዶክተር አሸብር የሚለኪን አናቴን በደል የምከፍልበትን የመጨረሻውን ክፉ በቀል እያሰብኩ ነው ያደኩት፡፡ ኒውክሌር ቦንብ ቢኖረኝ እያልኩ፣ ወለጄ ቀለመወርቅ ጣቢ አጥለውና ቁልቃን አሜነዋለሁ፡፡ የቀለመወርቅ ባርኔጣ ከነራስ ቅሉ በርሮ ኪንያ ጠረፍ ቢገኝ ግድ አለኝ? እነዛን የአሜሪካ ላሞች እንደ አ.ላማ ፊት ለፊት አቁሜ በመድፍ ነገር ሆዳቸውን ብደረማምስው፣ ወተታቸው ወደ ሰማይ ጎኖ አዲስአበባ ላይ እንደ ነጭ ዝናብ ቢዘንብ...እችን ያህል ሊሰማኝ ነው? ወተታቸው ወደ ሰማይ ጎኖ አዲስአበባ ላይ እንደ ነጭ ዝናብ ቢዘንብ...እችን ያህል ሊሰማኝ ነው?

በአውቶሞቢል፣ በታክሲ፣ በአውቶብስ የሚጓዘውን ሕዝብ እንዳች ኃይል ኖሮኝ አፋፍሼ ቀበና ብከተው አይወጣልኝም፡፡ የአሳት ዴንጋይ እንዲያወርድ አማዚአብሄርን ብዙ ቀን ለምኜዋለሁ፡፡ ብከተው አይወጣልኝም፡፡ የአሳት ዴንጋይ እንዲያወርድ አማዚአብሄርን ብዙ ቀን ለምኜዋለሁ፡፡ 'ለአነዚህ ሚን ዝም ሊል፤ "እግዚአብሄር ለአዲስ አበባ ህዝብ አዝኖ ሳይሆን ህዝቡን ተፀይፎ፣ 'ለአነዚህ ሚን

አላት ያባክናል?' ብሎ ትቷቸው ነው" እያልኩ አሰብለሁ።

ቢሆንም አንድ ቀራፎ አስተማሪ አቃጉ ከፈተብኝ ብዬ አልተዘናጋሁም። ብዙ ሰዎች ጎበዝ ተማሪ ነህ ሊሉኝ ይገርመኛል። እኔ ምንም የተለየ ነገር አላደርግም። አስተማሪው ሲናገር፣ የግፍኩትንም ሳነብ፣ ከዚህ በፊት የማውቀውን ታሪክ የምሰማ ነበር የሚመስለኝ። ፈተናዎችን ሁሉ እኔ ራሴ ያወጣኋቸው አስኪ መሰለኝ ነበር መልሶቻቸውን ጠንቅቄ የማውቀው። በትምህርት ቤታችን ማንም ጎበዝ ነኝ የሚል ተማሪ ሊያድግ ከእኔ ጋር እኩል ለመሆን ይመኛ ነበር ብል ማጋነን አይሆንም። እነሱ አስከሚያድጉ ቆሜ አጠብቃቸው ይመስል !! "የዛሬ ምናምን ዓመት አሸብር የደረሰበት እንደርሳለን" የዛሬ ምናምን ዓመት አሸብር የኒውክሌር ቦምብ ባለቤት ይሆናል.... በምምም

ምናልባት አዚሁ የቀረችው ልጁን ስለወደደችው ይሆናል።

መጀመሪያ መኪናውን ውጭ ጋር ያቁምና ተያይዘው ይሄዱ ነበር። ከመሄዳቸው በፊት ዋጋ ቢሏ ትጠራኝና "አሸብር ና እችን መኪና ወልውል!" ትላለች።

ጣጢዬ አሁን እኮ ነው ያሳጠበኳት!" ይላታል። አርሱ የዋጋ ቢሏ መልዕክት ተንቀጥቅጦ የሚታዘዛት ሚስኪን መኖሩን ማሳየት መሆኑን መቼ አውቁ።

ቆይቶ አቤት አየገባ መቆየት ጀመረ።

"አሸብር ና ለስላሳ ግዛ ና ቢራ ግዛ" ብታምኑም ባታምኑም ኮንዶም ሁሉ ታስዝኝ ነበር። መላላኬ ሳይሆን በዛ እድሜ ፋርማሲ ሂዶ ኮንዶም መግዛት ያሳቅቀኝ ነበር። ፋርማሲስቶቹ በትዝብት ያዩኛል፤ "የተቀደደ ሱሪውን ሳይቀይር..." በሚል ግርምት...ሱሪው የተቀደደ ሰው እንትን እያደርግም የተባለ ይመስል።

ከዛ ማደር ጀመሩ። በጨለማ በዛ በኮረኮንች መንገድ ቢራ ተሸክሜ እጄን የፌስታሉ እጄታ እየከረከረኝ የተላላኩበት ጊዜ መቼም አይረሳኝም (አስከዛሬ አቃ በፌስታል መያዝ አልወድም።)አቂዬ የግቢው በር ላይ ብርድ እያቆራመታት ቆማ ትጠብቀኛለች፤ ገብቼ ቢራውን ስሰጥ ዛፒ ልከ ከፍሪጅ ያወጣችው ያህል ከእጄ ላይ ትወስድና፣

"እንካ ሁለት ፓኬት ሮዝማን ግዛና ና" ትላለች።

በመጨረሻ ጠቅልሎ ገባና አብረው መኖር ጀመሩ። መኪና ማጠብ ቋሚ ስራዬ ሆነ። እውነቱን ለመናገር ጥሩ ባል ነበር። ዋሲሁን ይባላል። ቤቱ የባለትዳር ቤት እንዲመስል የተቻለውን ሁሉ ይጥር ነበረ። ዛፒ ግን የሚቋቋማት ዓይነት 'ሚስት' አልነበረችም። ጉራዋ ፀጉር ያስነጫል፣ በውበቷ ስትመካ ልክ የላትም። የእናቷ ጫማ ውስጥ ዘላ የገባች ጉረኛ ! አቤት ጉረኛ ሴት እንዴት እንደምትቀፍ። ከምትናገራቸው አስር ዓረፍተ ነገሮች፣ አስራ አንዱ ስለራሷ ውበት፣ ስለቆዳዋ ጥራት፣ ስለጣቶቿ አለንጋነት፣ ስለልብስና ሽቶዎቿ 'ብራንድ' በቀጥታ አልያም በተዘዋዋሪ ይተርካሉ ።

ዘላ የተዘፈቀችበት ትዳር ከጭፈራ ቤት መዳራት በምን እንደሚለይ ገና ያልገባት እካሷ ብቻ ሀሲናዋን ጥሎ ያደገባት ከንቱ ነበረች። ዋሲሁን ውጭ መመገብ አይወድም። የታሸጉ ምግቦችን ገና ሲመለከታቸው ያንገሸግሸዋል። አንጀራ በሽሮ ወጥ ነፍሱ ነው። ዛፒ ታዲያ ቤት ውስጥ ለባለቤቷ ምግብ አብስሎ ማቅረብን ብሴት ልጅ ላይ የሚፈፀም ታላቅ በደል አድርጋ ነበር የምታየው።

"የአበሻ ወንድ ጓዳለጓዳ ካልተንደፋደፈች ሚስቱ ሚስት አትመስለውም። ሴት እደባባይ መውጣቷ ያማቸዋል" የምትለው ከእናቷ የወረሰችው ዘይቤ አላት። በጓዳም በአደባባይም ምንም የማትፈይድ የወሬ ቋት። ኩኪስ አልያም ፅጨማቂ ነገር ከፍሪጅ ታወጣና ሶፏዋ ላይ እግሯን አጣጥፋ ቴሌቪዥን

እያየች ትበላለች፣ ትጠጣለች። ስለፋሽን ሳታቋርጥ ትቀባጥራለች፣ በዓለም ላይ ስላሉ የቅንጦት ሆቴሎችና ጌጣጌጦች "ዋ...ው" እያለች ትቋምጣለች። ቤቷም የለችም፣ የምትመገውም ቤታ የለችም። የትም የሌለች የውሀ ላይ ኩበት ነገር!!

ዋሲሁን ያደገበትን የቤተሰብ ስነስርዓት፣ የኢትዮጵያዊነት ወግ ምሳ ተዘጋጅቶ፣ ቡና ተፈልቶ፣ ቤቱ ሞቅ ብሎ እንደሚጠብቀው በማመን እንደ አባወራ ምሳ ሰዓት ላይ ሲመጣ ዛፒ ጠረጴዛው ላይ እግሯን ሰቅላ ዙሪያዋን የጥፍር ቀለም ጠርሙሶች ከበዋት ቤቱ በአልኮል ሽታ ታፍኖ ስትቆነጃጅ ያገኛታል። ማታ ሲመጣ ዛፒ ሰባብሳ እንዲወጡ ስትጠብቀው ይደርሳል።

"ሃኒ ዎከ እናድርግ" ትለዋለች፣ ባል ጋር መታየት እንጂ የባልን መሸት ማየት አልፈጠረባትም፣ የሆሊዉድ ተረቶች ባዶ ጭንቅላቷን ሞልተውት ነበር። ከንዱን ይዛ መንገድ ላይ ስትውረገረግ ብጤዎቿ፣ "ዋው ምናይነት ጥምረት ነው? ማች ያደርጋሉ" እያሉ ያወሩላታል።

ሚስኪን ዋሲሁን ሳይወድ በግድ እግሩ አስኪቀጥን ሲዞር አምሽቶ እኩለ ሌሊት ላይ ስልችት ብሎት ይመለሳሉ። የተሰቀለችበት ባለ ተረከዝ ጫማ ለመራመድ ስለማይመቻት ከንዱ ላይ ተዘፍዝፋ ትወናገራለች።

"ሃኒ ዲጄው 'ሽቶሽ ብራንዱ ምንድን ነው?' ሲለኝ ሰምተኸዋል?"

"አልሰማሁትም" ይላል ትክት ብሎት።

"ሃሃሃሃሃሃ ጠጥተህ ነበር ብ...ዙ...ሰካራም ሃሃሃሃሃ" ትላለች እየተለፋደደች። አብሯት አይስቅም።

"በናትህ ቀሚሴ ላይ ዋይን ደፋብኝ ያ ወልካፋ አስተናጋጅ" ትላለች ረኸም የራት ቀሚሷን እያላየችው።

"ይታጠባል...ደግሞ አንቺ ስታልፊ እኮ ነው የገጨሽው" ይላታል ስልችት ብሎት።

"እዚህ አገር ምን ላውንደሪ አለ? ሰባት መቶ ዶላር የወጣበት ቀሚስ እንደቀልድ - ምን አይነት አገር ነው?" ብላ ቀሚሷ በአደባባይ ባለመከበሩ አስራ አምስት ቀን ታወራለች። ስለ ተራ ቀሚስ ሳይሆን ስለ ባንዲራ መደፈር የምታወራ ነው የምትመስለው።

ጧት ተነስቶ በተሰላቸ መንፈስ ወደ ስራ ሲሄድ ዛፒ እትሰማም አትለማም - ተኝታለች። ምሳ ሰዓት እንደገና ጓደኞቿ ጋር እንደሄደች ትደውልለትና፣ "ምሳህን ውጭ ብላ ሃኒ" ትለዋለች፣ በዛውም 'እያችሁ ባሌን ሳዘውር' እያለች ለከንቱ ጓደኞቿ። ምሳ፣ ራት፣ ቁርስ በአበሻ ባህል ከምግብ የዘለለ ፋይዳ ያለው ጉዳይ መሆኑ ለዛፒ አልታያትም ነበር።

የቤተሰብ እትብት ከእናት ማዕድ ጋር እንደሚያያዝ ማን ይመክራታል? ዋሲሁን ለአንድ ዓመት አብሯት ቆየና ከቃ ደግ ሳይናገር፣ "አንቺ ጋር አንግዲህ በቃኝ" ብሏት ሄደ...!! መሄድ ብቻ

አይደለም፣ ዓመት በልሞላ ጊዜ ውስጥ ድል ባለ ሰርግ ሌላ ሴት አገባ። ዛር መጀመሪያ፣ "ጥርግ ይበል! ለምለ ወንድ!" አለች። ቆይታ፣ "ይሄ ችጋራም ፒዛ እንኳን ሙሳላት ያለማመድኩት እኔ ነበርኩ፣ ጥጋበኛ የደሀ ልጅ!" ማለት ጀመረች። በመጨረሻ ፎቶውን እያየች ማልቀስ ሆነ ሰራዋ።

ዛር ቢበዛ ቆንጆ ናት። ልብሶቿ ጌጣጌጦቿ የብዙ ሴቶች የቁም ቅዠት። ግን ዋሲሁን ከሄደ በኋላ ወንድ የሚባል አልቀርብ አላት። ይፈሯታል። የተጋነነ ቁንጅናዋና ውድ ጌጣጌጦቿ የማትደፈር ግዙት ስለሚያስመስላት የሚመኟት እንጂ ድፍሮ የሚቀርባት ጠፋ።

የእበሻ ወንድ ተመካከሮ ሸሸ...

ዛር ታዲያ የለየላት ሰካራም ሆነች። ማታ ማታ ሰክራ ትመጣና፣

"ለቴፒድ፣ ቅቤያም ሴቶቻችሁ ጋር እየሄዳችሁ ተጋደሙ። ቦርጫም ሴቶቻችሁን እንዘፋዝፉ፣ በምን አባታችሁ ዕድላችሁ ነው እኔን የምትሰሙት!? እዛ የጉራጌ ጫማ ደንቅረው የቻይና ሱሪ ውስጥ የታቆጠሩ ኋላ ቀር ሠራተኛ ሴቶቻችሁ ጋር ኑሩ! 'ጎ ቱ ሄል' ቆሻሾች! ቦርጫሞች! ቦጂም አጠገብ አልፋችሁ የማታውቁ" አያለች በረንዳዋ ላይ ቆማ ድፍን የአበሻን ወንድ ትሳደባለች ።

በጣም ስከር ብላ ጨርቅ ሆና ያመጣት ባለታክሲ ግቢ ውስጥ ደግፎ አስገብቷት ሲመለስ ትጠራኛለች፣

"አሸብር ና ጫማዬን አውልቅ!"

ጫማዋን እወልቅላታለሁ። እች የውሻ ልጅ! የእግሮቿ ጣቶች የመላዕክትን ጣቶች ይመስላሉ፣ አረዛዘማቸው፣ ጥራታቸው።

"ቀስ በል አንተ ! ሶሉን ልትገነጥለው ነው። የእናትህን ኮንን ጫ...ማ አደረከው። ይሄኮ - አራት መቶ ዶላር የወጣበት ነው። በዚች ችጋራም አገር ወረቀት ሲመነዘር ስንት ይሆናል - አንደኛ አይደል ከከላስ የወጣኸው" (እደነግጣለሁ። ማን ነገራት? ስለመፈጠሬም የማታስታውስ ሴት ደረጃዬን እውቀቸው..።)

"እስኪ አሰበዋ፣ እኔ የቻይና ሽራ ጫማ የምደነቅር መሰለህ?" እየለፈለፈች መኝታ ክፍሏ አስገባታለሁ። አቤት ሽቶዋ! ቆም ብላ አልጋውን በጥላቻ ታየውና፣ ወደ ሳሎን ትነፋኛለች። እያንዘፋዘፍኩ ሳሎን ሶፋው ላይ አስተኛታለሁ። እየለፈለፈች እንቅልፍ ይወስዳታል።

ጧት ምንም እንዳልተፈጠረ አታናግረኝም፣ መኖሬም ትዝ አይላትም።

ዛሬን አጠላታለሁ።ጉረኛ ናት። ሰው ትንቃለች። ማን የማይደበቀው ህቅ ከአናቷ ትሻላለች። ድካት አቲዬን ትጠራትና፣

"ያውልሽ ይሄን ውሰጅ!" ብላ ጉና ያልተከፈተ ውድ ሽቶ ትሰጣታለች።

አቲዬ ግን አጀን የሆነ ነገር ሲቆርጣት ብቻ ቁስሉ ላይ ስትረጨው ነው የማያት::

ሴላ ቀን አቲዬን ትጠራትና፣ "እስቲ ቡና አፍይ!" ትሊታለች:: አቲዬ ሽር ጉድ ብላ፣ አሜሪካ ቤቱን ነፍስ ትዘራበታለች:: ዛፒ ግን ቡና አትጠጣም:: አቲዬም ስለምትፈራ አትጠጣም፣ አነሳስታ ወደ ቤት ትመለሳለች::

ዛፒ አዕምሮዋ ጤነኛ አለመሆኑን መጠራጠር ጀምሬ ነበር::

አንድ ቀን ሰላማዊት የምትባል የሰፈራችን ልጅ አገባችና ሰፈሩ በሞራራ ቀውጢ ሲሆን ዛፒ ጠራችኝ፣

"ማናት ያገባችው?" አለችኝ::

ነገርኳት::

"ቆንጆ ልጅ ናት እንዴ?"

"አንድ ቀን ጋሽ ዋሲሁን ጋር ሆናችሁ አሟት በመኪና ሆስፒታል የወሰዳችኋት ልጅ ናት እኮ::"

"እና አሷ ልጅ ቆንጆ ናት እንዴ?"

ምን ልበል፣ ጨነቀኝ:: "እኔ እንጃ!" አልኩ::

ዝም ስትል፣ የጨረሰች መስሎኝ ልሄድ ስል፣

"መልኳ ከእኔ ይበልጣል ?" አለችኝ::

"ኧረ..." ብዬ ሳቅኩ::

"ምን ያስቅሽል? ዝም ብለህ የጠየቅኩህን አትመልስም?" አለች በቁጣ::

ፈገግታዬ ፊቴ ላይ ከስሞ፣ "እንች ላይ...ሜፍሽ ላይ አትደርስም፣ እንች እኮ በጣም ቆንጆ ነሽ አልኳት:: ከልቤ ነበር የተናገርኩት::

ትኩር ብላ አየችኝና፣ ወደ መኝታ ክፍሏ ገባች:: የክፍል ደረጃዬን የማታውቀው እንዳስገረመኝ ቆንጅናዋን አይቼው የማላውቅ መስሏት ነበር መሰል::

"ምን አስለፈለፈኝ" እያልኩ ወደ ቤቴ ገባሁ:: ግን ያደነቅኳት ሳይሆን ልኳን የነገርኳት ያህል ውስጤን ደስ ብሎት ነበር::

አየው እንግዲህ፣ "የነገር አመጣጥ እንደ ውሀ አፈላለስ ነው" ነው የሚለው መጣፉ:: ይሄን ነው...ጠብ...ጠበጠብ...ፈስስ፣ ኮለል...ጎረፍ...ዣቅዣቅዣቅ፣ ከዛ ግንድ የለ ድንጋይ ይፈራረጥሞል:: ጠብታው መኝታ ቤቱ ነው፣ ግንዱ ሰርቪስ...:: አስቴር አወቀ ዛፒ መኝታ ቤት ድምጽዋን ከፋ

አድርጋ ትዘፍናለች። ምን አያለች - አኔንጃ !! ምናልባት እንዴት አንደምትጎርፍ፣ እየመኪረችት ይሆናል። አስቴር እኮ ዘፋኝ አይደለችም መካሪ ናት። ስንቱ መኝታ ቤት እየገባች በጆሯቸው የሚሆንም የማይሆንም ነገር ሹክ ስትል ከርማለች። አስቴር ሴረኛ ናት!! የዛፒ ዓይን አንደ እንቴና መዛ ወዲያው አሳድጎናል፣ ሳድግ የባሰ ፈሪ ሆንኩ።

ክፍል አስራ ሰድስት

ጥቁር አምበሳ፣ ኮከበ ፅባህ፣ ምኒሊክ፣ መነን፣ አዲስ ከተማ፣ ድልበር፣ ቦሌ ከሚማሩ የአሰረኛ ክፍል ተማሪዎች ሁሉ፣ "አንደኛ ጎበዝ አንተ ነህ" አሉና የምስክር ወረቀት ሸለሙኝ። እኔ ግን ጥቁር አምበሳ፣ ኮከበ ፅባህ፣ ምኒሊክ፣ መነን፣ አዲስ ከተማ፣ ድልበር፣ ቦሌ ከሚማሩ ሌት ተማሪዎች ሁሉ አንደኛ ቆንጆ የሆነችው ዮርዳኖስ የት ተቀምጣ ይሆን እያልኩ በዓይኔ ከተሰበሰቡት ሰዎች መሀል እየፈለግኳት ነበር።

ዮርዳኖስ ማለት ማንም አይደለችም፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ከመሬት ተነስታ ጉንጩን የሳመችኝ ልጅ ናት። ጉንጩን ሳይሆን በቀኝ በኩል ከከንፈሬ ጥግ ሁለት...እረ አንድ ተኩል ሴንቲ ሜትር ርቀት ላይ ነው የሳመችኝ (ለምላ ጉንጭ።)

ዮርዳኖስ ቀይ ልጅ ናት። ለነገሩ ቀይ ሳትሆን ጠየም ያለች ግን ቀይ ዳማ እንደሚሉት ሳትሆን አትቀርም። አቦ የራሷ ጉዳይ ገደል ትግባ ብትፈልግ ኤጭጭ!! ይሄው ስንት ጊዜ ሴትም ቀንም ዮርዳኖስ ቀይ ናት ቀይ ዳማ' አያልኩ ስዘብር ማደር ከጀመርኩ። እንኳን ሴት ልጅ፣ ቆንጆ ወጣት ሴት ልጅ፣ ነፍስ ካወቅኩ ጀምሮ ሰው ሲስመኝ የመጀመሪያዬ ስለነበር ዮርዳኖስ ጉንጩን ሳይሆን ልቤ ላይ እንደሳመችኝ አርግጠኛ ነበርኩ። ማስረጃ ብባል፣ ከዛን ጊዜ ጀምሮ አተነፋፈሴ ልኮ አይደለም፤ ሳያት የሆነ ነገር ያፍነኛል። ሳላያት እንደ ነብር አዳኝ ትገፋሬን ውጪ በጉጉት በዓይኔ አፈልጋታለሁ። ሳላያት ታፍኜ ሳያትም ታፍኜ ልሞት ሆነ።

"እንች ዮርዳኖስ የምትባይ፣ ምን ቆርጦሽ ነው ኧረ ከከንፈሬ እንድ ተኩል ሴንቲሜትር ርቀት ላይ በሚሞቅና በሚለሰልስ አርጥብ ከንፈርሽ የሳምሽኝ?" ብላት ደስታዬ። ግን ታፍኛለሁ!!

አርብ ቀን ከትምህርት ቤት ወጥቼ ወደ ቤቴ አሄዳለሁ። ምንም እያስብኩ አልነበረም። ዝም ብዬ እየተራመድኩና በግዴለሽነት ሁሉንም ከፊቴ ያለውን ነገር እየተመለከትኩ አራመዳለሁ።

"አሸብር!" አለችኝ ከኋላዬ።

ስሜ ሲጠራ የምደነግጠውን ያህል የሰይጣን ስም ቢጠራ እንኳን አልደነግጥም። ሰዎች ስሜን ሲጠሩኝ ከዝምታዬ ባሕር በምላላቸው መንጠቆ ጠልፈው ያወጡኝ ይመስለኛል።

ቁራሽ ጠሪዋ ዮርዳኖስ ስትሆን ደግሞ፣ በመንጠቆው ላይ መረብ ተተበተብኩ !! ከእኔ ጋር

ብዙ ሰዎች ወደኋላ አብረው ዞሩ:: ሰዉ ሁሉ ሳይጠራ ሲዞር፣ ጠሪዋን ተመልከቶ ደሰ ካሉችው ስሙን 'አሸብር' ሊያስብል ያሰበ ይመስል እኔ ለተጠራሁት መዓት ሰው ዞረ::

ዮርዳናስን ዞሬ እየኋት:: ጉርድ ቀሚሷ በደንብ አላራምዳት ስላለ በእጇ ሰብሰብ አድርጋ ወደ እኔ ትጣደፋለች:: እግሯ ቀይ ነው:: ባቷ ፍርጥም ያለ ከአድሜዋ በላይ ትልቅ የሚያስመስላት ነው:: ባቷ ብቻውን አስራሁለተኛ ክፍል ይመስለኛል:: ጡቶቿ ደግሞ እዛና እዚህ ይሊጋሉ:: ስትጣደፍ፣ በሁለት እጆቿ ከንዶች ገፋ አድርጋ ታረጋጋቸዋለች:: ፀጉርዋ አጭር ነው:: ግንባሯ ትንሽ ወጣ ያለ:: ቀረበችኝና ፈገግ አለች:: ዓይኖቿ እንዴት ያምራሉ::

ኡፍፍፍፍፍፍፍፍፍ አሁን ስትጠራኝ መኪና እየነዳሁ ቢሆን ኖሮ ከዓይኖቿ ለማምለጥ ሰል ፊት ለፊት የሚያላዝነው ቦት መኪና ጋር አላተም ነበር:: የያዘው ነዳጅ ይዘረገፍና ከዮርዳናስ ፈገግታ አሳት ለኩሶ ጭሱ ፀሐይን ጥቁር ጉልቻ አስክትመስል የሚያጥን:: ሰማይ የሚነካ አሳት ይነሳ ነበር:: በቁሜ ቅዠት ስጀምር ታወቀኝ::

"እንዴት ነው የምትሮጠው ወተት ጥደሃል ቤትህ ?" ቀለደች::

አልሳቅኩላትም:: ስላልሳቅኩላት ግን ራሷ ከመሳቅ አልታቀበችም:: እየሳቀች ወሬዋን ቀጠለች::

"ቤትህ በዚህ በኩል ነው እንዴ ?"

"እዎ"

"እኔ ግን አይቼህ አላውቅም_"

ዝም አልኩ:: ካላየችኝ ምን ይሁን፣ ወሬዋን ቀጠለች::

...ፏ...

አዎ

...ፏ...

አዎ

...ፏ...

አዎ

"አዎ ብቻ ነው እንዴ የምታውቀው ?"

"አይ" አላታለሁ:: እነጋገሬ ሴት የመፍራት ሳይሆን ሰው የመሰልቸት ነበር:: እንዳንዴ የሰዎች ንግግር ይረዝምብኛል::

"ሰላም" ሲሉኝ ይረዝምብኛል:: ሰ..ላ...ም፣ እጃቸውን አንስተው፣ ግንባራቸውን ነቅንቀው፣ ፈገግ

ብለው:: አንዳንዴም እጃቸውን ለሰላምታ ዘርግተው፣ ይሄን ሁሉ ነገር አድርገው፣ "ሰላም ብቻ !!

ዝም አለች:: አብረን ሄድን ሄድንና የሆነ መገንጠያ ላይ ስንደርስ ከንዴን ይዛ አቆመችኝና ተንጠራርታ ሳመችኝ:: ምንም አላማ የሌለው፣ ምክንያት የሌለው ወይም "ደፋር ነኝ እየሆ" የሚል ምናልባትም፣ "ዘመናዊ ነኝ መንገድ ላይ የወንድ ጉንጭ መሳም አልፈራም" አሳሳሚ የሆነ ድምፅ አለው፣ የሚያቋጭ ዓይነት ድምፅ:: የመምጠጥ አይነት ድምፅ:: የበዛ ግለኝነቴን ምጥጥ አድርጋ የሐሳብ ሀይቄን አደረቀችው:: የሰው አለማያ ሆንኩ !! ባደረቀችው የብቸኝነት ኩሬ ራሷን ሞላችው::አዚህ ዮርዳኖስ የምትባል ውሃ የሞላችው ባህር ውስጥ ልቤ እምልጠኝ ገባ:: ይሄው አስባታለሁ፣ የተረገመች ዮርዳኖስ !!

እየጠበቀችኝ ይሁን እየተገጣጠምን ብቻ ከዛን ጊዜ በኋላ በየቀኑ እንነናኝ ጀመረ:: ቢቆይ ግን ጉዳዩ የነፍስ ቀጠሮ ሆነ:: ጠበቅኩሽ ላለማለት በቀስታ እየተራመድኩ እጓዛለሁ፣ ከየትኛውም ርቀት ላይ አውቃታለሁ::

ፊት ለፊት ሳላያት መንፈሷ እዛ አካባቢ ካረበበ ትካሻዬ ሹክ ይለኛል:: ትከብደኛለች፣ "ሃይ አሹ" የሚል ድምጽ አጠብቃለሁ:: "ሃይ አሹ" ትሰኛለች ውስጣችን ያውቃል እንደምንጠባበቅ:: ከዛም ታወራኛለች::

"ዛሬ ይበርዳል!"

"አዎ"

"ሆም ዎርክ ሰራህ ?"

"አዎ"

.

.

"አዎ ብቻ ነው የምታወቀው::"

"አይይ_":: አሁን ግን ምን ማውራት እንዳለብኝ እያሰብኩ ነው...! ችግሩ፣ አሰቤ ላልጨርስ አንደርሳለን::

ስንመለስም እንገናኛለን:: ስንመለስ መለያያችን ላይ ትስመኛለች፣ "ቻው" ከሚል ስርቅርቅ ያለ መለያየቱ ያስከፋው ድምፅ ጋር ከንፈሯ ጆሮዬ ላይ ያቋጫል::

አንዴ መሀል ጉንጬ ላይ፣ አንዴ ዝቅ አንዴ ከፍ እያለች ትስመኛለች:: በየቀኑ ትስመኛለች:: ገዘም ብዬ አላማለሁ:: ከንፈሯ ከብ ነው፣ በሃሳቤ ስትስመኝ ከብ ቅርፅ ጉንጬ ላይ የታተመ ይመስለኛል፣ የሳምንቱ ከቦች ተቆላልፈው፣ ቅዳሜ የአሎምፒክ አርማ ጉንጬ ላይ ታትሞ በጥልህ ይታየኛል:: አንዱ ከብ አንደ ደቡብ አሞ ሴቶች፣ ከንፈሬን ተልትሎ ከንፈሬ ላይ ተንጠልጥሎ እየሁት - በህልሜ!

አንድ ቀን ግጥም ጻፍኩ። በህይወት ዘመኔ የጻፍኩት ብቸኛ ግጥም ነበር። ወደፊትም ግጥም አልጽፍም !! ግጥም ያስጠላኛል። ሰው ዝም ማለት እያለለት፣ ለማውራት ቃል መጠምዘዝ መድከም ምን ያደርግለታል? - 'ቢፅፍ ላይጠቀም፣ ባይፅፍ ላይጎዳ' ባይ ነኝ። ደግሞ አዲስ ግጥም ሰምቼ አላውቅም። ግጥሞች ሁሉ አንድ ናቸው፤ ደራሲያቸው ይለያይ እንጂ ባይ ነኝ።

አኔን የገረመኝ (ርእሱ)

አኔን የገረመኝ፣

እኔ የጠላሁትን፣

አኔነት ሳትጠላ፣

ልጅቱ ስትለመኝ !!

በቃ !! ይሄው ነው ግጥሙ።

ግጥም ማለት ቤት የሚመታ፣ ቀለሙ፣ ስንኙ የሚሉ ለምቾን ተዋቸውና ግጥም ማለት እስክርቢቶ ሳትጨብጥ ወረቀት ፊትህ ሳይነጠፍ አንደ እፍ ወለምታ ከከንፈርህም፣ ከነፍስህም፣ ከለዕምሮህም የሚያመልጥ አውነት ነው። ለምሳሌ በዚች ዓለም ላይ ከሰማኋቸው ግጥሞች አሳዛኙ የአቲዱ ግጥም ነው። ርእሱ፣ "እሺ"፣ ግጥሙም፣ "እሺ" - አበቃ።

ማንም ለጀመረው የትዕዛዝ ስንኝ፣ አቲዱ 'እሺ' የሚል ግጣም እየሰራችለት፣ የማንም ቤት እንዲቆም አድርጋለች። የአኔ አናት ገጣሚ ናት።

"ቤት ጥረጊ!"

"እሺ!"

"ልብስ አጠቢ!"

"እሺ"

"ሂጂና ላሙና ግዢ!"

"እሺ"

"እንጀራ ጋግሪ!"

"እሺ"

"ደመወዝሽን ሌላ ቀን ውሰጂ!"

"አሺ"

ግጥም ይሄ ነው !! ከትዕዛዙ አኩል ይሁንታው ዜማ ሲፈጥር። እናም ያሉትን ሲሆኑ።

ቤት መምታት ይሄ ነው። መጥፎ ቃል የደህ ሰጋ ለብሶ አዛዥ ቤት ሲያድር፣ በዓመቱ አይኑ በምኞት የሚዛብር 'ገጣሚ' "ውይ...ዘላለም ልፈጥፈጥልሽ፣ ልቆራመትልሽ" ቢል አይገባኝም። ግጥም ከቃል ሊጭበረበር ሳይሆን፣ ከነፍስ ሲመዘዝ ከሕይወት ሲቀመም ነው ቤት የሚመታው።

ቢሆንም ግጥም ገጠምኩ። አላሰብኩም፣ አልደለዝኩም፣ አልሰረዝኩም። አንድ ደብተሬ ጀርባ ላይ በቀጥታ ጻፍኩት። ያውም ኬሚስትሪ የሚባል ትምህርት እየተማርን ልክ ሰልክ ቁጥር እንደሚጽፍ ሰው ሳላሰብ ግጥም ጻፍኩ። ከብዙ ዓመት በኋላ ይሄን ግጥም ያሳየሁት ገጣሚ፣ "ጭብጡ የላላ ወይታች የተጻፈ ስድ ፅሁፍ ነው የሚመስለው" አለኝ። ጉዳዬ አልነበረም። ድሮስ መቼ ግጥም መጻፌ ገረመኝ። በልጅቱ ጉንጭን፣ ያውም አንድ ተኩል ሳንቲሜትር ለከንፈሬ የቀረበ ቦታ ላይ መሳሜ እንጂ !!

ዮርዳኖስ አንድ ቀን ጠራችኝ፣ "አሹ" ብላ !!

"አሹ" ማለት ለካ አሸብር ማለት አይደለም፣ በጭራሽ። "አሹ" ማለት ከአሸብር ጋር የሚገናኘው ሁለቱም አጠራር ስለሚያስደነግጡኝ ብቻ ነው እንጂ አሸብር "አሹ" አይደለም። ከየት አመጣችው ግን እች ዮርዳኖስ !! ደግሞ "አሹ" ከአሸብር ይረዝማል። "አሹ"፣ ሙሉ ቀን ጀሮ ላይ ያቃጭላል - አይገርምም ?

ከተማሪዎች ሁሉ እንደኛ ወጥቼ የተሸለምኩ ቀን ሌሊት ከእንቅልፌ ነቃሁ። ምን እንዳነቃኝ አይገጣ። ፀጥታው የነቃ ያስተኛል እንኳን የተኛ ሊቀሰቅሰ። ግን ነቃሁ። ነቃሁና ልክ ዓይኔን ስከፍት፣ ዮርዳኖስ ያንኳኳችውን በር የከፈትኩ ይመስል ምስሏ ፊት ለፊቴ ተደቀነ። ልትስመኝ ስታምጠመጥ፣ ስትስቅና "አሹ" ስትለኝ፣ "ፍቅር ይዞኛል" የሚል የማልፈልገው ዓረፍተ ነገር ከምኔ እንዳመለጠ ሳላውቅ ፈነዳ - ....ቡምምምምምምምምምምምምምምምም ፍቅር - እርፍ !!

ልክ እንደ ማጥሙ ያልፈለኩት እንባ ጉንጬ ላይ ተንኳለለ። በምድር ላይ አለኝ ከምለው አንድ የሆነ እምነት የተካኳድኩ መሰለኝ። ለነብስ ጉዳይ የተበደርኩት ብር ከኪሴ የጠፋ ያህል ተሰማኝ።

አንባዬን ጠረግኩና መብራቱን አበራሁት። ፊት ለፊት ያለው ግድግዳ ላይ በፈሰስታል የተሰቀለ የአቲዬ ልቃቂት። ራቅ ብሎ ትንሽ መጋረጃ እንደ ዕቃ ቤት የምንጠቀምባትን ቦታ የከለሉት፣ ከመጋረጃዋ ፊት ለፊት አቲዬ ፍራሽ ላይ አሮጌ ብርድ ልብስ ለብሳ ኩርምት ብላ ተኝታለች። ቤታችን አስጠላኝ። ራሴ አስጠላኝ። አስረኛ ከፍል አስጠላኝ። ከአሁን በኋላ ስንት ዓመት ተምሬ ነው ስራ የምይዘው?

አቲዬ ድንገት ባነነችና፣ "አሸብር ምነው አመመህ እንዴ?" አለችኝ፣ ከወገቧ ቀና ብላ። ዝም ብዬ አየኋት። አቲዬ አያረጅች ነው። ደረቷ ከስት ብሷል። ፊቷ ላይ ማዲያት ነገር አለ።

ግንባሯ ላይ ብዙ መስመሮች ተጋድመዋል። እንገቷ ስር ያለው ቆዳም ሁሽብሽቧል። እስከዛሬ አላየኋትም ወይስ "እውር ያደርጋል" የሚሉት ፍቅር የእኔን ዓይን ገለጠው ? ገመናዬን አላይዳ፣ 'ልክህን እወቅ!' ሊለኝ። አቲዬን ስራ እስክምይዝ በምን ላፅናናት?

"አቲ ደስ ብሎኝ ነው" አልኳት ፈገግ ለማለት እየሞከርኩ።

"አሰይ፣ ኧረ ደስ ይበልልኝ..." አሉች ከእኔ የበለጠ ፈገግ ብላ። ምኑንም ሳትሰማ፣ 'ምን ተገኘ?' አንኳን አላለችኝም። በቃ ደስ ካሰኝ ደስ ይላታል።

"ከአዲሰ አበባ ተማሪዎች ሁሉ አንደኛ ወጥቼ ሰልፍ ሜዳ ተማሪዎች ፊት ተሸለምኩ" አልኳት፤ 'አዲስ አበባ' ያልኩት ሆን ብዬ ነበረ። 'የገፋሽ ሕዝብ ሰነፍ ነው፣ ያንከራተተሽ ሕዝብ ልጆች በአንቺ በተንከራታቱ፣ በአንቺ ልጅ አፈር ድሜ ግቧል። ተበልጠዋል። በሉጅ አዙር በልጠሻቸዋል' ለማለት፣ ሌላም ለማለት_

አቲዬ ፊቷ በፍርሀት ተወረረ፣ "ልጄን የሰው ዓይን ውስጥ ሊያስገቡብኝ" አለች።

"አቲዬ ደግሞ፣ ሁልጊዜ እንተያይ የለ" አልኳት። ዓይን ውስጥ ግን ገብቻለሁ ልከ ነው። ዮርዳኖስ የምትባል ቡዳ በልታኛለች - በከንፈሯ !!

"በል ጧት ሂድና ማለፍህን ንገራት!" አለችኝ በአገጯ ወደ ዛፒ ቤት እየጠቆመች። አቲዬ ከሚገርመኝ ባህሪዋ ማንንም በሰም አትጠራም። ተመልከቱ ምን ያህል እንደተበደለች እች ሴት። የሰውን ስም መጥራት በራሱ መናቅ አንዳይመስልባት ትፈራለች - ትፈራለች !! እናም ለዛፒ ምን ብዬ እንደምትግራት አሰብኩ።

'ዛፒ እንደኛ ወጣሁ'_'ዛፒ አለፍኩ'_,ዛፒ ሰካራም...ዛፒ ጠብራራ ዮርዳኖስን አፈቀርኳት... ኤፍፍፍፍፍፍ ላብድ መሰለኝ። መብራቱን አጠፋሁት። ጨለማው ውስጥ ዮርዳኖስ ገጭ አለች - እች ግንባራም ! አግራ ቀይ ነው። ጡቶቿ ትልልቅ ናቸው። ስትራመድ ይነቃነቃሉ። ግን ጡት ሲቶችን ይከብዳቸዋል...አይከብዳቸውም? - ታዲያ 'ዮርዲ' ለምንድን ነው ሰትራመድ ጎበጥ የምትለው።

"ዮርዲ" ነው ያልኩት ? ሃሃሃሃሃሃሃ ከአቲዬ ቀጥሎ በዚች ምድር ያቆለመጥኩት ስም እሠ_

ክፍል አስራ ሰባት

ጠዋት ዩኒፎርሜን ለብሼ ደብተሮቼን እዘጋጀሁና እየቀፈፈኝ ወደ ትልቁ ቤት ሄጀ እንኳኳሁ።

"ማነው?" አለችኝ ዛፒ። ደነገጥኩ።

"እ...ኑ ነኝ" አልኩ አየፈራሁ።

ማባ ክፍት ነው"። ገፋ ሳደርገው የሚያብረቀርቀው የጣውላ በር ድምፅ ሳያሰማ ተከፈተ - ከፍቱን ነው ያደረው ማለት ነው። ዝርክርክ ያለው ሳሎን ጋር ተቆጠጥኩ። ዛፒ ሶፋው ላይ የለል ልብስ ጣል አድርጋ ተኝታለች። ፊቷ የተቀመጠው ጠረጴዛ ላይ የሻይ ብርጭቆ፣ የውሃ ጠርሙስ፣ ሩቡ ብቻ የተበላ ሰላጣ፣ ምንም ያልተነካ ዳቦ ዝርክርክ ብሏል። ብዙ ምግብ ማቅረብና ምንም አለመብላት ልማዷ ነው - ይገርመኛል።

"ምንድነው በጧቱ?" አለች እየተነጫነጨች። ድምጿ የወንድ ይመስላል - ጎርንኗል።

"እ...ትምህርት ቤት - ከሁሉም ትምህርት ቤቶች እንደኛ ወጣሁና ...ል...ንገርሽ ብዬ ነው" ድምጼ ተንቀጠቀጠብኝ።

ቆጥ ብላ ግራ በገባው ፊት አየችኝ። የሌሊት ልብሷን ትከሻዋና ትከሻዋ አካባቢ ይዛ አስተካከለች፤ አቤት ደረቷ ቅላቱ ይንበገቦጋል። ከኋላው ቢጫ መብረት የበራበት መሰተዋት ይመስላል።

"እኔ ምናግባኝ ታዲያ?!" የምትል መሰሎኝ ነበር። ድንገት የሆነ ነገር ትዝ እንዳለው ሰው ፈገግ ብላ፤

"እና ላመኛ! እንደዚህ ነው እንዴ የምስራች የሚነገረው? መርዶ አስመሰልከው እኮ!" አለችኝና ሁለት ኢጀቿን እንደ ከንፍ ዘረጋቻቸው፤ ያውም በፈገግታ። ሁለት ጡቶቿ አፈጠጡብኝ።

ግራ ገብቶኝ እንደቆምኩ፤ "ና እንጂ ሳመኝ!" ብላ ጮኸችብኝ።

በደመነፍስ እየተደነቃቀፍኩ ሄጄ...ሄጄ...ሄጄ..ሄጄ..ሄጀ..ሄጀ እጀቿ ሲጠመጠሙብኝ ሁሉ እርምጃዬን ያቆምኩ አልመሰለኝም። ጥብቅ ኢድርጋ አቅፋኝ፤ "ንበዝ የኔ ወንድም አኮራብሀለሁ!" አለችኝ፤ በለው...!! ከሽ አለ የሻዩ ብርጭቆ ከጠረጴዛው ላይ ወድቆ። "ይሰበር ተወው!" አለችኝና ጉንጩን ስማ ለቀቀችኝ። ይሄ ቤት ለካ የወይዘሮ አጥፍወርቅ ቤት ነው !!

ከዛፒ ጋር እንደወጣሁ በደስታ ሰከሬ መንገዱን ሁሉ፤ ሰውን ሁሉ እየሁት። መቼ ነው ይሄ ትልቅ የመኪና ኪራይ ማስታወቂያ ነዳጅ ማደያው ፊትለፊት የተሰቀለው ? መቼ ነው ይሄንኛው ሕንፃ ተሰርቶ ያለቀው? ወቸ ጉድ አዲስአበባ እንዴት ተለውጣለች? ከሆነ አገር የመጣሁ መሰለኝ። ደግሞ ደስ የሚል ነገር ይሸተኛል። አፍንጫዬም ዛሬ ገና የተከፈተ ይመስል...።

ዮርዳኖስ ጋር ስንገናኝ፣ "ምነው?" አለችኝ።

"እ" አልኳት።

"እይ ቆመህ ሳገኝህ ነዋ" አለችኝ። ለካስ ዮርዳኖስን ቆሜ አልነበረም የምጠብቃት። ያልጠበቅኳት

መስዬ ነበር መጠበቅ የነበረብኝ። ሳመችኝ ጉንጩን። ዛፒና ዮርዳኖስ እኔ በምባል ኳስ በከንፈራቸው እየተቀባበሉ 'ቮሊ ቦል' የሚጫወቱ መሰለኝ። "ተስመህ ትወጣለህ፣ ስመው ይቀበሉሀል" የሚል ትንቢት ከሰማይ የታወጀም መሰለኝ። ድፍን አዲስአበባ አንደ ዳቦ፣ አንደ ዘይት፣ አንደታክሲ እኔን ለመሳም የተሰለፈ መስሎ ተሰማኝ። (ቀስ ትደርሳላችሁ አትጋፉ...ሂሂሂሂ)

ዮርዳኖስ ፈገግ ብላ አፍንጫዋን በመቀሰር ጠጋ አሉችኝና፣ "ደግሞ አሪፍ ሽቶ፣ አፉፉፉፉፉፉ ያደረጉብህ ማነው?" አሉችኝ። አፈርኩ። ለካ የዛፒ ሽቶ ነው ሲከተለኝ የነበረው። የዛፒ ሽቶ የዋዛ አልነበረም። ከዚች ቀን ጀምሮ እድሜ ልኬን ሲከተለኝ ነው የኖረው። ሲያሳድደኝ ሳይሆን ሲከተለኝ። የሆነ ዙፊያዬን ከብቦ እንደ እናት አቅፎኝ።

ሰው ወደ ውስጥ የሚሰበው አየር 'አከስጅን'፣ ወደ ውጭ የሚያስወጣው ካርቦንዳይአከላይድ' እያሉ ያስተማሩን ቅኔ ነበር - ሳይንሳዊ ቅኔ !! አሁን አሸብር ወደ ውስጥ የሚሰበው ፍቅር፣ መፈቀር፣ መከበር፣ መፈለግን ነው። ወደ ውጭ የሚተነፍሰው እርካታ። የአየር ብክለት ማለት ሌላ ትርጉም የለውም አኮ - የተገፉ፣ የተገለሉ፣ የተናቁ፣ ሕዝቦች ጥላቻን ወደ ውስጣቸው ስበው መልሰው ጥላቻን ወደ መላው ዓለም መተንፈሳቸው ነው። መፍትሄው የፍቅር ችግኝ በልባቸው መትከል ነው። እነሆ ዮርዳኖስ የተከለችውን ዝግባ ዛፒ የምትበል ዝናብ ስታረሰርሰው ዘርፈፍ ብሎ በቀለ። ሕያውነት ከሰሩ አረፍ የሚልበት ጥላ ሆነ።

እኔማ ዛፒ ጥቁር ደመና እዝላ እያጉረመረመች ሰማይ ላይ ተንጠልጥላ ሳያት፣ መሽቆጥቆጥና ጥላቻዬን እንደ ዣንጥላ ሰዘረጋ ነበር የኖርኩት። ከፋትም ጉልበት የሚኖረው እንደከፋት ልንቀበለው በተዘጋጀነው መጠን ነው።

ክፍል ሰላሳ ሰምንት

"እንተ ሴት ነህ እንዴ?" ብላ ዛፒ ሳቀችብኝ። አፈርኩ። እንደኛ መውጣቴን ምክንያት በማድረግ ዛፒ ልብስ ልትገዛልኝ ጠሰደችኝና 'ምረጥ!' ስትለኝ መጀመሪያ አጄ እንድ ቀሚስ ሳይ አረፈ። ለአቲዬ ልኳ የሚሆን ቀሚስ ነበረ። ለዛ ነበር የሰቀችው።

ልብስና ጫማ ገዛችልኝ። የሱሪዬን ቁጥር ስጠየቅ አላውቅም ነበር። ሱሪ ገዝቼ አላውቅማ፣ የጫማ ቁጥርም አላውቅም። የሀብታም ልጆች ልብስና ጫማቸው ከሰቅ የተገዛ ሳይሆን አብሯቸው የሚወለድ ይመስለኝ ነበረ።

ሃሃሃ...ግን ይሄው ሁሉ ነገር ሱቅ ውስጥ አለ - ሸቀጥ ነው። ያው እዛጋ ቶማስ የሚባሰው ሁልጊዜ በሴት የሚከበበው የከፍላችን ልጅ ጫማ - ይሄው የራሄል ቦርሳ - እረ ጉድ የቲቸር ተስፋ የጥቁር ባለ ብዙ ኪስ ጃኬትም ያውና። ትንሽ ብቆይ እነዛ 'ውድ ነን' የሚሉ ልጆች እዚህ ተደርድረው ሲሸጡ አገኛቸው ይሆናል።

ቢገርም... - ሁለት ሱሪ፣ አንድ ጫማ፣ ሁለት ሸሚዝና አንድ ሹራብ - ነፍስ ካወቅኩ ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ ልብስ ከሰቅ ገዛሁ። ለካሁት። መስተዋቱ ፊት ስቆም ደነገጥኩ። 'ልብስ ማለት ተራ ድሪቶ ነው' ምናምን የሚሉ ሰዎች እንዴት ጅሎች ናቸው አባካችሁ! ራሴን በመስተዋት ሳየው ታላቅ ፍንዳታ አዕምሮዬ ውስጥ ተፈጠረ።

አወራረዳለሁ ጥቁር አምበሳ፣ ኮከበ ፅባህ፣ ምኒሊክ፣ መነን፣ አዲስ ከተማ፣ ድልበር፣ ቦሌ ከሚማሩ ጐማሪዎች ሁሉ አንደኛ ቆንጆና ወንዳወንድ አቋም ያለኝ ልጅ እኔ ነኝ !! አፎይ! ከቤተክርስቲያን ሃጢያቱን ተናዞ እንደወጣ ሰው ሸከሜ ቀለለኝ -አደግኩ ደግሞ !! የክፍሌን ልጆች በየቤታቸው አየሄድኩ እጅን ኪስና ኪሴ አስገብቼ "ሃይ!" ማለት አማረኝ።

ዛፒ የለበስኩት አዲስ ሹራቡ ላይ የነበረውን ወረቀት ከኋላ ከሩን በጥርሷ በጥሳ አላቀቀችልኝና፣ "አንተ ልጅ ቆንጆ አኮ ነህ" አለችኝ። በሙቅ ውሃ በተሞላ ገንዳ ውስጥ የመግባት ያህል ቃሏ ይሞቅ ነበር። ቆንጆ መሆን ማለት የአፍንጫ መሰልከከ፣ የዓይን መንከባለል፣ የጥርስ መደርደርና ንጣት ማለት አልነበረም። ለኔ ቆንጆ ማለት በሰው ዓይን መሙላት ማለት ሆነልኝ።

ዝም ብላችሁ የሕይወት መንገዳችሁን ዙሩና ተመልከቱ! አለቀ ያላችሁበት ቦታ ላይ የነበረውንና የሚመጣውን የሚያያይዝ ድልድይ ይኖራል። ይሄን ድልድይ የሚያምኑ 'ፈጣሪ ነው' ይሉታል፣ የማያምኑ 'የስነሕይወት መርህ ነው' ይሉታል። ለእምነቱም ለሳይንሱም ግድ የማይሰጣቸው አድል ይሉታል። እኔ ግን ይሄ አንዱ በዛ አንዱ በዚህ የሕይወቴን ተራዳ እየደገፈ የሚያቆመው ከአቲዬ ድፍን ሃምሳ ብር የተበደረው አግዚያብሔር ነው አላለሁ።

እንዲያ ነው የመቀጠላችን ስንከሳር ባማረ የሕይወት አትሮኖስ ላይ ተቀምጦ የሚገለጠው። ዛፒ ልብስ ከገዛችልኝ ከሳምንት በኋላ ትምህርት ቤት ቁጭ ብዬ መቁረጫ የሌለው ሃሳብ ውስጥ ተዘፈቅኩ። አንደ ቀልድ ነበር ሀሳቡን የጀመርኩት። ልብሴ የብዙዎች ፊት እንዲበራ አደርጓል፤ መንገድ ላይ ሴቶች ያዩኛል። አንዳንዴ ማፍጠጣቸው ሲበዛ፣ "እነዚህ ሴቶች ግን ያልለበሰ ሰው፤ ያላብረቀረቀ ነገር 'አብስትራክት' ይሆንባቸዋል - ዶሎ አይታያቸውም" እያልኩ አሰባለሁ።

የርዳናስ ከንዴን ጨምድዳ መሄድ ከጀመረች ቆየች። ጓደኞቿ "'ኤከለሬይ' ነገር ነሽ ይሄ ልጅ ለካ ገና በፊት ውበቱ ታይቶሻል።" እንዳሏት ነገረችኝ። እግረ መንገዷን፣ "ዛሬ ስለለበስክ ሳይሆን በፊት ከነድሪቶህ ሰው ሳያይህ በፊት ነው የቀረብኩህ" መልዕክት ማስተላለፏም እንደሆነ እንጃ !! እውነቱን ለመናገር ሰው ራሱ ወዳድ ነው። በዚህ ሁሉ ሃሳቤ ውስጥ አንድ ጊዜ እንኳን ስለ አቲዬ አላሰብኩም። እኔነት ሲያደከመው የኖረ ሰው ሸክሙን ጣጥሎ ብቻውን የሚቆምበት ቀን ስለ ለይደለ - ጥፋታችንን ብቻችንን የምንጋፈጥበት፣ ራሳችንን የምንወቅስበት፣ ደስታና ስኬታችንን ብራሳችን ልፋት ያመጣነው ነው' የምንልበት - ቦታ ራሳችንን ብቻ የምንሆንበት፣ የዛን ቀን እንደዛ ሆኜ ነበር። ታዲያ ውጤት ነበረው። በውስጤ የተተረማመሱ ሀሳቦች በስርዓት ተሰደሩ። "ሞተዋል"

ያልኳቸው ጉዳዮች ለፈራቸውን አያራገፉ በሀሊናዬ አደባባይ በትንሳኤ ቆሙ። ፍቅር - የሴት ይሁን የእናት አገር ይሁን የፈጣሪ ያልለየለት ባለ ብዙ ዘርፍ ፍቅር ባዶውን የኖረ የልቤ መስቀል ላይ እንደገና የተሰቀለ መሰለኝ። እንደ ባንዲራ ቤሕይወት መዝሙር ታጅቦ ወደነፍሴ ከፍታ ቀስ እያለ የሚሳብ ፍቅር።

እንደ ሰው ስንቆጠርና ቤተሰብ፣ ጓደኛ፣ ጎረቤት፣ መንደርተኛ፣ አገሬው ቦታ ሲሰጠን ወይም የሰጠን ሲመስለን ከማሕበረሰብ ያፈነገጠ ውስጣዊም ውጪያዊም ስብዕናችንን ሰልቶን እንዲያሳምር ውስጣችን ራሱን ይመክራል። እንደዛ ነው የሆንኩት። እና ደግሞ ፈሪም ሆንኩ፣ የሆነ ነገር መፍራት ጀመርኩ ።

እንደ ሰው ከመቆጠር ስናልፍና አንፋሽ አከንፋሻችን ሲበዛ የሰልቶ መሬ የሆንን እየመሰለን እንደገና ያገናንበት እንረግጣለን። መልካም መካሪ ካገኘን ወደ ሰልፋችን የመመለሳችን ነገር ያውም በጭብጨባ ታጅቦ ይደገማል። ካልሆነ ግን ማንነት፣ ስም፣ አለማ፣ ስብዕና "እብድ የበላው በሶ" ሆኖ ይቀራል። የታዋቂ እውቅና መንኮታኮቱ፣ የአገር ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ በልክ እንዳልተሰፋ ቀሚስ መንዘላዘሉ፣ የትውልድ ሽሽት ከመጥበሻው ወደ እሳቱ የመሆኑም ነገር ሁሉ የማንነትን ሰልፍ መሳት ነው። አጉል ወደድኩ ብሎ ሰልፍ ስትጥስ የሚያጨበጭበልህ፣ ጠላሁ ብሎ ጎትቶ ከሰልፍህ የሚያስወጣህ በምላባት ምድር ጥላቻና ፍቅር አኩል የጥፋት መንገድ መሆናቸው የሚገባህ እንዲህ ራስህ ጋር ሃቅ ሃቁን ስትነጋገር ነው።

አናም ባነንኩ !! እኔ ማነኝ? እኔ አሸብር ነኝ። እናቴ አፀደ ትባላለች። በዚህች ምድር ላይ የስጋ ዘመድ የምንለው የለንም። እናቴ በየሰዉ ቤት እንጀራ ትጋግራለች፣ ልብስ ታጥባለች፣ እንደ ሰው ተከብራ አታውቅም። ተስፋ የምታደርገው እኔን ብቻ ነው። ብቸኛ አላማዬ እገር፣ ሕዝብ፣ ወገን አይደለም እናቴ ናት !!

ማንም በፖለቲካ አመለካከት ቢራኮት፣ ማንም ማንንም ቢከሰል ስሜት አይሰጠኝም። የትኛውም አምነት 'ወየልህ!' ቢል፣ በዚያ በዚህ ቢፈልግ በአምላኩ፣ ቢያሻው በፖለቲካው ተከልሎ ቢቧደን 'እችን ታህል' አይገርመኝም። እናቴን ነፃ ለማውጣት የሕይወት ጦርነት ውስጥ ያለሁ ታጋይ ነኝ፤ ሆቺ ሚኒ ነኝ ፣ ግዙፉን 'አምባገነን ሕዝብ' ከትንሽ የእናትነት ግዛቴ የማባርር ቼጉቬራ ነኝ፤ በስግብግብና ራስ ወዳዶች ክንድ ሰር በፅናት አልፈ የሚስኪን እናቴን ከፍታ በሚያረጋግጥ አብዮት ምድርን የምንጥ - አንጀላ ዴቪስ ነኝ፣ ፋራንዝ ፋኖን ነኝ።

የእናቴ ጠላት ድህነት አይደለም - 'ስለነፃነት የሚቀባጥረው ሕዝብ' አንጂ። የሕዝብ ልጅ የሚበል ቀልድ አይገባኝም። የእናቴ ብቻ ልጅ ነኝ። ፅንፈኛ ነኝ፣ ዘረኛ ነኝ፣ አከራሪ ነኝ - ከእናቴ ጋር በሜፍን የተሰለፍኩ 'ሌላው የተረገመ ነው' ብዬ የማምን ዘረኛ ነኝ። 'ከእናቴ ወዲያ ታጋሽ፣ ጨዋ፣ ለሰው ልጅች አሳቢ፣ አዋቂ ጀግና ዘር የለም የምል !! አከራሪ ነኝ፤ ከእኔ እናት ሌላ ሌላ እናት እናት የማይመስለኝ። እናም ጠላቴ ሕዝብ ነው። ሕዝብን መበቀል ቀላል ነው። ምክንያቱም ጠላትህ የትም የሚገኝ እንደ ትቢያ አያፈስክ የትም የምትበትነው ገለባ ነው። አሱሶማሪ ብትሆን

ከጠመጃህ ስር ጠላትህ አለ። ጥላቻ አዕምሮው ውስጥ እየዘራህ ሰይጣን ታፈራለህ። ሹፈር ብትሆን የጠላትህ ነፍስ በእጅህ ነው፣ ይዘኸው ገደል ልትጥለው ትችላለህ። ማዝገኛ ወላ አናፂ ብትሆን የምትሰራለት ቤት በላዩ ላይ ፈርሶ እንዲቀብረው የማድረግ ሰልጣን በእጅህ ነው። ባለሰልጣን ከሆንክማ፣ "አባቡም ከአግርህ፣ ዱላውም ከእጅህ" ብትፈልግ ቀይሸብር፣ ወንጀለኛ፣ ምናምን ቅብርጥስ ብለህ በየመንገዱ ትደፋዋለህ። ካሻህ ኤድሚ ልኩን በድህነት እንዲማቅቅ ታደርገዋለህ።

ደግሞ ለበቀልህ 'ማን ይተባበረኛል?' ብለህ አትሰጋም፣ ሕዝቡ ራሱ ለመባረክ ስትቆም ነጠላውን አጣፍቶ ከጎንህ ነው። ለማረድ ስትቆምም ቢለዋውን ስሎ ከጎንህ ነው። ከሌላ ዓለም ረዳት መጥራት ላያሻህ፣ ወንድሙ ላይ የሚጨከን 'ፈሪሃ አግዚአብሄር' ያለው ሕዝብ ጠላትህ ከሆነ አደግድገ ለበቀልህ ታዛኝ ነው።

ደነዝ ሕዝብ፣ ደነዝ መሪ እንደሚወልድ አስኪገባው ትጫወትበታለህ። ጭራቅ ሕዝብ፣ ጭራቅ መሪዎች እንደሚፈለፍል አስኪያውቅ ታሸዋለህ። አዎ ጠላትህ ሕዝብ ከሆነ በቀልህ ቦታ እና ሂዜ ላይመርጥ የትም ሊፈፀም ይችላል። ደግሞ ታዝበህ ከሆነ ከልብህ የሕዝብ ጠላት ከሆንክ ሕዝብ ይወድሃል። ስላንተ ይዘምራል። 'ጅግና!' አያለ ሲያወሳህ ይኖራል። ለምን መሰለህ፣ ውለጡ ያለውን ጭካኔ ነው በአደባባይ ያሳየኸው !!

ወዳጅን አየካደና እየቀረጠፈ ውለታውን ትቢያ የሚያለብስ ሕዝብ የእናቴን ጉልበት እንደምስጥ መጥቦ 'እንጨቷን' አስቀረ ብዬ አላዝንም። ሰው እሆናለሁ። በእኔ ሰው መሆን ትላንት ፍሬ የምትሰጥ ለምለም ዛፍ የነበረች ሕዝብ ያደረቃት እናት የምትባል 'እንጨት' ከማገዶነት አቆፍ ተመልሳ እንደ አሴይ ብትር ትለመልማለች።

ያኔ በልጅ ልጆቿ ልብ ውስጥ ከቅዱሰቅዱሳኑ ለዘላለም በክብር ትቀመጣለች። ...ቱ ! አሸብር አይደለሁማ !

አዎ ታጋይ ነኝ !! ታጋይ በሴት አይፈተንም። ሴቷ ቀይ አግር ቢኖራትም፣ ዐይኗ ቢያምርም፣ ተንጠራርታ ብትሰምም፣ ስሟ ዮርዳኖስ ቢሆንም፣ ማታ ማታ ትዝ ብትልም፣ ከነድሪቶዬ ብትቀርበኝም የጠላት ልጅ ያው ጠላት ነው !! ዮርዳኖስን ርግፍ አድርጌ ተውኳት !

ከባድ አልነበረም። እንዲያውም ዐይኔን ስገልጥ ዮርዳኖስ ለእኔ ሽክም ነበረች።

ቡቢልጣ ብልጥ ሴትነት ነገን አሻግራ ያየች፣ መረቧን ተሸክማ ግራ በገባው አሳ ዙሪያ የምትሽከረከር ብልጥ ሴት። እሾሁን አራግፋ ልትቀርጥፈው !! ተውኳት።

"ልብሱን ሲቀይር ተወኝ" አለች ተባለ፤ እሷ የድሮ ልብሴን የሆነች ይመስል። ብዙ ፆታዊ ግንኙነቶች ላይ አለመፈለግ ከህደት ተደርጎ ይታያል።

ክፍል አስራ ዘጠኝ

አስራ ሁለተኛ ክፍል ከፍተኛ ውጤት አምጥተው ዩኒቨርስቲ ሊገቡ ከተዘጋጁ ጥቂት ተማሪዎች መካከል አንዱ እኔ ነበርኩ - አራት ነጥብ ፣ አራት ነጥብ የሚባል አንድ ጠመንጃ ይዤ ለትጥቅ ትግል ዩኒቨርስቲ ወደሚባል ጫካ ልዘምት ተዘጋጀሁ::

ዛፒ አንድ የናጠጠ የሃብታም ልጅ ሊኖረው ከሚችለው በላይ ልብስና ጫማ፣ ሊሎችም ቁሳቁሶችን ከአገር ዉስጥ ብቻ ሳይሆን ከቤተሰቦቿም ጭምር አስመጥታ አምባሻበሽችኝ:: ምርር ያለ ቤተሰባዊ ፍቅር ውስጥ ገብተን ነበር:: ዐይኗ ይወደኝ ነበረ ያስታውቃል:: በተላይ አስራ ሁለተኛ ከፍል ተፈትኜ ውጤት ስጠብቅ ከዛፒ ጋር ያላለፍነው ጊዜ የማይረሳ ነበረ::

ያልዞርንበት መዝናኛ አልነበረም:: የትም ስትሄድ ከኛ አለሁ:: እኔን "ወንድሜ" ብላ ማስተዋወቅ እንዴት እንደሚያኮራት ዐይቼ ራሴን ለወንድምነት አሳልፌ ሰጥቻለሁ:: የእውነትም ደግሞ ወንድሟ አመሰል ነበረ:: ዛፒ ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለአቲዬም ደግነቷ ተንሰራፍቶ ነበር:: ማታ ማታ ቡና ተፈልቶ በረንዳ ላይ ወይም ሳሎን ደስ የሚል ጊዜ ሦስታችንም እናሳልፋለን::

ዛፒን ከምኞት ጋር ያገለለ ዓለም እኔና አቲዬንም ከጉስቁልና ጋር የተፋ ሕይወት በምን ሂሳብ እንዳቀላቀለን ባይገባኝም ቅልቅሉ ግን ከልብ የሆነ ቤተሰባዊ ትስስርን ፈጥሮ ነበረ::

እንድቀን "አቲዬ!" አልኳት፣

"አቤት!"

"ምን ብሆን ደስ ይልሻል?"

"ኧረ እኔ ምን አውቄ፣ እኔ ትምርት የለኝ አላቀው" ብላ ሳቀች::

"ማዲለሽም ተምሬ እኔ ልጅሽ ምን ብሆንልሽ ደስ ይልሻል?"

"እሷን አማከራት አስቲ" አለችኝ ዛፒን ማለቷ ነበር::

"አቲ ዛሬ ካልነገርሽኝ አልለቅሽም ራስሽ ንገሪኝ!"

ትንሽ አሰበችና፣ "ዶክተር" አለችኝ በሳቅ:: ሁለታችንም በሳቅ ፍርስስስስ አልን::

እነጋገሯ በዕርግጥም ያስቅ ነበር:: ህክምና የመማሬ ብቸኛ ምክንያት ይሄው ነው!! ሕዝቤኝ ወገኔን ከበሽታ ለመታደግ ምናፃፆን ብዬ አልነበረም!! እናቴ፣ የምወዳት እናቴ፣ የአዕምሮዋ ጥግ የታላቅነት መጨረሻ የመሰላትን ነገር ለመሆን እንጂ!!

የዩኒቨርስቲ ቆይታዬ የደስታና የቅንጦት ነበረ:: ዛፒ ውብ ሆና ግቢ ስትመጣ ዐይኑን የማይጥልባት ተማሪ አልነበረም:: ብዙ ሰው እናቴ ያደርጋት ነበረ:: ሴቶቹ የዛፒ ጫማና ልብስ ላይ ዐይናቸው

ይነሰነሳል:: ከዚህ የቆንጆ ዘር በረከቱን ሊካፈሉ የቋመጡ፤ በሰልምልም ፀይን፣ በጪሞ መሳይ ፈገግታ ሊቀርቡኝ ሲዞሩኝ ነበር:: 'ፀዳ ያለ ልጅ' ይሉኛል:: ሃሃሃሃሃሃሃሃሃ !! አላልኳችሁም፣ በድፍን ማምት ወደድን ብለው ከሰልፍ ሊያስወጡ መሞከር ይሄ ነው እኮ::

የወደዱኝን ያክበሩኝን ሁሉ በቁምነገር ባለመቁጠር በቀሌን እንድ ብዬ ጀመርኩ:: ኮተታሞቹ የማቢ ልጆች ራሳቸውን ችለው መቆም ይፈራሉ:: ሴቶቹ ወንድ ታዛ ሰር ካልተጠለሉ ሰው የሆኑ አይመስላቸውም:: ወንዶቹ የተፈጥሮን ፆታዊ መፈላለግ ሳይንስ ሊያደርጉት ጅራት ሲቆሉ፣ ግራ የገባቸው የከተማ ልጆች ጭልጥ ወዳለው ማሕበራዊ አንስሳነት ሲወርዱ፣ በማቢያቸን ውስጥ እንደበው መኖርን ያጣጣምኳት እኔ ክፍ ባለ ከብር እየተማርኩ ሁሉንም ተማሪ ፅንፍ በሌለው ጥላቻና ንቀት አመለከት ነበረ::

ሾቀውን የሚወድ ሕዝብ ግን ከጎኔ ነበር ! አሹዬ፣ አሹነት፣ ..ሹ፣ ..ሽቢ፣ ...ሹሹ፣ ከቢተሰቦቻቸው የወረሱት አባብነት የሰም ማንድ ላይ ሲጠመጠም ላለመነደፍ ልቤን ቆዳ አልብሼው ነበረ:: ማቆላመጥ የሚወድ ሰው ጤነኛ አይመስለኝም:: እሞክበርባሪ ነጋዴ ነው የሚመስለኝ:: በየሰሙ ላይ 'ዬ' መለደፍ የፍቅር ሃዋሪያ መሆን ይመስላቸዋል::

የቢተሰቦቻቸው መርዝ አልሰራ ሲል፣ (የተመረተበት ጊዜ አልፎ እንዳይሆን ሰግተው) ከፊልምም ከመጽሄትም አዳዲስ መርዝ አየተሸከሙ ብቅ ይላሉ:: በአነጋገር፣ በአለባበስ፣ በአስተያየት፣ በአግር፣ በዳሌ፣ በጣት፣ በፀጉር እናም በመጨረሻ በሃሜት፣ "ይሄ ልጅ ሴት አይመቸውም እንዴ? ማን ያውቃል? ዘመኑ ከፉ ነው እናትዬ፣ እንትን እንዳይሆን"::

እነሱ ጋር ያልሆነ፣ እነሱን ያልፈለገ ጭራ አለው፤ ደብቆት ነው እንጅ:: ቀንድ አለው፣ ጥፍር አለው:: በዚህች ምድር ላይ እንደመናቅ የሚያም ነገር የለም:: ንቀቴ አመማቸው !!

ቡምምምምምምምምም እውነት ፈነዳ !! "ይሄ ቀብራራ አዚህ ይኮፈሳል እናቱ እንጀራ ጋጋሪ፣ ልብስ አጣቢ ነች አሉ":: ጮማ ወሬ ተገኘ:: ዳሌያቸውን እየናጡ ፀጉራቸውን እየነሰነሱ፣ ጅራታቸውን ከሚቆሉላቸው ወንዶቻቸው ጋር አወሩ:: ተሳለቁ:: ሊያሸማቅቁኝ ሞከሩ፤ ራሳቸውን ችለው መቆም ሲፈሩ፣ የአፉኝት ልጆች በልበሰ አጣቢ ልጅ ሳቁ:: የቤታቸውን አጠራቅመው ለዘመን መለወጫ ቤታቸውን የሚያፀዱ ሁሉ፤ ሰው ለራሽ ጠጉራቸው ራሳቸው ላይ ጀልቶ ቢሆም በጸሎት የሚፈታ ሁሉ፣ ተብረቅርቀው 'ሰው ነን' ሊሉ:: ልክ ለልክ ከተዋወቅን ቆየኝና ይሄም ጥይታቸው ከሸፈ::

ቢሆንም እኔ እሸብር 'ላይፍ' በሚሉት ጋጋታ ውስጥ ከሙታን ጋር ማነበር አለመጠጣቴ እንዳበገናቸው ወደ 'ዱፍትርናው' ተንደረደርኩ:: ልማዴ ነው ሰለኔ የሚንጫጫቤትን ትንሽ አያደረግኩ ማለፍ:: እንከን ፈላጊዎች ሚዛናቸው ከአሉባልታ ሌላ ምን ሊሰፍር...ቡፋፋፋፋ፣ ለማሸነፍ የተጠራሁ መሆኔ ሲገባኝ ተሸናፊ አቆላምጦም ይሁን ሳያቆላምጥ ሲጠራኝ አቤት አልልም:: አቤት ብትላቸው ቃላቸው አንድ ነው፣ "ኑ ና አብረን እንውደቅ!"

ክፍል ሀያ

የሕክምና ትምህርቴን ከጀመርኩ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የአንዲት ሴት አስከሬን እየሁ። እድሜዋ ሃምሳ የነበረ አሁን ግን ዘላለም የሆነ ጠይም ሴት። አስከሬኑ ሰተማሪዎች የተግባር ልምምድ ትምህርት የሚውል ነበር። ሁላችንም ለአስከሬን አዲስ ስለነበርን አንዳንዶቹ ደነገጡ፣ አንዳንዶቹ ተንቀጠቀጡ፣ አንዳንዶቹ ሊያስመልሳቸው ሞከረ (አንዲት ልጅ አስመልሷታል) - እኔ ግን እንባዬ መጣ።

ሰው ሞቶ ሲያዩት አንዴት ያሳዝናል - ኢትዮጵያዊ ሞቶ ሲያዩት እንዴት ያሳዝናል። የአንድ ሚሰኪን ኢትዮጵያዊ አስከሬን ማየት ከሞት ከራሱ የበለጠ ያሳዝናል፣ ያስደነግጣል። ከዛ ቢኋላ በስራ አጋጣሚ በርካታ የፈረንጅ አስከሬን አይቻለሁ። ግን የፈረንጅ አስከሬን እንደ ኢትዮጵያዊ አስከሬን አያስደነግጥም። ባዕድ ምድር ላይ የኢትዮጵያን ባንዲራ ስትመለከቱ የሚሰማችሁ የደመንፍስ ድንጋጤ ዓይነት፣ ግውዝ ኢትዮጵያዊ አስከሬን ስታዩ ሕይወት ያለው ኢትዮጵያዊነት ረብቦበት ይታያችኋል።

ኢትዮጵያዊት እናት ሞታ ስትታይ አንዴት እንጀት ትበላለች መሰላችሁ። ዝም ይላል የሞተ ሰውነ እጅና አግሩን አላርፎ ዝም !! ሰው እየጮኸ፣ እየተንጫጫ ወደ ዝምታው ነው የሚሮጠው። እና ይህች ሴትዮ ዝምታዋ ላይ ደርሳ ነበረ። "ምነው ዘርፌ በሆነች"።

ከፉ ነገር አይቼ ለዘርፌ ያልተመኘሁበት፣ ለቀለመወርቅ ያላጨሁበት ብቸኛ ቀን ነበር። እንደውም 'ዘርፌንም ከዚህ ይሰውራት' አልኩ። አንዳንድ ሰው በቁጣ፣ "ዝም በል!" ሲል "እፍህን ዝጋ" ማለቱ ብቻ አይደለም። ከዛ ያለፈ አርግማን ነገር አለው። 'መምራት የምንፈልገው ሬሳን ነው ካላሉ በስተቀር ለምንድን ነው መሪዎች ህዝባቸውን፣ "ዝም በል!" የሚሉት። ዝምታ ሰላም አይደለም፣ አሁን ይህች ሴት 'ሰላማዊ' ናት ? ዝምታ ኩርፊያ አይደለም። ይህቺ ሴት አኩርፋለች ? ዝምታ ትዕግስት አይደለም፣ይህች ሴት ታጋሽ ናት ?

በምድርም የተመቻት ዓይነት ሴት ስላልነበረች ነው መሰል በጣም የተጎሳቆለ ሰውነት ነበረ ያላት፤ አስከሬን እንቱ አይባልም የተባለ ይመስል እንቺ ነበር ሁላችንም የምንላት። እንግዲህ መፅሐፉ፣"የብልሆች አግር ወደ ሀዘን ቤት ነው" የሚለው ለምን እንደሆነ የገባኝ አሁን ነው። ሕክምና የምማረውም ለምን እንደሆነ የገባኝ አሁን ነው።

"ፍጠን እሸብር ሰዎች ዝምታቸው ላይ ሳይደርሱ" የሚል መልዕክት በውስጤ ያጣድፈኛል።

ሰዎች ከፉም ይሁኑ ደግ፣ የሚጠቅምም ነገር ይናገሩ የማይጠቅም ዝባዝንኬ፣ ብቻ ዝምታቸው ላይ እንዳይወድቁ መሮጥ አለብኝ። ልቤ ታዲያ ደረቴን ፈጥርቆ የወጣ አስኪመስለኝ ይመታል፣ ታፍኖ የኖረ ሚሰኪን ሳያልፍለት አንዳይሞት፣ በደሉን ሳይተነፍስ ዝም አንዳይል፣ የብዙ ብዙ በደል መቃብር እንደሆነ ወደ መቃብር እንዳይወርድ እኔ አሸብር ዶክተር እሆናለሁ። ሰው ከቀኑ

አያልፍም ቢባልም ቅሉ፤ ቀኑን አስካላወቅነው ድረስ ቀን ለመጪመር እንሮጣለን - ማምሻም እድሜ ነዋ!!

ለእኔ ለሙ በሁለት ይከፈላል፤ አናቴ አቲዱ እና ሌላው !! አቲዱ ትኑርልኝ፤ በቃ መኖር ያለባት ለሙ ናት:: እኔ ልጇ ባልሆንም አቲዱ መኖር አለባት:: ሌሎችም ይኑሩ፤ አቲዱ መኖርዋን፣ ኖራም ያንን አዘቅት መሻገሯን እንዲመሰከሩ !! እንግዲህ አንድ አስክሬን ነው ይሄን ሁሉ የሚያላስበኝ::

አኔኮ አስክሬን ሲባል የሚያብረቀርቅ ልብስ የሚለብስና ለአራት የሚሸከሙት አልጋ ነበር የሚመስለኝ:: ሞት እንዳለ አወቅኩ፣ ሰማሁ ሳይሆን አየሁት:: ሞት ያፈረሰውን የሕይወት ዙሟ አየሁት:: ያውም አናት የምትባል ዋና ከተማ:: መምህራችን ረዳት ፕሮፌሰር ዘሩ ፊታችን ለተጋደመው አስክሬን የሚሰጡትን ትልቅ ክብር እና አንክብካቤ ሳይ ገረመኝ:: አንዳንድ ዶክተሮች በሕይወት ላለ በሽተኛ ከሚያደርጉት እንክብካቤ በጣም የተሻለ ነበር:: ይህ አስክሬን ከዛ በኋላ ያለ ሕይወቴን ቀይሯል:: አስተሳሰቤን ቀይሯል:: ሞት ማለት አርግማን መሆኑን እምኖለሁ (ሳይንሱ ባይልም::) ዝምታ ጤናማ አይደለም፣ ከጭቆና ሁሉ የከፋው ጭቆና "ዝም በሉ!" ማለት መሆኑን አስክሬኑ አየጮኸ ይመሰክራል::

ለሰዎች ማዘን፣ በተለይ ዝም ለሚሉ ሰዎች የጀመርኩትም ያኔ ሳይሆን አይቀርም:: ቢሆንም አስክምመረቅ ሲበዛ ዝምተኛ ነበርኩ:: ውስጤ የሞተ ነገር ነበረ - ትንሳኤ የሚያሻው:: ትንሳኤው በር ድረስ ታደርሰኝ ዘንድ የተሰጠችኝ ደግሞ ዛፒ ነበረች:: የኔ ሚስኪን ዛፒ፣ ማራ የገባት ሙሴ፤ የድህነትን ባህር በፍቅር በትር እየከፈለች አኔና አናቴን ያሻገረች መሪ ነበረች::

ዛፒ ምንም እንኳን በግል ሕይወቷ ደስተኛ ባትሆንም፣ ሙሉ የዩኒቨርስቲ ወጪዬን ልክ በፍርድ ቤት እንደተወሰነበት ሰው ላታስተጓጉል ትሸፍንልኝ ነበር:: አደረገችልኝ ብዬ አይደለም የማመሰግናት፤ ደግነቷ አያሸማቅቅም፣ ከርሷ ብር መውሰድ መብቴ እንዲመስለኝ አድርጋ ነው የምትረዳኝ:: "አሹ አስኪ ዛሬ ጥናት ከሌለህ ራት ጋብዘኝ" ትልና ራት ትጋብዘናለች::

በእኔና በዛፒ መካከል ለቁጥር የሚያዳግት የእድሜ ልዩነት አለ፣ ግን ጓደኛዋ የሆንኩ መስሎ እንዲሰማኝ አድርጋኛለች:: የመጨረሻዋ ውብ ሴት ብትሆን እንኳን ከልሰልትነት ዙፋን ታምዘግዝጋ ታቸ የምትገኝበት የዝቅታ ዘመን አለ:: ለሴት ልጅ ይሄ ከባድ ነው:: ቢሆንም ሴቶች ከወንዶች በላይ ውድቀትን ዘንጠው እየሳቁ መቀበል ይችሉበታል:: በአርግጥ ዛፒ አንዳንዴ በተጨናነቀ ሁኔታ ውስጥ ባለሁበት ሰዓት ከግቢ ትጠራኛለች፣ እንቢ ማለት አልችልም::

አቤት እሄዳለሁ:: ራቧን ጣል አድርጋ ደብሯት አነኛታለሁ:: ከዚህ ድብርቷ ላወጣት እሞክራለሁ::

በየቀኑ እደውልላታለሁ፣ ሲመቸኝ ወጣ ብለን እንገናኛለን::

የአዲስአበባ ወንድ እንደፈራ፣ ዛፒም እንደደበራት አምስት ዓመታት ነንዱ:: በዚህ ብቸኝነትና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆናም ግን ደግነቷ ልክ አልነበረውም::

ተመርቄ እስክምወጣ ሁለት ጊዜ ቤተሰቦቿ ጋር ውጭ ሄዳ ወደ አንድ ዓመት ስትቆይ እንኳን ጠቀም ያለ ፕንዘብ ለእኔም ለአቲዬም መላኳን አጽርጣ አታውቅም ነበር። ይፈጥንብኛል ታሪኬ። በፍጥነት በሚበር መኪና መስኮት የምቃኘው እስኪመስለኝ ሁሉም ነገር ወደኋላዬ የሚፈተለከው በደንብ እንኳን ሳልመለከተው ነበር።

አቲዬ ቀስ በቀስ የሰው ቤት ሰራዋን እያቆመች የተወሰኑ ቤቶች ብቻ ለዛውም ሰርግ ሲኖር በኮንትራት ወጥ መሥራት የመሳሰለ ሥራ ላይ ብቻ ተወሰነች። ሰውነቷ ግን በጣም ተጎሳቁሎ ነበር። ድህነት የማይፋቅ አሻራውን ቆዳዋ ላይ አትሞ ቀርቷል። እጆቿ 'መሻከር' የሚለው ቃል በማይገልፀው መልኩ ተፍረከርከዋል። ዐይኗ ለዘመናት በተጋፈጠችው የአሻሮና የማገዶ ጭስ እንዳያገገም ሆኖ ተጎድቷል። ከዚህ ሁሉ በላይ ግን አቲዬ ልክ በሌለው ፍርሀት ውስጥ ተዘፍቃ ነበር። ከቀን ወደ ቀን ዝምታዋ እየከበደ የሚሄደው። ዝምታ አፈራለሁ። ዝምታዋና ፍርሃቷ በጣም ይበዛብኛል - በተለይ ፍርሃቷ።

አንዳንዴ በዚህ ባህሪዋ እበሳጭና አጮህባታለሁ። "ምን ላድርግ ብለህ ነው አሹዬ" ስትለኝ እንባዬ ይመጣል። የመንደሩ ትንንሽ ልጆች ጋር መንገድ ላይ ስትገናኝ ቆማ ልታሳልፋቸው ትሞክራለች። ኳሶቹው ወደ ግቢ ቢገባባቸው በሁለት እጇ አንስታ ትሰጣቸዋለች። የሆነ ቦታ ሄዳ እንደ ትልቅ ሰው ወንበር ላይ ከመቀመጥ ይልቅ እየፈራች ምንጣፍ ላይ ወይም ቁጢጥ ብላ አንድ ጥግ ትቀመጣለች። ማንም ሲመጣ ወንበር ትለቃለች። ታክሲ ውስጥ ሳይቀር አንድ ቀን ለአንዲት ልጅ ቦታ ልትለቅ ስትሞክር እጇን ይዤ በብስጭት አስቀምጫታለሁ። በቃ አዕምሮዋ ውስጥ "ትንሽ ነሽ" የሚል ክፉ መሀተም አኑረውባታል።

ድህነት ፕንዘብ የሚገዛውን ነገር ብቻ አይደለም የሚያሳጣው። በነገሮች ሁሉ ሰልፍህን ከኋላ ያደርገዋል። አንዳንዴ ከአቲዬ በአስተሳሰብም በፕንዘብም የሚያንሱ መንደርተኞች አቲዬን ሲያዩ ራሳቸውን ሊቆልሉ ሲሞክሩ አያየሁ ይገርመኛል። በቃ ይህቺ አዲስ አበባ ዝቅ ሲሉላት ሰው እናት ላይ ቆማ ልትጨፍር ይዳዳታል - ራሷ እናት ላይ ማንም ሲፈነጭባት እትነቃም እንጂ !!

ክፍለ ሀየ አንድ

ዩኒቨርስቲ ውስጥ የነበረኝ ሕይወት የአንድ መልካም ተረት ፍፃሜ ይመስል ነበር። ልክ "... ከዛም በሰላምና በደስታ ይኖሩ ጀመር" ተብሎ እንዳለቀ ተረት። ብር አልቸገርም ነበር - እድሜ ለዛፒ። ጊዜ ባገኘሁበት ቀን ሁሉ አቲዬን አያታለሁ። በየቀኑም እደውላለሁ። አቲዬን በስልክ ማውራት ከባድ ነው። በቃ ጥያቄዎቿ አንድ ዓይነት ናቸው፤ "እንጀራው ጥሩ ነው...?"፣ "ልብስህ አልቀሸሸም...?"፣ "ንባብ አታብዛ፣ በጊዜ ተኛ፣ ራስህን ያምህል፣ ማታ ማታ ጋቢ ልበስ፣ አሹ... ደሞ እጅህን ወጣ ወጣ አታድርግ የሰው ፀይን ጥሩ አይደለም" ሁሉንም በጥሞና አዳምጣታለሁ፤

ስለራሷ ስጠይቃት "እኔ ምን አለብኝ ብለህ" ብቻ ነው መልሷ። አቲዬ የሚያስቃይ የወገብ ህመም

እንዳለባት እንኳን ያወቅኩት ከተመረቅኩ ከሁለት ዓመት በኋላ ነበር። እንዳልፈጨነቅ ደብቃኝ፤ ፍፁም በተረጋጋ ሕይወት ውስጥ ትምህርቴ ላይ ብቻ መሉ ሐሳቤን ሰብስቤ እንዳጠና...። የሰው አፈጣጠሩ አየገረመኝ፣ የበሽታ መከሰቻው ምክንያት ብዛት እና መንገድ አያስደነቀኝ፣ በዛውም የሰው ልጅ ምህረቱ ባይበዛለት በቀናት እድሜ ከምድር ተጠራርጎ የሚጠፋ ትቢያ መሆኑ አያስደመመኝ፣ ሰው የምጠላው አኔ የሰው ጣላት የሆነ በሽታ ጋር ድብብቆሽ ስጫወት ወደ መመረቂያዬ ተቃረብኩ።

"ሴት አይቀርብም" ይሉኛል። ይሄም እንደ ጨዋነት ተቆጥሮልኝ ነበር። እኔ ባጠቃላይ ሰው ነው የማልቀርበው። ለምን ለይተው፣ "ሴት አይቀርብም" እንደሚሉኝ ይገርመኛል። ሊጀመር ማንም ጋር በሚያገናኘኝ የትምህርትና መሰል ጉዳዮች ከሴትም ይሁን ከወንድ ርቄ አላውቅም።

ዩኒቨርስቲ ውስጥ ለዛውም የሕክምና ትምህርት ላይ ብቸኛ መሆን ቀላል ነገር አይደለም። ቢሆንም ከማይረባ መጠላለፍና በሕይወቴ አንድ እርምጃ አልፍ በማያደርገኝ ጉዳይ ውስጥ ገብቼ የመዳከር ፍላጎቱ አልነበረኝም። ለምሳሌ ፆታዊ ፍቅር !! ወንድ እና ሴት ቁመው ወይም አንድ ጥግ ተቀምጠው ያንን ሁሉ ሰዓት ሲቆዩ ምን ጉድ እንደሚያወሩ ይገርመኛል። ፍቅር ለምን አይይዘኝም ብዬ ያሰብኩት አንዲት ልጅ አንዳፈቀረችኝ የነገረችኝ ጊዜ ነው። ማህሌት ነው ለሚ፤ መጀመሪያ ስታፈጥብኝ አጋጣሚ መስሎኝ ነበር፣ ሲደጋጋም የሆነ ነገር ፈልጋ ይሆናል ብዬ ቻላ አልኩት። ከዛ ከበቡችኝ። አየር ሆነች። ላይብረሪ ካለሁ፣ አለች። የሆነ ቦታ ከተቀመጥኩ፣ ከሆነ ቢታው ፊትለፊት፣ ከኋላ ወይም ከጎን አለች። ባለፍኩበት ታጋጥመኛለች። ከሰላሳ መንታ እህቶቿ ጋር ወደ ዩኒቨርሲቲው አብራ የገባች አስኪመስለኝ በዛችብኝ። በመጨረሻ ወደደኩህ አለችኝና አርፍ !!

እንደው አጋጣሚውን አልለፈው ምንስ አባቴ በ.ከደኝ ባባቱ ወንድ አይደለሁ አልኩና ልሞክር ወሰንኩ፣ ግን ልጅቱ በቀጣዩ ቀን ሰለቸችኝ !!

ቢቆ 'አግዘአብሔርን ባፈቅር ይሻላል የሴት ፍቅር አያዋጣም' አልኩ። ሳይቆይ ግን ዓለም አግዜርን የሚያፈቅርበት አካሄድ እኔ ከማፈቅርበት ጋር አልገናኝም አለኝ። አንድ አግዜርን በስንት መንገድ እንደሚያፈቅሩት ስመለከት አፈቃቀሬ የተሳሳተ ይሆን እንዴ ብዬ ፈራሁ።

እንድ ቀን ከግቢ ወጥቼ የተማሪው ኪስ ሞላ ሲል የሚያዘወትራት ፊስቶራንት ሄድኩ። ምሳዬን አዘዝኩ ስጠብቅ የዲፓርትመንቴ ልጆች መጡና ፊት ለፊት ተቀመጡ - ሦስት ሴቶች። ብዙ አዘንኩ ስጠብቅ የዲፓርትመንቴ ልጆች መጡና ፊት ለፊት ተቀመጡ - ሦስት ሴቶች። ብዙ ሴቶች ሲሰበሰቡ ጎብረተሰቡ የሚነባቸውን የፆታ ተፅእኖ ቀንበር የሰበሩት ይመስላቸዋል መሰል ድፍረት ይጨምራሉ - ፍክክ ብለው ማሣውራት መሳቅ ምናምን...።

ያዘዝኩት ምግብ ሞሱን እያግተለተለ መጣ። አስተናጋጁ ነጎትን በሰሆን ይዘልኝ የመጣች ነው የመሰለኝ። ርቦኝ ስለነበረ የምገበው ሽታ የተለየ ሆነብኝ። እንጉቴን ዝቅ አድርጌ ዐይኖቼን ጨፈንኩ፣ ጸሎት ይመስላል፣ ግን አልነበረም። በሚራሽ !! መቼ እንደጀመርኩት ባላስታውስም፣ በተለይ

ርቦኝ የሚበላ ነገር ሳገኝ፣ ደሰ የሚል ምግብ ሲቀርብልኝ ሁልጊዜም እንዲህ አደርጋለሁ። ጥልቅ የሆነ ሰሜት ውስጤን ይሞላውና የሚያስገርም የእፍታ ዝምታ ውስጥ እገባለሁ። ለምተው የረሀብ ዘመኔ እጭር የህሊና ጸሎት !

ቀጥ ሰል ሴቶቹ በግርምት አፋቸውን ከፍተው ያዩኛል። ፊታቸው ላይ ማከበር፣ መቀራረብ መፈለግ ነበር። ልክ እንደማላውቃቸው ሰዎች ችላ ብያቸው መብላት ጀመርኩ። በልቼ እንደጨረስኩ ቡና አዘዝኩ። እንዴ ወይኔ መጣች...ኤጭጭጭጭ !

"ሰላም ላንተ ይሁን፣ አሸብር!"

"ሃይ!" አልኳት ባጭሩ፣ ስናገር ሊያገላኝ ነበር።

"መቀመጥ ይቻላል ?" አለች ለመቀመጥ መንገድ ጀምራ። ከዛም እንደ እኔ ቡና አዘዘችና ወሬ ጀመረች።

"ስታመሰግን አየህህ ከርስቲያን እንደሆንክ እናውቅም ነበር" አለች ፈገግታዋ ፊቷ ላይ እየተንተገተገ፣ አልመለስኩላትም።

"ፈሎሽፕ አለን ብንጋብዝህ ደስ ይለናል። በቃ አብረን ጌታን ማምለክ ነው አላማው። ዕርብና ቅዳሜ ከሰዓት ነው ፕሮግራሙ" የሆነች ወረቀት ሰጠችኝና እመሰግናኝ ቡናዋን ሳታጋምሰው ሄደች። ከጓደኞቿ ጋር ተያይዘው ወጡ። ተመራርጠው ጓደኛ የሆኑ ይመስል ሦስቱም በቁመትም በቅጥነትም አንድ ዓይነት ነበሩ።

እንግዲህ ይሄ ምግብ ሲቀርብ ማቀርቀሬ ነው የ"የአብረን እናምልክ!" ግብዣ ያመጣብኝ፣ ወላ ያመጣልኝ። ዝም ብዬ ሳስብ "እነዚህ ሊጅች ጋር እንዴት ነው በጋራ የምናመልከው?" ብዬ ገረመኝ። እኔ ለየትኛውም እምነት፣ ለየትኛውም አምልኮ ግድ ያለኝ ሰው አይደለሁም። በሕይወቴ ሙሉ የፀለይኩበት ቀን ኖሮ አያውቅም። እግዚአብሔር የእኔ ብቻ ሰለሚመስለኝ ሌሎች ጋር በጋራ ማምለኩም፣ መዘመሩም ምኑም ትዝ ብሎኝ አያውቅም።

እግዚአብሔር እኔ ጋር በመተባበር አዲስ አበባን ድራሽዋን ለማጥፋት አስከመረቅ እየጠበቀኝ አልያም እንደ ኖህና ቤተሰቡ እኔና እቲዬ ወደ መርከቡ እንድንገባ ፈልጎ የጥፋት ውሀውን ያዘገየው ሰለሚመስለኝ ማንም ጋር ማምለክ ፈልጌ አላውቅም። ስለዚህ በተጋበዝኩበት ቀን ቀረሁ። ንዝንዛቸው ግን መቆሚያ መቀመጫ አሳጣኝ። አንድ ቀን፣ "ይቅርታ የምትሉበት ቦታ መሄድ ስለማልፈልግ ካሁን በኋላ በዚሁ ብናቆም" አልኳት አንዷን በቁጣ።

አዎ ተቆጥቼ ነበር !! እግዚአብሄርን በምኞት የሚያውቁት ሞልቃቆች የቻፕስቲክ መግዣ ቢያጡ፣ "እግዚአብሔር ማነው?" የሚሉ...እግዚአብሄርን እንዲያስተዋውቁኝ አልፈልግም። አይቻቸዋለሁ በዩኒቨርስቲ ቆይታዬ፣ ዶሮ ሦስት ጊዜ ሳይጮህ ጴጥሮስ ጌታን ሦስት ጊዜ እንደካደው ኮሚያትት መዝሙር እያንጎራጎሩ አንሱ ራሳቸው የሃብታም መኪና ጡሩንባ ባምባረቀ ቁጥር ከራሳቸው ሰላሳ ጊዜ ሲክካዱ።

አይቻቸዋለሁ የጌታ የማዳን ድንበር አቃቂና ኮተቤ ድረስ ብቻ ይመሰል የአዲስ አበባ ልጆች ብታ ተጠራርተው፣ "በጌታ ፍቅር" ምላ ሲገባበዙ፣ ቸርች ሲሄዱ - በፅንፍየለሽ ከተማዊ ዘረኝነት የሚነበብ ነገር ሲዋዋሱ። አይቻቸዋለሁ በየአምነቱ ተባድነው ሲናቆሩ፣ ሲጠዛጠዙ። አቶ እና እናቴ አግዚአብሄርን ገደል ጫፍ ላይ እንደተንጠለጠለ ገመድ የሙጥኝ ብለን ሕዝብ ከዘ ከዚህ ሲገፋን፣ ድህነት አጃችንን እየቀጠቀጠ የመዳኛ ገመዳችንን ሊያስለቅቀን ሲታገል፣ "እንለቅም" ብለን የተረፍን ሚስኪኖች ነን። "ሰው አትመልከት አግዜርን እንጂ" ይሉኛል፣ 'አብረን እናምልክ!' ብሎ ጠርቶ 'ሰው አትመልከት!' ማለት ምንድን ነው?

አግዚአብሄርን የማረፊያ ምቹ ሳሎን ሳይሆነን በፊት የውሽንፍርና የማዕበል መሻገሪያ ድልድያችን ሆኖ አናውቀዋለን። መዝሙር በአፋችን የለም፣ እንጠቅሰው ምዕራፍ፣ እንመዛው ቁጥር የለንም፣ ግን አንድ ነገር አናውቃለን፣ አግዚአብሄር ራሱን ያስተዋወቀን "እደርጋለሁ፣ አሰራለሁ" እየለ በመፅኸር ሳይሆን እየሰራና እያደረገ ነው። ፅኑ ክንዱን እያሳየ። ያለፈኸውንን ነገር ሁሉ አንደትቢያ ሊበታትነው አኔና እናቴ የዐይን ምስክሮች ነን። ሽባ ተተረተረ ቢሉን፣ አውር በራ ቢሉን፣ ሰማይ ቢከፈት፣ ምድር ቢናወጥ፣ ተዓምር ቢነግሩን...መልሳችን አንድ ነው፣

"አልሰሜን ግባ በለው፣ አግዚአብሄር ለእኛ ያደረገውን ነው ለሌሎች ያደረገው"። ከራሱ ከፈጣሪ የተሰበከን ነን - በሰራው !!

ምግብ ፊቴ ሲቀርብ ውስጤ በመደነቅ ይሞላል...እነዚህ በመከራ ጩኸት እና በነፍስ ዋይታ ሳይሆን በመዝሙር የተጠሩ ቆንጆዎች ይህን ብነግራቸው ያምናሉ ?...መሪር ትዝታ አለኝ። እንጀራ በቆረስኩ ቁጥር እንደወጥ የማጠቅሰው ፅልመት።

ሕፃን ሆኜ ከአቲዬ ጋር ልብስ የምታጥብበት ቤት እንሄዳለን። አቲዬ የተቆለለ ቆሻሻ ልብሳቸውን ስታጥብ ባለቤቶቹ አጥንቱ ብቅ ጥልቅ እያለ የሚንተከተከ ቀይ ወጥ በረንዳቸው ላይ በተልቅ ብረት ድስት ጥደው አያለሁ።የሚንተከተከ ሽሮ አያለሁ። የሚጋር ትኩስ እንጀራ አያለሁ። ደግሞ ሽታው አፌን በምራቅ ይሞላዋል - ያቅለሸልሸኛል።

አኔና አቲዬ ቁርስ ሳንበላ ነው የምንወጣው። አቤት ምሳ ሰዓት አራራቁ። የአቲዬ አሰሪዎች ልጆቻቸውን ከሚጫወቱበት ለምሳ ይጠሯቸዋል። አቧራ የነካ የልጆቻቸውን ልብስ ከላያቸው ላይ ገፍፈው ወደ አቲዬ የልብስ ቁልል ይጥሉና ይዘዋቸው ወደቤት ይገባሉ። በመቀነሻ ሰሀን ወጡን፣ አጥንቱን ጭምር ጨልፍ አድርገው ቀንሰው ይገባሉ። ከመጨለፋቸው በፊት በሞልፋው አንድ ሁለቴ ማሰል ማሰል ያደርጉታል፣ አጥንቱና ወጡ ይደበላለቃል ። ይርበኛል !! በጣም ይርበኛል። ወጡ ሲንተከተከ ድምፁ እስከዛሬ ጆሮዬ ላይ አለ። የአነዛ ሰዎች ድምፃቸው ይለማኛል፣ "ብሉ እንጂ አጥንቱን ምነው ፈራችሁት?" እየተባባሉ። "አልጫው አልጣፈጣችሁም እንዴ?" እየተባባሉ። ትሪ፣ ጭልፋ ሲንኳኳ ይሰማኛል። ብቅ ብዬ ባያቸው አወዳለሁ።

አባወራው፣ "እስቲ የአጥንት መቅጥቀጫ አምጪ!" ይላል ሰጋውን የተገፈፈ ነጭ እንቢልታ

የሚያህል ቅልጥም ወድሮ ወደ በረንዳው እየወጣ። 'ከሸ' ያደርገውና አንጋጥጦ መቅኒውን ይሰባል። ጉሮሮው ወደ ላይ ወደታች ይንቀሳቀሳል። የእኔም ጉሮሮ ይንቀሳቀሳል። ምራቄን ደጋግሜ አውጣለሁ።

የቅልጥሙ መርዘም እና ሰውዬው ወደ ሰማይ ወድሮ ጫፉን እቅ ውስጥ አስገብቶ ሲመጠው ሰማይ ላይ ያለውን ደመና በቀስም የሚመጠው ይመስላል።

"አይደ_ወደቀ" ይላል ወደ መሬት እያየ። ሚስቱ ጉርሻ ጠቅልላ ወደ በረንዳ ትወጣለች፣ "እችን ብቻ አፈር ስሆን!" እያለች - በውጥ የረሰረሰ ጉርሻ። 'ውስጡ የተከተፈ ሲጋ ወይም እንቁላል ሊኖረው ይችላል' አላለሁ በሆዴ። አንከርፍፋ ባሏን አንዲንርስላት ትለምነዋለች። "ውይ ምን ላይ ይቀመጥ ሆዴ አኮ ሞላ" ይላል፡ "ለዚህች ቦታ አይጠፋም በሞቴ"። እቃን ይከፍትና ጉርሻው አንዳይንጠባጠብ የግራ እጁን መዳፍ ከታችኛው ከንፈሩ ስር ይገድበዋል። ጉርሻውን በሁለት ትንፌቱ ምልቶ እያላመጠ ተከታትለው ወደ ውስጥ ይገባሉ።

"አሸብር!" ትለኛለች አቲዬ ድንገት። ማፍጠጤ ሲበዛ፣ "እንካ ብስኩት ማዛና ና!" ብላ አሮጌ መሀረቧን ፈትታ አንድ ብር ትሰጠኛለች። አንድ ብሩን ስታወጣ መሀረቡ ባዶ ይሆናል። ብስኩት ገዝቼ አመለሳለሁ። ዛሬ ላይ ሳስበው የሚቆጨኝ ለአቲዬ ብስኩት አልሰጣትም ነበር። ብቻዬን አበላለሁ። በሩ ይከፈትና "አፀደ አቺን ለቅለቅ አድርጊያት ልጅቱ ሲንቀጠቀጠዙ ወጥ ደፋበት"። አንዳች የሚያከል የሰውየውን ኮት ትጨምራለች - ባለቤቷ። ሁልጊዜም በሩ ሲከፈት ሰላን ይዛ የምትወጣና "ምሳችሁን ብሉ!" የምትል ይመስለኝ ነበር፣ ግን ብላን አታውቅም።

እንዳንዱ ቤት ደግሞ ቁራሽ እንጀራ (ወጥ የነካካ) በሰሃን ይዘው ይወጡና፣ "እናትዱ አቧን ለቅለቅ አድርገሽ ስትጨርሺ አቺን ብይ" ትላለች አሰሪዋ። 'አቧን ለቅለቅ' ያለቻት ቢደረደር ሱቅ የሚሞላ ድርቶ ነው። በነባራችን ላይ በራሴ ገጠመኝ እንዳየሁት ብዙ ሚስቶቹ ከቆዎች፣ ስስታሞችና ታላቅነታቸውን ለማሳየት ሠራተኛ የሚበድሉ ናቸው። ባሎቻቸው ይሻላሉ። አቲዬ ታዲያ፣ "አሹ አችን ብላ" ትልና ፈገግ ብላ ሰሃኑን ለኔ ሰጥታ ስራዋን ትቀጥላለች። አቲዬ ስትበላ አይቻት አላውቅም። ይዝመኛል። አቲዬ ካለምጣብ መኖር የምትችል አየመሰለኝ በእርግጥም አገረም ነበር።

ርሃብ አንደ ብርድ፣ አንደ ሙቀት አንደ ደስታ አንደ ሃዘን ሰውነታችን ውስጥ የሚፈጠር ስሜት ብቻ የሚመስለላቸው ምኞች አሉ። ርሃብ በሽታ ነው ። ቆሻሻ የሆነ በሽታ ነው። ዘመን ተሻግረው ስለ ሰባ ሰባት ድርቅ ሲያወሩ፣ ስለ ስልሳ ስድስት ርሀብ ሲደለኩሩ፣ እዚሁ በረንዳቸው ስር ከነእናቱ የተቆራመድንበት ስንት አሰቃቂ ቁን አልፏል። ስንት ከፉ ቀናት ወደ ውስጥ አስለቅሰውናል። መሐል አዲስ አበባ በረሀብ የሚሞት የለም ሲሉኝ፣ 'ጥጋበኞች' የምላቸው ዛሬ ስንቶች ናቸው?

ይሄ ልመናን ስራው ያደረገ ለማኝ ይመስለናል የሚራበው። አሱ ከብሩንም ይሉኝታውንም ጥሎ ሆዱን ሞልቶ፣ "የአዲሳባ ሕዝብ ውሉ ይግባ" አያለ ያድራል። መቀመጫዋን እያየሁ

በወይንህ የምትከተላት ዘናጭ ቆንጆ ሆዷ ቢፈተሽ ግን ማን ያውቃል፣ ቡቃን ሰብሶ ላጥቆጡን እንጠልጥሎ ከሥራ የሚወጣውን ጎልማሳ ብትመረምረው ግን ሙሉቀን አህል በአፉ አልዘረም ይሆናል። 'ራበኝ!' ለማለት ይሉኝታ ያነቀው ባለዲግሪ ረሀብተኛ ነው አለ ስንለው እዚህ ግባ በማይባል በሽታ ከንበል የሚለው። በሰራዬ የገጠሙኝ አልፍ ናቸው። ዘናጭ ረሀብተኞች።

ረሀብተኛው ርሃቡ አስኪጥለው የሚንጠራወት፣ በየበረንዳው ጃንሆውን ወዝቶ የምታየው ህዝብ የበላውን እንዲያንሸራሽርለት የፈለገ ብቻ እንዳይመስልህ፣ ይሄ ፈርማታው ላይ ያልደረሰ ጅምር ቢራ አራቱ ሊሆን ይችላል። ወዳጄ ፀጉራሙ በግ ነው አለ ሲባል የሚሞተው !!

አናም እነዛ የርሃብ ዘመኖች አልፈው፣ ጭሱ የሚመዘዘ ሽፍንፍን ያለ ቋንጣ ፍርፍር ፊቴ ሲቀርብ ሳልወድ በግድ እንጉቴን ደፍቼ፣ አንዳንዴም እንባዬ እየመጣ አግዚአብሄርን እንዲህ አለዋለሁ፣ "እቤት ማጥገብ ስትችልበት" በታ !! ምግብ ሲቀርብ ምንግዜም የምለው ይሄንን ነው። እንደውም ለአግዚአብሄር አይደለም ለራሴ ነው፣ "ይሄ አግዚአብሄር ማጥገብ ሲችል" የምለው። ልቤ ታዲያ ያውቃል፣ "ቀላል ይችላል" ይለኛል !! ይሄንን የነፍስ ወማ ያዩት ሞልቃቆች ታዲያ፣

"ጌ...ታ ሆ...ይ ይሄን ምግብ ባርከልን" የምል መስሏቸው፣ "አብረን እናምልክ!" ይሉኛል። አግዚአብሄርን በእውነትና በመንፈስ ለማምለክ፣ መንፈስህን በደቆሰ የሕይወት ከንድ ስር እየለህ፣ የእውነት መዳን፣ የእውነት ትንሳኤ፣ መሞሩን በመጀመሪያ አመነ። በተመረጠ ቃል፣ በጣፈጠ ዜማ መራር አውነትህን 'ለአግዚአብሄር አብረን እንንገረው' ብትለኝ አዘው የለመድከበት ነው የምልህ ፤ አዘው የለመድከበት !! ያውም ከጉረት ጋር፣ "ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል"።

ከፉል ሀያ ሁለት

አንዳንዱ ሰው ዘመንን ተሸግሮ ታሪክን ተረማምዶ ከዓለማችሁ ሊያደናቅፋችሁ ፈታችሁ ይጋረጣል። 'ቆሎ ተምሬ ይሄንን ህዝብ የምጠይወትበት ሙቼ ነው?' አያልኩ ሳስብ፣ 'የምበሳለው እንዴት ነው?' አያልኩ ባምስለሰለ መመሪቂያ ቀኔ ደረሰ። ያስተማሩን የተከበሩ መምህራኖቻችን መድረኩ ላይ በየመሣሪያ ልብሶቸው ተቀምጠዋል። ወደ በኋላ ዶክተር የእኔ አምላክ ይነሱና፣ "ተመርቃችኋል ወደ ምድር ሁሉ ሂዱ ይሄንን ሕዝብ ፍዳውን አብሉት" ማለታቸው አይቀርም - ባይሉም ለእኔ ትርጉሙ ያ ነው !! ይሄን ሁሉ ዓመት ስማር የሕክምና ስነምግባር ከሕዝብ ከፋት በልሶ ልቤን ሊያራራው አልቻለም።

እኔ ግራ የገባኝ፣ "ሕዝቡ ማነው ?" የሚለው ጥያቄ ነው።

ሕዝቡ የገፋቸው ብዙ አቲዩዎች አሉ። ገፈውን ከተገፈው ያልለየ በቀል ያን ያህል አያረካም፣ ሕዝቡ ማነው...? አንዳንዴ ደሃው ከፍ ሲል ሌላ ደሃ እየገፋ፣ የተገፋው ነፃ ሲወጣ የባሰ ገፈ

ሲሆን እያየሁ ሁሉንም በጅምላ ጠራርጌ አገር እንደሳር አዲስ ትውልድ ቢያቆጠቁጥባት ይሻላል እላለሁ።።

የዚህ ህዝብ 'ዘርፌ' የምትባል አመልካች ጣቱ፣ 'ቀለመመርቅ' የሚባል አውራጣቱ ብቻ ጋንግሪን አንደለከፈው እግር ተቆርጦ የሚጣል አይደለም።። አገር በሙሉ፣ ሙሉ አካሉ ተበላሽቷል፣ በከፋት ደዌ ነፍርቋል።።

ምፅዓት፣ "አቃቃው ፈረሰ ዳቦው ተቆረሰ" ዓይነት የምድር አቃቃ ፍፃሜ እስመሆኑ የገባኝ ያኔ ነው።። የናህ ውሀ፣ የሎጥ እሳት አንደምርቃት ቀኔ ይናፍቀኛል።። በየሆቴሉ ሕዝቡ ሲበላ ሲጠጣ፣ ሆዱን የሞላበትን ሰሃን ጓዳ ውስጥ የምትፈትግ የአሱን ወጥ የምትቃቅል የራባት ወጥ ቤት ከኋላው በግፍ አንደምትገረድ እየታየኝ አበሳጫለሁ።። "እና ምን ይጠበስ ይልሀል" ሕዝቡ፣ 'አንድ በአንድ ነበር ሜንጦ ላይ አያንጠለጠሉ መጥበስ' አላለሁ እኔ።።

ሲፋቀር፣ ሲጋባና ሲወልድ ያበሳጨኛል።። አንዱ ሞቶ ሌሎች ሲቀበሩ ሲሄዱ 'መሞት አልነበረበትም' እይነት ጩኸታቸውና የአዞ አንባቸው ያስጠላኛል።። ሰዎች ታምመው ደፋ ቀና ተብሎላቸው መሞታቸው ይቆጨኛል።።

የሎጥ እሳት...እሳት...እሳት...እሳት !! በየመንገዱ ይሄ ጨብራራ ፀጉራቸው በእሳት ተያይዞ ሲጮኩ ማየት አፈልጋለሁ።። ጅምላ ጨራሽ መሳሪያ ለሙ ራሱ ይማርከኛል።። ይሄን በጅምላ ከፋትን ባህሉ ያደረገ ከቃ ህዝብ በጅምላ ቡምምምምምምምምምም!! ፭ጭ!!

ሸክ ብዬ የበቀል ደወል በሚደወልበት ቀን ወደ መመረቂያ አዳራሹ ገባሁ።። ሁሉም ያየኛል - አውቃለሁ።። ምክንያቱም ጎበዝ ነበርኩ፣ ጎበዝ ነኝ...!! እዛጋ የተቀመጠው ዋንጫ የእኔ ነው፣ ይሄን ሕዝብ ኮሶ የማጠጣበት።። ምድረ ኩታራ ሥራ ፈላጊ፣ "የክብር እና የሙያ ስም አሳዳጅ ሁሉ ዐይናቸው እያየ በፊታቸው እንደምነግስ በመወረግ ዛሬ እንደምቀባ ያውቃሉ።። ለበቀል እንደምቀባ እያውቁም።። ዩኒቨርስቲ ሰይጄን ሰላ ወደ ሕዝብ አንገት በመዓረግ ልታውዘገዝግ ነው..መጣሁልሽ አዲስ አበባ ሃሃሃሃ እያቃሰትሽ ከፊቴ ልትሰለፊ፣ ምጥ አያጣደፈሽ አድነኝ ልትይ፣ ደምሽ አየተንዠቀዠቀ አትርፊኝ ልትይ ሃሃሃሃ !!

እንኳን ደስ አላችሁ!

እንኳን ደስ አላችሁ!

እንኳን ደስ አላችሁ! አልልል

ተመልሰው ከኋላ ወንበር ማን እንደተቀመጠ። ኮፈኑ ፀጉር ጣል ጣል ያደረገባት፣ ያበሻ ቀሚስ የለበሰች፣ ከዘመናት ጉሰቁልናዋ አዲስ ልብስና ሹርባዋ ያልታደጋት ሚስኪን እናቴ - አቲዬ... እናቴ !! ለቤት ሳያት ለውነቴ እንዴት አልህ እንደሚሞላው !! አዳራሹ እንደዛሬ ሙሉ ሁኖ አያውቅም፤ አዚህ አዳራሽ ውስጥ ታላላቅ ምሁራን በተገኙበት አራት አምስት ጊዜ ተገኝቼ እውቃለሁ፣ ዛሬ ግን ሙሉ ነው - አቲዬ አሊቾ !!

የሕዝቡ ብዛት ግርግሩ ግራ እንዳጋባት ከዛፒ ጎን ተቀምጣለች፣ 'አልመጣም፣ ብላ አስቸግራ ነበር ፈርታ። አቲዬኮ ይሄን ሁሉ ዘመን 'ሰው' የዋለበት ውላ አታውቅም። እንግዳ እንኳ እነዛፒ ቤት ከመጣ ምግብ አቀራርባ ወደ ጓዳ ነው ሩጫዋ። ሰውን ፊት ለፊት ቁጥ ብላ አታይም፤ ቀምሶዋታል ለብዓዊነቷን። 'ሰው ፊት እንዲህ አይቆምም' እያሉ፣ 'እቃ እንዲህ አይያዝም' እያሉ፣ 'ምን ትንከረፈፈያለሽ?' አያሉ፣ የእኔን እናት ካላላነሱ ትልቅ መሆን የማይችሉ ይመስል ምድረ ገለባ አስኪቢቃው እናቴ ላይ ተጨማልቋል።

ዛፒ እጇን አውለበለበችልኝ ! ደግሞ ፈገግታዋ። እንዴት ነው ደስ ያሉት። ሳላስበው አፍጥጬባቸው ነበር ለካ። አቲዬ በሰሰት እንደምታየኝ ከዚህ ርቀት አውቄያለሁ። የአርሷ መሊህ ጥቁር መነናፀፊያ ለብሼ ሰላሳ ስምንት አመት የተኛችበትን የድህነት አልጋ፣ የመገፋት አልጋ፣ የመከላፊትና የመናቅ አልጋ፣ "አንች ሴት ልጅሽ ደርሶልሻል ተሸከመሽ ሂጅ" ልላት ፊቷ ቆሜያለሁ። ሃሌሉያያያያያያያ እኔ ዶክተር አሸብር ነኝ !! ዶክተር አሸብር በአምላክ !! የተገፋችው የተናቀችው የአፀደ ልጅ!!

አንኳን ደስ አላችሁ፣

አንኳን ደስ አላችሁ፣

አንኳን ደስ አላችሁ።

አንዳንዱ ሰው ዘመንን ተሻግሮ፣ ታሪክን ተረማምዶ ከዓላማችሁ ሊያደናቅፋችሁ ፊታችሁ ይጋረጣል...ለምሳሌ ሂፖክራጥስ። ይሄ ሰው የዘርፌ የበኸር ልጅ አስኪመስለኝ፣ የቀለመወርቅ የነፍስ ወዳጅ ነው ብዬ አስከጠረጥር ዛሬ ቅጥልልል ነው ያደረገኝ። በጓሁሰት የምርቃት ቀኔ ፊቴ ተጋርጦ ማንም ሳያዘው ቪማግሌ ይሆናል ? (ወይስ የአዲስ አበባ ህዝብ ፊርቶ 'ከአሸብር ጋር አስታርቀኝ' ብሎ ልኮት ነው...?)

የሕክምና ዶክተር ሲመረቅ ቃለ መሀላ እንደሚፈፅም ባውቅም ረስቼው ነበር። በዚህች ቀን ግን የሂፖክራጥስ መሃላ የሚባለውን አስመራቂው ዶክተር ቃል በቃል እያነበቡ ደግመን እንድንናገር ሲያደርጉን፣ ሆን ተብሎ አሻጥር የተፈፀመብኝ አስኪመስለኝ ከፍቶኝ ነበር።

እንዴት ነው፣ 'ሕዝብን ሙያዬን ተገን አድርጌ አልጎዳም' ብዬ የምምለው ?

በምንስ ሂሳብ ነው በጨዋነት የህመምተኛውን ክብርና ስብዕና በሚጎዳ መልኩ ምንም መጥፎ ነገር ላላደርግ ብዬ የምምል የምዝተው ? ይሄ ሕዝብ አናቴ ላይ በነፍሰ ሊጋዋ ሊጫወትባት ሂፖክራተስ ከነመሀላው የት ነበረ::

እሺ ቀልድ፣ ሕዝቡ "ልጅ አይደለህም" ብሎ የወረወረኝ እኔ፣ ሕዝቡ ከአሜሪካ ላሙ አኩል ሊያየኝ ያልፈለገ እኔ፣ "ሕዝቡን እንደ ቤተሰቤ የሕዝቡን ልጅ እንደራሴ ልጅ ላይ" ብዬ እንድምል ሂፖክራተስ ሽምግልና ፊቴ ቆመ:: ይሄ "ዶክተር" ለመባል የቸኮለ ሁሉ የተባለውን በተመስጦ ይደግማል::

"በሕክምና ወቅት የምሰማውን የህመምተኛውን ሚስጥርም ሆነ የግል ጉዳይ በታማኝነት ልጠብቅ..." ወቸ ጉድ !

"...ሕዝቤን ከልብ በመነጨ ፍቅር፣ ስብዓዊነት እና ሙያዊ ስነምግባር ላገለግል..." ካለፍኩበት የትምህርት ውጣ ውረድ ይልቅ ይህን ታላቅ መሃላ ማለፍ ከባድ ነበረ:: ያውም እኮ በአግዚአብሄር ስም፣ በእኔና በሉቲዬ አግዚአብሄር ስም::

ግን አንድ እውነት ልንገራችሁ መሃላው ልብን ያርዳል:: ምንድን ነው የተማረን ሰው ሬሪ ማድረግ፤ ከውስጤ የፎከርኩበት በቀል ሲተን፣ አግዚአብሄር የበቀል ብትሬን ከአጀ ላይ ፈልቅቆ ሲወስድ ይሰማኛል:: ሰምል እንባዬ በዐይኔ ሞልቶ ነበር::

ግን ምን አደረገ የአዲስአበባ ሕዝብ ?ሕይወት ሰለሜ ሰለሜ እያጫወተው ከከፉው ኋላ ከፉ ተሰልፎ ማለቂያ በሌለው የከፋት ሰልፍ፣ አንድ አለንጋ ከኋላው እያራወጠው የሚኖር ሚስኪን - ምን አደረገ ?? ልጆቻችን ተመረቁልን ብሎ አልጋው ላይ አያቃሰተ እየጠበቀን ይሆናል:: ውጋቱን ችሎ፣ ቁርጠቱን ችሎ፤ ዘናጩ የአዲስ አበባ ሕዝብ ስንት ዓይነት ጉዳቱን በልብሱ ሸፋፍኗታል - ኤዲያ በቃ 'አፉ' ብዬዋለሁ !!

ኤፍፍፍፍፍፍፍፍፍ ራሴን ቀለለኝ:: ስሜ ከመድረክ ሲጠራ አዳራሹ በሳቅበጨበጨ ሲናወጥ መድረክ ላይ ቆሜ ተመለከትኩ:: የማታጨበጭብ ብቸኛ ታዳሚ አቲዬ ነበረች:: "የሰው ዐይን ልጄን..." እያለች እኮ ነው መች አጣሁት:: እናም አልኩ፤ "እሁቴ ዛፒ እወድሻለሁ" ሁሉም ወደኋ ዞሮ አጨበጨበ:: እንዴ፤ ዛፎ አለቀሰች !! አቲዬን አየኋት ዛሬ ድረስ ቪዲዮውን ሳየው አልቅስ አልቅስ ይለኛል:: አቲዬን ስሟን ብቻ እንደጠራሁ እንባዬ ተዘረገፈ በቃ!!

ሌሊቱን ሙሉ ምን ብዬ እንደማመሰግናት አጥንቼ ነበር እኮ !!

*** *** ***

ሕይወት እንደ ሰዓት ናት:: በሙላትና በጉድለት መሐል ይዛ የምትነጉድ:: ሁልጊዜ ትቅጥራለች:: ሩብ ጉዳይ፣ አስር ጉዳይ፣ አምስት ጉዳይ - ትሞላለች ፣ ከአምስት፣ ከአስር፣ ከሩብ - ትተርፋለች !!

ውስጤ ፍፁም ሰላም ይሻል። ጥላቻና በቀል በመቀመር ያሳለፍኩትን መራር የወጣትነት ዘመኔን ለማካካስ ስለ ሰላም ብቻ ማሰብ እሻለሁ። ለዓለም ሕዝብ ሁሉ ሰላም።

አንም እንዲህ አሰብኩ፣ ድንገት የዘገየ የጸሎት ምላሽ ተልኮ ኒውክሌር ቦምብ እጄ ቢገባ ወስጄ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ "ያውላችሁ ለሰላማዊ ጉዳይ፣ ለኃይል ማመንጫ፣ ምናምን ማለት የለም፣ 'በሕግ አምላክ ውሰዱልኝ...' ይልቅ በጅምላ ሕዝብ የሚፈጁትን ወባና ኤችአይቪ አንዋጋው ዘንድ መከላከያውን በገፍ ላኩልንማ" - አላቸዋለሁ !! ፈገግታ ልቤ ውስጥ አለ። ልቤ ፈገግታን እየተለማመደች ነው።